# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

**በባሌ ዞን ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የ'ሙዳ' ስርዓተከበራ እና መንፈሳዊ ጉዞ**

**በ**

**ሰሎሞን ተሾመ ባዬ**

2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ለ ፎክሎር ፒ.ኤች.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሰሎሞን ተሾመ ባዬ

2010 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

**በባሌ ዞን ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የ'ሙዳ' ስርዓተከበራ እና መንፈሳዊ ጉዞ**

**በ**

**ሰሎሞን ተሾመ ባዬ**

**2010 ዓ.ም**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| አማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ________________ | ______________ |
| **ፈታኝ ስም** | **ፊርማ** |
| ________________ | ______________ |
| ________________ | ______________ |

# ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በዚህ መልክ እንዲዘጋጅ ከፍተኛ ጥረት ላደረጉት፣ ጥልቅ ዕውቀታቸውን ላካፈሉኝ፣ በመልካምነትና በትዕግስት ለረዱኝ አማካሪዬ ዶ/ር ታደሰ በሪሶ እጅግ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ የእርስዎ ጥልቅ ዕውቀት፣ ትጋት፣ ሰው አክባሪነትና መልካምነት ለእኔ ትልቅ ትምህርት የሰጠኝ ነውና አመሰግናለሁ፡፡

ለጥናቱ ግብዐት የሚሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበራችሁን መረጃ ሰጪዎቼ ለዚህ ጥናት መሳካት የማይተካ ውለታ አላችሁና እጅግ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኛ ለሆናችሁት ለአቶ ኑማን መሐመድ፣ ለአቶ መሐመድ ሰዒድ አህመድ እና ለሐጂ አብዱልናስር አህመድ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡

ለድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጤና ጣቢያ ሰራተኛ ለሆናችሁት ለአቶ አህመድ አማን እና ለአቶ አደም መኖሪያ ቤታችሁን ማረፊያ እንዲሆነኝ ስለፈቀዳችሁልኝ አመሰግናለሁ፡፡ የመካነ ቅርሱን ካርታ ለሰራህልኝ ለአቶ የኀላሸት ወርቁ፣ በመካነ ቅርሱ ላይ ጥናት እንዳካሂድ ምክር ለለገሳችሁኝ ለአቶ ናትናኤል ወንዴ እና ለአቶ ኤልያስ ጠሃ፣ የመንፈሳዊ ሙዚቃዎችን ስኬል በኖታ ለሰራህልኝ ለአቶ ሰርፀፍሬ ስብሃት እንዲሁም ጽሑፉን በማንበብ አስተያየት ለሰጣችሁኝ ለአቶ መሐመድ ገመቹ፣ ለአቶ ብሩ ጸጋዬ  እና ለአቶ ተሻገር አስማረ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡

መረጃዎችን ከኦሮምኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ በመተርጎም ለረዳችሁኝ ለአቶ ወጋየሁ ንጋቱ እና ለአቶ ደጋጋ ጉደታ፣ ለጥናቱ ግብዐት የሚሆኑ መረጃዎችን፣ መጻሕፍትን፣ ሰነዶችንና ፎቶግራፎችን ለሰጣችሁኝ ጓደኞቼና ወዳጆቼ፣ በተለይ ለዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ እንዲሁም የጽሑፉን ቅርጽ በኮምፒውተር በማስተካከል ለረዳሽኝ ወ/ት መስከረም አረጋይ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ የሁልጊዜ ድጋፋችሁ ለማይለየኝ ቤተሰቦቼ ለአባቴ አቶ ተሾመ ባዬ፣ ለእናቴ ወ/ሮ ሰብለወርቅ መንግስቱ፣ ለወንድሞቼ ዘለዓለም ተሾመ እና ብሩክ ተሾመ፣ ለእህቶቼ አስቴር ተሾመ እና ሰላም ተሾመ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ከእናንተ ጋር እንዴት ልተዋወቅ ቻልኩኝ? ብዬ ሁልጊዜ አስባለሁ፡፡ ትውውቃችን በአጋጣሚ ይሁን አልያም በውሳኔ ባላውቀውም፣ በተገናኘን ወይም እኔን ባስታወሳችሁኝ ቁጥር የምታደርጉልኝ ምርቃትና ጸሎት ሁልጊዜ ከአዕምሮዬ አይጠፋም፡፡ የእናንተን ስም መግለጽ አግባብ ባለመሆኑ ብተወውም፤ ትናንትም ሆነ ዛሬ ላለን ወዳጅነት፣ ነገም ለሚኖረን የሕይወት ቁርኝት ከፍተኛ አክብሮትና ምስጋና አለኝ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ


አጠቃሎ ........ vii
1.መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........ 4
1.2. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች ........ 6
1.3 የጥናቱ ዓላማዎች ........ 7
1.4. የጥናቱ ወሰን ........ 8
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታዎች ........ 9
1.6. የጥናቱ አወቃቀር ........ 10
2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ የጽንሰሃሳባዊ እና የንድፈሃሳባዊ ዳሰሳ ........ 11
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 11
2.2. ጽንሰሃሳባዊ ዳሰሳ ........ 21
2.2.1. የስርዓተከበራ ምንነት ........ 21
2.2.2. የስርዓተከበራ አይነቶችና ባህርያት ........ 24
2.2.3 የስርዓተከበራ አላባውያን ........ 25
2.2.4 የስርዓተከበራ መሰረቶች ........ 26
2.2.4.1 የክወና ምንነት፣ ባህርያትና አላባውያን ........ 26
2.2.5 የመንፈሳዊ ጉዞ ምንነትና ባህርያት ........ 31
2.2.6 የውሕደት ምንነትና ባህርያት ........ 35
2.2.7 የሙዳ ምንነት ........ 41
2.3 የጥናቱ ንድፈሃሳቦች ........ 46
2.4 የጥናቱ ሞዴል ........ 50
3. የጥናቱ ስነዘዴ ........ 54
3.1 የጥናቱ አይነት ........ 54
3.2 የመረጃ አይነቶች ........ 55
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 55
3.3.1 ምልከታ ........ 56
3.3.2 ቃለመጠይቅ ........ 57

3.3.3 የንጥል ማሳያ ጥናት ..... 58
3.3.4 የተተኳሪ ቡድን ውይይት ..... 59
3.4 የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ ..... 60
3.5 የመረጃ ማያ ስልት ..... 61
3.6 የመረጃ መፈከሪያ ስልት ..... 62
3.7 የጥናቱ ስነ-ምግባር ..... 63
4. የሼኽ ሁሴን ማንነት እና የመካነ ቅርሱ ትዕምርታዊ ውክልና ..... 65
4.1. የሼኽ ሁሴን ታሪክ ..... 66
4.1.1 የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ታሪክ ..... 67
4.1.2 የሼኽ ሁሴን የውልደት ዘመን ..... 68
4.1.3 የሼኽ ሁሴን የዘርሃረግ ..... 70
4.2 የሼኽ ሁሴን ሰብዕናዊ እሳቤዎች ..... 75
4.2.1 የሼኽ ሁሴን ሰብዕናዊ እሳቤዎች ከአፍቃሪዎቻቸው አንጻር ..... 75
4.2.2 የሼኽ ሁሴን ሰብዕናዊ እሳቤዎች ከተቃዋሚዎቻቸው አንጻር ..... 98
4.3 የሼኽ ሁሴን ባህርያትና ትዕምርታዊ ውክልና ..... 101
4.4 የመካነ ቅርሱ እሳቤና ትዕምርታዊ ውክልና ..... 108
4.4.1 የመካነ ቅርሱ እሳቤ ከሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች አንጻር ..... 108
4.4.2 የመካነ ቅርሱ እሳቤ ከሼኽ ሁሴን ተቃዋሚዎች አንጻር ..... 119
4.4.3 የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መልክዓምድርና አንድምታው ..... 123
4.4.4 የቀናት ውክልናዊ አንድምታ ..... 128
4.5 የሼኽ ሁሴን ኃይማኖታዊ ሚና እና የቴክኖሎጂ አስተዋጽኦ ..... 131
4.5.1 የሼኽ ሁሴን ኢማምነትና እስልምናን የማስፋፋት ሚና ..... 131
4.5.2 የሼኽ ሁሴን የቴክኖሎጂ አስተዋጽኦ ..... 135
5. የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች አጠቃላይ ገጽታ ..... 140
5.1 የእስልምና ኃይማኖት በባሌ ዞን ..... 140
5.2 የእስልምና ኃይማኖት በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ..... 148
5.3 አብይ የእስልምና አስተምህሮዎች በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ..... 150
5.3.1 የሱኒ አስተምህሮ በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ..... 151
5.3.2 የሺዓት አስተምህሮ በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ..... 155
5.3.3 የሱፊዝም ፍልስፍና በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ..... 157
5.3.4 የኦርቶዶክስ እና የፖፑላር እስልምና በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ..... 169

5.4 የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች የኢኮኖሚ መሰረት ........ 171
5.5 የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች ያላቸው ማህበራዊ አደረጃጀት ........ 173
5.5.1 ደርጋ ........ 173
5.5.2 ኡሌ ........ 179
5.5.3 ገሪባ ........ 184
5.3.4 መናኝ ........ 188
6. የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ገጽታ ........ 190
6.1 የድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ጉዞና የትራንስፖርት ሁኔታ ........ 190
6.2 የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ጉዳዮች ........ 192
6.2.1 መንፈሳዊ ጉዳዮች ........ 193
6.2.2 ፖለቲካዊ ጉዳዮች ........ 196
6.2.3 ተቃዋሚ ኃይሎችና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች ........ 210
6.2.4 ማሕበራዊ ጉዳዮች ........ 211
6.2.5 ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ........ 214
6.2.6 ጉብኝት ........ 215
6.2.7 ሕገ-ወጥ ተግባራት ........ 216
6.3 የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ያለው ባህርይ ........ 216
7. ከሙዳ በዓል በፊት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ........ 224
7.1 የሀሽ አዘገጃጀት ስርዓት ........ 224
7.2 ሀሽ የመቀባት ስርዓት ........ 228
7.3 ጀዋሩ የማዘጋጀት ስርዓት ........ 232
7.4 ደገሌ የማሰናዳት ስርዓት ........ 234
7.5 ደንቂ የማዘጋጀት ስርዓት ........ 239
7.6 መንፈሳዊ ተጓዦችን የመቀበል ስርዓት ........ 242
8. በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ........ 244
8.1 የሙዳ በዓላት የአጀማመር ስርዓተከበራዎች ........ 244
8.1.1 የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል የአጀማመር ስርዓት ........ 245
8.1.2 የኢድ-አል-አድሃ (የሐጅ) በዓል የአጀማመር ስርዓት ........ 246
8.2 የዋሬ ስርዓተከበራ ........ 250
8.2.1 የዋሬ ስርዓተከበራ የአጀማመር ስርዓቶች ........ 251
8.2.2 የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና ........ 258

8.2.3 የሂክማ ስርዓት ... 265
8.2.4 የአርጆማ ስርዓት ... 269
8.2.5 ስለት የማስገባት ስርዓት ... 274
8.2.6 የጨንጫ ስርዓት ... 275
8.2.7 የምርቃ ስርዓት ... 277
8.2.8 የእርግማን ስርዓት ... 283
8.2.9 የምህላ ስርዓት ... 290
8.2.10 የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና ... 293
8.3 የዝክሪ ስርዓተከበራ ... 294
8.3.1 የሐጂ አደም ሀድራ ... 295
8.3.2 የአብሮኜ ዝክሪ ... 299
8.3.3 የዶውሪ ስርዓት ... 305
8.4 በከራ ጉዶ እና በቅጽር ግቢው ውስጥ የሚከወኑ ስርዓቶች ... 306
8.4.1 የግቢውን ዋና የመግቢያ በር የመሳለም ስርዓት ... 308
8.4.2 ገሞዎችን የመሳለም ስርዓት ... 309
8.4.3 ዘምዘም የመጠጣትና ሰውነትን የማሻሸት ስርዓት ... 313
8.4.4 ጀዋራ የመቀባት ስርዓት ... 317
8.4.5 ስለት የመሳል ስርዓት ... 319
8.5 በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ ስርዓቶች ... 321
8.6 መንፈሳዊ ተጓዦችን የመሸኘት ስርዓት ... 325
9. በሙዳ በዓላት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች እና ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች ... 327
9.1 በሙዳ በዓላት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ... 327
9.1.1 የመካነ ቅርሱ ተቃዋሚዎች አስተምህሮ መስፋፋት ... 327
9.1.2 የትምህርት መስፋፋት ... 331
9.1.3 የኑሮ ውድነት ማሻቀብ ... 332
9.1.4 የዶዶቲ ተክል መራቆት ... 333
9.1.5 የቴክኖሎጂ ውጤቶች መስፋፋት ... 333
9.1.6 የንግድ እንቅስቃሴዎች ... 335
9.1.7 የስልጣን ይገባኛል ሽኩቻ ... 337
9.1.8 ለመካነ ቅርሱ የሚደረግ ጥንቃቄ መላላት ... 337
9.1.9 የመሰረተ ልማቶች አለመሟላት ... 338

9.1.10 የተለያዩ አካላት ያላቸው የግል ፍላጎት ..... 342
9.2 በሙዳ በዓላት ላይ ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች ..... 344
9.2.1 የመካነ ቅርሱ የቦታ ለውጥ ..... 344
9.2.2 የሼኽ ሁሴን ውልደትና ሕልፈት ..... 345
9.2.3 መካነ ቅርሱ የነባር ሕዝቦች የኃይማኖት ማዕከል መሆን ..... 346
9.2.4 የመካነ ቅርሱ የኃይማኖት ማዕከልነት ድጋሚ መጠናከር ..... 349
9.2.5 አንዳንድ የሙዳ ስርዓተከበራዎች መጀመር ..... 350
9.2.6 የጣሊያን ወረራ ..... 352
9.2.7 አጼ ኃይለሥላሴ መካነ ቅርሱን መጎብኘታቸው ..... 353
9.2.8 የባሌ ገበሬዎች አመጽ ..... 354
9.2.9 ለመካነ ቅርሱ ትኩረት መስጠት መጀመር ..... 358
10. ማጠቃለያ ..... 361
የይሁንታ ሀሳቦች ..... 367
ዋቢ ጽሑፎች ..... 370
አባሪ፤- የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ ስርዓተከበራ አከዋወን፣ መስተጋብር፣ ውህደት እና መንፈሳዊ ጉዞው ያለውን ባህርይ መተንተን ነው፡፡ የሙዳ በዓላት በመካነ ቅርሱ በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ የመታሰቢያ ስርዓቶች ናቸው፡፡ ጥናቱ ይዘታዊ ምርምር የጥናት አይነትን የተከተለ ነው፡፡ ለጥናቱም ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ ንጥል ማሳያ ጥናትና የተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያላቸውን ትርጉም በፍከራ ለማሳየት ጥናቱ ክወና ተኮር ስልትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ስልት ባህላዊ እሳቤዎችን፣ ትዕምርቶችንና ውክልናዊ ትርጓሜዎችን ማህበረሰቡ በራሱ አዕምሯዊ ግንዛቤ እንዴት እንደሚረዳ የሚያሳይ ነው፡፡ ጥናቱ የክወና፣ የትዕምርታዊና የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳቦችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ የጥናቱም ዋና ዋና ዓላማዎች በሼኽ ሁሴንና በመካነ ቅርሱ ላይ ያሉ እሳቤዎች፣ የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ያላቸው ኃይማኖታዊና ማህበራዊ ዳራ፣ መንፈሳዊ ጉዞው ያለውን አነሳሽ ምክንያቶቸና ልዩ ባህርያት፣ የሙዳ በዓላት ከመድረሳቸው በፊትና በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች፣ በስርዓተከበራዎቹ ላይ የሚስተዋሉ ውሕደቶች፣ በበዓላቱ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችና ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች ተተንትነዋል፡፡ የሙዳ በዓል ሼኽ ሁሴንን፣ መንፈሳዊ ተጓዦችን፣ መካነ ቅርሱንና የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎችን በአንድ ላይ የሚያገናኝ ማዕከል እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በዓሉም የመንፈሳዊ ተጓዦችን ማንነት የሚገልጽ፣ ያላቸውን አመለካከት የሚቀርጽና የሚወስን እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የሙዳ በዓልን በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች፣ የተለያዩ ኃይማኖት ተከታዮችና የውጭ አገር ዜጎች በጋራ ያከብራሉ፡፡ ይህም ልዩ ባህርይ የሙዳ በዓል የባህልና የኃይማኖት በሓውርታዊነት ባላት ኢትዮጵያ አብሮ ሊያኖረን ካስቻሉን ረቂቅ ማህበራዊ ስሪቶች መካከል አንዱ ማሳያ ነው፡፡ መካነ ቅርሱም የፓን-ኢትዮጵያ፣ የአንድነት፣ የመደመር፣ የሕብረትና የእኩልነት ተምሳሌት ነው፡፡ ይህ ጥናት በባህል፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካና በልማት ላይ ለሚዘጋጁ አገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ፖሊሲዎች በግብዐትነት የሚያገለግል ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱን የፖሊስ አውጭና አስፈጻሚ አካላት፣ በመካነ ቅርሱና በአካባቢው የልማት ስራ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበረሰቡን ለመረዳት መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

# 1.መግቢያ

በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች መንፈሳዊ ጉዞ (Piligrimage) የሚካሄድባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ እነዚህ ቦታዎች በክርስትና፣ በእስልምና፣ በዋቄፈና እንዲሁም በሌሎች ሀይማኖቶች ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ጉዞ የሚካሄድባቸው ቦታዎች እንደተጓዦቹ የኃይማኖት ዳራ የተለያዩ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ መንፈሳዊ ቦታዎች ተመሳሳይ የኃይማኖት ዳራ ያላቸው ግለሰቦች የሚሄዱባቸው ሲሆኑ፣ የተወሰኑት ደግሞ የተለያየ የኃይማኖት ዳራ ያላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች በጋራ መንፈሳዊ ጉዞ ያካሂዱባቸዋል፡፡

Pankhurst (1994:940)[1] በአገራችን የተለያዩ ቦታዎች የእስልምና፣ የክርስትና እና የሀገር በቀል ሀይማኖት ተከታዮች ያላቸውን የዘርና የሀይማኖት ድንበር በማለፍ በጋራ የሚያመልኳቸው መንፈሳዊ ቦታዎችና የሚፈጽሟቸው መንፈሳዊ ስርዓተከበራዎች (Rituals) መኖራቸውን ይገልጻል፡፡ ‹Ritual› የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ስርዓት፣ በዓል፣ ስነስርዓት፣ ክብረ በዓል እና ስርዓተከበራ በሚሉ ቃላት በተለያዩ ምሁራን ይተረጎማል፡፡ በዚህ ጥናት ቃሉ ስርዓተከበራ በሚል ተተርጉሟል፡፡

የተለያየ የኃይማኖት ዳራ ያላቸው ግለሰቦች በጋራ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያካሂዱባቸውና አምልኮ የሚፈጽሙባቸው ቦታዎች የተለዩ ባህርያት ይኖራቸዋል፡፡ ከእነዚህ ባህርያት መካከል ውሕደት (Syncretism) አንዱ ነው፡፡ ውሕደት የሚለውን ጽንሰሃሳብ የተለያየ ዳራ ያላቸው ኃይማኖቶችና ባህሎች በአንድ ላይ ሲገናኙ የሚፈጥሩት ጥምረት ነው (Rudolph,2004:82)፡፡ ይህ አይነት የኃይማኖትና የባህል ውሕደት ከሚስተዋልባቸው የአገራችን መንፈሳዊ ቦታዎች መካከል አንዱ ጥንታዊውና በርካታ መንፈሳዊ ተጓዦች ለአምልኮ የሚሄዱበት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ (Shrine) ነው፡፡

---

[1] - በዚህ ጥናት ውስጥ የተገለጹ አመታት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር የቀረቡ ከሆነ አመተ ምህረት (ዓ.ም) በሚል የተለዩ ናቸው፡፡ በሂጅራ (የእስልምና የቀን አቆጣጠር) የቀረቡ ከሆነ (ሂጅራ) በሚል የተለዩ ሲሆን፣ በአውሮፓ የዘመን አቆጣጠር የቀረቡት እንዳለ ተቀምጠዋል፡፡ የምሁራን ስም ስራቸው በተዘጋጀበት ቋንቋ መሰረት የቀረበ ነው፡፡ ምሁራንን በአክብሮታዊ (በአንቱታ) መግለጽ ተገቢ ቢሆንም ይህ የአክብሮት አገላለጽ የምሁራኑን ጾታ አያሳይም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ስማቸው የተገለጸ ምሁራንን በአንተታና በአንቺታ አቅርቤያለሁ፡፡

‘Shrine’ የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በአረብኛ ‘ማዛር’ በሚል ይተረጎማል፡፡ ይህን ቃል በአማርኛ በትክክል የሚገልጸው ቃል አላገኘሁም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ለቃሉ አቻ ይሆናል ብዬ ያሰብኩትን ‘መካነ ቅርስ’ የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ፡፡ ‘መካነ ቅርስ’ የሚለው ቃል ከነብያት፣ ከቅዱሳን ወይም ከፈጣሪ ወዳጆች ጋር ተያይዞ የሚገነባ ኪነህንጻን ወይም ኪነህንጻዎች የሚገኙበት ስፍራን የሚገልጽ ሲሆን፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራዎቹ በመሄድ ነብያትን፣ ቅዱሳንን ወይም የፈጣሪ ወዳጆችን እንደሚዘይሩ (እንደሚጎበኙ) Renard (2009፡221) ይገልጻል፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን እንደተመሰረተ የሚነገር ተፈጥሯዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ስፍራ ነው፡፡ መካነ ቅርሱ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በባሌ ዞን፣ በጎሎልቻ ወረዳ በአናጂና ቀበሌ ይገኛል፡፡ የአናጂና ቀበሌ ከአዲስ አበባ በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በ610 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ ደግሞ በ180 ኪ. ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

“ድሬ” መካነ ቅርሱ የሚገኝበት የአናጂና ቀበሌ ሌላው የመጠሪያ ስያሜ ነው፡፡ “ሼኽ ሁሴን” መካነ ቅርሱን የመሰረቱት ሲሆኑ፣ በተከታዮታቸው ዘንድ ቅዱስ፣ ነብይና ሰውን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኙ እንደሆኑ ይታመንባቸዋል፡፡ “ሼኽ” የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን፣ ቃሉ በተለያዩ የእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮዎች የተለያዩ እሳቤዎች አሉት፡፡ በቃሉ ላይ ያሉ የተለያዩ እሳቤዎች እንዳሉ ሆነው፣ በጥቅሉ መሪ፣ አባት፣ አንጋፋ፣ ከፈጣሪ ጋር ልዩ ቅርበት ያለውና ሰውን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝ የሚሉ ትርጓሜዎች እንዳሉት Renard (2009፡220) ይገልጻል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለሚስተዋለው የኃይማኖትና የባህል ውሕደት የተለያዩ ኃይማኖቶች በተለያዩ ወቅቶች በስፍራው ላይ የፈጠሩት ተጽዕኖ እንዲሁም የተለያየ ኃይማኖት ተከታዮች ወደ ስፍራው ለአምልኮ መሄድ በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኃይማኖትና የባህል ውሕደት ከሚስተዋልባቸው መንፈሳዊ መገለጫዎች መካከል በበዓላት አከባበር ላይ የሚቀርቡ ክወናዎች (Performances) በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአገራችን የእስልምና ሀይማኖት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው ነው፡፡ ስፍራው የእስልምና ሀይማኖት በኢትዮጵያ በተለይም በደቡብ ምስራቅ የአገሪቷ አካባቢዎች እንዲስፋፋ ከፍተኛ መሰረት የጣለ እንደሆነ Trimingham (1952:253) እና Braukämper (1989:15) ይገልጻሉ፡፡ ስፍራው ከእምነት ማዕከልነቱ በተጨማሪ የተጠናከረ

የኃይማኖት ትምህርት ማሰልጠኛ ተቋም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች የሚመጡ ደረሳዎች (ተማሪዎች) በመካነ ቅርሱ መንፈሳዊ ትምህርት ይማራሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ (Muuda)[2] በዓላት በአመት ሁለት ጊዜ በደማቅ ሁኔታ ይከበራሉ፡፡ "ሙዳ" የሚለው ቃል ስርወ-ምንጩ አፋን ኦሮሞ ነው፡፡ ሙዳ እንደ አውዱ ሁኔታ ግስ ሲሆንና ስም ሲሆን የተለያየ ትርጉም እንዳለው Jeylan (2005፡26) ይገልጻል፡፡ ሙዳ የሚለው ቃል ግስ ሲሆን ሶስት ትርጉሞች አሉት፡፡ እነሱም፡- መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ፣ መቀባትና ስጦታ መስጠት ወይም መስዋዕት ማቅረብ ናቸው፡፡ ሙዳ የሚለው ቃል ስም ሲሆን ደግሞ ሶስት ትርጉሞች አሉት፡፡ እነሱም፡- ቅባት፣ መንፈሳዊ ጉዞና መንፈሳዊ ተጓዥ ናቸው፡፡ ሙዳ ከእነዚህ ትርጓሜዎች በተጨማሪ ሹመት የሚል ትርጉም አለው፡፡

ከእነዚህ ትርጉሞች እንደምንረዳው ሙዳ የሚለው ቃል መንፈሳዊ ጉዞን፣ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግን፣ መንፈሳዊ ተጓዥን፣ መቀባትን፣ ለመቀባት የሚያገለግል ቅባትን፣ ስጦታ መስጠትንና ሹመትን የሚገልጽ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ሙዳ የሚለው ቃል በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ በዓላትን፣ በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን፣ ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞን እንዲሁም ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርግን ተጓዥ የሚገልጽ ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከበሩ ሁለት የሙዳ በዓላት 'ሐጅ' እና 'ዛህራ ገልገላ ኀበና' በሚሉ ስያሜዎች ይታወቃሉ፡፡ ለሐጅ እና ለዛህራ ገልገላ ኀበና የሚከበሩት የሙዳ በዓላት እያንዳንዳቸው እስከ 10 ቀናት የሚሸፍኑ ደማቅ ኃይማኖታዊ በዓላት ናቸው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓተከበራዎች አሉ፡፡ እነዚህን ስርዓተከበራዎች የሙዳ በዓል ከመድረሱ በፊትና በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ናቸው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና፣ የክርስትና፣ የዋቄፈና እና የሌሎች ሀይማኖቶች ተከታዮች፣ የተለያየ ብሔር ተወላጆች እንዲሁም የውጪ አገር ዜጎች በጋራ አምልኮ ይፈጽማሉ፡፡

በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይም በርካታ ቁጥር ያላቸው መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅትም እስከ 500,000 ተሳታፊዎች በዓመት ሁለት ጊዜ ወደ ስፍራው እንደሚመጡ ይገመታል፡፡ ለመንፈሳዊ ስርዓት ወደ ስፍራው የሚመጡ

---

[2] - በዚህ ጥናት በሳባ ፊደል ሲጻፉ የአነባበብ ስህተት የሚፈጥሩ የኦሮምኛ ቃላትን በትክክለኛው አነባበብ እንዲነበቡ በሚል በቅንፍ ውስጥ በላቲን ፊደል ተጽፈዋል፡፡

ሰዎች ብዛታቸውን በሚመለከት የተለያዩ መረጃዎች አሉ፡፡ Braukämper (1977:126) 100,000 ሲል፣ Sintayehu (2000፡2) ደግሞ ከ200,000 በላይ ይላል፡፡

500,000 የሚለው ቁጥር በ2008 ዓ.ም የሙዳ በዓል ከመስከረም 10 እስከ መስከረም 22 ድረስ ሲከበር ካየሁት ህዝብ በመነሳት የገመትኩት ነው፡፡ ለዚህ ግምቴ መነሻ ምክንያት የሆኑኝ መንፈሳዊ ተጓዦችን ወደ ስፍራው የሚያመላልሱ የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች የቆረጡት የመውጫ ትኬት ብዛትና በስፍራው የተገኙ ሌሎች ግለሰቦች ያቀረቡት ግምት ናቸው፡፡ በዚሁ ዓመት በበዓሉ ላይ የተገኙ ሰዎች ብዛት 1 ሚሊዮን እንደሆነ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮና የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በጋራ ሪፖርት አድርገዋል፡፡

ይህ ሀይማኖታዊ ስፍራ በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ ለአምልኮ የሚሄድበት በመሆኑም ይመስላል Braukämper (1984: 773) መካነ ቅርሱን “የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ መካ” በሚል ይገልጸዋል፡፡ ከኢትዮጵያ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ወደ መካነ ቅርሱ ስለሚሄዱ Eliyas (2002፡19) “ትንሿ ኢትዮጵያ” ብሎ ገልጾታል፡፡ እነዚህ አገላለጾች እንዳሉ ሆነው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከኢትዮጵያዊያን ውጪ ያሉ ሕዝቦችን፣ ከእስልምና ውጪ ያሉ የሌሎች ኃይማኖት ተከታዮችን ጭምር በአንድ የሚያገናኝ በመሆኑ “ትንሿ ዓለም” በሚል መግለጽ ያስችላል፡፡

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

በዚህ ርዕሰጉዳይ ላይ የፒ.ኤች.ዲ. ማሟያ ጽሑፍ እንዳዘጋጅ መነሻ የሆኑኝ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

**አንደኛ፡-** በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከበሩ የሙዳ በዓላት ልዩ ባህርያት አሏቸው፡፡ ከእነዚህ ልዩ ባህርያት መካከልም የተለያየ የሀይማኖትና የባህል ዳራ ያላቸው ህዝቦች በጋራ የሚከውኑት እንዲሁም የክርስትና፣ የእስልምና እና የዋቄፈና ሀይማኖት ተቋማት ዘንድ የሚከናወኑ አንዳንድ ስርዓቶች የሚንጸባረቅበት መሆኑ ነው፡፡ ይህ መሆኑም ስርዓተከበራው የሀይማኖትና የባህል ውሕደት እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል፡፡ እንደዚህ አይነት ልዩ ባህርይ ያላቸውን የአገራችን ሀብቶች በትኩረት ብናጠና የኢትዮጵያን ልዩ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ፍልስፍናዊና ታሪካዊ ገጽታ በተወሰነ መልኩ እንድንረዳ ያስችላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እንደዚህ አይነት ባህርይ ያላቸው ሀብቶቻችን የሀይማኖትና የባህል በሓውርታዊነት (Diversity) ባላት አገራችን አብሮ ሊያኖሩን ያስቻሉንን ረቂቅ ማህበራዊ ስሪቶች (Social fabrics) ለመረዳት ያስችላሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ በመሆኑም ይህንን ጥናት ባካሄድ 'ድብቅ ምስጢር' በሚመስለኝ ረቂቅ ማህበራዊ ስሪትና ልዩ አስተሳሰብ ላይ የተወሰነ ግንዛቤ አገኛለሁ በሚል እምነትና ፍላጎት ነው፡፡

**ሁለተኛ፡-** በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ የተሰሩ ወይም ሌሎች ርዕሰጉዳዮችን ሲያነሱ ስለመካነ ቅርሱ የሚገልጹ የምርምር መጣጥፎች፣ መጻሕፍት፣ የመመረቂያ ጽሑፎችና የኢንቬንተሪ ሪፖርቶች በተለያዩ አጥኚዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ትምህርት ክፍሎች 3 የባችለር ዲግሪ እና 5 የማስተርስ ዲግሪ መመረቂያ ጥናቶች ተሰርተዋል፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ 1 የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ጥናት በውጪ አገር ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም 3 መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል፡፡

በመካነ ቅርሱ ወይም በሌሎች ርዕሰጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገው ስለመካነ ቅርሱ የተወሰነ መረጃ የሰጡ 9 አርቲክሎች በውጭ አገርና በአገር ውስጥ ተመራማሪዎች ተጽፈዋል፡፡ ከእነዚህ ጥናታዊ ጽሑፎች በተጨማሪ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም በባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጁ 3 የኢንቬንተሪ ሪፖርቶች አሉ፡፡[3]

ከእነዚህ የተለያዩ ስራዎች መካከል የተወኑት ስለሙዳ ስርዓተከበራና ስለመንፈሳዊ ጉዞና ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች ከተነሱበት የጥናት ወሰን አንጻር ስርዓተከበራዎቹን በጥልቀት ያላጠኗቸው በመሆኑ እንዲሁም በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚገኙ ቃላዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶች ላይ ትኩረት በማድረግ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ አገር ዩኒቨርሲቲዎች የተሰራ የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ባለመኖሩ ይህን ጥናት እንዳደርግ መነሻ ምክንያት ሆኖኛል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በስፍራው ላይ ያለውን የጥናት ክፍተት በተወሰነ ደረጃ ለመሙላት ያስችላል፡፡

**ሶስተኛ፡-** በሙዳ በዓላት ወቅት በአገራችን የሚገኙ የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የውጭ አገር ዜጎች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ እነዚህ ሕዝቦችም የእስልምና፣

[3] - ከመካነ ቅርሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አርቲክሎች፣ ጥናታዊ ጽሑፎች፣ መጻሕፍትና ኢንቬንተሪዎች ይዘት በምዕራፍ 2 ተብራርቷል፡፡

የክርስትና፣ የዋቄፈና እንዲሁም የሌሎች ኃይማኖቶች ተከታዮች ናቸው። ይህ ሁኔታ የተለያየ ባህልና ኃይማኖት ያላቸው ሕዝቦች በአንድነት አምልኮ እንዲፈጽሙ ምክንያት ሆኗል። ይህ መሆኑ የእርስበርስ ትውውቅ፣ መከባበር፣ አንድነትና ሰላም ከመፍጠር አንጻር ከፍተኛ አገራዊ ጠቀሜታ አለው። ይህ አገራዊ ጠቀሜታ ከሙዳ ስርዓተከበራ አንጻር እንዴት እንደሚንጸባረቅና ስፍራው ያለውን ልዩ ባህርይ ለማጥናት ያለኝ ፍላጎት ይህንን ጥናት እንዳካሂድ ምክንያት ሆኖኛል።

በእነዚህ መነሻ ምክንያቶች ላይ ተመስርቶ የተካሄደው ይህ ጥናት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ያላቸውን የአከባበር ስርዓቶች ያላቸውን ክወና፣ መስተጋብር፣ በክወናዎች ላይ የሚስተዋሉ የሀይማኖትና የባህል ውሕደቶች እንዲሁም ወደ ስፍራው የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች ያላቸውን ባህርይ የሚያሳይ ነው።

ይህ ጥናት በሼኽ ሁሴን ታሪክ፣ በመካነ ቅርሱ ታሪክ፣ የሙዳ በዓላት ከመድረሳቸው በፊት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች፣ በበዓሉ ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች፣ ከሙዳ በዓላት ካለፈ በኋላ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች፣ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች፣ ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ያለው ባህርይ፣ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ኪነሕንጻዎችና ታሪካቸው፣ የሼኽ ሁሴን የሀይማኖት፣ የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ አስተዋጽኦዎች፣ በሼኽ ሁሴን ላይ የሚነገሩ ሚቶች እንዲሁም በሙዳ በዓላት ላይ የተስተዋሉ ለውጦችና የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በተለያየ ደረጃና አይነት በመካነ ቅርሱ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች ያልዳሰሷቸውን እንዲሁም በትኩረት ያላጠኗቸውን ርዕሰጉዳዮች በስፋት የሚያይ በመሆኑ በመካነ ቅርሱ ያለውን የጥናት ክፍተት ለመሙላት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል።

## 1.2. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

- በሼኽ ሁሴን ማንነትና በመካነ ቅርሱ ላይ ያሉ እሳቤዎች ምንድን ናቸው?
- የመካነ ቅርሱና የአካባቢው ነዋሪዎች ያላቸው ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎች ምንድን ናቸው?
- ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚካሄድ መንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ምክንያቶችና ያለው ልዩ ባህርያት ምንድን ናቸው?

- ❖ የሙዳ በዓላት ከመድረሳቸው በፊትና በበዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ምን ምን ናቸው?
- ❖ በሙዳ ስርዓተከበራዎች፣ በሼኽ ሁሴን ማንነት እና በመካነ ቅርሱ እሳቤዎች ላይ የሚስተዋሉ ውሕደቶች ምንድን ናቸው?
- ❖ በሙዳ ስርዓተከበራ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች እና ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች ምን ምን ናቸው?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

## አብይ ዓላማ

- ✓ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ ስርዓተከበራ አከዋወን፣ መስተጋብር፣ ውህደት እና መንፈሳዊ ጉዞው ያለውን ባህርይ መተንተን።

## ንዑስ ዓላማዎች

- በሼኽ ሁሴን ማንነትና በመካነ ቅርሱ ላይ ያሉ እሳቤዎችን ማሳየት።
- የመካነ ቅርሱና የአካባቢው ነዋሪዎች ያላቸውን ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎች መግለጽ።
- ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚካሄድ መንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ምክንያቶችንና ያለውን ልዩ ባህርያት መግለጽ።
- የሙዳ በዓላት ከመድረሳቸው በፊትና በበዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን በቅደም ተከተል መተንተን።
- በሙዳ ስርዓተከበራዎች፣ በሼኽ ሁሴን ማንነት እና በመካነ ቅርሱ እሳቤዎች ላይ የሚስተዋሉ ውሕደቶችን መግለጽ።
- በሙዳ ስርዓተከበራ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን እና ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶችን ማሳየት።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በርዕሰጉዳይና በቦታ የተወሰነ ነው። ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በተለያዩ ወቅቶች በርካታ መንፈሳዊ ጉዞዎች ይካሄዳሉ። በስፍራውም በርካታ ስርዓተከበራዎች በተለያዩ ወቅቶች ይከወናሉ። በስፍራው የሐጅ እና የዛሕራ የሙዳ በዓላት፣ የመውሊድ (የነብዩ መሃመድ የውልደት ቀን መታሰቢያ) በዓል፣ የአሹራ በዓል[4]፣ የኢድ-አል-ፈጥር (የረመዳን) በዓል፣ የዕለትዕለት የአምልኮ ስርዓተከበራዎች፣ ሳምንታዊ የወዳጃ ስርዓት እንዲሁም ልዩ ወቅታዊ ጉዳዮች (ድርቅ፣ የዝናብ እጥረት፣ ጦርነት ወይም ወረርሽኝ) ሲከሰቱ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ናቸው።

ይህ ጥናት ከርዕሰጉዳይ አንጻር በሙዳ በዓላትና በበዓላቱ ወቅት ወደ ስፍራው በሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች ላይ የሚያተኩር ነው። በመሆኑ የመውሊድን፣ የአሹራን፣ የኢል-አል-አድሃን፣ የዕለትዕለትን፣ የወዳጃ ስርዓትን እንዲሁም ልዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ሲከሰቱ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን አያካትትም።

የሙዳ በዓላት በአናጂና ቀበሌና በአካባቢው በሚገኙ አራት የተለያዩ ቦታዎች ይከበራሉ። እነዚህም ቦታዎች የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ቅጽር ግቢ፣ የዶዶታ ተራራ፣ የአበልቃሲም ተራራና በአርሲ ዞን የሰኪና ቀበሌ ናቸው። በበዓላቱ ወቅትም በእነዚህ ስፍራዎች መንፈሳዊ ጉዞ ይካሄዳል። ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር በዶዶታና በአበልቃሲም ተራራዎች ላይ እንዲሁም በሰኪና ቀበሌ የሚከበሩትን የሙዳ በዓላት አያካትትም።

በእነዚህ ስፍራዎች የሚከበሩ የሙዳ በዓላትን ማካተት ያልተቻለበት ዋና ዋና ምክንያቶች፣ ስፍራዎቹ ከመካነ ቅርሱ እርቀት ስላላቸው፣ ወደ ስፍራዎቹ ለመጓዝም ረጅም ሰዓት የእግር ጉዞ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ከፍተኛ ተራራዎችን መውጣት ስለሚያስፈልግ፣ ከመካነ ቅርሱ ወደ ቦታዎቹ ለመድረስ የሚያስችል የመኪና መንገድ ባለመኖሩ እንዲሁም ያለው የእግር መንገድ አመቺ ባለመሆኑ ነው።

---

[4] - ስለ አሹራ በዓል ምንነት በምዕራፍ አምስት ተብራርቷል።

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ ከጠቀሜታዎቹ መካከል በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ ስለድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አካባቢያዊ፣ ታሪካዊና ሚታዊ ጉዳዮችን እንዲሁም በውስጡ ስለሚገኙ ተፈጥሯዊ፣ ቃላዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶችን ለአንባቢ ያስተዋውቃል፡፡
- ✓ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላትና መንፈሳዊ ጉዞ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ከዚህ በፊት የተካሄደ ጥናት የለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በፎክሎር፣ በሶሻል አንትሮፖሎጂ፣ በታሪክ፣ በሙዚቃ፣ በሀይማኖት፣ በባህልና በቅርስ ዙሪያ ጥናት ለሚሰሩ አካላት የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፡፡
- ✓ የሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን በመሰነድ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡
- ✓ የፎክሎር ጥናቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ታህታይ መዋቅር (Base structure) ለመረዳት መሰረት ናቸው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ታህታይ መዋቅር ከሚያሳዩ ፎክሎሮች መካከል ስርዓተከበራን መሰረት በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚዘጋጅ የባህል ፖሊሲ፣ የትምህርት ስርዓት፣ የልማትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ግብዓት በመሆን ያገለግላል፡፡
- ✓ በኢትዮጵያ ያለውን የእስልምና ኃይማኖትና የተከታዮቹን አጠቃላይ ገጸ-ትባሬ (Eschatology) በማጥናትና ከነባር ባህሎች ጋር ያለውን የውሕደት ባህርይ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የእስልምና ኃይማኖት ከሌላው ዓለም በተለየ በኢትዮጵያ ያለው ልዩ ባህርይ እንዲታወቅ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የኢትዮጵያ የእስልምና ኃይማኖት ጥናት የአፍሪካ ተኮር የማንጸሪያ ስልት (Afro-centric perspective) መሰረት በማድረግ እንዲጠና አቅጣጫ በማሳየት አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- ✓ በጥናቱ ከሚገኘው ውጤት መነሻነት በአገራችን ያለውን የኃይማኖት ስርዓት፣ የሰው ልጅ አምልኳዊ እሳቤ፣ እሴት፣ የኃይማኖት ታሪክ ወይም ውሕደት ላይ ሀገር በቀል ንድፈሃሳቦችን (Indigenous theories) ለማፍለቅ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

## 1.6. የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በአስር ምዕራፎች የተከፈለ ነው። በምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ ጠቀሜታዎች ተካተዋል። ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፎች ዳሰሳ ነው። ይህ ክፍል የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን፣ ጽንሰሃሳባዊ ዳራንና የጥናቱ ንድፈሃሳቦችን የያዘ ነው። ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ስነዘዴ ነው። በዚህ ክፍል የጥናቱን ስነዘዴንና ስነምግባርን የሚገልጽ ነው። ምዕራፍ አራት፡- የሼኽ ሁሴን ታሪክ፣ ሰብዕና፣ ሚና እና በመካነ ቅርሱ ላይ ያሉ እሳቤዎችን የሚያሳይ ነው። ምዕራፍ አምስት፡- የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ እና የአናጂና ቀበሌና የአካባቢው ነዋሪዎች ያላቸውን ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ የሚያሳይ ነው።

ምዕራፍ ስድስት፡- የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ያለውን ባህሪና ተጓዦች ወደ ስፍራው የሚሄዱባቸውን ጉዳዮች የሚያሳይ ነው። ምዕራፍ ሰባት፡- በዓላቱ መከበር ከመጀመራቸው በፊት የሚከወኑ ቅድመ ሙዳ ስርዓተከበራዎች የተተነተኑበት ነው። ምዕራፍ ስምንት፡- በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተ ከበራዎች ባላቸው የክዋኔ ቅደም ተከተል መሰረት የቀረበበት ነው። ምዕራፍ ዘጠኝ፡- በሙዳ በዓል ላይ ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች እና የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች የተገለጹበት ነው። ምዕራፍ አስር፡- የጥናቱ ማጠቃለያ፣ የጥናቱ ግኝቶችና የይሁንታ ሃሳቦችን ይዟል። በጥናቱ ውስጥ ዋቢ ጽሑፎች፣ ፎቶ ግራፎች፣ ካርታዎችና የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር ተካተዋል።

## 2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ የጽንሰሃሳባዊ እና የንድፈሃሳባዊ ዳሰሳ

ይህ ምዕራፍ ሶስት አብይ ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ አንደኛው፤ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ነው፡፡ ሁለተኛው ጽንሰሃሳባዊ ዳራ ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ የጥናቱ ንድፈሃሳቦችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ አብይ ክፍሎች በተናጠል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶች በውጭ አገር እና በአገር ውስጥ ምሁራን ተካሂደዋል፡፡ ከጥናቶቹ መካከል የተወሰኑት መካነ ቅርሱን ብቻ በሚመለከት የቀረቡ ሲሆኑ፣ የተወሰኑት ደግሞ ሌሎች ርዕሰጉዳዮችን ሲዳስሱ ስለመካነ ቅርሱ በተወሰነ ደረጃ የገለጹ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች በምርምር መጣጥፍ፣ በመመረቂያ ጥናቶች፣ በመጻሕፍትና በኢንቬንተሪ ሪፖርቶች መልክ የቀረቡ ናቸው፡፡ የእነዚህን ስራዎች የትኩረት አቅጣጫና ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት በቀረቡበት ቅርጽ መሰረት ቀጥለን እንመልከት፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ ጥናት በማድረግ የምርምር መጣጥፍ ያሳተሙ ምሁራን 6 ናቸው፡፡ የእነዚህ ምሁራን ስራዎች በቀረቡበት አመት ቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡፡

Cerulli, Enrico (1922) “The Folk-Literature of the Galla of Southern Abyssinia.” በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ በጥናቱም ሼኽ ሁሴንን የሚያወድሱ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥሞችን በመሰብሰብ ተንትኗል፡፡

Andrzejewski, B. Witalis (1972) “Allusive Diction in Galla Hymns in Praise of Sheikh Hussien of Bale.” በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ በዚህ ጥናትም በሼኽ ሁሴን ላይ የሚነገሩ አፈታሪኮችን፣ ገድሎችን እንዲሁም የቦታና የሰው ስሞች የቀረቡባቸውን የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥሞች አቅርቧል፡፡

አጥኚው በ1975 ደግሞ “A Genealogical Note Relevant to the Dating of Sheikh Hussein of Bale.” በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ ጥናቱ በዋናነት የሼኽ ሁሴንን የውልደት ዘመንና ያላቸውን የዘር ሀረግ አሳይቷል፡፡

Braukämper, Ulrich (1977) "Islamic Principalities in Southeast Ethiopia between the Thirteenth and Sixteenth Centuries." በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ ጥናቱም ከ13ኛው እስከ 16ኛው መቶ ክ/ዘመን በደቡብ ምስራቅ የአገሪቷ አካባቢዎች የእስልምና ሀይማኖት የመስፋፋት ታሪክን እንዲሁም የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለእስልምና ሀይማኖት መስፋፋት ያበረከተውን አስተዋጽኦ አሳይቷል፡፡

አጥኚው በ1984 ደግሞ "The Islamization of the Arsi-Oromo." በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ ጥናቱም በአርሲና በባሌ ማህበረሰቦች ዘንድ እስልምና የተስፋፋበትን ታሪክና የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የነበረውን ሚና አሳይቷል፡፡

Baxter, Paul (1987) "Some Observations on the Short Hymns Sung in Praise of Sheikh Nur Hussein of Bale." በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ በዚህ ጥናትም የሼኽ ሁሴንን ገድል የሚገልጹ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥሞችን አቅርቧል፡፡

Jeylan W. Hussein (2005) "The Functional of African Oral Arts: The Arsi-Oromo Oral Arts in Focus." በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ በጥናቱም የሼኽ ሁሴንን ታሪክ፣ ወደ ቦታው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ፣ አርሲዎች በሼኽ ሁሴን ላይ የሚናገሩትን ሚቶችና አፈታሪኮች፣ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ይዘትና ያለው ጠቀሜታ፣ የባሮ ከዋኞች ክወናቸውን የሚያቀርቡበት ስልትና የአድማጩ ስሜትን፣ በዋሬ (waare)[5] ላይ የሚቀርቡ የሂክማ ስርዓትና የዝክሪ ስርዓት፣ ወደ ድሬ በሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞና በኦሮሞ ብሔር የዋቄፈና ኃይማኖት መሰረት ወደ አባ ሙዳ (Abbaa Muudaa) በሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ መካከል ያለውን ተመሳስሎ፣ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለሰሜን ምስራቅ ሙስሊሞች ያለው ጠቃሚ ምልክትነት፣ በመካነ ቅርሱ በሚከወኑ ስርዓቶችና በመካ በሚካሄዱ ስርዓቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎ እንዲሁም የአርሲ ኦሮሞዎች በመካነ ቅርሱ ግንባታ ወቅት ያላቸውን ሚና አቅርቧል፡፡

Østebo, Terji (2009) "Religious Change and Islam, The Emergence of the Salafi Movement in Bale." በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ በዚህ ጽሑፍም በባሌ የሰለፊያ አስተምህሮ እንቅስቃሴ አጀማመር፣ መስፋፋት፣ እድገት እንዲሁም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለሱፊዝም አስተምህሮ መስፋፋት ያበረከተውን አስተዋጽኦ ተገልጿል፡፡

---

[5] - ስለ ዋሬ ምንነትና በዋሬ ላይ የሚቀርቡ ስርዓቶች በምዕራፍ 8 ቀርቧል፡፡

አጥኚው በ2014 ደግሞ "Claims for Authority at the Shrine of Shykh Husayn, Ethiopia." በሚል ርዕስ የምርምር መጣጥፍ ጽፏል፡፡ በጽሑፉም የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች የነበራቸውን ታሪክና በአሁኑ ወቅት ባለው የመካነ ቅርሱ አመራር ላይ የሚነሳውን የይገባኛል ክርክር ተብራርቷል፡፡

በእነዚህ ምሁራን የቀረቡ የምርምር መጣጥፎች ስለሼኽ ሁሴን የትውልድ ዘመንና ያላቸው የዘር ሃረግ፣ ስለሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ፣ ስለባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥሞች፣ ከእስልምና ሀይማኖት መስፋፋት ጋር በተያያዘ መካነ ቅርሱ የነበረው ሚና፣ የአስተዳደር ክርክሮችና ስለዋሬ ስርዓት የሚገልጹ ናቸው፡፡ እነዚህ አጥኚዎች (ከጀይላን በስተቀር) ስለሙዳ በዓላት፣ መንፈሳዊ ጉዞና የኃይማኖት ውሕደት ምንም አይነት መረጃ አልሰጡም፡፡ የጀይላን ጥናትም ቢሆን በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ የተወሰኑ ስርዓቶችን በጥቂቱ ከመግለጽ ባለፈ ዝርዝርና ጥልቅ መረጃ አይሰጥም፡፡

በሼኽ ሁሴንና በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ዙሪያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባችለርና የማስተርስ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሑፎች ያዘጋጁ አጥኚዎች 8 ሲሆኑ፣ የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሑፍ በውጪ አገር ዩኒቨርሲቲ በ1 አጥኚ ተሰርቷል፡፡ የእነዚህን ምሁራን ስራዎች በቀረቡበት አመት ቅደም ተከተል ቀጥለን እንመልከት፡፡

Eshetu Setegn (1973) "Sheikh Hussayn of Bale and His Followers." በሚል ርዕስ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በታሪክ ትምህርት ክፍል ሰርቷል፡፡ በጥናቱም ስለሼኽ ሁሴን ታሪክ፣ ስለመካነ ቅርሱ ታሪክ፣ በአካባቢው የእስልምና ኃይማኖት የመስፋፋት ታሪክና የሼኽ ሁሴን ገድላት ተገልጸዋል፡፡ በዚህ ጥናት የሙዳ በዓላት በዓመት ሁለት ጊዜ እንደሚከበሩ ከመግለጽ ባለፈ የቀረበ ተጨማሪ መረጃ የለም፡፡

ሐሊማ መሐመድ (1973 ዓ.ም.) "ለባሌው ሼኽ ሁሴን የተገጠሙ ግጥሞች፡፡" በሚል ርዕስ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ሰርታለች፡፡ የጥናቱ አብይ ዓላማ ሼኽ ሁሴንን ለማወደስ የሚቀርቡ የባሮ መንፈሳዊ ግጥሞችን ማሳየት ነው፡፡ ይህ ጥናት የባሮ ግጥሞች ያላቸውን አውዳዊ ትርጉም የሚያሳይ ሲሆን፣ ስለሼኽ ሁሴን ታሪክም በተወሰነ ደረጃ የተገለጸበት ነው፡፡ በዚህ ጥናት የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በሙዳ በዓላት ወቅት እንደሚቀርቡ ከመግለጽ ባለፈ ስለሙዳ በዓላትና መንፈሳዊ ጉዞው የቀረበ ተጨማሪ መረጃ የለም፡፡

ዳንኤል አባተ (1984 ዓ.ም) "በሰኪና የኑር ሁሴን ስርዓተ-አምልኮና ድራማዊ ገጽታ፡፡" በሚል ርዕስ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም በትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ሰርቷል፡፡ ጥናቱም በቀድሞው የአርሲ ክፍለ ሀገር በአሚኛ ሲፈ አውራጃ በሚገኘው ሰኪና በሚባል ስፍራ የተሰራ ነው፡፡ በጥናቱም ስለሼኽ ሁሴን ተዓምራት የሚነገሩ ታሪኮችን፣ ተዓምራታቸውን የሚገልጹ የባሮ ግጥሞችንና በስፍራው የሚከወኑ ስርዓተ-አምልኮዎችን አሳይቷል፡፡ ይህ ጥናት በሰኪና ላይ በመሰራቱ ከእኔ ጥናት ጋር ቢለያይም በቦታው የሚከወኑ አንዳንድ ስርዓቶች በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚከወኑ ስርዓቶች ጋር ተመሳሳይ በመሆናቸውና ሼኽ ሁሴንን ማዕከል ያደረገ አምልኮ ስለሚፈጸም ከእኔ ጥናት ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡

Umer Nure (2006) "The Piligrime to Dirre Sheikh Hussein: Its Social Organazation and Overhual Roles." በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ሰርቷል፡፡ የጥናቱ አብይ ዓላማ የድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ጉዞ ያለውን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ስርዓተከበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እንዲሁም ያለውን ሁለንተናዊ ሚና ማሳየት የሚል ነው፡፡

የጥናቱ ንዑስ ዓላማዎች የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአካባቢው እስልምና ከመስፋፋቱ በፊትና ከተስፋፋ በኋላ ያለውን ሁኔታ መዳሰስ፣ የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ያላቸው ማህበራዊ አደረጃጀት እንዴት እንደተዋቀረና መካነ ቅርሱ ለአካባቢው ነዋሪዎች ያለውን አገልግሎት መፈተሽ፣ ማህበራዊ፣ ስርዓተከበራዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በአካባቢው ነዋሪዎችና በመንፈሳዊ ተጓዦች መካከል የፈጠሩትን ግንኙነቶች ማሳየት የሚሉ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ዓላማዎች በተጨማሪ በአመት ሁለት ጊዜ የሚካሄዱ ስርዓቶችንና ያላቸውን ትዕምርታዊ እሴቶች መዳሰስ፣ በስርዓተከበራው ወቅት የደርጋዎች (የነዋሪዎች)[6]፣ የመካነ ቅርሱ መሪዎችና የኡሌዎች (የመንፈሳዊ ሙዚቃ ከዋኞች)[7] ሚናና ያላቸውን ደረጃ መተንተን እንዲሁም መንፈሳዊ ተጓዦቹ ለመካነ ቅርሱ ያላቸውን አመለካከት፣ ሰላምና አንድነትን ለመፍጠር፣ ግጭቶችን ለመፍታት፣ ለሀይማኖት መቻቻል፣ ለባህል ልውውጥ፣ ለተለያዩ ብሔሮች የእርስበርስ ግንኙነትና ለአካባቢ ጥበቃ መካነ ቅርሱ ያለው ሚና እንዲሁም በየጊዜው

---

[6] - ስለደርጋዎች ምንነትና ያላቸውን ማህበራዊ አደረጃጀት በሚመለከት በምዕራፍ 5 ቀርቧል፡፡

[7] - ስለኡሌዎች ምንነት፣ የማዕረግ አሰጣጥ ስርዓትና የሚያቀርቡት ክወና ያለውን ባህርያት በሚመለከት በምዕራፍ 5 ቀርቧል፡፡

የመጡ ለውጦችን መመርመር የሚሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ጥናቱ እስልምና በኦሮሞ ሀገረሰባዊ ሀይማኖት ውስጥ እንዴት እንደቆየና የኦሮሞ ሀገረሰባዊ ሀይማኖትና እስልምና ያላቸውን የእርስበርስ ተጽዕኖ አሳይቷል፡፡

ይህ ጥናት በእኔ ጥናት ውስጥ በዋናነት የሚነሱትን የሙዳ ስርዓተከበራ፣ መንፈሳዊ ጉዞና የኃይማኖት ውህደት በተወሰነ ደረጃ አካቷል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት በሙዳ በዓላት ወቅት በተለያዩ ቦታዎች የሚካሄዱ ስርዓተከበራዎችን በአንድ ምዕራፍ ስር በንዑስ ርዕስነት የቀረበ በመሆኑ የስርዓቶችን ክወና በዝርዝርና በጥልቀት አላሳየም፡፡ ይህ ጥናት ከጥናት ስነዘዴ አንጻር ውስንነቶች አሉት፣ ውስንነቱም በጣም ሰፋፊ ርዕሶችን በአንድ ጥናት ውስጥ ለመዳሰስ ከመፈለግ የመጣ ነው፡፡ ይህ መሆኑም ጥናቱ ሰፊ ርስስጉዳዮችን የዳሰሰ ነገር ግን ርዕስጉዳዮቹን ከማስተዋወቅ ባለፈ በጥልቀት ያላጠና ሆኗል፡፡ ይህ ድክመትም በጥናቱ ዓላማዎች ብዛት የመጣ መሆኑ በግልጽ ያሳያል፡፡ የእኔ ጥናት በሙዳ ስርዓተከበራና መንፈሳዊ ጉዞው ላይ ትኩረት በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ ያልተነሱ ጉዳዮችን በጥልቅ የሚያጠና ነው፡፡

Abinet Eshete (2011) “Impacts of Piligrimage Tourism: The Case of Bale Dire Sheikh Hussein.” በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአርኪዮሎጂና ሔሪቴጅ ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ሰርቷል፡፡ የጥናቱ ዓብይ ዓላማ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለባሌ ማህበረ-ባህላዊ እድገት ያለውን ጠቀሜታ ማሳየት ነው፡፡ የጥናቱ ንዑስ ዓላማዎች ድሬ ሼኽ ሁሴንን የኢኮኖሚ ቱሪዝም መዳረሻ ማድረግ፣ መካነ ቅርሱን ለሀይማኖት ቱሪዝም ጥናት ማሳያ ማድረግ፣ መካነ ቅርሱ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ሀይማኖታዊ ማዕከላት እንዴት የበለጠ ሀይማኖታዊ የበላይነት እንደፈጠረ መመርመር፣ አካባቢያዊ የቱሪስት ኢንዱስትሪን ማሳደግና የጎብኚዎችን ምቾት መጠበቅ፣ መንፈሳዊ ቦታው ላይ ያሉ የተለያዩ ተግዳሮቶችን መመርመር፣ የቱሪስቶች ልምድና በአካባቢው ላይ ያላቸውን አድናቆት ማሳደግ የሚሉ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ የተወሰኑ ስርዓቶችን በአንድ ምዕራፍ ስር በንዑስ ርዕስነት ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ስለ ስርዓተከበራዎቹ ዝርዝርና ጥልቅ መረጃ አይሰጥም፡፡

Eliyas Teha (2012) “Understanding Rituals and Analyzing Songs Performed at Dirre Sheikh Hussein.” በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ሰርቷል፡፡ የጥናቱ አብይ ዓላማ የድሬ ሼኽ ሁሴን የተለያዩ ስርዓተከበራዎች ያላቸውን ሀቲት (Discourse) እና በማዕከሉ የሚገኙ የተለያዩ ቡድኖች

ያላቸውን አመሰራረት ማሳየት ነው። የጥናቱ ንዑስ አላማዎች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ለመሄድ ያነሳሳቸውን ምክንያቶች ማሳየት የሚሉ ናቸው። ከእነዚህ ዓላማዎች በተጨማሪ የኦርቶዶክስ እስልምና ተከታዮች (Orthodox Muslims) ስለመንፈሳዊ ጉዞውና ስለተጓዦቹ ያላቸውን አመለካከት መለየት፣ በመካነ ቅርሱ ከሚከወኑ ስርዓተከበራዎችና መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ጋር የተገናኙ ሀቲቶችን መግለጽ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች ያሉት ለውጦች በመካነ ቅርሱ ሚና ላይ ያሳደሩትን ተጽዕኖ መረዳት የሚሉ ናቸው።

ይህ ጥናት ሶስት ትኩረቶች አሉት። አንደኛው መንፈሳዊ ጉዞ ነው። ሁለተኛው ስርዓተከበራ ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ነው። በጥናቱም ወደ ስፍራው የሚደረግ ጉዞ ያለውን ዓላማዎችና ባህርያት ተገልጿል። በጥናቱ የስርዓተከበራ ክፍል ስር የዋሬ ስርዓትን እንዲሁም በስርዓቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን ግለሰባዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ በሚል በሶስት ተከፍለዋል። እነዚህን ሶስት ጉዳዮች ለማብራራት የተወሰኑ ማሳያዎችን (Cases) ጥናቱ ተጠቅሟል። የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ አጀማመር፣ ማን እንደሚከውነውና ምን ምን ርዕሰጉዳዮች እንደሚገለጽበት ጥናቱ አሳይቷል።

በጥናቱ በዋሬ ስርዓት ላይ የሚገኙ ሰዎች ከሚመጡበት ዓላማ አንጻር መልዕክት የሚያደርሱ (ስለት ለማስገባትና ለማመስገን)፣ በዓሉን ለማስተባበር፣ የባሮ ባለሙያዎች፣ ተመልካቾች፣ ደርጋዎች (ነዋሪዎች) እና የመንግስት ባለስልጣናት በሚል በስድስት ተመድበዋል። በዋሬ ስርዓት ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን ደግሞ ግለሰባዊና የጥቂት ቡድኖች ጉዳይ እንዲሁም ሰፊ ማህበራዊና ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች በሚል በሁለት ጠቅላላ ምደባዎች ቀርበዋል።

ይህ ጥናት ስለመንፈሳዊ ጉዞ፣ ስለዋሬ ስርዓትና ስለባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ የግጥም ይዘት የሚያሳይ መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይቀራረባል። ነገር ግን ጥናቱ በሙዳ በዓላት ወቅት በተለያዩ ስፍራዎች ከሚካሄዱ ስርዓቶች መካከል የዋሬ ስርዓትን ብቻ በተወሰነ ደረጃ የሚገልጽ ነው። ይህ በመሆኑም ጥናቱ በዋሬ ላይ የሚከናወኑ ስርዓቶችን በቅደምተከተልና በስፋት አያሳይም። በዚህ ጥናት የተገለጹ ጉዳዮች በራሳቸው በጣም ሰፋፊና ራሳቸውን ችለው ሊጠኑ የሚገባቸው ጉዳዮች የተገለጹበት ነው።

ይህ መሆኑ ከጥናት ስነዘዴ አንጻር ስህተት ይስተዋልበታል። ይህ የስነዘዴም ስህተት ከጥናቱ ዓላማዎች ብዛት የመጣ መሆኑ ያሳያል። የእኔ ጥናት በሙዳ በዓላት ወቅት የሚቀርበውን

የዋሬ ስርዓት በጥልቅ የሚያይ ከመሆኑም በተጨማሪ በሌሎች ስፍራዎች የሚካሄዱ ስርዓቶችንም በዝርዝርና በጥልቀት የሚያጠና ነው። ስርዓቶቹም ያላቸውን የውሕደት ባህርይ ያጠናል። ጥናቱ በበዓላት ወቅት ከሚቀርቡ የተለያዩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች መካከል ባሮን ብቻ የሚያሳይ ነው። የእኔ ጥናት ከባሮ በተጨማሪ በመካነ ቅርሱ የሚከወኑ ሌሎች መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን ያካተተ ነው።

Makonnin Raggaasaa (2008 ዓ.ም) “Xinxala Ayyaanafi Fakkoommiiwwan Sirna Raawwii Muuda Diree Sheek Huseen” በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በኦሮምኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ሰርቷል። የጥናቱ አብይ ዓላማ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ ስርዓተከበራ አከዋወን መፈተሽ የሚል ነው። የጥናቱ ንዑስ ዓላማዎች ደግሞ የሙዳ በዓል ታሪክ፣ አጀማመር፣ ተሳታፊዎችና መቼት ለይቶ ማስቀመጥ፣ የሙዳ አከባበርን መለየት፣ በስፍራው የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን በጥልቀት መተንተንና የአከባበር ስርዓቶችን ማሳየት፣ የመንፈሳዊ ሙዚቃዎችን ዓላማና ጠቀሜታ በዝርዝር ማቅረብ እንዲሁም የሙዳ በዓልን ፋይዳ መግለጽ ናቸው።

በዚህ ጥናት የሼኽ ሁሴን ታሪክና ስራቸው፣ የሙዳ በዓል አጀማመር፣ የሙዳ ተሳታፊዎች አይነት፣ የድሬ መንፈሳዊ ጉዞ መቼት፣ የሙዳ በዓላት ክዋኔ፣ በስፍራው ላይ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችና በቦታዎቹ የሚከወኑ ስርዓቶች፣ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ምንነትና መልዕክቶቹ፣ የቱፍታ ስርዓት፣ የምርቃት ስርዓት፣ የእርግማን ስርዓት፣ የሙዳ በዓል ሁለንተናዊ ጠቀሜታ እንዲሁም በበዓሉ ላይ የተስተዋሉ ለውጦችና ቀጣይነት ቀርበዋል።

ይህ ጥናት በእኔ ጥናት ውስጥ የሚነሱትን የሙዳ በዓል አጀማመር ታሪክ፣ የሙዳ በዓላት የአከባበር ስርዓተከበራዎችን፣ የሙዳ በዓል ሁለንተናዊ ጠቀሜታ እንዲሁም በበዓሉ ላይ የተስተዋሉ ለውጦች ማካተቱ ከእኔ ጥናት ጋር ይቀራረባል። ነገር ግን ጥናቱ እነዚህን ስርዓተከበራዎች ከመግለጽ ባለፈ በጥልቅ ያልዳሰሰ፣ በሙዳ በዓል ወቅት የሚከወኑ ሁሉንም ስርዓቶች ያላካተተ እንዲሁም በስርዓቶቹ ያለውን የኃይማኖት ውህደት ያላጠና መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ልዩነት አለው። በመሆኑም ይህ ጥናት ከሌሎች ጥናቶች በበለጠ ከእኔ ጥናት ጋር ቢቀራረብም ከርዕሰ ጉዳይ ስፋትና ጥልቀት አንጻር ልዩነት አለው።

Muhaammadkiyaar Mahmud (2008 ዓ.ም) “Qaacceessa Fayyadama Afaanii Baaroo Dirree Sheek Huseen Keessatti” በሚል ርዕስ የማስተር ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በኦሮምኛ

ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ሰርቷል። የጥናቱ አብይ ዓላማ በጎሎልቻ ወረዳ በድሬ ሼኽ ሁሴን በእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የሚቀርበው የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ የአፋን ኦሮሞ አጠቃቀምን መግለጽ የሚል ነው። የጥናቱ ንዑስ ዓላማዎች በጎሎልቻ ወረዳ በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚቀርበው ባሮ የአፋን ኦሮሞ አጠቃቀምን መለየት፣ በባሮ ዚክራ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ አጠቃቀም መለየት፣ የቦታ ስሞች የተሰየሙበትን ምክንያት መለየት የሚሉ ናቸው። በጥናቱም የባሮ ምንነት፣ በባሮ ዚክራ ውስጥ የዘይቤ አጠቃቀምን ከንግግር ስርዓት፣ የቃላትና የምሳሌያዊ አነጋገር በሚል ቀርቧል። የባሮ ግጥም ይዘቶች ደግሞ ልመናን፣ የውስጥ ስሜትን፣ ታጋሽነትን፣ ፖለቲካን፣ ውግዘትንና ማህበራዊ ጉዳይን የሚገልጹ በሚል ተመድበው ቀርበዋል።

Gemechu J. Geda (2013) "Pilgrimages and Syncretism: Religious Transformation among the Arsi Oromo of Ethiopia" በሚል ርዕስ የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ጥናት በጀርመን አገር ባይሮይት ዩኒቨርሲቲ ሰርቷል። የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረት መንፈሳዊ ጉዞ የሚደረግባቸውና በሙስሊም ወንድ ቅዱሳንና በሙስሊም ሴት ቅዱሳት የተመሰረቱ የሀይማኖት ማዕከላት እንዲሁም የኢሬቻ መንፈሳዊ ጉዞ ነው። በሙስሊም ወንድ ቅዱሳን ከተመሰረቱት መካነ ቅርሶች መካከል የሼኽ ሁሴንና የሼህ ሶፍ ዑመር እንዲሁም በሴት ሙስሊም ቅዱስ የተመሰረተውን የአዮ ሞሚና (የፈረቃሳ) መካነ ቅርስ አጥንቷል።

ጥናቱ በሙስሊም ወንድ ቅዱሳን ከተመሰረቱ መንፈሳዊ ማዕከላት መካከል የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን በንዑስ ርዕስነት በአንድ ምዕራፍ ይዳስሳል። በጥናቱም ስለሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አመሰራረት ታሪክ፣ ወደ ስፍራው ስለሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች ባህርያት፣ በመካነ ቅርሱ ስለሚከበሩ በዓላት እንዲሁም በበዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓቶች ያላቸው የኃይማኖት ውህደት ተብራርቷል።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ፣ በሶፍ ዑመር መካነ ቅርስ፣ በአዮ ሞሚና መካነ ቅርስና በሆራ አርሰዲ በሚከበረው የኢሬቻ በዓል የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች ያላቸውን ባህርያትና በስፍራዎቹ የሚከወኑ ስርዓቶችን ማሳየት ነው። የዚህ ጥናት ዓላማና የትኩረት አቅጣጫ ከእኔ ጥናት ጋር ቢለያይም፣ በእኔ ጥናት ውስጥ የሚጠኑ ርዕሰጉዳዮች ተነስተውበታል። ከእነዚህ ነጥቦች መካከል ስለሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ታሪክ፣ ስለሙዳ በዓል አከባበር፣ የኃይማኖት ውህደትና ወደ ስፍራው የሚካሄዱ መንፈሳዊ ጉዞዎች ያላቸውን ባህርያት በተወሰነ ደረጃ መዳሰሱ ከእኔ ጥናት ያመሳስለዋል።

በዚህ ጥናት በንዑስ ርዕስነት በአንድ ምዕራፍ የቀረበው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከበሩ የሙዳ በዓላትና ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ የእኔ ጥናት ዋና ትኩረቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በእኔ ጥናት በዝርዝር የሚተነተኑና በዋና ርዕሰጉዳይነት የሚጠኑ በመሆናቸው በጥናቶቹ የትኩረት አቅጣጫ ላይ ልዩነት አለ፡፡

ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጋር የተያያዙ 3 መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ያላቸውን ይዘትና ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ቀጥለን እንመልከት፡፡

Temam Haji-Adam (2010) "Qarooma Kuush, Seenaa Ummata Oromoofi Gahee Dirree Sheek (Nuur) Huseen" በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ በመጽሐፉም የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኦሮሞን ባህልንና እስልምናን ከማስፋፋት አንጻር ያለው ሚና እንዲሁም በአጼ ምኒልክና በልጅ እያሱ ዘመነ መንግስት መካነ ቅርሱ የነበረው የፖለቲካ ሚና የሚሉት ርዕሶች ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በዚህ መጽሐፍ በአመት ሁለት ጊዜ የሙዳ በዓላት በመካነ ቅርሱ መከበራቸውን ከመግለጽ ባለፈ የቀረበ ተጨማሪ መረጃ የለም፡፡

Østebo, Terji (2012) "Localising Salafism: Religious Change among Oromo Muslims in Bale, Ethiopia" በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ በመጽሐፉም የሰለፊያ አስተምህሮ በኢትዮጵያና በባሌ መቼና እንዴት እንደተስፋፋ፣ እስልምና በባሌና በደቡብ ምስራቅ የአገሪቷ አካባቢዎች እንዴት እንደተስፋፋ፣ የሰለፊያ አስተምህሮን የሚቃወሙ አስተሳሰቦችን፣ ሰለፊያ ከመንግስት የፖለቲካ ስርዓት ጋር ያለውን ግንኙነት በስፋት ተካቷል፡፡ ከእነዚህ ነጥቦች በተጨማሪ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን አጠቃላይ ገጽታና የሙዳ በዓላት አከባበርን በጥቂቱ አሳይቷል፡፡ ይህ መጽሐፍ ስለሙዳ በዓላት የአከባበር ስርዓት በጥቂቱ ማቅረቡ፣ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሱፊስት አስተምህሮን በማስፋፋት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦና የሰለፊያ አስተምህሮ ያስከተለበትን ተግዳሮት ማሳየቱ ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ ደረጃ ይቀራረባል፡፡

መሐመድ ሼህ ሁሴን ዳውድ (አመት የለውም) ‹‹አላሁሙ-እርሐም ሼከና ሁሴን ቁጥበል-ሐበሸ›› በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ በመጽሐፉም የሼኽ ሁሴን ታሪክ፣ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ግንባታዎች፣ የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች የአኗኗር ሁኔታ፣ የሼህ ሁሴን ባህርይ እንዲሁም የእሳቸው ምርጥ ንግግሮችና ምክሮች በሚሉ ርዕሶች የቀረበ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ስለሙዳ በዓላት የአከባበር ስርዓት የገለጸው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን

አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይና አካባቢውን ለማስተዋወቅ በሚል ዓላማ በጥቂት ገጾች የተዘጋጀ መጽሐፍ በመሆኑ ለእኔ ጥናት የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ ጥናት በማድረግ የቀረቡ 3 የኢንቬንተሪ ሪፖርቶች አሉ፡፡ እነዚህ ኢንቬንተሪዎች Sintayehu Tola (2001) "The Conservation of Dirre Sheikh Hussein Heritage Site" በሚል ርዕስ በኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ Areba Abdella and *et al* (2003) "Dirre Sheikh Hussein Shrine: To Be Inscribed In Regional, National and World Heritage List" በሚል ርዕስ በባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም Hailemelekot Agizew and Mulugeta Abegaz (2015) "The Dirre Sheikh Hussein Religious, Cultural and Historical Site" በሚል ርዕስ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ናቸው፡፡

እነዚህ ሶስት ኢንቬንተሪዎች የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ያለውን የሚዳሰስና የማይዳሰስ ሀብቶች፣ እየተካሄዱ ያሉ የቅርስ እንክብካቤና ጥበቃ ስራዎች፣ ተከታታይ ልማት እንዲካሄድ መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች እንዲሁም የአስተዳደር እቅድን የሚገልጹ ናቸው፡፡ የኢንቬንተሪ ሪፖርቶቹም አካባቢውን የማስተዋወቅ ዓላማ ይዘው የተሰሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሙዳ በዓላት በመካነ ቅርሱ እንደሚከበሩ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ሶስቱም ኢንቬንተሪዎች በዓላቱን በጥልቀት አያሳዩም፡፡

የዚህ ጥናት ዋና የትኩረት ነጥቦች በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩትን የሙዳ በዓላት ያላቸውን የአከባበር ስርዓቶች፣ ወደ ስፍራው የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች ያላቸውን ባህርይ እንዲሁም በበዓላቱ ወቅት በሚቀርቡ ክወናዎች ላይ የሚስተዋሉ የሀይማኖትና የባህል ውሕደቶችን ማጥናት ነው፡፡ እነዚህ ዋና ነጥቦች ከጥናቱ ውስጥ አንፃር ለማሳየት የሚረዱ ተጨማሪ ነጥቦች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ነጥቦችም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና የአካባቢው ነዋሪዎች አጠቃላይ ገጽታ፣ የሼኽ ሁሴን ታሪክ፣ የሼኽ ሁሴን ሰብዕና፣ የሼኽ ሁሴን የተለያዩ ሚናዎች፣ ስለሼኽ ሁሴን የሚነገሩ ሚቶች፣ የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ያለው ባህርይ፣ ተጓዦች ወደ ስፍራው የሚሄዱባቸው ጉዳዮች፣ በሙዳ በዓላት ወቅት በመካነ ቅርሱ የተለያዩ ቦታዎች የሚከወኑ ስርዓቶች፣ በሙዳ በዓል ላይ ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶችና የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ነጥቦች በተለያዩ አጥኚዎች በተወሰነ ደረጃ የተገለጹ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶች እነዚህን ጉዳዮች በዝርዝርና በጥልቀት አላጠኗቸውም፡፡ ለዚህም ጥናቶቹ

በመካነ ቅርሱ ያሉ ጉዳዮችን ለማስተዋወቅ በሚል፣ ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮችን ሲገልጹ በንዑስ ርዕስነት ስለመካነ ቅርሱ በመግለጻቸው፣ ሰፊ ርዕሰጉዳዮችን ለማጥናት ባላቸው ፍላጎት ምክንያት ስርዓቶችን በተወሰነ ደረጃ ከመግለጽ ባለፈ በጥልቀት ባለማጥናታቸው ወይም ጥናቶቹ የተሰሩበት የትምህርት ደረጃ እንደዋና ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በስፍራው ላይ በሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎችና መንፈሳዊ ጉዞዎች ላይ ብቻ በማተኮር በፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ደረጃ የተዘጋጀ የመጀመሪያ ጥናት ነው፡፡ ይህ መሆኑ በስፍራው ከተሰሩ ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በፊት በተለያየ ደረጃ እና አይነት በመካነ ቅርሱ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች ያልዳሰሷቸውን ወይም በጥልቅ ያላጠኗቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በዝርዝር የሚያሳይ በመሆኑ በመካነ ቅርሱ ዙሪያ ያለውን የጥናት ክፍተት በተወሰነ ደረጃ የሚሞላ ነው፡፡

## 2.2. ጽንሰሃሳባዊ ዳሰሳ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ስለስርዓተከበራና ስለክወና ምንነት፣ አይነት፣ ባህርይና አላባውያን፣ ስለመንፈሳዊ ጉዞና ስለውህደት ምንነትና ባህርያት እንዲሁም ስለሙዳ በዓላት ምንነት ይቀርባል፡፡

### 2.2.1. የስርዓተከበራ ምንነት

ስርዓተከበራ የሚለው ቃል የእንግሊዘኛውን "Ritual" የሚገልጽ ነው፡፡ "Ritual" የሚለው ቃል የላቲን ቃል ከሆነው *"Ritus"* የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም ልማድ ወይም ነባር ባህል ማለት ነው (Kyriakidis,2007፡290)፡፡ ስርዓተከበራ ከኃይማኖት ጋር በእጅጉ የተያያዘ እንደሆነ Rappaport (1999:25) ይገልጻል፡፡ በመሆኑም የስርዓተከበራን ምንነት ከማየታችን በፊት ስለ ኃይማኖት (Religion) ምንነት በጥቂቱ እንመልከት፡፡ የኃይማኖትን ምንነት በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን አስፍረዋል፡፡ ነገር ግን ጽንሰሃሳቡ እጅግ በጣም ሰፊና ውስብስብ በመሆኑ ወጥ የሆነና ሁሉንም ሊያግባባ የሚችል ብያኔ የለም፡፡ ለጽንሰሃሳቡ ወጥ ብያኔ ባይኖርም በኃይማኖት ላይ ብያኔ ከሰጡ ምሁራን መካከል የተወሰኑትን ለማሳያነት ቀጥለን እንመልከት፡፡

Tylor (1979[1873]:10) ኃይማኖት "በመንፈሳዊ ኑባሬዎች (Spiritual Beings) ማመን ነው፡፡" በማለት ይበይነዋል፡፡ በዚህ ብያኔ ኃይማኖት ከሚታመንባቸው ነገሮች፣ ሁነቶችና ጉዳዮች ካላቸው መንፈሳዊነት አንጻር የሚገለጽ ነው፡፡ Durkheim (1995[1912]:10) "ኃይማኖት ከተቀደሱ ነገሮች ጋር የተዛመዱ እምነቶችንና ድርጊቶችን ያዋሃደ ስርዓት ነው፡፡" በማለት ይበይነዋል፡፡ እንደ ዱርካሂም አገላለጽ የተቀደሰ ነገር የሚባለው በምድር የሌሉና የማይታዩ ወይም በምድር ላይ ያሉና የሚታዩ ማንኛውንም መንፈሳዊ ነገሮች የሚያጠቃልል ነው፡፡

Vergot (1997:16) ደግሞ ሀይማኖት ልዕለተፈጥሯዊ ኑባሬ (Supernatural Being) ወይም ልዕለሰብዓዊ ኑባሬን (Superhuman) የምንገልጽባቸውን ስነልሳናዊ ገለጻዎች፣ ስሜቶች፣ እንቅስቃሴዎችና ትዕምርቶች አጠቃሎ እንደሚይዝ ይገልጻል፡፡ ይህም ብያኔ ኃይማኖትን ከገለጻና ከተግባቦት አንጻር የሚገልጽ ነው፡፡ Geertz (1966፡4) ደግሞ ኃይማኖትን

> በሰዎች ሀሳባዊ ስርዓት ውስጥ ዓብይ ቅደም ተከተላዊ ህግጋትን የሚያኖር ነው፡፡ በሃሳባዊ ስርዓቱም ኃይለኛ፣ ተጽዕኖ ፈጣሪና የረጅም ጊዜ ስሜትና ፍላጎት የሚወስን ሲሆን ወደ እነዚህ እሳቤዎች ለመቅረብ ስሜቶችንና ፍላጎቶችን ፍጹም እውነታዊ በማስመሰልና ከእውነታ ጋር በእጅጉ በማገናኘት የሚቀርብ ትዕምርታዊ ስርዓት ነው፡፡

በማለት ይበይነዋል፡፡ በዚህ ብያኔ ኃይማኖት ሰዎች እንዴት እንደሚያምኑ እንደሚያደርግ፣ ያለውን ዓላማ፣ ግብ፣ ሀሳባዊ ስርዓት እንዲሁም የማሳመኛ መንገድን የሚገልጽ ነው፡፡ ከእነዚህ ብያኔዎች ኃይማኖት በመንፈሳዊ፣ በልዕለሰብዓዊ፣ በልዕለተፈጥሯዊ ኑባሬዎችና በቅዱስ ነገሮች ማመን፣ እነዚህን ኑባሬዎችና ነገሮች የምንገልጽባቸው መንገዶች፣ የሰውን ልጅ ከመንፈሳዊ ኃይል ጋር መስተጋብርና ተግባቦት የሚፈጥር ሀሳባዊ ስርዓት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ከኃይማኖታዊ ተግባራት መካከል ስርዓተከበራ አንዱ ነው፡፡ ስለ ስርዓተከበራ ምንነትና ባህርያት ቀጥለን እንመልከት፡፡

የስርዓተከበራ ጽንሰሀሳብ በጣም ሰፊ፣ ውስብስብ፣ ተለዋዋጭና በሰው ልጅ የታሪክና የባህል ጥናት ውስጥ በጣም ልዩ ስፍራ የሚሰጠው እንደሆነ Salamone (2004:XI) ይገልጻል፡፡ ስርዓተከበራ በፎክሎር ጥናት ውስጥ በሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Custom) የፎክሎር ዘውግ ስር ይመደባል (Dorson, 1972)፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድ ማህበረሰቡ በተደጋጋሚ የሚከውነው ድርጊትና ቅደምተከተላዊ ስርዓትን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ጥበቦች ጥቅል መጠሪያ ነው (Dorson, 1972፡3-4)፡፡ ጥበቦቹም የማህበረሰቡ፣ የፎክ ቡድኑ (Folk Group) ወይም የቤተሰቡ አባል ከእምነት፣ ከበዓል ቀናት፣ ከምርት ማምረት፣ ከእርግዝና፣ ከውልደት፣ ከግዝረት፣

ከጋብቻ፣ ከሞት ወይም ከሌሎች ሁነቶች ጋር በማያያዝ ይከውናቸዋል፡፡ እነዚህን ልማዶች ማህበረሰቡ በመኖሪያ ቤት፣ በመኖሪያ አካባቢ፣ በቤተክርስቲያን፣ በመስኪድ፣ በመካነ ቅርስ ወይም በሌሎች ስፍራዎች በጋራ ይፈጽማል፡፡

የስርዓተከበራን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ አጥኚዎች የተለያዩ ብያኔዎችን አስፍረዋል፡፡ ምሁራኑ ስርዓተከበራን ሲበይኑ በዋናነት ከሁለት ሰፋፊ ርዕሰጉዳዮች አንጻር ነው፡፡ እነሱም ስርዓተከበራን ከቅርጽ (Form) እና ከአገልግሎት (Function) አንጻር ናቸው፡፡ Rappaport (1999:24) ስርዓተከበራ በአብዛኛው የማይቀያየር፣ መደበኛ የድርጊት ቅደም ተከተልና የከዋኞች ፈጠራ የማይታከልበት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይህ ብያኔ ስርዓተከበራን ከቅርጽ አንጻር የሚገልጽ ነው፡፡

Eriksen (2001:215) ስርዓተከበራዎች በህግ የታቀፉ ሕዝባዊ ሁነቶች ሲሆኑ፣ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በመሬት ያለ አካልና በመንፈሳዊ ነገር መካከል ግንኙነት መፍጠሪያ መንገድ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ Cooke and Macy (2005:21) ስርዓተከበራ የባህልን ጥልቅ እሴት ማሳየት ብቻ ሳይሆን ባህልን የመፍጠር፣ የመጠበቅና እውቅና የመስጠት ሚናም ያለው መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ብያኔዎች ደግሞ ስርዓተከበራን ከአገልግሎት አንጻር የሚገልጹ ናቸው፡፡

Firth (1967፡12) "ስርዓተከበራ እንደ መደበኛና ሂደታዊ የትዕምርቶች ስብስብ የሚወሰድ ሲሆን፣ የማህበራዊ ተግባቦት ምልክት (Code) ነው፡፡" በማለት ስርዓተከበራን ከቅርጽና ከአገልግሎት አንጻር ይበይነዋል፡፡ በተመሳሳይም Gruenwald (2003፡2) "ስርዓተከበራ የሰው አዕምሮ የሚገልጸው ነጻ ባህሪ ነው፡፡" በማለት ስርዓተከበራን ከባህርያትና ከአገልግሎት አንጻር ይበይነዋል፡፡

ከእነዚህ ብያኔዎች በመነሳት ስርዓተከበራዎች አንድ ማህበረሰብ ያለውን ባህል መነሻ በማድረግ ከማህበራዊና ሀይማኖታዊ ዋጋ አንጻር ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸውን ክወናዎች በቅደምተከተላዊ ስርዓት፣ በተደጋጋሚና በመደበኛነት የሚከውናቸው ጠቃሚ ድርጊቶችና ሕዝባዊ ሁነቶች ናቸው፡፡ ስርዓተከበራዎቹ የከዋኞቹን መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊና ማህበራዊ ደረጃን ከፍ በማድረግ ከመንፈሳዊ ሀይሎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር፣ ባህልን ለመፍጠር፣ ለመጠበቅና እውቅና ለመስጠት እንደሚያገለግሉ መረዳት እንችላለን፡፡

### 2.2.2. የስርዓተከበራ አይነቶችና ባህርያት

በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚከወኑ በርካታ መንፈሳዊ ስርዓተከበራዎች አሉ፡፡ ስርዓተከበራዎቹ ከሚቀርቡባቸው ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ምክንያቶች፣ ከተሳታፊዎች አይነት፣ ብዛትና ከሚያዳርሱት መልከዓምድራዊ ሽፋን አንጻር አይነታቸው የተለያየ ነው (ሰሎሞን፣ 2007 ዓ.ም፣162)፡፡ የተለያዩ ምሁራን የስርዓተከበራዎችን በተለያዩ አይነቶች ይመድቧቸዋል፡፡ ከእነዚህ ምሁራን መካከል የተወሰኑትን ለማሳያ እንመልከት፡፡

የስርዓተከበራ አይነቶች በርካታ መሆናቸውን Turner (1967፡6)፣ Green (1997፡735)፣ Bell (1977:94) እና Sims and Stephens (2005:110-125) ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህ የስርዓተከበራ አይነቶች መካከል በድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓቶች (Calendrical rites) ስር ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓቶች በጊዜ የተገደቡ፣ የሚከወኑበት ወቅት የታወቀ፣ ከተፈጥሯዊ የወቅቶች ሁኔታና የማህበረሰቡ ሕይወት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓቶች ወቅታዊ (Seasonal) እና የመታሰቢያ (Commemorative) በሚል በሁለት እንደሚመደቡ Bell (1977:103) ትገልጻለች፡፡

የመታሰቢያ ስርዓቶች በአንድ አገር ወይም ማህበረሰብ ላይ የተከሰቱ ልዩ ታሪካዊ ገጠመኞችን ለማሰብ ወይም በአንድ ኃይማኖት አስተምህሮ ውስጥ የኃይማኖቱ ዋና ምሰሶ የሆኑ ቅዱሳን የተወለዱበትን፣ ልዩ ተዓምራት የፈጸሙበትን ወይም ያረፉበትን ቀን ለማሰብ በሚል የሚከወኑ ናቸው (Bell, 1977፡105)፡፡ ከእነዚህ ሁለት ምደባዎች የሙዳ በዓላት አንደኛው የሼኽ ሁሴንን የውልደት ቀንን እንዲሁም ሁለተኛው ነብዩ ኢብራሂም ልጁን ለመሰዋት የተዘጋጀበትን ቀን (ኢድ-አልአድሃ) ምክንያት በማድረግ የሚከበሩ በመሆናቸው በመታሰቢያ ስርዓተከበራ ስር ይመደባሉ፡፡ እነዚህ የሙዳ የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓተከበራዎች በጨረቃ የጊዜ ቆጠራ (Lunar calender) መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የጨረቃ የጊዜ አቆጣጠርን መሰረት አድርገው የሚከበሩ አመታዊ በዓላት በቋሚ ቀን አይውሉም፡፡ የሙዳ በዓላትም ቋሚ ቀን የላቸውም፡፡

የመታሰቢያ ስርዓተከበራዎች የተለያዩ ባህርያት አሏቸው፡፡ ከእነዚህ ባህርያት መካከል ዋና ዋናዎቹ አምስት እንደሆኑ Grimes (1982:541) ይገልጻል፡፡ እነሱም፡- አንደኛ፣ ተደጋጋሚ ሲሆኑ፣ በአመት ውስጥ በተወሰነ ጊዜና ቦታ የሚከወኑ ናቸው፡፡ ሁለተኛ፣ መንፈሳዊ ሲሆኑ፣ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መንፈሳዊ ድርጊቶችን ይይዛሉ፡፡ ሶስተኛ፣ ቋሚና የማይለወጡ

ድርጊቶች አሏቸው፡፡ አራተኛ፣ ቀደም ካሉ ታሪኮችና ሚቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ አምስተኛ፣ ሆነ ተብለው (Intentional) የሚከወኑ ሲሆኑ፣ ክዋኔያቸውም በውስን ትርጓሜ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ እነዚህ የመታሰቢያ ስርዓተከበራ ባህርያት በድሬ ሼኽ ሁሴን በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት የሚንጸባረቁ ናቸው፡፡ ሙዳ የሚለው ቃል ስርዓተከበራዎችን የሚገልጽ በመሆኑ በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን "የሙዳ ስርዓተከበራዎች" በሚል መግለጽ ይቻላል፡፡

## 2.2.3 የስርዓተከበራ አላባውያን

ስርዓተከበራ የተለያዩ አላባውያን (Elements) አሉት፡፡ እነዚህ የስርዓተከበራ አላባውያን አምስት እንደሆኑ Cooke and Macy (2005፡52-53) ይገልጻሉ፡፡ እነሱም፡- አንደኛ፣ ሁሉም ስርዓተከበራዎች ሁለት ነገርን ይገልጻሉ፡፡ አንደኛው ማህበረሰቡ ዓለምን እንዴት እንደሚረዳ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ስርዓተከበራ በራሱ የማህበረሰብን አረዳድ የሚቀርጽ መሆኑን ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ሁሉም ስርዓተከበራዎች አማኞች በአስተሳሰብ እንዲያድጉ ወይም እንዲበለጽጉ የመርዳት እድል አላቸው፡፡ ሶስተኛ፣ በስርዓተከበራው ላይ የሚታመነው መንፈሳዊ ኃይል (አካል) ወደ ሰማይ ያረገ (ያልሞተ) እንደሆነና በማህበረሰቡ ዘንድ ሕያው ሆኖ የሚኖር ተደርጎ ይታመናል፡፡

አራተኛ፣ አማኞች ከሚያምኑት መንፈሳዊ ኃይል (አካል) ማግኘት የሚፈልጉትን ጥበቃ (Salvation) ለማግኘት በሚል ለሌሎች አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ይህ አገልግሎትም የጥበቃ ዋስትና ማግኛ አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ አምስተኛ፣ ስርዓተከበራዎች የወዳጅነት ማጠናከሪያ መድረኮች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡም ስርዓተከበራዎችን ለመፈጸም በሚሰባሰብበት ወቅት አጋጣሚውን ለእርስበርስ መረዳዳት ይጠቀምበታል፡፡

እነዚህን አምስት የስርዓተከበራ አላባውያንን Cooke and Macy (2005) የለዩት በክርስትና ኃይማኖት ከሚከወኑ ስርዓተከበራዎች በመነሳት ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ አላባውያን በሁሉም ኃይማኖቶችና እምነቶች ውስጥ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን እንደሚያጠቃልሉ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ የስርዓተከበራ አላባውያን በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት በሚከወኑ ስርዓተከበራዎችና መንፈሳዊ ጉዞዎች ውስጥ የሚታዩ ናቸው፡፡ እነዚህ አላባውያን በሙዳ በዓል ወቅት እንዴት እንደሚንጸባረቁ በጥናቱ በተለያዩ ምዕራፎች ተተንትነዋል፡፡

## 2.2.4 የስርዓተከበራ መሰረቶች

ስለስርዓተከበራ ብያኔ ለመስጠት፣ ቅርጹንና ባህርያቱን ለመግለጽም ሆነ ለማጥናት የሕልውና መሰረት የሆኑ ጉዳዮችን ከግምት ማስገባት አለብን። የስርዓተከበራ መሰረቶች የሚባሉት ክወና (Performance)፣ ትዕምርት (Symbol)፣ ሚት (Myth) እና መንፈሳዊ ሙዚቃ (Hymn) መሆናቸውን Firth (1967)፣ Rappaport (1992)፣ Gruenwald (2003) እና Cooke and Macy (2005) ይገልጻሉ። እነዚህ የስርዓተከበራ መሰረቶች ምንነትና ባህርያት በአጭሩ እንመልከት።

### 2.2.4.1 የክወና ምንነት፣ ባህርያትና አላባውያን

ክወና ለስርዓተከበራ ዋና መሰረት ነው። ክወና ለስርዓተከበራ ያለውን አስፈላጊነት በሚመለከት Rappaport (1992:250) "ክወና ከሌለ ስርዓተከበራ የለም" በማለት ይገልጻል። ክወና ሰፊ ጽንሰሃሳብ ሲሆን፣ ሁላችንም በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ በክወና ውስጥ የምንቆይና ጥበባዊ ስራዎችን በድምጽና በአካል የመከወን ክህሎት እንዳለን Fine (1984:1) ትገልጻለች። ይህንንም የመከወን ችሎታችንን በመጠቀም በዘፈን፣ በንግግር ወይም በድርጊት አድማጭ ፊት ስናቀርብ ያለውን ማህበራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ እንጂ የተዘጋጀ መመሪያ ወይም መነሻ ስልት (Model) በመጠቀም አይደለም።

ክወና ፎክሎሮች በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በሚቀርቡበት ወቅት የጥበቡ አቅራቢ የሚያሳየውን ባህርይ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የድምጽ አቀራረብ፣ የሚቀርበውን ነገር፣ የአድማጩን ሁኔታ፣ ጥበቡ የሚቀርብበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ማህበራዊ ሁኔታንና ማህበራዊ አጋጣሚን አጠቃሎ የሚይዝ ነው። ክወና ጥበባዊ የመግባቢያነት ስልት መሆኑን Bauman (1992:41) ይገልጻል። ይህም ማለት ክወና የማህበረሰቡን ስነልቡና፣ ባህል፣ አመለካከት እንዲሁም ማህበራዊ አጋጣሚን መሰረት በማድረግ አድማጭ በሚረዳበትና የተግባቦት እንቅፋት በማይፈጥር መልኩ የሚቀርብ ነው።

Bauman (1992:45-48) የክወና ባህርያትን በሶስት ይመድባቸዋል። እነሱም፦ አንደኛ፦ በእቅድ የሚቀርብ መሆኑ፦ ክወና ከቦታና ከጊዜ አንጻር በእቅድ የሚመራ ነው። እቅዱም በሁለት አይነት ገደብ ሊከፈል ይችላል። የመጀመሪያው የጊዜ ገደብ ሲሆን፣ በዚህ ገደብ መሰረትም ክወናዎች በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በሚቀርቡበት ወቅት ቋሚ የሆነ የጊዜ እቅድ አላቸው። የክወናው የጊዜ ርዝማኔና የመከወኛ ወቅት ገደብ ያላቸውና የክወናው መጀመሪያና

መጨረሻ በግልጽ የሚታወቅ ነው። ሁለተኛው፤ የቦታ ገደብ ነው። በዚህ ገደብ መሰረትም ክወናዎች የሚቀርቡት ውስን፣ ቋሚ ወይም የተደነገገ የመከወኛ ስፍራ ላይ ነው። ይህ ማለት ግን ክወናው ሁል ጊዜ በአንድ ቋሚ ቀን ወይም ቦታ ብቻ የተወሰነ ነው ማለት አይደለም።

ሁለተኛ፡- ሕዝባዊ ቅንጅት ያለው መሆኑ፡- ክዋኔዎች በሚቀርቡበት ወቅት ለሁሉም ተመልካቾች እንዲታይ በሚል ግልጽ በሆነ ሁኔታ ነው። ክወናዎቹንም ማንኛውም ተመልካች ሊከታተላቸውና ሊሳተፍባቸው በሚችል መልኩ የሚቀርቡ ናቸው። ክወናዎች ሁሉም ማህበረሰብ በጋራ የሚፈጥራቸው ህዝባዊ ሁነቶች በመሆናቸው ሰዎች እርስበርስ እንዲቀራረቡ ምክንያት ይሆናሉ። ሶስተኛ፡- ማህበረሰባዊ ነጸብራቅ መሆኑ፡- የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ አመለካከትና ፍልስፍና በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በሚቀርቡ ክወናዎች አማካኝነት ይገለጻል። ማህበረሰቡ ማንነቱን በሙዚቃ፣ በሰውነት እንቅስቃሴ፣ በንግግር እንዲሁም በሌሎች መንገዶች ይገልጻል። ክወና ማህበረሰቡ ማንነቱን ለሌሎች የሚያሳውቅበትና የሌላውንም ማህበረሰብ ማንነት የሚረዳበት ነው። በመሆኑም ክወና የእርስበርስ የመግባቢያ ቋንቋ ነው።

እነዚህ ሶስት የክወና ባህርያት በድሬ ሼኽ መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት በሚከወኑ ክወናዎች ላይ የሚታዩ ናቸው።[8] ማንኛውም ክወና ትርጉም እንዲኖረው አላባውያን ሊኖሩት ይገባል። የክወና አላባውያን የሚባሉት ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ትዕምርትና ማህበራዊ ኃይል እንደሆኑ Alexander (2006፡32-37) ይገልጻል። እነዚህ አላባውያን ከሌሉ ክወናው ሊተገበር አይችልም። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎች ላይ እነዚህ አራት የክወና አላባውያን አሉ። በሙዳ በዓል ወቅት እነዚህ የክወና አላባውያን ያላቸውን ባህርያት በየምዕራፉ በሚቀርቡ የሙዳ ስርዓተከበራ ክወናዎች ተብራርተዋል።

### 2.2.4.2 የትዕምርት ምንነት

በስርዓተከበራ ላይ የሚቀርቡ ክወናዎች ያላቸው ቅደምተከተል፣ የሚቀርበው ማህበራዊ ድራማ፣ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ቀለም፣ ቁጥር፣ ቅርጽ፣ መጠን፣ ክወናው ሲቀርብ ከዋኞች የሚጠቀሟቸው ልዩ ምልክቶች (Codes)፣ የክወና ትረካዎች፣ ድግግሞሾች፣ ቦታዎችና ግለሰቦች ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ውክልና አላቸው። ስርዓተከበራ ትርጉም የሚኖረውና የእርስበርስ ተግባቦት የሚፈጥረው እያንዳንዱ ድርጊትና እንቅስቃሴ ትዕምርት ሲኖረው ነው። ትዕምርት ለስርዓተከበራ መሰረት መሆኑን Cooke and Macy (2005፡14) "ስርዓተከበራ

[8] - የሙዳ ስርዓተከበራ ክወናዎች ያላቸውን ባህርያት በምዕራፍ 7 እና 8 በዝርዝር ቀርቧል።

የሚተገበር ትዕምርት ነው፡፡" በማለት ይገልጹታል፡፡ በመሆኑም ትዕምርት የሌለው ስርዓተከበራ የለም፡፡

በተመሳሳይም ስርዓተከበራዎች እንደ ትዕምርት እንደሚታዩ Firth (1967፡12) "ስርዓተከበራ እንደ መደበኛና ሂደታዊ የትዕምርቶች ስብስብ የሚወሰድ ሲሆን፣ የማህበራዊ ተግባቦት ምልክት ነው፡፡" በማለት ይገልጻል፡፡ ማንኛውም ስርዓተከበራ በራሱ ትዕምርት ነው፡፡ በስርዓተከበራ ወቅት ትዕምርቶች በከዋኞችና በተመልካቾች መካከል ተግባቦትን የሚፈጥሩት ከዚህ በፊት የነበራቸውን ትርጓሜ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ትርጓሜውም የእኛን ግንዛቤ፣ ስሜት፣ ፍላጎት፣ ዕይታ፣ ትምህርትና ልምድ ያማከለ ነው፡፡

## 2.2.4.3 የሚት ምንነት

ሚት ከረጅም ዓመታት በፊት የተከሰቱና በማህበረሰቡ ዘንድ እውነት ናቸው ተብለው የሚታመኑ ድርጊቶች የሚነገሩበት የቃል ትረካ (Oral narrative) አይነት እንደሆነ Finnegan (1992:138) ትገልጻለች፡፡ Bascom (1965:4) ደግሞ ሚት ቃላዊ ትረካ መሆኑን ገልጾ ከሌሎች ቃል ትረካዎች የሚለየው ቅዱሳዊ (Sacered) መሰረት ያላቸው ሀሳቦችን የያዘ፣ እውነት እንደሆነ የሚታመን ድርጊት፣ አሁን ካለንበት ዓለም የተለየ ዓለም በነበረበት በድሮ ጊዜ የተከናወኑ ድርጊቶችን የሚገልጽ እንዲሁም በአብዛኛው ከስነመለኮትና ከመንፈሳዊ ስርዓተከበራዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን ይገልጻል፡፡ እነዚህ ብያኔዎች ሚት በማህበረሰቡ ዘንድ እውነት እንደሆኑ የሚታመንባቸውን ድርጊቶች፣ ቅዱሳዊ መሰረት ያላቸው ድርጊቶችና አሁን ካለው በተለየና በድሮ ዘመን የነበረ ድርጊትን የሚገልጽ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

እነዚህ ብያኔዎች በተወሰነ ደረጃ ስህተት ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሚት የሰው ልጅ ያለውን ረቂቅ አዕምሯዊ ሀሳብን የሚገልጽበት ነው፡፡ ይህ በመሆኑ የሰው ልጅ ከዕለትተዕለት ሕይወቱ ጋር የተቆራኙና በየዘመኑ የሚፈጠሩ ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚገልጽበት ነው፡፡ ስለሆነም ሚት የድሮ ዘመን ድርጊትን ወይም ቅዱሳዊ ሀሳቦችን ብቻ የሚይዝ አይደለም፡፡ ሚት በድሮ ዘመንም፣ በአሁን ዘመንም ያለና የሁሉም ሀሳቦች መነሻ ነው፡፡ በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ያሉ ሀሳቦች በሚት አማካኝነት የሚገለጹ እንደሆኑ Bollas (1987፡277) "ሚት "የሚታወቁ ግን ያልተገለጹ" ("Unthought known") ሀሳቦችን የሚገልጽ ነው፡፡" በማለት ይበይነዋል፡፡

አንድ ሀይማኖት፣ ባህል ወይም ማህበረሰብ እውነተኛ ድርጊቶች ናቸው ብሎ የሚያምናቸው ጉዳዮች በሌላው ዘንድ ሚቶች ሊሆኑ ይችላሉ (Leeming, 2010፡8)። ማህበረሰቡ በሀይማኖቱ፣ በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በባህላዊና በስነ-ልቡናዊ እይታ እውነት ነው ብሎ የሚያቀርባቸው ሁነቶች አሉ። እነዚህ እውነት ናቸው ብሎ የተቀበላቸው ሁነቶች የማንነቱ መሰረቶች ናቸው። በመሆኑም በሼኽ ሁሴን ማንነት ላይ የሚነገሩና የእሳቸው ወዳጆች የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት እውነተኛ ድርጊቶች ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ሚቶች አሉ። ከእነዚህ ሚቶች መካከል የሼኽ ሁሴን በፈጣሪ ዘንድ መመረጣቸውን፣ እሳቸው ከመወለዳቸው በፊት፣ ሲወለዱና ከተወለዱ በኋላ ተደርገዋል ተብለው የሚታመኑ ድርጊቶችን የሚገልጹ ናቸው። እነዚህ ሚቶች ለመካነ ቅርሱና ለሙዳ ስርዓተከበራዎች መሰረቶች ናቸው።

### 2.2.4.4 የመንፈሳዊ ሙዚቃ ምንነት

ሀገረሰባዊ ሙዚቃ (Folk music) በሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ (Performing Folk Art)[9] የፎክሎር ዘውግ ስር የሚመደብ ነው (Dorson, 1972)። በሀገረሰባዊ ሙዚቃ ውስጥ የምናገኘው ግጥም በአብዛኛው የማህበረሰቡን ባህል፣ አካባቢ፣ ታሪክና ኃይማኖት የሚገልጽ፣ ሀገር በቀል የዜማ (የቅኝት) ስልቶችን የሚጠቀም፣ የድምጽ ምቱ ባህላዊ የሆነ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎቹም ከአካባቢው በተገኙ ግብዓቶች የተሰሩና የማህበረሰቡን ባህል የሚያንጸባርቁ ናቸው (ሰሎሞን፣2007ዓ.ም፡216)። ከእነዚህ ባህርያት በተጨማሪ Titon (1992:167) ሀገረሰባዊ ሙዚቃ በአንድ አካባቢ የሚኖር ወይም አንድ የዘር ሀረግ ያለውን ማህበረሰብ ባህል መሰረት በማድረግ በቃል በመስማትና በማስታወስ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል፣ በክወና እንዲሁም በፊት ለፊታዊ ተግባቦት የሚተላለፍና በእለትተእለት ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚከወን እንደሆነ ይገልጻል።

ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎች ካላቸው ባህርያት አንጻር መንፈሳዊ እና ዓለማዊ በሚል ይመደባሉ። መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በተለያዩ ኃይማኖት አስተምህሮ መሰረት ለአምልኮ፣ ለምስጋና ወይም ለምህላ በሚል የሚከወኑ ናቸው። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ጉዳዮች ሲከወኑ የሚዜሙ 8 አይነት መንፈሳዊ ሙዚቃዎች አሉ። እነዚህም ባሮ፣ ሰርመዴ፣ ሹቢሳ፣ መንዙማ፣ ሰላሞ፣ እንጉርጉሮ፣ አቶረራ እና ዜከራ ናቸው።

---

[9] - Dorson (1972) ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብን "Performing Folk Art" ከሚለው በተጨማሪ "Folk Art" በሚል የእንግሊዝኛ ቃልም ሰይሞታል።

የተለያዩ አጥኚዎች እነዚህን መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ሲገልጹ ሁለት አብይ ስህተቶችን ይፈጽማሉ፡፡ አንደኛው ስህተት መንፈሳዊ ሙዚቃዎቹን ዝምሬ (Chant)፣ ውዳሴ (Mass)፣ ዜማ (Hymn) እና ዘፈን (Song) በሚሉ የተለያዩ ቃላት ይገልጿቸዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቃላት የመንፈሳዊ ሙዚቃ ቅርጽ (Musical form) ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላት በመካነ ቅርሱ የሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን በትክክል የማይገልጹ በመሆናቸው በዚህ ጥናት ሁሉም መንፈሳዊ ሙዚቃ በሚል ስያሜ ተገልጸዋል፡፡ ሁለተኛው ስህተት፣ በመካነ ቅርሱ የሚቀርቡ የተለያዩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን ባሮ በሚል መግለጽ ነው፡፡ ነገር ግን ባሮ የራሱ ዜማ፣ ቅኝትና አከዋወን ያለው አንድ የመንፈሳዊ ሙዚቃ አይነት ነው፡፡

በሙዚቃ፤ በተለካ ወሰነ ርቀት (Interval) ውስጥ የሙዚቃ ድምፆች፤ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ (ከታች ወደ ላይ) ወይም፣ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ (ከላይ ወደ ታች) ሲደረደሩ፤ “ድምፆቹ በስኬል ተቀመጡ” ይባላል፡፡ ይህም በሌላ አባባል “ቅኝት” የሚሰኘውን ጽንሰሃሳብ ያመለክታል፡፡ ይኸው አደራደራቸው፣ በባህርይ የሚያመጣውን ድምፀት ደግሞ፤ “ላህየ ቃና” (Mode) የሚሰኘውን ሙዚቃዊ መገለጫ ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ፤ “ዐቢይ ላህየ ቃና” (Major Scale/ Mode) ስንል፣ ወይም “ንዑስ ላህየ ቃና” (Minor Scale/ Mode) የሚባሉትን ዐበይት መደባት ማንሳት እንችላለን፡፡ “በቅኝት” እና “በላህየ ቃና” ውስጥ፣ እንደየባህሉ የተለያዩ ዓይነት የድምፅ መደብ ያላቸው ቅኝቶች ይወጣሉ፡፡ አፍሪካን፣ አውሮፓን እና ኤዥያን ባካለለ መልኩ የቅኝት መደብ ሲወጣ፡- ዲያቶኒክ ስኬል /Major and Minor/ (ባለ 8 ድምፅ ድርደራ)፣ ፔንታቶኒክ ስኬል /Major and Minor/ (ባለ 5 ድምፅ ድርደራ)፣ ክሮማንቲክ ስኬል (ባለ 12 ድምፅ ድርደራ) ሊባሉ ይችላሉ፡፡

የኢትዮጵያ የሙዚቃ ስኬል አጠቃቀም በጂኦግራፊያዊ ሁኔታው ላይ ተመሥርቶ የተለያየ መልክ የያዘ ነው፡፡ ሰሜናዊውና መካከለኛው፡- ፔንታቶኒክ፣ ምሥራቃዊው፡- ሐርሞኒክ ማይኖር፣ ደቡባዊው እና ምዕራባዊው፡- ፔንታቶኒክ እና ዲያቶኒክ ስኬልን ይጠቀማል፡፡[10] በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በቅላፄ እና በአጨዋወት ሥልት የራሳቸው የሆኑ መልኮች ቢኖሯቸውም፤ በሙዚቃዊ ስኬል አጠቃቀም ግን በመሠረታዊነት በሁለት ቅኝቶች ላይ የተመሠረቱ እንደሆኑ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁለት ሙዚቃዊ ቅኝቶችም “ትዝታ ሜጀር” እና “ዶሪያን ፔንታቶኒክ ስኬል” ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሁለት የሙዚቃ

[10] - እንደ ደራሼ ያለው ብሔረሰብ ደግሞ ከእነዚህ መደቦች ወጣ ያለ ባለ 12 ቶን ስኬል ይጠቀማል፡፡

ቅኝቶችም፣ በይበልጥ "ለዶሪያን ፔንታቶኒክ ስኬል" ያደሉ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በርካታ ናቸው፡፡[11]

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች የሚከውኑ ባለሙያዎች "ኡሌ" በሚል የማዕረግ ስም ይጠራሉ፡፡[12] እነዚህ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በዜማና በቃል ግጥም አማካኝነት የሚቀርቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ስምንት መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በዜማ የተለያዩ ሲሆኑ ያላቸው ቃል ግጥም ግን በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው፡፡ ቃል ግጥም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ገጠመኞችን ተንተርሰው ድረሳ (Composition) የሚካሄድባቸውና የተፈጠረውን ድረሳም በቃል ከሰው ወደ ሰው ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ መሆናቸውን Finnegan (1977፡3) ትገልጻለች፡፡ ቃል ግጥሞች በግጥም ቅርጽና በቃል የሚቀርቡ ናቸው፡፡

## 2.2.5 የመንፈሳዊ ጉዞ ምንነትና ባህርያት

ከኃይማኖታዊ ተግባራት መካከል ወደ ቅዱስ ስፍራዎች የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ (Pilgrimage) አንዱ ነው፡፡ መንፈሳዊ ጉዞ በሁሉም ኃይማኖቶች የሚገኝና ዓለምአቀፋዊ ሁነት ነው፡፡ መንፈሳዊ ጉዞ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ኃይማኖታዊ ጉዳዮችን ለመፈጸም ረጅም ርቀት የሚያደርገው የጉዞ ሂደት እንደሆነ Stoddard (1997፡49) ይገልጻል፡፡ San (2001፡11) እና Kaplan (2010፡151) መንፈሳዊ ጉዞ አምልኳዊና እምነታዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም ወደ ቅዱስ ስፍራ የሚደረግ ጉዞ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

በተለያዩ አካላት የሚደረግ ጉዞ "መንፈሳዊ ጉዞ" ለመባል ማሟላት የሚገባው አምስት መስፈርቶች እንዳሉ Pankhurst (1994፡935) ይገልጻል፡፡ እነሱም፡- ጉዞ መደረግ፣ ጉዞው ቋሚ መዳረሻ ያለው፣ ወደ ቅዱስ ስፍራ የሚደረግ ጉዞ በተወሰነ ጊዜ፣ ቀን ወይም ወቅት የተገደበ መሆኑ፣ በተወሰነ የጊዜ ገደብ በሚፈለገው ስፍራ መድረስና ጉዞው በተናጠል ሳይሆን በቡድን መደረጋቸው ናቸው፡፡

ለሙዳ በዓላት ወቅት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች መዳረሻ ስፍራቸው ቋሚ ሲሆን ስፍራውም አናጂና ቀበሌ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነው፡፡ መካነ ቅርሱም ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ ወደ ስፍራው የሚደረጉ ጉዞዎች በሙዳ በዓላት

[11] - ስለ መንፈሳዊ ሙዚቃዎቹ ባህርይ በምዕራፍ 8 እና 9 ተብራርቷል፡፡

[12] - ስለኡሌ ማዕረግ አሰጣጥ ሂደት በምዕራፍ 5 የቀረበ ሲሆን፣ በሙዳ ስርዓተከበራ ወቅት የሚከወኑ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ያላቸውን ባህርይ በምዕራፍ 8 ተተንትኗል፡፡

ወቅት የሚደረጉ ናቸው። የሙዳ በዓላት በየአመቱ ቋሚ ናቸው። ነገር ግን የበዓላቱ ቀናት በአመቱ ውስጥ በአንድ በተወሰነ ወቅት፣ በተለያዩ ቀናት ላይ የሚውሉ ናቸው። በመሆኑም የበዓላቱ ወቅቶች ቋሚ ቢሆኑም ቀናቱ ግን በየአመቱ ይለያያሉ።

ተጓዦቹም ወደ ስፍራው ሲሄዱ በቡድን በመሆን በበዓላት ወቅት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በመካነ ቅርሱ በመድረስ፣ በዓላቱ ሲጠናቀቁ ወደ መኖሪያ ስፍራቸው በመመለስ የሚከውኑት መንፈሳዊ ጉዞ ነው። በመሆኑም ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች በ Pankhurst (1994) የተገለጹ የመንፈሳዊ ጉዞ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ናቸው።[13] ሙዳ የሚለው ቃል ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎችን የሚገልጽ በመሆኑ በበዓላቱ ወቅት የሚደረጉ ጉዞዎችን "የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞዎች" በሚል መግለጽ ይቻላል።

የመንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ምክንያቶች (Motives) በዋናነት ኃይማኖታዊ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ኃይማኖታዊ ጉዳዮች በተለያዩ ንዑስ ደረጃዎች እንደሚመደቡ Stoddard (1997፡56) ይገልጻል። እነሱም፡- የተሻለ ነገር ለማግኘት፣ ለማመስገን፣ ኃይማኖታዊ ትዕዛዝን ለመፈጸም፣ ንስሃ ለመግባት፣ ህግን ለማክበር፣ ክብር ለማግኘትና ለጽድቅ በሚሉ ሰባት ደረጃዎች ይከፍላቸዋል። የመንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ምክንያቶች መንፈሳዊ ስሜትን ለማርካት፣ የቡድንን ማንነትና ሕብርን ለመመስረት፣ ለፈውስ፣ ስጦታ ለመስጠት፣ ለንግድ፣ ለመዝናናት አልፎአልፎም ወንጀል ለመፈጸም እንደሆኑ Pankhurst (1994፡947-950) ይገልጻል። ከእነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ መንፈሳዊ ተጓዦችም ለበረከት፣ ማህበራዊ ደረጃን ከፍ ለማድረግ፣ የእርቅ ስርዓት ለመፈጸም፣ ጋብቻ ለመፈጸም፣ ምህላ ለመፈጸም፣ እርግማን ለመፈጸምና የፖለቲካ ርዕዮትን ለማስፋፋት በሚል ዓላማ ወደ ቅዱስ ስፍራዎች ይሄዳሉ።

ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረጉ የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞዎች የተለያዩ አነሳሽ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ የሚካሄዱ ናቸው። አነሳሽ ምክንያቶቹም መንፈሳዊ ተጓዦች በሕይወታቸው ማግኘት የሚመኙትን ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንዲሚሉላቸው ለመጠየቅ፣ የጠየቁት ነገር ሲሳካ ለማመስገን፣ ከሰሩት ኃጽያት ለመሰረይ፣ የሼኽ ሁሴንን ትዕዛዝ ለመፈጸም፣ ያለባቸውን ግዴታና ውዴታ ለመወጣት፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ክብርን ለመጎናጸፍ፣ ከሞት በኋላ ነፍሳቸው ገነት እንድትገባ ለመለመን፣ ከደረሰባቸው አካላዊና መንፈሳዊ ህመም ለመፈወስ፣ በመካነ ቅርሱ ለሚገኙ የኃይማኖት አባቶች፣ ነዋሪዎች ወይም በዓላትን ጠብቀው በመምጣት

---

[13] - የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ያላቸው ባህርያት በምዕራፍ 6 በዝርዝር ቀርቧል።

ምጽዋዕትና እርዳታ ለሚፈልጉ ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎችን ለመስጠት፣ ለንግድ፣ ለጉብኝት፣ ማህበራዊ ደረጃን ከፍ ለማድረግ፣ የፖለቲካ ርዕዮትን ለማስፋፋት፣ የእርቅ ስርዓትን ለመፈጸምና የተለያዩ ወንጀሎችን ለመፈጸም በሚል የሚካሄዱ ናቸው፡፡[14]

የመንፈሳዊ ጉዞ አይነቶችን በተለያዩ መስፈርቶች መመደብ ይቻላል፡፡ እነዚህን መስፈርቶች Stoddard (1997፡57) ከጉዞው ርቀት፣ ከጉዞው ድግግሞሽ፣ ከጉዞው የእንቅስቃሴ ሂደት፣ መንፈሳዊ ቦታው ከሚገኝበት መልክዓምድራዊ አቀጣጫ፣ የመንፈሳዊ ቦታው ጠቃሚነት፣ የመንፈሳዊ ተጓዦች አነሳሽ ምክንያትና ከመንፈሳዊ ተጓዦች ባህርያት በሚሉ መስፈርቶች በሰባት ይከፍላቸዋል፡፡ ከእነዚህ የመክፈያ መስፈርቶች አንጻር የድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ያለው ባህርይ እንደ መንፈሳዊ ተጓዡ ማንነት የሚለያይ ነው፡፡ ይህም ለምሳሌ ተጓዡ ከሚነሳበት ቦታ፣ ወረዳ፣ ክልል ወይም አገር መሰረት በማድረግ ከርቀት አንጻር አካባቢያዊ፣ አገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ብለን በመስፈርት መለየት እንችላለን፡፡

ከድግግሞሽ አንጻር ደግሞ መንፈሳዊ ተጓዡ ወደ ስፍራው ከሚሄድበት አንጻር በተደጋጋሚ፣ በአመትና አልፎአልፎ በሚል፣ ከጉዞው እንቅስቃሴ ሂደት አንጻር በአንድነት ወይም በተመሳሳይነት፣ በክብና በቅደምተከተል በሚል መመደብ ይቻላል፡፡ በዓለምአቀፍ ደረጃ በተለያዩ ኃይማኖቶች ዘንድ ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸውና መንፈሳዊ ጉዞ የሚደረግባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል በክርስትና ኃይማኖቶች ዘንድ እየሩሳሌም (እስራኤል)፣ በእስልምና ኃይማኖት መካ-መዲና (ሳውዲ አረቢያ)፣ በቡድሂዝም ኃይማኖት ዘንድ ቡዳጋያ (ሕንድ) በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ ስፍራዎች መካከል ወደ እየሩሳሌምና ወደ መካ-መዲና በርካታ ቁጥር ያለው መንፈሳዊ ተጓዥ ከኢትዮጵያ ይሄዳል፡፡

በአገራችን በተለያዩ ኃይማኖቶች ዘንድ ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸውና በርካታ ቁጥር ያለው መንፈሳዊ ተጓዥ የሚሄድባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል በኦርቶዶክስ ተዋህዶ የክርስትና ኃይማኖት ቁልቢ ገብርኤል፣ ላሊበላ ውቅር ቤተክርስቲያናት፣ አክሱም ጽዮን ማርያም፣ ግሸን ማርያምና ደብረ ሊባኖስ ገዳም ይጠቀሳሉ፡፡ በእስልምና ኃይማኖት አልነጃሺ፣ ድሬ ሼኽ ሁሴን፣ ሶፍ ዑመር፣ አልከስዬና ፈረቀሳ ይጠቀሳሉ፡፡ በኦሮሞ ብሔር የዋቄፈና ኃይማኖት ተከታዮች የአባ ሙዳ መንፈሳዊ ጉዞና ሆራ አርሰዲ (ቢሾፍቱ ከተማ) ይጠቀሳሉ፡፡

[14] - የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ምክንያቶች በምዕራፍ 6 በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

ከእነዚህ መንፈሳዊ ጉዞዎች መካከል አንዳንዶቹ ተመሳሳይ ኃይማኖት ያላቸው ግለሰቦች ብቻ የሚሄዱባቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል የቁልቢ ገብርኤል፣ የላሊበላ ውቅር ቤተክርስቲያናት፣ የአክሱም ጽዮን ማርያም፣ የግሸን ማርያም፣ የደብረ ሊባኖስ ገዳም፣ የአልነጃሺ፣ የአባ ሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ የሚካሄድባቸው ቅዱስ ስፍራዎች ይጠቀሳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የኃይማኖት ድንበር ክለላን በማለፍ ከተለያየ ኃይማኖት የመጡ ግለሰቦች በጋራ የሚሄዱባቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል የድሬ ሼኽ ሁሴን፣ የሶፍ ዑመር፣ የአልከስዬ፣ የፈረቀሳና የሆራ አርሰዲ ቅዱስ ስፍራዎች ይጠቀሳሉ፡፡

Punkhurst (1994፡938-942) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አስር ቦታዎች ከሚካሄዱ መንፈሳዊ ጉዞዎች በመነሳት ጉዞዎቹ ያላቸውን ባህርይ በአራት ይመድባቸዋል፡፡ እነሱም፣ የአንድ ብሔር አባላት ብቻ የሚሄዱበት፣ የተለያየ ብሔር ያላቸው ሰዎች በአንድ የሚሄዱበት፣ የፖለቲካ ድንበርን (የዓለምአቀፍ ወይም የአገር ድንበርን) በመሻገር የሚሄዱበት፣ የተለያየ ኃይማኖት ያላቸው ሰዎች በአንድ የሚሄዱበት ናቸው፡፡ የተለያየ ኃይማኖት፣ ብሔርና ቋንቋ ያላቸውና የኃይማኖትና የብሔር ድንበርን እንዲሁም ዓለምአቀፍና አገራዊ ድንበርን በመሻገር ግለሰቦች በጋራ መንፈሳዊ ጉዞ ከሚያደርጉባቸው ቅዱስ ስፍራዎች መካከል አንዱ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መሆኑን Punkhurst (1994፡939) ይገልጻል፡፡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና፣ የክርስትና የዋቂፈና ኃይማኖት ወይም የሌላ ኃይማኖት ተከታዮች ለአምልኮ ይሄዳሉ፡፡

በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የኦሮሞ፣ የጉራጌ፣ የሲዳማ፣ የሱማሌና የአማራ ብሔር ተወላጆች ወደ ስፍራው እንደሚሄዱ Eshetu (1973) ይገልጻል፡፡ በመረጃ ስብሰባዬ ወቅት ከእነዚህ ብሔር ተወላጆች በተጨማሪ የስልጤ፣ የአርጎባ፣ የዱቤ[15] እና የትግሬ ብሔር ተወላጆች ወደ ስፍራው እንደሚሄዱ ተመልክቻለሁ፡፡ ከአገር ውጪም ከኬንያ፣ ከሱማሊያና ከኢራን መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ በመሆኑም ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ በኃይማኖት፣ በጾታ፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በመደብና በሌሎች ምክንያቶች የተለያዩ ግለሰቦች በጋራ የሚደርጉት ነው፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ እንደድሬ ሼኽ ሁሴን አይነት የተለያየ የኃይማኖትና የብሔር ዳራ ያላቸው ግለሰቦች የሚሳተፉባቸው መንፈሳዊ ጉዞዎች ሶስት ልዩና የጋራ ባህርያት እንዳላቸው Levine

[15] - የዱቤ ማህበረሰብ በባሌ ዞን በጋሰራ፣ በጃራ፣ በቤልቱና በደሎ መና ከተሞችና አካባቢያቸው እንዲሁም በሱማሌ ክልል የሚኖር የራሱ ቋንቋና ባህል ያለው ሕዝብ ነው፡፡

(1974፡44 እና 50) ይገልጻል፡፡ ባህርያቱም የተለያየ የኃይማኖት ዳራ ያላቸውን ኢትዮጵያውያንን በአንድ ስፍራ ያገናኛሉ፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያየ ብሔር ያላቸው ቡድኖች አንድ ላይ ያሰባስባሉ እንዲሁም ፓን-ኢትዮጵያን ያሳያሉ፡፡

## 2.2.6 የውሕደት ምንነትና ባህርያት

ውሕደት (Syncretism) የሚለው ቃል ስርወ-ምንጩ የግሪክ ቃል ከሆነው '*syn-kretismos*' ሲሆን፣ ቃሉን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው የታሪክና የፖለቲካ ፍልስፍና ምሁሩ ፕሉታርክ ነው (Kippenberg, 2004፡29 እና Kane, 2017፡13)፡፡ ፕሉታርክ ቃሉን የተጠቀመው በግሪኮ-ሮማን ዘመን (ከ300 BC እስከ 200 CE) በተለያዩ የኃይማኖት አስተምህሮዎች መካከል የተፈጠረውን ልዩነት ማቀላቀል (Fusion) የሚለውን ሃሳብ ለመግለጽ እንደነበር Rahaman (2016፡51) ይገልጻል፡፡ Kane (2017፡13-59) ደግሞ ፕሉታርክ በ2ኛው መቶ ክ/ዘመን ቃሉን በተጠቀመበት ወቅት ክሪታኖች[16] በመሃላቸው ያለውን የፖለቲካ ልዩነት በማጥበብ ወደ አንድ ማዋሀድ የሚል ጽንሰሃሳብን ለመግለጽ እንደነበር ይገልጻል፡፡

ውሕደት የሚለውን ቃል "ሁለት ወይም ከዛ በላይ ባሉ ኃይማኖቶች መካከል ያለ የለውጥ ሂደት ነው፡፡" በማለት Braukämper (1992፡194-195) ይበይነዋል፡፡ ይህ ብያኔ ውሕደት የለውጥ ሂደት እንደሆነ ያሳያል፡፡ Kane (2017፡4) ውሕደት "በኃይማኖቶች ቅልቅል ውስጥ የሚከሰት የትግል ሁነት ነው፡፡" በማለት ብያኔ ይሰጣል፡፡ ይህ ብያኔ ውሕደት በኃይማኖቶች መካከል የእርስበርስ ውድድር እንደሆነ ያሳያል፡፡ Rudolph (2004:82) ውሕደት የተለያየ ዳራ ያላቸው ሀይማኖቶችና ባህሎች በአንድ ላይ ሲገናኙ የሚፈጥሩት ጥምረት መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይህ ብያኔም ውሕደት በግንኙነት ምክንያት የሚፈጠር ጥምረት እንደሆነ ያሳያል፡፡ Rahaman (2006፡51) ደግሞ ውሕደት "ብዝሃ ባህሎች በአንድ ላይ በመገናኘት ጠንካራ የባህል ጥርቅም (Cultural amalgam) እና ሕብር (Harmony) ለመፍጠር የሚረዳ በጣም ጠቃሚ መደላድል ነው፡፡" በማለት ውሕደትን ካለው ጠቀሜታ አንጻር ይበይነዋል፡፡

ውሕደት ለሚለው ቃል በቀላሉ ብያኔ ለመስጠት አስቸጋሪና ጽንሰሃሳቡም ውስብስብ መሆኑን Baird (2004፡2) ይገልጻል፡፡ ቃሉም ካለው ውስብስብነት በተጨማሪ በቃሉ ላይ በየዘመኑ

---

[16] - ክሪታኖች በወቅቱ የነበሩ ቡድኖች ስያሜ ነው፡፡ ቃሉ አሉታዊ ትርጉም ያለው ሲሆን "አደገኛ ቦዘኔ" እንደማለት ነው፡፡ ቡድኖቹ እራሳቸውን ክሪታን በሚል ይጠሩት ነበር (Kane, 2017)፡፡

የነበሩት ግንዛቤዎችና እሳቤዎች የተለያየ መሆን በቀላሉ ብያኔ መስጠት አዳጋች አድርጎታል። ቃሉ በየዘመኑ የነበረውን እሳቤ በአጭሩ ቀጥለን እንመልከት።

ውሕደት በየዘመኑ የነበረውን የእሳቤ ለውጥ Kane (2017፡13-59) እንደሚከተለው ይገልጸዋል። ፕሉታርክ በ2ኛው መቶ ክ/ዘመን ቃሉን ከተጠቀመበት ጊዜ ጀምሮ ቃሉ አንድነት፣ ሕብረትና የጋራነት የሚል ትርጓሜ መያዝ ጀመረ። 19ኛው እና በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን የኃይማኖት ታሪክ ምሁራን ቃሉን ሲጠቀሙ የተለያዩ ኃይማኖቶች ያላቸውን የእርስበርስን ቅልቅል (Mixing) ለመግለጽ ነበር። በ17ኛው መቶ ክ/ዘመን በሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ በተፈጠረው የኃይማኖት አስተምህሮ ልዩነት ምክንያት በ17ኛው እና በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ በነበሩ የክርስቲያን ኃይማኖት ምሁራን ዘንድ ቃሉ እንደስድብ ይወሰድ ነበር። በ19ኛው ክ/ዘመን እና በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ አጋማሽ ላይ ቃሉ አወንታዊም አሉታዊም ትርጉም መያዝ ጀመረ። በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ አንስቶ እስከ አሁን ዘመን ውሕደት የሚለው ቃል በራሱ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ትርጉም የሌለው ተደርጎ ይወሰዳል።

በኃይማኖት ታሪክ አጥኚ በሆኑ ምሁራን ዘንድ ውሕደት የሚለው ቃል በተለያየ ዘመን የተለያዩ እሳቤዎች ነበሩት። እነዚህ እሳቤዎች ያለፉበትን የእድገት ደረጃዎች Kane (2017፡61-62) በአራት ይመድባቸዋል። እነሱም፡- አንደኛው፣ “ዕውቅና የመስጠት ደረጃ” (“Recognizing ubiquity”) ነው። ይህ ደረጃ ከ19ኛው መቶ ክ/ዘመን አጋማሽ እስከ 20ኛው መቶ ክ/ዘመን አጋማሽ ድረስ በጀርመንና በአካባቢው አገራት የተስፋፋበት ነው። በዚህ ደረጃም ውሕደት ዓለምአቀፋዊ መሆኑን፣ ከአንድ ኃይማኖት ባለፈ ሁሉም ኃይማኖቶችን የሚገልጽ መሆኑንና በውጭ እይታ የጥናት ዘዴ የሚያጠኑ ምሁራን (Etic scholars) ዘንድ በቃሉ ላይ ያላቸው ግንዛቤ የተቀየረበት ነው።

በዚህም የእይታ ዘዴ የኃይማኖት ምሁራን እንደኃይማኖተኛና ኃይማኖቱን እንደሚተገብሩ አማኞች ሳይሆን፣ ገለልተኛና የውጭ ተመልካች ሆነው ማጥናት ጀመሩ። ሁለተኛው፣ “ውሕደትን ግልጽ የማድረግ ደረጃ” (“Elucidating syncretism”) ነው። ይህ ደረጃ ከ1960 እስከ 1980ዎቹ ድረስ የነበረ ነው። በዚህ ደረጃም ስለውህደት ምንነት፣ ባህርያትና አይነት በግልጽ የተገለጸበትና ኃይማኖትን በውጭ እይታ የጥናት ዘዴ ማጥናት በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋበት ነው።

ሶስተኛው፣ “ቅየጣን የማድነቅ ደረጃ” (“Celebrating mixture”) ነው። ይህ ደረጃ በ1990ዎቹ የነበረ ነው። በዚህ ደረጃም የራስን ባህል በመያዝ የአውሮፓን ቅኝ ገዢ ባህልን መታገል የተጀመረበት ሲሆን፣ ውሕደት የኃይልና የትግል ስሜትን ከፍ ያደርጋል በሚል እንደመሳሪያነት እንዲያገለግል ትኩረት የተሰጠበት ነው። አራተኛው፣ “ግንዛቤን የማካተት ደረጃ” (“Incorporating cognition”) ነው። ይህ የውሕደት እሳቤ አሁን (በዚህ ዘመን) የደረሰበት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃም ውሕደት እንዴት እንደሚከሰት፣ እንደሚተገበርና እንደሚፈጠር እንዲሁም በኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ (Cognitive theory) ያለውን አተያይና አተገባበር ማጥናት ላይ ትኩረት የተሰጠበት ነው። እነዚህ አራት የእድገት ደረጃዎች ውሕደት በሚለው ቃል ላይ በተከታታይ በሚነሱ ጥያቄዎችና እሳቤዎች ላይ ምሁራኑ ያላቸውን ጥልቅ እይታዎች ያሳያሉ። ከእነዚህ በተጨማሪም በቃሉ ላይ በሂደት የተለወጡ ግንዛቤዎችን ያሳያሉ።

ውሕደት የሚለው ጽንሰሃሳብ በተለያየ ዘመን የተለያዩ የኃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የፍልስፍናና የታሪክ እሳቤዎችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውል ነበር። ጽንሰሃሳቡ ጥቅም ላይ ሲውል በተለያዩ ቃላት ነው። ከእነዚህ ቃላት መካከል ቅልቅል (Mixture)፣ ተጽዕኖ (Inculturation)፣ ነባርነት (Indigenization)፣ አውዳዊነት (Contextualization)፣ መፈጠር (Bricolage)፣ መበከል (Contamination)፣ መሰንጠቅ (Interpenetation)፣ ግንኙነት (Creoization)፣ መዳቀል (Hybridity)፣ መገናኘት (Synergy)፣ መበየድ (Blending) የመሳሰሉት ቃላት ጥቅም ላይ ውለው እንደነበር Kane (2017) ይገልጻል።

እነዚህ ቃላት ጽንሰሃሳቡን ለመግለጽ በተለያየ ወቅት ጥቅም ላይ ውለዋል። ነገር ግን ቃላቱ ካላቸው ትርጓሜ፣ አጠቃቀም፣ ታሪካዊ ዳራ፣ የዕውቀት ዘርፍ ዳራ እንዲሁም ይዘት አንጻር ተቀባይነት አላገኙም። እነዚህ ቃላት ለምን ውሕደት የሚለውን ጽንሰሃሳብ መግለጽ እንዳልቻሉ Kane (2017፡92) ከተነተናቸው ቃላት መካከል የተወሰኑትን በምሳሌነት እንመልከት።

ግንኙነት (Creoization) እና መዳቀል (Hybridity) የሚሉት ቃላት በቅኝ ግዛት ዘመን በባህሎች መካከል የተፈጠረውን ቅልቅል የሚገልጹ ናቸው። በተለይ መዳቀል የሚለው ቃል በድህረ ቅኝ ገዢ ንድፈሃሳብ (Post-Colonial theory) አራማጆች ዘንድ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። ቃሉም የቅኝ ገዢ ስርዓት ያለውን ባህል በተገዢው ሕዝብ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ የሚገልጽ ነው። ነገር ግን ውሕደት የሚለው ቃል ከኃይማኖት ጋር የተያያዘ መሆኑ፣ እድገትን፣ ቅኝ ገዢነትንም ሆነ

ቅኝ ተገዢነትን የማያመለክት መሆኑ እንዲሁም ከዚህ በፊት የነበሩ የተለያዩ ነገሮች በፈጠሩት ግንኙነት አዲስ ነገር መፈጠርን ብቻ የሚገልጽ አለመሆኑ ከእነዚህ ቃላት የተለየ ያደርገዋል፡፡

መፈጠር (Bricolage)[17] የሚለው ቃል በክላውድ ሌቪ-ስትራውስና በሌሎች ምሁራን ዘንድ ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡ ቃሉም ሁኔታዎች እንደሚፈልጉት ከነባሩ ባህል የተለያዩ ነገሮችን በመውሰድ አዲስ የባህል ቅርጽ መፍጠርን የሚገልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ውሕደት ከተለያዩ ነገሮች የሚፈጠር ቢሆንም አዲስ የባህል ቅርጽ መፍጠር ብቻ አይደለም፡፡ ውሕደት የተለያዩ መንፈሳዊና ቁሳዊ ግብዓቶችን በመውሰድ ነባሩን ባህል በአዲስ አውድ (Context) መግለጽ ነው፡፡ ከእነዚህ ሀሳቦች እንደምንረዳው ውሕደት ከኃይማኖት ጋር የተያያዘ መሆኑ፣ የአንዱ ኃይማኖት ወይም ባህል በሌላው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አለመሆኑ፣ ከዚህ በፊት የነበሩ የተለያዩ ነገሮች በፈጠሩት ግንኙነት አዲስ ነገር መፈጠርን የሚገልጽ ቢሆንም አዲስና ልዩ የባህል ቅርጽ መፍጠር አለመሆኑን እንዲሁም የተለያዩ መንፈሳዊና ቁሳዊ ግብዓቶችን በመውሰድ ነባሩን ባህል በአዲስ አውድ መግለጽ ማለት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ውሕደት የሚለውን ቃል በርካታ አጥኚዎች ቃሉን ከመጠቀም ባለፈ በትክክለኛው መንገድ እንደማይጠቀሙ Martine and Leopold (2004፡93-108) ይገልጻሉ፡፡ አጥኚዎች ቃሉን ሲጠቀሙ ከመረጃቸው በመነሳት መሆን እንዳለባቸው Martine and Leopold (2004) ገልጸው፣ አጥኚዎች ውሕደት የሚለውን ጽንሰሃሳብ ሲጠቀሙ ሶስት ጉዳዮችን ግዴታ ከግምት ማስገባት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡ እነሱም፡- አንደኛ፣ በመረጃዎች መካከል ያለውን ዝምድና በመፈተሽ በአንድ ውስን ጊዜና ቦታ የተፈጠረን ውሕደት ማረጋገጥ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

ሁለተኛ፣ ሁለትና ከዛ በላይ ባሉ ባህሎች መካከል ባለው ግንኙነት በድንገት የተጨመረ ወይም የተቀነሰ፣ የተለወጠ ወይም/ እና የተተካ እንዲሁም የተጣመረ ነገር በመረጃ ውስጥ መኖር ግዴታ ነው፡፡ ሶስተኛ፣ መረጃዎችን ከታሪካዊና ከአንትሮፖሎጂያዊ መረጃዎች ጋር በማነጻጸርና በማወዳደር ገለጻ መስጠት ግዴታ ነው፡፡ በዚህ ጥናት እነዚህን ሶስት ግዴታዊ ጉዳዮች ከግምት በማስገባት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላትና የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ውሕደቶችን ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡

---

[17] - ‘bricolage’ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ክላውድ ሊቪ-ስትራውስ ነው፡፡ ቃሉም ‘bric-a-brac’ የሚለው የእንግሊዝ ቃል ሊተካው እንደሚችል Kane (2017፡95) ይገልጻል፡፡

የውሕደት ተፈጥሯዊ ባህርያት ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት Martine and Leopold (2004፡106) ይገልጻሉ፡፡ ደረጃዎቹም፣ አንደኛው፣ "ማህበራዊ (Social)" ደረጃ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ኃይማኖታዊ ይዘትንና ኃይማኖታዊ ድንበርን ለመለየትና ለመቆጣጠር ኃይልን ተግባራዊ ማድረግን የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው፣ "ትዕምርታዊ (Semiotic)" ደረጃ ነው፡፡ ይህ ደረጃ የውሕደት አፈጣጠር በኃይማኖቱ ላይ ያለው አንድምታዊና ለውጣዊ ተጽዕኖን የሚያሳይ ነው፡፡ ሶስተኛው፣ "ኮግኒቲቭ (Cognitive)" ደረጃ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ጽንሰሃሳባዊ ጥምረትና ኃይማኖታዊ ምደባ ያላቸውን ባህርያት የሚያብራራ ነው፡፡

አጥኚዎች ውሕደት የሚለውን ጽንሰሃሳብ በጥናታቸው ሲጠቀሙ እነዚህን የውሕደት ተፈጥሯዊ ባህርያት ከግምት ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም አጥኚዎች በውሕደት ላይ ያገኙት መረጃ በየትኛው የውሕደት ደረጃ ላይ ያለ እንደሆነ በግልጽ እንዲተነትኑ ይረዳል፡፡ በዚህ ጥናት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላትና የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ውሕደቶች የኮግኒቲቭ ደረጃ ላይ ሊመደቡ የሚችሉ ባህርያት አላቸው፡፡ ይህ ባህርያቸውም በሙዳ ስርዓተከበራዎችና እሳቤዎች ላይ ይንጸባረቃል፡፡

በአገራችን የተለያዩ መንፈሳዊ ቦታዎች የውሕደት ባህርይ አላቸው፡፡ በእነዚህ ስፍራዎች ውሕደት የተከሰተበትን አራት ምክንያቶች በምሳሌ በማስደገፍ Punkhurst (1994፡940-942) ያብራራል፡፡ እነሱም፡- አንደኛው፣ በሀገረሰባዊ ኃይማኖት (Traditional religion) የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞን በአንድ አምላክ ከሚያምኑ (Monothesist) ሌሎች ኃይማኖቶች ጋር የተወሰነ ማቻቻል በማድረግ ሲቆይ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ውሕደት ከተፈጠረባቸው መንፈሳዊ ስርዓተከበራዎች መካከል ኢሬቻን ይጠቅሳል፡፡ ኢሬቻ በኦሮሞ ብሔር የዋቄፈና ኃይማኖት አስተምህሮ ለፈጣሪ ምስጋና ለማቅረብ የሚከወን መንፈሳዊ ስርዓት ነው፡፡ ስርዓቱም ውኃ ባለባቸው አካላት (በወንዝ፣ በኃይቅ ወይም በኩሬ)፣ በተራራማ ወይም በኮረብታማ ስፍራዎች እንዲሁም በመኖሪያ ቤት አካባቢ የሚከወን ነው፡፡

ሁለተኛው፣ በአንድ አምላክ ከሚያምኑ ኃይማኖቶች መካከል አንዱ ሀገረሰባዊ ዕምነቶችን (Traditional beliefs) በመለወጥና በእነሱ ቦታ በመተካት እንዲሁም ነባር የሆኑ መካነ ቅርሶችንና አልፎአልፎ የተወሰኑ ቀደምት ትግበራዎችን ሲወስድ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ውሕደት ከተፈጠረባቸው መንፈሳዊ ስፍራዎች መካከል የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን ይጠቅሳል፡፡ በመካነ ቅርሱ የተከሰተው ውሕደት የተለያዩ ሕዝቦችና ኃይማኖቶች በስፍራው

በነበራቸው ታሪክ ምክንያት እንደሆነ "በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነባር የሆነው የሲዳማ ሕዝብ ነው። እነሱም የእስልምናን ኃይማኖት ተቀበሉ። ከዛ በኋላ ስፍራው በኦሮሞዎች ተያዘ። ይህም በመካነ ቅርሱ ውሕደት እንዲከሰት ምክንያት ሆነ።" በማለት Punkhurst (1994፡941) ይገልጻል።[18]

ሶስተኛው፣ ሁለት ኃይማኖቶች ጎን ለጎን ሲገኙ ነው። በዚህ ምክንያት ውሕደት ከተፈጠረባቸው መንፈሳዊ ስፍራዎች መካከል ዙቋላን ይጠቅሳል። የዙቋላ ተራራ በቢሾፍቱ ከተማ አካባቢ የሚገኝ ነው። በተራራ ላይ የዋቄፈና ኃይማኖት የማምለኪያና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሆነው የአቡየ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን በአንድ አካባቢ ይገኛሉ። አንዳንድ መንፈሳዊ ተጓዦችም ወደ ስፍራው በሚሄዱበት ወቅት የዋቄፈናም የክርስትናም መንፈሳዊ አምልኮዎች እንደሚፈጽሙ ይገልጻል።

አራተኛው፣ ከተለያዩ ኃይማኖቶች ውስጥ ያሉ መንፈሳዊ ጉዳዮችን በመውሰድ አዲስ የአምልኮ ስርዓት ሲፈጠር ነው። በዚህ ምክንያት ውሕደት ከተፈጠረባቸው መንፈሳዊ ስፍራዎች መካከል ፈረቃሳን ይጠቅሳል። ፈረቃሳ በአርሲ ዞን፣ አቦምሳ ከተማ አካባቢ የሚገኝ የአምልኮ ስፍራ ነው። ስፍራው ቅዱስ እንደሆኑ በሚታመኑት በአዮ ሞሚና የተመሰረተ ነው። አዮ ሞሚና በወሎ የጁ ከክርስቲያን ቤተሰቦች እንደተወለዱና በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ላይ ወደ አርሲ በመምጣት የእስልምና ኃይማኖትን እንደተቀበሉ Punkhurst (1994) ይገልጻል። Gemechu (2007) ደግሞ የእሳቸው ማንነት አከራካሪና ግልጽ ያልሆነ መሆኑን ይገልጻል።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የውሕደት ባህርያት እንደሚስተዋሉ የተለያዩ ምሁራን ገልጸዋል። እነዚህ ምሁራንም Baxter (1987)፣ Andrzejewski (1974)፣ Punkhurst (1994)፣ Braukämper (1984 እና 2002)፣ Mohamed (2005 እና 2015)፣ Umer (2006)፣ Østebo (2012)፣ ዳንኤል (2006 ዓ.ም)፣ Gemechu (2013) እና Abbas (2014) ናቸው። በእነዚህ ጥናቶች ውህደት መኖሩ ቢገለጽም፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከወኑ ስርዓተከበራዎች፣ በሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች፣ በቁሳዊ ባህሎች፣ በትዕምርቶች፣ በመንፈሳዊ ሙዚቃዎችና ከሌሎች መገለጫዎች አንጻር ያሉትን የውሕደት ባህርያትና ደረጃዎች በጥልቀት የሚያሳዩ አይደሉም። በዚህ ጥናት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላትና በሚደረጉ የመንፈሳዊ ጉዞዎች ስርዓት ውስጥ የሚታዩ ውሕደቶችን፣ የውሕደቶቹ መነሻ ምክንያቶችን፣

---

[18] - የመካነ ቅርሱ ታሪክን በሚመለከት በምዕራፍ 4 ተብራርቷል።

ውሕደቶቹ ስፍራውን እንዴት ልዩ ገጽታ እንዳላበሱት፣ ውሕደቶቹ ለመካነ ቅርሱ የፈጠሩለትን ተጨማሪ እሴቶች እንዲሁም የውሕደቶቹ ደረጃዎችና ባህርያት በጥናቱ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተተንትነዋል፡፡

## 2.2.7 የሙዳ ምንነት

ሙዳ (Muuda) የሚለው ቃል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ በዓላትን፣ በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን፣ ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞን እንዲሁም ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርግን ተጓዥ የሚገልጽ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከበሩ በዓላት፣ ስርዓተከበራዎችና መንፈሳዊ ጉዞዎችን የሚገልጸው ሙዳ የሚለው ቃል ስያሜ በ'ዋቄፈና' ኃይማኖት አስተምህሮ ከሚካሄደው የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ መነሻ እንዳደረገ Umer (2006፡60) ይገልጻል፡፡ ዋቄፈና የኦሮሞ ብሔር ነባር ሀይማኖት ነው፡፡[19] የዋቄፈና ሀይማኖት ተከታዮች 'ዋቄፈታ' በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡

በዋቄፈና ሀገረሰባዊ ሀይማኖት አስተምህሮ 'ዋቃ' ዋናው መሰረት ነው፡፡ 'ዋቃ' የሚለው ቃል የተለያዩ እሳቤዎችን የሚይዝ ነው፡፡ ዋቃ በአንድ በኩል አምላክን (ፈጣሪን) ሲገልጽ በአንድ በኩል ደግሞ ሰማይን የሚገልጽ መሆኑን Tilahun (1989:586) እና Bartels (1990:89) ያሳያሉ፡፡ ዋቃ የሚለው ቃል እነዚህን ሁለት የተለያዩ እሳቤዎች የሚገልጸው በፊደሎቹ አጻጻፍ ልዩነት እንደሆነ Bartels (1990) ይገልጻል፡፡[20] Gemetchu (1994:82) ዋቃ የሚለው ቃል አምላክንና ሰማይን የሚገልጽ እንደሆነ ጠቅሶ፣ ሰማይ የሚለው እሳቤ ከምድር በላይ ያሉ አካላትን፣ ሰማያትን፣ ዋቃን መጠበቅ እንዲሁም ገነትን አጠቃሎ የሚገልጽ መሆኑን አብራርቷል፡፡

ሙዳ የዋቄፈና ሀይማኖት ተከታዮች በስምንት አመት አንድ ጊዜ ለቃሉ (ለአባ ሙዳ) ክብር ለመስጠት የሚካሄድ ስርዓት ነው፡፡ Asmarom (1973፡10) እና ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ (2000 ዓ.ም፡116)፡፡ በዋቄፈና ሀይማኖት አስተምህሮ አምላክ የመረጣቸው መንፈሳዊ አባቶችና የአምላክ መልዕክተኞች አባ ሙዳ ወይም ቃሉ በመባል ይጠራሉ፡፡ የአባ ሙዳ መቀመጫ በባሌ

---

[19] - ይህ ሀይማኖት ዋቄፈና ከሚለው ስያሜ በተጨማሪ 'መንዶዩ' በሚል ይጠራል (ድሪቢ፣2007ዓ.ም፣234)፡፡

[20] - ይህ ሀሳብ በኦሮምኛ ቋንቋ የ'ዋቃ' የመጀመሪያው ፊደል 'ካፒታል' (Waaqa) ሲሆን 'አምላክ' የሚል ትርጉም አለው፡፡ የዋቃ የመጀመሪያው ፊደል 'ስሞል' (waaqa) ሲሆን ደግሞ 'ሰማይ' የሚል ትርጉም አለው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህ የ Bartels (1990) አገላለጽ የእንግሊዘኛውን የቃላት እሳቤ (የ'God' እና የ'god') በኦሮምኛ ቋንቋ ላይ ለመጫን የተደረገ ሙከራ ይመስላል፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አጻጻፍ ይህ አይነት የመጀመሪያ ፊደል 'ካፒታልነት' እና 'ስሞልነት' መሆን የሚፈጥረው የትርጉም ልዩነት የለም፡፡

ዞን በመደወላቡ የሚገኘው የወላል ተራራ መሆኑን Huntingford (1955፡83) ይገልጻል። በዋቄፈና ሀይማኖት አስተምህሮ በስምንት አመት አንድ ጊዜ ወደ አባ ሙዳዎች የሚደረግን መንፈሳዊ ጉዞ የሚያካሂዱ ግለሰቦች "ጂላ" (Jila) በሚል ስያሜ ይጠራሉ (Mohamed, 2015)።

ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በ227 ኪ. ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው መደወላቡ የአባ ሙዳ ዋና መቀመጫና በብሔረሰቡ ታሪክ ልዩ ስፍራ የሚሰጠው ነው። መደወላቡ በአሁኑ ወቅት የቦታ መጠሪያ ስም ነው። ነገር ግን በኦሮሞ ሚት መሰረት ወላቡ የመጀመሪያው ፍጡር የተፈጠረበት ነው ድሪቢ (2007 ዓ.ም፡235)። በዋቄፈና ሀገረሰባዊ ሀይማኖት መሰረት ፍጥረት ሁሉ የተገኘው ከውኃ ነው፡፡ ውኃው የሚገኘው ደግሞ በወላቡ ነው፡፡ ወላቡ የተባለው ኅዋ (universe) ነው (ብሩ፣ 2008 ዓ.ም)፡፡ ኅዋውም ከፍጥረታት በፊት የነበረ ድቅድቅ ጨለማ፣ ድቡልቡልና ድፍን ነበር፡፡

ሙዳ የሚለው ቃል የዋቄፈና ሀይማኖት ተከታዮች በስምንት አመት አንድ ጊዜ ለቃሉ ወይም ለአባ ሙዳ ክብር ለመስጠት የሚካሄድ መንፈሳዊ ጉዞና የሚከወኑ ስርዓቶችን እንዲሁም በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ በዓሎችን፣ ስርዓተከበራዎችን፣ መንፈሳዊ ጉዞዎችንና መንፈሳዊ ተጓዥን የሚገልጽ ነው። በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከበሩ ሁለት የሙዳ በዓላት መካከል፣ የመጀመሪያው በዓል 'ሐጅ' በሚል ስያሜ ይታወቃል። ሁለተኛው በዓል 'ዛሕራ ገልገላ ጎበና' በሚል ስያሜ ይታወቃል። የእነዚህን በዓላት ምንነት በተናጠል ቀጥለን እንመለከታለን።

## 2.2.7.1 የሐጅ (የኢድ-አል-አድሃ በዓል) ምንነትና የአጀማመር ታሪክ

ሐጅ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች በአመት አንድ ጊዜ ወደ ሳዑዲ አረቢያ መካ የሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዞ ነው። ሐጅ የእስልምና ኃይማኖት ዋና መሰረታዊ ህግጋት ከሆኑ 5 መሰረታዊ ትዕዛዞች መካከል አንዱ ነው። በእስልምና ኃይማኖት አምስቱ ዋና መሰረታዊ ትዕዛዞች የሚባሉት፤ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ማመን፣ ነብዩ መሃመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆኑን ማመን፣ በቀን 5 ጊዜ በተወሰኑ ሰዓታት ስግደት (ሶላት) መፈጸም፣ ከአመታዊ ገቢ ላይ የተወሰነውን ያህል አቅም ለሌላቸው ድሆች መስጠት (ዘካ)፣ በረመዳን ወር መጾም እና የኃይማኖቱ ተከታይ በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ 1 ጊዜ በገንዘብና በአካል ብቁ ሲሆን ወደ መካ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ (ሐጅ) ናቸው።

በእስልምና ኃይማኖት ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ በሚታመነው መካ የሚደረጉ ጉዞዎች ዑምራ እና ሐጅ በሚል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ የዑምራ ጉዞ በአመቱ ውስጥ በሚገኙ በማንኛውም ወቅቶች ወይም ቀናት መካን ለመጎብኘት የሚደረግ ጉዞ ሲሆን፣ ሐጅ ደግሞ ለተወሰኑ ቀናት በአመት አንዴ ብቻ የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ነው፡፡ የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ የሚደረገው በእስልምና ኃይማኖት የጊዜ ቆጠራ (ሂጅራ) መሰረት ነው፡፡ የሂጅራ የዘመን አቆጣጠር መነሻው በ622 ነብዩ መሐመድና ጥቂት ተከታዮቻቸው ከመካ ወደ መዲና ያደረጉትን ጉዞ ነው፡፡ ይህን ጉዞ መነሻ በማድረግ አመት አንድ ብሎ መቆጠር እንዲጀመር ያደረገው ሁለተኛው ካሊፍ ኡመር ኢብን አል-ካታብ በ644 ላይ ነው፡፡ ነብዩ መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ጉዞ ያደረጉበት ቀን ሐምሌ (ጁን፣ 16 ቀን 622) በመሆኑ ይህ ቀን የሂጅራ የቀን መቁጠሪያ አንድ ብሎ የተጀመረበት ነው (Gulevich, 2005፡254)፡፡

የሂጅራ የቀን አቆጣጠር መነሻ ያደረገው የጨረቃ ዑደትን ተከትሎ ይቆጠር ከነበረው የነባሩ የአረብ የቀን አቆጣጠር ባህል ነው፡፡ ይህ የጨረቃ የቀን አቆጣጠር በቅዱስ ቁርዓን (2+189) ላይ ከሰፈረውና አዲስ የጨረቃ መወለድ የሰው ልጅ የጊዜ መስፈሪያ እንደሆነ ከሚገልጸው ጋር የሚያያዝና ቁርዓናዊ መሰረት ያለው ነው፡፡ በጨረቃ አቆጣጠር ጨረቃ አዲስ ተወልዳ ስትጠፋ (ስትሞት) እንዲሁም ድጋሚ ስትወለድ ያለው ሂደት 12 ጊዜ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ አመት 12 ወራት ይኖሩታል፡፡ ነገር ግን ጨረቃ በአንድ ዑደት (ተወልዳ እስክትሞት) እና ጨረቃ ፀሐይን ለመዞር 29.53059 ቀናት ይወስድባታል፡፡ ይህ በመሆኑ በፀሐይ አቆጣጠር (መሬት ፀሐይን የመዞር ሂደት) በአመት ውስጥ ካሉት 365.2422 ቀናት በ11 ቀናት ወደ ኋላ ይቀራል (Gulevich, 2005)፡፡

በአውሮፓ የዘመን አቆጣጠር በ11 ቀናት በመቅረቱ ምክንያት የእስልምና በዓላት በአንድ አመት ውስጥ ሁለት ጊዜ ሊከበሩ ይችላሉ፡፡ በአውሮፓ የቀን አቆጣጠር በ1943 የእስልምና አዲስ አመት (የሙሐራም ወር የመጀመሪያው ቀን) በጥር (ጃኑዋሪ 8) እና በነሐሴ (ዲሴምበር 28) ሁለት ጊዜ እንደተከበረ Gulevich (2005፡254) ይገልጻል፡፡ ይህን አይነት አጋጣሚ በኢትዮጵያም በ2009 ዓ.ም መከሰቱን አስተውያለሁ፡፡ በ2009 ዓ.ም የሐጅ በዓል መስከረም 2 ቀን እና ነሐሴ 27 ቀን በአንድ አመት ውስጥ ሁለት ጊዜ ተከብሯል፡፡

በጨረቃ አቆጣጠር መሰረት የእስልምና በዓላት መቼ ዕለት እንደሚውሉ በትክክል እንዳይታወቅና በሁሉም ዓለም የሚገኝ የኃይማኖቱ ተከታይ በተመሳሳይ ዕለት በዓላትን

እንዳያከብር ምክንያት ሆኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሳዑዲ አረቢያ ያለውን የጨረቃ ዑደት መነሻ በማድረግና በመገናኛ ብዙሃን በሚደረግ የመረጃ ተስተላልፎ በተለያየ የዓለም ክፍል የሚገኝ የኃይማኖቱ ተከታይ በተመሳሳይ እለት በዓላትን እንዲያከብር ጥረት ይደረጋል፡፡

ሐጅ በእስልምና የጊዜ አቆጣጠር ካሉት 12 ወራት መካከል በዱል-አል- ሒጃ ወር ወደ ሳዑዲ አረቢያ መካ ከተማ የሚካሄድ መንፈሳዊ ጉዞ ነው፡፡ ዱል-አል-ሒጃ በሂጅራ የጊዜ ቆጠራ የመጨረሻው ወር ነው፡፡ የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ በዓለም ላይ የሚገኙ የእስልምና ኃይማኖት በአንድ ላይ የሚገናኙበት በመሆኑ የአንድነትና የሕብር ተምሳሌት ነው፡፡ የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ በዱል-አል-ሒጃ ወር በ8ኛው ቀን የሚጀምር ሲሆን፣ ለ6 ተከታታይ ቀናት የሚከወን ነው (Gulevich, 2005)፡፡ መንፈሳዊ ጉዞውም በእያንዳንዱ ቀን በመካና በአካባቢው የሚገኙ የተለያዩ ቅዱስ ስፍራዎችን መጎብኘትና በስፍራዎቹም መንፈሳዊ ክወናዎችን መከወን ያካትታል፡፡ ወደ መካ የሐጅ ጉዞ ያካሄደ ሰው ልዩ ክብር ይሰጠዋል፡፡ በመጠሪያ ስሙ ላይም ማዕረግ ይጨመርለታል፡፡ ማዕረጉም ለወንድ ‘ሐጂ’ ሲሆን፣ ለሴት ደግሞ ‘ሐጃህ’ በሚል ይታወቃል፡፡

የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ የሚጠናቀቀው በዱል-አል-ሒጃ ወር በገባ በ10ኛው ቀን ነው፡፡ ይህ 10ኛው ቀን የኢድ-አል-አድሃ የበዓል ቀን ነው፡፡ የዚህ በዓል ታሪካዊ መነሻ ከነብዩ ኢብራሂም (አብርሃም)፣ የኢብራሂም ሁለተኛ ሚስት ከሆነችው ሐጋርና ከልጁ እስማኤል ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ታሪኩም ኢብራሂም (አብርሃም) ከመጀመሪያ ሚስቱ ሳራ ጋር ለረጅም አመት አብረው ቢቆዩም ልጅ መውለድ አልቻሉም፡፡ በዚህ ምክንያት አብርሃም ከሐጋር ልጅ ይወልዳል፡፡ በዚህ ድርጊቱ ሳራ ስለቀናች ሐጋርና ልጇ ወደ በረሃ ተሰደዱ፡፡ ከአመታት በኋላ ፈጣሪ አብርሃምን ልጅህን ሰዋልኝ ሲል በህልሙ ትዕዛዝ ሰጠው፡፡ አብርሃምም ልጁን ለመሰዋት ፍቃደኛ በመሆን በተራራ ላይ ወስዶት አንገቱን ሊያርደው ሲል ፈጣሪ በልጁ ምትክ በግ እንዲሰዋ አድርጓል፡፡ በዚህም ድርጊቱ አብርሃም ለፈጣሪ ያለውን ታማኝነት አስመስክሯል፡፡

ይህ የአብርሃምና የልጁ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ (ዘፍ፣22+1-8) እና በቅዱስ ቁርዓን (ሱራ 37+102-105) ሰፍሯል፡፡ በሁለቱ ቅዱስ መጻሕፍት ላይ የቀረበው ታሪክ በይዘት ተቀራራቢ ቢሆንም የጎላ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በቀረበው ታሪክ አብርሃም ሊሰዋ የነበረው ከሳራ የወለደው ልጁን ይሳቅን መሆኑን፣ አብርሃም እስማኤልን የወለደው አገልጋይ ከነበረችው ሐጋር መሆኑን ይገልጻል፡፡

በቅዱስ ቁርዓን በቀረበው ታሪክ "ኢብራሂም ልጁን ሊሰዋ ተዘጋጀ" ይላል እንጂ የትኛውን ልጁን እንደሆነ አይገልጽም። ስለሐጋርም ማንነት አይገልጽም። ኢብራሂምና እስማኤል ካዕባን እንደገነቡ ይገልጻል። ነገር ግን በእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ ኢብራሂም ሊሰዋው የተዘጋጀው እስማኤልን እንደሆነ፣ አብርሃም ሐጋርንና እስማኤልን ከቤት አስወጥቶ ወደ በረሃ እንደሰደዳቸው፣ አላህ በበረሃ ውኃ በማፍለቅ ሐጋርንና እስማኤልን እንዳጠጣ፣ ከአመታት በኋላም ኢብራሂም ልጁን ሊሰዋ መምጣቱን፣ መላኩ ጅብሪል (ገብርኤል) መጥቶ በልጁ ምትክ በግ እንዲሰዋ ትዕዛዝ መንገሩን፣ ኢብራሂም ሁለተኛ ልጁን ይሳቅን ስለመውለዱ፣ ኢብራሂም ድጋሚ ሐጋርና ልጁን ሳያይ ለአመታት እንደቆየና ልጁን ድጋሚ ያየው ሐጋር ከሞተች በኋላ መሆኑ ይታመናል።

የዱል-አል-ሒጃ ወር በገባ በ10ኛው ቀን የሚከበረው በዓል ከኢድ-አል-አድሃ በተጨማሪ የ"መስዋዕት" በዓል በሚል ስያሜም ይታወቃል። 10ኛው ቀን በተለምዶ በአገራችን የ"አረፋ" በዓል ተብሎ ይጠራል። አረፋ በ9ኛው ቀን የሚውል በዓል እንጂ በ10ኛው ቀን የሚከበረው የኢድ-አል-አድሃ በዓል አይደለም። የኢድ-አል-አድሃ በዓልን ምክንያት በማድረግ ከተለያዩ የአገራችን አካባቢዎችና ከሌሎች የዓለም አገራት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በርካታ መንፈሳዊ ተጓዦች ይሄዳሉ። ይህ መንፈሳዊ ጉዞና የሚከበረው በዓልም የ"ሐጅ ሙዳ" ይባላል። የሐጅ የሙዳ በዓልም መከበር የሚጀምረው የዱል-አል-ሒጃ ወር በገባ በ10ኛው ቀን በሚከበረው የኢድ-አል-አድሃ በዓል እለት ነው።

### 2.2.7.2 የዛሕራ ገልገላ ጎበና ምንነትና የአጀማመር ታሪክ

'ዛሕራ ገልገላ ጎበና' በኦሮምኛ የሙሉ ጨረቃ ምሽት የሚል ትርጉም አለው። ይህም በዓሉ መከበር የሚጀምረው ሙሉ ጨረቃ በምትወጣበት ዕለት መሆኑን ለማመልከት ነው። እነዚህ የሙዳ የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓተከበራዎች በጨረቃ የጊዜ ቆጠራ መሰረት ያደረጉ ናቸው። የጨረቃ የጊዜ አቆጣጠርን መሰረት አድርገው የሚከበሩ አመታዊ በዓላት በቋሚ ቀን አይውሉም። የሙዳ በዓላትም ቋሚ ቀን የላቸውም። የሐጅ በዓል በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበር በመሆኑና በመገናኛ ብዙሃን ስለሚገለጽ መቼ እንደሚከበር ይታወቃል። የዛሕራ ገልገላ ጎበና በዓል ግን በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ብቻ የሚከበር ነው። ይህ በመሆኑም በዓሉ የሚከበርበትን ቀን የሚቆጥሩት የጨረቃን የጊዜ አቆጣጠር በትክክል የሚያውቁ የአካባቢው የኃይማኖት አባቶች ናቸው።

የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል የሚውልበት ቀን የራሱ የአቆጣጠር ስልት አለው። ይህም በሂጅራ የጊዜ ቆጠራ በ6ኛው ወር (ጁማዳ አል-አክሂራ) አጋማሽ ላይ ነው። በዓሉም በ6ኛው ወር አጋማሽ በ15ኛው ቀን ላይ ወይም ከ15ኛው ቀን አቅራቢያ ጨረቃ ሙሉ ሆና በምትወጣበት ዕለት የሚከበር ነው። በዓሉ ከጨረቃ ሙሉ መሆን ጋር የተያያዘ በመሆኑ ቋሚ ቀን የለውም። የዛሕራ ገልገላ ኅበና የሚውልበት ወርና ቀን የሼኽ ሁሴን ጨረቃ ወይም ወር ("Ji'a Sheek Huseen") ይባላል።

የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል አጀማመር ላይ የሚነገሩ ሶስት ቃላዊ ታሪኮች አሉ። እነሱም፦ አንደኛው፤ ተማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ መገናኘትን የሚገልጽ ነው። ይኸውም ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት በስፍራው ያስተምሯቸው የነበሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ሀይማኖታዊ ትምህርት ለማስተማር ይሄዱ ነበር። በወቅቱ በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ተሰማርተው የነበሩ የእሳቸው ተማሪዎች አንድ ቀን ቀጠሮ ተይዞ ለመጀመሪያ ጊዜ በቀድሞ ትምህርት ቤታቸው አናጂና እንዲገናኙ ይደረጋል። እነዚህ ተማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙበት ቀን በዛሕራ ገልገላ ኅበና ዕለት ነው። ይህን ታሪካዊ አጋጣሚ መነሻ በማድረግ ዕለቱ መታሰብ ተጀመረ።[21]

ሁለተኛው፣ የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል የሼኽ ሁሴን የልደት ቀንን ለማሰብ የሚከበር መሆኑን የሚገልጽ ነው። እሳቸው የተወለዱት በየካቲት ወር በዛሕራ ገልገላ ኅበና ዕለት እንደሆነ ይታመናል። ይህ ዕለት ነብዩ መሐመድ የተረገዙበት ቀን እንደሆነም ይታመናል። በዓሉም የሚከበረው ሼኽ ሁሴን የተወለዱበትን ዕለት ለማሰብ ነው። ሶስተኛው፣ ከሼኽ ሁሴን ሕልፈት ጋር ተያይዞ የሚነገር ነው። ይኸውም የእሳቸው ሕልፈት በነሐሴ ወር በዛሕራ ገልገላ ኅበና ዕለት እንደሆነ ይታመናል።[22] በዓሉም የእሳቸውን የሕልፈት ዕለት ለማሰብ የሚከበር ነው።

## 2.3 የጥናቱ ንድፈሃሳቦች

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎችን፣ መንፈሳዊ ጉዞዎችንና ክወናው ያለውን ውሕደት ማጥናት ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በጥልቀትና በስፋት ለመተንተን ሶስት ንድፈሃሳቦች ተግባራዊ ተደርገዋል። እነሱም፣ በሙዳ በዓላት ላይ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችንና የሚደረጉ መንፈሳዊ

---

[21] - ሼኽ መሐመድ ሐጂ አብዱልቃድር፣ አናጅና ቀበሌ፣ መስከረም 10 ቀን፣ 2008 ዓ.ም።

[22] - አቶ ኑማን ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7 ቀን 2007 ዓ.ም።

ጉዞዎችን ለመተንተን የክወና ንድፈሃሳብን (Performance Theory) እና ትዕምርታዊ ንድፈሃሳብን (Symbolism) እንዲሁም በክወናዎቹ ውስጥ የሚስተዋሉ ውሕደቶችን ለመተንተን የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብን (Cognitive Theory) ተጠቅሟል።

የክወና ንድፈሃሳብ የፎክሎር ሕይወት የሆነውን ክወና መሰረት ያደረገና ከ1970ዎቹ ወዲህ የተጀመረ የፎክሎር ንድፈሃሳብ ነው። ክወና በሚቀርብበት ወቅት በተለያየ ሁነት እንዲቀርብ የሚያደርጉ ጉዳዮች አሉ። እነዚህን ጉዳዮች ከክወና፣ ከክወና ለውጥ፣ ከከዋኝና ከታዳሚ አንጻር በሚል Bauman and Charles (1990) እና Bauman (1992) ገልጸዋል። የእነዚህን ምሁራን ሀሳብ በአጭሩ ቀጥለን እንመልከት።

ክወና በተለያየ ሁኔታ እንዲከወን ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች አሉ። እነሱም፣ መቼት (Setting)፣ አሀድ (Text)፣ ትረካ፣ መልዕክት፣ ሕግና ማዕቀፍ (Frame) ናቸው። የክወና ለውጦች የሚባሉት በክወናው ወቅት ከአውዱ ውጪ (Decontextualization)፣ ድግመ-አውዳዊ (Recontextualization) እና በአውዱ ውስጥ (Intertextualization) የሚከሰቱ ናቸው። እነዚህ የክወና ለውጦች ያላቸውን ልዩነትና የሚፈጥሩት ፍከራዊ ልዩነቶች የክወናውን ትርጓሜ ያሳያሉ። ክወና ከከዋኞች አንጻር በተለያየ ሁኔታ እንዲከውን ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች አሉ። እነዚህም ውድድር፣ አቅም፣ እውቀት፣ ልምድ፣ ውጤታማነትና ፈጠራ ናቸው። ከታዳሚ አንጻርም በክወናው ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ምክንያቶች አሉ። እነዚህም ተሳትፎ፣ አድናቆት፣ ምላሽ፣ ሜታ ዲስኮርስ (Meta discourse)፣ ሜታ ትረካ (Meta narrative) እና የተግባቦት እንቅስቃሴዎች የሚገለጹበት ሁኔታና ዓላማ ናቸው።

የክወና ንድፈሀሳብም በክወና፣ በክወና ለውጦች፣ በከዋኞችና በታዳሚዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳየት የሚረዳ እንደሆነ Schenchner (2004) ይገልጻል። የክወና ንድፈሀሳብን መሰረት በማድረግ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎች፣ ስርዓተከበራዎቹ ያላቸውን የክወና ቅደም ተከተል፣ በክወናው ላይ ለውጥ የሚፈጥሩ ጉዳዮች፣ የክወናው መልዕክት፣ የክወናው መዋቅር፣ ለክወናው ትዕምርት የሆኑ ጉዳዮች፣ ትዕምርቶቹ ያላቸውን ትርጓሜና የሚፈጥሩትን ተግባቦት፣ ክወናው በታዳሚውና በከዋኙ መካከል ስለሚፈጥረው ተግባቦት፣ በክወናው ወቅት በታዳሚውና በከዋኙ ላይ የሚፈጥረው የስሜት ለውጥና ለለውጡ የሚሰጥ ምላሽ በትንታኔ ለማሳየት ተሞክሯል።

ስርዓተከበራ ትርጉም የሚኖረውና የእርስበርስ ተግባቦት የሚፈጥረው እያንዳንዱ ድርጊትና እንቅስቃሴ ትዕምርት ሲኖረው ነው፡፡ ስርዓተከበራዎች እንደ ትዕምርት እንደሚታዩም Firth (1967፡12) "ስርዓተከበራ እንደ መደበኛና ሂደታዊ የትዕምርቶች ስብስብ የሚወሰድ ሲሆን፣ የማህበራዊ ተግባቦት ምልክት ነው፡፡" በማለት ይበይነዋል፡፡ ትዕምርቶች በከዋኞችና በተመልካቾች መካከል ተግባቦትን የሚፈጥሩት ከዚህ በፊት የነበራቸውን ትርጓሜ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ትርጓሜውም የእኛን ግንዛቤ፣ ስሜት፣ ፍላጎት፣ ዕይታ፣ ትምህርትና ልምድ ያማከለ ነው፡፡ በስርዓተከበራ ላይ የሚቀርቡ ክወናዎች ያላቸው ቅደምተከተል፣ የሚቀርበው ማህበራዊ ድራማ፣ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ቀለም፣ ቁጥር፣ ቅርጽ፣ መጠን፣ ክወናው ሲቀርብ ከዋኞች የሚጠቀሟቸው ልዩ ምልክቶች፣ የክወና ትረካዎች፣ ድግግሞሾች፣ ቦታዎችና ግለሰቦች ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ውክልና አላቸው፡፡

የትዕምርታዊ ንድፈሃሳብም እነዚህን ማህበራዊና ባህላዊ ውክልናዎች ያላቸውን ትርጉም፣ ልዩ ዋጋ፣ ውክልና፣ መልዕክትና የሚፈጥሩትን ስነልቡናዊ ለውጦች የምናጠናበት እንደሆነ Turner (1969)፣ Geertz (1973)፣ Sahlins (1976) እና Bell (1977) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ጥናት ትዕምርታዊ ንድፈሃሳብን መሰረት በማድረግ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ያላቸው የክወና ቅደምተከተል፣ ከዋኞቹ የሚጠቀሟቸው ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ውክልና፣ የሚቀርቡ ክወናዎች የሚፈጥሩት የእርስበርስ ተግባቦትና የሚያሳዩት የኃይል መስተጋብር በትንታኔ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ንድፈሃሳብ ከክወናዎች በተጨማሪ ቦታዎችና ግለሰቦች ያላቸውን ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ምልክት ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ በሰው ልጅ አዕምሮ (Mind) ላይ ትኩረት የሚያደርግ የስነልቡና (Psychology) ንድፈሃሳብ አካል ሲሆን፣ በ1970ዎቹ መተዋወቅ የጀመረ ነው፡፡ ይህ ንድፈሃሳብ በኃይማኖት ጥናት ውስጥ የቅርብ ዘመን ንድፈሃሳቦች ከሚባሉት መካከል አንዱ ሲሆን፣ በኃይማኖት ጥናትም እንደ በይነዲስፕሊናዊ (Interdisciplinary) የጥናት አተያይና እንደ ገላጭ የጥናት አተያይ የሚያገለግል ነው (McCauley, 2010፡780)፡፡ የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ የአስተሳሰብ ሂደቶችን (The thought processes) በመረዳት የሰው ልጅን ባህርይ ወይም ጸባይ የሚተነትን ነው፡፡ የንድፈሃሳቡ ዋና እሳቤ የሰው ልጅ ለስሜቱ በጣም ቅርብ የሆኑ ነገሮችን መምረጥ የሚችል አመክኖዓዊ ኑባሬ (Logical being) ነው ከሚል አመለካከት እንደሆነ Aminorishe (2014፡36) ይገልጻል፡፡

የንድፈሃሳቡ ዋና ትኩረት የሰው ልጅ ኃይማኖታዊ እሳቤዎችን ወይም ቁሶችን በሚመለከት ያለውን የአዕምሮ ውክልናዎች (Mental representations) ተመሳስሎ ላይ፣ የተመሳስሎዎቹ የግንዛቤያዊ ገለጻ ላይ፣ ኃይማኖቶቹ ያላቸውን እምነት፣ ተግባራት እንዲሁም ስርዓታዊ ገጽታዎች ላይ ነው (McCauley, 2010፡782)። በዚህ ንድፈሃሳብ መሰረት ስለኃይማኖት አመጣጥ፣ ምንነትና ከኃይማኖት ጋር የተያያዙ እሳቤዎች ሲፈተሹ ከሰው ልጅ አዕምሮ ጋር በማያያዝ ነው፡፡

ይህ ንድፈሃሳብ የሰው ልጅ ለምን በልዕለሰብዓዊ አካላት ያምናል? ለምን የተወሰኑ ኃይማኖታዊ ስርዓቶችን ከሌላው በተሻለ ይመርጣል? እንዴት የቁሶችን ትዕምርታዊ ትርጓሜ ይወስናል? የተወሰኑ የውሕደት ቅርጾች ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ለምን ይደጋገማሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚረዳ ነው፡፡ ከእነዚህ ጥያቄዎች አንጻር የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ Tremlin (2006፡6) "አምላክ በዋናነት የሚገለጸው እንደ ሰው ልጅ አዕምሯዊ ግንዛቤ እንጂ እንደ ስነመለኮታዊ ወይም እንደ ማህበራዊ ወይም እንደ ባህላዊ እሳቤዎች አይደለም፡፡" የሚል መልስ እንዳለው ይገልጻል፡፡

በንድፈሃሳቡ መሰረት ለእነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የሚገኘው የአዕምሮ ጠቀሜታዊ ስርዓት ነው፡፡ ዋና ማዕከሉም ወደ ሰውነት የሚቀርብና የሚርቅ ጉዳይ ላይ ሲሆን፣ ጉዳዩም በሰው ልጅ ውስጣዊ ዓለም (Inner world) እና በውጪው ዓለም፣ ተጨባጭ ስርዓትና አዕምሯዊ እሳቤ መካከል ባለ መስተጋብርና ትንተና የሚገለጽ ነው፡፡ የዚህ ንድፈሃሳብ ዋና ትኩረት የሰው ልጅን ኃይማኖተኛነት ማሳየት ነው፡፡ የሰው ልጅ ብቻ ነው ኃይማኖታዊ እሳቤዎችን በአዕምሮ የሚይዝና ኃይማኖታዊ እሳቤዎቹን በግሉ ትኩረት የሚሰጣቸው፡፡ በዚህ መሰረትም ፈጣሪና አዕምሮ ይገናኛሉ፡፡ ምክንያቱም ልዕለሰብዓዊ ኑባሬና የኃይማኖት ስርዓት በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ስለሚቀመጡ፣ ስለሚተኩና ስለሚቀያየሩ ነው፡፡

የ20ኛው መቶ ክ/ዘመን የዲቨሎፐመንታል ስነልቡና ምሁር ፒያጌት የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ ሁለት ዓብይ እይታዎች አሉት ይላል (Aminorishe, 2014፡38)። እነሱም፣ አንደኛው ለማወቅ የሚደረግ ሂደት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለማወቅ የሚያስችለንን ችሎታ ለማግኘት የምናልፍበት ደረጃ ነው፡፡ ይህ ጥናት የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብን መሰረት በማድረግ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ያላቸውን ባህርያት፣ በክወናዎቹ ውስጥ የሚታዩ የኃይማኖትና የባህል ውሕደቶችን፣ ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርጉ ግለሰቦች

በሼኽ ሁሴን ላይ ያላቸው እምነትንና እሳቤ እንዲሁም አማኞች በቦታው ላይ ያላቸውን እሳቤ አሳይቷል፡፡

## 2.4 የጥናቱ ሞዴል

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎችንና ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞን መተንነተን ነው፡፡ እነዚህ ስርዓተከበራዎች ያላቸውን ትርጓሜ፣ ትረካ፣ የአከዋወን ስርዓትና ያላቸውን ቅደምተከተል እንዲሁም ያላቸውን አውዳዊ ሁነት ለማሳየት የክወና፣ የትዕምርትና የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳቦችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡

የእነዚህን ንድፈሃሳቦች አተያይና በሙዳ በዓል ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን ለማያያዝ ጥናቱ የክወና ሞዴልን (Performance model) ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይህንን የፎክሎር ሞዴል የፈጠረው Charles Joyner (1975) ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከወነውን የሙዳ ስርዓተከበራ መተንተን ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ተግባራዊ የተደረገውን ሞዴል "የሙዳ ክወና ሞዴል" በሚል መግለጽ ይቻላል፡፡

ከስርዓተከበራ አንጻር የክወና ሞዴልን ተግባራዊ ስናደርግ፣ ስርዓተከበራዎችን ከተለያዩ መሰረታዊ ጉዳዮች አንጻር መመልከት ይኖርብናል (Joyner, 1975)፣ (Bell, 1977) እና (Rappaport, 1999)፡፡ እነዚህም መሰረታዊ ጉዳዮች ስርዓተከበራን ከድርጊት፣ ከቦታ፣ ከጊዜ፣ ከታሪክ፣ ከአውድ፣ ከለውጥ፣ ከከዋኝ፣ ከነባር ባህሎች፣ ከማህበራዊ መዋቅር፣ ከአዕምሯዊ ስዕል (Cognitive map)፣ ከቅርጽ፣ ከሜታ ተግባቦት (Meta communication) እና ከተጽዕኖ (Reflexivity) አንጻር መተንተን አለብን፡፡

ከእነዚህ የምሁራን ሀሳቦች በመነሳት በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ የተደረገውን የሙዳ ክወና ሞዴል ከሼኽ ሁሴን፣ ከመካነ ቅርስ፣ ከማህበራዊ አደረጃጀት፤ ከመንፈሳዊ ጉዞ፣ ከመንፈሳዊ ተጓዥ፣ ከወቅታዊ ሁኔታና ከታሪካዊ ሁኔታ አንጻር ተተንትኗል፡፡ ይህን የሙዳ ክወና ሞዴል መሰረት በማድረግ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን የእርስበርስ ግንኙነት እንደሚከተለው በግራፍ ቀርቧል፡፡




**የሙዳ ክወና ሞዴል ግራፍ መግለጫ፡-**

***ሀ/ ሼኽ ሁሴን፤-*** ሼኽ ሁሴን የድሬ ሼኽ ሁሴንን መካነ ቅርስ የመሰረቱ ናቸው፡፡ ለሙዳ በዓል የሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦች የእሳቸው አፍቃሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ በመካነ ቅርሱ ለሚታመኑ፣ ለሚከወኑና ለሚነገሩ ነገሮች ሁሉ መሰረት ሼኽ ሁሴን ናቸው፡፡ ሼኽ ሁሴን ለመካነ ቅርሱ፣ ለበዓላቱ፣ ለመንፈሳዊ ጉዞውና ለኃይማኖታዊ አስተሳሰቡ ዋና መሰረትና ማዕከል ናቸው፡፡

***ለ/ መካነ ቅርስ፤-*** የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሼኽ ሁሴን አማካኝነት የኃይማኖት ማዕከል የሆነ ስፍራ ነው፡፡ ስፍራው ለበርካታ አመታት ያህል የተለያዩ ኃይማኖታዊ ስርዓተከበራዎች ሲከወኑበት የቆየ ነው፤ አሁንም እየተከወነበት ይገኛል፡፡ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎችም ስፍራውን በልዩ እሳቤ የሚያዩትና ልዩ መንፈሳዊ ኃይል አለው ብለው ያምናሉ፡፡ የሙዳ በዓላትም በስፍራው በዓመት ሁለት ጊዜ ይከበራሉ፡፡

**ሐ/ ማህበራዊ አደረጃጀት**፤- በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚኖሩ ማህበረሰቦች የተለያዩ ማህበራዊ ደረጃ አላቸው። ይህ ማህበራዊ ደረጃቸውም በመካነ ቅርሱ ታሪክ፣ ከግለሰቦች ሚና፣ ከግለሰቦች የዘርሃረግ፣ ካላቸው ልዩ ችሎታና ባህርይ ጋር የተያያዘ ነው። በማህበራዊ ደረጃ መዋቅር መሰረት በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን በመምራት፣ በመከወን እንዲሁም መካነ ቅርሱ ካለው ታሪካዊ ዳራ ጋር በተያያዘ የግለሰቦች ሚና ይወሰናል።

**መ/ መንፈሳዊ ጉዞ**፤- በሙዳ በዓላት ወቅት እስከ አምስት መቶ ሺሕ የሚገመት ሕዝብ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋል። ይህ መንፈሳዊ ጉዞም የተለያዩ ባህርያት አሉት። እነዚህ ባህርያትም በሙዳ በዓላት የአከዋወን ስርዓት ላይ የተለያዩ ለውጦችን ፈጥረዋል። መንፈሳዊ ጉዞውም ለሙዳ በዓላት ሕልውና ዋና መሰረት ነው።

**ሠ/ መንፈሳዊ ተጓዥ**፤- ለሙዳ በዓላት እስከ አምስት መቶ ሺሕ መንፈሳዊ ተጓዥ ወደ መካነ ቅርሱ ጉዞ ያደርጋል። መንፈሳዊ ተጓዡም የተለያዩ አነሳሽ ምክንያቶችን መሰረት በማድግ ወደ መካነ ቅርሱ ይሄዳል። የመንፈሳዊ ተጓዥ አነሳሽ ምክንያቶችም በሙዳ በዓላት ላይ የተለያዩ ለውጦች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል። መንፈሳዊ ተጓዥም ለመካነ ቅርሱ፣ ለበዓላቱና ለመንፈሳዊ ጉዞው ሕልውና ዋና መሰረት ነው።

**ረ/ "መሰረታዊ ግንኙነት"**፤- በዚህ የክወና ሞዴል መሰረታዊ ግንኙነት ተብለው የተገለጹት አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ተፈጥሯዊ ግንኙነት ነው። ግንኙነቱም የአንዱ መኖር ለሌላው የመኖር መሰረት ወይም የአንዱ መጉደል ለሌላው መጥፋት ምክንያት የሚሆኑትን ነው። በዚህ እሳቤ መሰረት ሼኽ ሁሴን፣ መካነ ቅርስ፣ ማህበራዊ አደረጃጀት፣ መንፈሳዊ ጉዞና መንፈሳዊ ተጓዥ ያላቸውን መሰረታዊ የእርስበርስ ግንኙነት ነው። ይህ የእርስበርስ ግንኙነትም ለሁሉም መኖር ዋና የሕልውና መሰረት ነው። ለዚህ ሁሉ መሰረታዊ ግንኙነት ዋና ማዕከሉ ሼኽ ሁሴን ናቸው።

**ሰ/ "ምክንያታዊ ግንኙነት"**፤- በዚህ የክወና ሞዴል ምክንያታዊ ግንኙነት ተብለው የተገለጹት አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ወቅታዊ ግንኙነት ነው። ግንኙነቱም የአንድ ነገር በሆነ ወቅት ላይ መከሰት በሌላው ላይ ወቅታዊ ወይም ዘለቄታዊ ለውጥ የሚፈጥር ነው። በዚህ እሳቤ መሰረት ታሪካዊ ሁኔታዎችና ወቅታዊ ሁኔታዎች በመካነ ቅርሱ፣ በሙዳ በዓላት፣ በመንፈሳዊ ጉዞና

በመንፈሳዊ ተጓዥ ላይ የፈጠሩትን ለውጦችና ያላቸውን የእርስበርስ ግንኙነት የሚያመለክት ነው፡፡

**ሸ/ ሙዳ፤-** በዚህ የክወና ሞዴል ዋናው ማዕከል ሙዳ ነው፡፡ ሙዳ በዓመት ሁለት ጊዜ በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከበር በዓል ነው፡፡ ሙዳ የሁሉም ማዕከል የሆኑትን ሼኽ ሁሴንን በዋና መሰረት በመያዝ፣ በመካነ ቅርሱ፣ በማህበራዊ አደረጃጀቱ፣ በመንፈሳዊ ጉዞውና በመንፈሳዊ ተጓዡ መካከል ያለን የእርስበርስ ግንኙነት የሚመሰርት፣ የሚወስንና የሚመራ ነው፡፡ ሙዳ የእነዚህ ሁሉ አገናኝ ነው፡፡ ሁሉም ጉዳዮች ከሙዳ ጋር፤ ሙዳም ከሁሉም ጉዳዮች ጋር የቀጥታ ግንኙነት አለው፡፡

# 3. የጥናቱ ስነዘዴ

ይህ ምዕራፍ ሁለት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ አንደኛው፣ የአጠናን ስነዘዴ ሲሆን፣ በዚህ ክፍል የጥናቱ አይነት፣ የመረጃ አይነቶች፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ፣ የመረጃ ማያ ስልት እንዲሁም የመረጃ መፈከሪያ ስልት ይቀርባል፡፡ ሁለተኛው፣ ደግሞ የጥናቱ ስነ-ምግባር ነው፡፡

## 3.1 የጥናቱ አይነት

ይህ ጥናት ይዘታዊ ምርምር (Qualitative research) የጥናት አይነትን የተከተለ ነው፡፡ በይዘታዊ የምርምር አይነት ለጥናቱ የሚሆኑ ንድፈሀሳባዊ፣ ኢፒስቲሞሎጂያዊ፣ ስነዘዴያዊ ስልቶችና የሚጠኑ ርዕሰጉዳዮች በጣም ሰፊ ናቸው፡፡ በመሆኑም ስለይዘታዊ የምርምር አይነት ወጥ የሆነ ብያኔና ገጽታ አናገኝም፡፡ ስለይዘታዊ የምርምር አይነት ወጥ የሆነ ብያኔና ገጽታ ማግኘት ባይቻልም እንዴት ምርምሩ እንደሚካሄድ የሚያሳዩ የተወሰኑ የጋራ ገጽታ እንዳሉት Kothari (2004) ይገልጻል፡፡ እነሱም፡- ለጥናቱ ትክክለኛ የጥናት ዘዴዎችንና ንድፈሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ይጠናል፣ የሚጠኑ ጉዳዮችን በጥልቀት ለመረዳት ከአውድና ከውስን ማሳያዎች (Context and Cases) ይነሳል፣ መረጃዎችን ከመስክ በመሰብሰብ ውስብስብ የሆነውን ማህበራዊ ሁኔታ ያሳያል፣ ለጥናት በሚያመች መልኩ ውስን በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ መረጃዎችን ማግኘት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይጠቀማል፡፡

ይህ ጥናት ይዘታዊ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩትን የሙዳ በዓላት ቅድመ ዝግጅት፣ በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን፣ በሼኽ ሁሴን ማንነትና ሰብዕና ላይ የሚነገሩ ታሪኮችና ሚቶችን፣ በበዓላቱ ላይ ተጽዕኖ የፈጠሩ ሁነቶችንና ወደ ስፍራው የሚካሄዱ ጉዞዎችን በቅደም ተከተል ይገልጻል፡፡ በበዓላቱ ወቅት የሚቀርቡ ክወናዎች ያላቸውን አውዳዊ ትርጉም፣ በበዓላቱ ወቅት የሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ያላቸውን ባህርይ፣ በበዓሉ ላይ የሚስተዋሉ ለውጦች እንዲሁም በቀጣይ ህልውናው ላይ ተግዳሮት የሚፈጠሩ ሁነቶችን ከመስክ በተገኙ መረጃዎች በጥልቀት ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 3.2 የመረጃ አይነቶች

የመረጃ አይነቶች በሁለት ይከፈላሉ (Kothari, 2004:97)፡፡ እነሱም:- ቀዳማይ መረጃ (Primary data) እና ካልዓይ መረጃ (Secondary) ናቸው፡፡ ቀዳማይ መረጃዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የምናገኛቸው፣ ትኩስና የአዲስነት ባህርይ ያላቸው ሲሆኑ፣ ካልዓይ መረጃዎች ደግሞ ከዚህ በፊት በሌሎች አጥኚዎች የተሰበሰቡና ተደራጅተው ወይም ተተንትነው የሚገኙ ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የተጠና ነው፡፡ የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩትን የሙዳ በዓላት ላይ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች፣ ስርዓተከበራዎቹ ያላቸውን ውሕደትና ወደ ስፍራው የሚደረግ ጉዞን ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎች አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

ቀዳማይ መረጃዎች የሚገኙት ደግሞ በዓላቱ ሲከወኑ በማየትና ከቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች የሚገኙ መረጃዎችን በመሰብሰብ ነው፡፡ በቀዳማይ መረጃዎችም የተገኙ መረጃዎች የሙዳ በዓላት አከባበር ሂደቶች፣ የአከዋወን ስርዓቶች፣ የበዓሉ ተሳታፊዎች ስሜትና የግል ገጠመኝ ናቸው፡፡ በካልዓይ መረጃዎች ደግሞ በስርዓተከበራ፣ በሙዳ በዓል፣ በውሕደት፣ በመንፈሳዊ ጉዞ፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች በተመሳሳይ ርዕሰጉዳይ ላይ ከተጻፉ መጻሕፍት፣ ሰነዶች፣ የመመረቂያ ጽሑፎች፣ የምርምር መጣጥፎች፣ የኢንቬንተሪ ሪፖርቶችና ከሌሎች የታተሙና ያልታተሙ ጽሑፎች የሚገኙ ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም እነዚህን የመረጃ ምንጮች በግብዐትነት በመጠቀም የተሰራ ነው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች ቀዳማይና ካልዓይ እንደሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮችን የምናገኘው ከመስክ ስራ (Field work) ነው፡፡ በመስክ ስራ ወቅት መረጃዎችን የምንሰበስብባቸው ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ለፎክሎር ጥናት የሚያገለግሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታና ቃለመጠይቅ እንደሆኑ Goldstein (1964:77) ይገልጻል፡፡ ይህ ጥናት ከምልከታና ከቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተጨማሪ የንጥል ማሳያ ጥናት (Case study) እና የተተኳሪ ቡድን (Focus group) ውይይት ተጠቅሟል፡ ስለመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምንነትና በዚህ ጥናት እንዴት ተግባራዊ እንደተደረጉ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 3.3.1 ምልከታ

ምልከታ አጥኚዎች በመስክ በመገኘት በቀጥታ መረጃ የሚሰበስቡበት ዘዴ ነው፡፡ ከመስክ የሚገኙ መረጃዎችንም በማየት፣ በመስማት፣ በመዳሰስ፣ በማሽተትና በስሜት የሚቀርቡበትን አውድ መሰረት በማድረግ የምንሰበስብበት ዘዴ መሆኑን Goldstein (1974:77) እና Spsford and Jupp (2006:57) ይገልጻሉ፡፡ ምልከታ በመስክ ያሉ መረጃዎችን በአይታ ከማግኘት በተጨማሪ በዙሪያችን ያለውን ተጨባጭ አካባቢ እንድንረዳ፣ በአዕምሯችን ውስጥ የነበረውን ቀደምት አዕምሯዊ ስዕል ከነባራዊው ዓለም ጋር በማገናዘብ ትክክለኛና ተጨባጭ ስዕል እንዲኖረን ይረዳል፡፡ ምልከታ የምናካሂድባቸው አውዶች በተለያዩ መንገዶች ሊገኙ ይችላሉ፡፡

እነዚህን አውዶች Goldstein (1974:81-82) ተፈጥሯዊና አርቲፊሻል በሚል በሁለት ሲመድባቸው፤ ፈቃደ (1991 ዓ.ም፡122-124) ደግሞ በእነዚህ ሁለት ምደባዎች ላይ ቅንብር ተፈጥሯዊ (Induced natural) የሚል አውድ በመጨመር በሶስት ይከፍላቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ምልከታ የሚካሄደው የሙዳ በዓላት በሚከበሩበት ቦታና ቀናት በመገኘት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የተካሄደበት የምልከታ አውድ ተፈጥሯዊ ነው፡፡

Kothari (2004:96) ምልከታ የተደራጀ (Structured) እና ያልተደራጀ (Unstructured) በሚሉ ሁለት አይነት ስልቶች እንደሚመደብ ይገልጻል፡፡ የተደራጀ ምልከታ ለገለጻዊ ጥናቶች (Descriptive studies) የመረጃ መሰብሰቢያነት ሲያገለግል፣ ያልተደራጀ ምልከታ ደግሞ ለምርምራዊ (Explanatory) ጥናቶች ያገለግላል፡፡ የዚህ ጥናት አይነት ገለጻዊ በመሆኑ የተደራጀ ምልከታን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ የተደራጀ ምልከታ በሶስት መንገድ እንደሚካሄድ Kothari (2004:96) ይገልጻል፡፡ እነሱም፡- አጥኚው በመስክ ላይ የሚከወኑ ድርጊቶችን ከከዋኞቹ ጋር በመሆን ድርጊቶቹን እየተገበረ ምልከታ የሚያደረግበት ተሳታፊ ምልከታ (Participant)፣ አጥኚው ከዋኞቹ የሚከውኗቸውን ድርጊቶች ሳይከውን ምልከታ ብቻ የሚያደርግበት (Non-participant) እና ከዋኞቹ ድርጊቶችን በሚከውኑበት ወቅት አጥኚው በስፍራው ስለመኖሩ ፍንጭ ሳይሰጥና ከዋኞቹም ሳያውቁ በድብቅ ምልከታ የሚያደርግበት ናቸው፡፡

ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ ቀዳማይ መረጃዎች ሶስቱንም የምልከታ ስልቶች ተግባራዊ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በምልከታ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል የሙዳ ስርዓተከበራ ክወናዎች ያላቸውን ቅደም ተከተል፣ የስርዓቱ መሪዎች የሚከውኗቸው ድርጊቶች፣ ታዳሚዎች የሚከውኗቸው ድርጊቶች፣ የበዓሉ ታዳሚዎች በስርዓቱ ወቅት ያላቸው የስሜት ለውጥና

የሰውነት እንቅስቃሴ፣ በስርዓቱ ወቅት የሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች፣ ክወናዎቹ በአቅራቢዎቹና በታዳሚዎቹ ላይ የሚፈጥሩት የስሜት ለውጥ፣ በስርዓቱ ወቅት ምርቃትና እርግማን ሲያካሂዱ የሚያደርጉት እንቅስቃሴዎች፣ በበዓሉ ወቅት የሚጠቀሟቸው ቁሳዊ ባህሎችና መሰል ጉዳዮች ናቸው፡፡

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ በመስክ የቆየሁባቸው በአጠቃላይ 41 ቀናት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ቀናት መካከል በዓላቱ በሚከበሩበት ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አናጂና ቀበሌ በ5 ዙር ምልልስ ለ31 ቀናት ቆይቻለሁ፡፡ በመካነ ቅርሱ የቆየሁባቸው የመስክ ቀናትም አንደኛ ዙር፤ ከጥቅምት 28 እስከ ህዳር 2 ቀን 2007 ዓ.ም፣ ሁለተኛ ዙር፤ ከሚያዝያ 6 እስከ ሚያዝያ 11 ቀን 2007 ዓ.ም፣ ሶስተኛ ዙር፤ ከመስከረም 8 እስከ መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም፣ አራተኛ ዙር፤ ከመጋቢት 25 እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 2008 ዓ.ም እንዲሁም አምስተኛ ዙር፤ ከነሐሴ 25 እስከ ጳቅሜ 1 ቀን 2009 ዓ.ም ናቸው፡፡ በምልከታ የተገኙ መረጃዎችም በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በመቅረጸ-ድምጽና በማስታወሻ ደብተር ተሰንደዋል፡፡

### 3.3.2 ቃለመጠይቅ

ቃለመጠይቅ መረጃ ሰብሳቢውና መረጃ ሰጪው በፊትለፊት ወይም በስልክ በመገናኘት በቃል ወይም በድምጽ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ቃለመጠይቅ የተደራጀ (Structured) እና ያልተደራጀ (Unstructured) በሚሉ ሁለት አይነት ስልቶች እንደሚመደብ Kothari (2004:98) ይገልጻል፡፡ የተደራጀ ቃለመጠይቅ መረጃ ሰብሳቢው ቀደም ሲል የተዘጋጀባቸውን ጥያቄዎች ብቻ የሚጠይቅበት ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት ቀኖናዊ፣ ቅደምተከተላዊ፣ እንደሁኔታዎች የማይለወጥ፣ በጣም ቴክኒካል የሆነና ግትር ነው፡፡

ያልተደራጀ ቃለመጠይቅ ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው ቀደም ሲል የተዘጋጀባቸውን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ከመረጃ ሰጪው ሀሳብ ተነስቶ ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን የሚያነሳበት ነው፡፡ ይህ የቃለመጠይቅ ስልት ነጻነት ሰጪ፣ ጥልቅ መረጃዎችን የሚያስገኝ፣ እንደሁኔታዎች የሚለዋወጥና ሁኔታው የማይፈቅድ ከሆነ አጥኚው አንዳንድ ጥያቄዎችን የሚተውበት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ያልተደራጀ የቃለመጠይቅ ስልትን መሰረት በማድረግ ከመረጃ ሰጪዎች መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በቃለመጠይቅ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል የሼኽ ሁሴንና የተከታዮቻቸውን ታሪክ፣ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ኪነህንጻዎች ታሪክ፣ የሙዳ በዓላት መቼና እንዴት ሊጀመሩ እንደቻሉ፣ በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ድርጊቶች ያላቸው ትርጓሜ፣ በበዓሉ ላይ በጊዜ ሂደት የተቀየሩ ነገሮች፣ የስርዓቱ አስፈጻሚዎች አመራረጥ ሂደትና መሰል ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመስክ የተካሄደው ቃለመጠይቅ በመረጃ ሰጪዎች የናሙና (Sampling) ዘዴዎች የተወሰነ ነው፡፡

በጥናቱ ላይ የተሳተፉ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ብዛት 41 ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎችም ከጾታ አንጻር 9 ሴቶችና 32 ወንዶች ናቸው፡፡ መረጃ ሰጪዎችም ከ28 እስከ 73 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ መረጃ ሰጪዎች የተመረጡበት ዋና ዋና መስፈርቶች ያላቸው የዕድሜ ደረጃ፣ የዕውቀት ደረጃ፣ ለስፍራው ባላቸው ቅርበት፣ በተደጋጋሚ ወደ ስፍራው መምጣት፣ ባላቸው ማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም የስራ ኃላፊነት ናቸው፡፡

### 3.3.3 የንጥል ማሳያ ጥናት

የንጥል ማሳያ ጥናት አንድ የጥናት የምርምር ስልት ሲሆን፣ በነጠላ ወይም አነስተኛ ቁጥር ባለው ተፈጥሯዊ መቼት አማካኝነት ማህበራዊ ሁነቶችን በጥልቀት የምንረዳበት እንደሆነ Bloor and Wood (2006:27) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ዘዴም ጥቂት ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን፣ ድርጊቶችን፣ የክወና አንጓዎችን (Episodes)፣ ሁነቶችን፣ ክወናዎችንና ማህበራዊ መዋቅሮችን መሰረት በማድረግ በተወሰነ ርዕሰጉዳይ ላይ ጥልቅ መረጃ እንድናገኝ፣ ውስን መረጃዎች ያላቸውን ልዩነቶችና ተመሳስሎ እንዲሁም ያላቸውን ሕብርና አጠቃላይነት (Unity and Wholeness) በጥልቀትና በስፋት እንድንረዳ ይጠቅማል፡፡

ይህ ጥናት የንጥል ማሳያ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን መሰረት በማድረግ የሙዳ በዓልን የሚያከብሩ ሰዎች ለምን እንደሚያከብሩ፣ የግለሰቦች ልዩ የህይወት ገጠመኞች፣ እንዴት በዓሉን ማክበር እንደጀመሩ፣ በበዓሉ ላይ ያስተዋሉት ለውጥ፣ መንፈሳዊ ቦታው የግል ችግራቸውን እንዴት እንደፈታላቸው ወይም ምን አይነት ችግር ደርሶባቸው ከዛ ችግራቸው እንዴት እንወጣለን የሚል እምነት እንዳላቸውና በሼኽ ሁሴንና በመካነ ቅርሱ ላይ ያላቸውን እሳቤና መሰል ጉዳዮች አይቷል፡፡ በዚህ ዘዴ የተገኙ መረጃዎችንም ጥናቱ በማሳያ በመግለጽ ለማብራራት ጥረት አድርጓል፡፡

በዚህ ዘዴም የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች ብዛት 11 ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ 6ቱ ሴቶች ናቸው። በንጥል ማሳያ ጥናት ዘዴ ከግለሰቦች በተጨማሪ ውስን የሆኑ ስርዓቶችንና ቦታዎችን ብቻ በማየት መተንተን ያስችላል። በመሆኑም በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ውስን ስርዓቶችንና ልዩ መንፈሳዊ ዋጋ ያላቸው ቦታዎችን ብቻ በተናጠል መርጦ በመውሰድ ያላቸውን ልዩ ባህርይ ለመተንተን ጥረት ተደርጓል።

### 3.3.4 የተተኳሪ ቡድን ውይይት

ጥናት በሚከናወንበት ወቅት ግለሰቦችን በተናጠል ቃለመጠይቅ ከማድረግ በተጨማሪ የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማድረግ መረጃዎች ይሰበሰባሉ። የተተኳሪ ቡድን ውይይት በሶስት መንገዶች ሊደራጅ እንደሚችል Payne and Payne (2004:103) ያብራራሉ። እነሱም፡- በርካታ ሰዎችን በአንድ ላይ በመሰብሰብ የሚካሄድ ሕዝባዊ ውይይት፣ ቁጥራቸው ከ8 እስከ 10 የሆኑና የተለያዩ ሰዎችን በማሰባጠር በአንድ ላይ በመሰብሰብ ማወያየት እንዲሁም ውስን ቁጥር ያላቸው መረጃ አቀባዮችን ብቻ በመሰብሰብ ማወያየት ናቸው።

ይህ ጥናት ከእነዚህ ሶስት የተተኳሪ ቡድን የውይይት መንገዶች መካከል ሁለቱን ተጠቅሟል። እነሱም፡- ውስን ቁጥር ያላቸው የሀይማኖቱ መሪዎች፣ የመንፈሳዊ ሙዚቃ ባለሙያዎች (ኡሌዎች)፣ የበዓሉ ተሳታፊዎችንና ሌሎችን በማሰባጠር እንዲሁም ውስን ቁጥር ያላቸውን መረጃ አቀባዮች ብቻ በአንድ ላይ በመሰብሰብ ማወያየት ናቸው። በእነዚህ የውይይት መንገዶች መሰረት የተወሰኑ አከራካሪ ጉዳዮችን ወይም ርዕሶችን በመምረጥ እንዲወያዩ በማድረግ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል። በተናጠልና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የሚገኙ መረጃዎችም በመቅረጸ-ድምጽና በማስታወሻ ደብተር ተሰንደዋል።

ውስን ቁጥር ያላቸው የመረጃ ሰጪዎችን በማሰባሰብ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ያካሄድኩት 2 ጊዜ ነው። የቡድን ውይይት ያደረኩበት ቀናትም መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም እና መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ.ም ናቸው። በመጀመሪያው የቡድን ውይይት ተሳታፊ የነበሩት 6 መረጃ ሰጪዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህም ውስጥ ሴቶች 2 ናቸው። በሁለተኛው፣ የቡድን ውይይት ተሳታፊ የነበሩት 8 ሲሆኑ፣ ከእነዚህም ውስጥ ሴቶች 3 ናቸው።

## 3.4 የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ

ለፎክሎር ጥናት፣ በመስክ ስራ ወቅት ከመረጃ ሰጪዎች የሚገኙ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው፡፡ ፎክሎር የሰው ልጅ የእለትተእለት ድርጊት በመሆኑ ስለፎክሎር መረጃ በምንሰበስብበት ወቅት ማንኛውም ሰው መረጃ ሰጪ ሊሆን ይችላል (Jackson, 1987:42)፡፡ ፎክሎር የእለትተእለት ድርጊት በመሆኑ ማንኛውም ሰው መረጃ መስጠት ይችላል ሲባል፣ ሁሉም ሰው ስለጉዳዩ እኩል እውቀት አለው ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም ካሉት ሰዎች መካከል በርዕሰጉዳዩ ላይ የተሻለ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉትን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ የመረጃ ሰጪዎች ማንነት ደግሞ የመረጃውን ተአማኒነት፣ ጥልቅነትና አስተማማኝነት የሚያሳይ በመሆኑ መረጃ ሰጪዎችን በጥንቃቄ መምረጥ ይኖርብናል፡፡

ተመራማሪዎች ሁለት አይነት የናሙና አመራረጥ አይነቶች በመጠቀም መረጃ ሰጪዎችን መለየት እንደሚችሉ ያለው (2004 ዓ.ም፡120) ይገልጻል፡፡ እነሱም እድል ሰጪ (Random or Probability sampling) እና ወሳኝ (Nonprobablity) ናቸው፡፡ ይህ ጥናት በተካሄደበት ወቅት መረጃ ሰጪዎች የተመረጡት በወሳኝ ናሙና ዘዴ ነው፡፡ ይህ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመራማሪው የራሱን ልምድ፣ እውቀትና ግምገማ ወይም የሌሎች መረጃ ሰጪዎችን ጥቆማ መሰረት በማድረግ የሚፈልገውን መረጃ ይሰጡኛል የሚላቸውን አካላት እንዲመርጥ የሚያስችል ነው፡፡ ወሳኝ ናሙና በርካታ ዘዴዎችን የያዘ ነው፡፡

ከእነዚህ በርካታ የወሳኝ ናሙና ዘዴዎች መካከል ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃ ሰጪዎች በሶስት ዘዴዎች ተመርጠዋል፡፡ አንደኛው፡- ለመረጃው የተሻለ ቀረቤታ ያላቸው ባለሙያዎች የተመረጡበት የናሙና ዘዴ (Handpicked) ነው፡፡ ይህ የናሙና ዘዴ በጣም ውስን፣ ሳቢ፣ ጠቃሚና ወሳኝ የሆነ ጉዳይን በአዕምሯችን ይዘን ስለዛ ጉዳይ መረጃ ለማግኘት ይረዳሉ የምንላቸውን ጥቂት ባለሙያዎች ብቻ የምንመርጥበት መሆኑን O’Leary (2004:110) ይገልጻል፡፡

በዚህም መስፈርት የሙዳ በዓልን ከሚያስፈጽሙ የሀይማኖት አባቶች፣ ስርዓቱ ሲከወን በተደጋጋሚ ካዩ፣ በዓሉን ለረጅም አመታት ካከበሩ፣ በስርዓቱና በመካነ ቅርሱ ዙሪያ ጥናት ካደረጉ ምሁራን፣ ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች (ደርጋዎች)፣ ከመንፈሳዊ ሙዚቃ ባለሙያዎች (ኡሌዎች)፣ ከመካነ ቅርሱ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ሰራተኞችና ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች መካከል የተሻለ እውቀት አላቸው የሚባሉትን ጥቂት ባለሙያዎች

ከእያንዳንዱ ዘርፍ በመምረጥ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህ ዘዴ የተመረጡ መረጃ ሰጪዎችም የድሬ ሼኽ ሁሴን ታሪክ፣ የሙዳ በዓል አጀማመር ታሪክ፣ በስፍራው እንዴት የተለያየ ሀይማኖት ያላቸው ሰዎች ሊመጡበት እንደቻሉ፣ በስርዓተከበራው ላይ እንዴት ውሕደት ሊከሰት እንደቻለና ሌሎች ጥያቄዎችን በመጠየቅ በጣም ሳቢና አመራማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡

ሁለተኛው፡- የጠቋሚ ናሙና ዘዴ (Snowball) ነው፡፡ ይህ ዘዴ መረጃ ሰጪዎች ለአጥኚው በሚሰጡት ጥቆማ መሰረት መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ግለሰቦች የሚመረጡበት መሆኑን O'Leary (2004:110) ይገልጻል፡፡ የጠቋሚ ናሙና ዘዴንም በመጠቀም በውስን ርዕሰጉዳዮች ላይ የተሻለ ዕውቀት አላቸው የሚባሉ ግለሰቦችን በሌሎች ግለሰቦች ጥቆማ መሰረት በመለየት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህ ዘዴም በተለያዩ የእድሜ ደረጃ ያላቸው ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም የተለያየ የሀይማኖት ዳራ ያላቸውና መረጃ ለመስጠት ፍላጎት ያላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ከተለያየ አካባቢ ወደ ስፍራው የሚመጡና የተለያየ ብሔር ተወላጅ ከሆኑ ግለሰቦች መረጃ ተሰብስቧል፡፡

ሶስተኛው፡- ንጥል ናሙና ዘዴ (Case-type) ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተመራማሪውን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የአንድ ሰውን፣ ቡድንን ወይም ማህበረሰብን ባህርይ በጥልቅና በስፋት ለማጥናት የሚያስችል ነው (ያለው፣2004 ዓ.ም፡134)፡፡ በዚህ ዘዴም በዓሉን ለማክበር ከሚመጡ ግለሰቦች፣ በዓሉን በበላይነት ከሚመሩ የሀይማኖት አባቶችና ከነዋሪዎች ጥቂት ግለሰቦችን በመምረጥ የህይወት ገጠመኛቸውን፣ በበዓሉ ላይ ተግዳሮት የፈጠሩ ሁነቶችንና ባስተዋሉት ለውጥ ላይ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህ የንጥል ናሙና ዘዴም በመጠቀም 11 መረጃ ሰጪዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ እነዚህ ሶስት የናሙና ዘዴዎች ስለሙዳ ስርዓተከበራ ክወናዎች ጥልቅ መረጃዎችን ለማግኘት አስችለዋል፡፡ በናሙና ዘዴዎቹም አማካኝነት የተለያየ የእውቀት ደረጃ፣ የእድሜ ደረጃ፣ ጾታ፣ አካባቢያዊና ሀይማኖታዊ ዳራ ያላቸው ግለሰቦች በመረጃ ሰጪነት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 3.5 የመረጃ ማያ ስልት

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሁለት የማያ (Perspective) ስልቶች ታይተዋል፡፡ እነሱም፡- ውስጣዊ (Emic) እና ውጫዊ (Etic) ናቸው፡፡ ውስጣዊ የማያ ስልት እውነታን በውስጥ አወቅ መንገድ ለመረዳት የሚያስችል ነው፡፡ ስልቱም ሰዎች በዙሪያቸው ያለውን ዓለም በራሳቸው መንገድ እንዴት እንደሚረዱ፣ ግለሰቦች ያላቸውን ሀሳብና ሁኔታ እንዴት ቅርጽ

እንደሚያሲዙ፣ ሰዎች ምን እንደሚያስቡ፣ የሚከውኑትን ነገር ለምንና እንዴት እንደሚከውኑና ባለው ማህበራዊ ሁኔታ እንዴት ባህርያቸው እንደተቀረጸ ከመረጃ ሰጪዎች የምናገኛቸውን መረጃዎች የምናይበት ነው (Given, 2008:249)።

ውጫዊ የማያ ስልት ደግሞ እውነታን ከውጪ ለመረዳት የሚያስችል ነው፡፡ ስልቱም ሳይንሳዊ የተጠይቅ ትንተናን መሰረት በማድረግ እውነታን ካለው ባህላዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች የምንረዳበት እንደሆነ Given (2008:249) ይገልጻል፡፡ በዚህ ጥናት ከመረጃ ሰጪዎች አስተሳሰብና ዓለምን ከሚረዱበት ከራሳቸው እይታ በመነሳት፤ ከውስጣዊ እይታ ወደ ውጫዊ የማያ ስልት መረጃዎችን ለመረዳት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 3.6 የመረጃ መፈከሪያ ስልት

ይህ ጥናት ይዘታዊ በመሆኑ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በንጥል ማሳያ ጥናትና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች ያላቸውን ትርጉም በፍከራ (Interpretation) ለማሳየት ጥናቱ ክወና ተኮር ስልትን (Performance-Centered Approach) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ስልት ባህላዊ እሳቤዎችን፣ ትዕምርቶችንና ውክልናዊ ትርጓሜዎችን (Metaphoric meanings) ማህበረሰቡ በራሱ ኮግኒቲቫዊ ግንዛቤ (Cognitively) እንዴት እንደሚረዳ የሚያሳይ ነው፡፡

ክወና ሁለት ጉዳዮችን ይይዛል (Bauman, 1975:290)። አንደኛው፡- ጥበባዊ ድርጊት (Artistic action) ሲሆን፣ ይህም ፎክሎሮች የሚተገበሩበትን መንገድ፣ ድርጊትና ሂደት ይገልጻል፡፡ ሁለተኛው፡- ጥበባዊ ሁነት (Artistic event) ሲሆን፣ ይህም የክወናውን ሁኔታ፣ የከዋኙን፣ የታዳሚውን፣ የአውዱን ሁኔታዎችና ጥበባዊ ቅርጹን ያካትታል፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች የክወና ተኮር ስልትን በፎክሎር ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ዋና ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት የክወና ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርገው የክወና ተኮር ስልት የፎክሎር ክወናዎችን፣ ፎክሎሮቹን በሚከውናቸው ቡድን ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ባህላዊ ጉዳዮችን፣ ትዕምርቶችንና ውክልናዎችን እንዲሁም የአውዱን፣ የከዋኙንና የታዳሚውን አጠቃላይ ሁነቶች ለመፈከር የሚረዳ ነው፡፡

በስርዓተከበራ ክወና ወቅት ሁለት አብይ መልዕክቶች እንደሚተላለፉ Rappaport (1992:250) ይገልጻል፡፡ አንደኛ፡- በስርዓተከበራው ቅደምተከተል መሰረት የማይቀያየር መልዕክት ነው፡፡

ይህም ማህበራዊና ስነ-ፈለጋዊ ስርዓትን (Social and Cosmological order) ያሳያል፡፡ ሁለተኛው፡- በስርዓተከበራው ወቅት በሚከሰቱ አዳዲስ ነገሮች ሳቢያ የሚከወኑ ነገሮች የሚይዙትና የሚቀያየር መልዕክትን ያሳያል፡፡ የክወና ተኮር የመፈከሪያ ስልትም በሙዳ በዓላት ወቅት ክወናው ያለውን ቋሚና የሚቀያየር መልዕክት እንዲሁም የክወናውን ጥበባዊ ድርጊትና ጥበባዊ ሁነት ለመረዳት ያስችላል፡፡ በዚህ ጥናት የክወና ተኮር ስልትን መሰረት በማድረግ የክወና አላባውያንን (Elements)፣ የክወናው ትረካን (Narrative) እንዲሁም የክወናውን ትርጓሜ በፍካሬ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 3.7 የጥናቱ ስነ-ምግባር

ይህ ጥናት በተካሄደበት ወቅት መጠበቅ የሚገባኝን ስነምግባራዊ ጉዳዮች በመረዳት ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡፡ በምርምር ስራ ወቅት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገቡ ስነምግባራዊ ጉዳዮች በርካታ መሆናቸውን Henn and *et al* (2006:67-95) ይገልጻሉ፡፡ በእነዚህ ምሁራን ከቀረቡ ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን እንመልከት፡፡

መረጃ ሰጪዎች ፍቃደኛ ሆነው መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ፣ ከነሱ ፍቃድ ውጪ መረጃ አለመውሰድና መረጃ እንዲሰጡ አለማስገደድ፣ የድምጽ፣ የፎቶግራፍና የቪዲዮ መረጃዎችን በግለሰቦች ፍቃድ ማንሳት፣ መቅረጽና መጠቀም፣ የግለሰቦችን ምስጢር መጠበቅ፣ ከፍቃዳቸው ውጪ ምስጢራቸውን እንዲናገሩ አለማስገደድ፣ መረጃ ሰጪዎች በሚሰጡት መረጃ ምክንያት የአዕምሮና የአካል አደጋ እንደማይጋለጡ ማረጋገጥና የሚያውቁትን መረጃ በመተማመን እንዲሰጡ ማድረግ፣ መረጃዎችን ለግል የፖለቲካ ዓላማ አለማዋል፣ የጥናቱን ዓላማ፣ የአጥኚውን ማንነትና ዓላማ በግልጽ ማስተዋወቅ፣ መረጃ መሰብሰብ ከመጀመር በፊት ከመረጃ ሰጪዎች ጋር መቀራረብ፣ ቤተሰባዊ ግንኙነት መፍጠር እንዲሁም ለበርካታ ቀናት በቦታው መቆየት፣ ለመረጃ ሰጪዎች ታማኝ መሆንና የሚሰጡትንም መረጃ ማክበር፣ እራስን ከአድሏዊ አስተሳሰብ ማራቅ፣ እራስን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ማመሳሰልና የሚፈጽሟቸውን ማንኛውንም ድርጊቶች ማክበር፣ አጥኚው እንዲፈጽም የሚፈቀድለትን ድርጊቶች በሙሉ ፍቃደኝነት መፈጸም በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

በጥናቱ ወቅትም የመረጃ ሰጪዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ፣ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ግለሰቦችን ስም ባለመጥቀስ፣ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር ቤተሰባዊ ቅርርብ በመፍጠር፣ የመረጃውን ዓላማና ለምን ጉዳይ ጥናቱን እንደማካሂድ በግልጽ በማስረዳት ተአማኝነትና

ወንድማዊነት ግንኙነት በመፍጠር፣ ከአድሏዊነት በመራቅና ለመረጃው ተአማኝ በመሆን መረጃ ሰብስቢያለሁ፡፡ በመሆኑም በምሁራኑ የተገለጹትን የምርምር የስነ-ምግባር ደንቦች በማስታወስና ለደንቦቹም ተገዢ በመሆን ጥናቱን ለማካሄድ ተችሏል፡፡

# 4. የሼኽ ሁሴን ማንነት እና የመካነ ቅርሱ ትዕምርታዊ ውክልና

በዚህ ክፍል የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ታሪክ፣ የሼኽ ሁሴን የውልደት ዘመንና እድገት፣ የዘርሃረግ፣ በአፍቃሪዎቻቸውና በተቃዋሚዎቻቸው ዘንድ ያለውን የእሳቸው ሰብዕናዊ እሳቤዎችና ትዕምርታዊ ውክልናዎች፣ በመካነ ቅርሱ ላይ የእሳቸው አፍቃሪዎችና ተቃዋሚዎች ያላቸው እሳቤዎች፣ የመካነ ቅርሱ መልክዓምድራዊ አንድምታ እንዲሁም የሼኽ ሁሴን ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚና ይቀርባሉ።

የሼኽ ሁሴን ታሪክና ማንነት የተቆራኘው ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጋር ነው። በተመሳሳይም የመካነ ቅርሱ ምንነትና ታሪክ የተቆራኘው ከእሳቸው ጋር ነው። የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከ950 ዓመት በፊት የተመሰረተ እንደሆነ የሚገመት ተፈጥሯዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶችን አጣምሮ የያዘ ስፍራ ነው።[23] የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በባሌ ዞን፣ ጎሎልቻ ወረዳ በአናጂና ቀበሌ ይገኛል። የአናጂና ቀበሌ ከአዲስ አበባ በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በ610 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ ደግሞ በ180 ኪ. ሜትር ርቀት፣ በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል።

የአናጂና ቀበሌ ከባህር ጠለል በላይ በ1,500 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። ስፍራው በ$7^0 80' 00''$ ሰሜን እና በ$41^0 00' 00''$ ምስራቅ የሀሳብ መስመር እንደሚገኝና አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 23,300 ሄክታር እንደሆነ Hailemelekot and Mulugeta (2015:2-5) ይገልጻሉ። ስፍራው በባሌ ተራሮችና በዋቤ ሸበሌ ሸለቆ መካከል የሚገኝ በአብዛኛው ሜዳማ የሆነ ነው። የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን በሰሜን የዋቤ ሸበሌ ወንዝ፣ በደቡብ የኤጀትራቲ ወንዝ፣ በምስራቅ የቀቀለም ወንዝና በምዕራብ የበሀራ ወንዝ ያዋስኑታል። በመካነ ቅርሱ ክልል ውስጥ የደደላ ተራራ፣ የቀጨምሳሬ ተራራ፣ የአበልቃሲም ተራራ፣ የኩባዩ ተራራ፣ የዋቤ ሸበሌ ሸለቆ፣ የአይናገኜ ወንዝ፣ የጂና ወንዝ፣ የቆርጋ ወንዝና የአይናገኜ ገደል ይገኛሉ።

---

[23] - ይህ የመካነ ቅርሱ የእድሜ መረጃ የቃል ታሪክን መሰረት ያደረገ ነው። የመካነ ቅርሱን እድሜ የሚጠቁም የአርኪዮሎጂ ጥናት የለም። በመሆኑም የቀረበው መረጃ ስለትክክለኛነቱ ተጨማሪ ጥናት ይጠይቃል።




## 4.1. የሼኽ ሁሴን ታሪክ

የሼኽ ሁሴን ታሪክ የሚጀምረው ከቤተሰባቸው ነው፡፡ በመሆኑም የእሳቸውን ታሪክ ከማየታችን በፊት በቤተሰባቸው ላይ የሚነገሩ ታሪኮችን መመልከት ይኖርብናል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍልም የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ታሪክ፣ የሼኽ ሁሴን የውልደት ዘመን እንዲሁም የዘርሃረጋቸውን በሚመለከት መረጃዎች ይቀርባሉ፡፡

### 4.1.1 የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ታሪክ

ስፍራው ስያሜውን ያገኘው በፈጣሪ የተመረጡና ታላቅ የሀይማኖት አባት እንደሆኑ በሚታመነው በሼኽ ሁሴን ስም ነው። የሼኽ ሁሴን አባት ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ ሰዒድ አብደላህ ናቸው። አባታቸው ከሼኽ ኢብራሂም በተጨማሪ ሼኽ ኢብራሂም ቢን መልካይ፣ ጀማል ካያ እና ኑር አህመድ በሚሉ ስሞች ይጠራሉ። የሼኽ ሁሴን እናት ሽምሲያ ናቸው። እናታቸው ከሽምሲያ በተጨማሪ አዮ ማኪዳ በሚል ስም ይጠራሉ። ሼኽ ኢብራሂም ሶስት ልጆች አሏቸው። ስማቸውም ሰይድ ኑር ሁሴን፣ ሰኢድ መሃመድና ሰኢድ ሱሌይማን እንደሆነ Eshetu (1973:2) ይገልጻል።

የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦችን በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ሀሳቦችን አቅርበዋል። Braukämper (2004:132) ከዛሬ 800 ዓመት በፊት የሼኽ ሁሴን አያት የሆኑት ሰዒድ አብደላህ ከአረቢያ በሱማሊያ በኩል አድርገው ወደ አናጂና እንደመጡ ይገልጻል። ሌሎች ምሁራን ደግሞ የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ሳይሆኑ እራሳቸው ሼኽ ሁሴን ከኢራቅ ወደ ስፍራው መምጣታቸውን የሚገልጹ አሉ። ከእነዚህ መካከል Smith (1896:125)፣ Neumann (1902:ገጽ የለውም) እና Cerulli (1922:152) ሼኽ ሁሴን ከኢራቅ ባግዳድ ከተማ ተነስተው በሐረር በኩል ወደ ስፍራው መምጣታቸውን ይገልጻሉ። ይህንን ሀሳብ የሚደግፍ መረጃ ማግኘቱን Temam (2002:24) ገልጿል።

በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት ስለሼኽ ሁሴንና ስለእሳቸው ቤተሰቦች ታሪክ በሚመለከት የተለያዩ መረጃዎችን አግኝቻለሁ። ከቡድኑ አባላት መካከል አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ሼኽ ኢብራሂምና ባለቤታቸው ሽምሲያ ከየመን አገር ተነስተው በሱማሊያ- መርካ በኩል ወደ ባሌ እንደመጡ ይገልጻሉ።[24] አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ደግሞ የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ከኢራቅ አገር ባግዳድ ከተማ ተነስተው በሱማሊያ- በርበራ በኩል ወደ ባሌ እንደመጡ ይገልጻሉ።[25] ሁሉም የተተኳሪ ቡድን አባላት የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ከውጭ አገር እንደመጡ እንዲሁም ሼኽ ሁሴን የተወለዱትና ያደጉት ባሌ ዞን አናጂና ቀበሌ እንደሆነ ይስማማሉ። የእሳቸው ቤተሰቦች ከየመን እንደመጡ የሚገልጹ መረጃ ሰጪዎች ከአገራቸው የወጡበትን ምክንያት እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

---

[24] - አቶ ኑማን መሃመድ፣ ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድና አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም።

[25] - ወ/ሮ ሀሊማ ዑስማንና ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም።

የሼኽ ሁሴን አባትና እናት ከአገራቸው የመን የወጡት ከሰው ጋር በነበራቸው ጠብ ምክንያት ነው፡፡ የጠቡ ምክንያትም የሼኽ ሁሴን እናት ‘መሐልል’ ናቸው፡፡ ‘መሐልል’ ማለት ቀደም ሲል ባል የነበራቸውና የፈቱ ማለት ነው፡፡ እሳቸውም ከቀድሞ ባላቸው ጋር ተፋተው ነው ሼኽ ኢብራሂምን ያገቡት፡፡ ሼኽ ኢብራሂምን አግብተው ሲኖሩ የቀድሞ ባላቸው ‘የእኔን ልጅ ነው ያረገዘችው፣ ስለዚህ ሌላ ባል ማግባት አትችልም’ በሚል ጠብ ተፈጠረ፡፡ በዚህ ምክንያት ሀገራቸውን ጥለው ወጡ፡፡ ከአገራቸው የመንም በሱማሊያ በኩል አናጂና ገብተው መኖር ጀመሩ፡፡[26]

የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ከኢራቅ ባግዳድ እንደመጡ የሚገልጹ መረጃ ሰጪዎች ደግሞ “የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ወደ አናጂና የመጡት በወቅቱ በስፍራው ይኖር የነበረው ሕዝብ የአላህን መንገድ እንዲከተልና የእስልምና ኃይማኖትን እንዲያስተምሩ በሚል በአላህ ታዘው ነው፡፡” የሚል ምክንያት ያቀርባሉ፡፡[27] መረጃ ሰጪዎች እነዚህን ሀሳቦች ቢያቀርቡም፣ የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ወደ አናጂና ለምን ሊመጡ እንደቻሉ በትክክል አይታወቅም፡፡

## 4.1.2 የሼኽ ሁሴን የውልደት ዘመን

ሼኽ ሁሴን እጅግ የተከበሩ የሀይማኖት አባትና ከፈጣሪ ልዩ ሀይል የተሰጣቸው ትልቅ ኢማም እንደሆኑ ተከታዮቻቸው ያምናሉ፡፡ ሼኽ ሁሴን በተከታዮቻቸው ዘንድ ትልቅ መንፈሳዊ አባትና ሰውን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኙ፣ የፈጣሪ መልዕክተኛ፣ የፈጣሪ ባርያ፣ ፈጣሪ ልመናቸውን የሚሰማ፣ ቅን የፈጣሪ ሰው፣ በእሳቸው ስም የሚለምን ማንኛውም ሰው እንደሚሳካለት፣ በማንኛውም ሰዓት ለጠራቸው ሰው ፈጥነው እንደሚደርሱ፣ በየትኛውም ስፍራ እንደሚገኙ፣ በጭንቀት ወቅት ስማቸውን ጠርቶ ድረሱልኝ ላለ ሰው ፈጥኖ ደራሽ እንደሆኑ ይታመንባቸዋል፡፡ ሼኽ ሁሴን የተወለዱት መካነ ቅርሱ በሚገኝበት አናጅና ቀበሌ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ሼኽ ሁሴን የተወለዱትም በሂጅራ የዘመን አቆጣጠር በ6ኛው ወር (በጀማዲ-አስ-ሳኒ ወር) ማክሰኞ ሌሊት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ማክሰኞ የእሳቸው የመታሰቢያ ዕለት ነው፡፡

የሼኽ ሁሴንን የትውልድ ዘመን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች አሉ፡፡ Gemechu (2013) በ9ኛው መቶ ክ/ ዘመን መጨረሻ ተወለዱ ይላል፡፡ Andrzejewski (1975) በ12ኛው መቶ ክ/ ዘመን እንደተወለዱ ይገልጻል፡፡ Areba and *el al* (2003) ደግሞ በ11ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ እንደተወለዱ ይገልጻሉ፡፡ Braukämper (2004)፣ Lewis (1977)፣ Eshetu (1973)፣ Mohamed (1990) እና Temam (2002) ሼኽ ሁሴን በ12ኛው እና በ13ኛው መቶ ክ/ዘመን መካከል የኖሩ መሆናቸውን

---

[26] - አቶ ኑማን መሃመድና አቶ አብዱልናስር አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡
[27] - ወ/ሮ ሀሊማ ዑስማንና ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ይገልጻሉ፡፡ Smith (1896) እና Neumann (1902) ሼኽ ሁሴን ከ300 አመት በፊት የኖሩ ናቸው ይላሉ፡፡

Cerulli (1922) እና Trimingham (1952) ደግሞ 1880ዎቹ የአርሲን ጦር በመምራት ከንጉስ ምኒልክ ጦር ጋር እንደተዋጉ ይገልጻሉ፡፡ ይህ የCerulli (1922) እና የTrimingham (1952) መረጃ ትክክል እንዳልሆነ Braukämper (2004:134) የአርሲ ጦር ከንጉስ ምኒልክ ጦር ጋር በሚዋጋበት ወቅት የአርሲ ጦር ሼኽ ሁሴንን እንደ መንፈሳዊ መሪነት ይቆጥራቸው እንደነበር መረጃ ሰጪዎች እንደነገሩት ገልጿል፡፡

የእኔ መረጃ ሰጪዎች ሼኽ ሁሴን መቼ እንደተወለዱ ሁለት መረጃዎችን አቅርበዋል፡፡ አንደኛው፤ ከዛሬ 950 አመት በፊት እንደተወለዱ የሚገልጽ ነው፡፡[28] ይህ ደግሞ በ1057 ዓ.ም አካባቢ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው፤ በነብዩ መሀመድና በሼኽ ሁሴን ውልደት መካከል 5 ቀርን መኖሩን የሚገልጽ ነው፡፡[29] 1 ቀርን 100 ዓመት ነው፡፡ ይህ ማለት በሼኽ ሁሴንና በነብዩ መሃመድ መካከል የ500 ዓመት ልዩነት አለ፡፡ ነብዩ መሃመድ የተወለዱት በ570 C.E ነው (Gulevich, 2004:57)፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት ሼኽ ሁሴን የተወለዱት በ1062 ዓ.ም አካባቢ ነው ማለት ነው፡፡

የሼኽ ሁሴንን የውልደት ዘመን ከሚገልጹና ከላይ ከቀረቡ መረጃዎች መካከል ትክክለኛውን ማወቅ አይቻልም፡፡ በእኔ ግንዛቤ ሼኽ ሁሴን በ1060 ዓ.ም አካባቢ ወይም በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ ተወለዱ የሚለው መረጃ አሳማኝ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም ሶስት ምክንያቶችን እንደማሳያ ወስጃለሁ፡፡ አንደኛው፣ በዚህ ዘመን የእስልምና ኃይማኖት በባሌ ዞንና በአካባቢው በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋበት መሆኑ ነው፡፡[30] ሁለተኛ፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሼኽ ሁሴን እንደተገነቡ የሚነገርላቸው የባላና የዙቅጡም መስኪዶች ከዛሬ 900 ዓመት በፊት እንደተገነቡ የሚገልጹ አፈታሪኮች መኖራቸው ነው፡፡

ሶስተኛ፣ ሼኽ አብድ-አል-ቃዲር አል-ጀይላኒ (በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና አካባቢው አጠራር ሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ) በስፍራው መጥተው ከሼኽ ሁሴን ጋር መገናኘታቸውን የሚገልጹ

---

[28] - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ኡስማን፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

[29] - ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ ኢድሪስ እና አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

[30] - የባሌ ዞን፣ በዞን ደረጃ እራሱን ችሎ በአስተዳደር የተመሰረተው በ1952 ዓ.ም ነው (Goba Municipality, 1984)፡፡ በመሆኑም "ባሌ" የሚለው ስያሜ በወቅቱ የነበረውን የግዛት ክልል ሙሉለሙሉ የሚገልጽ አይደለም፡፡

አፈታሪኮች መኖራቸው ነው። ሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ በ1077 በኢራቅ አገር ጊለን (ኪለን) በምትባል ከተማ ተወልደው እስከ 1166 የኖሩ የሱፊዝም ሊቅ ናቸው። ሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ በሱፊዝም እስልምና ኃይማኖት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ተጽዕኖ የፈጠረውን የቃድሪያ ስርዓት የፈጠሩ ናቸው። የቃድሪያ ስርዓት በሱፊዝም ታሪክ የመጀመሪያው መደበኛ የሱፊዝም ስርዓት (Order)[31] ነው (Renard, 2009፡19)። በዚህ አፈታሪክ መሰረት ሼኽ አብዱልቃዲር በሕይወት የነበሩበት ዘመን ከሼኽ ሁሴን የውልደት ዘመን ጋር ተቀራራቢ መሆኑ ነው።

### 4.1.3 የሼኽ ሁሴን የዘርሃረግ

ስለ ሼኽ ሁሴን ከውልደታቸው ዘመን በተጨማሪ የዘር ሀረጋቸውን በሚመለከት የተለያዩ መረጃዎች አሉ። Eshetu (1973) እና Andrzejewski (1972) የነብዩ መሃመድ የአጎት ልጅ ከሆኑት አቂል- ኢብን- አቢ- ጣሊብ የዘር ሀረግ 12ኛ ትውልድ እንደሆኑ ይገልጻሉ። ምሁራኑ ይህንን የሼኽ ሁሴን የዘር ሀረግ መረጃ ያገኙት በረቢ- አል- ቁሉብ መጽሐፍ ላይ ከሰፈረው መረጃ ነው። መጽሐፉ "Kitab Rabi-al-Qulúb Fi Thikr Manaqib wa- Fada'il Sayyidina ash-Shaykh Nur Husayn" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን፣ ትርጉሙም ‹‹የጌታችን የሼኽ ሁሴንን ጸጋና ስጦታ በደስታ የሚገልጽ የልብ አነሳሽ መጽሐፍ›› ማለት ነው።[32] በእነዚህ ምሁራን ሀሳብ የሼኽ ሁሴን የዘር ሀረግ እንደሚከተለው ነው።

---

[31] - ስለሱፊዝም ምንነትና ስለሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ ማንነት በምዕራፍ 5 ቀርቧል።

[32] - ይህ መጽሐፍ ስለ ሼኽ ሁሴን ታሪክ የሚገልፅ ነው። መጽሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በ1926/27 በግብጽ ካይሮ ነው (Cerulli,1971)።




መርስዔህዘን (1999 ዓ.ም:225) ደግሞ ሼኽ ሁሴን ከነብዩ መሃመድ ቀጥታ የዘርሃረግ 26ኛ ትውልድ እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ ይህ መረጃ ትክክል አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም አንደኛ፤ መርስዔህዘን (1999 ዓ.ም) የእሳቸውን የዘርሃረግ ሲገልጽ "ኑር ሁሴን ሽምሱዲንን ወለደ" ይላል፡፡ ነገር ግን ሼኽ ሁሴን ሽምሱዲን የሚባል ልጅ የላቸውም፡፡ ሁለተኛ፤ መርስዔህዘን (1999 ዓ.ም) ባቀረበው የዘርሀረግ መዋቅር ልጅ እያሱ ከነብዩ መሃመድ የዘርሀረግ 72ኛ ትውልድ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህ አይነት የዘር ቆጠራ በአገራችን በነገሱ ንጉሶች ታሪክ ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የዘር ሀረግ ቆጠራ ለልጅ እያሱ የፖለቲካ ቅቡልነት ለማስገኘት በሚል የቀረበ ፕሮፓጋንዳ ይመስላል፡፡

አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቼ ሼኽ ሁሴን የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ አጎት እንደሆኑ ገልጸውልኛል፡፡[33] አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ግን 'እሳቸው በሕይወት በነበሩበት ወቅት ራሳቸውን የዚህ ዘር ወይም የዚህ ጎሳ ነኝ አላሉም፡፡ እሳቸውም ሲያስተምሩ ዘራችሁን አትቁጠሩ ብለዋል፡፡ በመሆኑም የእንትን ዘርና ጎሳ ናቸው ማለት ስህተት ነው፡፡' በማለት ይገልጻሉ፡፡[34]

በአሁኑ ወቅት የእሳቸው ዘር ነኝ የሚል ጎሳ ወይም ግለሰብ በአካባቢው ወይም በሌሎች የአገሪቷ ስፍራዎች አሉ ወይ? ስል በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት መረጃ ሰጪዎቼን ጠይቄ ነበር፡፡ የሁሉም መረጃ ሰጪዎቼ መልስ ማንም የእሳቸው ዘር ነኝ የሚል በአካባቢው አለመኖሩን የሚገልጽ ነው፡፡ ለዚህም በዋናነት የእሳቸው የዘር ሀረግ ተቋርጦ ሳይሆን ማንም ሰው የእሳቸው ዘር ነኝ ብሎ ዘሩን እንዳይቆጥር በማስተማራቸው እንደሆነ ገልጸውልኛል፡፡ መረጃ ሰጪዎቼ ይህን ቢሉም ሼኽ ሁሴን ከእነሱ ወገን እንደተወለዱ የሚያምኑ አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ሱማሌዎች፣ አርጎባዎች፣ ባሌዎች፣ አርሲዎችና ወሎዎች ይጠቀሳሉ፡፡

ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት አንድም እሳቸው የተከበሩ በመሆናቸው ሁሉም የእኔ ወገን ናቸው ከሚል ሽሚያ ሲሆን፣ አንድም ልጅነት ሁለት አይነት በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ልጅነት በስጋና በመንፈስ የሚገኝ በመሆኑ ነው፡፡ ሼኽ ሁሴንን የሚወድ ሰው የእሳቸው የዘርሀረግ ነኝ ይላል፡፡ በመንፈስ ልጅ ለመሆንና ለእሳቸው ያለውን ፍቅር ለመግለጽ በሚል ፍላጎት፡፡ ለዚህም ይመስላል በተለያዩ የአገራችን ቦታዎች የሼኽ ሁሴን ልጅ ወይም የልጅ ልጅ እዚህ ነው የኖሩትና የተቀበሩት የሚሉ አፈ-ታሪኮች የሚነገሩት፡፡[35]

ሼኽ ሁሴን በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች፣ በግብጽ፣ በቱኒዝያና በሌሎች የአፍሪካ አገራት፣ በየመን፣ በቱርክ፣ በህንድ፣ በእንግሊዝና በሌሎች የዓለም አገራት እየተዘዋወሩ ሀይማኖታዊ ትምህርቶችን ሲማሩና ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ እሳቸው ሀይማኖታዊ ትምህርት ከመማርና ከማስተማር በተጨማሪ በግብጽ የሼሪያ ፍርድ ቤት አባል በመሆን እንዳገለገሉ ይነገራል፡፡[36] ሼኽ ሁሴን በሕይወት ዘመናቸው በተለያዩ ስፍራዎች ኖረዋል፡፡ እነዚህ ስፍራዎችም አርሲ ዞን ውስጥ በሚገኝና ሰኪና በሚባል ስፍራ ለ50 ዓመታት፣ አርሲ ዞን ውስጥ የሚገኝና አረብልጅ

---

[33] - ሼኽ ቃሲም ሼኽ አደም፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 29 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[34] -አቶ ኢብራሂም ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 29 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፣ ሼኽ መሃመድ መሃሙድ፣ ሮቤ ከተማ፣ ጥር 15 ቀን 2008 ዓ.ም፣ አቶ ከዲር ወሌ፣ ጎባ ከተማ፣ ጥር 16 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[35] - ይህን የስጋና የመንፈስ ልጅነት ሀሳብን የነገሩኝ አቶ አሕመድ ዘካሪያ (ረዳት ፕሮፌሰር) ናቸው፡፡

[36] - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 9 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

በሚባል ስፍራ ለ100 ዓመታት፣ በተለያዩ የአፍሪካና የዓለም አገራት ለ50 ዓመታት እንዲሁም በአናጂና ለ70 ዓመታት ኖረዋል፡፡[37] በዚህ መሰረት ሼኽ ሁሴን ለ270 ዓመታት እንደኖሩ ያመላክታል፡፡ ይህ መረጃ እንዳለ ሆኖ ሼኽ ሁሴን በዚህ ዓለም ላይ የኖሩበትን አመት በሚመለከት 250 ዓመት፣ 280 ዓመትና 495 ዓመት እንደኖሩ የሚገልጹ መረጃዎችም አሉ፡፡

ሼኽ ሁሴን 3 ሚስቶች ነበሯቸው፡፡ እነሱም ሐጆሴ፣ ሰኪና እና ወቂት ናቸው፡፡[38] የሼኽ ሁሴን ልጆች 4 እንደሆኑ Braukämper (2004:132) እና Østebo (2012፡51) ይገልጻሉ፡፡ እኔ ያገኘሁት መረጃ የእሳቸው ልጆች 5 መሆናቸውን ነው፡፡ እነሱም መሃመድ ተማም፣ ኑርላህ አህመድ፣ አብዱልሂ ፋራዲስ፣ ፋጡማና ሱሌይማን ናቸው፡፡ ሁሉም ልጆቻቸው ተወልደው ያደጉት አናጂና እንደሆነ ይታመናል፡፡ ነገር ግን ልጆቻቸው ወደተለያዩ አካባቢዎች ሀይማኖታዊ ትምህርት ለማስተማር ሄደዋል፡፡ በሄዱባቸው ስፍራዎችም የሀይማኖት ማስተማሪያ ማዕከላት መስርተዋል፡፡

ከልጆቻቸው መካከል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ እንደኖሩ፣ አስክሬናቸውም እዛው እንዳረፈ የሚታመነውና በስማቸው ገሞ (ቁባ) የተሰራላቸው መሃመድ ተማምና ፋጡማ ናቸው፡፡ ገሞ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም ህንጻ ማለት ነው፡፡ ቁባ ደግሞ የአረብኛ ቃል ሲሆን፣ ግንባታ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ገሞዎች (ቁባዎች) በተለያዩ ወቅቶች እምነቱን በማስፋፋት ከፍተኛ ሚና ያላቸው ታዋቂ የሀይማኖት ኢማሞች አስክሬናቸው ባረፈባቸው መካነ መቃብሮች ላይ ወይም በቦታው ለመጡ ታላላቅ የሀይማኖት ሰዎች መታሰቢያነት የተገነቡ ኪነ-ህንጻዎች ናቸው፡፡

ኑርላህ አህመድ በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሀላባ ዞን፣ አቢቾ በሚባል ስፍራ ሕይወታቸው እንዳለፈ ይነገራል፡፡[39] የኑርላህ አህመድ አጽም ባረፈበት በዚህ ስፍራም በስማቸው የተነገባ ገሞ አለ (Zena, 2014፡151)፡፡ በዚህ ገሞም በዓመት ሁለት ጊዜ፣ የሐጅና የዛህራ ገልገላ ኀበና የሙዳ በዓላት ይከበራሉ፡፡ በእነዚህ በዓላትም ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መሄድ ያልቻሉ የአካባቢው ሕዝብና ለአካባቢው ቅርብ የሆነ በሺሕ የሚቆጠር ሕዝብ ይገኛል (Zena, 2014፡151)፡፡

---

37 - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አቶ ኑማን ሼሕ መሃመድ፣ ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

38 - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አቶ ኑማን ሼሕ መሃመድ፣ ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

39 - አቢቾ፣ ከቆሊቶ ከተማ 3 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ከብላቴ ወንዝ አጠገብ የሚገኝ ነው፡፡

ኑርላህ አህመድ በሀላባ ሕይወታቸው ባለፈበት ወቅት አባታቸው ሼኽ ሁሴን የእስልምና ትምህርት ለማስተማር ጂንካ እንደነበሩ፣ ሼኽ ሁሴንም የልጃቸውን ማረፍ ሰምተው በስፍራው እንደመጡ፣ አካባቢው በአለት በመሞላቱ ምክንያት ለቀብር የሚሆን ጉድጓድ መቆፈር ባለመቻሉ ሼኽ ሁሴን ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሲጸልዩ በራሱ ጊዜ ድንጋዩ ተሰነጣጥቆ ለቀብር አመቺ መሆኑና የኑርላህ አህመድ አስክሬን መቅበር መቻሉ በአካባቢው በስፋት እንደሚነገር Zena (2014፡151-153) ትገልጻለች፡፡

አብዱላሂ ፋራዲስ በሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም ሱሌይማን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን ደግደግ በተባለ ስፍራ አስክሬናቸው አርፏል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሼኽ ሁሴን ልጆች አስክሬናቸው እንዳረፈ በሚታመንባቸው አካባቢዎችም በስማቸው ገሞ ተገንብቷል፡፡ በተመሳሳይም የሼኽ ሱሌይማን ደግደግ ልጅና የሼኽ ሁሴን ባሌ የልጅ ልጅ የሆኑት አው ሁሴን በሰሜን ሸዋ በሚገኘው የጎዜ መንደር ለረጅም ጊዜ እንደኖሩና ለስማቸውም የአው ሁሴን ዛውያ የሚባል መታሰቢያ መኖሩን ሐሰንና ሐሰን (2008 ዓ.ም፡45) ይገልጻሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት በደቡብ ክልል ከሚገኙ ሕዝቦች መካከል የሀላባና የስልጤ ሕዝቦች በብዛት ይመጣሉ፡፡ በተመሳሳይም ከሱማሌ ክልል የሱማሌ ሕዝቦችና ከአማራ ክልል የአርጎባ ሕዝቦች በብዛት ይመጣሉ፡፡ እነዚህ ሕዝቦች በብዛት ወደ መካነ ቅርሱ የመምጣታቸው አንዱ ምክንያት የሼኽ ሁሴን ልጆች በአካባቢዎቹ አስክሬናቸው ስላረፈና በስማቸው የመታሰቢያ ገሞ ስለተገነባ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለእነዚህ ሕዝቦች ትልቅ ክብር ይሰጣቸዋል፡፡ የተለየ የማረፊያ ስፍራና በስማቸው የተሰየመ ደገሌ አላቸው፡፡ ደገሌ የሚለው ቃል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብ የተሰሩ ቤቶችን የሚገልጽ ስያሜ ነው፡፡

የሀላባና የስልጤ ሕዝቦች፣ በአካባቢያቸው ከድሬ ሼኽ ሁሴን ጋር የሚያመሳስላቸው ወይም የሚያገናኛቸው መለያዎች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በሀላባ በኑርላህ አህመድ ገሞ የሙዳ በዓላት መከበራቸው፣ በስልጤ ዞን ውስጥ ከሚገኝ ቦታ አንስቶ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚያደርስ ዋሻ እንዳለ ይታመናል፡፡ የዚህ ዋሻ ስያሜ አይናገኜ ይባላል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም አይናገኜ የሚባል ዋሻ አለ፡፡ በስልጤ ዞን በአልከስዬ መስኪድ የሼኽ ሁሴን ዛውያ የሚባል ራሱን የቻለና የመውሊድን በዓል ለማክበር ከባሌ የሚሄዱ ግለሰቦች የሚያርፉበት ስፍራ አለ፡፡

## 4.2 የሼኽ ሁሴን ሰብዕናዊ እሳቤዎች

የሼኽ ሁሴንን ሰብዕና በሚመለከት የተለያዩ አካላት የተለያየ እሳቤ አላቸው፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል የሼኽ ሁሴን ሰብዕና ከአፍቃሪዎቻቸውና ከተቃዋሚዎቻቸው አንጻር ያለው እሳቤ ይቀርባል፡፡

### 4.2.1 የሼኽ ሁሴን ሰብዕናዊ እሳቤዎች ከአፍቃሪዎቻቸው አንጻር

ሼኽ ሁሴን በወዳጆቻቸው፣ በአፍቃሪዎቻቸው፣ በተከታዮቻቸውና በአማኞቻቸው ዘንድ እንዴት ይታሰባሉ? እንዴት ይገለጻሉ? እንዴት ይታመናሉ? አላቸው ተብሎ የሚታመነው ሰብዕና ምንድን ነው? እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን መግለጽ ሕብረተሰቡ በሼኽ ሁሴን ሰብዕናዊ እሳቤዎች ላይ ያለውን እምነት ያሳያል፡፡

ስሞች ኃይል አላቸው፡፡ መንፈሳዊ ስሞች መንፈሳዊ ኃይል (Divine power) አላቸው፡፡ ሼኽ ሁሴን ከ200 በላይ በሚሆኑ የቁልምጫ ስሞች እንደሚጠሩ ይነገራል፡፡ ከእነዚህ የቁልምጫ ስሞች መካከል አብዮ (አባቴ እንደማለት ነው)፣ ኑር ሁሴን (ብርሃናማው ሁሴን እንደማለት ነው)፣ ሼኽ-ና-ሁሴን (ሼኽ ሁሴን የሚለውን ስም በተለየ መንገድ እንደመጥራት ነው)፣ ሰዒዱ-ላራፊና (የምርጦች ምርጥ እንደማለት ነው)፣ ነቤ (ነብይ እንደማለት ነው)፣ ሮባ ባሌ (የባሌ ዝናብ እንደማለት ነው)፣ ገራደ ባሌ (የባሌ ገዢ (መሪ) እንደማለት ነው)፣ አብዮ ባሌ (የባሌ አባት እንደማለት ነው)፣ ገርቢቻ ረቢ (የአላህ ባሪያ እንደማለት ነው)፣ ባሕረ ባሌ (የባሌ ባህር እንደማለት ነው)፣ ሼኽ ሁሴን ባሌ (የባሌው ሼኽ ሁሴን እንደማለት ነው) የመሳሰሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ የቁልምጫ ስሞች ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ የእሳቸው አፍቃሪዎች በአብዛኛው ሼኽ ሁሴንን የሚጠሩባቸው ናቸው፡፡ ሼኽ ሁሴን በተወሰነ አካባቢ በሚኖር ማህበረሰብ ውስጥ የሚታወቁባቸው የቁልምጫ ስሞች አሏቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል በሱማሌ ወየስ በሚል፣ በአርሲ ሳዒዳ ጃኖ ገርቢ በሚል፣ በባሌ ሰዒላ-ላራፊና በሚል፣ በአፋር ሼኽ ራህመቶ በሚል፣ በቦረና ሁሴን ጠለል በሚል፣ በሕንድ ሐሚር በሚል የቁልምጫ ስም ይጠራሉ፡፡ ለሼኽ ሁሴን መጠሪያ የሆኑት እነዚህ የቁልምጫ ስሞችም የእሳቸውን መንፈሳዊ ኃይል የሚገልጹ መንፈሳዊ ስሞች ናቸው፡፡

ሼኽ ሁሴን በወዳጆቻቸው፣ በአፍቃሪዎች፣ በተከታዮቻቸውና በአማኞቻቸው ዘንድ ብዙ ናቸው፡፡ የተለያዩ ሰዎች በእሳቸው ላይ ያላቸው እምነት የተለያየ ነው፡፡ የሰዎቹ እምነትም መለያየት

የሼኽ ሁሴን ማንነት፣ ሰብዕናዊ እሳቤዎች እንዲሁም በእሳቸው ላይ ያለው ጽንሰሃሳባዊ አተያይ እንዲለያይ ምክንያት ሆኗል፡፡ ጽንሰሃሳባዊ እሳቤዎቹ በመለያየታቸውም ምክንያት በእሳቸው ላይ ወጥ የሆነ እሳቤ እንዳይኖር እንዲሁም በአማኞቻቸው ወገንም ሆነ በተቃዋሚያቸው ወገን ዘንድ የክርክር ምክንያት ሆነዋል፡፡ ሼኽ ሁሴን ማን ናቸው? ሼኽ ሁሴን ምንድን ናቸው? ሼኽ ሁሴን ከሌላው በምን የተለዩ ሆኑ? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ በአማኞቻቸው ዘንድ ያሉ የተለያዩ እሳቤዎችን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

እነዚህን እሳቤዎች ለመረዳት በሼኽ ሁሴን ላይ የሚነገሩ ሚቶች፣ ውክልናዊ ትዕምርቶችና በተለያዩ መንፈሳዊ መዚቃዎች አማካኝነት የሚቀርቡ ቃል ግጥሞች (Oral poems) ዋና መሰረቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥበባዊ ቅንጣቶች (Lores) በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በቅዱስ ቁርዓን እንደሚገኙ ትረካዎች የሼኽ ሁሴንን ማንነት የሚተርኩ ናቸው፡፡ ትረካዎቹም የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች በሼኽ ሁሴን ላይ ያላቸውን የነገረ ፍጥረት (Cosmological)፣ የነገረ ህላዌ (Ontological) እና የነገረ ተልዕኮ (Eschatological) እሳቤዎች የሚገለጹባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ትረካዎች በትዕምርት፣ በሚትና በግጥም ቅርጽ ሲቀርቡ በጣም ከፍተኛ በሆነ ምናባዊ የአገላለጽ መንገድን በመከተል ነው፡፡

የክርስትና ኃይማኖት ተከታዮች መጽሐፍ ቅዱስን ወይም የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ቅዱስ ቁርዓንን እንደ ቅዱስ አሀዶች (Sacred texts) እንደሚረዱት ሁሉ፣ እነዚህ ምናባዊ አገላለጾች ለሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ቅዱስ አሀዶች ናቸው፡፡ እነዚህን ቅዱስ አሀዶች የ"ሼኽ ሁሴን ገድል" በሚል መግለጽ ይቻላል፡፡ እነዚህ ቅዱስ አሀዶች በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በቅዱስ ቁርዓንና በሌሎች ኃይማኖታዊ ገድላት ላይ እንዳሉት ትረካዎች ወጥ የሆነ ትርጓሜ ስለሌላቸው፣ ሁሉም የራሱንና ትክክል ነው የሚለውን አንድምታ (Interpretation) ሊወስድ ይችላል፡፡ የቅዱስ አሀዶች አንድምታ በመለያየቱም አንድ ነጠላ ቀኖናዊ ትርጓሜ (Canonical version) የላቸውም፡፡ የሼኽ ሁሴንን ገድል ከሚገልጹ ቅዱስ አሀዶችን ከድርጊቶቻቸው ጋር በማያያዝ የሼኽ ሁሴንን ሰብዕና ለመገንባት ያላቸውን ጠቀሜታና በሼኽ ሁሴን ላይ ያሉ እሳቤዎችን ቀጥለን እንመልከት፡፡

**እሳቤ 1-** "ሼኽ ሁሴን ፈጣሪ የመረጣቸው ቅዱስ ናቸው፡፡" ይህ እሳቤ እሳቸው ከመወለዳቸው በፊትም ሆነ ከተወለዱ በኋላ በፈጣሪ ዘንድ ከሌሎች ሰዎች መካከል የተለዩ፣ ፈጣሪ ከመረጣቸው ቅዱሳን መካከል አንዱ የሆኑ፣ ቅዱሳን የሚከውኑትን ስራ ሁሉ የሰሩ፣ ተግባራቸው ሁሉ በፈጣሪ ዘንድ የተባረከና እንከን የለሽ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህንን እሳቤ የሚያሳዩ ሚቶች በሼኽ ሁሴን ላይ ይነገራሉ፡፡ እነዚህ ሚቶች በትረካና በግጥም ቅርጽ የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ሚቶች በሼኽ ሁሴን ላይ የሚንጸባረቀውን እሳቤ እንዴት እንደገነቡ ቀጥለን እንመልከት፡፡

ሼኽ ሁሴን ውልደታቸው ተአምራዊ እንደሆነ ተከታዮቻቸው ያምናሉ፡፡ ውልደታቸውን በተመለከተ ለአበልቃሲም በመላዕኩ ጅብሪል (መላዕኩ ገብርኤል) በኩል ከፈጣሪ ራዕይ ታይቷቸው እንደነበር ይታመናል፡፡ ፈጣሪ ጅብሪልን (ገብርኤልን) ወደ አበልቃሲም መልዕክት ይልከዋል፡፡ መልዕክቱም "ሔደህ ሁሴን የሚባል ህጻን ይወለዳል፣ የእሱንም ጸጉር ትላጫለህ፡፡" የሚል ነው፡፡ አበልቃሲም ከነብዩ አደም (አዳም) ጀምሮ እስከ ነብዩ መሃመድ ድረስ ያሉ 40 ነብያት ሲወለዱ የመጀመሪያ ጸጉራቸውን በፈጣሪ ትዕዛዝ የላጩ ቅዱስ ወልይ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ የሼኽ ሁሴንን ጸጉር ለመጀመሪያ ጊዜ የላጩት አበልቃሲም እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ሼኽ ሁሴን 41ኛው ናቸው፡፡

አበልቃሲም ጸጉር የሚላጩበት መላጫ ከገነት እንደመጣ ይነገራል፡፡ አበልቃሲም ነብዩ መሃመድን ከላጩ በኋላ ፈጣሪ በመንፈስ ኃይል "ይህንን መላጫ አስቀምጠው ወደፊት የምትላጨው ልጅ አለ፡፡" ይላቸዋል፡፡ መላጫውም ለ5 ቀርን (ለ500 ዓመት) ያህል በገነት ተቀመጠ፡፡ በነብዩ መሐመድና በሼኽ ሁሴን ውልደት መካከል 5 ቀርን አለ፡፡[40] ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ወቅት በስፍራው ልዩ ተዓምር መታየቱ ይነገራል፡፡ ይህንን ተዓምር መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> ሼኽ ሁሴን በሚወለዱበት ቀን መላዕኩ ጅብሪል ተልኮ 'የምትላጨው ልጅ ሊወለድ ነውና ሔደህ እየው' ይላቸዋል፡፡ ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ቀን በአካባቢው 40 ህጻናት ተወልደው ስለነበር 'የምላጨውን ሕጻን በምን ምልክት ልለየው' ሲል አበልቃሲም ጠየቀ፡፡ ጅብሪልም 'ልዩ ምልክት ታያለህ፡፡" አላቸው፡፡ አበልቃሲም እሺ ብለው ቦታው

[40] - ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ ኢድሪስ እና አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

ላይ ሲደርስ ሼኽ ሀሴን ሲወለዱ ብርሃን (ኑር) ሲበራ አዩ፡፡ በብርሃኑ ምልክትነትም አበልቃሲም ሼኽ ሁሴንን ለዩት፡፡[41]

"ኑር" በአረብኛ ብርሃን ወይም ጸዳል ማለት ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን ሌላው ስማቸው "ኑር ሁሴን" ነው፡፡ ኑር ሁሴን ማለት ብርሃናማው ሁሴን እንደ ማለት ነው፡፡ ይህ ስያሜም እሳቸው በተወለዱበት ማክሰኞ ሌሊት በአካባቢው የተለየ ደማቅ ብርሃን እንደበራ ከሚነገረው ሚት የተገኘ ነው፡፡ ይህን ብርሃን ፈጣሪ ለሼኽ ሁሴን ክብር ይሆን ዘንድ ያሳየው ተዓምር እንደሆነ የእሳቸው ተከታዮች ያምናሉ፡፡ ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ዕለት ብርሃን መብራቱንና ማክሰኞ ሌሊት መወለዳቸውን የሚገልጽ ቃል ግጥም አለ (ዳንኤል፣ 1984 ዓ.ም)፡፡ ይህ ቃል ግጥም የሚከተለው ነው፡-

Dheeratee samii bayee

Ballatee ardii gayee

Dhaloonni tolaa Baalee Halkan Kiibxataa ta'e

ትርጉሙም፡-

ወደ ሰማይ ብርሃኑ ወጣ

እስከ መሬትም ድረስ አበራ

በማክሰኞ ዕለት ሌሊት የባሌ ደስታ ሲወለድ፡፡

ማለት ነው፡፡ በዚህ ቃል ግጥም ሼኽ ሁሴን ማክሰኞ ዕለት ሌሊት መወለዳቸውን፣ በዕለቱም ሲወለዱ ብርሃን መታየቱንና የባሌ ደስታ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ወቅት ብርሃን ከመሬት ወደ ሰማይ እንደወጣ ወይም ከታች ወደ ላይ አቅጣጫ እንደሄደ ተመልሶም ወደ ምድር ወይም ከላይ ወደ ታች መምጣቱን ቃል ግጥሙ ያሳያል፡፡ በቃል ግጥሙ ሼኽ ሁሴን የባሌ ደስታ እንደሆኑ ቀርቧል፡፡ ባሌ በአሁኑ ወቅት እራሱን የቻለ የዞን አስተዳደር ያለው ነው፡፡ የባሌ ደስታ የሚለው አገላለጽ ሼኽ ሁሴን ባሌ ዞን ውስጥ መወለዳቸውንና ለባሌ ሕዝብ የደስታ ምንጭ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ነገር ግን የእሳቸው መወለድ ከባሌ ሕዝብ በተጨማሪ በእሳቸው ለሚያምኑና በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ለሚገኘው ሕዝብ ደስታ ነው፡፡

[41] - አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ እድሪስ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

የብርሃን ጸዳል ለሼኽ ሁሴን የበራላቸው ወይም በአካባቢው የታየው በውልደታቸው ወቅት ብቻ አይደለም፡፡ በጉልምስናቸው ወቅትም የብርሃን ጸዳል ከሰውነታቸው ይወጣ እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህም በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴንና ተከታዮቻቸው በነበሩበት ስፍራ ከባድ ዝናብ ዘነበ፡፡ በዝናቡ ምክንያትም አካባቢው በድቅድቅ ጨለማ ተሸፈነ፡፡ ከእሳቸው ተከታዮች መካከል ሲራጅ የሚባል ሰው "እርስዎ እውነተኛ የአላህ ሰው ከሆኑ ከዚህ ጨለማ አውጡን፡፡" በማለት ፈተናቸው፡፡ ሼኽ ሀሴንም አላህን መፈታተን ተገቢ አለመሆኑን ካስረዱት በኋላ ከትከሻቸው የችቦ ነበልባል የመሰለ የብርሃን ጸዳል ይበራ ጀመር፡፡ በዚህ ብርሃንም እየተመሩ እሳቸውና ተከታዮቻቸው ከድቅድቅ ጨለማው እንደወጡ የሚነገር ሚት አለ፡፡ ይህን ሚትም የሚደግፍ ቃል ግጥም አለ፡፡ ግጥሙም፡-

Maal siin jettee siraajin keessan siraajin koloobaa

Sheek Huseen maashoo kiyya ka dukkana roobaa.

ትርጉሙም፡-

ምን አሉት ሲራጅ፣ ሲራጅ የኮሎባው

ኑር ሁሴን ማሾዬ የድቅድቅ ጨለማው፡፡

ማለት ነው፡፡[42] በዚህ ቃል ግጥም የብርሃን ጸዳል የወጣው ከሼኽ ሁሴን ትከሻ አካባቢ ነው፡፡ ይህ መሆኑ ሼኽ ሁሴን ያላቸውን ብርሃን የመፈንጠቅ ልዩ ጸጋና ችሎታ ያሳያል፡፡ በቃል ግጥም ውስጥ ሲራጅ የኮሎባው የሚል ቃል አለ፡፡ ኮሎባ የሚለው ስያሜ ሁለት ነገርን ይገልጻል፡፡ አንደኛው፣ በአርሲ ዞን ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስም ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በአርሲ አብይ ጎሳዎች ስር በጂዳ ንዑስ ጎሳ ስር የሚገኝ ጎሳ መጠሪያ እንደሆነ ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ (1998 ዓ.ም፡218) ይገልጻል፡፡ በአካባቢው ግለሰቦች ሲጠሩ ከመለያ ስማቸው ላይ የተወለዱበትን አካባቢ፣ አባል የሆኑበትን ጎሳ ወይም የተለየ ገጠመኝ ያላቸውን ቦታ መጨመር የተለመደ ነው፡፡ በመሆኑም ሲራጅ የኮሎባው ሲባል፣ ሲራጅ የሚባል ግለሰብ የኮሎባ ጎሳ አባል እንደሆነ ወይም ኮሎባ በሚባል አካባቢ ተወላጅ እንደሆነ አመላካች ነው፡፡ በተመሳሳይ ስፍራው በጨለማ በተዋጠበት ወቅት እሳቸው ብርሃን እንዳበሩ የሚገልጽ ሌላም ቃል ግጥም አለ፡፡ ይህም

---

[42] - ይህን ቃለ ግጥም ያገኘሁት በካሴት ከታተመ መንፈሳዊ ሙዚቃ ነው፡፡

Assalaamuu aleeykum yaa abbaa biyyaa

Sheek Huseen maashoo kiyya ka dukkana roobaa.

ትርጉሙ፡-

አሰላም-አሌይኩም የአገር አባት

ኑር ሁሴን ማሾዬ የድቅድቅ ጨለማው፡፡

ማለት ነው፡፡[43] ከላይ የቀረቡት የሚትና የቃል ግጥም ማሳያዎች ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ወቅት በአካባቢው ብርሃን እንደበራ፣ በኃይለኛ ዝናብ ምክንያት ድቅድቅ ጨለማ በመፈጠሩ፣ ከጨለማው ለመውጣት የብርሃን ጸዳል በአካላቸው ላይ እንዳበሩ እንዲሁም ብርሃናቸው በቀን እንዳለው ብርሃን አይነት እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ሚቶችና ቃል ግጥሞች የሼኽ ሁሴንን ማንነት ከብርሃን ጸዳል ጋር እንዲያያዝ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ወዳጆቻቸው ሼኽ ሁሴንን ብርሃን እያሉ ይጠሯቸዋል፡፡

ቅዱስ ለሆኑ የኃይማኖት ሰዎች የብርሃን ጸዳል እንደወረደላቸው የመግለጽ ልማድ በሌሎች የአፍሪካ አገራት በሚገኙ የእስልምና ኃይማኖት ባህል ውስጥም ይገኛል፡፡ የሴኔጋል ቃል ግጥም ባለሙያዎች አብዱል አዚዝ የተባሉ የኃይማኖት ሰውን "የእስልምና ብርሃን (Lampa-lislaam)" በሚል እንደሚያወድሷቸው Jeylan (2005፡33) McLaughline (1997)ን በመጥቀስ ገልጿል፡፡ በተመሳሳይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አስተምህሮ ለቅዱሳን የኃይማኖት አባቶች በተለያዩ ወቅቶች የብርሃን ጸዳል እንደወረደላቸው ይታመናል፡፡ ከእነዚህ አባቶች መካከል አቡነ አኖሬዎስ (ትልቁ) አንዱ ናቸው፡፡ በአቡነ አኖሬዎስ (ትልቁ) የገድል መጻሕፍት ውስጥ ከቀረቡ የእሳቸው ገድላት መካከል የብርሃን ጸዳል እንደወረደላቸውና ብርሃን የወረደበትን ቦታንም "ሠናይ ብርሃን" ብለው ሰይመዋል (ዳንኤል፣2006 ዓ.ም)፡፡

የሼኽ ሁሴንን መወለድ ለአበልቃሲም የነገሯቸው ነብዩ መሃመድ መሆናቸውን ሐሊማ (1974፡10) እና Makonnin (2008 ዓ.ም፣5) ይገልጻሉ፡፡ Jeylan (2005)፣ Eliyas (2012)፣ Østebo (2015) እና Gemechu (2016) የሼኽ ሁሴንን መወለድ ለአበልቃሲም የነገረው ገብርኤል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እኔ በቃለመጠይቅ ወቅት በሰበሰብኩት መረጃ መሰረት የሼኽ ሁሴንን መወለድ የተናገረው መልዐኩ ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡ Jeylan (2005፡33) ሼኽ ሁሴን እንደሚወለዱ

[43] - ይህን ቃለ ግጥም ያገኘሁት በካሴት ከታተመ መንፈሳዊ ሙዚቃ ነው፡፡

ገብርኤል መናገሩ፣ የእሳቸውን ውልደት ከክርስቶስ ውልደት ጋር ያመሳስለዋል። ይህ የሼኽ ሁሴንና የክርስቶስ ውልደት ተመሳስሎ የሼኽ ሁሴንን ታላቅነት፣ በፈጣሪ መመረጥንና የእሳቸው መወለድ ለሰው ልጅ ያለውን ልዩ ጥቅም ያሳያል።

በቅዱስ ገብርኤልና በሼኽ ሁሴን መካከል በመልዕክት ልውውጥ ምክንያት የተፈጠረው ይህ ግንኙነት በሼኽ ሁሴን አማኞች ዘንድ ሶስት የተለዩ ባህርያት እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል። እነዚህም አንደኛ፣ በሼኽ ሁሴን የሚያምኑ የክርስትና እምነት ተከታዮች ከሌሎች መላእክት በተለየ ለገብረኤል የተለየ ፍቅር አላቸው። አብዛኛዎቹ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪ የሆኑ ክርስቲያኖች በኦርቶዶክስ ክርስትና ኃይማኖት ቀኖና መሰረት የወሩን 19ኛው ቀንና፣ አመታዊ የመታሰቢያ ቀናት የሆኑትን ታህሳስ 19 እና ሐምሌ 19 በልዩ ትኩረት አስበው ይውላሉ። ሁለተኛ፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪ የሆኑና የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች ሲምሉ (መሃላ ሲፈጽሙ) "ገብርኤልን" እያሉ እንደሆነ በመረጃ ስብሰባዬ ወቅት አስተውያለሁ። ይህን አይነት የመሃላ ሁኔታ ከዚህ በፊት የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ በሆኑ ግለሰቦች ዘንድ ሰምቼ አላውቅም። ሶስተኛ፣ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ሰኞ ዕለት የመልዐኩ ቅዱስ ገብርኤል የመታሰቢያ ቀን ነው።

በአብርሃማዊ ኃይማኖቶች (ክርስትና፣ እስልምና፣ ጁዲዝም፣ ባሃይና ሌሎች) ኃይማኖቶች አስተምህሮ ውስጥ መልዐኩ ቅዱስ ገብርኤል የአብሳሪነትና የመልዕክት አድራሽነት ሚና አለው። መንፈሳዊ ኃይል ከፈጣሪ ዘንድ ወደ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ሊላክ ሲል መንፈሳዊ መልእክቱን ለሚቀበለው ግለሰብ የሚናገረው ገብርኤል ነው። ይህም ገብርኤል ከሌሎች መላእክት በተለየ ከግለሰቦች ጋር መስተጋብር እንዳለው ያሳያል። በክርስትና ኃይማኖት አስተምህሮ የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ ለእናቱ ለቅድስት ማርያም ያበሰረው ገብርኤል ነው። በእስልምና ኃይማኖትም ለነብዩ መሃመድ ቅዱስ ቁርዓን ከሰማይ እንደሚወርድላቸው የነገራቸው ገብርኤል ነው። በሴኔጋል የቱባ መንፈሳዊ ስፍራ መስራች የሆኑት ሼኽ አሕመዱ ባምባ ምባኬ (1270-1346) በአካባቢው እስልምናን የሚያጠናክሩ ሙጃዲድ መሆናቸውን ፈጣሪ በመልአኩ ገብርኤል አማካኝነት መልዕክት እንደነገራቸው መታመኑን Ross (1996፣52) ይገልጻል።

**እሳቤ 2-** "ሼኽ ሁሴን ከፈጣሪ ዘንድ ልዩ ጸጋ የተሰጣቸው ናቸው።" ይህ እሳቤ እሳቸው ካላቸው ሰብዕና፣ አገልግሎት፣ ጸሎት ወይም ተመርጠው በመወለዳቸው ምክንያት ልዩ ጸጋ ከፈጣሪ የተሰጣቸው እንደሆነ ያሳያል። ይህ ልዩ ጸጋም ፈጣሪ ለሌላው ሰው ከሰጠው የተለየና የእሳቸው ብቻ የሆነ፣ በተሰጣቸው ጸጋም ከራሳቸው አልፈው ሌላውን የሚዋጁ፣ ጸጋቸው ለሌላውም መዳኛ የሚሆን፣ ጸጋቸው ከሳቸው በፊት ለነበረም ይሁን ከሳቸው በኋላ ለተፈጠረ ፍጡር ያልተሰጠ የእሳቸው ብቻ የሆነና የተለየ እንደሆነ ያሳያል። ፈጣሪ ለሼኽ ሁሴን ሰጥቷቸዋል ተብሎ የሚታመነው ልዩ ጸጋ ከሚገለጽባቸው ድርጊቶች መካከል የፈጸሟቸው ተዓምራት ናቸው።

የሼኽ ሁሴን ተዓምራት የሚጀምረው ገና በእናታቸው ማሕጸን ውስጥ ሳሉ እንደሆነ ይነገራል። ይኸውም እናታቸው የቀድሞ ባለቤታቸውን ፈተው ሼኽ ኢብራሂምን ባገቡበት ወቅት የቀድሞ ባለቤታቸው "ያረገዘችው ከእኔ ነው።" በሚል ግጭት ተነስቶ ጉዳዩ ሽማግሌዎች ጋር በቀረበበት ወቅት ነው። ይህንንም ተዓምር መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> የሼኽ ሁሴን እናት የቀድሞ ባላቸው 'ያረገዘችው ከእኔ ነው' ብሎ ሼኽ ኢብራሂምን ለሽማግሌዎች ይከሳቸዋል። ሽማግሌዎቹ ሁለቱንም ሲጠይቁ 'የእኔ ልጅ ነው፣ የእኔ ልጅ ነው' አሉ። ሼኽ ኢብራሂምም ለሽማግሌዎቹ 'ፍቀዱልኝና ልጥራው፤ የእኔ ልጅ ከሆነ ስጠራው አቤት ይላል።' አላቸው። ሽማግሌዎቹም ፈቅደው 'ጥራው' አሉት። ሼኽ ኢብራሂምም 'ሁሴን'፣ 'ሁሴን' ብለው ሲጣሩ፤ ሁሴን በእናቱ ማህጸን ውስጥ እያለ 'አቤት' አለ። ሽማግሌዎቹም የእሱ ልጅ እንደሆነ አረጋገጡ።[44]

በዚህ ሚት ውስጥ አራት ጉዳዮችን እናገኛለን። አንደኛ፣ ስለሼኽ ሁሴን እናት ማንነት ነው። እናታቸው የሼኽ ሁሴን አባት ከሆኑት ከሼኽ ኢብራሂም በፊት ሌላ ባል አግብተው የፈቱ መሆናቸውን ነው። ሁለተኛ፣ ሁሴን የሚለው የመጠሪያ ስም ለመጠሪያነት የወጣላቸው እሳቸው ከመወለዳቸው በፊት መሆኑን ነው። ሶስተኛ፣ የሼኽ ኢብራሂምን ልዩ ጸጋ የሚያሳይ ነው። አባታቸው "የእኔ ልጅ ከሆነ ስጠራው አቤት ይላል" ብለው አምነዋል። አምነውም "ሁሴን" ብለው ሲጠሩት በማህጸን ውስጥ ያለው ሁሴን "አቤት" በማለት ምላሽ ሰጠ። ይህ ደግሞ አባቱ ሼኽ ኢብራሂም ራሳቸው ልዩ ጸጋ እንዳላቸው ያሳያል። ልዩ ጸጋቸውም በማህጸን ያለ ጽንስ አንደበት አውጥቶ እንዲያናግራቸው የሚያስችል ነው። ወይም በማህጸን ውስጥ ያለው ጽንስ ከፈጣሪ በተሰጠው ልዩ ጸጋ መናገር እንደሚችል የሚያሳይ ነው። አራተኛ፣ ሼኽ

---

[44] - ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ ኢድሪስ እና አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም።

ሁሴን በእናታቸው ማህጸን ውስጥ ሆነው መናገራቸውን ያሳያል፡፡ ይህም ሚት ሼኽ ሁሴንና አባታቸው በፈጣሪ ዘንድ የተመረጡና የተለየ ጸጋ ያላቸው እንደሆኑ ያስረዳል፡፡

ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ወቅት ፈጣሪ የሰጣቸውን ልዩ ጸጋ ማሳየታቸውን የሚገልጽ ተመሳሳይ ሚት አለ፡፡ ይህም ሚት የሼኽ ሁሴን እናት እርጉዝ ሆና በአናጂና መንደር ስታልፍ "አላህ እዚህ ተወለድ ብሎኛል፣ የእኔ ስፍራ እዚህ ስለሆነ ልወለድ ብለው እናታቸው ማህጸን ውስጥ ሆነው እናታቸውን ጠየቁ፡፡ እናታቸውም እሺ አለች፡፡ ሼኽ ሁሴን ከእናታቸው ማህጸን ሲወጡ 'ረቢ አንዚልኒ ሙንዘላን ሙባረከን ወአንታ ኬይሩል ሙንዚሊን' እያሉ ነው፡፡›[45] የሚል ሚት አለ፡፡ ከማህጸን ሲወጡ የተናገሩትና በአረብኛ ቋንቋ የቀረበው አባባል ትርጉሙ 'ፈጣሪ ሆይ ከእናቴ ማህጸን ወደ መሬት በጸጋ አወራረድ አውርደኝ፡፡ አንተ ከጸጋ አውራጆች አንዱ ነህና፡፡' ማለት ነው፡፡

በዚህ ሚት ውስጥ አራት ጉዳዮችን እናገኛለን፡፡ አንደኛ፣ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርሱ በሚገኝበት አናጂና የተወለዱት በፈጣሪ ትዕዛዝ አማካኝነት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ሼኽ ሁሴን ከእናታቸው ማህጸን ሲውጡ መናገር ይችሉ እንደነበር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ካለው ተፈጥሯዊ የቋንቋ ለመዳ ባህርይ የተለየ ነው፡፡ እሳቸውንም የተለየ ተፈጥሯዊ ባህርይ እንደነበራቸው ያሳያል፡፡

ሶስተኛው፣ ሼኽ ሁሴን ፈጣሪን ያወቁት ወይም የፈጣሪን ችሎታ የተረዱት ካደጉ በኋላ በኃይማኖታዊ ትምህርት ሳይሆን በእናታቸው ማህጸን ውስጥ በጽንስነት ደረጃ ባሉበት ወቅት በደመነፍሳዊ ሂደት ነው፡፡ ይህም እሳቸው በፈጣሪ ተመርጠው እንደተፈጠሩና የእሳቸው የመፈጠር ምክንያት የፈጣሪ ልዩ እቅድ እንደነበረ ያሳያል፡፡ አራተኛ፣ ሼኽ ሁሴን ሲወለዱ የተናገሩት በአረብኛ ቋንቋ ነው፡፡ የአረብኛ ቋንቋ ደግሞ የእስልምና ኃይማኖትና የአረብ ባህል ማስፋፊያ ዋና መሳሪያ ነው፡፡ በቋንቋ ጥናት መሰረት የሰው ልጅ ቋንቋን የሚለምደው ከአካባቢው እንጂ በዘር ውርስ አይደለም፡፡ ነገር ግን በዚህ ሚት ሊተላለፍ የተፈለገው ጉዳይ ሼኽ ሁሴን የአረብ ዘር እንደሆኑ፣ የእስልምናን ኃይማኖት የተቀበሉት፣ የፈጣሪያቸውን ችሎታና ኃያልነት የተረዱት በእናታቸው ማህጸን እንዳሉ መሆኑን ነው፡፡

**እሳቤ 3-** "ሼኽ ሁሴን አማላጅም፣ አዳኝም ናቸው፡፡" ሼኽ ሁሴን ከፈጣሪ በተሰጣቸው ልዩ ጸጋ ምክንያት የሰው ልጅን ከአምላኩ ጋር ያገናኛሉ፣ በሰውና በፈጣሪ መካከል አገናኝ ድልድይ

[45] - አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ ኢድሪስ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

ሆነው ያገለግላሉ፣ ሰው ፈጣሪውን እንዳይረሳ፣ የፈጣሪውንም ትዕዛዝ እንዲያከብርና እንዲፈጽም ያደርጋሉ፣ ሰው ኃጽያት በመስራት ፈጣሪውን እንዳያስቀይም ይጥራሉ፣ በሰው ጥፋት ምክንያት ፈጣሪ ቁጣ እንዳይፈጽም ይለምናሉ እንዲሁም ሰውን ከፈጣሪ ጋር ያማልዳሉ፡፡ በዚህ እሳቤ ሼኽ ሁሴን የአማላጅነት ሚና አላቸው ማለት ነው፡፡ ይህን ሚናቸውን የሚገልጽ የእሳቸው መወድስ ቃል ግጥም አለ፡፡[46] ቃል ግጥሙም

አርሂብ ነብዬ

አርሂብ ነብዬ

አማላጅዬ፡፡

የሚል ነው፡፡ "አርሂብ" ማለት ይምጡ፣ ይግቡ ወይም እንኳን ደህና መጡ እንደማለት ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን ከፈጣሪ በተሰጣቸው ልዩ ጸጋና ችሮታ የሰውን ልጅ ከክፉ ነገር ይጠብቃሉ፣ ከሕመም ይፈውሳሉ፣ ጤናን ይሰጣሉ፣ ኃጽያትን ይሰርያሉ፣ ከሞት በኋላም ነፍስ በገነት ለዘለዓለም በደስታ እንድትኖር ያደርጋሉ፣ ሰውን ከፈጣሪ ጋር ያማልዳሉ፡፡ በዚህ እሳቤ ሼኽ ሁሴን ለሰው ልጅ የዋስ ጠበቃነትና የሙሉ ሀላፊነት ሚና አላቸው ማለት ነው፡፡

በሺዓት የእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ ልክ እንደሼኽ ሁሴን ቅዱስ ናቸው ተብለው የሚታመኑ ግለሰቦች የሰው ልጅን ከፈጣሪ ጋር የሚያማልዱ እንደሆኑ ይታመንባቸዋል፡፡ ይህ የአማላጅነት እሳቤም በሱኒ ዓለምም እንደ ሻሪፍ ወይም ሱፊስት ያሉት ይህንን ድርጊት የመፈጸም የመንፈስ ብቃት አላቸው፡፡[47] በክርስትና ኃይማኖትም ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የአስተምህሮ ክፍሎች የአማላጅነት እሳቤ አለ፡፡ እነዚህ ቅዱሳን ግለሰቦች የአምላክ የቅርብ ወዳጆችና በአምላክ የተወደዱ ("Befriended") እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በእስልምና የፍልስፍና ታሪክ ታዋቂ ከሆኑት ፈላስፎች መካከልም አል-ጋዛሊና ኢብን አራቢ የግለሰቦችን የቅዱሳንነት (Righteous) እና የመለኮታዊ ተመስጦ (Mystic) ባህርያት ትክክለኛ የኃይማኖት መንገድ እንደሆነ ያስተምራሉ (Fickeler, 2004፡ 253)፡፡

**እሳቤ 4-** "ሼኽ ሁሴን ለዘለዓለም ሕያው ናቸው፡፡" ሼኽ ሁሴን በአንድ ወቅት በምድር ላይ እንደ ሰው ሆነው፣ የሰው ባህርያትን ተላብሰው፣ እንደ ሰው ስጋ ለብሰውና እንደ ሰው ተወልደው የኖሩ መንፈስ እንጂ ሰው አይደሉም ተብሎ ይታመናል፡፡ ሼኽ ሁሴን ፈጣሪ ለሰው ልጅ መድሕንና አስተማሪ እንዲሆኑ የሰው ባህርይ አላብሷቸው በምድር ላይ ቆዩ እንጂ መንፈስ

[46] - በሉሌ መሃመድ አሊ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከቀረበ መንፈሳዊ ሙዙቃ የተወሰደ ነው፡፡
[47] - ስለሺዓት፣ ሱኒና ሱፊ የእስልምና አስተምህሮዎችና ፍልስፍናዎች በምዕራፍ 5 ተብራርቷል፡፡

ናቸው። በመሆኑም ሼኽ ሁሴን እንደ ሰው ምድር ላይ ስጋ ለብሰው ኖሩ እንጂ እንደ ሰው ሞተው አካላቸው መሬት አልተቀበረም፤ አረጉ እንጂ። እሳቸው በማረጋቸውም ለዘለዓለም ሕያው ናቸው። ለዘለዓለም ሕያው በመሆናቸውም ከሰው ልጅ ጋር ሁል ጊዜ አሉ።

ስርዓተከበራ ካሉት አምስት አላባውያን መካከል በስርዓተከበራው ላይ የሚታመነው መንፈሳዊ ኃይል (አካል) ወደ ሰማይ ያረገ (ያልሞተ) እንደሆነና በማህበረሰቡ ዘንድ ሕያው ሆኖ የሚኖር ተደርጎ መታመኑ እንደሆነ Cooke and Macy (2005፡52-53) ይገልጻሉ። በተመሳሳይም የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ሼኽ ሁሴን ወደ ሰማይ ማረጋቸውን ያምናሉ። ይህ እሳቤ ሼኽ ሁሴን እንደአምላክ (ፈጣሪ) መመልከትን የሚያሳይ ነው። ይህ የነገረ ተልዕኮ (Eschatological) አረዳድ የሼኽ ሁሴንን ዘለዓለማዊነት፣ ቅዱስነት፣ መለኮታዊ ኃያልነትና የመጨረሻ ተልዕኳቸው ሕያውነት እንደሆነ ያሳያል።

የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች የአምላክን እሳቤ ለሚወዷቸው ሼኽ ሁሴን ማጋራት ነው። ይህ አይነት የውሕደት እሳቤ የተለያዩ ባለጉዳዮችን ለማቀራረብ ከሚደረግ ፍላጎት የሚመነጭ ነው። ይህም ሁለት አይነት የእሳቤ ውሕደት ባህርይ አለው። አንደኛው፣ ኢ-አቻዊ ውሕደት (Syncretism of infidelity) ሲሆን፣ አቻ ያልሆኑ አካላትን በእኩል መመልከት ነው። ይህ የኢ-አቻዊነት ተመሳስሎ በአረብኛ "ኩፍር" ይባላል። ሁለተኛው፣ የሽርክና ተጋሪነት ውሕደት (Syncretism of polytheism) ሲሆን፣ የአንድ አምላክን ባህርይ ለሌላ አካል መስጠት ነው። እነዚህ ሁለት የውሕደት እሳቤዎች ሼኽ ሁሴንን ፍጹም ልዕለ ኃያል አድርጎ ከመቅረጽና ከጥልቅ ፍቅር የሚመነጩ ናቸው።

**እሳቤ 5-** "ሼኽ ሁሴን የፍጡራን ሁሉ አባት ናቸው።" ለሼኽ ሁሴን የሰው ልጅ ሁሉ እኩል ነው። የሰው ልጅ በኃይማኖት፣ በዘር፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በስልጣን፣ በአካባቢ፣ በአገርና በአሕጉር ደረጃ ያለው ልዩነት በእሳቸው ዘንድ ቦታ የለውም። እሳቸው ሁሉንም በአንድ ዐይን የሚያዩ፣ የሁሉም አባት ናቸው። የሼኽ ሁሴን አባትነት ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት፣ ለእጸዋት፣ ለግዑዝ አካላትና ለረቂቅ ፍጡራን ሁሉ ጭምር ነው።

በመሆኑም ሼኽ ሁሴን የፍጡራን ሁሉ አባት ናቸው። በፍጡራን ሁሉ አባትነታቸውም አንዱን ከሌላው አያለያዩም፤ አያዳሉም። ሼኽ ሁሴን የሁሉም ፍጡራን አባትነትን የሚገልጽና ከጎሽ ጋር የተያያዘ ሚት አለ። ይህ ሚትም በአንድ ወቅት አዳኞች ጫካ ውስጥ ጎሽ አግኝተው ሊገድሉት ሲሉ፣ ጎሹ የሼኽ ሁሴንን ስም ጠርቶ አድኑኝ ይላል። ሼኽ ሁሴንም የጎሹን

የድረሱልኝ ጥሪ ሰምተው ከአዳኞች እንዳዳኑት የሚገልጽ ነው፡፡ ይህንን ሚት የሚገልጽ ቃል ግጥም መኖሩን ዳንኤል (1984) ይገልጻል፡፡ ቃል ግጥሙም፤

Gafarsaan akkana jedhee qeyyee kaboobanee

Abbaa na dhaqqabee kana jabuu na qabee

Nuur Huseen baalen kanatti dhaqqabaa.

ትርጉሙም፡-

ጎሹ እንዲህ አለ መንደር ውስጥ ገብቶ

አባቴን ስጠራ ገዳዩ ደርሶብኝ

የባሌው ኑር ሁሴን መጡና አዳኑኝ፡፡

ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይም በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴን መንገድ ይሄዳሉ፡፡ በመንገዳቸውም ላይ ጂና የሚባል ወንዝ ያጋጥማቸውና ይሻገራሉ፡፡ ወንዙን እንደተሻገሩ ከወንዙ ውኃ የሚጠጡ ከብቶች ነበሩ፡፡ ከብቶቹም የሚጠጡትን ውኃ አቋርጠው ያለባቸውን ችግር ለሼኽ ሁሴን ነገሯቸው፡፡ ይህንንም ሚት የሚገልጽ ቃል ግጥም አለ፡፡[48] ቃል ግጥሙም፤

Gaafa laga jiinaa maal siin jedhe hooriin

Gurra kiyya laaltaa aabaa natii gorii

ትርጉሙም፡-

የጂናን ወንዝ የተሻገሩ ዕለት ከብቶች ምን አሉዎት

አባቴ ጎራ ይበሉና ኑሮዬን ይመልከቱ፡፡ ማለት ነው፡፡

**እሳቤ 6-** "ሼኽ ሁሴን በኃይማኖትና በመንፈስ ጽኑ ናቸው፡፡" ሼኽ ሁሴን ለ40 ዓመታት ያህል በአይናገኜ ገደል ውስጥ በጸሎት እንደኖሩ ይነገራል፡፡ የአይናገኜ ገደል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከዋናው የግምብ አጥር በግምት 3 ኪ.ሜትር ርቀት አለው፡፡ እሳቸውም በአይናገኜ ገደል ውስጥ በኖሩበት አመታት የተለያዩ ተአምራትን ማድረጋቸው ይነገራል፡፡ ከእነዚህ ተዓምራዊ ድርጊቶች መካከል ለ40 ዓመታት ያህል ግንባራቸውን እሾህ እንዲወጋው አድርገው ይሰግዱ እንደነበር፣ ለ40 ዓመት ያህል ሲርባቸው የአርጌሳ ቅጠል ይበሉ እንደነበር፣ ሲጠማቸው ጨው በውኃ በጥብጠው ይጠጡ እንደነበር፣ በሚቀመጡበት ዋሻ ውስጥ

[48] - በካሴት ከታተመ መንፈሳዊ ሙዚቃ የተወሰደ ቃል ግጥም፡፡

እሳቸውን ሊበሉ የመጡ እንስሳትን ረግመዋቸው እዛው ድንጋይ ሆነው እንደቀሩ ይነገራል፡፡[49] በአይናገኜ ገደል በሚገኝ ዋሻ ውስጥ የእባብ፣ የአዞና የዘንዶ ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ግን ምንነታቸውን መለየት የሚያዳግቱ የድንጋይ ቅርጾች ይገኛሉ፡፡



*ፎቶ፣ 1፡- በአይናገኜ ዋሻ ውስጥ የሚገኙና የአውሬ ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ድንጋዮች በከፊል፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

እነዚህ በፎቶ ግራፉ ላይ የሚታዩት ቅርጾች ሼኽ ሁሴን በዋሻ ውስጥ በሚኖሩበት ወቅት በሰይጣን ተልከው ሊበሏቸው የመጡ አውሬዎች እንደሆኑ ይታመናል፡፡ አውሬዎቹም በሼኽ ሁሴን እርግማን ወደ ድንጋይነት ተለውጠው እዛው የቀሩ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ የድንጋይ ቅርጾቹን በቅርብ እንዳየሁት የደረቀ አውሬ ይመስላሉ፡፡ በዚህ ዋሻ ውስጥ በሚገኙ የድንጋይ ቅርጾች ላይ የሚነገረው ይህ ሚትም በሼኽ ሁሴን አማኞች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አለው፡፡

አይናገኜ የሚለው ስያሜ የምን ቋንቋ ቃል እንደሆነና ትርጉሙ ምን ማለት እንደሆነ ላገኝ አልቻልኩም፡፡ ነገር ግን በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ "አይናኒያ" የሚል ቃል አለ፡፡ አይናኒያ ማለት ወደ ሲያል መግቢያ ድልድይ ነው፡፡ ይህ ድልድይም በእባብ ይመሰላል፡፡ ከዚህ መረጃ አይናኒያ በእባብ የሚመሰል ድልድይ ወይም እባብ ያለበት የሲያል መግቢያ ነው ማለት ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚገኘው አይናገኜ ዋሻ ስያሜ "አይናኒያ" ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በአይናገኜ ዋሻ መግቢያው ላይ ወደ ድንጋይነት ተቀይረው ነው ተብለው

---

[49] - አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ እድሪስ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

የሚታመኑ እባብ መሰል ቅርጾች ይገኛሉ፡፡ ዋሻውን እንደ ሲያል በመውሰድ ልክ እንደ አይናኒያ በሲያል መግቢያ ላይ እንዳለ የእባብ ድልድይ በአይናገኜም መግቢያ ላይ እባብ መሰል ቅርጾች አሉ፡፡

**እሳቤ 7-** "ሼኽ ሁሴን ፍጡር ሁሉ እንደሚያከብራቸው፡፡" ሼኽ ሁሴን የፍጡራን ሁሉ አባት እንደሆኑ ይታመናል፡፡ የሁሉም አባት በመሆናቸውም ፍጡራን ሁሉ ያከብሯቸዋል፡፡ ፍጡራኑም ለእሳቸው ያላቸውን ክብር ለመግለጽ የተለያዩ ድርጊቶችን እንደፈጸሙ የሚገልጹ ሚቶች አሉ፡፡ እነዚህም ሚቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ከአናጂና ቀበሌ በደቡብ አቅጣጫ ጬንቆርሳ የሚባል ቦታ አለ፡፡ በዚህ ቦታ በርካታ ቁጥር ያላቸው ድንጋዮች መስመር ሰርተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ድንጋዮች በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴን የዋቤ ሸበሌን ወንዝ ዱንቡሬ በሚባል ቦታ በኩል ተሻግረው ወደ አናጂና እየመጡ ነበር፡፡ እሳቸውም ጬንቆርሳ የሚባል ቦታ ሲደርሱ በአካባቢው የነበሩ ድንጋዮች በአንድ ቦታ መስመር ሰርተው 'እንኳን ደህና መጡ አባታችን፡፡' እያሉ ሰገዱላቸው፡፡[50] በስፍራው የሚገኙ ድንጋዮች በአንድ ቦታ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ድንጋዮቹ ሲታዩም እስካሁን ድረስ የሚሰግዱ የሚመስል ቅርጽ አላቸው፡፡

ውኃ ወደ ዝቅተኛ ቦታ እንጂ ወደ ከፍታ ቦታ አይፈስም፡፡ በጋሰራ ዞን ውስጥ በሚገኝ አካባቢ የዋቤ ሸበሌ ወንዝ የተለየ ባህርይ ይይዛል፡፡ ይህም የተለየ ባህሪው የዋቤ ሸበሌ ወንዝ ወደ ከፍታ ቦታ መፍሰሱ ነው፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው የዋቤ ሸበሌ ወንዝ ሼኽ ሁሴንን ሲከተል እንደሆነ ይነገራል፡፡ በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴን በመንገድ ሲሄዱ ወንዙ ከኋላቸው ይከተላቸዋል፡፡ እሳቸውም ከፍ ያለ ቦታ ሲደርሱ ወደ ከፍታው ይወጣሉ፡፡ በዚህም ጊዜ ወንዙ ተከትሏቸው ወደ ከፍታ ቦታ ወጣ፡፡ ከዚህን ጊዜ ጀምሮም የዋቤ ሸበሌ ወንዝ በዛው ቦታ መፍሰስ መጀመሩ ይነገራል፡፡

**እሳቤ 8-** "ለሼኽ ሁሴን ፍጡር ሁሉ ይታዘዛቸዋል፡፡" ሼኽ ሁሴንን ፍጡር ሁሉ ያከብራቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ፍጡር ሁሉ ስለሚያከብራቸውም የእሳቸውን ትዕዛዝ ይፈጽማል፡፡ ግዑዝ ፍጡራን ለእሳቸው መታዘዛቸውን የሚገልጹ ሚቶች አሉ፡፡ እነዚህም ሚቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

---

[50] - አቶ አብዱልናስር አህመድና አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

የደደላ ተራራ ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በግምት 4 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ይህ ተራራ ከርቀት ሲታይ የተኛ አንበሳ የሚመስል ቅርጽ አለው። ይህ ተራራ ስያሜውን ያገኘው ዶዶላ ከሚባለው ከተማ እንደሆነ ይነገራል። ለዚህም ምክንያቱ ተራራው በሼኽ ሁሴን ትዕዛዝ ከዶዶላ ተነስቶ በስፍራው እንደተቀመጠ ከሚነገረው ሚት ነው። የዶዶላ ከተማ በምዕራብ አርሲ ዞን የሚገኝ ሲሆን ከአናጂና ቀበሌ በግምት 300 ኪ.ሜትር ርቀት አለው። ይህን ተራራ በሚመለከት የሚነገረው ይህ ሚት በአካባቢው ማህበረሰብ የሚታመን ነው። ይህ እምነት እንዳለ ሆኖ ተራራው ስያሜውን ያገኘው ደደላ የሚባሉ ሴት ይኖሩበት ከነበረው ዶዶላ ከተማ ያፈሩትን ንብረት ሁሉ ሰብስበው በተራራው ላይ መኖር በመጀመራቸው እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ።[51]

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ 15 መስኪዶች አሉ። ከእነዚህ መስኪዶች መካከል ሼኽ ሁሴን ራሳቸው እንዳስገነቧቸው የሚታመኑ የባላና የዙቅጡም መስኪዶች ይገኛሉ። የባላ መስኪድ አሁን ላይ አገልግሎት አይሰጥም። የዙቅጡም መስኪድ የእድሳትና የማስፋፊያ ስራ ተሰርቶለት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። የዙቅጡም መስኪድ ግንባታ ላይ የሚነገሩ ሁለት ሚቶች አሉ። አንደኛው፣ የመስኪዱ ግንባታ ሐሙስ ከረፋዱ በ 9 ሰዓት ተጀምሮ አርብ ከጠዋቱ በ5 ሰዓት ተጠናቆ፣ የአርብ ጁምዓ ስግደት እንደተሰገደበት የሚገልጽ ነው። ይህ ሊሆን የቻለውም በሼኽ ሁሴን ጸሎትና ልዩ ኃይል እንደሆነ ይታመናል። ሁለተኛው፣ በመስኪዱ የውስጠኛው ክፍል ግድግዳ ላይ ትልቅ የድንጋይ ቋጥኝ አለ። ይህን ድንጋይ እኔ እንደለካሁት 3 ሜትር ርዝመት አለው። የድንጋዩ ውፍረት 50 ሴንቲሜትር ነው። የድንጋዩ ጎን የተሸፈነ በመሆኑ የጎን ቁመቱን መለካት አልቻልኩም። የጎን ቁመቱን መለካት ባልችልም መረጃ ሰጪዎቹ 3 ሜትር እንደሚገመት ነግረውኛል።[52] ይህ አንድ ወጥ ቋጥኝ ድንጋይ በዙቅጡም መስኪድ ግድግዳ ላይ ተጋድሞ ይገኛል።

[51] - አቶ አብዱልናስር አህመድና አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም።
[52] - ሼኽ መሐመድ ሐጂ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን፣ 2007 ዓ.ም።



*ፎቶ 2፣ በዙቅጡም መስኪድ ግድግዳ ላይ የሚገኝና 3 ሜትር ርዝመት ያለው አንድ ወጥ ረጅም የድንጋይ ቋጥኝ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

በዚህ ድንጋይ አመጣጥ ላይ የሚነገር ሚት አለ። ይህም መስኪዱ የተገነባበት ድንጋይ የመጣው ከአይናገኜ ገደል ነው። በገደሉም ለግንባታ የሚሆን ድንጋይን በመምረጥ በሰው ጉልበት ከአይናገኜ ገደል 3 ኪ.ሜትር በሚርቀውና መስኪዱ በሚገነባበት ስፍራ ይመጣል። ይህን ትልቅ ድንጋይ ለአገልግሎት እንዲውል ከቀረጹት በኋላ ተሸክመው ወደ ግንባታው ቦታ ለማምጣት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ሞከሩ። ነገር ግን አቃታቸው። ሼኽ ሁሴን ድንጋዩን እዛው ትተውት እንዲመለሱ ሰዎቹን አዘዟቸው፣ ሰዎቹም ትተውት ተመለሱ። በማግስቱ ጠዋት ድንጋዩ ሊቀመጥበት በታሰበው ቦታ ላይ ተስተካክሎ ተቀምጦ ተገኘ። ይህም የሆነው ሼኽ ሁሴን ድንጋዩ እንዲመጣ አዘውት እንደሆነ ይነገራል።[53]

**እሳቤ 9-** “ሼኽ ሁሴንን ያስቀየመ፣ ሊጎዳ ያሰበ ወይም የናቀ እጅግ ከባድ ቅጣት ይቀጣል።” ሼኽ ሁሴን በፈጣሪ ዘንድ የተከበሩና ፍጡራንን ሁሉ የሚያድኑ አባት እንደሆኑ ይታመናል። ነገር ግን ይህንን የእሳቸውን ልዩ ኃይልና ጸጋ ባለመረዳት ወይም በመናቅ በእሳቸው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ወይም እሳቸውን ሊያሳንስ ይችላል። ይህን የሚያደርግ ማንኛውም ፍጡር ከፍተኛ ቅጣት እንደሚቀጣ ይታመናል። በተለያየ ወቅት በሼኽ ሁሴን ላይ ክፋት ያሰቡና እሳቸውን የናቁ እንዴት እንደተቀጡ የሚገልጹ ሚቶች አሉ። እነዚህም ሚቶች የሚከተሉት ናቸው።

---

[53] - አቶ ኑማን መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 26 ቀን፣ 2009 ዓ.ም።

አበልቃሲም በፈጣሪ ትዕዛዝ የሼኽ ሁሴንን ጸጉር እንዲላጩ በተላኩበት ወቅት ‘እኔ የ40 ነብያትን ጸጉር የላጨሁ ነኝ። እንዴት የዚህን ሕጻን ፀጉር ላጭ ብሎ አላህ ይልከኛል?’ ብለው በፈጣሪ ላይ ቂም ይይዛል። ፈጣሪም የአበልቃሲምን ቂም መያዝ ባወቀ ጊዜ እጅግ አዘነ። አበልቃሲም ወደ ፈጣሪ ሲጸልዩ ፈጣሪም “በሕይወት ሁሉ የሰራኸውን ሽሬዋለሁ። ካሁን በኋላ የአንተን ጸሎት አልቀበልም።” አለው። አበልቃሲምም በሁኔታው እጅግ አዘኑ። አበልቃሲምም ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በግምት 10 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኝ ተራራ ሄዱ። በተራራው ላይም ለ40 አመታት በልቅሶና በጸሎት ፈጣሪ ይቅር እንዲላቸው ለመኑ። ፈጣሪም ጸጸታቸውን አይቶ ይቅር አላቸው። እሳቸው ለ40 አመታት የጸለዩበት ተራራም በስሙ አበልቃሲም ተራራ ተባለ።[54]

ከአናጂና ቀበሌ ወደ አርሲ ዞን ሴሩ በሚወስደው የመኪና መንገድ ላይ፣ በዋቤ ሸበሌ ወንዝ ሸለቆና በአይናገኜ ገደል ስር ሰው የሚመስሉ የድንጋይ ቅርጻቅርጽ አሉ። በሴሩ አካባቢ የሚገኙት በቡድን የሚጓዙ ሰዎች የሚመስሉ የድንጋይ ቅርጾች ናቸው። እነዚህ ቅርጾች እንዴት እንደተፈጠሩ የሚነገሩ ሁለት የተለያዩ ሚቶች አሉ። አንደኛው፣ ሼኽ ሁሴን በስፍራው በሚኖሩበት ወቅት እሳቸውንና የእሳቸውን ተማሪዎች ለማጥፋት የመጡ ጦረኞች በሼኽ ሁሴን እርግማን ባሉበት ወደ ድንጋይነት እንደተለወጡ ይነገራል። ሁለተኛው፣ ሼኽ ሁሴን ከተማሪዎቻቸው ጋር መንገድ በሚሄዱበት ወቅት የኢቱ ጎሳ ሰዎች ሰደቧቸው። እሳቸውም ረገሟቸው። እነሱም ባሉበት ወደ ድንጋይነት ተለወጡ። የሚል ነው።[55]

በዋቤ ሸበሌ ወንዝ ሸለቆ አንዲት ነፍሰጡር ሴትና አንዲት ሴት ቆመው የሚመስል የድንጋይ ቅርጽ አለ። ይህም ሁለት ሴቶች በምስጢር ክፉ ነገር ሲመካከሩ ሼኽ ሁሴን የልባቸውን ክፋት አይተው ረገሟቸው። በእሳቸው እርግማንም ሁለቱ ሴቶች ወደ ድንጋይነት እንደተቀየሩ ይታመናል። በአይናገኜ ገደል የሚገኘው ደግሞ የበሬ ምስል የሚመስል የድንጋይ ቅርጽ ነው። ይህም አንድ በሬ ሼኽ ሁሴንን ለመውጋት ተንደርድሮ ሲመጣ ረገሙት። በእሳቸው እርግማንም በሬው ወደ ድንጋይነት እንደተለወጠ ይታመናል።[56]

---

[54] - ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ እድሪስ እና አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም።
[55] - አቶ አብዱልናስር አህመድና አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም።
[56] - ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ አቶ አብዱልናስር አህመድና አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም።

**እሳቤ 10-** "ሼኽ ሁሴን በማንኛውም ሰዓትና ቦታ የሰው ስጋ ለብሰው በአካል ይመጣሉ።" ሼኽ ሁሴን በማንኛውም ሰዓትና በማንኛውም ስፍራ የሰው አካል ለብሰው ወይም ሰው ሆነው እንደሚመጡ ይታመናል። እሳቸው ሰው መስለው በአካል ሲመጡ የተለያየ ባህርይ በመላበስ ነው። ከእነዚህም ባህርያት መካከል እብድ መስለው፣ ለማኝ መስለው፣ ሰውነቱ የቆሳሰለ ሕመምተኛ መስለው ወይም ለዐይን የሚያጸይፍ ሰው መስለው እንደሚከሰቱ ይታመናል። ሼኽ ሁሴንም እብድ ወይም ለማኝ ሰው መስለው በመምጣት ገንዘብ እንዲሰጧቸው ሰዎችን ይጠይቃሉ ወይም መልዕክት ተናግረው ይሄዳሉ ተብሎ ይታመናል። እሳቸው በዚህ መልክ መጥተው የፈለጉትን የፈጸመ ሰው ትልቅ በረከት ያገኛል ተብሎ ይታመናል።

ይህ የሼኽ ሁሴን በአካል መከሰት ላይ የሚነገረው ሚት ወደ ስፍራው የሚመጣ አማኝ የሚያምነውና የሚቀበለው ነው። ይህ መሆኑም በእሳቸው የሚያምኑ ሰዎች ለማኝ፣ እብድ፣ በሽተኛ ወይም ለሰው እይታ የሚከብድ (የሚያስጸይፍ) ግለሰብ ካዩ ወይም እርዳታቸውን የፈለገ ከመሰላቸው በሙሉ ፍላጎትና በቅንነት ይረዱታል። የእርዳታቸውም ምክንያት "ይህ ግለሰብ ሰው ላይሆን ይችላል ምናልባትም ሼኽ ሁሴን ሊሆኑ ይችላሉ።" ብለው ማመናቸው ነው። ለመንፈሳዊ ጉዞ ወደ ስፍራው የሚሄዱ ሰዎች የተቸገሩ ሰዎችን ለመርዳት የሚያሳዩት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ ነው። ከእርዳታ በተጨማሪ በስፍራው የሚመጣ ሰው ለማኝም፣ በሽተኛም፣ እብድም ይሁን ወይም ለእይታ የሚከብድ ሰው ይሁን ይከበራል። ይህ የሼኽ ሁሴን ባህርይ እንደሆነ የሚነገረው ሚት በስፍራው እርስበርስ የመረዳዳት ፍላጎት ከፍተኛ እንዲሆን ምክንያት መሆኑን ያመለክታል።

ይህ በሼኽ ሁሴን ላይ የሚነገረው ሚት በተመሳሳይ ሁኔታም በሰዒድና ከዲር ላይም ይነገራል። ሰዒድና ከዲር ትልቅ የአላህ ባርያና ወልይ እንደሆኑ ይታመንባቸዋል። እሳቸውም በአካል ሰው መስለው በመምጣት "ገንዘብ ስጠኝ፣ እዘለኝ፣ አብላኝ ወይም አጠጣኝ" ይላሉ ተብሎ ይታመናል። በገነት ውስጥ የሚገኝ 'ማኡ ሃያት' የሚባል ውኃ አለ። ይህንንም ውኃ የጠጣ ለዘለዓለም ይኖራል ተብሎ ይታመናል። ሰዒድና ከዲር ይህንን የገነት ውኃ እንደጠጡ ይነገራል። የሰዒድና ከዲር መታሰቢያ ዕለት ቅዳሜ ነው። ቅዳሜ በእሳቸው ስም ቡና ይፈላል፣ ጫት እየተቃመ ይጸለያል፣ ይለመናል። በዕለቱ የተጎሳቆለ፣ የቆሸሸ ወይም በሽተኛ የሆነ ሰው የጠየቀው እርዳታ ሁሉ ይፈጸምለታል። ምክንያቱም ቆሻሻ ልብስ ለብሶ፣ ተጎሳቁሎ ወይም በሽተኛ መስሎ የመጣው ሰዒድና ከዲር ሊሆን ይችላል ተብሎ በመታመኑ ነው። በድሬ ሼኽ

ሁሴን መካነ ቅርስም ቅዳሜ ዕለት የከዲር ቀን በመሆኑ በእሳቸው ስም ይጸለያል። ቀኑም በልዩ ሁኔታ ይታሰባል።

የአበልቃሲም ተራራ ሙሉለሙሉ በቁጥቋጦ የተሸፈነ ነው። ተራራው በቁጥቋጦ ቢሸፈንም ከተራራው አናቱ ጀምሮ እስከ ተራራው እግር ስር ምንም አይነት ቁጥቋጦ ያልበቀለበት ደረቅ መሬት አለ። ይህ ደረቅ መሬት ከላይ ወደታች በቀጥታ መስመር የተሰመረ ይመስላል። ይህ መስመር ወደ ተራራው ቀረብ ያለ ሰው በቀላሉ ሊያየው የሚችል ነው። በተራራው ላይ ያለው መስመር እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ በአካባቢው የሚነገር ሚት አለ።

ይህም በተራራው አናት ላይ ላዚሙል ባህሪ የሚባሉ ሰው ይኖሩበት ነበር። ላዚሙል ባህሪ የሼኽ ሁሴን ተማሪ የነበሩ ናቸው። ከእለታት አንድ ቀን ላዚሙል ተራራው አናት ላይ ሆነው ወደታች ሲመለከቱ ስድስት ሰዎች በተራራው ስር ቁጭ ብለው ሲወያዩ ያያሉ። እሳቸውም፣ ቁጭ ብለው የሚወያዩት ሼኽ ሁሴንና ሌሎች አምስት ነብያት እንደሆኑ አስተዋሉ። ላዚሙልም ከተራራው በእግራቸው ወደታች ቢወርዱ እንደማይደርሱባቸው አወቁ። እሳቸውም ሊያገኟቸው ስለቸኮሉ ተራራውን እየተንሸራተቱ ወረዱ። በተራራው መሃል ለመሃል መስመር የሰራና ከላይ ወደታች የተሰመረ የሚመስለው ደረቅ መሬትም እሳቸው የተንሸራተቱበት እንደሆነ ይነገራል። ይህንን ሚት የሚገልጽ ቃል ግጥም አለ።[57] ይኸውም፡-

Lazim Bahriin qilee isini dhaaqaan

Qileen hin dararree, maqooleen hin dabaaree.

ትርጉሙም፡-

ላዚም ባህሪ ለአንተ (ለሼኽ ሁሴን) ሲል ከተራራ ላይ እራሱን ወረወረ

ተራራው እንቅፋት ሳይሆንበት ከውይይታችሁ ተቀላቀለ።

ማለት ነው። በዚህ ግጥም ላዚም (ላዚሙል ባህሪ) ተራራውን ተንሸራተው በውይይቱ ላይ መድረሳቸውን ይገልጻል። አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቼ ግን እሳቸው ተራራውን ተንሸራተው እንደወረዱ ሼኽ ሁሴንና ሌሎች ነብያት ከዐይናቸው መሰወራቸውን ይገልጻሉ።[58]

---

[57] - የሙዳ በዓል በመካነ ቅርሱ ሲከበር ከቀረበ መንፈሳዊ ሙዚቃ የተወሰደ።

[58] - አቶ አብዱልናስር አህመድና አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም።

**እሳቤ 11-** "ሼኽ ሁሴን በግለሰቦች አማካኝነት የትንቢት መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡" በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ወደ ፊት የሚፈጸምን ድርጊትን የሚያውቁና ትንቢት የሚናገሩ ግለሰቦች (Deviners) አሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ምልክቶችን፣ ድርጊቶችን፣ ሁኔታዎችን በጥልቅ በመረዳት ወይም በልዕለሰብዓዊ ኃይል መረጃ ሰጪነት ትንቢት ይናገራሉ፡፡ ግለሰቦች ትንቢት እንዲናገሩ ሼኽ ሁሴን ያዟቸዋል፤ መልዕክቱን ይነግሯቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ በዓል ወቅት ለበዓል በመጣው ሕዝብ ፊት ትንቢት የሚናገሩ ግለሰቦች አሉ፡፡

እነዚህ ግለሰቦች የሰይጣን መንፈስ የሚያናግራቸውና የቅዱስ መንፈስ የሚያናግራቸው በሚል በሁለት ይመደባሉ፡፡[59] የሰይጣን መንፈስ የሚያናግራቸው ትንቢት ተናጋሪዎች የሚባሉት ሰይጣን (ጂኒ) መልዕክት የሚልካቸው፣ በሰይጣን መንፈስ በመመራት የጥንቆላ ስራ የሚሰሩ፣ እርኩስ መንፈስ በላያቸው ላይ ያረፈባቸው ወይም የራሳቸውን የግል ፍላጎት የሚያንጸባርቁ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት የላቸውም፡፡ ግለሰቦቹም ሕዝቡ ፊት ትንቢት ለመናገር ሲሞክሩ፣ ሕዝቡ በተቃውሞ ያስቆማቸዋል፡፡

ቅዱስ መንፈስ የሚያናግራቸው ትንቢት ተናጋሪዎች የሚባሉት ፈጣሪ (አላህ) መልዕክት የሚልካቸው፣ ሼኽ ሁሴን መልዕክት የሚልካቸው፣ ቅዱስ መንፈስ በላያቸው ላይ ያረፈባቸው ወይም በጸሎትና በምህላ ከፈጣሪ ጋር የሚገናኙ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው፡፡ የሚናገሩትም ትንቢት ትክክለኛና ሙሉለሙሉ የሚፈጸም እንደሆነ ይታመናል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በአካባቢው፣ በዞኑ፣ በክልሉ፣ በአገሩ ወይም በዓለምአቀፍ ደረጃ ወደ ፊት የሚፈጸሙ ነገሮችን በትንቢት መልክ ለሕዝቡ ይናገራሉ፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚገኘው ሕዝብ የትንቢቶቹን እውነታነት በሙሉ ልቡ ይቀበላል፡፡ ትንቢቶቹም የሙዳ በዓላትን ለማክበር በስፍራው የሚገኝ ሕዝብ ወደ ፊት የሚከሰትን ነገር ዛሬ ላይ ሆኖ እንዲያውቅ ይረዳዋል፡፡ ይህ በመሆኑ መንፈሳዊ ተጓዦች ከሌላው የአካባቢያቸው ነዋሪ ሕዝብ በተለየ ስለ ወደፊቱ የማወቅ ወይም የመረዳት እድል አላቸው፡፡

**እሳቤ 12-** "የሼኽ ሁሴን የመንፈስ ልዕልና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡" የሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ልዕልና እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ በአናጂና በኖሩበት ዘመን ትልልቅ መንፈሳዊ ሰዎች፣ ነብያትና ወልዮች ወደ ስፍራው እንደመጡና ከእሳቸው ጋር እንደተገናኙ ይነገራል፡፡ ሼኽ ሁሴንን ለማግኘት ወደ ስፍራው የመጡ ነብያትና ወልዮች የመጡበትን መንገድ በሁለት ከፍሎ ማየት

---

[59] - ሼኽ ከዲር መሀመድ፣ አናጂና ነሐሴ 29 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

ይቻላል፡፡ አንደኛው መንገድ ወደ ስፍራው በመንፈስ የመጡ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በአካል ወደ ስፍራው የመጡ ናቸው፡፡

በመንፈስ ወደ ስፍራው እንደመጡና ከሼኽ ሁሴን ጋር እንደተገናኙ የሚነገርላቸው ነብዩ መሐመድ ናቸው፡፡ ነብዩ መሐመድ የእስልምና ኃይማኖት መስራች፣ ቁርዓን ከሰማይ የወረደላቸውና በአላህ ዘንድ የተመረጡ የመጨረሻው ነብይ ናቸው፡፡ ነብዩ መሐመድ በመንፈስ መጥተው ሼኽ ሁሴንን ባርከውና መርቀው እንደተመለሱ ይታመናል፡፡ ነብዩ መሐመድ በስፍራው በመጡበት ወቅት የሰገዱበት እንደሆነ የሚታመን ድንጋይ በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ ውስጥ ይገኛል፡፡ ድንጋዩ ጥቁር፣ ጠፍጣፋ ቅርጽ ያለውና ሰፋ ያለ ነው፡፡

ሼኽ ሁሴን ነብዩ መሐመድን ለመጎብኘት ወደ ሳዑዲአረቢያ መካ መሄዳቸው ይነገራል፡፡ እሳቸው ወደ መካ የሄዱበት በዋሻ ውስጥ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመካነ ቅርሱ ውስጥ በሚገኝ አይናገኜ ገደል ውስጥ አንድ ዋሻ አለ፡፡ ይህ ዋሻ ከድሬ ሼኽ ሁሴን እስከ መካ የሚያድርስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ነገር ግን የዋሻው ርቀት ምን ያህል እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ማንም ሰው ገብቶበት እንደማይታወቅ መረጃ ሰጪዎቼ ገልጸውልኛል፡፡ ሼኽ ሁሴን መካ ደርሰው ሲመለሱ ይዘውት እንደመጡ የሚታመንና "ደራራ በሹ" (Daarara Bashuu) በሚል ስያሜ የሚታወቅ ጥቁር ድንጋይ አለ፡፡ ይህ ጥቁር ድንጋይ ዙሪያውን በታጠረ ቅጽር ግቢ ዋናው የመግቢያ በር ስር ይገኛል፡፡

ዙሪያው በአጥር  የታጠረው ቅጽር ግቢ 12 መግቢያ በሮች አሉት፡፡  ከእነዚህ የቅጽር ግቢው በሮች መካከል ትልቁና ዋናው መግቢያ "ከራ ጉዶ" (Karra Guddoo) በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡[60] "ከራ ጉዶ" በኦሮምኛ ትልቅ መግቢያ እንደማለት ነው፡፡ ከራ ጉዶ ውበት ባላቸው የተለያዩ ቅርጾች የተሰራ በመሆኑ ከሌሎች በሮች በተለየ ልዩ የኪነ ህንጻ ጥበብ የሚታይበት ነው፡፡ በራፉም 3 ሜትር ከፍታና 2.15 ሜትር ስፋት አለው (Hailemelekot and Mulugeta,  2015:23)፡፡

---

[60] - መግቢያ በሩ ከዚህ ስያሜ በተጨማሪ ዙቅጡም በሚል ስያሜም ይጠራል፡፡



*ፎቶ፡- 3 የግምብ አጥሩ ዋና መግቢያ (ከራ ጉዶ) እና በስተቀኝ በኩል የሚገኘውን ደራራ በሹ የሚያሳይ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

12 ቁጥር በርካታ ኃይማኖታዊ ውክልና አለው፡፡ ከእነዚህ ውክልናዎች መካከል፣ በምድር ዙሪያ አድማስና ናጌብ የተባሉ ሁለት ተራራዎች ሲኖሩ፣ እያንዳንዳቸው 12 መስኮቶች አሏቸው፡፡ 12 ሊቀመላዕክት አሉ፡፡ 12 ሐዋርያት አሉ፡፡ የብርሃን መጠን በ12 ይከፈላል፡፡ 12 የብርሃንና 12 የጨለማ ሰዓታት አሉ፡፡ በኮከብ ቆጠራ (Zodiac Astrology) ስርዓት 12 ኮከቦች አሉ፡፡ 12 ቁጥር ካለው መንፈሳዊ ውክልናዎች በመነሳት የመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ 12 በሮች እንዲኖሩት የተደረገው ሆነ ተብሎ ይመስላል፡፡ ይህም የስፍራውን መለኮታዊነት ለማመላከት ነው፡፡

በመካነ ቅርሱ የሚገኘው አጥር መግቢያ በሮች በተለይ በምድር ዙሪያ ያሉት አድማስና ናጌብ የተባሉ ተራራዎች እያንዳንዳቸው 12 መስኮቶች ጋር የተያያዘ ይመስላል፡፡ ደራራ በሹ በሚል ስያሜ የሚታወቅ ጥቁር ድንጋይ ከቅጽር ግቢው ከዋና የመግቢያ በር በቀኝ በኩል መሬት ላይ ተተክሎ ይገኛል፡፡ መንፈሳዊ ተጓገሮችም ይህንን ድንጋይ እየተሳለሙ ወደ ቅጽር ግቢ ውስጥ ይገባሉ፡፡

ሼኽ ሁሴንን ለመጎብኘት ከባግዳድ እንደመጡ የሚነገርላቸውና የቃድሪያ ስርዓት መስራች የሆኑት ሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒ አንዱ ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴንና ሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ ስለኃይማኖት በሚጨዋወቱበት ወቅት በመሃላቸው ግጭት ተፈጠረ፡፡ የግጭቱም መንስኤ ‘‘እኔ በመንፈስ እበልጣለሁ፣ አትበልጥም’’ የሚል ፉክክር ነበር፡፡ በዚህ

ወቅት ሼኽ ሁሴን አንድ ተአምር ማድረጋቸው ይነገራል፡፡ ይህንንም ተአምር መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> ሼኽ ሁሴንና ሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒ በመንፈስ ‹እኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ› ብለው ፉክክር ገጠሙ፡፡ ሼኽ ሁሴንም፣ ሼኽ አብዱልቃዲርን ‹መጀመሪያ አንተ የመንፈስህን ሀይል አሳየኝ› አሏቸው፡፡ ሼኽ አብዱልቃዲርም ከሼኽ ሁሴን ዐይን ተሰወሩና ‹የት እንደሆንኩኝ ፈልገህ አግኘኝ› አሏቸው፡፡ ሼኽ ሁሴንም ‹አይቼሀለሁ በሲኦል ውስጥ ነህ› አሏቸው፡፡ አውቀሃል ብለው ከሲኦል ወጡ፡፡ ተራው የሼኽ ሁሴን በመሆኑ እሳቸውም ከሼኽ አብዱልቃድር ዐይን ተሰወሩና ‹የት ነኝ ፈልገህ አግኘኝ፡፡› አሏቸው፡፡ ሼኽ አብዱልቃዲርም ቢፈልጉ ቢፈልጉ ማግኘት አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም ‹በቃ አላገኘሁህም ከተደበክበት ውጣ አሏቸው፡፡› ሼኽ ሁሴንም ‹እዚህ ነኝ› አሉና ከሼኽ አብዱልቃዲር የአገጭ ጺም ውስጥ ቅማል ሆነው ገብተው ነበር ወጡ፡፡ አብዱልቃዲርም የሼኽ ሁሴንን የመንፈስ ኃይል የበላይነት አመኑና ይቅርታ ጠየቋቸው፡፡[61]

ይህ ሚት የሚያሳየን የተለያዩ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒ ወደ ስፍራው መጥተው ከሼኽ ሁሴን ጋር በአካል መገናኘታቸውን፣ የሼኽ ሁሴን የመንፈስ ልዕልና ከሼኽ አብዱልቃድር በላይ መሆኑንና ፈጣሪ ለሼኽ ሁሴን ከማንም በላይ ትልቅ ስጦታ የቸራቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ በሼኽ ሁሴን ሰብዕና ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ሚቶች ውስጥ 40 ቁጥር ተደጋግሞ ይነሳል፡፡ ሼኽ ሁሴን 40 ዓመት በአይናገኜ ዋሻ ጸልየዋል፡፡ አበልቃሲም ፈጣሪያቸውን በማስቀየሙ ለ40 ዓመታት በተራራ ላይ ጸሎት አድርጓል፡፡ አበልቃሲም የ40 ህጻናትን ጸጉር ላጭተዋል፡፡ 40 ቁጥር በእስልምና፣ በክርስትና፣ በዋቄፈና እንዲሁም በአይሁድ ኃይማኖቶች ውስጥ ልዩ መንፈሳዊ ውክልና አለው፡፡ ይህ ቁጥር በርካታ ውክልና ቢኖረውም ከጾምና ጸሎት ጋር በተያያዘ ክርስቶስ ለ40 ቀንና ለ40 ሌሊት በጁዲያን በረሃ ጾሟል፡፡ ሙሴ ለ40 ዓመታት በሲናይ ተራራ በጸሎት ቆይቷል፡፡ ነብዩ መሃመድ ለ40 ቀን ጾመዋል፡፡ ነብዩ መሃመድ በ40ኛው አመታቸው ነው ጅብሪል የተገለጠላቸው፡፡ ነብዩ መሐመድ በአስማትና በጥንቆላ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ለ40 ቀናት ቢጸልይም ይቅር እንደማይባል መናገራቸውን በሀዲስ መጽሐፍ ላይ ተገልጿል፡፡

በአንዳንድ የአገራችን አካባቢዎች ከመኖሪያ ቤት የመጣ እንግዳ 40 እርምጃ ያህል መሸኘት አለበት ተብሎ ይታመናል፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኃይማኖት ወንድ ሕጻን ልጅ ሲወለድ ክርስትና የሚነሳው በ40 ቀኑ ነው፡፡ በኦሮሞ የዋቄፈና ኃይማኖት ወንድም ይሁን ሴት ሕጻን

---

[61] - ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ እድሪስ እና አቶ ኑማን ሼኽ ሙሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

ሲወለዱ ወደ ገልማ ተወስደው የሀመቺሳ ስርዓት የሚፈጸምላቸው በተወለዱ በ40ኛ ቀናቸው ነው። በኦሮሞ የገዳ ስርዓት በአባትና በልጅ ገዳዎች መካከል የ40 ዓመት ልዩነት አለ። ከራባ ዶሪ የሚከተለው የገዳ መደብ አባል የሚሆኑት እድሜያቸው 40 ዓመት ሲሞላ ነው።

40 ቁጥር በእነዚህ ኃይማኖቶች የመስዋዕት፣ የቁርጠኝነት፣ የጸጸት፣ የስቃይ፣ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የመሸጋገር፣ የመታደስና የመንጻት ምልክት ነው። በድሬ ሼኽ ሁሴንም ይህ ቁጥር ከጸሎት፣ ከጾምና ከመታደስ ጋር ተያይዞ ይገኛል። በመሆኑም በዚህ ቁጥር አማካኝነት እንደሌሎች ነብያት ሁሉ የሼኽ ሁሴንን ተመሳሳይ ጸሎት፣ ቁርጠኝነት፣ መስዋዕትነት እንዲሁም የአበልቃሲምን መንጻት፣ መታደስና ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ መሸጋገርን ያሳያል።

በአበልቃሲም፣ በነብዩ መሃመድና በሙሴ ሕይወት ውስጥ የአምላክ ምላሽ የሚገኘው ከ40 ዓመት በኋላ ነው። ከ40 ዓመት በኋላ አምላክ አበልቃሲምን ይቅር አላቸው። ለነብዩ መሃመድ ጅብሪልን ላከለት። ለሙሴም አስርቱ ትዕዛዝ ያለበትን ጽላት ከሰማይ አወረደለት። ይህም ሙሉ የመንፈስ ጽዳት የሚመጣው፣ የውስጥ ችግራችን በሚወገደው፣ ወይም "ልብ በ40 ዓመት" እንደሚባለው ሙሉ ልብ የምንገዛውና ብቁ የምንሆነው በ40 አመት ሊሆን ይችላል።

አንድ ሀይማኖት፣ ባህል ወይም ማህበረሰብ እውነተኛ ድርጊቶች ናቸው ብሎ የሚያምናቸው ጉዳዮች በሌላው ዘንድ ሚቶች ሊሆኑ ይችላሉ (Leeming, 2010፡8)። ከላይ የቀረቡት እሳቤዎች የድሬ ሼኽ ሁሴን ማህበረሰብ በሀይማኖቱ፣ በእምነቱና በሼኽ ሁሴን ማንነት ላይ ባለው ማህበራዊ፣ ባህላዊና ስነ-ልቡናዊ እይታ መነሻነት እውነት ነው ብሎ የሚያምናቸው ናቸው። እነዚህ እውነት ናቸው ብሎ የሚያምናቸው ሁነቶች የማንነቱ መሰረቶች ናቸው። በመሆኑም በሼኽ ሁሴን ማንነት ላይ የሚነገሩና የእሳቸው ወዳጆች የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት እውነተኛ ድርጊቶች ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው እሳቤዎች የማህበረሰቡን ማንነትና እምነት የሚገልጹና የሚቀርጹ ናቸው።

### 4.2.2 የሼኽ ሁሴን ሰብዕናዊ እሳቤዎች ከተቃዋሚዎቻቸው አንጻር

ከሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ውጪ ያሉና እሳቸውን እንደ ቅዱስነት የማይቀበሏቸውና የሚቃወሟቸው አሉ። እሳቸውን ከሚቃወሙ አካላት መካከል የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታይ ሙስሊሞች በዋናነት ይጠቀሳሉ። በሰለፊያ የእስልምና አስተምህሮን በሚከተሉ ግለሰቦች ዘንድ

ሼኽ ሁሴን የሞቱና ምንም መንፈሳዊ ጥቅም የሌላቸው፣ መካነ ቅርሱም አስፈላጊ ያልሆነና መውደም ያለበት፣ የሙዳ በዓልም ከአላህ ጋር ለሚደረግ የክብርና የመንፈስ መጋራት (ሽርክ) የሚፈጥር ክፉ ድርጊት እንዲሁም ወደ ስፍራው የሚሄዱ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎችን "ኢ-አማኒያን" እንደሆኑ አድርገው ይመለከታሉ፡፡[62] በመሆኑም ለሰለፊያዎች መካነ ቅርሱም ሆነ የሙዳ በዓላት ምንም ዋጋ የሌላቸውና ከእስልምና ኃይማኖት ውጪ ናቸው፡፡

በክርስትና ኃይማኖት ስር በሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አማኞች ዘንድ ሼኽ ሁሴን የሚገለጹት በአሉታዊ ገጽታ ነው፡፡ የሶስቱም ኃይማኖቶች ተከታዮች ሼኽ ሁሴንን፣ መካነ ቅርሱን፣ የሙዳ በዓላትንም ሆነ ወደ ስፍራው የሚሄድን መንፈሳዊ ተጓዥ የሚገልጹበት መንገድ እጅግ በጥላቻ ነው፡፡ ስፍራው ላይ የሚካሄድ ስርዓተከበራ እንደ "ባዕድ አምልኮ"፣ ስፍራውም "የክፉ መንፈስ መሰባሰቢያ"፣ ወደ ስፍራው የሚሄድንም ሰው "ክፉ መንፈስ በላዩ ላይ ያረፈበት" እንደሆነ አድርገው ይገልጻሉ፡፡ በእነዚህ ሶስት የክርስትና ኃይማኖት ክፍሎች በሼኽ ሁሴንና በስፍራው ላይ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑ ያመሳስላቸዋል፡፡

ሶስቱም የክርስትና ኃይማኖት ያላቸው አመለካከት ተመሳሳይ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የክርስትና ኃይማኖት በሼኽ ሁሴንና በስፍራው ላይ የተለየ አመለካከት ስታራምድ ይስተዋላል፡፡ ይህም አስተሳሰብ ሼኽ ሁሴን ክርስቲያን ናቸው፤ ስፍራውም የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቀደምት ይዞታ ነበር የሚል ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የመነጨው ሼኽ ሁሴን እና አቡነ አኖሪዎስ አንድ ናቸው ከሚል እምነት ነው፡፡ አቡነ አኖሪዎስ በተለያዩ የአገሪቷ አቅጣጫዎች የክርስትናን ኃይማኖትን ያስፋፉ የአቡነ ተክለኃይማኖት 12 ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ናቸው (Taddesse,1972:176)፡፡[63] ከአቡነ ተክለኃይማኖት ደቀ መዛሙርት ውስጥ ሁለት አቡነ አኖሪዎስ የሚባሉ አሉ፡፡ ሁለቱ የሚለዩትም አቡነ አኖሪዎስ ትልቁና አቡነ አኖሪዎስ ትንሹ በሚል ነው፡፡ አቡነ አኖሪዎስ (ትልቁ) ወደ ባሌ ሄደው ክርስትናን ያስፋፉት እንደሆኑ ዳንኤል (2006 ዓ.ም፡336) ይገልጻል፡፡

ሼኽ ሁሴንና አቡነ አኖሪዎስ እንዴት ሊያያዙ እንደቻሉ ዳንኤል (2006 ዓ.ም፡336-340) አቡነ ጎርጎሪዎስ (1974 ዓ.ም)ን እና ጥላሁን መኮንን (1990 ዓ.ም)ን በመጥቀስ አብራርቷል፡፡

[62] - ስለሰለፊያ አስተምህሮ ምንነትና በመካነ ቅርሱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በምዕራፍ 5 እና 9 በስፋት ተብራርቷል፡፡

[63] - የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት 17 እንደሆኑ የሚገልጹ መረጃዎች መኖራቸውን ዳንኤል (2006 ዓ.ም፡41) ይገልጻል፡፡

ለዚህም ጉዳይ የሚነሱት ነጥቦች ሼኽ ሁሴን የሚጠሩበትና "ኑር ሁሴን" የሚለው የቁልምጫ ስም "አኖሪዎስ" ከሚለው ስም የመጣ ነው። አቡነ አኖሪዎስ ወደ አካባቢው ሲመጡ በቦታው ላይ ብርሃን እንደወረደላቸውና በዚህም ምክንያት ስፍራው "ሠናይ ብርሃን" ብለው ሰየሙት፣ አቡነ አኖሪዎስ በስፍራው ገዳም መስርተዋል፣ የአቡነ አኖሪዎስ የቀብር ስፍራ በትክክል ባይታወቅም በድሬ እንደሆነ ይታመናል የሚሉ ናቸው።

አብዛኛው የአውሮፓና የእስያ ፈላስፎች ዘንድ አፍሪካን "ጨለማ" አሕጉር ሕዝቦቿም "ኋላ ቀር"፣ "አመክንዮ አልባ" እና "መኃይም" አድርገው ይመለከታሉ። ልክ እንደ እነዚህ ፈላስፎች እሳቤ ሁሉ የሼኽ ሁሴን ተቃዋሚዎች በተለይ የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለእስልምና ኃይማኖት ታሪክ ምንም የማይጠቅምና እስልምናዊ ያልሆነ አድርገው ይመለከቱታል። የሙዳ በዓል ለማክበርና ለመዘየር ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚሄድን ሕዝብ "ኋላ ቀር"፣ "አመክንዮ አልባ" እና "መኃይም" አድርገው ይመለከታሉ።

ይህ አይነት እሳቤ የሚመነጨውም በሁለት አመለካከቶች ነው። አንደኛው፣ የዓለም አቀፍ ኃይማኖቶች (እስልምና እና ክርስትና) በተፈጠሩበት አካባቢ የነበራቸውን ባህልና ታሪክ እንዳለ ይዘው መቀጠል አለባቸው ከሚል አመለካከት የመጣ ነው። እነዚህ ዓለም አቀፍ ኃይማኖቶች በአፍሪካ አሕጉር ሲስፋፉ እንዴት ከነባር ኃይማኖቶችና እምነቶች ጋር ውሕደት ፈጥረው እንደቆዩ ካለመረዳት ነው። የዓለም አቀፍ ኃይማኖቶች በአፍሪካ አሕጉር ሲስፋፉ ቀደም ሲል የነበራቸውን ባህል በአፍሪካው ባህል በመቀየር፣ አፍሪካዊ መልክ ይላበሳሉ። ይህ ደግሞ እነዚህ ኃይማኖቶች እንዲስፋፉና ለረጅም ዘመናት ሕልውናቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ያስቻላቸው ባህርይ ነው።

አፍሪካ የተለያዩ ሕዝቦችና ባህሎች ግንኙነት የፈጠሩበት አሕጉር ነው። አፍሪካ የእስልምናን አስተምህሮ ሲቀበል እንደወረደ፣ በጣም አንጊና አማላይ አድርጎ ሳይሆን ከራሱ ነባር ባህል ጋር አቀራርቦ ነው( Lewis, 1966፡58-67)። የእስያና የአውሮፓ አሕጉራት እስልምናን ሲቀበሉ ከነባሩ ባህል ጋር በከፍተኛ ደረጃ አስተሳስረው (Synthesis) ነው። በአፍሪካ ግን እስልምና ሲስፋፋ ከነባሩ ባህል ጋር በውሕደት (Syncretist) ነው። ይህ የውሕደት ነባራዊ ሁኔታ በኢትዮጵያም ባለው የእስልምና ኃይማኖት የመስፋፋት ባህርይ እንደሆነ Trimingham (1952) ይገልጻል።

ይህ አይነት ባህርይ በእስልምና ብቻ ሳይሆን የክርስትና ኃይማኖት በኢትዮጵያ ሲስፋፋ ያለው ባህሪም እንደሆነ Ullendorff (1960) ይገልጻል። ሁለተኛው ደግሞ ከራስ እይታና በራስ መነጽር

ትክክለኛነት ከማየትና ከመፈረጅ የመጣ ግላዊ ማንጸሪያ ነው፡፡ ይህ አይነት አመለካከት በአውሮፓ ተኮር የማንጸሪያ ስልት (Euro-centric perspective) እና ግለተኮር የማንጸሪያ ስልት (Ethno-centric) መሰረት በማድረግ የእስልምናን ኃይማኖት ለማጥናትና ለመረዳት ከሚፈልጉ የዘርፉ ምሁራን የመነጨ ነው፡፡

እነዚህ አመለካከቶች ጽንፍነክ ፍረጃ (Extreme prejudice) ናቸው፡፡ እነዚህ ጽንፍነክ የፍረጃ አመለካከቶች በአፍሪካ አሕጉርም ሆነ በኢትዮጵያ ያለውን የእስልምና ኃይማኖት የመስፋፋት ታሪክ፣ አፍሪካዊያንም ሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለእስልምና ኃይማኖት መመስረትና መስፋፋት ያደረጉትን አስተዋጽኦ፣ እስልምና በአፍሪካና በኢትዮጵያ ያለውን መሰረትና የአተረጓጎም ቅጥ (Mode of interpretation) በቅርበት ካለማጥናት የሚመነጩ ናቸው፡፡ በመሆኑም በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ ያለውን የእስልምና ኃይማኖትና የተከታዮቹን አጠቃላይ ገጸ-ትባሬ (Eschatology) በማጥናትና ከነባር ባህሎች ጋር ያለውን የውሕደት ባህርይ በመለየት የአውሮፓዊ አስተሳሰቦችን መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ዋና ቁልፉ ለአፍሪካ የእስልምና ኃይማኖት ጥናት የአፍሪካ ተኮር የማንጸሪያ ስልት (Afro-centric perspective) መሰረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 4.3 የሼኽ ሁሴን ባህርያትና ትዕምርታዊ ውክልና

ሼኽ ሁሴን በተከታዮታቸውና በአፍቃሪዎቻቸው ዘንድ ወልይ፣ የፈጣሪ ባሪያ፣ የፈጣሪ ወኪል፣ እንደሰው በምድር ላይ የኖሩ ግን ሰው ያልሆኑ፣ ለችግር ጊዜ ደራሽ፣ አዳኝ፣ ከፈጣሪ ልዩ ጸጋ የተሰጣቸው ናቸው ተብለው እንደሚታመኑ ከላይ ተመልክተናል፡፡ አማኞች እነዚህን የሼኽ ሁሴንን የተለያዩ ሰብዕናዊ እሳቤዎች ለመግለጽ የተለያዩ ትዕምርቶችንና አገላለጾችን ይጠቀማሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ሼኽ ሁሴን "መድኃኒት" ናቸው፡፡ ሼኽ ሁሴን ለተቸገረ መፍትሄን፣ ለታመመ ጤናን፣ ለደኸየ ሀብትን የሚሰጡ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ባህርያቸው መድኃኒት፣ መድኃኒቴ፣ የዓለም መድኃኒት፣ የሰው ልጅ መድኃኒት በሚል ይወደሳሉ፡፡ ይህንንም የሚገልጽ ቃል ግጥም አለ፡፡[64] ቃል ግጥሙም፡-

Allahu Arahim Abbiyoo

Baare namaa saffisu

Madihaanitii madaa namaa fayyisu

---

[64] - ኡሌ መሃመድ አሊ በሙዳ በዓል ወቅት በመካነ ቅርሱ ካቀረበው መንፈሳዊ ሙዚቃ የተወሰደ፡፡

ትርጉሙ፡-

አላሁመ-እርሐም አባዬ

የሰው ቁስል የሚያድን መድኃኒት ኖት።

ማለት ነው። "አላሁመ-እርሐም" ማለት በአረብኛ "አላህ ሆይ ለሼኽ ሁሴን ቸሩ ምህረትህን ለግሰው።" ማለት ነው። ሼኽ ሁሴን "እኔን ያፈቀረኝ ሁሉ ከአላህ ምህረትን ይለምንልኝ" ብለው ኑዛዜ ተናግረዋል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም በጸሎት ወቅት፣ በሙዳ በዓል ላይ፣ በመንፈሳዊ ሙዚቃዎች ቃል ግጥም እንዲሁም በዘወትር ንግግር ውስጥ "አላሁመ-እርሐም ኑር ሁሴን" ("አላህ ሆይ ለሼኽ ሁሴን ቸሩ ምህረትህን ለግሰው።") የሚል አባባል የተለመደ ነው።

ሼኽ ሁሴን "ጀት" ናቸው። እሳቸው ለተቸገረ ፈጥነው የሚደርሱ፣ ስማቸው በተጠራበት ሁሉ የሚገኙ ናቸው ተብሎ ይታመናል። ይህም ባህርያቸው የጦር አውሮፕላን የሆነው የጀት ተምሳሌት እንዲሰጣቸው ሆኗል። በተጠሩበት የዓለም ቦታ ሁሉ በፍጥነት ይደርሳሉ።

ሼኽ ሁሴን "ባህር" ናቸው። ባህር ሰፊ ነው። ባህር ሁሉን በውስጡ የሚይዝ ነው። ባህር ሁሉን ቻይ ነው። ባህር የታጋሽነት ተምሳሌት ነው። ሁሉን ቻይ ወይም ታጋሽ ለማለት በአማርኛ ፈሊጣዊ ንግግር "እከሌ ሆዱ ባህር ነው።" ይባላል። ሼኽ ሁሴንም ሁሉን ያዥ፣ ሁሉን አቃፊ፣ ታጋሽና ቻይ እንደሆኑ ይታመናል። በዚህ እምነትም የሼኽ ሁሴን አንዱ የቁልምጫ ስም "ባህረ ባሌ" ነው። እሳቸውንም በዜማ ሲያወድሱ "ባህረዎ" በማለት ነው። ባህረዎ፣ ባህር የሆኑት እንደማለት ነው። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከወኑ የሙዳ በዓላት ወቅት ከሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች መካከል አንዱ ባሮ ነው። ባሮ የሚለውም ስያሜ ባህር ከሚለው የእሳቸው ባህርይ መሰረት ያደረገ እንደሆነ ይነገራል።[65]

ሼኽ ሁሴን "ፍትሃዊ" ናቸው። እሳቸው በሰዎች መካከል ባለ የዘር፣ የኃይማኖት፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና መሰል ደረጃዎች ልዩነት አያደርጉም። መድሎ የለባቸውም፣ የሰው ልጅ ሁሉ በእሳቸው ፊት እኩል ነው። ይህንንም ለመግለጽ "በሼኽ ሁሴን ፊት ሁሉም በአንድ እንቅብ ይቀርባል።" የሚል አባባል ከእሳቸው አፍቃሪዎች አንደበት መስማት የተለመደ ነው። እንቅብ አነስተኛ መጠን ያለው የሰፌድ አይነት ነው። በአንድ እንቅብ መቅረብም ሁሉም እኩል መሆኑን ለመወከል ነው።

[65] - ሼኽ መሐመድ ሐጂ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 25 ቀን 2009 ዓ.ም።

ሼኽ ሁሴን "የሁሉም ፍጡር" ናቸው። እስካሁን ወደ ምድር የመጡ ነብያትና ወልዮች የራሳቸው ስጦታ (ጸጋ) አላቸው። በስጦታቸውም በአካባቢያቸው ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥረዋል። ለምሳሌ፤ ነብዩ ሙሴ የተላከው ለእስራኤል ሕዝብ ነው። ጸጋውም የኦሪት ሕግን ማስተማር ነው። ኢየሱስ የተላከው ለእስራኤል ሕዝብ ነው። ጸጋውም ክርስትናን ማስተማር ነው። ነብዩ መሐመድ የተላኩት ለመዲናና ለአካባቢው ሕዝብ ነው። ጸጋቸውም እስልምናን ማስተማር ነው። ሁሉም ነብያትና ወልዮች የራሳቸው ተልዕኮና ጸጋ እንዳላቸው ሁሉ ሼኽ ሁሴንም የራሳቸው ተልዕኮና ጸጋ አላቸው ተብሎ ይታመናል። የሼኽ ሁሴን ተልዕኮ ለሰው ልጅና ለሌሎችም ፍጡራን ነው። ጸጋቸውም ፍጡራንን ሁሉ ማዳን፣ ከክፉ ነገር መጠበቅ ነው። ፍጡራንን ሁሉ ያለ አድሎ በእኩል ዐይን ማየት ነው። ይህንን የሚገልጽም

ሼኽ ሁሴን የሁሉ ናቸው

እስላም ክርስቲያን አይሉም እሳቸው።

የሚል ቃል ግጥም አለ።[66] በተመሳሳይም

አይሉም እሳቸው እስላምና አማራ

አስራ ሁለት ጅስሚ ከሆነ ጡሃራ።

የሚል ቃል ግጥም አለ። በዚህ ቃል ግጥም "አማራ" የሚለው ቃል ክርስቲያን ለማለት ነው። በአካባቢው የክርስትና ኃይማኖት ተከታዮችን አማራ በሚል መግለጽ የተለመደ ነው። "ጅስሚ" ማለት አካል ነው። የሰው ልጅ 12 አካል አለው። "ጡሃራ" ማለት ንጹሕ ማለት ነው። ይህ ቃል ግጥም ንጹሕ ሰው እስከሆነ ድረስ ሼኽ ሁሴን ሙስሊም፣ ክርስቲያን በሚል አይለዩም የሚል ትርጓሜ አለው። ለዚህም ይመስላል ሼኽ ሁሴን የሰው ልጅም፣ የእንስሳትም፣ የእጸዋትም አባት ናቸው የሚባለው።

ሼኽ ሁሴን "የሁሉም፣ ሁሉም የሼኽ ሁሴን" ነው። ይህ የሁሉምነትን እሳቤ Gadamer (1976) "ጥሪ" ("Adressing") በሚል ይገልጸዋል። ጋደመር ጥሪ የሚለውን እሳቤ ሲያብራራ መንገድ ላይ ስንሄድ የአዛን (አላህን የማወደስ ወይም የመጥራት ዜማ) ድምጽ ስንሰማ ጥሪው ለእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ነው። የኃይማኖቱ ተከታዮችም የአዛኑ ድምጽ ይጠራቸዋል። ምክንያቱም እነሱን ስለሚመለከት። ከእስልምና ኃይማኖት ውጪ ያለ ግለሰብ የአዛኑን ድምጽ

[66] - በመካነ ቅርሱ በሙዳ በዓል ወቅት ከቀረበ መንፈሳዊ ግጥም የተወሰደ።

ምናልባትም እንደውም ላይሰማው ይችላል፡፡ ጽምጹን ቢሰማም ጥሪው ለእሱ ስለላልሆነ ልቡ አይደነግጥም፡፡ በክርስትናውም የቤተክርስቲያን ደወል ወይም ቅዳሴ በተመሳሳይ ነው፡፡

በጋደመር እሳቤ የሼኽ ሁሴን ጥሪ የሚደርሰው ለሁሉም ፍጡር ነው፡፡ ለሰው ልጅም፣ ለእንስሳትም፣ ለአጸዋትም ጭምር፡፡ የእሳቸው ጥሪ ለሁሉም ኃይማኖት ተከታይ ነው፡፡ ጥሪው ለሙስሊሙም፣ ለክርስቲያኑም፣ ለዋቄፈታውም ለሁሉም ነው፡፡ ይህ የሼኽ ሁሴን ባህርይ ሁሉን አቃፊ፣ ሁሉን ሰብሳቢ፣ ሁሉን ጠባቂ ያደርጋቸዋል፡፡ ለሼኽ ሁሴን ሁሉም የ"እኛ" እንጂ "የእኛ እና የእነሱ" (we - they) አይነት አስተሳሰብ የለም፡፡ ፍጡር ሁሉ የሼኽ ሁሴን ነው፤ ሼኽ ሁሴን የሁሉ ፍጡር ናቸው፡፡ ይህ ባህሪያቸውም ሼኽ ሁሴን የአብሮነት፣ የእኩልነት፣ የጋራነትና የእኛነት ሻምፒዮን ናቸው፡፡

ሼኽ ሁሴን "ኦዳ" ናቸው፡፡ ኦዳ የዛፍ አይነት ነው፡፡ የኦዳ ዛፍ ሳይንሳዊ የቤተሰብ መጠሪያ "ሲካሞር" (Sycamore) ነው፡፡ በሲካሞር የቤተሰብ ስም የሚታወቁ የዛፍ አይነቶች የቅድስና ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በቅዱስ ቁርዓን፣ በመጽሐፈ ሔኖክ የሲካሞር ቤተሰብ ስለሆኑት የዛፍ ዘሮች ተጽፏል፡፡ ይህ ዛፍም በክርስትና፣ በእስልምና፣ በቡድኃ ሀይማኖቶችና በግብጽ ሚት የቅድስና ስፍራ አለው (Ross, 1966፡171)፡፡ የሲካሞር የዛፍ አይነት ያለውን ኃይማኖታዊ ውክልና Ross (1966) የገለጸበት መንገድ በጣም አስገራሚና ለኃይማኖት ጥናት ጠቃሚ ጥቆማ የሰጠ ነው፡፡ ይህም አዳምና ሔዋን በገነት የበሉት እጸበለስ የሲካሞር ዛፍ ፍሬ መሆኑን፣ ፍሬውንም ከበሉ በኋላ ሀፍረተ ስጋቸውን የሸፈኑት በሲካሞር ዛፍ ቅጠል መሆኑን፣ በቡድኃ ኃይማኖት ለቡድኃ መንፈስ ቅዱስ የተገለጸለት በሲካሞር ዛፍ ስር መሆኑን እንዲሁም በግብጽ ሚትም የሲካሞር ዛፍ የ"ዕውቀት ዛፍ" በሚል እንደሚጠራ ይገልጻል፡፡

በሲካሞር የዛፍ ቤተሰብ ውስጥ የሚመደበው የኦዳ ዛፍ ተምሳሌትነት ብዙ ነው፡፡ ኦዳ ቅርንጫፉ በጣም ሰፊ ቦታን የሚይዝ፣ ግንዱ በጣም ወፋፍራም፣ ስሮቹ በጣም ረጃጅም ናቸው፡፡ ይህንን ትልቅ ዛፍ የሚፈጥሩት የዛፉ ፍሬዎች ደግሞ በጣም ትንንሽ ናቸው፡፡ በመሆኑም ኦዳ ከትንሽ ተነስቶ ትልቅ የመሆን ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል (ሰሎሞን፣2002 ዓ.ም፡14)፡፡ በኦዳ ዛፍ ግንድ ላይ ያለው ፈሳሽ ለጸረተባይ መድኃኒትነት ያገለግላል፡፡ በመሆኑም በኦዳ ግንድ ላይ ትላትል አያርፍበትም፡፡ ይህም የኦዳ ዛፍ የ"ንጽሕና" ተምሳሌት ተደርጎ እንዲወሰድ ምክንያት ሆኗል፡፡

ኦዳ ሰፊ ቦታን የሚይዝ ጥላ ስላላው በስሩ ይታረፋል፣ እርቅ ይፈጸማል፣ ስብሰባ ይደረጋል፣ መንፈሳዊ ስርዓተከበራዎች ይፈጸማሉ። ከእነዚህ ባህላዊ እሳቤዎች በተጨማሪ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ ላይ የኦዳ ዛፍ በምልክትነት ይገኛል። ሼኽ ሁሴን ኦዳ ናቸው ማለት፣ የኦዳ ባህርይ አላቸው ማለት ነው። ሼኽ ሁሴን እንደ ኦዳ ሰብሳቢ ናቸው። ጥላ ናቸው። ሁሉን አቃፊ ናቸው። የሰላም አባት ናቸው። የእርቅ አባት ናቸው። የዕውቀት አባት ናቸው። የንጽሕና ተምሳሌት ናቸው። ማረፊያ ናቸው። እርኩስ ነገር የማይጠጋቸው መንፈስ ንጹሕ ናቸው። ለማለት ነው።

ሼኽ ሁሴን "በጣም ታጋሽና ለውሳኔ የማይቸኩሉ" ናቸው። ሼኽ ሁሴን ፈጣንነታቸውና ችኮላቸው የተቸገረ ሰውን ለማዳን ነው፤ በፍጥነት ከችግሩ ለመታደግ ነው። ነገር ግን እሳቸውን ቅር ላሰኘ ወይም እየሰራው ያለው ስራ መጥፎ ለሆነ ግለሰብ ወይም በሼኽ ሁሴን ስም የተረገመን ሰው ለመጉዳትና እርምጃ ለመውሰድ እጅግ ይዘገያሉ። ለዚህም ይመስላል "ሼኽ ሁሴን ለማዳን እንጂ ለመጉዳት አይቸኩሉም።" የሚል አባባል ከአፍቃሪዎቻቸው አንደበት መስማት የተለመደ ነው።[67] ከዚህ ባህርያቸውም የተነሳ ብዙን ጊዜ ሰዎች በፍጥነት እንዲሆን የሚመኙትን ክፉ ነገር፣ በሰዎች ላይ እንዲደርስ የሚፈልጉትን አደጋ ወይም እርግማን ቶሎ አልፈጸም በማለቱ ቅር ይሰኛሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አንዳንድ ግለሰቦች አልፎአልፎ አላስፈላጊ ባህርያትን ያንጸባርቃሉ። በዚህን ወቅት በብዙ ሰው አዕምሮ ውስጥ የሚመላለሰው ጥያቄ "ሼኽ ሁሴን ለምን ይታገሳል የሚል ነው።" ይህንንም ጥያቄ የሚመልሱት "የሼኽ ሁሴንን ትዕግስተኛነትና እንዴት ልጆቼን ልጉዳ ብለው አዝነው ነው።"[68] በማለት ነው። የሼኽ ሁሴን ትዕግስት ገደብ የለሽ እንደሆነ ቢታመንም፣ እርምጃ ከወሰዱ ደግሞ እርምጃቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የማያዳግም ነው።

የሼኽ ሶፍዑመር (ሱፊ ዑመር) ባህርይን ከሼኽ ሁሴን ገደብ የለሽ ትዕግስተኛነት አንጻር ሲነጻጸር ተቃራኒ እንደሆነ ይታመናል። ሼኽ ሶፍዑመር የሼኽ ሁሴን የቅርብ ጓደኛ፣ የሚወዷቸው ተማሪያቸውና የሼኽ ሁሴን ጀምዓ (ተከታይ) ዋና ኢማም ናቸው። ሼኽ ሶፍዑመር የሼኽ ሁሴን አማችና የሰኪና (የሼኽ ሁሴን ሁለተኛ ሚስት የነበሩ) ወንድም

---

[67] - ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 25 ቀን፣ 2009 ዓ.ም።
[68] - ሼኽ አሕመድ ሐጂ ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 10 ቀን፣ 2008 ዓ.ም።

እንደሆኑ መረጃ ሰጪዎቹ ገልጸውልኛል፡፡[69] Braukämper (2004:132) ደግሞ ሼኽ ሶፍዑመር የሼኽ ሁሴን አጎት (የእናታቸው የሸምሲያ ወንድም) ናቸው ይላል፡፡

ሼኽ ሶፍዑመር በባሌ ዞን ጃራ ወረዳ አመኛ በሚባል ቦታ የተወለዱ ሲሆን፣ ራሳቸው እንደመሰረቱት የሚነገረውና በተፈጥሮ ዋሻ ውስጥ የሚገኘው የሶፍዑመር መካነ ቅርስ ተጠቃሽ ነው፡፡ የሼኽ ሶፍዑመር መካነ ቅርስ በባሌ ዞን በዳዌ ቃቸን ወረዳ በሶፍዑመር ቀበሌ የሚገኝ የአገራችን የተፈጥሮ መስህብ ነው፡፡ መስህቡ ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ በ102 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ዋሻ ከተፈጥሯዊ መስህብነቱ በተጨማሪ ኃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች ያሉት ልዩ ስፍራ ነው፡፡ በዚህ ዋሻ በአመት 3 ጊዜ የሚከበሩ በዓላት አሉ፡፡ እነዚህን በዓላት ለማክበር በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋል፡፡

ሼኽ ሶፍዑመር በጣም ፈጣንና ትዕግስት የለሽ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ እርምጃ ሲወስዱም የእኔ ነው የሚል ርሕራሄ የላቸውም፡፡ ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ በሼኽ ሁሴንና በሼኽ ሶፍዑመር ላይ የሚነገሩ ሁለት ሚቶችን እንመልከት፡፡[70] አንደኛው ሚት

> በአንድ ወቅት የሼኽ ሁሴን ሚስት እህል ደጅ ላይ ፀሐይ እንዲያደርቀው አስጥተዋል፡፡ የተሰጣውንም እህል ሼኽ ሁሴን እንዲጠብቁ ያዟቸዋል፡፡ ሼኽ ሁሴንም እህሉን እየጠበቁ እያለ፣ ዶሮዎች እህሉን መብላት ይጀምራሉ፡፡ እሳቸውም ይብሉ የተረፈው ይበቃል ብለው ዝም አሏቸው፡፡ ሚስታቸውም ተመልሰው ሲመጡ ዶሮዎቹ እህሉን መሬት በትነው አገኙት፡፡ በዚህን ግዜ በጣም ስለተናደዱ ባለቤታቸው ሼኽ ሁሴንን ፊታቸውን በጥፊ መቷቸው፡፡ የሼኽ ሁሴንን መመታት ያዩት ሼኽ ሶፍዑመር የታጠቁትን ጎራዴ በፍጥነት አውጥተው የሼኽ ሁሴንን ሚስት አንገት ሊቆርጡ ጎራዴውን ሰነዘሩ፡፡ በመቅስፈት ሚስታቸው ከቦታው ተሰወሩ፡፡ ሚስታቸውም ከቆይታ በኋላ ተመለሱ፡፡ ሼኽ ሁሴንም ሚስታቸውን የነበርሽበትን ቦታ ለማንም እንዳትናገሪ ብለው አስጠነቀቋቸው፡፡ ሼኽ ሁሴን ሚስታቸውን ከሼኽ ሶፍዑመር ጎራዴ የሸሸጓቸው፣ የራሳቸው ሆድ ዕቃ (አንጀት) ውስጥ በማስገባት ነበር፡፡

የሚል ነው፡፡[71] ሁለተኛው ሚት

> በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴን ዛፍ ስር በተቀመጡበት፣ አንድ እሳቸውን የማይወድ ሰው ልጉዳ ብሎ አጠገባቸው ካለ ዛፍ ላይ በመውጣት ቅዘኑን እላያቸው ላይ ይለቅባቸዋል፡፡ ይህንን ሁኔታ ያዩ የነበሩት ሼኽ ሶፍዑመር በያዙት ጎራዴ ሰውየውን ሊመቱት ሲሉ፣ ሼኽ ሁሴን ይከለክሏቸዋል፡፡ ሼኽ ሁሴንም 'ተወው እንኳን የእሱ በሽታ ከሆዱ ወጣለት እንጂ እኔስ በአንድ ኩዳ ውኃ እለቃለቃለሁ፡፡' በማለት ሼኽ ሶፍዑመርን አረጋጓቸው፡፡

የሚል ነው፡፡[72]

---

69 - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አቶ ኑማን ሼሕ መሃመድ፣ ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

70 - ሼኽ ከዲር ሼኽ ኢብራሂም፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 29 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

71 - ሼኽ አብዱልናስር አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 28 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

በእነዚህ ሁለት ሚቶች የሼኽ ሁሴንን ታጋሽነት፣ ሩህሩህነትና አባትነት እናያለን። በተቃራኒው ደግሞ የሼኽ ሶፍዑመርን ትዕግስት አልባነት፣ ፈጣን እርምጃ ወሳጅነትና ቁራጥነት በሚቶቹ እናያለን። ሼኽ ሁሴን ብዙ ማውራት አይችሉም። ሼኽ ሁሴን ብዙ ማውራት አይወዱም፣ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጸሎት ነው የሚያሳልፉት። እንደበተርዕቱ የሚባሉም አይደሉም። መንፈሳዊ ትምህርት በየቦታው እየሄዱ የሚያስተምሩላቸው፣ መልዕክት የሚያደርሱላቸው፣ እንግዳ ሲመጣ የሚያስተናግዱላቸው ወዳጃቸው ሼኽ ሶፍዑመር ናቸው። ሼኽ ሶፍዑመር በተለያዩ አካባቢዎች በመሄድ ኃይማኖታዊ ትምህርት ስላስተማሩም ይመስላል በባሌ ዞን ውስጥ ብቻ ከአስራ አምስት በላይ ቦታዎች በእሳቸው ስም ይጠራሉ።[73]

በክርስትና ኃይማኖት መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልና መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የራሳቸው የባህርይ ውክልና እንዳላቸው ይታመናል። ቅዱስ ሚካኤል እጅግ ታጋሽና ለእርምጃ የማይቸኩል ነው። ቅዱስ ገብርኤል ደግሞ እጅግ ትዕግስት የሌለውና እርምጃው ፈጣን የሆነ ነው። ይህ የመላእክቱ ባህርያት በሼኽ ሁሴንና በሼኽ ሶፍዑመር ባህርያት ጋር ይመሳሰላል። ሼኽ ሁሴንና ቅዱስ ሚካኤል በገደብ አልባ ትዕግስት ይመሰላሉ። ሼኽ ሶፍ ዑመርና ቅዱስ ገብርኤል ደግሞ በፈጣን እርምጃ ይመሰላሉ። የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮች ፈጣን ውሳኔን ሲፈልጉ፣ የቅዱስ ገብርኤልን ስም ይጠራሉ።

የሼኽ ሁሴን ተከታዮች ደግሞ ከልባቸው የሚረግሙት ሰው ፈጣን እርምጃ እንዲወሰድበት ሲፈልጉ የሼኽ ሶፍ ዑመርን ስም ይጠራሉ። ነገር ግን ሼኽ ሶፍ ዑመርን ጠርተው ከተራገሙ በኋላ በግለሰቡ ላይ በተወሰደበት እርምጃ መጸጸት የለም። ምናልባት ግለሰቡ ጸጸት ከተሰማው ተመሳሳይ እርምጃ እሱ ላይም ይወሰድበታል ተብሎ ይታመናል።[74] ለዛም ይመስላል በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ የሼኽ ሶፍ ዑመርን ስም በተንሽ ትልቁ መጥራትና በእሳቸው ስም መማል በጣም የሚፈሩት። እንደ ሶፍ ዑመር ሁሉ አበልቃሲምም በጣም ቁጠኛ፣ እርምጃቸው ፈጣንና ትዕግስት የሌላቸው እንደሆኑ ይታመናል።

---

[72] -ሼኽ አብዱልናስር አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 28 ቀን፣ 2007 ዓ.ም።
[73] - አቶ መለሰ መስቀላ፣ ሮቤ ከተማ፣ ሚያዝያ 25 ቀን፣ 2007 ዓ.ም።
[74] - ሼኽ ከዲር ሼኽ ኢብራሂም፣ አናጂና ቀበሌ፣ ኀሐሴ 29 ቀን፣ 2009 ዓ.ም።

## 4.4 የመካነ ቅርሱ እሳቤና ትዕምርታዊ ውክልና

መልክዓምድርና ኃይማኖት ያላቸውን የእርስበርስ ትስስር በኃይማኖት ጥናት ውስጥ መመልከት እምብዛም አልተለመደም፡፡ ነገር ግን የኃይማኖት እሳቤ፣ የቅዱስነት እሳቤ፣ የኃይማኖት ታሪክና በኃይማኖቱ ውስጥ የተፈጸሙ ገድላት በቀጥታ ከመልክዓምድር ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ መልክዓምድር ከቅዱስነት፣ ከልዩ ክብርና ከፍጹምነት ጋር የተያያዙ ነው፡፡ እነዚህ እሳቤዎች አንድ የሚታይና ተጨባጭ የሆነ መልክዓምድርን ምናባዊና መለኮታዊ እውነታን ወደ ያዘ አካል ይቀይሩታል፡፡ በዚህ ክፍል መልክዓምድርና እምነት ያላቸውን የእርስበርስ ትስስር ለመረዳት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መገኛ የሆነው ድሬ በሼኽ ሁሴን በአፍቃሪዎች ዘንድ እንዲሁም በተቃዋሚዎቻቸው ዘንድ ያለው እሳቤ ይቀርባል፡፡

### 4.4.1 የመካነ ቅርሱ እሳቤ ከሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች አንጻር

የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች በቦታው (በመካነ ቅርሱ መገኛ) ላይ ያላቸው ቦታዊ እሳቤዎች (Spatial concepts) የተለያዩ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ቦታዊ እሳቤዎች መካከል የተወሰኑትን እንመልከት፡፡ ቦታው ያለው እሳቤ አንዱ መገለጫ ስያሜ ነው፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኝበት ቦታ ድሬ፣ ቢርካና አናጂና በሚሉ ስያሜዎች ይታወቃል፡፡ ስፍራው ‘ድሬ’ የሚለውን ስያሜ እንዴት እንዳገኘ የሚነገሩ ሁለት ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛው፣ በአፋን ኦሮሞ ‘ድሬ’ ማለት ሰፊ ሜዳማ መሬት ማለት ነው፡፡ ድሬ ሼኽ ሁሴን፣ ማለትም የሼኽ ሁሴን መሬት (ሜዳ) የሚል ትርጉም አለው፡፡ ሁለተኛው፣ ደግሞ ሼኽ ሁሴን ስፍራውን የኃይማኖት ማዕከል ከማድረጋቸው በፊት ድሬ የሚባል ሰው ይኖርበት ነበር፣ ቦታውም የእሱ ንብረት ነበር፡፡ እሳቸው ቦታውን ከያዙት በኋላ የእሱ ስም እንዳይረሳና አላህን ፍራቻ የእሱ ስም ከእሳቸው ስም ጋር ተደርቦ ‘ድሬ ሼኽ ሁሴን’ እንዲባል በማዘዛቸው ነው፡፡[75]

‘ቢርካ’ የአካባቢው ሌላው ስም ነው፡፡ ቢርካ ሼኽ ሁሴን አዘውትረው ይቀመጡበት የነበረ ቦታ ነው፡፡ ቢርካ እሳቸው አዘውትረው የሚቀመጡበት ቦታ አጠገብ የሚገኝ የውኃ ኩሬም ስያሜ ነው፡፡ ሰው መጥቶ ከኩሬው ውኃ ይወስዳል፡፡ ሰውም አንድ ችግር ሲያጋጥመው መሬትን በሁለት እጁ እየነካ ‘ቢርካ አማና’ (መሬቱ ሰላም ነው) ይላል፡፡ ‘አናጂና’ ሌላው የአካባቢው ስም ነው፡፡ አናጂና የተባለው ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት በአካባቢው ጂኒዎች (ሰይጣኖች) በብዛት ይኖሩ ነበር ይባላል፡፡ ሼኽ ሁሴንም በአካባቢው ሲንቀሳቀሱ ጂኒውን

---

[75] - ሼሕ ተማም ኢድሪስ እና ወ/ሮ ሀሊማ ቃሲም፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

ያገኙትና 'አንተ ማን ነህ?' ብለው ሲጠይቁት 'አና ጂን' አላቸው፡፡ በአረብኛ 'አና ጂን' ማለት 'እኔ ጂኒ ነኝ' ማለት ነው፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ስፍራው አናጂና እንደተባለ ይነገራል፡፡[76] በአካባቢው በብዛት የነበሩ ጂኒዎችም በሼኽ ሁሴን ጸሎት አማካኝነት ከአካባቢው መራቃቸው ይነገራል፡፡ በመካነ ቅርሱ ጂና የሚባል ወንዝ አለ፡፡ ይህ ወንዝ ስያሜውን ያገኘውም ከአናጂና እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከእነዚህ የቦታ ስያሜዎችም በመነሳት ቦታው ሜዳማ፣ በወቅቱ ጂኒዎች ያሉበትና በሼኽ ሁሴን ኃይል ስፍራው የተቀደሰ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ድሬ "በፈጣሪ የተመረጠ ቦታ" እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህ እምነት መሰረት ያደረገውም ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ወቅት ፈጣሪ የሰጣቸውን ልዩ ጸጋ ማሳየታቸውን ከሚገልጽ ሚት ነው፡፡ ይህም ሚት የሼኽ ሁሴን እናት እርጉዝ ሆና በአናጂና ስታልፍ "አላህ እዚህ ተወለድ ብሎኛል፣ የእኔ ስፍራ እዚህ ስለሆነ ልወለድ" ብለው እናታቸው ማህጸን ውስጥ ሆነው እናታቸውን መጠየቃቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ ፈጣሪ ድሬን ሼኽ ሁሴን እንዲወለዱበት፣ እንዲያድጉበት፣ እንዲያስተምሩበት፣ ተዓምራትን እንዲፈጽሙበት፣ ለሰው ልጅ ሁሉ መዳኛ እንዲሆን የመረጠው ስፍራ ነው፡፡ ይህ እሳቤ አምላክ መዲናን ለነብዩ መሐመድ፣ የሲናን ተራራ ለሙሴ፣ ቤተልሔምን ለኢየሱስ እንደመረጠ ሁሉ፣ ድሬንም ለሼኽ ሁሴን መምረጡን ያሳያል፡፡

ድሬ "የሼኽ ሁሴን መካነ መቃብር የሚገኝበት ቦታ" እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም እምነት ስፍራው የተቀደሰ፣ የሼኽ ሁሴን መንፈስ ያረፈበት እንደሆነ ያሳያል፡፡ የሼኽ ሁሴን አንዳንድ አፍቃሪዎች የእሳቸው መቃብር ድሬ ውስጥ በሼኽ ሁሴን ስም በተገነባ ገሞ ስር ይገኛል ብለው ያምናሉ፡፡ ነገር ግን ሼኽ ሁሴን የት እንደሞቱና የት ቦታ አስክሬናቸው እንዳረፈ በግልጽ አይታወቅም፡፡ አንዳንድ አፍቃሪዎቻቸው ደግሞ ሼኽ ሁሴን አርገዋል፡፡ በመሆኑም እሳቸው አልሞቱም፤ አስክሬናቸው በምድር ላይ የለም ብለው ያምናሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚገኙ 10 ገሞዎች መካከል ረጅም እድሜ ያስቆጠረው የሼኽ ሁሴን ገሞ ሲሆን፣ የ375 አመት እድሜ እንዳለው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፡2) ይገልጻል፡፡ የሼኽ ሁሴን ገሞ በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ መሃል ላይ በሚገኝ ተጨማሪ የግምብ አጥር ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ ገሞ የኪነ-ህንጻ ዲዛይኑና ትልቀቱ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ገሞዎች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ገሞው 45 ሜትር

[76] - አቶ አብዱልናስር አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ርዝመት፣ 35 ሜትር ስፋትና 3 ሜትር ከፍታ አለው (Hailemelekot and Mulugeta, 2015:28)። የሼኽ ሁሴን ገሞ በሚገኝበት አጥር ውስጥ የልጆቻቸው የፋጡማና የሼኽ መሃመድ ተማም ገሞዎች ይገኛሉ።

በሼኽ ሁሴን ገሞ አናት ላይ በአረብኛ ቋንቋ የተጻፉ ሁለት ጥቅሶች አሉ። አንደኛው ጥቅስ ‹አላሁመ-እርሐም ሊ ሼኽ ሁሴን አግሲና› የሚል ሲሆን፣ ትርጉሙም “አላህ ሆይ ለሼኽ ሁሴን ቸሩ ምህረትህን ለግሰው።” ማለት ነው። ሁለተኛው ጥቅስ ደግሞ ‹ላ ኢለላህ ኢላ-ላህ መሃመዱ ራሱል አላህ› የሚል ሲሆን፣ ትርጉሙም ‹ፈጣሪ አላህ ነው፣ መሃመድም የአላህ መልዕክተኛ ነው።› ማለት ነው። ይህ ገሞ ‹ከራ ሀሮ ሉኩ› እና ‹ከራ ጀጀባ› በሚል ስያሜ የሚጠሩ ሁለት መግቢያ በሮች አሉት። ገሞው ውስጡ ክፍት ሲሆን፣ 7 ወፋፍራም ምሰሶዎች አሉት።



*ፎቶ 4፡- አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለውና የአረብኛ ጽሑፍ ያለበት የሼኽ ሁሴን ገሞ ነው። ከፊት ለፊት በስተቀኝ በኩል የሚታየው የሼኽ መሃመድ ተማም ገሞ ሲሆን፣ ከፊት ለፊት በስተግራ በኩል የሚታየው ደግሞ የፋጡማ ገሞ ነው።። (ፎቶ በአጥኚው)።*

በድሬ የሼኽ ሁሴን ገሞ የተገነባበት ቦታ የእሳቸው አስክሬን መኖሩ ወይም አለመኖሩ በግልጽ አይታወቅም። ነገር ግን የእሳቸው የመቃብር ስፍራ ገሞው የተሰራበት ቦታ ላይ ወይም እዛው አካባቢ እንደሆነ ይታመናል። በሌላ መረጃ ደግሞ የእሳቸው ገሞ የተገነባበት ስፍራ የሼኽ ሁሴን መኖሪያ ቤት የነበረ እንጂ የመቃብር ስፍራ እንዳልሆነ አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቼ

ይገልጻሉ፡፡[77] የእሳቸው መቃብር በእሳቸው ስም በተገነባው ገሞ 40 ሜትር ርቀት ላይ ተመስጥሮ እንደሚገኝ መሐመድ (አመት የለውም፣ገጽ 6) ጠቁሞ፣ ቀብሩ እንዳይታወቅ ምስጢር የተደረገበት ምክንያቶች አንደኛው፣ በወቅቱ በሌላ አካባቢ የሚኖሩ የኑር ሁሴን አፍቃሪዎች አስክሬኑን አውጥተው እንዳይወስዱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ፈሪሃ-አላህ ያላደረባቸው ሰዎች በመካነ መቃብራቸው ላይ ቆመው እንዳይፈጋገሙበት ተሰግቶ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ከእነዚህ ሁለት ምክንያች በተጨማሪ የእሳቸው አስክሬን የት እንዳረፈ በትክክል እንዳይታወቅ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል በዋናነት ሁለት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡[78] አንደኛው፤ ሼኽ ሁሴን በአናጂና በተወለዱበት ቀን በተለያዩ አካባቢዎች 144 ህጻናት ተወልደዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በወቅቱ ነብዩ መሃመድ "ከእኔ በኋላ ነብይ አይወለድም፡፡ እኔ የመጨረሻው ነኝ፡፡ ምናልባት ነብይ ቢወለድ ኖሮ 'ሁሴን' ነብይ ይሆን ነበር፡፡" ብለው ተናግረዋል ተብሎ በሕዝቡ ዘንድ ይታመን ነበር፡፡ በዚህ አባባል ምክንያት በወቅቱ ሁሉም ሰው ይህንን አጋጣሚ የሚጠብቅና ምናልባት የእኔ ልጅ ይሆናል ብሎ ያስብ ነበር፡፡[79] በመሆኑም በወቅቱ የተወለዱ ህጻናትን ስም 'ሁሴን' ብሎ የመሰየም ልማድ በመኖሩ ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ወቅትም ሆነ ከመወለዳቸው በፊት የሚወለዱ ሕጻናት ስም 'ሁሴን' ተብለው ይሰየሙ ነበር፡፡ ለዚህም ይመስላል በተለያየ አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች በተለይም ሱማሌዎች፣ አርጎባዎች፣ ባሌዎች፣ አርሲዎች፣ ወረሼሆች፣ የመኖችና ኢሩቆች "ሼኽ ሁሴን የተወለዱት እኛ ጋር ነው፡፡" ብለው እንዲያምኑ ምክንያት የሆነው፡፡

ሁለተኛው፣ ምክንያት ደግሞ እንደ ውልደታቸው ሁሉ እሳቸው ከዚህ ዓለም በተለዩበት ወቅት የተፈጠረ ክስተት ነው፡፡ ይህም በእሳቸው የሕልፈት እለት ሼኽ ሁሴን መሞታቸውን ከአናጂና ወደ ሌላ ስፍራ መርዶ ሲላክ፣ ከሌላ አካባቢም በተመሳሳይ ሼኽ ሁሴን መሞታቸውን የሚገልጽ መርዶ ወደ አናጂና ይላክ ነበር፡፡ በወቅቱም በተለያዩ ቦታዎች 'ሁሴን' በሚል ስም የሚታወቁ በርካታ ሰዎች ሕይወታቸው አልፎ ነበር፡፡ ይህም ልዩ ክስተት ሁሉም በየአካባቢው "የሼኽ ሁሴን የመቃብር ስፍራ እዚህ ነው" በሚል የመታሰቢያ ገሞ እንዲገነባ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለዚህም ይመስላል በእሳቸው ስም የተገነቡ ገሞዎች በተለያዩ የአገሪቷ ስፍራዎች ያሉት፡፡

[77] - አቶ መሐመድ ሼኽ ሁሴን፣ አዲስ አበባ፣ ታህሳስ 5 ቀን 2010 ዓ.ም

[78] - ሼኽ አደም ገመዳ፣ ሼኽ አልይ ሱራና ሼኽ ጀይላን አመኖ፣ ሮቤ፣ ጥር 8 ቀን 2009 ዓ.ም፡፡

[79] - ሼኽ መሐመድ ሐጂ አብዱልቃዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 9 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

ከእነዚህ ስፍራዎች መካከል በአርሲ ዞን በአርባጉጉ፣ በኮፈሌ፣ በሺርካና በሰኪና፣ በባሌ ዞን በመደወላቡ እና በምስራቅ ሐረርጌ ዞን በጨርጨር ይገኛል።

የሼኽ ሁሴን የቀብር ስፍራ በትክክል የት እንደሆነ አይታወቅም። ነገር ግን የአካባቢው ሰዎችና የእሳቸው ተከታዮች አስክሬናቸው በአናጂና ቀበሌ ውስጥ በስማቸው በተገነባ ገሞ ስር እንዳረፈ ያምናሉ። ከመረጃ ሰጪዎች ባገኘሁት መረጃ መሰረት ለዚህ እምነታቸው መነሻ ምክንያቶች ሶስት ናቸው። አንደኛው፤ በሼኽ ሁሴን ስም የሚመጣውና የእሳቸውን አስተምህሮ የሚከተለው ምዕመን ቁጥር በስማቸው ገሞ ከተገነባባቸው ሌሎች ስፍራዎች በይበልጥ በድሬ መብዛት ነው። እንደእነሱም እምነት በሌሎች አካባቢዎች ያሉና የሼኽ ሁሴን የመቃብር ስፍራ ናቸው ወደሚባሉ ቦታዎች የሚሄደውን ሰው ቁጥር ብዛትና እዚህ ድሬ የሚመጣውን ሰው ቁጥር በማወዳደር በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር ህዝብ እዚህ መምጣቱ አንድ ምልክት እንደሆነ ያምናሉ።

ሁለተኛው፤ ለአምልኮ የሚመጡ ሰዎች በስፍራው መጥተው የእሳቸውን ገሞ ዞረው ሳያዩና ሳይዘይሩ (ሳይጎበኙ) ከተመለሱ ሼኽ ሁሴን በኢማና (በመንፈስ) መጥተው ‹ምነው እዚህ ደርሰህ ሳታየኝ ተመለስክ› ብለው ይቆጧቸዋል ተብሎ መታመኑ ነው። በርካታ ሰዎችም ይህ እንዳጋጠማቸው መናገራቸው የእሳቸው መቃብር እዚህ መሆኑ እንዲታመን አድርጓል። ሶስተኛው፤ በእምነታቸው፣ በምግባራቸውና በጸሎታቸው ለታወቁ ሰዎች ሼኽ ሁሴን በኢማና (በመንፈስ) መጥተው ‹የእኔ ማረፊያ እዚህ ነው› ብለው ነግረውናል የሚሉ ብዙ ሰዎች መኖራቸው ነው።

የሼኽ ሁሴን አስክሬን በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ አርፎ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ሼኽ ሁሴንም አርገው ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ስፍራው የሼኽ ሁሴን መኖሪያ ቦታ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ለእነዚህ ጉዳዮች ከእምነት አመለካከት ባለፈ ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም። ነገር ግን በእኔ እምነት ይህ ስፍራ እሳቸው የተወለዱበት፣ ያደጉበት፣ ሀይማኖታዊ ትምህርት ያስተማሩበት፣ ቤተሰብ መስርተው ወግ ማዕረግ ያዩበትና ረጅም ጊዜ በጸሎት የቆዩበት ነው። በመሆኑም የእሳቸው መለኮታዊ ኃይል (Divine power) ከሌሎች ቦታዎች በተለየ እዚህ ስፍራ ሊኖር እንደሚችል አመላካች ነገሮች መኖራቸውን አስተውያለሁ።

ከእነዚህ መካከል በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩና በመንፈስ የበቁ ወልዮችና ኢማሞች በስፍራው መጥተው በጸሎት ያላቸው መንፈሳዊ ኃይል እንደሚታደስና ተጨማሪ ሀይል እንደሚያገኙ

ማመናቸው፣ የተለያየ ችግር ያለባቸው ሰዎች በስፍራው መጥተው ከችግሮቻቸው እንደሚፈወሱ ማመናቸውና ሲፈወሱም ማየቴ፣ እጅግ አስደናቂ ተዓምራት በስፍራው በየጊዜው እንደተከሰተ መታመኑ፣ በሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ትዕዛዝ መሰረት ዓለማዊ ሕይወታቸውን ትተው በመመነን በስፍራው የሚኖሩ ሰዎች መኖራቸው በዋናነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ድሬ በተለያዩ ወቅቶች ወደ ስፍራው የመጡ ወልዮችና የኃይማኖት መሪዎች ያረፉበት የመቃብር ስፍራዎች የሚገኝበት ነው፡፡ በመቃብር ስፍራቸው ላይም ለመታሰቢያ የተገነቡ ገሞዎች መገኛ ነው፡፡ ከመቃብር ስፍራነቱም በተጨማሪ የቃድሪያ ስርዓት መስራች የሆኑት አብዱልቃዲር ጀይላኒ ከኢራቅ ባግዳድ በመጡበት ወቅት ድንኳናቸውን ጥለው ተቀምጠውበታል በሚባለው ስፍራ በእሳቸው ስም ገሞ ተገንብቷል፡፡ ይህ ገሞ በአካባቢው ከሚገኙ ገሞዎች መካከል ከሼኽ ሁሴን ገሞ ቀጥሎ በትልቅነቱ ሁለተኛ ነው፡፡ ገሞው የተገነባው በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ ነው፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ 10 ገሞዎች፣ የሼኽ ሁሴን ሼኽ ኢብራሂም፣ የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ፣ የፋጡማ ሼኽ ሁሴን፣ የሼኽ ማሃመድ ተማም ሼኽ ሁሴን፣ የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ፣ የሼኽ ኢብራሂም ቢን መልካይ፣ የአዮ ሽምሲያ፣ የሼኽ መሃመድ ሚስኪ፣ የሼኽ መሃመድ ሀጂ አህመድና የሼኽ ዑመር ሼኽ አልይ ናቸው፡፡

የሼኽ ሁሴን፣ የፋጡማ፣ የሼኽ ማሃመድ ተማም፣ የሼኽ አብዱልቃድር፣ የሼኽ ኢብራሂምና የአዮ ሽምሲያ ገሞዎች የተገነቡት በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ገሞዎቹንም ያስገነቡት ሼኽ መሃመድ፣ ሼኽ አባስና ሼኽ ቡሽራ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ ገሞዎች መካከል በ2007 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የተገነባው የሼኽ ዑመር ገሞ ነው፡፡ ይህ ገሞ የመካነ ቅርሱ አስተባባሪ ለነበሩትና በ2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት ሼኽ ዑመር ሼኽ አልይ መታሰቢያ እንዲሆን በመቃብራቸው ላይ የተገነባ ነው፡፡ ሼኽ ዑመር ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ የመካነ ቅርሱን አስተባባሪነት የተረከቡት ልጃቸው ሼኽ ፈይሰል ሼኽ ዑመር ናቸው፡፡

የድሬ መሰረት የሼኽ ሁሴን መካነ መቃብር ነው፡፡ ከሼኽ ሁሴን በተጨማሪም የእሳቸው አባት፣ እናትና ልጆች የመቃብር ስፍራ ነው፡፡ በተለያዩ ዘመን በስፍራው የኖሩ የተለያዩ ኢማሞችና ግለሰቦች የመቃብር ስፍራም ነው፡፡ የቅዱሳንና የኢማሞችን መካነ መቃብርን መነሻ አድርገው የተመሰረቱ መንደሮች ወይም ከተሞች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች አሉ፡፡ እነዚህ መንደሮች ወይም ከተሞች "ኒክሮፖሊስ" (Necropolis) በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ ድሬም በአገራችን ውስጥ ከተመሰረቱ መሰል ኒክሮፖሊስ መንደሮች መካከል አንዱ ነው፡፡

ድሬ “የተቀደሰ ስፍራ” እንደሆነ ይታመናል፡፡ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ካለባቸው ችግር ለመፈወስ፣ በሕይወታቸው በረከት ለማግኘት፣ ከምድራዊ ሕይወት በኋላ ነፍሳቸው በገነት እንድትኖር፣ የወደፊት ምኞታቸው እንዲሳካ በሚል ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ ስፍራው ላይም በመድረሳቸው ያሰቡት ሁሉ እንደሚሳካ በሙሉ ልባቸው ያምናሉ፡፡ ድሬን የሚረግጥ ሰው በሼኽ ሁሴን የተመረጠና የተፈቀደለት ብቻ ነው፡፡ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ማንኛውም ሰው ወደ ድሬ መሄድ ስለፈለገ ብቻ ተነስቶ አይሄድም፡፡ በስፍራው የሚመጣ ሰውም ተፈቅዶለት እንጂ ልምጣ ስላለ አይመጣም ብለው ያምናሉ፡፡

ግለሰቦች በራሳቸው ፍላጎት መሰረት ድሬ ለመሄድ ዝግጅት ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ነገር ግን ወደ ስፍራው እንዲሄዱ የሼኽ ሁሴን ፍቃድ ከሌለ ወደ ስፍራው ማንም መሄድ አይችልም፡፡ የሼኽ ሁሴን ፍቃድ ከሌለ በትራንስፖርት እጦት፣ በገንዘብ እጦት፣ በጤና እጦት፣ በመርሳት ወይም በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ሰበብ ሆነው ጉዞው ይደናቀፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የአንድ መረጃ ሰጪዬ ገጠመኝን እንደ ማሳያ እንመልከት፡፡

ማሳያ 1- ስማቸው ነስራ አደም ይባላሉ፡፡ እድሜያቸው በ50ዎቹ ውስጥ የሚገመት የ3 ልጆች እናት ናቸው፡፡ እሳቸውም በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ የሱማሌና የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ናቸው፡፡ በ2008 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ወደ ባሌ ጎባ በሚሄድ የሕዝብ ትራንስፖርት መኪና ላይ ነው የተዋወቅነው፡፡ እኔም እሳቸውም ለሙዳ በዓል ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን እየሄድን ነበር፡፡ እሳቸውም ‘ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ለመሄድ ማሰብ የጀመርኩት የዛሬ 20 ዓመት ነው፡፡ ሁልጊዜ በየዓመቱ የአረፋ በዓል ሲደርስ ድሬ እሄዳለሁ፣ የሼኽ ሁሴንን ደጅ እረግጣለሁ ብዬ እዘጋጃለሁ፡፡ በየአመቱ ሁልጊዜ ሰበብ አስባብ እየያዘኝ እቀራለሁ፡፡ የዛሬ 5 ዓመት ወደ ድሬ ልመጣ ከአዲስ አበባ ወደ ባሌ የአውቶቢስ ቲኬት ቆርጬ፣ እቃዬን አስተካክዬ፣ ጠዋት እንዳላረፍድ ባለቤቴን ቀስቅሰኝ ብዬ እኔም ሰዓት ሞልቼ ተኛሁኝ፡፡ ይገርምሃል ጠዋት ስነቃ ደነገጥኩኝ፡፡ ሰዓቱን አያለሁ ከቀኑ 3 ሰዓት ሆኗል፡፡ ባለቤቴም ከእንቅልፉ አልነቃል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው እስከ ጠዋት 3 ሰዓት የተኛሁት፡፡ ከዚህ በፊት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ወዲህ እንደውም እንቅልፍ አይወስደኝም፡፡ ያን ቀን በቃ አብዮ ሰይዱ-ላራፊና እርስዎ በጠሩኝ ጊዜ እመጣለሁ፡፡ ካሁን በኋላ የእርስዎ ደጅ እመጣለሁ ብዬ አላቅድም አልኩኝ፡፡ ይሄው ዘንድሮ በ20ኛው አመቴ ከተሳካልኝ ለመጀመሪያ ጊዜ እየሄድኩ ነው፡፡ አብዮ ካልፈቀዱ አሁንም ከመንገድ ልመለስ እችላለሁ፡፡

ወደ ድሬ ለመሄድ የሼኽ ሁሴን ፍቃድ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ ለመቅረትም የእሳቸው ፍቃድ አስፈላጊ ነው፡፡ የእሳቸው አፍቃሪዎች በሙዳ በዓላት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ድሬ ላለመሄድ ይወስናሉ፡፡ ወይም መሄድ ፈልገው በትራንስፖርት፣ በገንዘብ ወይም ስፍራውን ባለማወቅ ለመቅረት ይወስናሉ፡፡ የእነዚህ ግለሰቦች የድሬ ጉዞ በሼኽ ሁሴን ዘንድ ተቀባይነት

ካገኘና ከተፈለገ በምንም ምክንያት ከጉዟቸው ሊቀሩ አይችሉም ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የአንድ መረጃ ሰጪዬ ገጠመኝን እንደ ማሳያ እንመልከት፡፡

ማሳያ 2- ስሙ ስንታየሁ ይባላል፡፡ የ35 ዓመት ወጣት ነው፡፡ የሚኖረው በቦረና ዞን ያቤሎ ከተማ ነው፡፡ የተዋወቅነው በ2009 ዓ.ም ከሮቤ ወደ አናጂና በሚሄድ የሕዝብ ትራንስፖርት መኪና ውስጥ ነው፡፡ በጫወታችን መሀል አገሩን ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳየው ወደ ድሬም መጥቶ እንደማያውቅ ይነግረኛል፡፡ እንዴት ሊመጣ እንደቻለም ጠይቄው እንደሚከተለው አጫወተኝ፡፡ ወታደር ቤት ነበርኩኝ አሁን በጉዳት ምክንያት ጡረታ ወጥቻለሁ፡፡ ወታደር በነበርኩበት ወቅት አንድ ቀን ድንገተኛ የማጥቃት ትዕዛዝ ይሰጠንና ተኩስ ይጀመራል፡፡ በጦርነቱም ላይ ተመታሁና በጣም ተጎዳሁኝ፡፡ እራሴን ስቼ ነበር፡፡ ስነቃ መቀሌ አይደር ሆስቢታል እንደሆንኩኝ ጓደኞቼ ነገሩኝ፡፡ በወቅቱም እንደ ደመና ነገር ዐይኔን ጋረደኝ፡፡ ማየት አቃተኝ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለሁ ሆስቢታል ለ 3 ወር ቆይቼ አዲስ አበባ እህቴ ጋር ሄድኩኝ፡፡ እህቴም የሼኽ ሁሴን አፍቃሪ በመሆኗ ስለት ተሳለችልኝ፡፡ ስለቷም ደርሶ ከ1 ወር በኋላ አይኔ ማየት ጀመረ፡፡ ስለቱንም ለማድረስ ወደ ድሬ ለመሄድ ፈልኩኝ ግን ገንዘብ አልነበረኝም፡፡ እህቴም አረብ አገር ስለሄደች ገንዘብ ሳገኝ በሚቀጥለው አመት እሄዳለሁ ብዬ ዝም አልኩኝ፡፡ ይሄንን ወስኜ እንዳለሁ አንድ አብሮ አደግ ጓደኛዬን ድንገት መንገድ ላይ ተገናኘን፡፡ ስለነበርኩበት ሁኔታ ሳጫውተው በጣም አዝኖ ለጊዜው ይሆንሃል ብሎ ብዙ ብር ሰጠኝ፡፡ እኔም ሼኽ ሁሴን በገንዘብ አጦት ምክንያት አትቀርም ብለው ነው የሰጡኝ ብዬ አመንኩኝና በማግስቱ ወደ ድሬ ጉዞ ጀመርኩኝ፡፡

በግሌ "ማንኛውም ሰው ከሼኽ ሁሴን ፍቃድና ይሁንታ ውጪ ወደ ስፍራው ሊመጣ አይችልም፡፡" የሚለው እምነት ለዚህ ጥናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጎልኛል፡፡ ምክንያቱም ወደ ስፍራው ለጥናት እንደመጣሁ ለመካነ ቅርሱ ነዋሪዎችና ለመረጃ ሰጪዎቼ ስነግራቸው፣ ሁሉም ከፍተኛ ደስታ ይሰማቸው ነበር፡፡ የደስታቸው ምንጭ ከጥናቱ ባለፈ "ሼኽ ሁሴን ስለፈቀዱልህ ነው የምታጠናው፣ አንተም የሼኽ ሁሴን ሰው ነህ፡፡" ከሚል የወዳጅነትና የእኛው ወገን ነህ ስሜት የመነጨ ነው፡፡ ይህ አመለካከት ለስራዬ መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቶልኛል፡፡

ድሬ "የተለያዩ መንፈሶች የሚመጡበት ስፍራ" ነው፡፡ በድሬ የተለያዩ መንፈሶች እንደሚመጡ ይታመናል፡፡ መንፈሶቹም የሚመጡበት ባህርይ በሶስት መንገድ ነው፡፡ እነሱም፣ በመንፈስ፣ እንደ ሰው በአካልና በመንፈስም በአካልም ናቸው፡፡ በስፍራው ሼኽ ሁሴን በመንፈስና በአካል ይመጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በመንፈሳዊ ጸጋቸው የበቁ የሚባሉ ግለሰቦች ሼኽ ሁሴንን በመንፈስ እንዳዩ ይናገራሉ፡፡ ሼኽ ሁሴን በመንፈስ በሚታዩበት ወቅት በጣም ነጭና

የሚያንጸባርቅ ልብስ የለበሱ ሽማግሌ መስለው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡[80] ሼኽ ሁሴን ከመንፈስ በተጨማሪ የሰው ስጋ ለብሰው እንደ ሰው በአካል ይመጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ እሳቸውም እንደ ሰው በአካል በመምጣት መልዕክት ይናገራሉ፣ ያስጠነቅቃሉ፣ እርዳታ ይጠይቃሉ፣ ያበረታታሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

በድሬ የሰው አካል ለብሰው፣ እንደ ሰው ይመጣሉ ተብለው የሚታመኑ ክፉ መንፈሶች አሉ፡፡ እነዚህ ክፉ መንፈሶች “ሮሃኒያ” በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ ሮሃኒያዎች በሙዳ በዓል ወቅት ከሰው ጋር ሰው መስለው በመንቀሳቀስ ከስፍራው ሰው ጠልፈው ይወስዳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ሮሃኒያዎች የወሰዱትን ሰው ለሚፈልጉት ጊዜ ያህል እነሱ ዘንድ አቆይተው ይመልሱታል ወይም በዛው እንደወሰዱት ያስቀሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ስለሮሃኒያዎችና በእነሱ ስለተወሰዱ ግለሰቦች ገጠመኝ በስፋት ይነገራል፡፡ በሮሃኒያዎች ከተወሰዱ ግለሰቦች መካከል መረጃ ሰጪዬ አቶ መሐመድ አንዱ ነው፡፡ በሮሃኒያዎች በተወሰደበት ወቅት የሚያስታውሰውን እንዲህ አጫውቶኛል፡፡

> ማሳያ 3- የ5 ዓመት ልጅ እያለሁ ነው በሮሃኒያዎች የተወሰድኩት፡፡ ሁለት በጣም ወፋፍራም ሰዎች እጄን ግራና ቀኝ ይዘው ሄዱ፡፡ ይዘውኝ ሲሄዱ በአየር ላይ እንደሚሄድ ይሰማኝ ነበር፣ ጭውውው ይልብኝ ነበር፡፡ የት ይዘውኝ እንደሄዱ አላቅም፡፡ የማለውቀው ቦታ አሳርፈውኝ፣ እንደገና ይዘውኝ መሄድ ጀመሩ፡፡ እራሴን ያወኩት የሆነ ሜዳ ላይ ቁጭ ብዬ ስነቃ ነው፡፡ የት እንዳለሁ ማወቅ አቃተኝ፡፡ ቤተሰቦቼ በተቀመጥኩበት ቦታ መጥተው ሲወስዱኝ ትንሽ ትንሽ አስታውሳለሁ፡፡ በትክክል ከነቃሁ በኋላ ሮሃኒያዎች እንደወሰዱኝና በጠፋው በ5^ኛው^ ቀን ከወሰዱኝ ቦታ ትንሽ ራቅ አድርገው እንደመለሱኝ ቤተሰቦቼ ነገሩኝ፡፡ ልክ እንደኔ በዚህ አናጂና ቀበሌ ነዋሪ የሆነ አብዛኛው ሰው ተወስዷል፡፡

በ2009 ዓ.ም የሐጅ የሙዳ በዓል ወቅት መንፈሳዊ ተጓዦች በሚያርፉበት ስፍራ አንድ የ4 ዓመት ሕጻን አግኝቻለሁ፡፡ ህጻኑ ወደ ስፍራው የመጣው ከአባቱ ጋር ነው፡፡ አባቱም ከሱቅ እቃ ገዝቼ መጣሁ ብሎ እንደወጣ አለመመለሱንና ሰውዬው ከጠፋ 4^ኛ^ ቀኑ እንደሆነ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ነገሩኝ፡፡ የመረጃ ስብሰዬን ጨርሼ እስክመለስ ድረስም የሕጻኑ አባት አልመጣም፡፡ አባቱም በጠፋ በ12^ኛው^ ቀን በስፍራው ተመልሶ ሕጻኑን ይዞ ወደ አገሩ መመለሱንና ሰውዬውም ሮሃኒያዎች እንደወሰዱት በራሱ አንደበት ይናገር ነበር፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለመስክ በቆየሁባቸው ቀናት ከፍተኛ ፍርሃት ከፈጠሩብኝ ገዳዮች መካከል አንዱ ስለሮሃኒያዎች የምሰማው መረጃ ነው፡፡ ወደ ስፍራው ስሄድ የማርፍበት ቤት

---

[80] - ሼኽ ሙሐሙድ ሐጂ አብዱልቃድር፣ ሼኽ አሕመድ ሐጂ ከዲርና ሼኽ ከዲር መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 8 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

ከግምብ አጥሩ በግምት 5 ደቂቃ ያስኬዳል፡፡ ሌሊት የሚካሄዱ ክወናዎችን ተመልክቼና መረጃ ሰብስቤ ወደ ማረፊያ ቤት የምሄደው በአብዛኛው ከሌሊቱ 9 ሰዓት ገደማ ነው፡፡ በዚህ ሰዓት ወደ ማረፊያ ቤት ብቻዬን በጭለማ ስሄድና በማረፊያ ቤትም ብቻዬን ስተኛ፣ የሮሃኒያዎች ሰውን ጠልፈው የመውሰድ ጉዳይና የእኔም እጣፈንታ በእነሱ መወሰድ ይሆን? የሚል ጥያቄ በጣም የሚያስፈራኝና የሚያስጨንቀኝ ነበር፡፡

ድሬ "ከመካ እኩል" እንደሆነ ይታመናል፡፡ ለሐጅ በዓል ወደ ሳዑዲ አረብያ መካ የሚደረግ ሐጅ አለ፡፡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴንም ለሐጅ በዓል የሚደረግ ጉዞ አለ፡፡ እነዚህ ሁለት መንፈሳዊ ጉዞዎችና መንፈሳዊ ቦታዎች እኩል እንደሆኑ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ይታመናል፡፡ ሼኽ ሁሴን በአፍቃሪዎቻቸው ዘንድ "ነቤ" በሚል የቁልምጫ ስም ይጠራሉ፡፡ ነቤ የሚለው ስያሜ ነብይ ከሚለው የመጣ ነው፡፡ ነቤ የሚለው ስያሜም ሼኽ ሁሴን ነብይ ናቸው ለማለት ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም የነቤ ከተማ (መዲናት አል-ነቢ) በሚል የቁልምጫ ስም ይጠራል፡፡ ይህ ስያሜ ሼኽ ሁሴንን ከነብዩ መሐመድ ጋር እንዲሁም ድሬን ከመካ ጋር ማመሳሰልን ያመለክታል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን ለሐጅ በዓል በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ ለአምልኮ የሚሄድበት በመሆኑና መካነ ቅርሱ ከመካ እኩል የሚታሰብ በመሆኑ ይመስላል Braukämper (1984) መካነ ቅርሱን የ"ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ መካ" በሚል የገለጸው፡፡ Cerulli (1941) የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን የ"ደሃ ሰው ሐጅ" በሚል መግለጹን Eshetu (1973፡24) ጠቅሷል፡፡ በተመሳሳይም Baxter (1987) ገንዘብ ያለውና ሐብታም ሰው ወደ መካ ሲሄድ፣ ደሃው ግን ወደ ድሬ መሄዱ፣ መካነ ቅርሱን የ"ደሃ ሰው መካ" መሆኑን የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞች እንዳገኘ ይገልጻል፡፡

የ"ደሃ ሰው መካ" የሚለው አስተሳሰብ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚሄድ ሰው አብዛኛው ደሃ ከመሆኑ የተነሳ የመጣ ይመስላል፡፡ እንደሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሼኽ ሁሴን አማኞችም በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም አባባሉ በአንድ መልኩ ትክክል ይመስላል፡፡ ነገር ግን እጅግ ሐብታም የሆኑ ግለሰቦች የግል ሂሊኮፕተር ይዘው ወደ ድሬ የሚመጡ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች መኖራቸው ደግሞ ጉዳዩን ሙሉለሙሉ ከኢኮኖሚ አቅም ጋር ማያያዝ እንደማይቻል አመላካች ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በሳዑዲ አረቢያ መካ መካከል ያለውን ተመሳስሎ የፈጠሩና ስፍራዎቹም እኩል እንደሆኑ እንዲታመን ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮችም

መንፈሳዊ ተጓዦች ከተለያዩ ዓለማት ለሐጅ ወደ ድሬ መሄዳቸው፣ ስፍራው ቅዱስ እንደሆነ መታመኑ፣ የሼኽ ሁሴን መካነ መቃብር የሚዘየር መሆኑ፣ በስፍራው ዘምዘም (ቅዱስ ውኃ) መኖሩ፣ በስፍራው ነብዩ መሐመድ በመንፈስ እንደመጡ መታመኑ፣ ሼኽ ሁሴን ከመካ እንዳመጡት የሚታመንና “ደራራ በሹ” በሚል ስያሜ የሚታወቅ ጥቁር ድንጋይ መኖሩ፣ ሼኽ ሁሴን ነብዩ መሐመድን ለመጎብኘት ወደ መካ የሄዱበትና ከድሬ እስከ መካ የሚያደርስ ዋሻ እንዳለ መታመኑ እንዲሁም በሐጅ ጉዞ ወቅት በመካ ከሚከወኑ ድርጊቶች ጋር የሚቀራረቡ ስርዓተከበራዎች በስፍራው መከወናቸው ናቸው።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በሳዑዲአረቢያ መካ መካከል ተመሳስሎ ቢኖርም በርካታ ልዩነቶች አሉ። ከእነዚህ ልዩነቶች መካከል የስፍራዎቹ ታሪካዊ አመሰራረት፣ በየስፍራዎቹ የሚከወኑ መንፈሳዊ ክወናዎች፣ ወደ ስፍራዎቹ የሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦች ያላቸው የኃይማኖት ዳራ እንዲሁም ተጓዦቹ የሚኖራቸው ማህበራዊ ደረጃና የሚያገኙት ማዕረግ ይለያያል። በመካ በሚካሄደው የሐጅ ጉዞ ላይ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ የሆነ ግለሰብ ብቻ ነው የሚሳተፈው። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚካሄደው ሐጅ ግን ከእስልምና ኃይማኖት ተከታይ በተጨማሪ የክርስትና፣ የዋቄፈና ወይም የሌሎች ኃይማኖቶች ተከታዮች መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ። በመካ በሚካሄደው የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ ሄዶ የተመለሰ የማዕረግ ስም ይሰጠዋል። የማዕረግ ስሙም ለወንድ “ሐጂ” ሲሆን፣ ለሴት “ሒጃህ” ነው። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚካሄደው የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ አድርጎ የመጣ ግለሰብ ግን የሚሰጠው የተለየ ማዕረግ የለም።

የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከመካ እኩል እንደሆነ ያምናሉ። በተመሳሳይም የዋቄፈና ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ የኦሮሞ ዋቄፈታዎች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መሄድ ወደ መደወላቡ ከመሄድ ጋር እኩል እንደሆነ ያምናሉ። የድሬ ሼኽ ሁሴን ሙዳም የዋቄፈና ሀይማኖት ተከታዮች በስምንት አመት አንድ ጊዜ ለቃሉ (ለአባ ሙዳ) ክብር ለመስጠት ወደ መደወላቡ የሚካሄድ ሙዳ ጋር እኩል እንደሆነ ያምናሉ። ይህን አይነት አስተሳሰብ በጥናቱ ወቅት ማግኘቱን Huntingford (1955፡85) ይገልጻል። ወደ መደወላቡ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርግ የዋቄፈና ተከታይ “ጂዓ” የሚል የማዕረግ ስም ሲሰጠው፣ ወደ ድሬ የሚሄድ ግን የተለየ የማዕረግ ስም የለውም።

ድሬ "የሰው ልጅን በአንድ የሚያገናኝ" ስፍራ ነው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች (ከባሌ፣ ከወሎ፣ ከስልጤ፣ ከጉራጌ፣ ከጅማ፣ ከአርሲ፣ ከኢሉአባቦራ፣ ከወለጋ፣ ከቦረና፣ ከሱማሌ ወዘተ.) እንዲሁም በአሜሪካ፣ በአውሮፓና በሌሎችም የዓለም አገራት የሚገኙ የእሳቸው አማኝ የሆኑ ኢትዮጵያውን በመካነ ቅርሱ ይገኛሉ፡፡ ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ የሱማሌ፣ የኬንያ፣ የጅቡቲ፣ የየመን፣ የኢራንና የሳውዲ አረቢያ ዜጎች በዓሉን ለማክበር ይመጣሉ፡፡

በበዓሉ ላይም የተለያየ ብሔር ተወላጆች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የስልጤ፣ የጉራጌ፣ የትግሬ፣ የአርጎባ፣ የሱማሌ፣ የዱቤ፣ የአፋር፣ የከምባታ፣ የማረቆ፣ የሀላባ ወዘተ. ብሔር ተወላጆች በብዛት ይመጣሉ፡፡ የእስልምና፣ የክርስትና፣ የዋቄፈና እንዲሁም የሌሎች ሀይማኖት ተከታዮች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ በዓላት ላይ ከተለያዩ አካባቢዎች፣ አገሮች፣ ብሔሮችና ሀይማኖቶች የመጡ ሰዎች የሚገኙበት በመሆኑ በአገራችን ከሚገኙና በእስልምና፣ በክርስትና፣ በዋቄፈና ወይም በሌሎች ሀይማኖቶች ስርዓተከበራዎች ከሚፈጸምባቸው ስፍራዎች ልዩ ያደርገዋል፡፡

ድሬ ሼኽ ሁሴን የተለያዩ የዓለም ሕዝቦችን፣ የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችንና የተለያዩ ኃይማኖቶች ተከታይ የሆኑ ሕዝቦችን በአንድ የሚያገናኝ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ወደ መካነ ቅርሱ ስለሚሄዱ Eliyas (2002፡19) "ትንሿ ኢትዮጵያ" ብሎ ገልጾታል፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከኢትዮጵያዊ ዜጋ በተጨማሪ ሌሎች ሕዝቦች፣ ከእስልምና ውጪ ያሉ የሌሎች ኃይማኖት ተከታዮችን ጭምር በአንድ የሚያገናኝና "አንድነት በልዩነት ውስጥ" (''Unity through diversity'') የሚንጸባረቅበት የአገራችን ልዩ ስፍራ ነው፡፡ በመሆኑም ድሬ ሼኽ ሁሴን ለእኔ "ትንሿ ዓለም" ነው፡፡

## 4.4.2 የመካነ ቅርሱ እሳቤ ከሼኽ ሁሴን ተቃዋሚዎች አንጻር

የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታይ የሆኑ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖችና የዋቄፈና ኃይማኖት ተከታዮች ሼኽ ሁሴንን አይቀበሉም፡፡ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን አይፈልጉም፡፡ በስፍራው በሚካሄደው መንፈሳዊ ስርዓት ላይም አሉታዊ አመለካከት አላቸው፡፡ ከእነዚህ የኃይማኖት ክፍሎች መካከል የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተከታይ ምሁራን እንዲሁም መካነ ቅርሱን ከዋቄፈና

ኃይማኖት አንጻር በሚያጠኑ ምሁራን በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ የተለየ እሳቤ አላቸው።[81]

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተከታይ ምሁራን የሚያራምዱት የተለየ እሳቤ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን የመሰረቱት አቡነ አኖሪዎስ (ትልቁ) ናቸው የሚል ነው። አቡነ አኖሪዎስ በገድላቸው በምድረ "ወረብ"፣ "ጽጋጋ" ወደሚባል ስፍራ እንደሄዱ ተገልጿል። "ጽጋጋ" እና "ወረብ" በአሁኑ ወቅት የት አካባቢ እንደሚገኙ ሁለት የተለያዩ መረጃዎች ቀርበዋል። አንደኛው፤ "ጽጋጋ" እና "ወረብ" ከሙገር ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ነው (Taddesse, 1972:180)። ሁለተኛው፤ ደግሞ "ጽጋጋ" እና "ወረብ" በሰሜን ባሌ ከዋቤ ሸበሌ ወንዝ 15 ኪ.ሜትር እርቀት ላይ የሚገኙ ስፍራዎች መሆናቸውን አቡነ ጎርጎሪዎስ (1974 ዓ.ም) እና ጥላሁን መኮንን (1990 ዓ.ም) ማብራራታቸውን ዳንኤል (2006 ዓ.ም፡336) ይገልጻል።

በአሁኑ ወቅት "ጽጋጋ" እና "ወረብ" በሚሉ ስያሜዎች የሚጠራ ቦታ በባሌ ዞን ውስጥ መኖሩን የሚገልጽ መረጃ አላገኘሁም። ነገር ግን በጎባ ከተማ በሚገኘው የአቡነ ተክለኃይማኖት ገዳም ጋር በተገናኘ የሚነገር የቃል ታሪክ መኖሩን መረጃ ሰጪዎቼ ገልጸውልኛል። የቃል ታሪኩም ገዳሙ በሚገኝበት ስፍራ አቡነ ተክለኃይማኖት በሕይወት በነበሩበት ወቅት ከደቀመዝሙራቸው ከአቡነ አኖሪዎስ ጋር በመምጣት ክርስትናን እንዳስተማሩ የሚገልጽ ነው።[82] በጎባ ከተማ በሚገኘው የአቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ውስጥ በደባልነት የሚገኝና በአቡነ አኖሪዎስ ስም የተቀረጸ ጽላት አለ። ጽላቱ በገዳሙ የገባው በ1990ዎቹ መጀመሪያ ሲሆን፣ ጽላቱን ያመጡትም በወቅቱ የባሌ ሐገረ ስብከት ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሰላማ ናቸው። ጽላቱ ከገባ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሰኔ 18 አመታዊ የአቡነ አኖሪዎስ መታሰቢያ ቀን በመሆን ይከበራል።[83]

የክርስትና ኃይማኖት በባሌ ዞንና አካባቢው መስፋፋት በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሰው አጼ ዓምደ ጽዮን (1307-1336 ዓ.ም.) ስፍራውን በሸዋ ክርስቲያናዊ መንግስት ቁጥጥር ስር ማድረጋቸው ነው። ንጉሱ በቁጥጥር ስር ያዋሉትን አዲስ ግዛት ጦራቸው ሲቆጣጠር ጦሩን ተከትለው በርካታ የክርስትና ኃይማኖት መሪዎችና የኃይማኖት አባቶች ወደ ስፍራው በመሄድ ክርስትናን ይሰብኩ ነበር (Taddesse, 1972)። ይህ ሁኔታም እንደሌሎች አዳዲስ የንጉሱ ግዛቶች

---

81 - ይህን እሳቤ የምሁራን ያልኩት ስለጉዳዩ ምሁራኑ በግል ተነሳሽነት ካዘጋጇቸው ጥናቶች ባለፈ በኃይማኖቶቹ ሕጋዊ አካሄድ የተወሰነና በግልጽ የተንጸባረቀ አቋም ባለመኖሩ ነው።

82 - ሊቀህሩያን አድማሱ ስሜና ቀሲስ ስንታየሁ አስራቴ፣ ጎባ ከተማ፣ ጥር 15፣ 2008 ዓ.ም።

83 - አባ ወልደ ሚካኤል ገብረ እግዚአብሔር ጎባ ከተማ፣ መስከረም 5፣ 2010 ዓ.ም።

ሁሉ በባሌም ተመሳሳይ ድርጊት በመኖሩ የክርስትና ኃይማኖት አባቶች ወደ ስፍራው በመምጣት ክርስትናን ሊያስፋፉ ችለዋል፡፡

በባሌ ዞን በ14ኛው መቶ ክ/ዘመን የተገነባ ፍልፍል ቤተክርስቲያን በጎባ ከተማ አካባቢ ይገኛል (Merid, 1971:47)፡፡ ይህ ቤተክርስቲያን በአሁኑ ወቅት በጎባ ወረዳ ውስጥ ከጎባ ከተማ በግምት 10 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውና በተለምዶ የአቦ ዋሻ የሚባለው የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን በታነጸበት ቦታ የሚገኝ እንደነበር ይገመታል፡፡ ይህ ቤተክርስቲያን ከአንድ ወጥ ፍልፍል ድንጋይ የታነጸ እንደነበር ይነገራል፡፡ በአሁኑ ወቅት ጥንታዊው የአቦ ቤተክርስቲያን ፍርስራሹ ብቻ በስፍራው የሚገኝ በመሆኑ የቀደሞ ገጽታው ምን አይነት እንደነበር የሚጠቁም መረጃ የለም፡፡ የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ጽላትም በደባልነት በባለወልድ ቤተክርስቲያን ለረጅም አመታት ቆይቶ፣ የዛሬ 20 አመት በተሰራው አዲስ ፍልፍል ዋሻ ውስጥ እንዲያርፍ ተደርጓል፡፡ አዲሱ ፍልፍል ዋሻ ቤተክርስቲያን የታነጸው ጥንታዊው ቤተክርስቲያን የሚገኝበት ስፍራ ላይ ነው፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ የክርስትና ኃይማኖት ከባሌ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ በርካታ መረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህም በጎባ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ በፋሲልና በዓለም ጤና የገጠር ቀበሌዎች ጥንታዊ ቤተክርስቲያናት እንደሚገኙ፣ በደሎ መና ወረዳ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ኃይማኖታዊ ተጋድሎ መፈጸማቸውና ገዳም መመስረታቸው እንዲሁም ታቦተ ጽዮን ከትግራይ ተሰዶ በደሎ መና ወረዳ ሙሳ በሚባል ተራራ ላይ እንደተቀመጠ ይነገራል፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚገኝበት በጃራ ወረዳ ውስጥ በኩባዮ ተራራ፣ በአረብልጅ ተራራና በሐመራ ተራራ ላይ ጥንታዊ ገዳማት እንደሚገኙ፣ በበርበሬ ወረዳ ጥንታዊ ሰው ሰራሽ ዋሻ ቤተክርስቲያን እንደሚገኝ መረጃ ሰጪዎቼ ነግረውኛል፡፡[84] የእነዚህን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም፣ መረጃዎቹ በሕዝቡ ዘንድ በስፋት የሚነገሩና የሚታመኑ ናቸው፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን ከዋቄፈና ኃይማኖት አንጻር በሚያጠኑ ምሁራን የተለየ እይታዎች አሏቸው፡፡ ይኸውም መካነ ቅርሱ ለረጅም ዓመታት የዋቄፈና ኃይማኖት ማዕከል እንደነበር፣ ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ በዋቄፈና ኃይማኖት መሰረት የሚካሄደው የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ቅጣይ እንደሆነ እንዲሁም ሁለቱ መንፈሳዊ ጉዞዎች ተመሳሳይ መሰረት

[84] - አባ ወልደ ሚካኤል ገብረ እግዚአብሔር፣ ጎባ ከተማ፣ መስከረም 5፣ 2010 ዓ.ም፡፡

ያላቸውና የእርስበርስ መወራረስ ያላቸው እንደሆነ መግለጽ ናቸው፡፡ ከባሌ ዞን መደወላቡ አካባቢ በስምንት ዓመት አንዴ ይደረግ የነበረው የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ሲዳከምና እስልምና ሲጠናከር፣ አንዳንዶቹ ወደ መደወላቡ የሚደረገውን መንፈሳዊ ጉዞ ሲቀጥሉ አንዳንዶች ደግሞ መንፈሳዊ ጉዞ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ማድረግ ጀመሩ (Abbas, 2014፡179)፣ (Umer, 2006፡60) እና (Temam, 2002፡13)፡፡

በዚህም ምክንያት በሙስሊም ኦሮሞዎች ዘንድ ወደ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ ጉዞ የአባ ሙዳ ጉዞ ቀጣይ ተደርጎ መታሰብ እንደጀመረ Trimingham (1952፡256) ይገልጻል፡፡ ይህንን የምሁራን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በድሬ ሼኽ ሁሴን በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞና በዋቄፈና ኃይማኖት በስምንት አመት አንድ ጊዜ ከሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ጋር በማያያዝ ለማጥናት የሞከሩ ምሁራን አሉ፡፡ የእነዚህ ምሁራን ሀሳብ መሰረት ያደረገው ሁለቱ መንፈሳዊ ጉዞዎች ያላቸውን ባህርያት፣ በስፍራዎቹ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች፣ እሳቤዎችና ክልከላዎችን ነው፡፡

አናጂና በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ በሼኽ ሁሴን አማካኝነት የእስልምና ማዕከል ሆነ፡፡ የሼኽ ሁሴን ልጅ ኑርላህ አህመድ ስፍራውን በኃላፊነት በሚመሩበት ወቅት በአካባቢው ከባድ ረሃብ በመከሰቱ ምክንያት የእስልምና ማዕከልነቱ ተቋረጠ፡፡[85] በዚህም ምክንያት ስፍራው ለ400 ዓመታት ያህል የእስልምና ማዕከልነቱ ሙሉለሙሉ እንደተቋረጠ ይነገራል፡፡ በእነዚህ ረጅም ዓመታት ውስጥ ስፍራው የዋቄፈና ኃይማኖት ማዕከል በመሆን እንዳገለገለ መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ፡፡[86] በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ሼኽ መሃመድና ሼኽ አባስ ስፍራውን ድጋሚ የእስልምና ኃይማኖት ማዕከል አደረጉት፡፡[87] ሼኽ መሃመድና ሼኽ አባስ ወደ ስፍራው በመጡበት ወቅት የአናጂና ቀበሌ የሰባት የአርሲ ኦሮሞ የጎሳ መሪዎች ይዞታ ሲሆን በስፍራው የነበሩ ነዋሪዎች የዋቄፈና ኃይማኖትን ይከተሉ ነበር (Areba and *et al*, 2003:3)፡፡

---

[85] - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

[86] - አቶ ከዲር ወሌ፣ አቶ ኑማን መሃመድ፣ አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድና አቶ አብዱልናስር አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[87] - ስለሼኽ መሃመድና ስለሼኽ አባስ ማንነት በምዕራፍ 5 ቀርቧል፡፡

### 4.4.3 የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መልክዓምድርና አንድምታው

ቦታ የማህበረሰቡን አዕምሯዊ አስተሳሰብ የሚቀርጽና የሚገልጽ ትዕምርት ነው፡፡ ለኃይማኖት ጥናት የቦታ መልክዓምድራዊ ገለጻ ጠቃሚ ነው፡፡ ከኃይማኖት አንጻር ቦታ በራሱ የቅዱሳን መገኛ ተደርጎ ስለሚታመን የኃይል ስበት ማዕከል (Fields of force) እንደሆነ Fickeler (1962፤97) ይገልጻል፡፡ በአንድ አካባቢ የሚገኝ ተራራ፣ ወንዝ፣ ሜዳ፣ ግንባታ፣ የአየር ጸባይ፣ ዋሻ የመሳሰሉት በቦታው ላይ የሚኖረንን እሳቤ የሚቀርጹ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቦታዎች በራሳቸው የኃይማኖትን እሳቤ የሚቀርጹ፣ የሚገልጹና የሚይዙ ልዩ ምልክቶች ናቸው፡፡ በዚህ ባህርያቸውም መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡

በኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ መሰረት በቦታዎች ላይ ያለን ልዩ ልዩ ምልክቶች በአዕምሮ ውስጥ በማስገባት ትርጉም እንዲይዙና ለማህበረሰባዊ የጋራ እሳቤዎች መፈጠር እንደሚረዱ የሚያቀነቅነው "የአዕምሯዊ ካርታ" አስተሳሰብ ("Mental map'' school) ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ መሰረት ቦታ በሰው አዕምሮ ውስጥ ትርጉም ያለውና የሰው ልጅ ወደ ጎንና ወደ ላይ የሚኖረውን ግንኙነት የሚወስን እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ቦታዎች እንደ መጽሐፍ የሚነበቡና መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡ ቦታዎች ምልክት ሆነው ትርጉም የሚሰጡት በማይታየውና በማይጨበጠው ዓለም ውስጥ ያለን እሳቤ፣ በሚታየውና በሚጨበጠው ዓለም ውስጥ ካለ እሳቤ ጋር በኮግኒቲቭ በማገናኘት ነው፡፡ ምልክቶቹም የሚታዩን በምናባዊ የግንዛቤ ዐይን (Eye of the imaginative conscience) ነው፡፡ ይህ ምናባዊ የግንዛቤ ዐይን ደግሞ ትርጉሞች በአንድ በተወሰነ ማህበረሰብ፣ ባህል፣ ኃይማኖትና አካባቢ ያለን አውድ መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ምክንያት ሆኗል፡፡

ከእነዚህ ሀሳቦች በመነሳት ድሬ ልዩ ምልክት እንዳለው እንረዳለን፡፡ ድሬ፣ ሼኽ ሁሴን እንዲወለዱበት ቀድሞ በፈጣሪ የተመረጠ፣ እሳቸውም የተወለዱበት፣ ያደጉበት፣ የተማሩበት፣ ያስተማሩበት፣ ልዩ ልዩ ተዓምራት የፈጸሙበት፣ ከሰው ተሰውረው የጸለዩበት፣ ነብያትንና ወልዮችን የተቀበሉበት፣ የተቀበሩበት፣ መንፈሳዊ ኃይላቸው ያለበት እንዲሁም ለዘለዓለም ለሰው ልጅ መድህን እንድትሆን የመረጡት ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ የእሳቸው አፍቃሪዎች ያምናሉ፡፡ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ምናባዊ የግንዛቤ ዐይን ድሬ የምድር እምብርት (Pole of the Earth) ወይም የሕዋ ማዕከል (A cosmic center) ነው፡፡ ድሬ በአምላክ ምርጫ የተመሰረተ፣

የምድር እምብርት ወይም የሕዋ ማዕከል በመሆኑ የሰው ልጅ ከአምላኩ ጋር የሚገናኝበት ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ 15 መስኪዶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል 6 መስኪዶች ሚናራ ያላቸው ሲሆኑ 9 መስኪዶች ደግሞ ሚናራ የሌላቸው ናቸው፡፡ የእነዚህ መስኪዶች የፊት ገጻቸው ወደ መካ አቅጣጫ ነው፡፡ በመስኪዶቹም በቀን አምስት ጊዜ እንዲሁም በትልቁ የዙቅጡም መስኪድ የአርብ ጁምዓ የጋራ ስግደት ወደ ካዓባ አቅጣጫ በመዞር ይካሄድባቸዋል፡፡ ይህ የሁሉም የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ድርጊት ነው፡፡ ካዓባ አዳም (የመጀመሪያው የሰው ልጅ) አምላኩን ለማምለክ በምድር ላይ የሰራው የመጀመሪያው ግንባታ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በመካነ ቅርሱ በአንዳንዶች ዘንድ የሼኽ ሁሴን አጽም እንዳረፈበት በሚታመነው ቦታና በሌሎች ግለሰቦች የመቃብር ቦታ ላይ የተሰሩ ገሞዎች አሉ፡፡ ስፍራው የሼኽ ሁሴን መንፈስ የሚገኝበት ቅዱስ ቦታ ነው፡፡ የታመመ የሚድንበት፣ ያጣ የሚያገኝበት፣ ልጅ ያጣ የሚያገኝበት ቅዱስ ስፍራ ነው፡፡ ስፍራው የሰው ልጅን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ በስፍራው የነብዩ መሐመድ የልደት ቀን፣ የሼኽ ሁሴን ልደት ቀንና ሌሎች በዓላት የሚከበሩበት ነው፡፡ እነዚህ የስፍራው ሁነቶች ድሬን "የመንፈስ ኃይል የስበት ማዕከል" እና "የገነት መንደር" እንዲሆን አስችለዋል፡፡

ድሬ "ቅዱስ" ስፍራ ነው፡፡ በኃይማኖት ስርዓት ውስጥ አንድ ስፍራ ቅዱስ የሚባለው አራት መስፈርቶችን ሲያሟላ እንደሆነ Eliade (1959፣37) ይገልጻል፡፡ እነሱም፤ አንደኛ፣ ስፍራው የቃልኪዳን፣ የሕግ፣ የልዩ መለኮታዊ ትዕዛዝ ወይም መሰል አይነት ስምምነት (A break) ያለው ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ይህ ስምምነት ከአንዱ የሕዋ ክበብ (Cosmic region) ወደ ሌላ የሕዋ ክበብ (ከመሬት ወደ ገነት ወይም ከገነት ወደ መሬት ወይም ከመሬት ወደ መሬት በታች) የሚያገኛኝ ትዕምርት ያለው ነው፡፡ ሶስተኛ፣ ከገነት ጋር የሚኖርን ተግባቦት በአንድ ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ምልክቶች የሚገልጽ ነው፡፡ አራተኛ፣ በስፍራው በሚገኝ የሕዋ ነጥብ (Cosmic axis) ዙሪያ ዓለም መኖሯና ነጥቡ የዓለም ማዕከል መሆኑ ነው፡፡

በእነዚህ አራት መስፈርቶች መነሻነት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን ቀጥለን እንመዝነው፡፡ ድሬ ሼኽ ሁሴን እንዲወለዱበት፣ እንዲያስተምሩበትና ተዓምራትን እንዲፈጽሙበት በፈጣሪ የተመረጠ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ደግሞ ድሬ ለሰው ልጅ መድህን እንዲሆን ፈጣሪ

በቃልኪዳን የሰጠው ስፍራ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ድሬ የመለኮታዊ ትዕዛዝና የቃል ኪዳን ስምምነት አለው፡፡

በድሬ የፈጣሪ ቃልኪዳን መኖሩን የሚገልጽ የሼኽ ሁሴን ገሞ ይገኛል፡፡ በዚህ ገሞ አማካኝነት የሰው ልጅ ከሼኽ ሁሴን፣ የሰው ልጅ ከፈጣሪውና የሰው ልጅ ከገነት ጋር ይገናኛል፡፡ በዚህም ባህሪው ከምድር የሕዋ ክበብ ወደ ሰማየሰማይ የሕዋ ክበብ ጋር ያገናኛል፡፡ ይህ መሆኑ የሼኽ ሁሴን ገሞ የሕዋ ነጥብ በመሆን ምድርን ከገነት ጋር፣ ሰውን ከረቂቅ መንፈስ ጋር የሚያገናኝ የዓለም ማዕከል ነው፡፡ በእነዚህ ባህርያቶቹና በ Eliade (1959) መስፈርቶች መሰረት ስፍራው ቅዱስና የዓለም ስርዓትን (''System of the world'') አቅፎ የያዘ እንደሆነ ያሳያል፡፡



*ፎቶ 6፣ የሼኽ ሁሴን ገሞ የሚገኝበት የግንብ አጥር፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

የሼኽ ሁሴን ገሞ በስፍራው ካሉ ሌሎች ገሞዎች የተለየ የኪነህንጻ ጥበብ አለው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች በስፍራው እንደደረሱ የሚዘይሩት (የሚጎበኙት) ነው፡፡ የታመመ እንዲድን፣ ልጅ ያጣ እንዲወልድ፣ የተቸገረ እንዲያገኝ ስለት የሚገባበትና የሚለመንበት ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን ገሞ የመካነ ቅርሱ እምብርት ነው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦችን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን ወዳጆችን ከሼኽ ሁሴን ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ መሬትን ከሰማየሰማያት ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ ይህን ሚናውንም የኪነሕንጻው ዲዛይን ያመላክታል፡፡

ገሞው የሚገኘው በመካነ ቅርስ መሃል ላይ ነው። በዙሪያው ሁለት የግንብ አጥሮች አሉት። የሁለተኛው አጥር ከላይ በፎቶ ላይ እንደሚታየው የመርከብ ቅርጽ አለው። መርከብ መጓጓዣ ነው። ምድር በውኃ በተጥለቀለቀች ዘመን ፍጡራን የዳኑት በኖህ መርከብ ነው። የሼኽ ሁሴን ገሞም አማኞች ከክፉ ነገር የሚድኑበት፣ በመንፈስ ከፍ የሚሉበት፣ ዘራቸውንና ተስፋቸውን የሚያስቀጥሉበት የኖህ መርከብ ነው።

በገሞው አናት ላይ ወደ ሰማይ የወጣ ቀስት መሰል ጉጥ አለ። ይህ ጉጥ ምድርን ከሕዋ ጋር የሚያገናኝ ነው። በጉጡም ምክንያት ሕዋን ወደ ምድር ይስባል፤ ምድርንም ወደ ሕዋ ይወስዳል። ከገሞው ስር የሼኽ ሁሴን አጽም ይገኛል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ገሞው ሶስት አካላትን ያያዘ ነው። ሰማይን፣ መሬትንና ከመሬት በታች ያለን አካል። ይህ ሚናውም ገሞው በመሬት ላይ የሚገኝ የሕዋ እምብርት (Center of the universe) እንዲሆን አስችሎታል። ገሞው ባለው የሕዋ እምብርትነትም የማህበረሰቡን ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ስነልቡናዊ ሁነቶችን የመቅረጽ፣ የመወሰንና የመግለጽ ሚና አለው። ከዚህ አንጻር ገሞው ያለውን እሳቤያዊ ውክልና (Archetype) ስንመለከት ቅዱስነቱን፣ መንፈሳዊ ቅቡልነቱን (Eternal felicity)፣ መንፈሳዊ ፍርድ ሰጪነቱን፣ ምድርን ከገነት ጋር አገናኝነቱን፣ ሕዋ ተሻጋሪነቱን (Cosmic transcendence)፣ ተዓምራት ፈጻሚነቱንና የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ማንነት ወሳኝነቱን ያመላክታል።

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን በሰሜን የዋቤ ሸበሌ ወንዝ፣ በደቡብ የኤጀጉራቲ ወንዝ፣ በምስራቅ የቀቀለም ወንዝና በምዕራብ የበሀራ ወንዝ ያዋስኑታል። መካነ ቅርሱ በ 4 ወንዞች የተከበበ ነው። በወንዝ መከበብ የሰማያዊው የዔደን ገነት ምልክት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ (ኦሪት ዘፍ. 2+10-15) ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔደን ይወጣ እንደነበር፣ ከገነትም ፊሶን፣ ግዮን፣ ጢግሮስና ኤፍራጥስ የተሰኙ አራት ወንዞች ወጥተው ምድርን በተለያዩ አቅጣጫዎች እንደከበቡ ይገልጻል። በቅዱስ ቁርዓን (አብርሃም 14+23) ገነት የወተት ወንዝ፣ የወይን ወንዝ፣ የማር ወንዝና የፍራፍሬ ወንዝ የሚመነጩበት እንደሆነ ይገልጻል።

በመካነ ቅርሱ ክልል 3 ወንዞች ያልፉበታል። ወንዞቹም የአይናገኜ ወንዝ፣ የቆርጋ ወንዝና የጂና ወንዝ ናቸው። ይህ ደግሞ ገነት በቅዱስ ቁርዓን (ሱራ 56+31) "የውኃ መግነጢሳዊ ስሜት" ("Gushing water") በሚል እንደተገለጸው፣ መካነ ቅርሱም ለሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ልዩ የውኃ መግነጢሳዊ ስሜትን የሚሰጥና ሰማያዊውን የዔደን ገነት ቅርጽ በምድር ላይ የያዘ

ነው። ይህ የዔደን ገነት አምሳያ (Replica) በምድር ላይ የማስቀመጥ አንድምታዊ እሳቤ መካነ ቅርሱ እንደገነት የተቀደሰ ተደርጎ እንዲታሰብ ምክንያት ነው።

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በባሌ ሰንሰለታማ ተራሮችና በዋቤ ሸበሌ ሸለቆ መካከል የሚገኝ ሜዳማ ስፍራ ነው። በመካነ ቅርሱ ክልል ውስጥም የደደላ ተራራ፣ የቀጨምሳሬ ተራራ፣ የአበልቃሲም ተራራና የኩባዩ ተራራ ይገኛሉ። የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ዙሪያው በ 4 ተራራዎች የተከበበ ነው። በተራራ መከበብ የምድር ተምሳሌት ነው። በክርስትና ነገረ ፍጥረት (Cosmology) እሳቤ ምድር በተራራ የተከበበች ነች። በምስራቅ አድማስና በምዕራብ ናጌብ የተባሉ ሁለት ተራራዎች አሉ። እነዚህ ተራራዎች እያንዳንዳቸው 12 መስኮቶች አሏቸው። በተመሳሳይም በእስልምና ነገረ ፍጥረት እሳቤ ምድር በ2 ተራራዎች የተከበበች ስትሆን ተራራዎቹም 2 መግቢያ በሮች አሏቸው። መግቢያ በሮቹም በምስራቅ ያለው "ባክሁ" ሲሆን በምዕራብ ያለው ደግሞ "ረስቱኡ" ይባላሉ። ይህ የተራራ ከበባ የእስልምና ነገረ ፍጥረት እሳቤ "ቃፍ" ይባላል።

በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች የነገረ ፍጥረት እሳቤ መካነ ቅርሱ በተራራ መከበብ የምድር ተምሳሌትነት ነው። ፀሐይ በምድር ላይ በምስራቅ በአድማስ ተራራ ላይ ወጥታ፣ በምዕራብ በናጌብ ተራራ ላይ ትጠልቃለች። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም ፀሐይ በምስራቅ አቅጣጫ በሚገኘው የአበልቃሲም ተራራ ላይ ወጥታ፣ በምዕራብ አቅጣጫ በሚገኘው የደደላ ተራራ አናት ላይ ትጠልቃለች። ይህም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከምድር ጋራ ያለውን ተመሳስሎ ያሳያል። ምድር የፍጡራን መኖሪያ ብቸኛ ፕላኔት እንደሆነች ሁሉ፣ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም የፍጡራን ሁሉ የጋራ መሰብሰቢያና መዳኛ ስፍራ ነው።

በአፍቃሪዎቻቸው ዘንድ ሼኽ ሁሴን ያላቸው ሰብዓዊ እሳቤና የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አንድ አይነት ባህርይ አላቸው። ሼኽ ሁሴን የሁሉም ፍጡር አባት ናቸው። ሼኽ ሁሴን አቃፊ፣ ደጋፊና ሰብሳቢ ናቸው እንጂ ገፊና አግላይ አይደሉም። የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም የሁሉም ነው። ወደ መካነ ቅርሱ የሚሄድ ሰው ሁሉ በስፍራው ሲደርስ ነጻነት ይሰማዋል፤ የእኔነት ስሜት ይሰማዋል እንጂ የባይተዋርነት፣ የመገለልና የመነጠል ስሜት አይሰማውም። በመሆኑም ሼኽ ሁሴን የመካነ ቅርሱ፣ መካነ ቅርሱ የሼኽ ሁሴን አምሳያ ነው። ይህን የሼኽ ሁሴን ማንነትንና የመካነ ቅርሱን አምሳያዊ ትስስር በተሻለ መንገድ የሚገልጽ የግዕዝ አባባል አለ። አባባሉም "ሰብዕ ይቄድስ ለመካን፣ ወመካንስ ያከብሮ ለሰብዕ።" የሚል ሲሆን፣ ትርጉሙም፣ "ሰው ቦታን ይቀድሳል (ያነጻል)፣ ቦታ ደግሞ (በምላሹ) ሰውየውን ያከብረዋል

(ይዘክረዋል)" ማለት ነው። ሼኽ ሁሴንም የመካነ ቅርሱን ባህርይ ቀራጭ ናቸው። መካነ ቅርሱም የሼኽ ሁሴን ማንነት ነጸብራቅ ነው።

## 4.4.4 የቀናት ውክልናዊ አንድምታ

ቀናት በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ውክልና አላቸው። ሁሉም ቀናት እኩል ዋጋ የላቸውም። በወራትና በሳምንት ካሉት ቀናት መካከል የተለየ ማህበራዊና ኃይማኖታዊ ዋጋ ያላቸው የተወሰኑ ቀናት አሉ። በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ማክሰኞ የተለየ ክወና የሚፈጸምበትና ልዩ መንፈሳዊ ዋጋ ያለው ዕለት ነው። ለዚህ ሁለት ምክንያቶች ይገለጻሉ። አንደኛው፣ ማክሰኞ ሼኽ ሁሴን የተወለዱበትም፣ ሕይወታቸው ያለፈበትም ዕለት እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም ማክሰኞ የሼኽ ሁሴን ዕለት ነው። ማክሰኞ ሼኽ ሁሴን የሚለመኑበት፣ የሚዘከሩበትና የሚወደሱበት ዕለት ነው። አንዳንድ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች በዕለተ ማክሰኞ ከቤታቸው ሳይወጡ ቀኑን ሙሉ በዱዓ (በጸሎት) ያሳልፋሉ። አንዳንዶች ደግሞ በዚህ ዕለት መንገድ አይሄዱም፤ ስራ አይሰሩም።

ሁለተኛው ደግሞ ሼኽ ሁሴንና ተማሪዎቻቸው ማክሰኞ በጋራ ጸሎት የሚያደርጉበትና እቅድ የሚያወጡበት ዕለት እንደነበር ይነገራል። ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት እሳቸውና ተማሪዎቻቸው የሚከውኗቸውን ስራዎች በሳምንት ውስጥ ባሉት ቀናት የተከፋፈሉ ነበር። ከሳምንቱ ቀናት መካከል ማክሰኞ ዕለት እሳቸው ከተማሪዎቻቸውና ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በጋራ ዱዓ የሚያደርጉበት እንደሆነ መሐመድ (ገጽ፡28) ይገልጻል። በዕለቱም ከአካባቢው ርቀው የሚኖሩ ሰዎችም እሳቸው ዘንድ ማክሰኞ ዕለት በመምጣት አብረው ዱዓ ያደርጉ ነበር። ማክሰኞ ሼኽ ሁሴን ከተማሪዎቻቸው ጋር በመሆን የሳምንቱን ስራ የሚገመግሙበትና ለቀጣይ ሳምንትም የሚሰሩትን ስራ እቅድ የሚያወጡበት እለት እንደነበር ይነገራል።

በእነዚህ መረጃዎች መሰረት ማክሰኞ ዕለት እሳቸው ከተማሪዎቻቸውና ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር የሚገናኙበት፣ በጋራ ዱዓ የሚደረግበት፣ የሳምንቱ ስራ የሚገመገምበትና የቀጣይ ሳምንት ዕቅድ የሚወጣበት እንዲሁም የሼኽ ሁሴን የውልደትም የሕልፈትም መታሰቢያ ነው። ማክሰኞ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎችን ከሼኽ ሁሴን ጋር የሚያገናኝ፣ የሼኽ ሁሴን መንፈስ ለአማኞቻቸው ቅርብ የሚሆንበትና በሰው ልጅና በመንፈስ መካከል የጋራ የሕዋ ነጥብ (cosmic axis) የሚፈጥር ዕለት ነው። በተመሳሳይ ሼኽ ሶፍዑመር ማክሰኞ እንደተወለዱ ይታመናል። ማክሰኞ የሼኽ ሶፍዑመር የመታሰቢያ ዕለት ነው። በመሆኑም ይህ ዕለት በሼኽ ሁሴን ወዳጆች ዘንድ

ልዩና የተቀደሰ ነው። ይህንንም ለማሰብ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች መንፈሳዊ ስርዓቶችን ይፈጽማሉ፤ ለሼኽ ሁሴንም ያላቸውን ፍቅር ይገልጻሉ።

በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ከማክሰኞ በተጨማሪ ሁሉም የሳምንቱ ቀናት የራሳቸው መታሰቢያ አላቸው። በዕለቱም የሚታሰቡ አካላት "ችሎት" የሚቀመጡበት፣ ፍርድ የሚሰጡበት፣ አቤቱታ የሚሰሙበት፣ አማኞቻቸውን የሚቀርቡበትና መንፈሳቸውን በቀጥታ ከአማኞቹ ጋር የሚያገናኙበት እንደሆነ ይታመናል። የሳምንቱ የመታሰቢያ ቀናትም፣ ሰኞ የመላዕኩ ቅዱስ ገብረኤል መታሰቢያ ዕለት ነው። ማክሰኞ የሼኽ ሁሴን መታሰቢያ ዕለት ነው። ረቡዕ የሼኽ አብዱልቃደር ጀይላኒ መታሰቢያ ዕለት ነው። ሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒ የመጀመሪያው የሱፊስት አስተምህሮ ስርዓት የሆነውን የቃድሪያ ስርዓት መስራች ሲሆኑ፣ ሼኽ ሁሴንን ለመጎብኘት ከኢራቅ ባግዳድ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን እንደመጡ ይነገራል።

ሐሙስ የሰዒድና ባላባስ ዕለት ነው። ሰዒድና ባላባስ የጅማው ንጉስ እንደሆኑ ይነገራል። አርብ በእስልምና ኃይማኖት አማኞች በመስኪድ በመገኘት የጋራ ስግደት የሚፈጽሙበት የጁምዓ ዕለት ነው። ይህ ዕለት የሁሉም ነብያት ቀን እንደሆነና ሁሉም ነብያት አንድ ላይ የሚሰባሰቡበት እንደሆነ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ያምናሉ። ቅዳሜ የሰዒድና ከዲር መታሰቢያ ነው። ሰዒድና ከዲር ትልቅ የአላህ ባርያና ወልይ እንደሆኑ ይታመንባቸዋል። በገነት ውስጥ የሚገኝ 'ማኡ ሃያት' የሚባል ውኃ አለ። ይህንንም ውኃ የጠጣ ለዘለዓለም ይኖራል ተብሎ ይታመናል። ሰዒድና ከዲር ይህንን የገነት ውኃ እንደጠጡ ይነገራል። እሁድ የእረፍት ቀን ነው። እሁድ የጌታ (የፈጣሪ) ቀን ነው።

ከሳምንቱ ቀናት ውስጥ ለተወሰኑ ቀናት ልዩ ዋጋ መስጠት በተለያዩ ኃይማኖቶች፣ መንፈሳዊ ቦታዎችና ባህሎች ውስጥ የተለመደ ነው። በክርስትና ኃይማኖት የመላእክት፣ የሰማዕትና የቅዱሳን ወርኃዊና አመታዊ የመታሰቢያ ቀናትና ዕለተ እሁድ የተቀደሱ ስለሆኑ ስራ አይሰራም። አንዳንድ የአዮ ሞሚና (ፈረቀሳ) አፍቃሪዎች ረቡዕ፣ ሐሙስና ቅዳሜን በልዩ ሁኔታ ያከብራሉ። በእነዚህ ቀናት ከቤት አይወጡም፤ ስራ አይሰሩም። በአርሲ ኦሮሞዎች ባህል የዕርቅ ስርዓት የሚከወነው ማክሰኞ፣ ሀሙስ ወይም እሁድ ብቻ ነው (ሰሎሞን፣ 2002 ዓ.ም፣41)። በባህሉ መሰረት ረቡዕና አርብ የዱር እንስሳት ወሲብ የሚፈጽሙበት ዕለት (Guyyaa chegnoo) ናቸው። ሰኞ ደግሞ ሙታን ቤተሰቦችን የማሰቢያ ዕለት (Guyyaa ekeeraa) ነው። በእነዚህ ቀናት ዕርቅ ቢካሄድ ሰላማዊ መፍትሄ አይገኝም፤ እርቁም አይሰምርም ተብሎ ይታመናል።

በእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ አርብና ቅዳሜ ልዩ ዋጋ የሚሰጣቸው ቀናት ናቸው፡፡ አርብ የጋራ ስግደት የሚሰገድበት የጁምዓ ዕለት (ያውም-አል-ጁማ) ነው፡፡ አርብ በእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ልዩ መንፈሳዊ ዋጋ ያለው ዕለት ነው፡፡ በዕለቱ በጋራ የሚሰገድበትና የመገናኛ እንዲሆን የወሰኑት ነብዩ መሐመድ መሆናቸውን የታሪክ ጸሐፍት ይገልጻሉ (Gulevich, 2005፡372)፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም እንደሌሎች የእስልምና ተከታዮች ሁሉ በዕለቱ የጋራ ስግደት በትልቁ የሼኽ ሁሴን (ዙቅጡም) መስኪድ ይሰግዳሉ፡፡ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች በዕለቱ ከሚካሄድ ስግደት በተጨማሪ አርብ የሁሉም ነብያት የመታሰቢያ ዕለት እንደሆነ ማመናቸው ከሌሎች የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የተለየ ያደርጋቸዋል፡ ቅዳሜ የእረፍት ቀን ወይም የሰንበት ቀን (ያውም-አል-ሳብት) ነው (Gulevich, 2005)፡፡ ይህ ቀን የሳምንቱ የመጨረሻ ቀን በመሆኑ የእረፍት ቀን ነው፡፡ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ቅዳሜ የሰዒድና ከዲር መታሰቢያ ሲሆን፣ የእረፍትና የፈጣሪ ቀን እሁድ ነው፡፡

በዘመነ ሐዋርያት የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ስርዓተ አምልኮ የመፈጸሚያ ቀን እንደነበር የሐዲስ ኪዳን መረጃዎች (ሐዋ 20+7 እና 1ኛ ቆሮ 16+2) ያሳያሉ፡፡ በ4ኛው እና በ5ኛው መቶ ክ/ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች "ሰንበት" የሚለውንና "የጌታ ቀን" የሚለውን ስያሜ ለሁለት የተለያዩ ቀናት በመስጠት ይጠቀሙ ነበር (ዳንኤል፣2010 ዓ.ም፡104)፡፡ ሰንበት ሲሉ ሰባተኛዋን ቀን (ቅዳሜን) ሲሆን፣ የጌታ ቀን ሲሉ ደግሞ የሳምንቱን የመጀመሪያ ቀን (እሁድን) ማለታቸው ነው፡፡

በ350 ዓ.ም የተካሄደው የሎዶቅያ ጉባኤ "ክርስቲያኖች ሰንበትን (ቅዳሜን) ከስራ በመታገድ ማክበር የለባቸውም፣ የጌታ ቀን (እሁድ) የእረፍት ቀን ነው፡፡ የክርስቲያኖች ቀን ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ወደ አባቱ አርጓልና፡፡" ሲል እሁድን የጌታ ቀን አድርጎ በመምረጥ አጸደቀ (ዳንኤል፣2010 ዓ.ም)፡፡ በአገራችን እሁድን የዕረፍት ቀን አድርጎ መውሰድ ከሎዶቂያ ጉባኤ በኋላ የተጀመረ የክርስትናው አስተምህሮ ነው፡፡ በሼኽ ሁሴን ወዳጆችና በሌሎች የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ እሁድን የእረፍት ቀን አድርጎ መውሰድ አገሪቷ የምትከተለው የመንግስት የስራ ቀናት ፕሮግራም ተጽዕኖ በማሳደሩ ምክንያት የመጣ ይመስላል፡፡

ከአርብና ከቅዳሜ ቀናት በተጨማሪ በእስልምና ኃይማኖት ረቡዕና ሐሙስ ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል፡ በእነዚህ ቀናት የተለያዩ ስርዓቶች ይፈጸማሉ፡፡ እነዚህ ቀናት በምረቃት (አል-

ባራካሕ) ይመሰላል፡፡ ሰርግ ለመሰረግ፣ የመኖሪያ ቤት ወይም የመስኪድ ግንባታ መሰረት ለመጣል፣ ተማሪዎች የቁርዓን ትምህርታቸውን ሲጨርሱ የሚካሄድ የምርቃት ስርዓት (ዋሊማሕ አል-ቁርዓን) ሁሉ በእነዚህ ቀናት ቢከወኑ የተሻለ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በእስልምና ኃይማኖት፣ በክርስትና ኃይማኖትና በሌሎች እምነቶች ለልዩ ክወናዎች ልዩ ቀናትን መምረጥ ያለው እሳቤ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድም ይስተዋላል፡፡ ይህ መሆኑም በእስልምና እና በክርስትና ኃይማኖቶች አስተምህሮና በሌሎች እምነቶች ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችን በአንድ ያዋሐደ እንደሆነ ያመላክታል፡፡

## 4.5 የሼኽ ሁሴን ኃይማኖታዊ ሚና እና የቴክኖሎጂ አስተዋጽኦ

በዚህ ክፍል የሼኽ ሁሴን ኢማምነት፣ እስልምናን የማስፋፋት ሚና እንዲሁም የሼኽ ሁሴን የቴክኖሎጂ አስተዋፅኦ ይቀርባል፡፡

### 4.5.1 የሼኽ ሁሴን ኢማምነትና እስልምናን የማስፋፋት ሚና

ሼኽ ሁሴን ከአባታቸውና በወቅቱ ከነበሩ ሌሎች ግለሰቦች የቁርዓን ትምህርትን በትውልድ ስፍራቸው አናጂና እንደተማሩ ይነገራል፡፡ የቁርዓን ትምህርታቸውንም ለማሻሻል ባሌ ዞን ጊንር ወረዳ ሀረዋ ሚስራ በሚባል ቦታ በመሄድ ሼኽ ሙሳ ጋሪ ከሚባሉ የኃይማኖት ሊቅ ዘንድ ተጨማሪ የሀይማኖት ትምህርት ተምረዋል፡፡ ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ለተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት እንግሊዝ አገር እንደተማሩ ይነገራል፡፡ በግብጽ አገር በሚገኘው ታዋቂው የአል-አዛር ዩኒቨርሲቲ እንደተማሩ ይነገራል፡፡[88] ከእንግሊዝና ከግብጽ አገራት በተጨማሪ የመን፣ ቱኒዝያና ሕንድ አገራት ሄደው የተለያዩ ሀይማኖታዊ ትምህርቶችን እንደተማሩ ይነገራል፡፡[89]

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና ሀይማኖት ህግጋትና የቁርዓን ትምህርት ማስተማሪያ ጠንካራና የተደራጀ ተቋም ነበር፡፡ እሳቸው ዘንድ የሀይማኖት ትምህርት ለመማር ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚመጡ ተማሪዎች (ደረሳዎች) ነበሩ፡፡ እሳቸው በህይወት በነበሩበት ዘመን 6,666 ደረሳዎችን በአናጂና ሀይማኖታዊ ትምህርት ማስተማራቸው ይነገራል፡፡ በወቅቱ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በትክክል 6,666 ተማሪዎች መማራቸውን የሚገልጽ መረጃ

---

[88] - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 9 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡
[89] - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አቶ ኑማን ሼሕ መሃመድ፣ ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

መሰነድ ያስቸግራል። እሳቸውም ይህን ያህል ተማሪ አላስተማሩ ይሆናል። ይህ ቁጥር በእስልምና ልዩ ሀይማኖታዊ ውክልና አለው።

ይህም ቅዱስ ቁርዓን 6,666 ንዑስ ክፍሎች (Verses) አሉት። ይህ ቁጥር የእኩልነት፣ የፍትሃዊነትና የአቻቻይነት ምልክት ነው። ሼኽ ሁሴን 6,666 ተማሪዎች እንዳስተማሩ መነገሩ፣ ይህ ቁጥር አንድም ከቅዱስ ቁርዓን ክፍሎች ጋር ለማያያዝ፣ አንድም የሼኽ ሁሴንን ፍትሃዊነት፣ ሁሉን በእኩል ዐይን የማየትና የሁሉም ሕዝብ የመሆን ባህርይ ለመወከል የቀረበ ትዕምርት ሊሆን ይችላል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ሺሕ ዓመት" የሚል አገላለጽ አለ። እስራኤላዊያን ኢዮስያስ በነገሰ ጊዜ "ሺሕ ዓመት ንገስ" እያሉ ይመርቁት ነበር (2ኛነገሥ 11+12)። በተለምዶም "ሺሕ ያድርግህ፣ ሺሕ ሁን" የሚሉ ምርቃቶችና "ሺፈራው፣ የሺእመቤት፣ የሺጥላ" የሚሉ ስሞች የተለመዱ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ "ሺሕ" የሚለው ቃል ብዛትን እንጂ ሐሳባዊ ልኬትን አያሳይም (ስቡሕ፣1997 ዓ.ም)። ሺሕ የሚለው አገላለጽ ብዙ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው፣ የትየሌሌና እልፍአዕላፍ የሚለውን አገላለጽ የሚተካ ነው።

ሼኽ ሁሴን 6,666 ተማሪዎችን አስተምረዋል የሚለው አገላለጽ ምናልባት ልክ እንደ ሺሕ ሁሉ፣ 6,666 ብዙነትንና እልፍአዕላፍነትን የሚወክል ትዕምርታዊ ቁጥር እንጂ ሐሳባዊ ልኬት ላይሆን ይችላል። ለዚህ ሀሳብ ማጠናከሪያ የሚሆን አንድ ሚት በሼኽ ሁሴን ተዓምራት ላይ ይነገራል። ይህም ሚት

> በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴንን ለመግደልና አካባቢውን ለማጥፋት የኢቱና የሀርላ ጎሳ ሕዝቦች 6,666 ያህል ሆነው ጦርና ጎራዴ ይዘው ሲመጡ፣ አንድ የሼኽ ሁሴን ተማሪ ከሩቅ ያያል። በወቅቱም ሼኽ ሁሴን ቁርዓን እየቀሩ ነበር። ተማሪያቸውም በፍጥነት እስራቸው ደርሶ እረ ሊጨርሱን ነው፣ ጦር እየመጣ ነው። ይላቸዋል። ሼኽ ሁሴንም አንገታቸውን በቀስታ ወደ ጦሩ አቅጣጫ ዞር ሲያደርጉ፣ የመጣው ጦር በሙሉ ከመቅስፈት ባሉበት ቦታ ወደ ድንጋይነት ተለውጠውና ደርቀው ቀሩ።[90]

የሚል ነው። ይህ ሚት ሶስት ነገሮችን ያሳያል። አንደኛው፣ በወቅቱ የኢቱና የሀርላ ሕዝቦች በአካባቢው ይኖሩ እንደነበር ነው። ሁለተኛው፣ ሼኽ ሁሴን ዞር ብለው በማየት ብቻ ጦሩን ወደ ድንጋይነት መቀየራቸውን ነው። ይህም እሳቸው ያላቸውን ልዩ መንፈሳዊ ኃይል የሚያሳይ ነው። ሶስተኛው፣ እሳቸውንና አካባቢውን ሊያጠቃ የመጣው ጦር ብዛት 6,666 ተብሎ

---

[90] - አቶ አቡሻ ኃይሉ፣ ቢሾፍቱ፣ የካቲት 10 ቀን 2010 ዓ.ም።

የተገለጸው ጦሩ አንድ በአንድ ተቆጥሮ ሳይሆን የጦሩን ብዛት ለመግለጽ ነው፡፡ የጦሩም ብዛት 6,666 ተብሎ የተገለጸው "እጅግ ብዙ" ወይም "እልፍአዕላፍ" የሚለውን እሳቤ የሚተካ ቁጥር እንጂ ሐሳባዊ ቀመር አለመሆኑን ነው፡፡

በወቅቱ በመካነ ቅርሱ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመረቁ ወደ ተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች በመሄድ የራሳቸውን የእስልምና ትምህርት ቤቶችና ሀይማኖታዊ ስፍራዎች በመመስረት ያስተምሩና ሀይማኖቱን ያስፋፉ ነበር፡፡ የእሳቸው ተማሪዎች ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደተለያዩ አካባቢዎች ሄደው ሀይማኖቱን ለማስተማር ሲሰማሩ የሚሄዱበትን ማህበረሰብ ቋንቋ የማወቅና በማህበረሰቡ ቋንቋ ኃይማኖቱን የማስተማር ግዴታ እንደነበረባቸው ይነገራል፡፡[91]

ተማሪዎችም ቁርዓን ለማስተማር ከሄዱባቸው ቦታዎች በየ6 ወሩ እሳቸው ዘንድ በመምጣት ምርቃትና ተጨማሪ የሀይማኖት እውቀት ያገኙ ነበር፡፡ ተማሪዎቹም ወደ ስፍራው ሲመጡ በአካባቢው ስላጋጠማቸው ነገር ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ነበረባቸው፡፡[92] በወቅቱም ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች በመምጣት ከእሳቸው ዘንድ የተማሩ ደረሳዎች በተለያዩ አካባቢዎች በመሄድ የእስልምና ትምህርትን ያስፋፉ በርካታ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ እስካሁን ድረስ ከፍ ያለ ስም ያላቸውና ቅዱሳን እንደሆኑ የሚታመንባቸው ናቸው፡፡ በወቅቱ የእሳቸው ተማሪዎች በነበሩ የኃይማኖት አባቶች ስም በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች የተገነቡ የሀይማኖት ማዕከላት አሉ፡፡

ከእሳቸው ተማሪዎች መካከል ሼኽ ሶፍ ዑመር፣ ፋቂህ አቡን፣ ፋቂህ አልዲን፣ አቦ ኮይ፣ አልይ ባህሪ፣ ላዚሙል ባህሪ፣ አህመድ ነጃሺ፣ ሳሊሁ ናሕዊ፣ ሼኽ ቂምንይ፣ ሼኽ ኢብራሂም ዳሞሌ፣ ሐጂ ናስር፣ ሐጂ ሳቢር፣ ሐጂ ሻሌ፣ ሐጂ ሳዲቅ፣ አረብ ልጅ፣ ሼኽ መሃመድ ሚስኪ፣ ላዚሙል በክሪ፣ ኑር አሚን እና ሮባ ቢኑ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚገኙ ገሞዎች መካከልም የሼኽ ሁሴን ተማሪ በነበሩት ሼኽ መሃመድ ሚስኪ ስም የተገነባ ገሞ ይገኛል፡፡ በስፍራው የሼኽ መሃመድ ሚስኪ ገሞ መኖሩ እሳቸው አናጂና እንደኖሩና በስፍራው አስክሬናቸው እንዳረፈ አንድ ማሳያ ነው፡፡

---

[91] - አቶ መለሰ መስቀላ፣ ሮቤ፣ ጥር 17 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[92] - አቶ መለሰ መስቀላ፣ አቶ መንግስቱ አሸኔ፣ አቶ ከዲር ማሜ፣ ሮቤ፣ ጥር 17 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

የሼኽ ሁሴን ልጅ ሼኽ ኑርላህ አህመድ መካነ ቅርሱን በሚያስተዳድሩበት ወቅት በአካባቢው በተከሰተ ረሃብ ምክንያት መካነ ቅርሱ የነበረው የኃይማኖት ማዕከልነት ሙሉለሙሉ ተቋረጠ፡፡ በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን በሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞና በሼኽ አባስ አማካኝነት መካነ ቅርሱ ድጋሚ ተቋቋመ፡፡ ስፍራውም ድጋሚ የኃይማኖት ትምህርት ማዕከል በመሆን በርካታ ተማሪዎችን መንፈሳዊ ትምህርት አስተምሯል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በስፍራው ኃይማኖታዊ ትምህርት ይማራሉ፡፡ መካነ ቅርሱ ድጋሚ የኃይማኖት ማዕከል ከሆነ በኋላ ለተማሪዎች ማንበቢያ እንዲሆን የተገነባ ቤተመጻሕፍት አለ፡፡





*ፎቶ፣8 በመካነ ቅርሱ የሚገኝ ቤተመጻሕፍ ውጫዊ ገጽታ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

*ፎቶ፣9 የቤተመጻሕፍቱ ውስጣዊ ገጽታ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በመካነ ቅርሱ የሚገኘውና በአሁኑ ወቅት አገልግሎት የማይሰጠው ከላይ በፎቶግራፍ የቀረበው ጥንታዊ ቤተመጻሕፍት ራሱን ችሎ የተገነባ ነው፡፡ ቤተመጻሕፍትም ለመጻሕፍት መደርደሪያ በሚል በክፍሉ ግድግዳ ላይ በርካታ መደርደሪያዎች በድንጋይ ተሰርተው ይገኛሉ፡፡ ከላይ በፎቶ ግራፉ ላይ እንደሚታየው በቤተመጻሕፍት ውስጥ በቂ የፀሐይ ብርሃን እንዲኖር ጣሪያው መሃል ላይ የፀሐይ ብርሃን የሚያስገባ ስስና ነጭ ቀለም ያለው ቆርቆሮ አለው፡፡ በወቅቱ በፓፒረስና በብራና ላይ የተጻፉ የተለያዩ የሀይማኖት፣ የፍልስፍና፣ የስነምግባር መጻሕፍትና መዛግብት እንደነበሩ ይነገራል፡፡ በአሁኑ ወቅት እነዚህ መጻሕፍትና መዛግብት አብዛኛው

በግለሰቦች እጅ የሚገኙ ሲሆን፣ 11 መዛግብት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት እጅ ይገኛሉ።

### 4.5.2 የሼኽ ሁሴን የቴክኖሎጂ አስተዋጽኦ

ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ለአካባቢው አስተዋውቀዋል። ከእነዚህ መካከል የኪነ-ህንጻ ግንባታ፣ የውኃ ጉድጓድ ግንባታና የሰፋፊ እርሻ ቴክኖሎጂዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ 15 መስኪዶች አሉ። መስኪዶቹም ባላ፣ ዙቅጡም፣ ሼኽ አልይ፣ ሼኽ መሀመድ ቲልማ ቲልሞ፣ ሼኽ መሀመድ ቃሶ፣ ሼኽ ኡመር፣ ሼኽ አደም፣ ሐጂ አባስ፣ ሼኽ ኢብራሂም፣ ሼኽ ከዲር፣ ጎባ፣ ቂብላ፣ ማረፊያ እና ሐላጌ በሚሉ ስያሜዎች ይታወቃሉ። ከእነዚህም መካከል ከ900 አመት በላይ እድሜ እንዳላቸው የሚነገርላቸው የባላ እና የዙቅጡም መስኪዶች ይገኛሉ። የባላና የዙቅጡም መስኪዶችን ያስገነቡት ሼኽ ሁሴን እንደሆኑ ይነገራል።

በባላና በዙቅጡም መስኪዶች ግንባታ ላይ የሚነገሩ ሁለት ሀሳቦች አሉ። አንደኛው፤ ሼኽ ሁሴን የምህንድስና ባለሙያዎችን ከየመን አገር አስመጥተው እንዳስገነቡ የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በአካባቢው ይኖሩ እንደነበር የሚታመኑት የሀርላና የኢቱ ሕዝቦች በሼኽ ሁሴን ትዕዛዝ መገንባታቸውን የሚገልጽ ነው።[93] ሼኽ ሁሴን ከባላና ከዙቅጡም መስኪዶች በተጨማሪ የሳኬታን መስኪድ በሐረር እና የሔሮን መስኪድ በባሌ ዞን ቤልቱ ወረዳ እንደገነቡ ይነገራል።

---

[93] - ሼኽ አደም ከሪም እና አቶ ሀሰን አብደላ፣ ሮቤ ከተማ፣ ጥር 8 ቀን፣ 2008 ዓ.ም።



*ፎቶ፣ 10፣ የባላ መስኪድ ከፊል ገጽታን የሚያሳይ። (ከØstebo (2012) ጥናት የተወሰደ።)*

የባላና የዙቅጡም መስኪዶች መቼ እንደተገነቡ በትክክል ባይታወቅም፣ በቃል ከሚነገሩ ታሪኮችን መሰረት በማድረግ የባላ መስኪድ ከተገነባ 971 አመት እንደሆነው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፡2) ይገልጻል። የባላ መስኪድ በ1067 እንደተገነባ Østebo (2012፡52) ይገልጻል። Abinet (2011:52) ደግሞ መስኪዱ የ935 ዓመት እድሜ እንዳለው ይገልጻል። መስኪዱ ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ 9 ኪ. ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። የመስኪዱ ስፋት 40 ሜትር በ40 ሜትር ነው። በአሁኑ ወቅት የመስኪዱ አብዛኛው ክፍል የፈረሰ ሲሆን፣ ምሰሶዎቹና ከፊል ግድግዳው ብቻ ቀርተዋል። መስኪዱ በአሁኑ ወቅት ቋሚ አገልግሎት ባይሰጥም የተወሰኑ ግለሰቦች የመውሊድ በዓልን ያከብሩበታል።

የዙቅጡም መስኪድ ከተገነባ 944 አመት እንደሆነው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፡2) ይገልጻል። የዙቅጡም መስኪድ ከተገነባበት ዓመት ጀምሮ እስካሁን ድረስ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ይህ መስኪድ ሼኽ ሁሴንና የእሳቸው ተማሪዎች ከባላ ቀጥሎ የገነቡት ሁለተኛው መስኪድ ነው። የዙቅጡም መስኪድ 27.75 ሜትር ርዝመት፣ 22.35 ስፋትና 3 ሜትር ቁመት እንዳለው Hailemelekot and Mulugeta (2015:23) ይገልጻሉ። ግድግዳው ትልልቅ ድንጋዮችን በመደርደርና በማጣበቅ የተሰራ ሲሆን ጣሪያው ከእንጨትና ከአፈር የተሰራ ነው። ዙቅጡም በኪነ-ህንጻ አሰራሩ፣ በተጠቀሚቸው የመስሪያ ግብዐቶች፣ መስኪዱን ባቆሙት 31 ትልልቅ የድንጋይ ምሰሶዎችና ዲዛይኑ እጅግ ልዩና በወቅቱ የነበረውን የኪነ-ህንጻ ባህል የሚያሳይ የአገራችን ቅርስ ነው።



*ፎቶ 11፣ የዙቅጡም መስኪድ ውጪያዊ ገጽታ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

መስኪዱ በተለምዶ ዙቅጡም ይባል እንጂ ትክክለኛ ስሙ "ዘቀጡም" እንደሆነ መሐመድ (አመት የለውም፣ገጽ4) ይገልጻል፡፡ ቃሉም የአረብኛ ምህጻረ ቃል ሲሆን፣ ሙሉ ንባቡም "ዛውየቱ ቀርየቲ ጡላቢል መድረሳ" ነው፡፡ የአማርኛ ትርጉሙም "የሰፈሩ መድረሳ ተማሪዎች ጸሎት ቤት" እንደማለት ነው፡፡ በወቅቱ ሼኽ ሁሴን የባላ መስኪድን ትተው ለምን የዙቅጡም መስኪድን ሊገነቡና ለምን ቦታውን ለቀው እንደመጡ በትክክል ባይታወቅም በወቅቱ በአካባቢው የውኃ እጥረት መከሰቱና በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩ ተቃዋሚዎቻቸው ጋር በተከሰተ አለመግባባት እንደሆነ የሚነገሩ መላምቶች አሉ፡፡ ይህ መስኪድ በተለያዩ ወቅቶች በተደረገለት እደሳና የማስፋፋት ስራ ምክንያት እስካሁን እያገለገለ ይገኛል፡፡ የዙቅጡም መስኪድ የሼኽ ሁሴን መስኪድ በሚል ስያሜም ይታወቃል፡፡ መስኪዱን በኢማምነት ከ30 ዓመታት በላይ የመሩት ሼኽ ኢድሪስ አሰፋ ነበሩ፡፡ እሳቸውም በ2009 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ፣ ሼኽ መሃመድ አለሙ የተባሉ በእድሚያቸው ወጣት የሆኑ ኢማም መስኪዱን መምራት ጀምረዋል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን 9 ሰው ሰራሽ የውኃ ኩሬዎች አሉ፡፡ የውኃ ኩሬዎቹም ሀሮ ቁራ፣ ሀሮ ሉኩ፣ ሀሮ ድንኩሬ፣ ኡመሮ፣ ሀሮ አናኒ፣ ሀሮ ሼኽ መሃመድ ሚስኪ፣ ሀሮ ሐጂ አብዱልቃድር፣ ሀሮ ዲምቱና ሀሮ ሐርአዲ ናቸው፡፡ ሀሮ በኦሮምኛ ኩሬ ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ኩሬዎች መካከል ረጅም እድሜ ያስቆጠረው ሀሮ ቁራ ነው፡፡ ሀሮ ቁራ፣ የቁራ ኩሬ የሚል ትርጉም አለው፡፡ የውኃ ኩሬው የሚገኘው በባላ መስኪድ አጠገብ ነው፡፡ ኩሬው ከባላ መስኪድ ጋር አብሮ እንደተገነባ ይነገራል፡፡ ሀሮ ቁራ በአሁኑ ወቅት ምንም አይነት አገልግሎት

አይሰጥም። ይህ የውኃ ኩሬ ከአፍሪካ የመጀመሪያው የውኃ ማቆር ስራ ተግባራዊ የተደረገበት እንደሆነ ይገመታል።

ከሀሮ ቁራ ቀጥሎ የተገነባው ሀሮ ሉኩ ሲሆን፣ የ958 አመት እድሜ እንዳለው የድሬ ሼክ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፡3) ይገልጻል። የሀሮ ሉኩ የውኃ ኩሬ 8 ሜትር አማካይ ጥልቀት እንዳለው ይገመታል። ኩሬው ሼክ ሁሴን እራሳቸው ያስቆፈሩት እንደሆነ ይነገራል። ሼክ ሁሴን ኩሬውን ለምን ሊያስቆፍሩ እንደቻሉ ሁለት ምክንያቶች ይነገራሉ። አንደኛው፣ በአካባቢው የውኃ እጥረት ስለነበረ የዝናብ ውኃ እንዲጠራቀምበትና የአካባቢው ነዋሪዎችና ተማሪዎች የመጠጥ ውኃ እንዲያገኙ በሚል ዓላማ መገንባታቸው ነው።

ሁለተኛው፣ ደግሞ በአካባቢው የነበሩ ወፎች የሚጠጡት ውኃ አጥተው ስለተጠሙ ውኃ እንዲያገኙ በሚል ነው። ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ሁለተኛው ትረካ የኩሬው ስያሜ ሀሮ ሉኩ እንዲሆን መነሻ ሆኗል። ሀሮ ሉኩ የሚለው ቃል ኦሮምኛ ሲሆን ትርጉሙም የዶሮ ኩሬ ማለት ነው። ይህ ትርጓሜ በወቅቱ ወፍን እንደዶሮ የመቁጠር ወይም ዶሮንና ወፍን በአንድ ስያሜ የሚጠራበት ሁኔታም እንደነበር መገመት ያስችላል። ሀሮ ሉኩ በዙሪያው በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኝ ብቸኛ የውኃ ኩሬ ነው። ሀሮ ሉኩ ለዘምዘምነት (ለጸበልነት) ብቻ የሚያገለግል በመሆኑ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ ሌሎች የውኃ ኩሬዎች የተለየ መንፈሳዊ ዋጋ አለው።



*ፎቶ፡- 12፣ የሀሮ ሉኩ የዘምዘም (የጸበል) ኩሬ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

ሼኽ ሁሴን የአካባቢው ነዋሪዎችና እሳቸው ዘንድ ለትምህርት የሚመጡ ተማሪዎች በምግብ ራሳቸውን እንዲችሉ የእርሻ ቴክኖሎጂን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ በወቅቱ ሰፋፊ እርሻዎችን በማረስና ለእርሻ ምርት የሚያገለግሉ ዘመናዊ የማረሻ መሳሪያዎችን ከተለያዩ ዓለም አገራት በማስመጣት ይጠቀሙ እንደነበር ይነገራል፡፡ በወቅቱ የነበሩት ሰፋፊ እርሻዎች በአሁኑ ወቅት በባሌ ዞን በጎሎላቻ ወረዳና በጊንር ወረዳ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ይገኙ ነበረ፡፡[94]

እሳቸው እንዳስገነቧቸው የሚነገረው የባላና የዙቅጡም መስኪዶች ያላቸው የኪነ-ህንጻ ውበት፣ የአሰራር ሂደት፣ ለግንባታ የተጠቀሙባቸው ግብዐቶችና የመስኪዶቹ ዲዛይን የዘመኑን የስልጣኔ ደረጃ አመላካች ናቸው፡፡ ሼኽ ሁሴን ያስቆፈሯቸው የሀሮ ቁራና የሀሮ ሉኩ የውኃ ጉድጓዶች አሰራር፣ የአሰራር ሂደት፣ ዲዛይንና በወቅቱ የውኃ ማቆር ጽንሰሃሳብን ተግባራዊ ማድረግ መቻላቸው አስደናቂ ነው፡፡ እነዚህ የኪነ-ህንጻ፣ የውኃ ማቆርና የእርሻ ቴክኖሎጂዎች በወቅቱ በስፍራው ተግባራዊ መደረጋቸው ዘርፎቹ በአገር ደረጃ በዘመናዊ መንገድ እንዲስፋፉ መሰረት የጣለ ትልቅ አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህም በወቅቱ ስፍራው ደርሶበት የነበረውን ከፍተኛ የእድገት ደረጃና ያበረከተውን የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ትውውቅ አስተዋጽኦ ያሳያል፡፡

---

[94] - ሼኽ መሐመድ መሃሙድ፣ ሼኽ ቃሲም ሼኽ አደምና አቶ አብዱልፈታህ ሁሴን፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

# 5. የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች አጠቃላይ ገጽታ

በዚህ ምዕራፍ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በአናጂና ቀበሌ የሚኖሩ ነዋሪዎች ያላቸውን ኃይማኖት፣ የኢኮኖሚ መሰረትና ማህበራዊ አደረጃጀት ቀርቧል፡፡ በምዕራፉም የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ሁሉም የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች በመሆናቸውና የመካነ ቅርሱም መሰረት የእስልምና ኃይማኖት በመሆኑ ኃይማኖቱ በባሌ ዞን፣ በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ያለው ታሪካዊ ዳራ እንዲሁም በአካባቢው የሚገኙ አብይ የእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮዎች ተካተዋል፡፡ የባሌ ዞን እራሱን ችሎ በጠቅላይ ግዛት አስተዳደር የተመሰረተው በ1952 ዓ.ም ነው (Goba Municipality, 1984)፡፡ በመሆኑም “ባሌ” የሚለው ስያሜ በወቅቱ የነበረውን የግዛት ክልል ሙሉለሙሉ የሚገልጽ አይደለም፡፡

## 5.1 የእስልምና ኃይማኖት በባሌ ዞን

የእስልምና ሀይማኖት በአገራችን ውስጥ ካሉ መደበኛና ዓለም አቀፋዊ ሀይማኖቶች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ከአይሁድና ከክርስትና ሀይማኖቶች ቀጥሎ ረጅም እድሜ ያለው ነው፡፡ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች በነብዩ መሀመድ ትዕዛዝ በ7ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ (በ615 ዓመተ እግዚአ (A.D.)) ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ Trimingham (1952:44) እና Gulevich (2004:60) ይገልጻሉ፡፡ ይህ በዓለም የእስልምና ታሪክ “የመጀመሪያው ሂጅራ” ተብሎ ይታወቃል፡፡ በወቅቱም የነብዩ መሀመድን እንግዶች የተቀበሏቸው የአክሱም ንጉስ የነበሩት ንጉስ አልነጃሺ እንደሆኑ በስፋት ይነገራል፡፡

በመጀመሪያው ሂጅራ የሶሐቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መምጣት በባሌ ዞንና በሌሎች የአገሪቷ ደቡባዊ አካባቢዎች የእስልምና ኃይማኖትን ለማስፋፋት ምንም አይነት ተጽዕኖ አልፈጠረም፡፡ የእስልምና ሀይማኖት ባሌን ጨምሮ በሌሎች የደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች እንዲስፋፋ ንግድ ዋናው ምክንያት እንደሆነ Trimingham (1952:139) እና Taddesse (1972:43) ይገልጻሉ፡፡

ከ8ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ በኤደን ባህረሰላጤና በሱማሊያ የወደብ ከተሞች ሙስሊም ነጋዴዎች በስፋት መምጣታቸው የእስልምና ኃይማኖት በንግድ ምክንያት ወደ ባሌና አካባቢው እንዲገባ ምክንያት ነው (Østebo, 2012፡49)፡፡ በወቅቱም ከፍተኛ የንግድ ማዕከል በነበሩት የኤደን ባህረሰላጤ፣ የበርበራ፣ የሞቃዲሾና የዘይላ የወደብ አካባቢዎች የእስልምና ኃይማኖት የመስፋፋት እድል አግኝቷል፡፡ ከንግድ እንቅስቃሴ በተጨማሪ በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን ታላላቅ

ምሁራን በአካባቢው የእስልምናን ኃይማኖት ማስተማራቸው ኃይማኖቱ በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በወቅቱ ከነበሩ ምሁራን መካከል ሀጂ አባዲር በሐረር፣ ሸሪፍ ዮሱፍ በርስሃድል በሱማሊያና ሼኽ ሁሴን በባሌ በዋናነት ይጠቀሳሉ (Østebo, 2012፡50)፡፡

ሼኽ ሁሴን ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርግበትን የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በመመስረት፣ የእስልምና ማዕከል በማቋቋም፣ ሀይማኖታዊ ትምህርት በማስተማር፣ መስኪዶችን በመገንባት እንዲሁም በባሌ፣ በአርሲ፣ በሱማሊያ፣ በሐረርና በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የእስልምና ኃይማኖትን በማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ሐረር የእስልምና ማዕከል ከመሆኑ በፊት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና ማዕከል ነበር (Huntingford, 1955፡81)፡፡ በመሆኑም ባሌ በምስራቅ ኢትዮጵያ ቀደምት የእስልምና ማዕከል ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ9[ኛው] እስከ 13[ኛው] መቶ ክ/ዘመን ጠንካራ እስላማዊ ሱልጣኔቶች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሱልጣኔቶች ሰባት መሆናቸውንና ስያሜያቸው ፈጠጃር (ፈጠጋር)፣ ደዋሮ፣ ባሊ፣ ሀዲያ፣ ሸዋ፣ ይፋትና አፋር (አዳል) ናቸው (Taddesse, 1972)፡፡ እነዚህ ሰባት እስላማዊ ሱልጣነቶች ጠንካራና ሰፊ ግዛት የነበራቸው ቢሆንም፣ በወቅቱ ከእነዚህ በተጨማሪ ደራ፣ ወላስማ፣ ሞራ፣ አረባብኒ፣ ገበርጌ፣ ማርጋይ፣ አርነህ፣ ዋጅ፣ ጋንዝ፣ ሺርካ በሚል ስያሜ የሚታወቁ ሌሎች እስላማዊ ሱልጣኔቶች መኖራቸውን Trimingham (1952፡73)፣ Merid (1971:74) እና Braukämper (2004:14) ይገልጻሉ፡፡

በወቅቱ ጠንካራ ከነበሩ እስላማዊ ሱልጣኔቶች መካከል የባሊ ሱልጣኔት አንዱ ነው፡፡ የባሊ ሱልጣኔት ይገኝበት የነበረን መልክዓምድራዊ ስፍራ Braukämper (2004:181) ሲገልጽ "የባሊ ሱልጣኔት በሰሜን በደዋሮና በሺርካ፣ በምዕራብ በሀዲያ፣ በምስራቅ በአዳልና በደዋሮ እንዲሁም በደቡብ ባልተገለጸ ስፍራ ይዋሰናል" በማለት ነው፡፡ Taddesse (1972:142) ደግሞ "የዋቤ ሸበሌ ወንዝ የባሊ ሱልጣኔትን በሰሜን ከዳውሮና በሰሜን ምስራቅ ከአዳል ይለያል" ይላል፡፡

የባሊ ሱልጣኔት ከሀዲያ ሱልጣኔት አቅራቢያ የሚገኝ ሲሆን ስፋቱ 20 ቀናትና 6 ሰዓታት እንደሚወስድ፣ ጦር ሰራዊቱ 18,000 ፈረሰኛና በርካታ ሰራዊት እንደነበረው፣ ከዘይላ አጎራባች ቦታዎች በበለጠ እጅግ ለም መሬት፣ ብዙ ውኃና ተስማሚ የአየር ንብረት ያለው፣ ነዋሪዎቹም የመገበያያ ገንዘብ የሌላቸው ሲሆኑ፣ የሚገበያዩትም በምርት ልውውጥ እንደነበርና በተለያየ ወቅት ስልጣን በሚቀያየሩ ንግስቶች የሚመራ አስደናቂ አካባቢ እንደነበረ፣ አካባቢው ተራራማ

እንደሆነ፣ የእጸዋት ሀብቱ ከፍተኛ እንደሆነና ነዋሪዎቹ በንግድ ስራ በጣም ታዋቂዎች እንደሆኑ Braukämper (2004: 76- 81) የታሪክ ጸሐፊዎችን በመጥቀስ ይገልጻል፡፡

በተለያዩ ጸሐፊያን የቀረቡ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ Cerulli (1971:413- 418) የባሊ ሱልጣኔት የነበረውን ድንበር በሚመለከት በሰሜን ከደዋሮ ሱልጣኔት ጋር፣ በምዕራብ ከደቡብ ዝዋይ፣ በሰሜን ምስራቅ ከይፋት (ሐረር)፣ በደቡብ ከገናሌ ወንዝ፣ በምዕራብ ከሐዲያ ጋር ይዋሰን እንደነበርና ከኢትዮጵያ አካባቢዎች ለሕንድ ውቅያኖስ በጣም ቅርብ የሆነ ግዛት መሆኑን ይገልጻል፡፡ ከእነዚህ አካባቢያዊ ገለጻዎች በመነሳት የባሊ ሱልጣኔት በአሁኑ ወቅት ባለው የዞን አከላለል መሰረት በትክክል የት እንደሚገኝና የነበረው የግዛት ስፋት እስከ የት ድረስ እንደሚደርስ ማወቅ አይቻልም፡፡ ነገር ግን ከቀረቡት አዋሳኝ የሱልጣኔቶች የግዛት ድንበር እንዲሁም በወቅቱ ከተጠቀሱትና እስካሁንም ስያሜያቸውን ይዘው ከቀጠሉ የወንዝና የቦታ ስሞች መሰረት በማድረግ ግምት መውሰድ ያስችላል፡፡

ከተጠቀሱ ስሞች መካከል የዋቤ ሸበሌ ወንዝ በቀድሞው የዞን አከላለል የአርሲንና የባሌን ዞኖች ይለይ ነበር፡፡ የገናሌ ወንዝ የባሌንና የቦረናን ዞኖች ይለያል፡፡ የባሌ ዞን ከሐረርጌ ዞን ጋር በሰሜን ምዕራብ ይዋሰናል፡፡ በአርሲ ዞን ውስጥ ሺርካ የሚባል ቦታ አለ፡፡ በባሌ ዞን ውስጥ በሶፍዑመር ዋሻ አካባቢ "ባሊ" የሚባል ቦታ አለ፡፡ "ባሌ" የሚለው ስያሜ "ባሊ" ከሚባለው የእስላማዊ ሱልጣኔት ስም የተወሰደ መሆኑን የሚገልጽ አፈታሪክ በአካባቢው በስፋት ይነገራል፡፡ እነዚህን መነሻዎች መሰረት በማድረግ የባሊ እስላማዊ ሱልጣኔት ግዛት የአሁኑን የባሌ ዞንን ያጠቃልል እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡

የባሊ ሱልጣኔት ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኘው በአጼ ዓምደ ጽዮን (1307-1336 ዓ.ም.) ዜና መዋዕል ላይ እንደሆነ Taddesse (1972:142) እና Braukämper (2004:76) ይገልጻሉ፡፡ ስያሜው በዜና መዋዕሉ ላይ የሰፈረው በ1332 በሙስሊም ሱልጣኔቶችና በአጼ ዓምደ ጽዮን የክርስቲያን ጦር መካከል በተካሄደው ጦርነት በተሳተፉ ሱልጣኔቶች ስም ዝርዝር ውስጥ አይደለም፡፡ ስያሜው በዜና መዋዕሉ ውስጥ የሰፈረው በአንድ የጦርነት ግጥም ውስጥ ነው፡፡ በግጥሙም የባሊ ሱልጣኔት መሪ ስለነበሩት ንጉስ አሊ መገለጹ ነው፡፡ ለአጼ ዓምደ ጽዮን በተገጠመው መወድስ ግጥም ውስጥ ስለ ንጉስ አሊ የተገለጸው የሚከተለው ነው፡፡

ሀርበኛ ዓምደ ጽዮን

መላላሽ የወሰን

…….

ከወጅ ዜብዳናን ከገንዝ ጠጠንን

ምን ቀረህ በወሰን ከሀድያ አመኖን

ከባሊ አሊን ከደዋሮ ሄደራን

…….

ዓምደ ጽዮን ስም የዘራ

በወጅ እስከ በጥረአሞራ

ቃራ ይነስንስ ቃራ እንደጭራ

………..

ይህ በዜና መዋዕሉ ላይ የሰፈረው የመወድስ ግጥም አጼ ዓምደ ጽዮን የዘይላን የባህር ወደብና በአካባቢው የነበረውን የንግድ መስመር ለመቆጣጠርና ቦታውን በሸዋ ክርስቲያናዊ መንግስት ስር ለማካተት ከባሊ እስላማዊ ሱልጣነት መሪ ከነበሩት ንጉስ አሊ ጋር ጦርነት መግጠማቸውን ያሳያል፡፡ ይህ ጦርነትም የአጼ አምደ ጽዮን ጦር የባሊ እስላማዊ ሱልጣኔት መሪ የነበሩትን አሊን አሸንፎ ባሊን በሸዋ ክርስቲያናዊ መንግስት ስር እንዲተዳደር ምክንያት ሆኗል፡፡ አጼ ዓምደ ጽዮን በ1332 ባሊን በመቆጣጠር አካባቢውን በሸዋ ክርስቲያናዊ መንግስት ስር ማጠቃለል የቻሉ የመጀመሪያው ንጉስ ናቸው፡፡

በ15ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ የአዳል፣ የሀድያ፣ የፈጠጋርና የደዋሮ ሱልጣኔቶች መሪ የነበሩት አሚር ጀማል አል-ዲን (1433 A.D) ባሊን ለመውረር ጦር አዝምተው የተወሰኑ ቦታዎችን በቁጥጥር ስር አዋሉ፡፡ ጀማልን የተኳቸው ሺሃብ አል-ዲን አህመድ በድላይ ተመሳሳይ ወረራ በመፈጸም 1,000 ሙስሊሞችን በባሊ አሰፈሩ (Braukämper, 2004:77)፡፡ ሺሃብ አል-ዲን አህመድ በድላይ ከአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር በ1437 ዓ.ም ባካሄዱት ጦርነት የሞቱ ሲሆን፣ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ላይ አርቂ በድላይ በሚል ስም የሚታወቁት ናቸው (ተክለጻድቅ፣1966 ዓ.ም፣183)፡፡ ይህ ሁኔታ የእስልምና ኃይማኖት በባሌ ዞን በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ ኢማም አህመድ ቢን-ኢብራሂም አል-ጋዚ (በተለምዶ ግራኝ አህመድ በሚል ስም የሚታወቁት) በሐረሩ ሱልጣን አቡበከር ስር ሆነው በመዝመት በ1517 ዓ.ም የደዋሮ ገዢ የነበሩትን ፋኑኤልን በጦርነት አሸነፉ፡፡ በመቀጠልም ኢማም አህመድ ከሱልጣን አቡበከር ጋር ጦርነት ገጥመው አሸነፉ፡፡ በጦርነቱም ሱልጣን አቡበከር በመሞታቸው ኢማም አህመድ የሱልጣን አቡበከርን ወንድም ኡመር ዲንን በሱልጣንነት ሾሟቸው፡፡ በዚህ መንገድ ኢማም አህመድ ስልጣናቸውን ካደላደሉ በኋላ መላውን ኢትዮጵያ የመቆጣጠር እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ ኢማም አህመድ ስልጣናቸውን ካደላደሉና ጦራቸውን ካደራጁ በኋላ የአገሪቷን የተለያዩ ቦታዎች መቆጣጠር ጀመሩ፡፡

የኢማም አህመድ እንቅስቃሴን ለመግታት አጼ ልብነ ድንግል (ወናግ ሰገድ) በወቅቱ የባሌ ገዢ የነበሩትን ራስ ደገለሃንን በ1517 ዓ.ም ወደ አዳል ላኩ፡፡[95] ራስ ደገለሃን የዐጼ ልብነ ድንግል እህት የሆኑት የዓመተውጥን ባለቤትና የንጉሱ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ናቸው፡፡ ራስ ደግለሃን የበትረ አሞራ ጦርን የሚመሩ የባሌ ገዢ ነበሩ (ይልማ፣1959 ዓ.ም)፡፡ ራስ ደገለሃንም አዳል ዘምተው ድል አድርገውና ምርኮኞችን ይዘው በመመለስ ላይ በነበሩበት ወቅት ኢማም አህመድ ተከታትለው ምርኮኞቹን ማስመለሳቸውንና የራስ ደግለሃንን ጦር መበተናቸውን ተክለጻዲቅ (1966 ዓ.ም.፣ 190) ይገልጻል፡፡

በ1523 ዓ.ም. ቀደም ሲል የመቅደላ አምባ የወህኒ አዛዥ በኋላ የባሌ የሰላም ዘበኛ (ፖሊስ) ተቆጣጣሪና የከተማው ገዢ የነበረው ሻለቃ ፋኑኤል በኩረና የባሌ ወህኒ አዛዥ መቶ አለቃ አዳሉ ተሰማ[96] የጎበዝ አለቃ በማቋቋም ከግራኝ አህመድ ጋር ዙላህ በሚባል ቦታ ጦርነት ገጠሙ (ይልማ፣1959 ዓ.ም፣61 እና አእምሮ፣2000 ዓ.ም፣81)፡፡ ዙላህ የሚባለው ቦታ በአሁኑ ወቅት ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ በግምት በ5 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የኢማም አህመድን ጦር ይመሩ የነበሩት ቪዚር አድሊን የሚባሉ የጦር መሪ ናቸው፡፡

ኢማም አህመድ የዙላህ ጦርነትን በድል ካጠናቀቁ በኋላ በስፍራው የጦር ሰራዊት ማዕከል በማቋቋም የጦሩን ኃይል ማጠናከር ጀመሩ፡፡ ኢማም አህመድም ከባሌ ባገኙት ምርኮና ሀብት መድፎችና ሌሎች የጦር መሳሪያዎችን በመግዛት ከፍተኛ ትጥቅ ማሟላት ቻሉ፡፡ እሳቸውም

[95] - ራስ ደገለሃን በባሌ ዞን ጎባ ከተማ በስማቸው የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሰይሞላቸዋል ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት የትምህርት ቤቱ ስያሜ ተቀይሮ የባቱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚል ይጠራል፡፡

[96]- ይልማ ደሬሳ (1959 ዓ.ም) በመጽሐፉ መቶ አለቃ አዳሉ ተሰማን አንዴ በታሪክ አዳሉ፣ አንዴ አዳሉ በታሪክ በሚል ስም ይገልጻል፡፡

ባገኙት ትጥቅ መሳውን ኢትዮጵያ ለ15 አመት መቆጣጠር ቻሉ፡፡ ይህ የኢማም አሕመድ ድል በባሌና በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች የእስልምና ኃይማኖት እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል፡፡

16ኛው መቶ ክ/ዘመን የኦሮሞ ብሔር ከማዕከላዊው የክርስቲያን መንግስት ጋር ጦርነት ያካሄደበትና አብዛኛውን የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተቆጣጠረበት ወቅት ነው፡፡ የኦሮሞ ብሔር በባሌ ዞን መደወላቡ በሚባል ቦታ ቦረና እና በሬንቱማ በሚል በሁለት ኮንፌዴሬሲዮን ተደራጀ (ታቦር፣2006 ዓ.ም፣93)፡፡ ከመደወላቡ በበሬንቱማ ኮንፌዴሬሲዮን አደረጃጀት ስር ወደ መሃል የባሌ ዞን አካባቢዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የተንቀሳቀሰው የቢርመጂ ገዳ (1500 እስከ 1508 ዓ.ም) ጦር እንደሆነ ብሩ (2008 ዓ.ም፣ 317) ይገልጻል፡፡ በዚህ የገዳ ዘመን የተጀመረው እንቅስቃሴ በሜልባ ገዳ (1524 እስከ 1532 ዓ.ም) በከፍተኛ ደረጃ ተጠናከረ፡፡ የሜልባ ገዳ ጦር ወደ መሃል የባሌ ዞን ጉዞውን በጎባ ከተማ አቅጣጫ አደረገ፡፡ በዚህ አቅጣጫ የተንቀሳቀሰው የኦሮሞ ሜልባ ገዳ ጦር በጃዊ ጎሳ መሪነት በ1524 ዓ.ም ከአጼ ሰርጸ ድንግል ሰራዊት ጋር ጦርነት ጀመረ፡፡

በባሌ ዞንና በአካባቢ የሚገኘውን የአጼ ሰርጸ ድንግል ሰራዊትን የሚመሩት ራስ ፋሲል ነበሩ፡፡ ራስ ፋሲል የአጼ ሰርጸ ድንግል ወንድምና የጦሩ ዋና አዛዥ ናቸው፡፡ በባሌ ዞን ጎባ ከተማ አካባቢ መሰረቱን (ቤዙን) ያደረገው የንጉሱ የጦር እዝ "በትረ አሞራ" ተብሎ ይጠራል፡፡ በትረ አሞራ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተቋቋመ ስመጥርና የተፈራ ሰራዊት ነው (ይልማ፣1959 ዓ.ም፣228)፡፡ በወቅቱ ራስ ፋሲል በባሌ ዞን ጎባ ከተማ ቤተመንግስት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ ቤተ መንግስቱ ይገኝበት እንደነበር በሚነገር አካባቢ ያለ ተራራ እስካሁን ድረስ በስማቸው "ፋሲል ተራራ" ተብሎ ይጠራል፡፡

በ1524 ዓ.ም የኦሮሞ በሜልባ ገዳ ስር የሚመራው የጃዊ ጦርና የራስ ፋሲል ሰራዊት ጦርነት ገጠሙ፡፡ በሁለቱ ጦሮች መካከል ከፍተኛ ፍልሚያ ተደርጎ የኦሮሞ ሜልባ ጦር አሸነፈ፡፡ በጦርነቱም የበትረ አሞራ ጦር መሪ ራስ ፋሲል ተገደሉ (አጽመጊዮርጊስ፣2008 ዓ.ም.፡25)፡፡ ከራስ ፋሲል ሞት በኋላ የበትረ አሞራን ጦር ለመምራት የከምባታው ገዢ ራስ ሐመልማል ኃላፊነቱን ተረከቡ (ይልማ፣1959 ዓ.ም.፣ 227)፡፡ ይህ ጦርነት የኦሮሞ ጦር በገዳ ስርዓት ከተደራጀ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከማዕከላዊው መንግስት ጋር ያደረገው ጠንካራ ጦርነት ነው፡፡ ይህ ጦርነት በኦሮሞ ሕዝብና በማዕከላዊው የአማራ ክርስቲያን ጦር መካከል የተደረገ የመጀመሪያው ጦርነት መሆኑን አጽመጊዮርጊስ (2008 ዓ.ም፡26) "በፋሲል ሞት አማራና ኦሮሞ ደም ተቃባ" በማለት ገልጾታል፡፡ ይህ ጦርነት በአካባቢው ጠንካራ የነበረውን የበትረ

አሞራ ጦር በማዳከሙ ምክንያት የግራኝ አሕመድ ጦር በቀላሉ እንዲያሸንፍና የእስልምና ኃይማኖትን እንዲያስፋፋ ምክንያት ሆኗል፡፡

ከ19ኛው መቶ ክ/ዘመን በኋላ በባሌ ዞንና በአካባቢው የእስልምና ኃይማኖት ለመስፋፋት ምክንያት የንጉስ ምኒልክ ግዛት ማስፋፋት አንዱ ነው፡፡ የባሌ ዞንን በንጉስ ምኒልክ የግዛት ክልል ውስጥ የማድረግ ዘመቻን የመሩት ራስ ዳርጌ ሳህለስላሴ፣ ራስ ጎበና ዳጨና ደጃዝማች ወልደገብረኤል ናቸው፡፡ በዘመቻውም በነሐሴ ወር 1891 ባሌ በማዕከላዊው የሸዋ ግዛት ውስጥ ገባ (Bairu, 1975፡30) እና (Gebru, 1977፡241)፡፡ የሸዋ ነፍጠኛ ጦርም ባሌን እንደተቆጣጠረ ዋና መቀመጫውን በአሁኑ የዞን አደረጃጀት በጋሰራ ዞን፣ በጉራንዳ አደረገ፡፡ የነፍጠኛው ጦር በአብዛኛው የክርስትና ኃይማኖት ተከታይ ነበር፡፡ በመሆኑም ራስ ዳርጌ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንን መጀመሪያ በአዳባ ዞን ሀቆ በሚባል ቦታ፣ በመቀጠልም በጋሰራ ዞን ጉራንዳ በሚባል ቦታ የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንን አሰሩ፡፡

ከራስ ዳርጌ ቀጥሎ ባሌን ያስተዳደሩት ልጃቸው ደጃዝማች አስፋው ዳርጌ (1906) ጎባን የባሌ ዋና ከተማ አደረጉ፡፡ እሳቸውም በከተማው የቅዱስ ባለወልድን ቤተክርስቲያንን እንዲሁም ከእሳቸው ቀጥሎ ባሌን ያስተዳደሩት ራስ ናደው ኃይለሥላሴ (1906-1917) የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያናትን አስገንብተዋል (Sintayehu,1972፡22)፡፡ ይህም በአካባቢው የክርስትና ኃይማኖትን የማስፋፋት ስልት ነበር፡፡ የሸዋ ነፍጠኛ ሰራዊት የአካባቢውን ሕዝብ መሬት በመውሰዱና ከነዋሪው ላይ የጣለው የግብር ስርዓት በሕዝቡ ላይ ጫና ፈጥሮ ነበር (Ketema, 2001፡29)፡፡ በወቅቱም የባሌና የአካባቢው ሕዝብ ላይ የነፍጠኛው ስርዓት የፈጠረውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ለመቋቋም የእስልምና ኃይማኖት ለትግል ማካሄጃና መቃወሚያ ርዕዮት እንደነበር Trimingham (1952)፣ Braukämper (2002) እና Abbas (2014) ይገልጻሉ፡፡

የጣሊያን መንግስት አገራችንን (ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም) በወረረበት ወቅት ሕዝቡን ለመከፋፈል የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀም ነበር፡፡ ጣሊያን ከተጠቀማቸው የመከፋፈያ ስልቶች መካከል በኢትዮጵያ በነበሩት የመንግስት ስርዓቶች ወቅት ትኩረት አልተሰጣቸውም ለሚላቸው ኃይማኖቶች የተሻለ ቦታ መስጠት ነበር፡፡ በዚህ ስልት መሰረትም የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ለሆኑ ወገኖች ልዩ ድጋፍ በመስጠት ኃይማኖታቸውን በነጻነት እንዲከተሉና በዓላትን በጋራ እንዲያከብሩ ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ ይህ የጣሊያን የፖለቲካ ስልት በወቅቱ የእስልምና

ኃይማኖት ተከታዮች ላይ ይደርስ የነበረው የሀይማኖት ነጻነት እጦት እውነታን እንደመሳሪያ መጠቀሙን አመላካች ነው፡፡

የሞሶሎኒ መንግስት ለሙስሊሞች ልዩ ድጋፍ የሚሰጠው እርስበርስ ከመከፋፈል በተጨማሪ አረብ አገራት የጣሊያንን ቅኝ ገዢነት እንዲደግፉ በሚል ዓላማ ነበር (Erlich, 1994)። ይህም የአረብ አገራት በኢትዮጵያ የክርስቲያን ንጉሶች በእስልምና ኃይማኖት ላይ ላሳደረው ተጽዕኖ ልዩ ትኩረት እንዳላቸው በመገንዘብ የጣሊያን ፋሽስት መንግስት ጉዳዩን ለፕሮፓጋንዳ እንደተጠቀመበት Erlich (1994 እና 2007) ይገልጻል፡፡

የጣሊያን ወራሪ ኃይልም በአካባቢው የተነሳበትን ሕዝባዊ ተቃውሞ ለመቆጣጠር፣ በኢትዮጵያ ላይ አመጣለሁ የሚለውን የለውጥ ዓላማ ለሕዝቡ ለማሳመን፣ ሕዝቡ የጣሊያንን መንግስት እንዲደግፍ እንዲሁም ወረራውን ለመመከት በአካባቢው ጫካ የገባውን የባሌ አርበኛ ጦር ሕዝቡ ድጋፍ እንዳያደርግ ይጥር ነበር፡፡ የጣሊያንን ወረራ ለመመከት የባሌ ጦር በደጃዝማች በየነ መርዕድ (ከ1932-1934 የባሌ ገዢ የነበሩ) አስተባባሪነት ኡጋዴን ዘመተ፡፡ በጦርነቱም ደጃዝማች በየነ መርዕድ ተሰዉ፡፡ የካቲት 14 ቀን፣ 1928 ዓ.ም የጎባ ከተማ በጣሊያን ጦር ቁጥጥር ስር ዋለ፡፡

የጣሊያን ወረራ ለመመከት የባሌ አርበኞች ጫካ ገቡ፡፡ የባሌ አርበኞችን የመምራት ኃላፊነት የተረከቡት የተሰማ ልጆች ናቸው፡፡ የተሰማ ልጆች የሚባሉት ፊታውራሪ ተገኔ ተሰማ፣ ፊታውራሪ ጥላሁን ተሰማ፣ ካፒቴን አጥሬ ተሰማ፣ ፊታውራሪ መኩሪያ ተሰማና ፊታውራሪ አሻግሬ ተሰማ ናቸው፡፡ በተሰማ ልጆችና በሌሎች ጀግና አርበኞች መሪነት ለአምስት አመት ያህል በጣሊያን ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ፤ ለአገር ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፈሉ፡፡

በጣሊያን ወረራ ወቅትም ባሌ በሁለት ኮሚሳራትና በስድስት ዲስትሪክት ተደራጀ፡፡ ዲስትሪክቱም ጎባ፣ ዶዶላ፣ ደሎ፣ ጊንር፣ መጋሎና ሼኽ ሁሴን ናቸው (Mindaye, 2005፡72)። የጣሊያን መንግስት የባሌና የአርሲ ሙስሊሞችን ልዩ ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት አድርጓል፡፡ ከጥረቶቹም መካከል በ1929 ዓ.ም በባሌ የራይቱ እና በአርሲ የሱዴ እስላማዊ ሱልጣኔት እንዲመሰረቱ አደረገ፡፡ ፊታውራሪ ኑሆ ዳዲ የራይቱ ሱልጣንና የጣሊያን ምክር ቤት አባል እንዲሁም ሼኽ ሁሴን ኪሞ የሱዴ ሱልጣን መሪ ተደርገው ተሾሙ፡፡

በወቅቱ የድሬ ሼኽ ሁሴን ኢማም የነበሩት ኢማም መሃመድ ሰዒድ ደግሞ የባሌ ኢማም በመሆን ተመረጡ፡፡ እነዚህ ሶስት ሙስሊም ባለስልጣናትም በጣሊያን አገር ሮም ከተማ ግብዣ ተደርጎላቸው ከሞሶሎኒ ጋር እንደተገናኙ Temam (2002፡48) ይገልጻል፡፡ በወቅቱም ጣሊያን ሐጂ እስማኤል ወለሼን ዋዚር እንዲሁም ሐጂ መሐመድ ሲራጅን የባሌ ቃዲ (የእስልምና ኃይማኖት ጉዳዮች ተጠሪ) አድርጎ ሾማቸው (Østebo, 2015፡126)።

በጣሊያን ወረራ ወቅት በባሌ የተለያዩ አካባቢዎች መስኪዶች ተገነቡ፡፡ የጣሊያን መንግስትም በጎባ፣ በጊንር፣ በደሎ መና እና በዶዶላ መስኪዶችን ሲገነባ ለሼኽ አብዱልራህማን ሐጂ ሉጊና ለሼኽ ኢብራሂም ሻፊ ወርሃዊ ደሞዝ በመክፈል በዶዶላና በኮፈሌ አካባቢ የእስልምና ኃይማኖታዊ ትምህርት እንዲያስፋፉ ጥረት ያደርግ ነበር (Østebo, 2015፡127)። የጣሊያን መንግስት ከእነዚህ ጥረቶች በተጨማሪ የተለያዩ ግለሰቦችን ከባሌ ወደ ጅማ በመላክ ኃይማኖታዊ ትምህርት እንዲማሩ ያደርግ ነበር፡፡ ግለሰቦቹም በጅማ ሰኮሩ ወረዳ በሚገኝ አባርቲ የተባሉ ሼኽ ጋር ለትምህርት ይሄዱ ነበር፡፡ በወቅቱም መምህር የነበሩት ሼኽ አልይ ሸሮ ይባላሉ፡፡ በወቅቱ የጣሊያን መንግስት በጅማ የእስልምና ትምህርት ቤት ማዕከል አቋቁሞ ነበር፡፡ የትምህርት ቤቱ ስም ደር አል-ኡሉም አል- ኢስላሚያ ይባላል (Temam, 2002፡46)።

## 5.2 የእስልምና ኃይማኖት በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

የእስልምና ኃይማኖት በአናጂና ቀበሌና በአካባቢው መተዋወቅ የጀመረበትን ዘመን በትክክል ማወቅ አይቻልም፡፡ ነገር ግን ከ8ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ በኤደን ባህረሰላጤና በሱማሊያ የወደብ ከተሞች ሙስሊም ነጋዴዎች በስፋት መምጣታቸው የእስልምና ኃይማኖት በአካባቢው እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል፡፡ በኤደን ባህረሰላጤ መግባት የጀመረው የእስልምና ኃይማኖት በንግድ ምክንያት ወደ ባሌና አካባቢው እንደተስፋፋ ይታመናል፡፡

በአሁኑ ወቅት ባለው አደረጃጀት የአናጂና ቀበሌና አካባቢው ለሐረርና ለሱማሊያ ድንበርተኛ በመሆኑ ከሌሎች የባሌ ዞን አካባቢዎች በበለጠ የእስልምና ኃይማኖት በአካባቢው ሊስፋፋ የሚችልበት እድል አለ፡፡ አካባቢው ለኤደን ባህረሰላጤ፣ ለበርበራ፣ ለሞቃዲሾና ለዘይላ ወደቦች ካለው መልካምድራዊ ቅርበት በተጨማሪ የሲራራ ነጋዴዎች መተላለፊያ መንገድ እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህም የእስልምና ኃይማኖት ከሌሎች የባሌ ዞን አካባቢዎች በቀዳሚነት በአካባቢው እንዲስፋፋ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

የእስልምና ኃይማኖት በአናጂና ቀበሌና በአካባቢው በ8ኛው መቶ ክ/ዘመን ሊተዋወቅበት የሚችልበት እድል ቢኖርም፣ በከፍተኛ ደረጃ ሊስፋፋና ሊጠናከር የቻለው በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን ነው፡፡ ኃይማኖቱ በአካባቢው እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱት በወቅቱ ከአረብ አገር ወደ ስፍራው እንደመጡ የሚታመነው የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የእስልምና ኃይማኖትን በማስፋፋት የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም በአካባቢው ኃይማኖቱ በይበልጥ መሰረት የያዘው ሼኽ ሁሴን ከተወለዱ በኂላ ነው፡፡

ሼኽ ሁሴን ፈጣሪ የመረጣቸው እንደሆኑ በተከታዮቻቸው ይታመንባቸዋል፡፡ እሳቸው በአካባቢው መወለድ ስፍራው የእስልምና ኃይማኖት ማስፋፊያ፣ የኃይማኖት ማስተማሪያ ማዕከልና የኃይማኖቱ ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ መታመኑ በአካባቢውና በሌሎች የአገሪቷ አካባቢዎች ኃይማኖቱ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከሼኽ ሁሴን መንፈሳዊነት በተጨማሪ እሳቸው ከአረብ አገራት ጋር ያላቸው ግንኙነትና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማስመጣት በአካባቢው የንግድ ስራ ማጠናከራቸው የእስልምና ኃይማኖት በአካባቢው እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል (Teshome, 2008:34)፡፡

ሼኽ ሁሴን በኖሩበት ዘመን በአካባቢው የባላና የዙቅጡም መስኪዶችን በመገንባት፣ 6,666 ተማሪዎችን የኃይማኖት ትምህርት አስተምረው በማስመረቅ፣ በኃይማኖት ዕውቀታቸውና በአዲስ የኃይማኖት አስተምህሮ የሚታወቁ ግለሰቦች ከተለያዩ አለም አገራት ወደ ስፍራው መምጣታቸው፣ በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ታዋቂና የኃይማኖት ዕውቀታቸው ከፍተኛ እንደሆነ የሚነገርላቸው ግለሰቦችን በማፍራት በአካባቢው ለእስልምና ኃይማኖት መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ከሼኽ ሁሴን ሕልፈተ ሕይወት በኂላ የእሳቸው ልጆች፣ ተማሪዎችና ተከታዮቻቸው ስፍራውን በመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ ነገር ግን ከእሳቸው ሕልፈት በኂላ ስፍራው የእስልምና ኃይማኖት ማዕከልነቱ እየቀነሰ ሄዶ፣ በተለያዩ ምክንያቶች ስፍራው ለ400 ዓመታት ያህል የእስልምና ኃይማኖት ማዕከልነቱን አጣ፡፡

በግራኝ አህመድ ጦርነት ወቅት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የነበረበትን ሁኔታ በትክክል ማወቅ አይቻልም፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያት በግራኝ አህመድ ወገን የነበሩትና በወቅቱ የነበረውን የጦርነት ታሪክ የጻፉት አህመድ ቢን-አብዱልቃድር ወይም አረብ ፋቂህ በሚል ስም የሚታወቁት ስለ መካነ ቅርሱም ሆነ ስለአካባቢው ወረዳዎች ምንም አይነት ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በአረብ ፋቂህ ጽሑፍ ውስጥ ስለመካነ ቅርሱ የቀረበ ማስረጃ ባይኖርም የአናጂና

ቀበሌና አካባቢው ግራኝ አህመድ ከተነሱባቸው የሐረርና የሱማሊያ አካባቢዎች መልክዓምድራዊ ድንበርተኝነት ያለው ነው፡፡ ስፍራውም ከሐረርና ከሱማሊያ ድንበር በመሆኑ የግራኝ አህመድ ጦር ወደ ባሌ ዞን ሲገባ በዚህ አካባቢ ሊያልፍ እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡

በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን ከሐረር ወደ ስፍራው የመጡት ሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞና ሼኽ አባስ በአናጂና ቀበሌ የተለያዩ ግንባታዎችን አካሄዱ፡፡ እነሱም በስፍራው ላይ ያካሄዱት ግንባታ የእስልምና ኃይማኖት በአናጂናና አካባቢው ድጋሚ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ምክንያት ሆኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ኪነ-ሕንጻዎች ሼኽ መሃመድና ሼኽ አባስ የገነቧቸው ናቸው፡፡ ከግንባታው ዘመን በኋላ ስፍራው ቋሚ የእስልምና ኃይማኖት ማዕከል ሆነ፡፡

በጣሊያን ወረራ ወቅት የጣሊያን መንግስት ድሬ ሼኽ ሁሴንን ከስድስቱ የባሌ ዲስትሪክቶች መካከል አንዱ በማድረግ የአስተዳደር ክልል አደረገ፡፡ በወቅቱ የድሬ ሼኽ ሁሴን ኢማም የነበሩት ኢማም መሃመድ ሰዒድ ደግሞ የባሌ ኢማም በመሆን ተመረጡ፡፡ እሳቸውም ከራይቱ ሱልጣን ፊታውራሪ ኑሆ ዳዲ እና ከሱዴ ሱልጣን ሼኽ ሁሴን ኪሞ ጋር በጣሊያን አገር ሮም ከተማ ግብዣ ተደርጎላቸው ከሞሶሎኒ ጋር ተገናኝተዋል፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅት የድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ በዓል በጣሊያን መንግስት ደረጃ እውቅና ተሰጥቶት ነበር፡፡ በበዓላት ወቅትም የራይቱና የሱዴ ሱልጣኔት መሪዎች እራሳቸው በመካነ ቅርሱ ይገኙ ነበር፡፡

## 5.3 አብይ የእስልምና አስተምህሮዎች በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

መካነ ቅርሱ የሚገኝበት የአናጂና ቀበሌ የሕዝብ ብዛት 4,000 እንደሆነ የጎሎልቻ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አመታዊ ሪፖርት (2006 ዓ.ም.) ይገልጻል፡፡ የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ሙሉለሙሉ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ በአካባቢው የኦሮምኛ፣ የአማርኛና የሱማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ቋንቋዎች መካከል በስፋት የሚነገረው የኦሮምኛ ቋንቋ ነው፡፡ የኦሮምኛ ቋንቋ ከኢትዮጵያ በተጨማሪ በኬኒያና በሱማሊያ ይነገራል፡፡ በአናጂና ቀበሌ የሚገኙ ነዋሪዎች ሁሉም የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ናቸው፡፡ እስልምና በአብራሃማዊ ኃይማኖቶች ምደባ ውስጥ የሚካተት ዓለም አቀፍ ኃይማኖት ነው፡፡

የእስልምና ኃይማኖት በሁሉም ዓለማት አንድ ወጥ ሥርዓት (ሱና) ያለው ቢሆንም፣ በአስተምህሮዎችና በሕግጋቶች ልዩነት ምክንያት በተለያዩ ክፍሎች ይመደባል፡፡ እነዚህም ሱኒ፣

ሺዓትና ኢባዲ (ካሪጂትስ) እንደሆኑ Gulevich (2004፡48) ይገልጻል፡፡ ከእነዚህ ሶስት አብይ ክፍሎት በተጨማሪም ሱፊዝም፣ ኦርቶዶክስ፣ ፖፑላር የተሰኙ የእስልምና ፍልስፍናዎች፣ ስርዓቶችና ድርጊቶችም አሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ በዓላት ወቅት ከሚከወኑ ስርዓተከበራዎች በተለያዩ የእስልምና አስተምህሮዎች፣ ድርጊቶችና እምነቶች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ስርዓተከበራዎች መካከል የተወሰኑት ከእነዚህ የእስልምና አስተምህሮዎችና ድርጊቶች ውጪ ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች የሀገረሰባዊ እምነት ባህርያት ያላቸው ናቸው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን፣ የመካነ ቅርሱን የአስተዳደር ታሪክና በአናጂና ቀበሌ ነዋሪዎች መካከል ያለውን የኃይማኖት አስተምህሮ ልዩነት ለመረዳት እንዲረዳን የእነዚህን አስተምህሮዎች፣ ስርዓቶችና ድርጊቶች ምንነት ማየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑ በዚህ ክፍል የእነዚህን አስተምህሮዎች ምንነት፣ በመካከላቸው ያለውን ልዩነትና ከባሌ ዞን፣ ከአናጂና ቀበሌና አካባቢ ጋር ያላቸውን ታሪካዊ ትውውቅ በጥቂቱ እንመለከት፡፡

## 5.3.1 የሱኒ አስተምህሮ በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

ሱኒ በዓለም ላይ ከሚገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች መካከል 85 ፐርሰንት የሚከተለው አስተምህሮ ነው (Gulevich, 2004)፡፡ ሱኒ የሚለው ቃል “ሱና” ከሚለው የመጣ ነው (Gulevich, 2004)፡፡ ትርጉሙም ምሳሌ እንደማለት ነው፡፡ ቃሉም የነብዩ መሐመድን ምሳሌነት የመከተል መሰረታዊ እሳቤን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ የሱኒ አስተምህሮ ቅዱስ ቁርዓንን መከተልና የነብዩ መሐመድን ምሳሌነት መከተል ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ቀደም ባሉት አመታት የካሊፌትን ስልጣን ይቀበሉ ነበር፡፡ ካሊፌት የእስልምናውን ዓለም የፖለቲካ መሪና የኃይማኖቱ ጠባቂ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሱኒ የእስልምና አስተምህሮ በስሩ ማሊኪ፣ ሐንባሊ፣ ሐናፊና ሻፊ ንዑስ ክፍሎችን እንደሚይዝ Gulevich (2004) ይገልጻል፡፡

ወሐቢዝም ከእነዚህ ንዑስ ክፍሎች መካከል በሐንባሊ ስር የሚመደብ ንዑስ ክፍል (Sect) ነው (Gulevich, 2004፡49)፡፡ ወሐቢዝም ስያሜውን ያገኘው የአስተምህሮው መስራች ከሆኑት ከሼኽ ሙሐመድ ኢብን አብደ አል- ወሐብ (1703-1791) ነው፡፡ በዚህ ጥናት ወሐቢዝም ከሚለው ስያሜ ይልቅ ሰለፊዝም የሚለውን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ለዚህም ምክንያቴ ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም፣ አንደኛው፣ ወሐቢዝም የሚለው ስያሜ በአብዛኛው እንደ ስድብ ስለሚወሰድና አሉታዊ ትርጓሜ ስለሚሰጠው ነው፡፡ ሁለተኛው፣ በባሌ ዞን የተለያዩ አካባቢዎች፣ በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

የሚገኙ የወሐቢያ አስተምህሮ ተከታዮች እራሳቸውንና የሚያራምዱት አስተምህሮን የሚገልጹት ሰለፊዝም (ሰለፊያ) በሚል ነው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የሰለፊዝም አስተምህሮው ተከታይ የሆኑ መረጃ አቀባዮቼ ወሐቢያ የሚለውን ስያሜ ሙሉለሙሉ አይቀበሉትም፡፡

ሰለፊዝም የሚለው ስያሜ በተለያዩ ወቅቶች የተነሱ እንቅስቃሴዎችን የሚገልጽ ነው፡፡ አንደኛው፣ በአረብያ ባህረገብ፣ ናጂድ በተባለች መንደር የተወለዱት ሼኽ ሙሐመድ ኢብን አብደ አል- ወሐብ በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን የተጀመረውን የወሐቢያ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ነው፡፡ ሁለተኛው፣ ሼኽ ጀማል አል-ዲን አል-አፍጋኒ (1897)፣ ሼኽ መሐመድ አብዱህ (1905) እና ሼኽ ራሺድ ራዲ (1935) በተባሉ የእስልምና ምሁራን አማካኝነት በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን በግብጽ የተጀመረውን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ነው፡፡ ስያሜው እነዚህን የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የሚገልጽ በመሆኑ ብዥታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በዚህ ጥናት ሰለፊዝም (ሰለፊያ) የሚለው ስያሜ በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን በሼኽ ሙሐመድ ኢብን አብደ አል- ወሐብ የተጀመረውን የወሐቢያ እንቅስቃሴን የሚገልጽ ነው፡፡

ሰለፊ የሚለው ቃል ሥርወ-ምንጩ አል-ሳፍ አል-ሳሊሕ ከሚለው የአረብኛ ቃል ሲሆን፣ ለአላህ ወይም ለቀደምቶች ጥልቅ አክብሮት ወይም ፍቅር መስጠት የሚል ትርጉም አለው፡፡ (Østebo, 2008፡18)፡፡ ሼኽ አብዱል ወሐብ በወቅቱ ተስፋፍተው የነበሩና ከትክክለኛ የእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ ውጪ የሆኑ ተጻራሪ ናቸው ብሎ የሚያምናቸውን እምነቶችና ድርጊቶች ለመቃወምና ለመቀየር ይህን አስተምህሮ መጀመራቸው ይነገራል፡፡ ይህ አስተምህሮ መሰረቱ ቅዱስ ቁርዓን በተጻፈበትና በቀጥታ መተርጎም አለበት እንዲሁም ለእስልምና ሕግና ተግባራት የነብዩ መሐመድ ሱና (ምሳሌ) ብቻ መርሕ መሆን አለበት የሚሉ ናቸው፡፡ ወሐቢዝም ከእነዚህ ሁለት መሰረታዊ አስተሳሰቦች ውጪ ያሉ የእስልምና ተከታዮችን "ኢ-አማኒያን" በሚል ይፈርጃቸዋል፡፡

አምላክ አንድ አላህ ነው፡፡ ለአላህ የሚገባው አምልኮና ፍቅር ለሌላ መስጠት ማሻረክ ነው፡፡ ማሻረክ ደግሞ ሰዎች ለአላህ ያላቸውን እምነት ይረብሻል በሚል ምክንያት በመንፈሳዊ ተጓዦች የሚዘየሩ (የሚጎበኙ) መካነ ቅርሶች፣ የቅዱሳን መካነ መቃብሮችና ሌሎች ቦታዎች እንዲወድሙ ድጋፍ ያደርጋል (Gulevich, 2004፡50)፡፡ በዚህ አስተምህሮውም ይመስላል ካሉት የሱኒ እስልምና ንዑስ ክፍሎች መካከል የሐንባሊ ንዑስ ክፍል፣ በተለይም ሰለፊዝም በጣም ወግ አጥባቂ (Conservative) እንደሆነ የሚታመነው፡፡

የሰለፊያ አስተምህሮ ሼኽ ሙሐመድ ኢብን አብደ አል- ወሐብ (1703-1791) የተጀመረና በሳዑዲአረብያ የተስፋፋ ነበር፡፡ ይህ አስተምህሮ እስከ 20ኛው ክ/ዘመን ድረስ ከሳዑዲአረብያ በስተቀር በሌሎች አገራት በሚገኙ የእስልምና አስተምህሮዎች ላይ ተጽዕኖ አልፈጠረም ነበር፡፡ ይህ ሁኔታም በኢትዮጵያ ውስጥ ተመሳሳይ ነው፡፡ ሰለፊዝም በኢትዮጵያ መተዋወቅና መስፋፋት የጀመረው ጣሊያን አገሪቱን በወረራ በያዘችበት ወቅት ነው (Erlich, 2007፡67)፡፡ በወረራው ወቅት የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የትምህርት እድል በውጪ አገራት እንዲያገኙ፣ የኃይማኖት ትምህርት ቤቶችን (መድረሳ) እንዲያስፋፉ፣ ለሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ ወደ ሳዑዲአረቢያ እንዲሄዱ፣ መስኪዶችን እንዲገነቡና ዓመታዊ በዓላትን በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲያከብሩ ጣሊያን ሙሉ ድጋፍ ያደረግ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ወደ ውጪ አገር ሄደው ኃይማኖታዊ ትምህርት ተምረው የተመለሱ ግለሰቦች የሰለፊያ አስተምህሮን በኢትዮጵያ ለማስተዋወቅ እድል አገኙ፡፡

በባሌ ዞን የሚከወኑ አንዳንድ የእስልምና ኃይማኖት መንፈሳዊ ድርጊቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተቃወሙት ሼኽ መሐመድ ቃጢባ እንደሆኑ Østebo (2009፡465) ይገልጻል፡፡ ሼኽ መሐመድ ቃጢባ የባሌ ዞን የጎሎልቻ ወረዳ ተወላጅ ሲሆኑ፣ ለ23 ዓመታት ለትምህርት በሐረር፣ በወሎና በአል-አዛር ዩኒቨርሲቲ ቆይተው በ1940ዎቹ ወደ ባሌ በተመለሱበት ወቅት በአካባቢው በሚከወኑ አንዳንድ የእስልምና ኃይማኖት ድርጊቶች ላይ ተቃውሟቸውን ማሰማት ጀመሩ፡፡ እሳቸው በወቅቱ ከተቃወሟቸው ድርጊቶች መካከል ከበሮ (ድቤ) በመምታት መንፈሳዊ ሙዚቃ መከወንና የእስልምና ህግ በሚያዘው መሰረት ስግደት አለመስገድን ነበር፡፡ ሼኽ መሐመድ በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚካሄድ መንፈሳዊ ጉዞንና በስፍራው የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ላይ ምንም አይነት ተቃውሞ አላሰሙም፡፡ በመሆኑም ሼኽ መሐመድ የእስልምና አስተምህሮ እንዲቀየር ግፊት አድራጊ እንጂ የሰለፊያ አስተምህሮ አስተዋዋቂ ተደርገው እንደማይወሰዱ Østebo (2009፡466) ይገልጻል፡፡

የሰለፊያ እንቅስቃሴ በባሌ ዞን የተጀመረው በ1963/4 በሼኽ መሐመድ-አሚን ጫፉ ነው፡፡ (Østebo, 2009፡468)፡፡ እሳቸው በባሌ ዞን ሮቤ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ነጋዴ ናቸው፡፡ በሮቤ ከተማ ኑር መስኪድ ከ10 እስከ 12 አባላት ያሉት ቡድን (ጀምዓ) መሰረቱ፡፡ ቡድኑ በተመሰረተበት ወቅትም ትምህርታቸውን ከአል-አዛር ዩኒቨርሲቲ የጨረሱት ሐጂ መሐመድ ሐጂ ሙስጠፋ የባሌ ቃዲ ሆነው ተሾሙ፡፡ እሳቸውም በአካባቢው የሚከወኑ አንዳንድ

የእስልምና ድርጊቶችን፣ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞንና የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን በመስኪድ በሚሰበሰብ ሕዝብ ፊት በይፋ መቃወም ጀመሩ፡፡

በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ የሳዑዲአረቢያ መሪ የነበሩት ንጉስ ፈይሰል ከሌሎች አገራት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር፣ የሰለፊያን አስተምህሮ በሌሎች አገራት ለማስፋፋትና ለማጠናከር እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ በዚህ እንቅስቃሴም በ1962 ከኢትዮጵያ በርካታ ግለሰቦች ሳዑዲአረቢያ በሚገኘው የመዲና እስላማዊ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት እድል በማግኘት መማር ጀመሩ፡፡ ይህ የትምህርት እድል ጉዞ የ"80ዎቹ ጉዞ" በመባል ሲታወቅ፣ በዚህ ጉዞ ምክንያት ሳዑዲአረቢያ ከሄዱት መካከል ሼኽ አቡበከር መሐመድ አንዱ ናቸው (Østebo, 2009፡468)፡፡ እሳቸውም ከሳዑዲአረቢያ በ1969 ወደ ባሌ ዞን በመመለስ የሰለፊያን አስተምህሮ ማስፋፋት ጀመሩ፡፡

ሼኽ አቡበከር በ1971 በአርብ የጁምዓ ዕለት "ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ ጉዞ ክልክል ነው፡፡ ሙዳን ማክበር ክልክል ነው፡፡ መውሊድ ማክበር ክልክል ነው፡፡ አውሊያ ልጅ አይሰጡም፡፡ አውሊያዎች ሞተዋል፡፡ የሞተ ደግሞ መልስ አይሰጥም፡፡ አውሊያ ለአላህ ቅርብ ናቸው፤ ጸሎታችንን ለአላህ ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን ሞተዋል፡፡" በማለት በይፋ ተቃውሞ ማሰማታቸውን Østebo (2015፡43) ይገልጻል፡፡ ከዚህን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ግለሰቦች አማካኝነት የሰለፊያ አስተምህሮ በባሌ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ተስፋፉ፡፡

በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ከሚገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች መካከል የተወሰኑት የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች ናቸው፡፡ እነዚህ የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ክልል ውጪ በግምት 50 ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተመሰረተው አነስተኛ መንደር ውስጥ ይኖራሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ክልል ውስጥ በሚገኘው አነስተኛ መንደር ውስጥ ግን የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች እንደሌሉ መረጃ ሰጪዎቹ ገልጸውልኛል፡፡[97] በአናጂና ቀበሌ የሚገኙ ነዋሪዎች ሁሉም ነዋሪዎች የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ቢሆኑም፣ የተለያየ የእስልምና አስተምህሮ ተከታይ ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑም አልፎአልፎ በመካከላቸው ግጭት ይከሰታል፡፡

ይህ የኃይማኖታዊ አስተምህሮ ግጭት ከአካባቢው ነዋሪዎች በተጨማሪ ወደ መካነ ቅርሱ መንፈሳዊ ጉዞ ከሚያደርጉ ግለሰቦች ጋርም አልፎአልፎ ይከሰታል፡፡ ይህ የኃይማኖት

[97] - ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 9 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

አስተምህሮ መለያየት የሚፈጥረው ግጭት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይ ለውጥ ከፈጠሩ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ከበዓላቱም በተጨማሪ ለመካነ ቅርሱ የወደፊት ሕልውና ላይ እንደ ተግዳሮት ከሚነሱ ችግሮች መካከልም ይጠቀሳል፡፡[98]

## 5.3.2 የሺዓት አስተምህሮ በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

ሺዓት በዓለም ላይ ከሚገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች መካከል 15 ፐርሰንት የሚከተለው አስተምህሮ ነው (Gulevich, 2004)፡፡ ሺዓት የሚለው ቃል የመጣው "ሺዓት አሊ" ከሚለው ነው፡፡ "ሺዓት አሊ" ማለት የአሊ ተከታዮች ማለት ነው፡፡ አሊ የነብዩ መሐመድ አጎት የሆኑት አቡ ጣሊብ ልጅና የነብዩ መሐመድ ልጅ የፋጢማ ባል እንደሆኑ Ellewood and Alles (2007፡419) ይገልጻሉ፡፡ ሺዓቶች ቅዱስ ቁርዓንን መከተልና የነብዩ መሐመድን ምሳሌነት መከተል የሚለውን ይቀበላሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅትና ቀደም ሲል የነበሩ ታላላቅ የኃይማኖት መሪዎች የሚያራምዱትን የኃይማኖት አስተሳሰብ ይቀበላሉ፡፡ የካሊፌት ስልጣንንም ይቀበላሉ፡፡ ነገር ግን ስልጣኑ ከአሊ የዘር ሀረግ በቀጥታ ከሚገናኝ በካሊፍነት መመረጥ አለበት ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህ መሰረትም የነብዩ መሐመድ የልጅ ልጅና የፋጢማ ልጅ የሆኑትን አሊ በካሊፌትነት በመቁጠራቸው ምክንያት ከነብዩ መሐመድ ሕልፈት በኋላ የመጀመሪያ ካሊፍ የነበሩትን አቡ በከርን አይቀበሏቸውም (Gulevich, 2004)፡፡

ሺዓቶች በኢማም ብዛትን መሰረት በማድግ በመካከላቸው ልዩነት ምክንያት በሶስት ይመደባሉ፡፡ እነሱም አምስቶች፣ ሰባቶችና አስራ ሁለቶች ናቸው፡፡ አምስቶች ከ19ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ጀምሮ እስከ 1963 በየመን ስልጣን ላይ ነበሩ፡፡ ሰባቶች በ10ኛው መቶ ክ/ዘመን በግብጽ የፋቲሚድ ስርወ መንግስትን በመመስረት ለ200 ዓመታት ያህል በግብጽ ስልጣን ላይ ነበሩ፡፡ አስራ ሁለቶች ከሌሎች ሺዓቶች በቁጥር የሚበልጡ ሲሆን በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን የሳፋቪድ ስርወ መንግስትን በመመስረት በኢራን ስልጣን ላይ ነበሩ (Ellewood and Alles, 2007፡ 420)፡፡

ሺዓቶች ወደ ቅዱስ ስፍራዎች መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ፣ የቅዱስ ግለሰቦችን መካነ ቅርስ ይዘይራሉ (ይጎበኛሉ) እንዲሁም በስፍራውም የተለያዩ ኃይማኖታዊ ስርዓተከበራዎችን

---

[98] - አስተምህሮዎቹ እንዴት የተግዳሮትና የለውጥ ምክንያት እንደሆኑ በምዕራፍ ዘጠኝ በስፋት ተብራርቷል፡፡

ይፈጽማሉ። ይህ የሺዓቶቹ መንፈሳዊ ድርጊት በድሬ ሼኽ ሁሴን ከሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ፣ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች የሼኽ ሁሴንን ቅድስና ማመንና በእሳቸው መካነ ቅርስ ለዝየራ ከመሄዳቸው ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህንን ድርጊት ሱኒዎቹ ይቃወሙታል። የሱኒዎቹ የተቋውሞ ምክንያት እነዚህ ድርጊቶች ድንበር በመሻገር የ"ሽርክ" ባህርይ አላቸው በማለት ነው። "ሽርክ" ማለት ለአንድ አምላክ (አላህ) መደረግ የሚገባውን እምነትና መስጠት የሚገባውን ክብር ለሌላ ማካፈል ነው።

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለ200 አመታት ያህል በቤተሰብ ውርስ በሚተላለፍ የኢማምነት ስልጣን ይመራ ነበር። ይህ የኢማምነት ስልጣን በአሁኑ ወቅት ተቋርጧል። "ኢማም" የሚባለው በሺዓቶች ለማህበራዊና ኃይማኖታዊ መሪ የሚሰጥ የማዕረግ ስም ነው። በሺዓቶች የነብዩ መሐመድ የአጎት ልጅ ከሆኑት የአሊ የዘር ሃረግ ያለው ብቻ ካሊፍ መሆን እንዳለበት ያምናሉ። በድሬ ሼኽ ሁሴንም ቀደም ሲል በነበረው የኢማምነት ስርዓት የሼኽ መሐመድ ቲልማ ቲልሞ የዘር ሀረግ ያላቸው ብቻ ማህበራዊ፣ ኃይማኖታዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ይመሩ ነበር። ይህ የስልጣን ውርስ የሺዓት የእስልምና አስተምህሮ ከመካነ ቅርሱ ጋር ያለውን ትስስር ያመላክታል።

ሺዓቶች ከሱኒዎች የሚለዩት "ሙስሊሙ ትክክለኛ ነገርን ከማን ይማር?" በሚለው ጥያቄ ላይ ነው። ሱኒዎች ከቁርዓንና ከሐዲስ ብቻ ሲሉ፣ ሺዓቶች ደግሞ ከኢማሞች መማር እንደሚቻል ይቀበላሉ። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኢማምነት ስልጣን በነበረበት ወቅት ኢማሞች ማህበረሰቡን ስነምግባር፣ ኃይማኖት፣ ማህበራዊ ትስስር ያስተምሩና ይቆጣጠሩ ነበር። ይህም የሺዓት አስተምህሮ ከመካነ ቅርሱ ጋር ያለውን ትስስር ያሳያል።

ሺዓቶች በ669 የኢማም ስልጣን የያዙትን የሁሴንን መገደል ለማሰብ በሙሐራም ወር በ10ኛው ቀን የአሹራን በዓል ያከብራሉ (Ellewood and Alles, 2007፡ 420)። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም በእስልምና የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር (ሙሐራም) ከገባበት ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ ለተከታታይ 10 ቀናት የአሹራ በዓል ይከበራል። ዋናው የአሹራ በዓል ወሩ በገባ በ10ኛው ቀን ይከበራል። የአሹራ በዓል በመካነ ቅርሱ ከሚከበሩ ትልልቅ በዓላት መካከል አንዱ ሲሆን፣ የራሱ የአከባበር ስርዓት አለው። የአሹራ በዓል በመካነ ቅርሱ መከበሩ የሺዓት አስተምህሮ በስፍራው ያለውን ተጽዕኖ ያሳያል።

ሺዓቶች በፋቲሚድ ስርወ መንግስት ዘመን በ970 በግብጽ የመሰረቱት ታዋቂው የአል-አዛር ዩኒቨርሲቲ ይጠቀሳል፡፡ ሼኽ ሁሴን በግብጽ አል-አዛር ዩኒቨርሲቲ እንደተማሩና በግብጽ የሼሪያ ፍርድ ቤት አባል በመሆን ማገልገላቸው ይነገራል፡፡ ሼኽ ሁሴንም መካነ ቅርሱን ሲመሰርቱ የዩኒቨርሲቲ ቅርጽ እንዲይዝ አድርገው ነበር፡፡ ከትምህርት በተጨማሪ ሺዓቶች በውብ የኪነሕንጻ ግንባታዎች ይታወቃሉ፡፡ ከግንባታዎቻቸው መካከል በኢራን የሚገኘው የኢስፋሃን ግንባታ አንዱ ነው፡፡ በኢስፋሃን ግንባታና በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚገኘው የሼኽ ሁሴን ገሞ ግንባታ መካከል ከፍተኛ ተመሳስሎ አለ፡፡ ይህም የሺዓቶች የግንባታ ስልት ከሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ግንባታዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያመላክታል፡፡

ሶስተኛው የእስልምና አስተምህሮ ኢባዲ (ካሪጂትስ) ነው፡፡ የዚህ አስተምህሮ ተከታይ ኢባዶች ቁጥራቸው በጣም ትንሽ ነው፡፡ ልዩነታቸው የስልጣን ውርርስን በሚመለከት ሲሆን፣ በኃይማኖቱ ብቁ የሆነ ማንኛውም ግለሰብ የካሊፌትነት ስልጣን ሊኖረው ይገባል በማለት የሱኒዎችንና የሺዓቶችን ሀሳብ ይቃወማሉ፡፡ ይህ የካሊፌትነት ስልጣን ከተወሰኑ አመታት በፊት ሙሉለሙሉ ሲቀር፣ የሁለቱ አስተምህሮዎች ልዩነት በኃይማኖታዊ ስርዓተከበራዎች ክወና ላይ መመስረት ጀመረ (Gulevich, 2004)፡፡

### 5.3.3 የሱፊዝም ፍልስፍና በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

ሱፊዝም በዓለም ላይ ባሉ የሱኒና የሺዓት የእስልምና አብይ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝና የተለየ አስተሳሰብ ያለው ነው፡፡ ሱፊዝም በፈጣሪና በሰው መካከል በቀጥታ አዕምሯዊና መንፈሳዊ ግንኙነት የመፍጠር ዓላማ ያለው ፍልስፍና እና ተግባር ነው (Khanam, 2009፡8)፡፡ በሱፊዝም ፍልስፍና መሰረት ከፈጣሪ ጋር አዕምሯዊና መንፈሳዊ ግንኙነት የሚፈጥሩ መንፈሳዊ መሪዎች ‘ሱፊ’ ይባላሉ፡፡

‘ሱፊ’ የሚለው ቃል ያለውን ሥርወ-ቃል በሚመለከት በምሁራን መካከል ክርክር አለ፡፡ ይህ ክርክር እንዳለ ሆኖ የቃሉን ሥርወ-ቃል በሚመለከት Gulevich (2004)፣ Renard (2005)፣ Khanam (2009) እና Muhammad (1404 ሂጅራ) የሚከተሉትን ገልጸዋል፡፡ እነሱም አንደኛ፣ ‘ሱፊ’ የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው ‘ሰፍ’ የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም መስመር፣ ተርታ ወይም ረድፍ ማለት ነው፡፡ ስያሜውም በነብዩ መሐመድ ዘመን በስግደት ወቅት በመጀመሪያ መስመር ወይም ረድፍ ላይ ይቆሙ የነበሩ ጠንካራ ግለሰቦችን ለመግለጽ ያገለግል ነበር፡፡

ሁለተኛው፣ ‘ሱፊ’ የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው ‘ሱፋ’ የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም መካ በሚገኘው የነብዩ መሐመድ መስኪድ መግቢያ በር ላይ የሚገኝ በረንዳን ይገልጻል፡፡ በወቅቱም መኖሪያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች የመስኪዱ መግቢያ በረንዳ ላይ ይቀመጡ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎችን በረንዳ ላይ የሚቀመጡ ሰዎች መሆናቸውን ለመግለጽ ‘የሱፋ ሰዎች’ (‘አስሐበ ሱፍ’) በሚል ይጠሩ ነበር፡፡ ሶስተኛ፣ ‘ሱፊ’ የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው ‘ሱፍ’ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ሐር ማለት ነው፡፡ ይህም ሱፊዎች በአብዛኛው ይለብሱት የነበረውና ከሐር ክር የተሰራ ልብስ መነሻ ያደረገ ነው፡፡ አራተኛ፣ ‘ሱፊ’ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ከሆነው ‘ሶፊያ’ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ጥበብ ማለት ነው፡፡ አምስተኛ፣ ‘ሱፊ’ የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው ‘ሰፋ’ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ንጹሕ ማለት ነው፡፡

ሱፊዝም፣ በአረብኛው አጠራር ‘ተሰዉፍ’ በሚል ይታወቃል፡፡ ‘ተሰዉፍ’ ማለት አንድ አማኝ ልቡናውን (ቀልቡን) በማጽዳት የአምላክን ሕያውነት የመረዳትና ከአምላክ ጋር ያለውን ቅርበት ለማጠናከር የሚያልፍበት ሂደት ነው፡፡ ሱፊዝም እራሱን የቻለ የእስልምና ንዑስ ክፋይ ወይም የአስተምህሮ ፈለግ (School of thought) አይደለም፡፡ ነገር ግን በመንፈሳዊ ልዕልና (Mystical) ላይ መሰረት በማድረግ እስልምናዊ አስተምህሮዎችና ተግባራት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው (Gulevich, 2004፡50)፡፡ መንፈሳዊ ልዕልና ማለት የሰው ልጅ ሊፈጽማቸው የማይችሉና በፈጣሪ ብቻ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን መከወን የሚያስችል ኃይል ነው፡፡ መንፈሳዊ ልዕልና ከእስልምና በተጨማሪ በክርስትና፣ በጁዲዝምና በሌሎች ኃይማኖቶች ዘንድ የተለመደ ነው፡፡

ሱፊዝም ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ምግባራዊ፣ ጥበባዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ቅርጽ የሚያሲዝ ፍልስፍና ነው፡፡ የፍልስፍናው መሰረት በፈጣሪና በሰው ልጅ መካከል የአዕምሮና የመንፈስ የቀጥታ ግንኙነት መፍጠር ነው፡፡ በዚህም ፍልስፍና በፈጣሪና በሰው ልጅ መካከል ግንኙነት የፈጠሩ፣ ከፈጣሪ የተመረጡ፣ ፈጣሪ የላካቸው መልዕክተኞች፣ ነብያትና ቅዱሳን የነበራቸውን መንፈሳዊ ልዕልና መነሻ ያረገ ነው፡፡ እነዚህም አዳም፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን፣ ኢየሱስ፣ መሐመድና ሌሎች ታሪካቸው በቅዱስ ቁርዓንና በሐዲስ ላይ የተገለጹት ነብያት እንዲሁም ከቅዱስ ቁርዓንና ከሐዲስ ውጪ ያሉና በየአገራቱ የኖሩ በእውቀታቸው ወይም በመንፈሳዊ ኃይላቸው ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡

በሱፊዎች ዘንድ በመንፈሳዊ መንገድ ለሚጓዝ ማንኛውም ሱፊ ነብያትና አውሊያ (ቅዱሳን ግለሰቦች) ዋና ምሳሌዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህን ነብያትና አውሊያ አንድ የሚያደርጓቸው የጋራ

ባህርያት እንዳላቸው Renard (2005፡2) ይገልጻል፡፡ የጋራ ባህርያቱም ከፈጣሪ ጋር ያላቸው ቅርብ ግንኙነት፣ ተዓምራዊ ድርጊትን ለመፈጸም ልዩ ኃይል ስለተሰጣቸው እንዲሁም በመንፈሳዊ ኃይል ለመመራትና በጉዟቸውም ወደ ኋላ እንደማይሉ ሙሉ እምነት ማግኘታቸው ነው፡፡

የሱፊዝም ፍልስፍና መሰረቶችና ተግባሮች በርካታ መሆናቸውን Renard (2005)፣ Khanam (2009) እና Muhammad (1404 ሂጅራ) ካህናም (2009) ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ሱፊዝም የተጀመረው ቅዱስ ቁርዓን ለነብዩ መሐመድ እንደወረደላቸው እንደሆነ ሱፊስቶች ማመናቸው ነው፡፡ ቁርዓን በወረደበት ወቅት ለነብዩ መሐመድ ዕውቀት በሁለት መንገድ እንደተገለጠላቸው ያምናሉ፡፡ አንደኛው፣ በቃል መልክ በቁርዓን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መለኮታዊ ኃይል በልባቸው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ለሱፊዎች ሁለት አይነት ዕውቀት አለ፡፡ አንደኛው፣ 'የመጽሐፍ ዕውቀት' ('ኢልም-ኢ-ሰፊና') ነው፡፡ ይህም በቁርዓንና በሐዲስ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝና በቃል መልክ የወረደ ነው፡፡ ሁለተኛው፣ 'የልብ ዕውቀት' ('ኢልም-ኢ-ሲና') ነው፡፡ ይህም በልብ ውስጥ የገባ መለኮታዊ ኃይል ነው፡፡ በዚህ መሰረት የኃይማኖት ምሁራን (ኡለማ) ቁርዓንንና ሐዲስን የሚያውቁና የመጽሐፍ ዕውቀት ያላቸው ሲሆኑ፣ የልብ ዕውቀት ባለቤቶች ደግሞ ሱፊስቶች ናቸው፡፡

በሱፊዝም ፍልስፍና ነብዩ መሐመድ የነበራቸው የልብ ንጽሕና (ተሰዉፍ) ለዚህ ማዕረግ እንዳበቃቸው ያምናሉ፡፡ ነብዩ መሐመድም ከነበራቸው የልብ ንጽሕና ምክንያት ቅንጦት ያለው ኑሯቸውን ትተው ቀላል ኑሮ መኖር መጀመራቸው፣ እጅግ ደግና ለሰው አዛኝ መሆናቸው፣ ብዙ ጊዜያቸውን በስግደት፣ በጾም፣ በጸሎት፣ ኃይማኖታዊ ዕውቀትን በማዳበር ማሳለፋቸውና ሀብት የማካበት ፍላጎታቸው ዝቅተኛ እንደነበር ያምናሉ፡፡ እነዚህ የነብዩ መሐመድ ሰብዕናዎችና ድርጊቶች ለሱፊዎች የሕይወት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

የእስልምና እምነትና ተግባራት ከሶስት አላባውያን የተመሰረተ ነው፡፡ እነሱም በአላህ ማመን ('ኢማን')፣ እስላማዊ ሕግጋትን መተግበር ('ኢታህ') እና መልካም ስራ መስራትና ታማኝ መሆን ('ኢህሳን') ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሶስት አላባውያን መካከል ሱፊስቶች መልካም ስራ መስራትና ታማኝ መሆን ('ኢህሳን') ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ "ኢህሳን" የአምላክን ትዕዛዝ በሙሉ ፍላጎት፣ ልፋትና ቀናዒነት በጥራት የመከወን ሂደት ነው፡፡ አምላክን መፍራት ('ተቅዋ') ለሱፊዎች ዋና የእምነታቸው መሰረት ነው፡፡ "ተቅዋ" ነፍስን በማሰልጠንና በመግራት

ዘለዓለማዊ ማረፊያዋ በመልካም ስፍራ እንዲሆን ማድረጊያ መንገድ ነው። የፈጣሪን ታላቅነት ከልብ ውስጥ በማስረጽ ራስን በመንፈስና በምግባር መልካም ሰብዕና ማላበስ ነው። የዚህ ድርጊትም መሰረቱ የምንመኘውን ነገር ተስፋ ማድረግ እንደሆነ ሱፊዎች ያምናሉ። ተስፋው በጎ ነገር እንዲገጥመን፣ ገነት (ጀነት) እንድንገባ፣ ከክፉ ነገር እንድንጠበቅ ሊሆን ይችላል።

የሱፊዝም ፍልስፍና ከነብዩ መሐመድ ዘመን ጀምሮ ያለና የእስልምና ኃይማኖት በሚገኝባቸው አገሮች ሁሉ ለመስፋፋት የቻለ ነው። በተለያዩ ዘመናት በኖሩ ሊቃውንት አማካኝነት የተፈጠሩ የሱፊ ስርዓቶች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ መካከል የቃድሪያ፣ የቺሺቲ፣ የሻታሪያ፣ የሳማኒያ፣ የናቅሽባንዲያ፣ የሐልቬቲያ፣ የኒማት፣ የባይራሚያ፣ የቤክታሺያ፣ የካልዋቲያ፣ የሻዲልያ ወዘተ. ስርዓቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህ ስርዓቶች በየአገራቱ በሚገኙ የሱፊ ሊቃውንት አማካኝነት የተስፋፉ ናቸው።

ከእነዚህ የሱፊዝም ሊቃውንት መካከል በነብዩ መሐመድ ዘመን የነበሩት ሳልሞን አል- ፐርሺያ (ፐርሺያ) እና የነብዩ ወራሾች አቡበከርና ዑመር በዋናነት ይጠቀሳሉ። ከነብዩ ሕልፈት በኋላም ሐሰን አል- በስራ (ደቡብ ኢራቅ)፣ ታዋቂዋ የሱፊ ሴት ሊቅ ራቢያ አል- ዐዲዊያ (ኢራቅ)፣ ዱዑን-ኑን (ግብጽ)፣ ባያዚድ አል- ቢስታም (ኢራቅ)፣ ሐሳጅ አል- ባግዳድ (ኢራቅ)፣ ኢብራሂም ኢብን አድሃም (ባልክ)፣ አል ፈራቢ (ቱርክ)፣ አቡ-አል-ኢብን-አቪሲና (ማዕከላዊ ኢሲያ)፣ አህመድ-አል-ኃዛሊ (ማዕከላዊ ፐርሺያ)፣ አብድ-አል-ቃዲር አል-ጀይላኒ (ባግዳድ) የመሳሰሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

### 5.3.3.1 የቃድሪያ ስርዓት በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

ሱፊዝም በአናጂና ቀበሌና አካባቢው የእስልምና ኃይማኖት መተዋወቅ ከጀመረበት ከ8ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ የታወቀ አስተሳሰብ እንደሆነ ይገመታል። ከሱፊዝም ፍልስፍናዎች መካከል የቃድሪያ ስርዓት አንዱ ነው። የቃድሪያ ስርዓትን የፈጠሩት አብድ-አል-ቃዲር አል-ጀይላኒ ናቸው። ሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ በሱፊዝም እስልምና ኃይማኖት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ተጽዕኖ የፈጠረውን የቃድሪያ ስርዓት የፈጠሩ ናቸው። የቃድሪያ ስርዓትን በመፍጠራቸውም በሱፊዝም ታሪክ የመጀመሪያው መደበኛ የሱፊዝም ስርዓት መስራች ናቸው (Renard, 2009፡19)። ይህ የቃድሪያ ስርዓት መጠሪያውን ያገኘውና በስፋት የተስፋፋው ከሼኽ አብዱልቃድር ሕልፈት በኋላ ነው።

የቃድሪያ ስርዓት በዋናነት የሚያተኩርባቸው ነጥቦች የሰው ልጅ ያለውን መንፈሳዊ ተፈጥሮ ለቁሳዊ ዓለም ብቻ እንዳይጠቀም፣ ከራስ ጋር የሚኖረን ቆይታ የውስጣችንን ዓለም ለማጠንከር እንደሚረዳ፣ ነፍስን ለማጥራትና የአላህን ትዕዛዝ ለመፈጸም ቀናኢ መሆን፣ ራሳችንን ለሰፊ ጊዜ መመልከት፣ የሞራል ልዕልና በመፍጠር መንፈሳችንን ማጥራት የመሳሰሉት እንደሆኑ ሙሐመድ (አመት የለውም፡23) ይገልጻል፡፡ የቃድሪያ ስርዓት አብይ የስርዓተከበራ ክወናዎች ተግባራዊ በማድረግ ላይ የተመሰረተ ነው (Renard, 2009፡189)፡፡ እነዚህ ስርዓተከበራዊ ክወናዎችም መሰወር ወይም መሸሸግ (Retreat)፣ አተነፋፈስን መቆጣጠር (Breath control)፣ መመሰጥ (Contemplation) እና ጾም (Fasting) ናቸው፡፡

የቃድሪያ ስርዓት በባሌ እንዴት ሊተዋወቅ እንደቻለ ሁለት ሀሳቦች አሉ፡፡ አንደኛው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መስራች የሆኑት ሼኽ ሁሴን ከአብዱቃዲር ጀይላኒ ጋር በአካል በተገናኙበት ወቅት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በ15ኛው መቶ ክ/ዘመን በሸሪፍ አቡበክር አብደላህ ኢድሪስ አማካኝነት ነው (Lewis, 1955፡592)፡፡ ሼኽ አብዱልቃድር ከባግዳድ ወደ አናጂና በመምጣት ከሼኽ ሁሴን ጋር በአካል እንደተገናኙና እሳቸውን ዘይረው ወደ አገራቸው እንደተመለሱ በስፋት ይነገራል፡፡ ይህ አፈታሪክ ሼኽ ሁሴን በነበሩበት ዘመን የቃድሪያ ስርዓት በአካባቢው የመስፋፋት እድሉ ከፍተኛ እንደነበር ያሳያል፡፡ ሼኽ አብዱልቃድር ወደ ስፍራው በመጡበት ወቅት ድንኳናቸውን ጥለው ያረፉበት ቦታ ላይ በስማቸው የተገነባ የማስታወሻ ገሞ አለ፡፡



*ፎቶ፣ 13፡- የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ መታሰቢያ ገሞ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

ከላይ በፎቶ ግራፉ ላይ የቀረበው ገሞ የእሳቸውን ክብር መግለጫ፣ በስፍራው መጥተው እንደነበር ለማስታወስ በመታሰቢያነት የተገነባና ወደ ስፍራው የሚመጣ አማኝ የእሳቸውን በረከት እንዲያገኝ በሚል የተገነባ ነው። ይህ ገሞ የተገነባው በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ላይ ሲሆን፣ ገሞውንም ያስገነቡት ሼኽ ቡሽራ አል-ከሪም እንደሆኑ ይነገራል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒ መታሰቢያ ገሞ ከአናጂና በተጨማሪ በሐረር ከተማም ተገንብቷል። ከኢትዮጵያም ውጪ በኤርትራ (ምጽዋ) እና በጅቡቲ የሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒ መታሰቢያ ገሞ መኖሩን Trimingham (1952፡139-142) ይገልጻል።

በባሌ ዞን በሱፊ ፍልስፍና መስፋፋት ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉት ሐጂ ናስር ናቸው (Braukämper, 2004)። ሐጂ ናስር በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን በሊቢያ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው በመጨረሻም በባሌ ዞን አጋርፋ ወረዳ በአጋርፋ ከተማ አካባቢ የኖሩ ቅዱስ የሱፊ ሰው እንደሆኑ ይታመናል። የሐጂ ናስር ወራሽ የሆኑት ሼኽ እስማኤል ሼኽ አብዱልወሃብ (1790-1860)፣ የወሎው ሼኽ ማሩፍ ጉዱ፣ ሼኽ አብዱልወሃብ (1839-1942)፣ ሼኽ የኑስ (1810-1870) እና ሌሎችም የኃይማኖት ምሁራን በአጋርፋና በሌሎች የባሌ ዞን ወረዳዎች የሱፊ ፍልስፍናን በማስፋፋት እንደሚታወቁ Østebo (2015፡75) ይገልጻል። በአሁኑ ወቅት በአጋርፋ ከተማ አካባቢ የሐጂ ናስር መቃብር እንደሆነ በሚታመነው ስፍራ በስማቸው መካነ ቅርስ ተገንብቶ ይገኛል። መካነ ቅርሱንም በእሳቸው ቤተሰብ የሚመራ ሲሆን፣ በርካታ ሕዝብ ወደ ሐጂ ናስር መካነ ቅርስም በመሄድ የመውሊድ በዓልን ያከብራል።

ከእነዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ወቅቶች ለእስልምና ኃይማኖት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጾኦ ያበረከቱ የሱፊ ሊቃውንት በባሌ ዞንና በአካባቢው አሉ። ለእነዚህም ሊቃውንት በተለያዩ የዞኑ አካባቢዎች ገሞ (ቁባ) ተንብቶላቸዋል። ከእነዚህ ሊቃውንት መካከል ሼኽ ሶፍዑመር፣ ሼኽ አበልቃሲም፣ ሐጂ ናስር፣ ሐጂ ሻሌ፣ ሼኽ ዳውድ፣ ሼኽ ኢብራሂም ዳሞ፣ ሼኽ ሱሌይማን፣ ሼኽ ቂሞኜ፣ ኑር አሚን፣ ኑር አዳሞኖዬ፣ ኑር አብዲዮ፣ አዮ ሞሚና፣ ሼኽ ሐሰን ዑስማን፣ ሼኽ መሃመድ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

### 5.3.3.2 የሁሴኒያ ስርዓት በአናጂና ቀበሌና አካባቢው

ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት የጀመሩትና የራሳቸው የሆነ የሱፊ ስርዓት እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህም የሱፊ ስርዓት ‘ሁሴኒያ’ በሚል ስያሜ እንደሚታወቅ መረጃ ሰጪዎቼ ገልጸውልኛል፡፡[99] ‘ሁሴኒያ’ የሚለው የአረብኛ ቋንቋ የአገላለጽ ስርዓት ሲሆን፣ የአማርኛ ትርጉሙ ‘የሁሴን’ እንደማለት ነው፡፡ ይህ ስርዓት በወቅቱ ሼኽ ሁሴን ለተማሪዎቻቸው ከሚያስተምሯቸው የቁርዓንና የሀዲስ ትምህርቶች በተጨማሪ ለሕይወታቸው ይጠቅማል የሚሉትን የግል አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ እምነትና ድርጊትን የያዘ ነው፡፡ የሁሴኒያ ስርዓት መሰረት ያደረገው በድርጊትና በልብ ንጽሕና (ተሳዉፍ) ላይ ነው፡፡

የሼኽ ሁሴን የሁሴኒያ ስርዓት ከቁርዓንና ከሀዲስ መጻሕፍት ውስጥ የማይገኙ ሀሳቦችን የያዘ ነው፡፡ በወቅቱም ሼኽ ሁሴን “አላህ በቁርዓን ውስጥ እንድንከውን ካዘዘን ድርጊቶች በተጨማሪ ሌሎች ድርጊቶችም አሉ፡፡ እነዚህን ድርጊቶች እሱ ለመረጣቸው ቅዱሳን ብቻ የሚገልጻቸው ናቸው፡፡” የሚል ሀሳብ ያራምዱ እንደነበር ይነገራል፡፡ በዚህም እምነት መሰረት መከወን አለባቸው የሚሏቸውን ድርጊቶች እየከወኑ፣ ተማሪዎቻቸውም እንዲከውኑ ያደርጉ ነበር፡፡

ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት በሁሴኒያ ስርዓት መሰረት ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ድርጊቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ አንደኛ፣ ራስን መቻል ነው፡፡ ይህም የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ራሳችንን ችለን መስራት እንደሚገባ የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህም ስራዎች ለስግደት የሚሆን የሶላት ውኃን ከወንዝ ራሳችን መቅዳት፣ የሚያስፈልጉንን ምግብና መጠጥ በራስ ማዘጋጀት፣ የመጠጥ ውኃ ራሳችን ከወንዝ መቅዳት ወይም አልባሳትን ራሳችን ማጠብ ናቸው፡፡ በወቅቱም ሼኽ ሁሴን ራስን መቻል ከፈጣሪ ልዩ በረከት እንደሚያስገኝ ያስተምራሉ፡፡

ሁለተኛ፣ መሰወር ወይም መደበቅ ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን ለተወሰነ ጊዜ ማንም ወደ ማያገኛቸው ቦታ በመሄድ ተደብቀው ይቆያሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉትም ለራሳችን ብቻ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ለተማሪዎቻቸው ምሳሌ ለመሆንና ለራሳቸው ጊዜ ለመስጠት ነው፡፡ ሶስተኛ፣ ለረጅም ጊዜ በጾም መቆየት ነው፡፡ በወቅቱም ሼኽ ሁሴን ረጅም ጊዜያቸውን በጾም፣ በጸሎትና ኃይማኖታዊ ትምህርቶችን በማጥናትና ለተማሪዎቻቸው በማስተማር ያሳልፉ ነበር፡፡ ሼኽ

---

[99] - ሼኽ አሕመድ ሼኽ መሀመድ ሳፊ (አናጂና ቀበሌ)፣ አቶ ተሾመ ብርሃኑ (አዲስ አበባ ከተማ) እና አቶ መሐመድ ሼኽ ሁሴን (አዲስ አበባ ከተማ)፡፡

ሁሴን ለ40 ዓመታት ያህል በአይናገኜ ገደል ውስጥ ከሰው ተለይተው በጾምና በጸሎት እንደኖሩ ይነገራል፡፡

አራተኛ፣ ብዙ አለማውራት ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን ብዙ ማውራት የማይወዱና ዝምተኛ እንደነበሩ ይነገራል፡፡ በወቅቱም እሳቸውን በመወከል ሀሳባቸውን የሚያቀርቡላቸውና ከእንግዶች ጋር የሚወያዩላቸው ሼኽ ሶፍ ዑመር ነበሩ፡፡[100] እሳቸውም "ብዙ ማውራት የሚወድ ሰው፣ ብዙ በማውራቱ ምክንያት ውሸት የመናገር እድሉ ከፍተኛ ሲሆን ለወሬ ሱስ ይዳረጋል፡፡ ይህ ደግሞ ከሰውም ከፈጣሪም ያቀያይማል፡፡" ብለው ያስተምሩ እንደነበር ይነገራል፡፡ ሼኽ ሁሴን ብዙ አለማውራት የአንድ ሰውን አዋቂነት ያሳያል የሚል አስተምህሮ ነበራቸው፡፡ እሳቸውም "የሰው ምላስ አንበሳ ነው፡፡ አንበሳና የራስ ምላስ ደስ የሚሉት መቆጣጠር ከቻልን ብቻ ነው፡፡ መቆጣጠር ካልቻልን ሁለቱም እኛን ያጠፉናል፡፡" የሚል ምሳሌ ነበራቸው (Eshetu, 1973፡10)፡፡

አምስተኛ፣ ብዙ ጊዜን በጸሎት ማሳለፍ ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን ረጅም ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በጸሎት እንደነበር ይነገራል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ግለሰብ ለምን በተደጋጋሚ ለረጅም ሰዓት እንደሚጸልዩ ይጠይቃቸዋል፡፡ ሼኽ ሁሴንም "ይህንን ዛፍ ተመልከት፡፡ ዛፉ ቢቆረጥ በየትኛው አቅጣጫ ይወድቃል?" ብለው ጠየቁት፡፡ የግለሰቡን መልስ ሳይጠብቁ ራሳቸው "ዛፉ የሚወድቀው በተቆረጠበት አቅጣጫ በኩል ነው፡፡ የእኔም ድርጊት ተመሳሳይ ነው፡፡ ከሕልፈቴ በኋላ ነፍሴ ገነት የምትገባው በጸሎቴ አማካኝነት ወደ አላህ ስላዘነበልኩ ነው፡፡" በማለት እንደመለሱለት ይነገራል፡፡[101]

ስድስተኛ፣ ለራስም ሆነ ለሰዎች መልካም መሆን ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን ሰው ለራሱ መልካም መሆን እንዳለበት ያስተምሩ ነበር፡፡ ሰው ለራሱ መልካም ሲሆን፣ ራሱን ከክፉ ነገር ሲጠብቅና ለራሱ መልካም ነገሮችን ሲያደርግ ፈጣሪውን ያስደስታል፡፡ ፈጣሪውም መልካም ነገር ያደርግለታል፡፡ ሁሉም ሰው እርስበርሱ እንዲዋደድ፣ እንዲረዳዳና መልካም አሳቢ እንዲሆን አንዱ ሌላውን ከረዳ ፈጣሪ በእጥፉ እንደሚሰጠው ያስተምሩ ነበር፡፡

ሰባተኛ፣ ጫት መቃምን መደገፍ ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን ጫት ባይቅሙም፣ ጫት የሚቅምን ሰው እንደማይቃወሙና መቃምን ያበረታቱ እንደነበር ይነገራል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ግለሰብ "ጫትን መቃም ጥሩ አይደለም፡፡ ጫት ሰውነትን ያደክማል፤ የወሲብ ፍላጎትንም ይቀንሳል፡፡

---

[100] - ሼኽ አሕመድ ሐጂ ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 26 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡
[101] - ሼኽ ሙኽሙድ ሼሕ ኢስሪስ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

በመሆኑም እርስዎ ጫትን መቃምን መደገፍ ይተዉ፡፡" ይላቸዋል፡፡ እሳቸውም "አዎ ጫት ሰውነትን ያደክማል፤ የወሲብንም ፍላጎት ይቀንሳል፡፡ ሰውነትን ሳያደክሙና የወሲብ ፍላጎትን ሳይቀንሱ የአላህ አገልጋይ መሆን አይቻልም፡፡" በማለት እንደመለሱለት ይነገራል፡፡[102] በወቅቱም ሼኽ ሁሴን ጫት መቃም ሰውነትን ለማድከም፣ የወሲብ ፍላጎትን ለመቀነስ፣ ሀሳብን ለመሰብሰብ፣ ለተመስጦ፣ እራስን ለማንጻትና ከፈጣሪ ጋር በመንፈስ ለመገናኘት እንደሚጠቅም ያስተምሩ እንደነበር ይነገራል፡፡

ከጫት ጋር በተያያዘ Cerulli (1971፡429-431) የገለጸው ተመሳሳይ መረጃ አለ፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ግለሰብ ሼኽ ሁሴንን "ጫትን ማበረታታት የለብዎትም፡፡ ምክንያቱም ጫት በሲዖል ውስጥ ካለ ሁኔታ ጋር የሚያመሳስለው አራት ባህርያት አሉት፡፡ እነሱም፣ ምግብ ይዘጋል፣ ከሰው ይነጥላል፣ እንቅልፍ ይከለክላል እንዲሁም የወሲብ ፍላጎትን ይቀንሳል፡፡" ይላቸዋል፡፡ ሼኽ ሁሴንም በጥሞና ካዳመጡት በኋላ "እስቲ ጥያቄ ልጠይቅህ፣ ልብ ብለህ አዳምጠኝ፡፡" አሉትና ወደ ጥያቄያቸው ገቡ፡፡ "ነብዩ መሐመድ ብዙ ምግብ ይመገቡ ነበር?" ብለው ሲጠይቁት "አይ" ሲል መለሰ፡፡ "ነብዩ ከሰው የተነጠሉ ነበሩ?" ብለው ሲጠይቁት "አይ" ሲል መለሰ፡፡ "ነብዩ ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ነበራቸው?" ብለው ሲጠይቁት "አይ" ሲል መለሰ፡፡ ሼኽ ሁሴንም "ጫት መቃም ሰውን ወደ ኃጽያት ከሚገፉ ነገሮች ይቆጥባል፡፡ በመሆኑም ጫት መቃም ነብያት ወደአላቸው ባህርያት ያቀርባል፡፡" በማለት መለሱለት፡፡

ጫት የተቀደሰ ተክል እንደሆነ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ መንፈሳዊ ተጓዦች ያምናሉ፡፡ የጫት ተክል አፈጣጠርን በሚመለከት የሚነገር ሚት አለ፡፡ ይህን ሚት መረጃ አቀባዩ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡[103]

> በገነት ውስጥ 'ማኡ ሃያት' የሚባል ውኃ አለ፡፡ ይኸን ውኃ የጠጣ ለዘለዓለም ይኖራል፡፡ አንድ ጊዜ ከዲር፣ ኤልያስና ዙልቀርኔይኒ የሚባሉ ሰዎች ይህንን ውኃ ፍለጋ ጉዞ ጀመሩ፡፡ በጉዟቸው ላይ ከዲር "ፈጣሪ ሆይ፤ ይኸን ውኃ መጀመሪያ ለጓደኞቼ፣ ቀጥሎ ለእኔ ስጠኝ" አለ፡፡ ኤልያስ "ፈጣሪ ሆይ፤ መጀመሪያ ለእኔ፣ ቀጥሎ ለጓደኞቼ ስጠን" አለ፡፡ ዙልቀርኔይኒ ደግሞ "ፈጣሪ ሆይ፤ ለእኔ ብቻ ስጠኝ" አለ፡፡ በጉዟቸው ላይም ከዲርና ኤልያስ ውኃውን አግኝተው ጠጡ፡፡ ዙልቀርኔይኒ በስፍራው ሲደርስ ውኃው ደርቆ በቦታው አንዲት ተክል በቅላ አገኘ፡፡ ተክሏም ጫት ነበረች፡፡ ዙልቀርኔይኒም ጫቷን ሰባብሮ በላት፡፡ እሱም እዛው ላይ ሞተ፡፡ በእሱ ቀብር ላይም የጫት ተክል በቀለ፡፡ በዚህም ምክንያት ጫት የዙልቀርኔይኒ ልጅ እንደሆነ ይታመናል፡፡

---

102 - አቶ ነስረዲን ሀሰን፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

103 -ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ዑስማን፣ አናጂና ቀበሌ፣ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

በዚህ ሚት መሰረት ጫት መቃም ሲጀመር ዙልቀርኔይኒ ይታሰባል፡፡ ጫት ሲቃም እሱን ማሰብ ለእሱ ፋቲያ እንደመቅራት ይቆጠራል፡፡ "ፋቲያ" ለሞተ ሰው የነፍስ ማስማሪያ የሚቀራ ነው፡፡ አባት ከሞተ በኂላ ልጁ ለአባቱ ፋቲያ ይቀራል፡፡ ምክንያቱም ልጁ ቁርዓን መቅራት የተማረው ከአባቱ በመሆኑ ነው፡፡ ለዙልቀርኔይኒም ጫት ልጁ ነው፡፡ የጫት አባት እሱ ነው፡፡ ምክንያቱም ከእሱ ነውና ጫት የተፈጠረው፡፡ በዚህ ምክንያትም ይመስላል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከወኑ የተለያዩ መንፈሳዊ ስርዓቶች ጫት በመቃም የሚከወኑ ናቸው፡፡ ወደ ስፍራው የሚሄደው አብዛኛውም መንፈሳዊ ተጓዥ በስፍራው በሚኖረው ቆይታ ወቅትም ጫት የመቃም ልምድ አለው፡፡ በመካነ ቅርሱ ጫት በጸሎት፣ በተለያዩ የሙዳ ስርዓተከበራዎች በሚከወኑበት፣ በወዳጃ (በሳምንታዊ የጸሎት ፕሮግራም)፣ በዶውሪ (በጋራ ስብሰባ)[104] ወቅት ይቃማል፡፡ በስፍራውም ጫት መቃም ይበረታታል፡፡

ስምንተኛ፣ ዕውቀት ያለተግባር ጥቅም የለውም፡፡ ሼኽ ሁሴን የተማረና አዋቂ ሰው የዓለም ብርሃን እንደሆነ ያምኑ ነበር፡፡ የተማረ ሰው ግን የዓለም ብርሃን የሚሆነው ዕውቀት ስላለው ሳይሆን ዕውቀቱን በተግባር ካዋለ ብቻ እንደሆነ ያስተምራሉ፡፡ ተግባሩም አላህን ለማወቅ፣ ለማስደሰትና ሰውን ለመርዳት የሚውል መሆን እንደሚገባ ያስተምራሉ፡፡ ዘጠነኛ፣ መልካም ድርጊት መልካም ነገርን ያስገኛል፡፡ ሼኽ ሁሴን "ዕውቀት ብርሃንን ያስገኛል፤ ሶላት ወደ ገነት ያስገባል፤ እርዳታ መስጠት ሰውን ከመጥፎ መንፈስ ይጠብቃል፡፡" ብለው ያስተምሩ ነበር (Eshetu, 1973፡10)፡፡

ይህ አስተምህሮ በቅዱስ ቁርዓን ወይም በሐዲስ ውስጥ የሚገኝ ባይሆንም እሳቸው ሰዎች መልካም ነገር ማድረግ ያለውን ጥቅም የሚያስተምሩበት ሀሳብ ነው፡፡ በዚህ የሼኽ ሁሴን አስተምህሮም ይመስላል ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርጉ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች እርስበርስ ለመረዳዳት፣ ለተቸገረ ሰው እርዳታ መስጠትና እርስበርስ ያላቸው ፍቅርና የወንድምአማችነት ስሜት ከፍተኛ የሆነው፡፡

አስረኛ፣ የአልኮል መጠጥ ሐራም ነው፡፡ በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴንና ፋቂሕ የሚባሉ ግለሰብ በአካባቢው በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጅ የአልኮል መጠጥ ሐራም (ክልክል) ነው ወይስ ሐላል (ክልክል አይደለም) በሚል ይከራከራሉ፡፡ ፋቂሕ የአልኮል መጠጥ ሐላል ነው ብለው ሕዝቡን እንዲጠጣ የሚያበረታቱና እሳቸውም የሚጠጡ ነበሩ፡፡ ሼኽ ሁሴን ደግሞ የአልኮል መጠጥ

[104] - ስለዶውሪ ስርዓት በምዕራፍ 8 ተብራርቷል፡፡

ሐራም ነው የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ ሁለቱ እየተከራከሩ ሳለ፣ አንዲት ሴት በአጠገባቸው ስታልፍ አይታቸው ቆመች፡፡ ሴትየዋም "አንዴ በጀርባዬ ስላዘልኩት ህጻን ብነግራችሁ ፍቃደኛ ናችሁ?" ስትል ጠየቀቻቸው፡፡ እነሱም "አዎ ንገሪን" አሏት፡፡ ሴትየዋም "ይህን በጀርባዬ የምታዩትን ሕጻን የወለድኩት ከራሴ ልጅ ነው፡፡ በእለታት አንድ ቀን ልጄ የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ ሰክሮ እቤት መጣና፣ በተኛሁበት ደፈረኝ፡፡ ከዛም ይህንን ልጅ አርግዤ ወለድኩኝ፡፡ እስቲ ፍረዱኝ ይህንን ህጻን ከራሴ ልጅ ወልጄዋለሁ አሁን ህጻኑን ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጨነቀኝ፡፡" ስትል ትጠይቃቸዋለች፡፡

በሴትየዋ ንግግር ሼኽ ሁሴን ደንግጠው ከተቀመጡበት በመነሳት ፊጣሪያቸውን ካመሰገኑ በኋላ "እህስ አሁን ተመለሰልህ?" በማለት ፋቂህን ጠየቁቸው፡፡ ፋቂህም "አዎ የአልኮል መጠጥ ሐራም መሆኑን አምኛለሁ፡፡" አሉ፡፡ ሼኽ ሁሴንም በፍጥነት ወደ መንደራቸው ሄዱ፡፡ ከሰባት ቀናት በኋላ ፋቂህ ሞተ፡፡ ሼኽ ሁሴንም የፋቂህን ሞት ሲሰሙ "የአልኮል መጠጥ መያዣው ጋን ተሰበረ፡፡" ማለታቸውን Cerulli (1971፡425) ይገልጻል፡፡[105]

ለዚህም ይመስላል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚገኝበት አካባቢ የአልኮል መጠጥ የተከለከለ ነው፡፡ ወደ ስፍራው ለመንፈሳዊ ጉዞ የሚመጣ ሰው ወደ ስፍራው ከመምጣቱ ከሶስት ቀን በፊት ማንኛውም አይነት የአልኮል መጠጥ እንዲጠጣ አይፈቀድለትም፡፡ በስፍራውም ሆነ በሼኽ ሁሴን ወዳጆች ዘንድ የአልኮል መጠጥ ሐራም ነው፡፡ የአልኮል ሐራምነት በእስልምና ኃይማኖትም ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ነገር ግን በኦርቶዶክስ ክርስትና ኃይማኖትና በዋቄፈና ኃይማኖት የአልኮል መጠጥ መጠጣት ይፈቀዳል፡፡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ጉዞ የሚያድርግ የእስልምና፣ የክርስትና፣ የዋቄፈና ወይም የሌላ ኃይማኖት ተከታይ የሆነ ማንኛውም ግለሰብ በስፍራው የአልኮል መጠጥ መጠጣት እንዲሁም ወደ ስፍራው ከመምጣቱ ከሶስት ቀን ወዲህ የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ መምጣት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

በሼኽ ሁሴን አስተምህሮ 3 ቁጥር ሙሉ፣ ንጹሕና ትክክል የመሆን ተምሳሌት ነው፡፡ 3 ቁጥር የሰው ልጅን የተፈጥሮ ባህርያትን ይወክላል፡፡ እነዚህም 3 የተፈጥሮ ባህርያት መንፈስ (Sprit)፣ ነፍስ (Soul) እና አካል (Body) ናቸው፡፡ እነዚህ የተፈጥሮ ባህርያት ሙሉና ንጹሕ የሚሆኑት

---

[105] - ቼሩሊ ይህን ማስረጃ ያገኘው የሼኽ ሁሴንን ገድል ከሚገልጸው "ኑዛት አል- አስራር" ከተሰኘ የአረብኛ መዝገብ ነው፡፡ የአረብኛው መዝገብ ሙሉ ርዕስ "Kitab Nuzhat al-Asrar Wa-Taharat al-Awzar" የሚል ነው፡፡ ትርጉሙም፣ "የነፍስ ደስታና ከክፉ ስራ መንጻት" ማለት ነው፡፡ ይህ መዝገብ በካይሮ በ1928 መታተሙንም Cerulli (1971) ይገልጻል፡፡

በ3 ቀናት ውስጥ ነው። ለዚህም ነው መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ከመምጣታቸው ከ3 ቀናት በፊት ከአልኮል መጠጥ፣ ከወሲብና ከሌሎች ክልከላዎች የሚቆጠቡት። በባህላዊ የዳኝነት ስርዓትም ለምስክርነት የሚጠሩ ሰዎች ቁጥር 3 ነው። ምክንያቱም 3 የሙሉነት፣ የትክክለኛነትና የታማኝነት ተምሳሌት ነውና። ይህ በ3 ቁጥር ላይ ያለው እሳቤ በክርስትናም ሆነ በእስልምና ኃይማኖቶች ተመሳሳይ ነው።

በወቅቱ ሼኽ ሁሴን ለተማሪዎቻቸው እነዚህንና መሰል ስነምግባራዊ ሀሳቦች ለመግለጽና ለማስረጽ በምሳሌ ያስተምሩ ነበር። ከእነዚህ ምሳሌዎች መካከል የተወሰኑትን እንመልከት። ለሼኽ ሁሴን “4 ነገሮች፣ በ4 ነገሮች ይጠፋሉ”። እነሱም፤ ጨው ውኃ ውስጥ ሲገባ፣ አሳ ከውኃ ሲወጣ፣ ቅቤ እሳት ውስጥ ሲገባ እንዲሁም ኃጽያት የአላህ ይቅርታ ሲደረግበት ይጠፋል። በተመሳሳይም ለእሳቸው “4 ነገሮች፣ በ4 መንገዶች ይገኛሉ”። እነሱም፤ መልካምነት በማስተዋል፣ ዕውነት በፍቅር፣ ክብር በትዕግስት እንዲሁም ሰላም በመልካም አስተሳሰብ ይገኛሉ።

ሼኽ ሁሴን 4 ነገሮችን ማድረግ አስፈላጊ እንደሆኑ ያስተምራሉ። እነሱም፤ ያስቀየሙንን ይቅርታ ማድረግ፣ ለተቸገሩ እርዳታ መስጠት፣ ማዳመጥ ለሚፈልጉ መናገር እንዲሁም መጥፎ ለሆኑ ሰዎች መልካም መሆን ናቸው። ሼኽ ሁሴን “4 ነገሮች ኖሮት፣ 4 ነገሮች የሌለው ሰው በዚህች ዓለም ሕይወቱ የተበላሸና በመጨረሻው ዓለምም (አኬራ) የከሰረ ነው። እነሱም ከበርቴ ሆኖ ለድሆች ያላዘነ፣ ጤነኛ ሆኖ አምስት ጊዜ ሶላት ያልሰገደ፣ ዕውቀት (ዒልም) እያለው ለበጎ ምግባር ያላዋለው እና ያላመነ (ሙኒፊቅ) ብቻ እንጂ ያመነ (መዕሚን) ወዳጅ የሌለው ነው።” ብለው ያስተምሩ ነበር።

በእነዚህ የሼኽ ሁሴን አስተምህሮዎች 4 ቁጥር ተደጋግሞ ተገልጿል። 4 ቁጥር ፈጣሪ የፈጠራቸውን ቁሳዊ ፍጡሮች ይወክላል። 4 የመሬት (የምድር) ተምሳሌት ነው። በዚህም ምድር 4 ማዕዘን ባለው ቅርጽ (Squire) ትመሰላለች። ምድር በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ 4 አብይ አቅጣጫዎች ትከፈላለች። ገነትን የሚያጠጧት 4 ወንዞች ናቸው። የምድር ማዕዘናት 4 ናቸው። በምድር ላይ 4 ነፋሳት አሉ። በመሆኑም 4 ቁጥር የሁሉም ነገር ማንጸሪያ ነው። 4 ቁጥር የተፈጥሮ ምሉዕነት ማሳያ ነው። ለዚህም ይመስላል በሼኽ ሁሴን የተምሳሌት አስተምህሮዎች ውስጥ 4 ቁጥር በተደጋጋሚ የቀረበው።

ከላይ ከቀረቡት የሼኽ ሁሴን ስርዓት (ሁሴኒያ) አስተምህሮ የነፍስ ንጽሕናን፣ የእርስበርስ ፍቅርን፣ መረዳዳትን፣ እራስን ለፈጣሪ ማስገዛትን፣ አብዛኛውን ጊዜ በጸሎትና በጥሩ ምግባር ማሳለፍን፣ መሰወርን፣ እራስን መቻልና መሰል ስነ-መለኮታዊና ስነምግባራዊ ጉዳዮች የሚያስተምር ነው፡፡ ይህም በተወሰነ ደረጃ በወቅቱ በአካባቢው ተስፋፍቶ እንደነበር ከሚገመተው ከቃድሪያ ስርዓት ጋር በተወሰነ ደረጃ ይመሳሰላል፡፡ ከቃድሪያ ስርዓት በተጨማሪ በኢትዮጵያና በአጎራባች አገራት በተለያዩ ወቅቶች ከተስፋፉት የአህመዲያ፣ የሳሊሒያ (ራሺዲያ)፣ የሚርጋኒያ (ቻትሚያ)፣ የቲጃኒያና የሳማኒያ ስርዓቶች ተስፋፍተው ነበር (Trimingham, 1952፡ 242-247)፡፡

የሁሴንያ ስርዓት እነዚህ የእስልምና ስርዓቶች ካላቸው አስተምህሮ ጋር ያለው ዝምድና ወይም ልዩነት ምን እንደሆነ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት መኖር አለመኖሩ በግልጽ አይታወቅም፡፡ በመሆኑም የሁሴኒያ ስርዓት ከሌላው የተለየና የሼኽ ሁሴን የራሳቸው ፈጠራ ነው? ወይስ ከቃድሪያ ስርዓት የተወሰደ ነው? ወይም ከሌሎች ስርዓቶች የተወሰደ? እንዲሁም በአሁኑ ወቅት አለ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ጥልቅ ጥናት የሚጠይቅ ነው፡፡

## 5.3.4 የኦርቶዶክስ እና የፖፑላር እስልምና በአናጂና ቀበሴና አካባቢው

የኦርቶዶክስ እስልምና (Orthodox Islam) እና የፖፑላር እስልምና (Popular Islam) እምነቶች፣ አስተምህሮዎችና ድርጊቶች በተለያዩ የዓለም አገራት በሚገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚተገበሩ ናቸው፡፡ የእነዚህን እምነትና ድርጊት Gulevich (2004፡51) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡ የኦርቶዶክስ ኃይማኖት እምነቶችና ድርጊቶች በአብዛኛው በኃይማኖት መሪዎች፣ አስተማሪዎችና የስነመለኮት አጥኚዎች ድጋፍና ዕውቅና የተሰጣቸው ናቸው፡፡ የፖፑላር ኃይማኖት ደግሞ ከ"ሰፊው ሕዝብ" (Ordinary) ልብና አዕምሮ የሚመነጩ እምነቶችና ድርጊቶች ናቸው፡፡

በፖፑላር ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ከሚታመኑና ተግባራዊ ከሚደረጉ ድርጊቶች መካከል የቅዱሳን ወይም የነብያትን ዓመታዊ የውልደት (መውሊድ) እና የሕልፈት (ኡርስ) ቀናትን ማክበር፣ ኃይማኖታዊነታቸውን ሌላው እንዲያውቅ የተለያዩ ድርጊቶችን መፈጸም፣ የተለየ ልብስ መልበስ፣ ወደ ከፍተኛ ስሜት የሚያሻግሩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን (ሳማ) መከወንና ወደ ቅዱሳን መካነ ቅርሶች መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ የፖፑላር ኃይማኖት

ድርጊቶች አልፎአልፎ በኦርቶዶክስ ኃይማኖት ዘንድ ተቀባይነት ስለሌላቸው ወይም ተጻራሪ ስለሆኑ ተቃውሞ ይደርስባቸዋል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የፖፑላር እስልምና ኃይማኖት እምነቶችና ድርጊቶች ይከወናሉ፡፡ ከእነዚህ እምነቶችና ድርጊቶች መካከል የሚከተሉት በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በዓመት ሁለት ጊዜ የሙዳ በዓላትን ለማክበር መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ይሄዳሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦችም የሼኽ ሁሴንን መካነ መቃብር ይጎበኛሉ፡፡ በስፍራው የነብዩ መሐመድ የውልደት ቀን (መውሊድ)፣ የሼኽ ሁሴን የውልደት ቀን (ዛሕራ ገልገላ ጎበና) እና የአሹራ በዓላት በድምቀት ይከበራሉ፡፡ በስፍራው ወደ ከፍተኛ ስሜት የሚያሻግሩ የተለያዩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ይከወናሉ፡፡ አንዳንድ ግለሰቦች ካላቸው ኃይማኖታዊና ማህበራዊ ደረጃ አንጻር የተለዩ አልባሳትን ይለብሳሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ጉዞ መደረጉ፣ ሼኽ ሁሴን በአፍቃሪዎቻቸው ዘንድ ቅዱስ መሆናቸው፣ የእሳቸው መቃብር መጎብኘቱ፣ በስፍራው የተለያዩ ስርዓተከበራዎች መከወናቸው፣ በስርዓተከበራው ወቅትም መንፈሳዊ ሙዚቃዎች መከወናቸው፣ የአሹራ፣ የመውሊድ፣ የሐጅና የዛህራ ገልገላ ጎበና በዓላት መከበራቸው፣ ለረጅም ዓመታት መካነ ቅርሱ በኢማም የስልጣን ማዕረግ መመራቱ፣ የኪነሕንጻው አሰራር እንዲሁም የቃድሪያ ስርዓት በስፍራው መስፋፋቱ የሚያሳየው ዋና ነጥብ አለ፡፡ ይህ ዋና ነጥብም የሺዓት የእስልምና አስተምህሮ፣ የሱፊ ስርዓት፣ የኦርቶዶክስና የፖፑሊስት እስልምና ድርጊቶች በስፍራው ጠንካራ መሰረት እንዳላቸው ነው፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ የሱኒ የእስልምና አስተምህሮ የሆነው ሰለፊያ በአካባቢው ተስፋፍቷል፡፡ ይህም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የተለያዩ የእስልምና አስተምህሮዎች አሻራቸውን ያሳረፉበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ መሆኑም የአስተምህሮዎቹ ድርጊቶችን አነባብሮ የያዘና ያዋሐደ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ውሕደትም በአሁኑ ወቅት በሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎች ላይ ይንጸባረቃል፡፡

ውሕደት "ሁለትን ወይም ከዛ በላይ ባሉ ኃይማኖቶች መካከል ያለ የለውጥ ሂደት ነው፡፡" በሚል Braukämper (1992፡194-195) ሲበይነው፣ Rahaman (2016፡51) ደግሞ ውሕደት "ብዝሃ ባህሎች በአንድ ላይ በመገናኘት ጠንካራ የባህል ጥርቅም (Cultural amalgam) እና ሕብር (Harmony) ለመፍጠር የሚረዳ በጣም ጠቃሚ መደላድል ነው፡፡" በማለት ውሕደትን ካለው

ጠቀሜታ አንጻር ይበይነዋል። ከእነዚህ ብያኔዎችና ከላይ በቀረቡ መረጃዎች መሰረት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የተለያዩ የእስልምና አስተምህሮዎችና የሌሎች ኃይማኖቶች ተጽዕኖ ያረፈበት ነው። በስፍራውም የተለያዩ ብሔረሰቦችና የውጪ አገር ዜጎች ለአምልኮ ይመጣሉ። ይህ መሆኑ ስፍራው የውሕደት ባህርይ እንዲኖረውና ስፍራውም የባህል ጥርቅም እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል።

## 5.4 የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች የኢኮኖሚ መሰረት

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና አካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች የተለያየ የገቢ ምንጭ አላቸው። የተወሰኑት በከብት እርባታና በእርሻ የሚተዳደሩ ናቸው። የተወሰኑት ደግሞ በቋሚ ወይም ለበዓላት ወቅት ብቻ የንግድ ስራ በመስራት እንዲሁም ከቱሪዝም አገልግሎት በሚያገኙት ገቢ ይተዳደራሉ። የአብዛኛው ነዋሪ የገቢ ምንጭ የተመሰረተው በሙዳ በዓላት ወቅት በሚሰበሰብ ገንዘብና ወደ ቦታው የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በሚሰጡት ስጦታ ላይ ነው።

በመካነ ቅርሱና በአካባቢው የእርሻ ስራ ማከናወን አይቻልም። የእርሻ ስራም ክልክል ስለሆነ የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ከአካባቢው ራቅ ባሉ ቦታዎች የእርሻ ስራ ይሰራሉ። ለዚህም በዋናነት ሶስት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። እነሱም፤ አንደኛው፡- የአካባቢው አፈር ለም ባለመሆኑና የአየር ጸባዩም ሞቃታማ መሆን ነው። የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መገኛ ስፍራ ቆላማ የአየር ንብረት አለው። የአየር ጸባዩም ሞቃታማና ደረቃማ ነው። ከድሬ ሼኽ ሁሴን ጤና ጥበቃ ማዕከል የተገኘ ሪፖርት (2006 ዓ.ም.) እንደሚያመለክተው የአካባቢው የሙቀት መጠን ዝቅተኛው 14 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 37 ዲ.ሴ ነው። በሁሉም ወራት ያለው የሙቀት መጠን በእነዚህ ዲግሪ ሴንቲግሬዶች መካከል የሚገኝ ነው።

አካባቢው በአመት ከ2 እስከ 4 ወራት አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛል። የዝናብ ወቅቶቹም ክረምት (ነሐሴ ወር)፣ በልግ (መስከረም) እና ጸደይ (ሚያዝያ እና/ወይም ግንቦት) ናቸው። በእነዚህ ወራትም ቢሆን አካባቢው አነስተኛ የዝናብ መጠን የሚያገኝ ሲሆን፣ አማካኝ የዝናብ መጠኑ ከ50 ሚሊሜትር በታች ነው። በአመት ውስጥ ከ8 እስከ 10 ወራት ያህል ሞቃታማና ደረቃማ የአየር ጸባይ እንዳለው የጎሎልቻ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት አመታዊ ሪፖርት (2006 ዓ.ም) ያመለክታል።

ሁለተኛው፡- ሼኽ ሁሴን በአካባቢው ዛፍ እንዳይቆረጥና መሬት እንዳይታረስ አስተምረዋል የሚል ነው፡፡[106] ሶስተኛው፡- በነዋሪውና በምዕመናኑ መካከል ያለ የቃል ኪዳን ስምምነት ነው፡፡ ይህም ነዋሪው እዚህ የመጣው ቅርሱን ለመጠበቅ ነው፡፡ ሕዝቡ ወደ እርሻ ስራ ከተሰማራ ቅርሱን ላይንከባከብ ይችላል፡፡ በመሆኑም ምዕመናኑ "እናንተ ቅርሱን ጠብቁልን እኛ የእናንተን ቀለብ እንችላለን፡፡" የሚል የቃል ስምምነት አለ፡፡[107] በእነዚህ ምክንያቶች በአካባቢው የእርሻ ስራ የማይካሄድ በመሆኑ የተወሰኑ ነዋሪዎች ከአካባቢው ውጪ በሌሎች ቦታዎች ላይ የእርሻ ስራ ያከናውናሉ፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኝበት የአናጂና ቀበሌ የቦታ ግብር ለመንግስት አይከፈልበትም፡፡ ቦታው ላይ ግብር እንዳይከፈል የወሰኑት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ናቸው፡፡ በወቅቱ የመካነ ቅርሱ ኢማሞችና የአካባቢው ሽማግሌዎች ቦታው እንዳይገበርበት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቤቱታ ያቀረቡበትንና ያስፈቀዱበትን ሁኔታ መረጃ አቀባዬ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ቦታው የመንግስት ግብር እንዳይጣልበት በየደረጃው ላለ የመንግስት አካል ሲጠይቁ ሊፈቀድላቸው ስላልቻለ ኢማሞችና ሽማግሌዎች ተመርጠው ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ጋር ሄደው ይግባኝ አሉ፡፡ እሳቸውንም ‹እርስዎ ግብር እንዲያነሱልን ለመጠየቅ መጠናል፡፡ የመጣነውም በይግባኝ ነው፡፡› አሏቸው፡፡ እሳቸውም ‹መሬት ሁሉ የሚገበር በመሆኑ ትገብራላችሁ፡፡› ብለው መልስ ሰጡ፡፡ እነሱም ‹እርስዎ እምቢ ካሉ ይግባኝ እንጠይቃለን› አሉ፡፡ እሳቸውም ‹የዚህች አገር የመጨረሻው ውሳኔ ሰጪ እኔ ነኝ ለማን ነው ይግባኝ የምትሉት?› ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ እነሱም ‹ወደ አላህ፤ ለአላህ እንከስዎታለን› ሲሉ መልስ ሰጡ፡፡ ንጉሠ ነገስቱም በመልሳቸው በጣም ተደነቁ፡፡ ንጉሡም ፍቃደኛ በመሆናቸው ፍርዱን ኢማሞቹና ሽማግሌዎቹ በሚፈልጉት መንገድ ፈረዱላቸው፡፡*[108]

በዚህ ውሳኔ መሰረት ቦታው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ግብር አይከፈልበትም፡፡ ይህ የንጉሱ ውሳኔ በመንግስትና በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲመሰረት ምክንያት ሆኗል፡፡ በወቅቱም ለአቤቱታ በሄዱ ኢማሞችና የሀገር ሽማግሌዎች ግብዣ መሰረት ንጉሱ ቦታውን እንዲጎበኙ፣ ለአካባቢው ማህበረሰብ እርዳታ እንዲሰጡ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ እንዲሰራ፣ በሙዳ በዓላት ወቅት ቋሚ የአይሮፕላን ትራንስፖርት ከአዲስ አበባ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን የቀጥታ በረራ አገልግሎት እንዲሰጥ፣

---

[106] - ሼኽ ቃሲም ሀጂ አወል፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡
[107] - አቶ መሃመድ ሰኢድ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡
[108] - ሼኽ አህመድ ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 13 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ጥርጊያ የመኪና መንገድ ተሻሽሎ እንዲሰራና ንጉሱ ለመካነ ቅርሱ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።

## 5.5 የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች ያላቸው ማህበራዊ አደረጃጀት

የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች "ሰኪና" በሚል ስያሜ ይጠራሉ። ሰኪና የሚለው ስያሜ የነዋሪዎች ጥቅል መጠሪያ ሲሆን፣ በስሩም የተለያየ ማህበራዊ አደረጃጀት ያላቸው ነዋሪዎችን የያዘ ነው። ሰኪናዎች ካላቸው ማህበራዊ አደረጃጀት በአራት ይመደባሉ። እነሱም ደርጋ፣ ኡሌ፣ ገሪባና መናኝ ናቸው። የእነዚህን ማህበራዊ ደረጃ በተናጠል ቀጥለን እንመልከት።

### 5.5.1 ደርጋ

በድሬ ሼኽ ሁሴን በቋሚነት የሚኖሩ ሰዎች "ደርጋ" በሚል ስያሜ ይጠራሉ። ደርጋ የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን፣ ሶስት ትርጉም አለው (Østebo, 2005)። አንደኛው፤ የሱፊዎች መሰብሰቢያ ነው። ሁለተኛው፤ የሱፊ ስርዓተከበራ የሚካሄድበት ቦታ ነው። ሶስተኛው በሱፊ የእምነት ቦታ የሚኖሩ ነዋሪዎች ማለት ነው። አንድ ሰው ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መጥቶ በተከታታይ ለ6 ወራት ያህል ከቆየ ደርጋ ይሆናል። ነገር ግን ወደ ስፍራው የመጣ ሰው 6 ወር እስከሚሞው ድረስ እንደ እንግዳ እንጂ እንደ ደርጋ አይቆጠርም። በድሬ የሚኖሩ ደርጋዎች በሶስት ማህበራዊ አደረጃጀት ይከፈላሉ። የማህበራዊ አደረጃጀቱም በቤተሰብ የዘር ሃረግ ላይ የተመሰረተ ነው። ቤተሰቦቹም የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ ቤተሰብ፣ የሼኽ አባስ ሰኢድ አቡበከር ቤተሰብና የሰኪና ቤተሰብ በሚል ይጠራሉ።

በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ (በ1790ዎቹ) የሐረሩ ንጉስ አሚር አብዱል ሸኩር (1783-1794) ሼኽ መሃመድንና ሼኽ አባስን ወደ አናጂና እንደላኳቸው Ahmed (1997) እና Braukämper (2004) ይገልጻሉ። እነሱም በአሁኑ ወቅት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኙትን የተለያዩ ኪነሕንጻዎች በመገንባት ስፍራው ድጋሚ የእስልምና ኃይማኖት ማዕከል እንዲሆን አድርገዋል። ከሼኽ መሃመድና ከሼኽ አባስ ጋር በመሆን ኪነሕንጻዎቹን የገነቡ የአካባቢው ሰዎች አሉ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ሼኽ ያህያ ሰካ፣ ገኖ አደም አሎላ፣ ሱፋ ጎርፌ፣ ደንቦባ ቲይሴ፣ ሰካ ለቦ፣ አበሶ ኩሻ፣ ቢዱ ሳኢዶና አሎ አህመድ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን ያለው የደርጋዎች ማህበራዊ አደረጃጀት አንደኛው፣ የሼኽ መሃመድ ቤተሰብ ነው። ይህ ማህበራዊ አደረጃጀት የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ የዘር ሃረግ ያላቸውና

የእሳቸው ቤተሰብ የሆኑትን የሚገልጽ ነው፡፡ “ቲልማ ቲልሞ” የሚለው ስያሜ የሼኽ መሐመድ የቅጥያ ስም እንጂ የአባታቸው ስም አይደለም፡፡ ትርጉሙም የወተት ምንጭ እንደማለት ነው፡፡ የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ ታሪክ በትክክል አይታወቅም፡፡ የእሳቸውን ውልደት በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች አሉ፡፡ ከእነሱም መካከል Braukämper (2004:138) ሼኽ መሃመድ ውልደታቸው በርበራ (ሱማሊያ) ነው ይላል፡፡

Umer (2006:23) ደግሞ የእሳቸው ውልደት አርሲ መሆኑንና የዋዎ ጎሳ እንደሆኑ ገልጿል፡፡ Areba and *et al* (2013:2) ደግሞ አርሲ ዲድዓ በሚባል ቦታ ተወለዱ ይላሉ፡፡ የእኔ መረጃ ሰጪዎቼ ግን እነዚህን መረጃዎች አይቀበሏቸውም፡፡ መረጃ ሰጪዎቼ እሳቸው የአረብ ዘር ያላቸው ሲሆን የተወለዱትና ያደጉት ባሌ ዞን ጊንር ከተማ ሲሆን፣ እሳቸውም ለትምህርት ወደ ሐረር ሄደው ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ወደ ስፍራው እንደመጡ ይገልጻሉ፡፡[109]

ሼኽ መሃመድ ከሼኽ አባስ ጋር በመሆን ወደ ስፍራው መጥተው የሼኽ ሁሴንን፣ የመሃመድ ተማምን፣ የፋጡማን፣ የሼኽ ኢብራሂምን፣ የአዮ ሽምሲያ ገሞዎችና በስማቸው የተሰየመውን የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ መስኪድን ገንብተዋል፡፡ በወቅቱ የገሞዎቹን ዲዛይን የሰሩትና ግንባታውን በበላይነት ይቆጣጠሩ የነበሩት ሀዲስ የተባሉ የመናዊ የኪነህንጻ ባለሙያ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ሀዲስ በሐረሩ ንጉስ አሚር አብዱል ሽኩር ትዕዛዝ ወደ ስፍራው እንደመጡ ይነገራል፡፡ ሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ አምስት ልጆች አሏቸው፡፡ የእሳቸው አምስቱም ልጆች በተለያየ ዘርፍ በመካነ ቅርሱ ላይ ስልጣን ተሰጧቸዋል፡፡ የእሳቸው አምስት ልጆች ስምና የተሰጣቸው ስልጣን በእድሜ ቅደም ተከተል (ከታላቅ ወደ ታናሽ) መሰረት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1- ኢማም ሻፊ ………………. መካነ ቅርሱን የማስተዳደር ስልጣን፣
2- ሼኽ ቡሽራ ከሪም ………….. የኪነህንጻ ግንባታ፣ እድሳትና ጥበቃ ስልጣን፣
3- ሼኽ አብዱላሂ …………….. የፍትህ/ የፍርድ ስልጣን፣
4- ሼኽ አህመድ ………………… መንፈሳዊ ትምህርት የማስተማር ስልጣን፣
5- ሼኽ አቡሳኒ ………………….. መንፈሳዊ ትምህርት የማስተማር ስልጣን አላቸው፡፡

---

109 - አቶ ኑማን መሃመድ፣ አቶ አብዱልናስር አህመድ፣ አቶ መሃመድ መሃሙድና ሼኽ ከሪም አብዳ፣ አናጂና ቀበሌ፣ የካቲት 5 ቀን 2009 ዓ.ም፡፡

ከሼኽ አቡሳኒ በስተቀር የተቀሩት አራቱ የሼኽ መሃመድ ልጆች የሞቱትና አጽማቸው ያረፈው በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነው። ሼኽ አቡሳኒ ቁርዓን ለማስተማር ሐረር ተልከው እዛው አርፈዋል። አጽማቸው ያረፈውም በሐረር ነው። በሼኽ መሃመድ ልጆች ውሳኔና ስልጣን መሰረት የመካነ ቅርሱ ማንኛውም ድርጊቶች ይፈጸሙ ነበር። ለእነዚህ አምስት ልጆች የተሰጠው ስልጣን ከቤተሰብ ወደ ቤተሰብ በውርስ የሚተላለፍ ነው። በመሆኑም የኢማም ሻፊ ቤተሰቦች (የእሳቸው የዘር ሃረግ ያላቸው) መካነ ቅርሱን የማስተዳደር ስልጣን ሲኖራቸው፣ የሼኽ ቡሽራ ከሪም ቤተሰቦች ደግሞ ኪነህንጻዎችን የመገንባትና የማደስ ስልጣን አላቸው። ከእነዚህ ስልጣኖች መካከል ከፍተኛው ስልጣን መካነ ቅርሱን በሚመለከት ውሳኔ መስጠትና ማስተዳደር ነው።

የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች "ኢማም" የሚል የማዕረግ ስም ይሰጣቸዋል። የኢማምነት ስልጣን ከአባት ወደ ልጅ በሚተላለፍ ውርስ የሚገኝ ነው። አባት ከዚህ ዓለም በሕልፈት ሲለይ የኢማምነት ስልጣኑ ለልጅ ይተላለፋል። በዚህ ቤተሰባዊ ውርስ መሰረት የድሬ ሼኽ ሁሴንን መካነ ቅርስ በአስተዳዳሪነት የመሩ ኢማሞች የሚከተሉት እንደሆኑ Østebo (2014:7) ይገልጻል።

ሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ
(በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ኢማም የነበሩ)

↓

ሼኽ አብዱላሂ
(በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን አጋማሽ ኢማም የነበሩ)

↓

ሼኽ መሃመድ ሳፊ
(አጼ ምኒልክ ባሌን ከማስገበራቸው በፊት ኢማም የነበሩ

↓

ኢማም አብዱል ቃድር
(አጼ ምኒልክ ባሌን ባስገበሩበት (1892) ወቅት ኢማም የነበሩ)

↓

ኢማም መሃመድ ሰኢድ
(በጣሊያን ወረራ (1935-1942) ወቅት ኢማም የነበሩ)

↓

ኢማም መሃሙድ
(ከጣሊያን ወረራ በኋላ ኢማም የነበሩና በ1977 ወደ ሱማሊያ የተሰደዱ)

ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፈው ቤተሰባዊ የኢማምነት ስልጣን ውርስ እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት ድረስ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ የደርግ መንግስት የአገሪቷን ስልጣን በተቆጣጠረበት ወቅት የመካነ ቅርሱ የኢማምነት የስልጣን ውርርስ ሙሉለሙሉ ተቋረጠ፡፡ ለዚህም በታሪክ የባሌ ገበሬዎች አመጽ በሚል ስያሜ የሚታወቀው ወታደራዊ የአመጽ እንቅስቃሴ በዋና ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡ በ1956 ዓ.ም የተጀመረው የባሌ ገበሬዎች አመጽ የደርግ መንግስት ስልጣን ላይ በወጣበት ወቅትም እንደቀጠለ ነበር፡፡ በወቅቱም የባሌ ገበሬዎች አመጽ መሪዎች በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በአካባቢው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር፡፡ በአመጹ ወቅት መካነ ቅርሱን ያስተዳድሩ የነበሩት ኢማም መሃሙድ መሃመድ ሰኢድ ነበሩ፡፡

ኢማሙም የሕዝቡን አመጽ ይደግፉ እንደነበር ይነገራል፡፡ በወቅቱም የደርግ መንግስት ጦርነቱን አሸንፎ አካባቢውን በቁጥጥር ስር ማዋል ቻለ፡፡ ኢማም መሃሙድም በ1969 ዓ.ም

በስደት ወደ ሱማሊያ ሄዱ። ኢማሙ ሱማሊያ በመግባታቸው መካነ ቅርሱ ያለ ኢማም እንዳይቀር በሚል ኢማም ሙዲን ስልጣኑን ያዙ።

የኢማሙን ስደት ምክንያት በማድረግ የደርግ መንግስት በመካነ ቅርሱ ለረጅም አመት ሲተገበር የነበረውን ቤተሰባዊ የስልጣን ውርርስ እንዲቋረጥ አደረገ። በመንግስት ውሳኔም ከአናጂና ቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በሕዝበ ውሳኔ መካነ ቅርሱን የሚቆጣጠሩ ግለሰቦች እንዲመረጡና መካነ ቅርሱም በነዋሪዎችና በመንግስት መዋቅራዊ አደረጃጀት በቀበሌና በገበሬ ማህበራት የበላይ ውሳኔ ሰጪነት እንዲተዳደር ተደረገ። ከኢማም መሃሙድ በመቀጠል ኢማም ሙዲን ለተወሰነ ጊዜ የኢማምነት ስልጣኑን ቢይዙም ድርጊቱ ሕገወጥና የሕዝብን ውሳኔ ያላከበረ ነው በሚል የመንግስት ውሳኔ የአስተዳደር ስልጣናቸውን ለቀቁ። በዚህም ምክንያት ለ200 ዓመት ያህል የቆየው የኢማምነት ስልጣን ሙሉለሙሉ ተቋረጠ። በአሁኑ ወቅትም የኢማምነት የአስተዳደር ስርዓት የለም።

ሁለተኛው የደርጋዎች ማህበራዊ አደረጃጀት የሼኽ አባስ ሰኢድ አቡበከር ቤተሰብ ነው። የሼኽ አባስ ቤተሰቦች የሚባሉት የእሳቸው የዘር ሀረግ ያላቸው ናቸው። የሼኽ አባስን ታሪክ በተመለከተ ሁለት መረጃዎች አሉ። አንደኛው፣ ከአርሲ ዞን እንደመጡ የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከይፋት የመጡ የአርጎባ ብሔር ተወላጅ ናቸው የሚል ነው። ሼኽ አባስ ለመንፈሳዊ ትምህርት ወደ ሐረር የሄዱና ከሼኽ መሃመድ ጋር አብረው ከሐረር ወደ አናጂና የመጡ ናቸው። እሳቸውም ትምህርታቸውን ጨረሰው ወደ ድሬ በመምጣት ቁርዓን አስቀርተዋል። አሁን ድረስ በስማቸው የሚጠራና እሳቸው ያስገነቡት መስኪድ በመካነ ቅርሱ ይገኛል። በመካነ ቅርሱም እሳቸው አዘውትረው ይቀመጡበት እንደነበር የሚነገርና በእሳቸው ስም የተሰየመ 'የሐጂ አባስ መቀመጫ' የሚባል ቦታ አለ። በአሁኑ ወቅት ይህ ስፍራ ከዚህ ስያሜው በተጨማሪ 'አውቶቢስ ማዞሪያ' እና 'አደባባይ' በሚሉ ስያሜዎችም ይጠራል።

ሶስተኛው የደርጋዎች ማህበራዊ አደረጃጀት የሰኪና ቤተሰብ ነው። የሰኪና ቤተሰብ የሚባሉት ከሼኽ መሃመድና ከሼኽ አባስ የዘር ሃረግ ውጪ ያሉት የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። ሰኪና በሚል ስያሜ የሚጠሩት ቤተሰቦች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አናጂና በመምጣት እዛው መኖር የጀመሩትን ነው። ሰኪናዎች የሀይማኖት በዓላትን ለማክበር፣ ስፍራውን ለኑሮ በመምረጥ፣ ለቁርዓን ትምህርት፣ ለቁርዓን ትምህርት አስተማሪነት፣ በቤት ሰራተኝነት ለመቀጠር፣ የንግድ ስራ ለመስራት ወይም በመንግስት ስራ (ትምህርት ቤት፣ ጤና ተቋም ወዘተ.) ተቀጥሮ ለመስራት ወደ ስፍራው በመምጣት የሚኖሩ ናቸው።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በደርግ ዘመን በኢማም ማዕረግ መመራት ተቋርጦ በቀበሌ አስተዳደርና በሕዝብ መመራት ጀመረ፡፡ በዚህ ወቅት በሕዝብ በመመረጥ የአስተዳደር ስልጣኑን የተረከቡት የሼኽ አባስ ቤተሰቦችና ሰኪናዎች ናቸው፡፡ የኢማም መሪነትን በመተካት ማስተዳደር የጀመሩት ሼኽ ዑመር ሼኽ አልይና ሼኽ ከዲር ሀጂ ናቸው፡፡ ሼኽ ዑመር ሼኽ አልይ በ2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የእሳቸውን ስልጣን ልጃቸው ሼኽ ፈይሰል ሼኽ ዑመር ተረክበዋል፡፡

ከደርግ መንግስት ውድቀት በኋላም መካነ ቅርሱ የሚተዳደረው በነዋሪው ሕዝብና በመንግስት የአስተዳደር አካላት ነው፡፡ ውሳኔዎች የሚወሰኑት ከቀበሌ አመራር አካላትና ከሕዝብ ጋር በጋራ በመወያየት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የመካነ ቅርሱን የማስተዳደር ስልጣን የያዙት ሼኽ ፈይሰል ሼኽ ዑመርና ሼኽ ከዲር ሀጂ ናቸው፡፡ ሼኽ ፈይሰል ሼኽ ዑመር ያላቸው ስልጣንም በከራ አካባቢ የሚካሄደውን የሼኽ ዑመርን ሀድራ መምራት ነው፡፡ ሼኽ ከዲር ሀጂ ደግሞ በከራው ላይ የሚከወኑ የሙዳ በዓላትን የመምራት ስልጣን አላቸው፡፡[110] በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ የኢማምነት ስልጣን የለም፡፡ የኢማምነት ስልጣን ያለው በመስኪድ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በመስኪድ ውስጥ የሚካሄዱ ስርዓቶችን የሚመሩ ሰዎች የኢማምነት ማዕረግ አላቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት በተለምዶ አይሮፕላን ማረፊያ በሚባለው ቦታ የአረፋ በዓል ዕለት ጠዋት የሚካሄደውንና በዙቅጡም መስኪድ አርብ ዕለት የሚካሄደውን የጁምዓ ስግደት የሚያሰግዱት ኢማም ሼኽ አብዱልቃድር ሼኽ መሃመድ ሳፊ ናቸው፡፡ እሳቸው የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ መስኪድ ኢማም ናቸው፡፡ ከእሳቸው በታች የሆኑና የተለያዩ መስኪዶችን የሚመሩ ሌሎች ኢማሞች አሉ፡፡

ይህ አይነት በዘር የሚተላለፍ የኢማምነት ስልጣን ለ200 ዓመታት ያህል በድሬ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በቅዱስና በታላላቅ ኢማሞች አማካኝነት የተመሰረቱና በእነዚህ ግለሰቦች የመቃብር ስፍራን መሰረት አድርገው በአገራችን ውስጥ ከተመሰረቱ መሰል ኒክሮፖሊስ መንደሮች መካከል ድሬ አንዱ ነው፡፡ ይህ የኢማምነት የስልጣን ሚና በሺዓት የእስልምና አስተምህሮ የተለመደና ዋና የስርዓቱ ትግበራ መሰረት ነው፡፡ በሺዓቶች ዘንድ ቅዱሳንና ኢማሞች የሰው ልጅን ከአምላክ ጋራ የሚያማልዱ እንደሆኑ ይታመናል (Momen, 1985፣116)፡፡ በዓለማችንም እንደ ናጃፍ፣ ካርባላ፣ ካዛሚና፣ ሳመራ፣ ማሻድና ቆም የተሰኙ የሺዓት ቅዱስ ማዕከላት

[110] - በከራው ላይ የሚካሄዱ ስርዓተከበራዎችን በምዕራፍ 8 ተብራርተዋል፡፡

በኢማሞችና በቤተሰባቸው አማካኝነት የተቋቋሙና በኢማሞች የቀጥታ የዘር ሐረግ የሚመሩ ናቸው።

የመካነ ቅርሱ ደርጋዎች (ነዋሪዎች) በእነዚህ ሶስት ማህበራዊ አደረጃጀቶች መሰረት ለቅርሱ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋሉ። ባላቸው ማህበራዊ ደረጃም የተለያዩ ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን ይመራሉ። ለሙዳ በዓላት የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦችን ያስተናግዳሉ። በመካነ ቅርሱ በሚኖሩ ደርጋዎች መካከል ቤተሰባዊነትን መሰረት ያደረገ ማህበራዊ አደረጃጀቶች ቢኖሩም እርስበርስ ያላቸው ቅርርብ ከፍተኛ ነው። የመካነ ቅርሱ ደርጋዎች እርስበርስ ቅርርብ ቢኖራቸውም "የኢማምነት ስልጣን ይመለስልን" የሚል ጥያቄ በሚያነሱት የሼኽ መሃመድ ቤተሰቦችና የኢማምነት ስልጣንን መመለስ በሚቃወሙ የሼኽ አባስ ቤተሰቦችና ሰኪናዎች መካከል አልፎአልፎ አለመግባባት ይከሰታል።

በ1999 ዓ.ም በሼኽ መሃመድና በሼኽ አባስ ቤተሰቦች መካከል የተነሳው አለመግባባት ወደ ግጭት አምርቶ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ። የግጭቱ ምክንያትም የሼኽ መሃመድ ቤተሰብ የሆኑት ኢማም ሙህይ አል-ዲን የመካነ ቅርሱ ኢማም ይሁኑ የሚል ነበር። ኢማም ሙህይ በ2005 የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ኢማም እንዲሆኑ የፌዴራል መንግስት ባለስልጣናት መፍቀዳቸውንና ኢማምነቱን እንዲረከቡ ደብዳቤ እንደተሰጣቸው Østebo (2014:1) ይገልጻል።

ይህ የስልጣን ይገባኛል ግጭት ሼኽ መሃመድና ሼኽ አባስ ወደ ስፍራው በመጡበት ወቅት እርስበርስ ካለመግባባት የተጀመረ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ።[111] በሁለቱ መካከል በተፈጠረው ግጭት ሼኽ መሃመድ አሸናፊ ሆነው ስልጣኑን መያዛቸው ይነገራል። በሁለቱ መካከል አለመግባባት ቢኖርም የእስልምናን ሀይማኖት በአካባቢው በማስፋፋትና ስፍራው የመንፈሳዊ ጉዞ ማዕከል እንዲሆን ተጋግዘው ይሰሩ እንደነበር መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ።[112]

## 5.5.2 ኡሌ

በመካነ ቅርሱ የሚከወኑ የተለያዩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን የሚከውኑ ባለሙያዎች 'ኡሌ' በሚል የማዕረግ ስም ይጠራሉ። መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን የሚያቀርቡ ኡሌዎች ይህንን ሙያ የሚለምዱበት መንገድ ይለያያል። የተወሰኑት ቀደም ሲል ከሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች

---

111 - የመረጃ ሰጪዎቹ ስም እንዳይገለጽ ስለተስማማን፣ ስማቸውን አልገለጽኩም።

112 - የመረጃ ሰጪዎቹ ስም እንዳይገለጽ ስለተስማማን፣ ስማቸውን አልገለጽኩም።

ግጥሞችን በመስማት፣ የድምጽ አወጣጡን (ዜማውን) በመልመድ፣ ቅኝቱን በመለማመድና አብዛኛዎቹ ሼኽ ሁሴን ለኡሌነት ሲመርጧቸውና በኡሌነት እንዲያገለግሉ ሲያስገድዷቸው እንደሆነ ይታመናል፡፡[113]

በመካነ ቅርሱ ታዋቂ ከሆኑ ኡሌዎች መካከል ኡሌ መሃመድ አሊይ እንዴት የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃን እንደተማሩ ሲገልፁ "እኔ ድሮ በትምህርቴ በጣም ጎበዝ ተማሪ ነበርኩኝ፡፡ ድምጼ በጣም ጥሩ ስለነበርም ትምህርቴን ስጨርስ ዘፋኝ መሆን እፈልግ ነበር፡፡ ባሮ እንድል ያደረጉኝ ሼኽ ሁሴን ናቸው፡፡ በዚህ ድምጽህ አገልግል ያሉኝ፤ እንጂ የእኔ ፍላጎት አልነበረም፡፡ ባሮ ስልም ግጥሙን ከየት እንደማመጣው አላውቅም፡፡"በማለት ነው፡፡[114]

መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን የሚከውኑ ግለሰቦች ችሎታውን ከመለኮታዊ ኃይል እንደተሰጣቸው ማመናቸው በተለያዩ ኃይማኖቶች አስተምህሮ የተለመደ ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አስተምህሮ ቅዱስ ያሬድ የግዕዝ፣ የዕዝልና የአራራይ ጸዋትወ ዜማዎችን እግዚአብሔር በሶስት ወፎች አማካኝነት እንደነገረው ይታመናል፡፡ በተመሳሳይም ታዋቂው ሮማዊ ፖፕ ግሪጎሪ ዜማን ከወፍ እንደሰማ ይነገራል፡፡

Finnegan (1977:188-201) በተለያዩ አገራት የሚገኙ የቃል ግጥም (Oral poetry) ከዋኞችን በማጥናት ሶስት አይነት ከዋኞች እንዳሉ ትገልጻለች፡፡ እነዚህ ሶስት የቃል ግጥም ከዋኞች ቋሚ ባለሙያዎች(Specialists)፣ ተዘዋዋሪ ባለሙያዎች (Free-lancer) እና ወቅታዊያን (Occasionalist) ናቸው፡፡ እነዚህን ሶስት የከዋኝ አይነቶች ያላቸውን ባህርያት በማቅረብ ግልጽ በሆነ መስፈርት መለየት እንደማንችል Finnegan (1977) ትገልጻለች፡፡ ሶስቱን የከዋኝ አይነቶች በግልጽ መለየት ባይቻልም፣ ኡሌዎች ካላቸው ባህርያት አንጻር በተወሰነ ደረጃ ከቋሚ ባለሙያዎች ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡ ቋሚ ባለሙያዎች ያላቸውን ባህርይ Finnegan (1977) እንደሚከተለው ገልጻለች፡፡

> ቋሚ ባለሙያዎች ከፍተኛ የክወና ችሎታ ያላቸውና በማህበረሰቡ ውስጥ በታወቀና በተከበረ ሀይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ ተቋም በመግባት ደረጃውን የጠበቀ መደበኛ ስልጠና የተከታተሉ ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣንና ክበሬታ አላቸው፡፡ ቋሚ ባለሙያዎች ሀይማኖታዊ ወይም መንግስታዊ ተቋማትን በመደገፍ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በእነዚህ ተቋማት ውስጥም የራሳቸው ስልጣንና ደረጃ ያላቸው ሲሆን፣ በሚያቀርቡትም ጥበብ የተለያዩ ሽልማቶችን የሚያገኙና ቋሚ ተቀጣሪ

[113] - ሼኽ ቃሲም ሐጂ አወል፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7፣ ቀን 2007 ዓ.ም፡፡
[114] - ኡሌ መሐመድ አልይ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 27 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ከዋኞች የሚያቀርቡት ክወና ሀይማኖታዊ ከሆነ በአብዛኛው ያላቸው የክወና ክህሎት ከመለኮት የተሰጣቸው ጸጋ እንደሆነ ስለሚታመን በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነትና ማህበራዊ ደረጃቸው ከፍተኛ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡

የመንፈሳዊ ሙዚቃ አቅራቢዎች (ኡሌዎች) ከቋሚ ባለሙያዎች የቃል ግጥም ምደባ ውስጥ ሊያስመድባቸው የሚችሉ ባህርያት አሏቸው፡፡ ከእነዚህ ባህርያት መካከል ከፍተኛ የክወና ችሎታ ያላቸው መሆኑ፣ ሀይማኖታዊ ተቋማትን የሚያገለግሉ መሆኑ፣ በሚያቀርቡት ጥበብ የተለያዩ ሽልማቶችን የሚያገኙ መሆኑ፣ የክወና ክህሎታቸው ከመለኮት የተሰጣቸው ጸጋ እንደሆነ መታመኑ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነትና ማህበራዊ ደረጃቸው ከፍተኛ መሆኑ ናቸው፡፡

ኡሌዎች የቋሚ ባለሙያ ባህርያት ቢኖራቸውም በእነዚህ የከዋኝ ዘርፎች ሙሉለሙሉ እንዳይመደቡ የተወሰኑ ባህርያትን አያሟሉም፡፡ ከእነዚህ ባህርያት መካከል ደረጃውን የጠበቀ መደበኛ ስልጠና የተከታተሉ አለመሆናቸው፣ የራሳቸው ማህበራዊ ስልጣን የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም ቋሚ ተቀጣሪ አለመሆናቸው ናቸው፡፡ ኡሌዎች በራሳቸው ጥረት፣ ፍላጎት ወይም በመንፈሳዊ ኃይል አስገዳጅነት ክወናቸውን ያቀርባሉ እንጂ ስለክወናው የሚያገኙት ስልጠና ሆነ የሚማሩበት መደበኛ የማስልጠኛ ተቋም የለም፡፡ ኡሌዎች በመለኮት በተሰጣቸው ጸጋ አማካኝነት ጥበቡን መከወናቸው ይታመናል፡፡ በመሆኑም ኡሌዎች ከእነዚህ ሶስት የአፍሪካ የቃል ግጥም ከዋኞች ምደባ የተለየ ባህርይ ያላቸው ናቸው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከወኑትን መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ለመከወንና የኡሌነት ማዕረግ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ከሚፈጽማቸው የተለያዩ ስርዓቶችና ቅደምተከተሎች አሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶችና ቅደምተከተሎች በመካነ ቅርሱ ለሚሰጡ የኡሌነት ማዕረግ አሰጣጥ ቋሚ መስፈርትና ሂደቶች ናቸው፡፡ የኡሌነት ማዕረግ አሰጣጥ ሂደትም የሚከተለው ነው፡፡

አንድ ሰው ኡሌ መሆን ከፈለገ፣ ኡሌ መሆን እንደሚፈልግ ቀደም ብሎ ለሙዳ በዓላት አስተባባሪዎችና ለአገር ሽማግሌዎች ይገልጻል፡፡ እነሱም የአንድ ወይም የሁለት ቀን ቀጠሮ ይሰጡታል፡፡ በቀጠሮው ቀንም በአንድ ላይ ተሰባስበው ክወናውን እንዲያቀርብ ያደርጋሉ፡፡ ክወናውን ሲያቀርብ የሼኽ ሁሴንን ታሪክና ገድል በትክክለኛ ግጥም ከገለጸና የድምፁ ኃይልና የዜማ አወጣጡ ጥሩ ከሆነ የአገልግሎት ዘመኑ እንዲረዝም፤ መልካም ዕድል እንዲገጥመው

ይመርቁታል። ነገር ግን የግጥሙ ይዘት፣ ቅኝቱና ድምጹ ጥሩ ካልሆነ በሌላ ጊዜ እንዲመለስና ድጋሚ እንዲታይ ያደርጋሉ።[115]

በአገር ሽማግሌዎችና በበዓላቱ አስተባባሪዎች ክወናውን እንዲያቀርብ የተመረጠ ሰው ረጅም ቁመትና መካከለኛ ውፍረት ያለው የ"ደንቄ" (Dhanqee) በትር ይሰጠዋል። ደንቄ የሼኽ ሁሴን ወዳጅ የሆኑ ሰዎች የሚይዙት በትር ሲሆን፣ አናቱ ላይ የባላ ቅርጽ ("Y") አለው። የደንቄ በትር በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል። ስያሜዎቹም 'የሼኽ ሁሴን ባላ'፣ 'የሼኽ ሁሴን ዱላ'፣ 'ባላ ባልቾ' እና 'ኡሌ ሼኽ ሁሴን' ናቸው። የደንቄ በትር የተሰጠው ከዋኝ በስድስተኛው ወር በሚከበረው የሙዳ በዓል ወቅት ሲመጣ፣ ከአገር ሽማግሌዎች መካከል ለአንደኛው የሚችለውን አንድ ነገር (ጫማ፣ ጃኬት፣ ሸርጥ፣ ሸሚዝ፣ ጀለብያ ወይም ሌላ ጥሩ ነገር) ስጦታ ይዞ ይመጣል። ስጦታውንም ይሰጣል። ይመረቃል፤ ፀሎት ይደረግለታል።[116]

ስጦታ ይዞ በመጣበት ወቅት ክወናውን ለማቅረብ በዋሬ ስርዓቱ ላይ ይገኛል። ዋሬ ስብሰባ ማለት ነው። ዋሬ የሚለው ቃል በመካነ ቅርሱ በርካታ ሰዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው የሚፈጽሙት ስርዓተከበራንና ስርዓተከበራው የሚፈጸምበትን ቦታ ይገልጻል። በዋሬው ላይ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን የሚመራው የፕሮግራም አስተባባሪ ለተሰበሰበው ሕዝብ ስሙንና መንፈሳዊ ሙዚቃ ሊያቀርብ እንደሚፈልግ ገልጾ፣ ክወናውን ሕዝብ ፊት እንዲያቀርብ ይጋብዘዋል። ሰውየውም ክወናውን ማቅረብ ይጀምራል።

ክወናውን የሚያቀርበው ሰው የኡሌነት ማዕረግ የሚሰጠው በዋሬ ላይ የተሰበሰበው ሕዝብ ነው። ሰውዬው ሕዝብ ፊት ክዋኔውን ሲያቀርብ፣ ሕዝቡ ግጥሙን፣ ድምጹን፣ ዜማውን በትክክል አቅርቧል ብሎ ካመነ ሽልማት ይሰጠዋል። ክወናውን አቅርቦ ሲጨርስ ይመረቃል፤ ይቀጥል ብለው ያሳልፉታል። ሕዝቡ ሲያጸድቅለት ከስድስት ወራት በፊት የተሰጠው የደንቄ በትር በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት እዛው ሕዝቡ ፊት ይሰጠዋል። ደንቄው የችሎታው ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ነው። ከዚህ በኋላ ሰውየው የኡሌነት ማዕረግ ያለው፤ በበዓላት ወቅት ዋሬ ላይ መንፈሳዊ ሙዚቃ እንዲከውን የተፈቀደለት ይሆናል።

ሰውየው ክወናውን ሲያቀርብ በግጥሙ፣ በድምጹ ወይም በዜማው ላይ ስህተት ከተገኘ ወይም ለኡሌነት አይበቃም ብሎ ሕዝቡ ካመነ ክወናውን ያስቆመዋል። ሕዝቡ ሰውየው ለክወናው ብቁ

---

115 -ሼኽ አሕመድ ሼኽ ኤልያስ፣ ነሐሴ 30 ቀን፣ 2009 ዓ.ም።

116 -ሼኽ ቃሲም ሐጂ አወል፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7፣ ቀን 2007 ዓ.ም።

ካልሆነ ሕዝቡ በጩኸት፣ በጭብጨባ ወይም አቁም በሚል ትዕዛዝ ያስቆሙታል። በዚህን ጊዜ ሰውየው ለሌላ ጊዜ ተጨማሪ እድል እንዲሰጠው ጠይቆ፣ ክወናውን ያቆማል። ለመንፈሳዊ ሙዚቃ ከዋኞች የሚሰጠውን የኡሌነት ማዕረግ ሕዝቡ የሚሰጠው በመሆኑ የተለየ ባህርይ አለው። ለኡሌዎች የደንቄ በትር የሚሰጥበት ሁለት ምክንያት አለው። አንደኛው፣ ኡሌ መሆናቸው በሕዝብ ፊት መረጋገጡን የሚገልጽ የምስክር ማስረጃ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና ሲያቀርቡ ደንቄውን በእጃቸው በመያዝና ወዲያና ወዲህ በማወዛወዝ ስለሚከውኑ ነው።

Bauman (1975፡11) የክወናን ጽንሰሃሳብ ሲያስረዳ፣ ክወና የተጠያቂነት (Accountability)፣ የውድድር (Competence) እና የግምገማ (Evaluation) ሂደቶችን ይዞ የሚገኝ እንደሆነ ይገልጻል። በዚህ ሀሳብ ክወና፣ ከዋኝንና ታዳሚን ፊት ለፊት የሚያገናኝ ነው። በክወናው ላይ ከዋኝና ታዳሚ የራሳቸው ሚና አላቸው። ከዋኙ በዕውቀትና በችሎታ በመታገዝ የሚያቀርበውን ክወና ባህሉ በሚፈቅደው መንገድ ለታዳሚው ተጠያቂነት ባለው አኳኋን ማቅረብ አለበት። አቀራረቡም ተግባቦታዊ ውደድር (Communicative competence) ያለው መሆን አለበት። ታዳሚው የሚያሳየው ባህርይ ወይም የሚከውነው ድርጊት የከዋኙን ክህሎት፣ አቅምና ውጤታማነት የሚወስን ነው። አስተያየቱም ከዋኙን የሚገመግም ነው። በመሆኑም Bauman (1975) እንደሚለው ታዳሚው ለከዋኙ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሰጪ ነው።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም ኡሌዎች የሚያቀርቡትን ክወና ሕዝብ ፊት በማቅረብ ይገመገማሉ። ሕዝቡም ለክወናው ዳኛና ፈራጅ  በመሆን የራሱን ውጤት ይሰጣል። ክወናው ባህሉን መሰረት ያላደረገ፣ ክህሎትና ዕውቀት የጎደለው ከሆነ ክወናውን በተቃውሞ ያስቆመዋል። ክወናው ትክክል ከሆነ በድጋፍ እንዲቀጥል በማድረግ ያጸድቅለታል። የሕዝብ ማጽደቅ ለከዋኙ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት ነው።

የኡሌነት ማዕረግ ማግኘት የሚችሉት ወንዶች ብቻ ናቸው። ሴቶች መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን አይከውኑም። ማዕረጉም የሚሰጣቸው ሰዎች ከወጣት እስከ ሽምግልና የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአሁኑ ወቅት ታዋቂ የሆኑ በርካታ ኡሌዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል ሀሰን ሙሳ፣ ኢብራሂም፣ ሲታ፣ መሃመድ አልይ፣ አደም፣ ነጋሽ፣ አሚን፣ ጀማል ሰሃባ፣ ሙሽመም፣ ሱሲና ሙስጠፋ በዋናነት ይጠቀሳሉ። በንጉስ ኃይለሥላሴ ዘመን ሱልጣን ጎሎልቻ እንዲሁም በደርግ ዘመን ከዲር ወሌንሶ የተባሉ ኡሌዎች በጣም ታዋቂ

ነበሩ፡፡ ማንኛውም ሰው ችሎታ ካለው የኡሌነት ማዕረግ ይሰጠዋል፡፡ ማዕረጉ በጎሳና በአካባቢ የተለየ ባይሆንም፣ የመንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና የሚያቀርቡ ኡሌዎች በአብዛኛው የአርሲና የባሌ ተወላጆች ናቸው፡፡ ከአርሲ ተወላጆች መካከል የአርሲ ዲድዓ አካባቢ ተወላጆች ቁጥር ይበዛል፡፡

### 5.5.3 ገሪባ

ገሪባ ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች በተለይ ከጅማ፣ ከአርሲ፣ ከባሌና ከኢሉአባቦራ የሚመጡ ናቸው፡፡ "ገሪባ" የሚለው ቃል "ገሪብ" ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም እንግዳ ማለት ነው (Jeylan, 2005፡30)፡፡ በተመሳሳይም Østebo (2015፡94) "ገሪባ" የሚለው የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም እንግዳ ነገር ወይም ከአንድ ውስን ቦታ የመጣ (Something peculiar or Strange) ማለት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ገሪባነት በሱፊ የእስልምና ፍልስፍናዊ እሳቤ ለዚህ ዓለም እንግዳነትን የሚገልጹበት ነው፡፡

በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም ገሪባዎች እራሳቸውን "የሼኽ ሁሴን እንግዳ ነኝ፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ገሪባዎች የሙዳ በዓል ከመድረሱ ከ3 ወይም ከ4 ወራት ቀደም ብለው ከሚኖሩበት አካባቢ በቡድን በቡድን በመሆን ወደ አናጂና ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ እነሱ በሚያልፉባቸው ቦታዎችም ምግብ፣ መጠጥና ማደሪያ እየለመኑ በእግር ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴንም ከደረሱ በኋላ ለወራት እዛው ይቆያሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን ገሪባዎች ወደ ስፍራው ሲመጡ የሚያርፉበት የተለየ ስፍራ አላቸው፡፡ ስፍራውም ጎምቢሶ አዮ ሀደ ገራዶ በሚል ስያሜ ይታወቃል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ውስጥ 5 ጎምቢሶዎች አሉ፡፡ ጎምቢሶ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም 'ማረፊያ' ማለት ነው፡፡ ጎምቢሶ የሙዳ በዓልን ለማክበር ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሰዎች የሚያርፉበት ሰፊ አዳራሽ ነው፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ጎምቢሶዎች፣ አቅዲ ሰላታ፣ አዮ ሀደ ገራዶ፣ ከራ፣ ሼኽ ቡሽራና ሼኽ አባስ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጎምቢሶዎች መካከል ጎምቢሶ ከራ ለበዓል ለሚመጡ ሰዎች ማረፊያነት ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ የአካባቢው ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ አስክሬኑ ከመቀበሩ በፊት የሚያርፍበት ነው፡፡



*ፎቶ 14፡- የጎምቢሶ አዮ ሀደ ገራዶ ከፊል ገጽታ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

ከእነዚህ ጎምቢሶዎች መካከል ረጅም እድሜ ያለው ጎምቢሶ አዮ ሀደ ገራዶ ነው፡፡ ይህ ጎምቢሶ ‹‹ቦቆሌ›› በሚል ስያሜም ይታወቃል፡፡ አዮ ሀደ ገራዶ የ211 አመት እድሜ እንዳለው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፡3) ይገልጻል፡፡ ይህ ጎምቢሶ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ ጎምቢሶዎች መካከል በስፋቱና በርዝመቱ ትልቁ ሲሆን፣ 52 ሜትር ርዝመትና 2 ሜትር ስፋት አለው (Hailemelekot and Mulugeta, 2015:28)፡፡ ጎምቢሶው ከፊት ለፊት ክፍት ሲሆን፣ 21 ትልልቅ የድንጋይ ምሰሶዎችና 18 በሮች አሉት፡፡ ጎምቢሶው በግምብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ላይ በሼኽ መሃመድና በሼኽ አባስ እንደተገነባ ይነገራል፡፡

የገሪባዎች አለባበስና የጸጉር አሰራር የተለየ በመሆኑ ከሌላው የአካባቢው ነዋሪ በቀላሉ ይለያሉ፡፡ አለባበሳቸውም አሮጌ፣ የተቀዳደደና የቆሸሸ ልብስ ያዘወትራሉ፡፡ ገሪባዎች ጸጉራቸውን ስለማይቆረጡ ረጅምና እርስበርሱ በወፍራሙ የተቆጣጠረ (ድሬድ) ነው፡፡ የገሪባዎች የኢኮኖሚ መሰረት ልመና ነው፡፡ እርግማናቸው ይደርሳል ተብሎ ስለሚታመን እነሱ ለምነው አይከለከሉም፡፡ ሁሉም ያለውን ይሰጣቸዋል፡፡



*ፎቶ፣15፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን ለሙዳ በዓል የመጡ ገሪባ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

ገሪባዎች ለአለባበሳቸው፣ ለአመጋገባቸው፣ ለአኗኗራቸውና ለአጠቃላይ ሕይወታቸው አይጨነቁም። ይህም ባህሪያቸው እራሳቸውን ለፈጣሪና ለሼኽ ሁሴን አሳልፈው በመስጠታቸው እንደሆነ ይታመናል። ግለሰቦች ለኃይማኖታቸው እራሳቸውን አሳልፈው መስጠት፣ መመልኮስ ወይም መመነን (Asceticism) ለምድራዊ ዓለም እምብዛም ትኩረት እንዳይሰጡ ያደርጋቸዋል። በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚኖሩ ወይም ከሌላ አካባቢዎች ለሙዳ በዓላት የሚመጡ ገሪባዎችም እራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ፣ የሼኽ ሁሴን አገልጋዮች፣ የፈጣሪ ባሪያዎች፣ የዚህች ምድር እንግዳዎች ናቸው።

በመካነ ቅርሱ የሚከወኑ የተለያዩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ከኡሌዎች በተጨማሪ በገሪባዎች አማካኝነትም ይከወናሉ። ገሪባዎች ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ወደ ስፍራው የሚመጡና የራሳቸው ባህርይ ያላቸው ፎክ ቡድኖች ናቸው። Finnegan (1977:188-201) በተለያዩ አገራት የሚገኙ የቃል ግጥም ከዋኞችን በማጥናት ከከፈለችበት ምደባ መካከል ገሪባዎች የተዘዋዋሪ ባለሙያዎች (Free-lancer) ዘርፍ ውስጥ ሊያስመድብ የሚያስችላቸው የተወሰኑ ባህርያት አሏቸው። ተዘዋዋሪ ባለሙያዎች ያላቸውን ባህርይ Finnegan (1977) እንደሚከተለው ገልጻለች።

> ተዘዋዋሪ ባለሙያዎች በአብዛኛው ከመንደራቸው፣ ከአካባቢያቸውና ከሚኖሩበት ማህበረሰብ በመውጣት ወደተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ጥበባቸውን የሚያቀርቡ ናቸው። ጥበባቸውንም ለገንዘብ ማግኛነት ወይም ለንግድ የሚያቀርቡ ናቸው። እነዚህም በተለያዩ ግብዣዎችና የሀይማኖት ስፍራዎች በመገኘት ሰዎችን በማሞገስና በማዝናናት ገንዘብና ሌሎች ሽልማቶችን የሚሰበስቡ ናቸው። እነዚህ ተዘዋዋሪ ባለሙያዎች ከአካባቢያቸው፣ ከቤተሰብ ወይም ከመደበኛ ተቋም ስልጠና የሚወስዱ ሲሆኑ፣ ክዋኔያቸውም እንደሚቀርብበት ሁኔታ የሚለያይና የወዲያው (immediate) ፈጠራዊ ባህርይ የሚታይበት ነው። በአብዛኛው እነዚህ ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከበሩና ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው።

ከላይ ከቀረቡት የተዘዋዋሪ ባለሙያዎች ባህርያት መካከል ገሪባዎችን በትክክል የሚገልጹ አሉ። እነዚህም ባህርያት መካከል ገሪባዎች ከመንደራቸው፣ ከአካባቢያቸውና ከሚኖሩበት ማህበረሰብ በመውጣት ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ጥበባቸውን የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ጥበባቸውንም ለገንዘብ ማግኛነት ወይም ለንግድ የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ከአካባቢያቸው ወይም ከቤተሰብ ስልጠና የሚወስዱ መሆናቸው፣ ክዋኔያቸውም እንደሁኔታው የሚለያይና የወዲያው ፈጠራዊ ባህርይ የሚታይበት መሆኑ ናቸው።

ከእነዚህ የተዘዋዋሪ ባለሙያዎች ባህርያት መካከል ደግሞ ከመደበኛ ተቋም ስልጠና የሚወስዱና በአብዛኛው በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከበሩና ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው የሚሉትን ባህርያት በከፊል አያሟሉም። ነገር ግን ገሪባዎች ከእነዚህ ባህርያት መካከል በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ስፍራና የሚሰጣቸውና የሚከበሩ ናቸው የሚለውን የተዘዋዋሪ ባለሙያዎች መስፈርት በተወሰነ ደረጃ ያሟላሉ። ገሪባዎች በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ይከበራሉ፤ የተራገሙት ይደርሳል ተብሎ ስለሚታመን ይፈራሉ። የመረቁትም ይደርሳል ተብሎ ስለሚታመን ምርቃታቸውን ለማግኘት እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በተቃራኒው በሼኽ ሁሴን ተቃዋሚዎች ዘንድ የተናቁ ናቸው።

ገሪባ የሚለው ቃልም ከነበረው አወንታዊ ትርጓሜ ወደ "ፋራ"፣ "ጅል" ወይም "መኃይም" ወደሚሉ አሉታዊ ትርጓሜ እየያዘ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ገሪባ የሚለው ቃል ገራባ (የጫት ትራፊ) ከሚለው ቃል ጋር የሚመሳሰል ይመስላል። ይህም ምናልባት ገራባ የሚለው ቃል ገሪባ ከሚለው የመጣ ሊሆን ይችላል።[117] ገሪባዎች በተለያዩ ስፍራዎች፣ የገበያ ቦታዎች፣ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ስፍራዎች የመንፈሳዊ ሙዚቃ ክወናዎች ያቀርባሉ። በሚያቀርቡት ክወናም

[117] - ይህን የገሪባ እና የገራባ ቃላት ተዛምዶ ሃሳብ ያገኘሁት ከጀይላን ወልይ (ፕሮፌሰር) ነው።

የተለያዩ የገንዘብ ስጦታዎችንና ሽልማቶችን ያገኛሉ። ገሪባዎች የገቢ ምንጫቸው የተወሰነው በልመና ነው። ከልመና በተጨማሪም መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን በመከወን ገቢ ያገኛሉ።

## 5.3.4 መናኝ

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ውስጥና በአካባቢ፣ በዋሻዎች ውስጥ፣ በጫካ ውስጥ ወይም የት አካባቢ እንደሚኖሩ በግልጽ በማይታወቅ ስፍራ የተለያዩ ግለሰቦች ይኖራሉ። እነዚህ ግለሰቦች ዓለማዊ ኑሯቸውን በመተውና ከሰው ተለይተው በስፍራው መንነው የሚኖሩ ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች ከእነሱ ፍላጎት (ውዴታ) ውጪ በሼኽ ሁሴን ትዕዛዝና ግዴታ በስፍራው የተቀመጡ ናቸው። ግለሰቦቹ በስፍራው የተቀመጡትም የተለየ የሼኽ ሁሴን ውዴታን ለመፈጸም እንደሆነ ይታመናል። እነዚህ ግለሰቦች በስፍራው የሚቀመጡት ሼኽ ሁሴን ስፍራውን እንዲለቁ ሲፈቅዱላቸው ብቻ ነው። በመሆኑም በስፍራው እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ሊቆዩ ወይም በአጭር ጊዜ ከስፍራው ሊለቁ ይችላሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን ጥቂት ቁጥር ያላቸው ግለሰቦች መንነው እንደሚኖሩ ይነገራል። እነዚህ ግለሰቦች በአብዛኛው ከሰው ተለይተው በጫካና በዋሻ የሚኖሩ በመሆናቸው ለአካባቢው ሰው እይታ ቅርብ አይደሉም። እነዚህ ሰዎች በጫካ ውስጥ ያገኙትን እንሰሳ እያደኑ፣ ቅጠላቅጠልና ስራስር እየበሉ እንደሚኖሩ ይነገራል። በድሬ ሼኽ ሁሴን መንነው ከሚኖሩ ሰዎች መካከል እማማ ተሚማ አንዷ ናቸው። እማማ ተሚማ እንዴት ወደ ስፍራው ሊመጡ እንደቻሉ እንደሚከተለው ገልጸውልኛል።

> እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ የአብዮ ጃለሎ (የሼኽ ሁሴን ወዳጅና ተከታይ) ነኝ። እዚህ ድሬ ከመጣሁ 18 አመት ሊሆነኝ ነው። 3 ልጆች ያሉኝ፣ ባለትዳርና የተደራጀ ሀብትና ንብረት ያለኝ ነበርኩኝ። እዚህ የመጣሁት የመጨረሻ ልጄን አራስ ሆኜ ነው። በወቅቱ የ26 አመት ወጣት ነበርኩኝ። እዚህ የመጣሁትም ሆነ እዚህ የምኖረው በአብዮ ትዕዛዝ ነው። የእሳቸው ውዴታ እስኪፈጸምና ስፍራውን ልቀቂ እስከሚሉኝ ጊዜ ድረስ እዚሁ እኖራለሁ።[118]

እማማ ተሚማ የቀድሞው ዓለማዊ ኑሯቸው የደስታና የተድላ ነበር። ከባለቤታቸው ጋር ንብረት አፍርተው ለረጅም ጊዜ በትዳር የኖሩት በሰበታ ከተማ ነው። እሳቸው በአናጂና ለመኖር ፍላጎት አልነበራቸውም። ወደ ስፍራውም እንዴትና በምን መንገድ እንደመጡም አያውቁትም። እማማ ተሚማ ከሚኖሩበት ጎምቢሶ አዮ ሀደ ገራዶ አካባቢ መራቅ አይፈቀድላቸውም። በሼኽ ሁሴን ትዕዛዝ በተወሰነላቸው ስፍራ ብቻ ይንቀሳቀሳሉ። ከሱቅ መግዛት የሚፈልጉት እቃ ካለ

[118] - እማማ ተሚማ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 28 ቀን 2008 ዓ.ም።

ሰው ይልካሉ እንጂ እሳቸው ከተከለለላቸው ድንበር አልፈው መሄድ አይችሉም፡፡ ይህ የመንቀሳቀስ ገደብ የተጣለባቸው ከሼኽ ሁሴን እንደሆነ ነግረውኛል፡፡

እኔም ለመረጃ ስብሰባ በመካነ ቅርሱ በነበርኩባቸው ወቅቶች እንደ እማማ ተሚማ አይነት ሌሎች መናኞች በስፍራው እንዳሉ ሰምቻለሁ፡፡ "በገደልና በጫካ ውስጥ ብቻውን ከ5 አመት በላይ የኖረ ስሙም ማህዲ የሚባል ሰው አለ፡፡ እሱ ከሰው ጋር አይገናኝም፡፡ ግን ልታየው ትችላለህ፡፡" ተብዬ በተለያዩ ወቅቶች ለ3 ጊዜ ያህል ሰውዬው ይኖራል ወደተባለበት አይናገኜ ገደል ብሄድም ላየው አልቻልኩም፡፡

የአናጂና ነዋሪዎች በተለያየ ወቅት ወደ ስፍራው መጥተው የሚኖሩ መናኞች እንዳሉና አብዛኛዎቹ ሕይወታቸው እዛው እንደሚያልፍ ሌሎች ደግሞ ወዴት እንደሄዱ ሳይታወቅ ከስፍራው እንደሚሰወሩ ነግረውኛል፡፡ የእነዚህ መናኞች ግዴታ፣ ውዴታና ትዕዛዝ ምን እንደሆነ ከእነሱ፣ ከሼኽ ሁሴንና ከፈጣሪ በቀር ማንም ምንም አያውቅም፡፡ እነዚህ መናኞች በሼኽ ሁሴን የተመረጡ፣ የተባረኩና የተመረቁ ናቸው ተብሎ በመታመኑ የአካባቢው ነዋሪዎችና ለበዓላት ወደ ስፍራው የሚመጡ ሰዎች ልዩ አክብሮት ይሰጧቸዋል፡፡ የእነሱንም ምርቃትና ጸሎት ለማግኘት የተለያዩ ስጦታዎችን ይሰጧቸዋል፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአገራችን ከሚገኙ ሌሎች እስላማዊ ማዕከላት በተለየ መልኩ ምነና የሚካሄድበት "ገዳም" ነው፡፡ በስፍራው የገዳምነትን ሕይወት የጀመሩት ሼኽ ሁሴን ናቸው፡፡ እሳቸው በአይናገኜ ገደል ለ 40 ዓመታት በዋሻ ውስጥ ብቻቸውን በጸሎት ኖረዋል፡፡ በሼኽ ሁሴን አርአያነት የተጀመረው የምነና ሕይወት መካነ ቅርሱን የ"ሙስሊም ገዳም" እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ ምነና የሺዓት አስተምህሮ፣ የሱፊዝምና የኦርቶዶክስ እስልምና ፍልስፍና አራማጅ ሙስሊሞች ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የክርስትና ኃይማኖትም ምነና የተደገፈ መንፈሳዊ ድርጊት ነው፡፡ በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የምነና ሕይወት መኖሩ ከሺዓት፣ ከሱፊዝም፣ ከኦርቶዶክስ እስልምና እንዲሁም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ድርጊቶች ጋር ውሕደት እንዳለ አመላካች ነው፡፡

## 6. የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ገጽታ

መንፈሳዊ ጉዞ አምልኳዊና እምነታዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም ወደ ቅዱስ ስፍራ የሚደረግ ጉዞ እንደሆነ San (2001፡11) እና Kaplan (2010፡151) ይገልጻሉ፡፡ በተለያዩ አካላት የሚደረግ ጉዞ "መንፈሳዊ ጉዞ" ለመባል ማሟላት የሚገባው አምስት መስፈርቶች እንዳሉ Punkhurst (1994፡935) ይገልጻል፡፡ እነሱም፡- ጉዞ መደረግ፣ ጉዞው ቋሚ መዳረሻ ያለው፣ ወደ ቅዱስ ስፍራ የሚደረግ ጉዞ በተወሰነ ጊዜ፣ ቀን ወይም ወቅት የተገደበ መሆኑ፣ በተወሰነ የጊዜ ገደብ በሚፈለገው ስፍራ መድረስና ጉዞው በተናጠል ሳይሆን በቡድን መደረጋቸው ናቸው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ መንፈሳዊ ጉዞ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች መዳረሻ ስፍራቸው ቋሚ ሲሆን ስፍራውም አናጂና ቀበሌ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነው፡፡ መካነ ቅርሱም ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ ወደ ስፍራው የሚደረጉ ጉዞዎች በሙዳ በዓላት ወቅት የሚደረጉ ናቸው፡፡ የሙዳ በዓላት በየአመቱ ቋሚ ናቸው፡፡ ተጓዦቹም ወደ ስፍራው ሲሄዱ በቡድን በመሆን በበዓላት ወቅት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በመካነ ቅርሱ በመድረስ፣ በዓላቱ ሲጠናቀቁ ወደ መኖሪያ ስፍራቸው በመመለስ የሚከውኑት መንፈሳዊ ጉዞ ነው፡፡

በመሆኑም ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች በ Punkhurst (1994) የተገለጹ የመንፈሳዊ ጉዞ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞና የትራንስፖርት ሁኔታ፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ጉዞ ለማድረግ ምክንያት የሚያደርጓቸውን ጉዳዮች እንዲሁም መንፈሳዊ ጉዞው ያለው ባህርይ ቀርቧል፡፡

### 6.1 የድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ጉዞና የትራንስፖርት ሁኔታ

ለሐጅና ለዛህራ ገልገላ ኅበና የሙዳ በዓላት ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎችና ከውጭ አገራት በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ጉዞ ያካሂዳል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚመጡት የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮችን በመጠቀም ነው፡፡ አማራጮቹም በእግር፣ በእንስሳት፣ በመኪና እና በሂሊኮፕተር ነው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦችም ከእነዚህ የትራንስፖርት አማራጮች መካከል የመኖሪያ ስፍራቸው ካለው ርቀት፣

ካላቸው የገንዘብ አቅም፣ ካላቸው የትራንስፖርት አማራጭ ወይም ቀደም ሲል በገቡት ስለት መሰረት የሚያመቻቸውን ይመርጣሉ፡፡

በርካታ መንፈሳዊ ተጓዦች በእግር ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ይመጣሉ፡፡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች የእግር ጉዞ የሚያደርጉት በቡድን በቡድን በመሆን ነው፡፡ በቡድን የሚሰባሰቡት መንፈሳዊ ተጓዦች በአንድ አገር ወይም መንደር የሚኖሩና በተለያዩ ጊዜያት አብረው ጉዞ የሚያደርጉ ወይም የአንድ ቤተሰብ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች በእግር ለመሄድ የሚፈልጉባቸው ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል የመኖሪያ ስፍራቸው ቅርብ መሆን፣ ከሚኖሩበት መንደር ወደ መካነ ቅርሱ የሚወስድ የመኪና ትራንስፖርት አለመኖር፣ ቀደም ሲል በእግር ለመምጣት ስለት መግባት ወይም ለስለት የሚሆን የእርድ ከብት ይዞ መምጣት ሊሆን ይችላል፡፡

በርካታ መንፈሳዊ ተጓዦች የእንስሳት ትራንስፖርት በመጠቀም ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ በአብዛኛው በእንስሳት የሚመጡ ሰዎች በተናጠል፣ የተወሰኑ የቤተሰብ አባላት ብቻ ወይም የተወሰኑ የቅርብ ጎረቤታሞች በአንድ ላይ በመሰባሰብ ይመጣሉ፡፡ ወደ ስፍራው የሚመጡ ሰዎች በአብዛኛው ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚጠቀሙት በቅሎ፣ ግመልና አህያ ነው፡፡ አካባቢው ቆላማ የአየር ጸባይ ስላለው እነዚህ እንስሳት ለሰውና ለቁሳቁስ ጭነት የተመረጡ ናቸው፡፡

እጅግ በርካታ ቁጥር ያለው መንፈሳዊ ተጓዥ ወደ ስፍራው የሚጓዘው በመኪና ትራንስፖርት ነው፡፡ ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በሶስት መንገድ የመኪና ትራንስፖርት ይጠቀማሉ፡፡ አንደኛው መንገድ በአንድ አገር ወይም መንደር የሚኖሩና ቋሚ መንፈሳዊ ተጓዦች በአንድ ላይ በመሆን አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቢሶችን በመከራየት ይመጣሉ፡፡ እነዚህ ተጓዦች መኪናዎችን የሚከራዩት ደርሶ መልስ በመሆኑ ተጓዦቹ መንፈሳዊ ጉዳዮቻቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ ለተወሰኑ ቀናት እዛው ይቆያሉ፡፡ ሁለተኛው መንገድ ከተለያዩ የባሌና የአርሲ ዞን ከተማዎች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሕዝብ ትራንስፖርት በተመደበው ታሪፍ መሰረት በመክፈል ወደ ስፍራው የሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦች አሉ፡፡

በሁለቱም በዓላት ወቅት በባሌና በአርሲ ዞን የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ስምሪት መሰረት በርካታ መለስተኛ የሕዝብ ትራንስፖርቶች በተለምዶ አይሱዙ ቅጥቅጥ የሚባሉት ይመደባሉ፡፡

በሁለቱ የሙዳ በዓላት ወቅት በልዩ የትራንስፖርት ስምሪት ከባሌ ዞን ከሮቤ፣ ከጃራና ከጊንር፣ ከአርሲ ዞን ከአሰላ፣ ከአሳሳ፣ ከሮቤና ከኢተያ እንዲሁም ከአዲስ አበባና ከአዳማ ከተማዎች እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን ደርሶ መልስ የትራንስፖርት አገልግሎት አለ። ይህ የትራንስፖርት አገልግሎት ከበዓላት ወቅት ውጪ የለም።

ከበዓላት ወቅት ውጪ መደበኛ ትራንስፖርት ከጎሎልቻ ወረዳ ዋና ከተማ ጃራ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን በሳምንት አንድ ቀን አገልግሎት ይሰጣል። ቀኑም በጃራ ከተማ የገበያ ቀን በሆነው ረቡዕ ዕለት ነው። ከዚህ መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ውጪ በየቀኑ የሌሊት ጉዞ ከጃራ እስከ መቻራ (ምስራቅ ሐረርጌ ዞን) የሚሄዱትን የሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም ይቻላል። ከእነዚህ አማራጮች በተጨማሪ በመስመሩ የሚሄዱ የንግድና የጭነት መኪናዎችን መጠቀም ይቻላል። ሶስተኛው መንገድ በራሳቸው የግል መኪና ቤተሰባቸውን ይዘው የሚመጡ ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች የተለያዩ የቤት አውቶሞቢሎችንና መለስተኛ የሕዝብ ትራንስፖርት መስጫ መኪናዎችን በመያዝ ወደ ስፍራው ይመጣሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የተገነባ የአይሮፕላን ማረፊያ አለ። በዚህ ስፍራ በሂሊኮፕተር የአየር ትራንስፖርት የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦችና ቱሪስቶች ይጠቀሙበታል። በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በሁለቱ የሙዳ በዓላት ወቅት ከአዲስ አበባ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን ቀጥታ አይሮፕላን የትራንስፖርት መስመር ነበር። ነገር ግን ይህ መስመር በደርግ ዘመነ መንግስት ሙሉለሙሉ ተቋርጧል። በአሁኑ ወቅትም መስመሩ እንደተቋረጠ ነው። በጣም ጥቂት ቁጥር ያላቸው መንፈሳዊ ተጓዦች የሂሊኮፕተር ትራንስፖርት በመጠቀም ወደ ስፍራው ይመጣሉ። በአሁኑ ወቅት ለሙዳ በዓል ቢያንስ አንድ ሂሊኮፕተር መምጣት የተለመደ ነው። አብዛኛውን ጊዜ በሂሊኮፕተር ትራንስፖርት የሚመጡት የመንግስት ባለስልጣናት፣ የግል ሂሊኮፕተር ያላቸው ባለሃብቶችና ስፍራውን ለመጎብኘት የሚመጡ ቱሪስቶች ናቸው።

## 6.2 የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ጉዳዮች

የመንፈሳዊ ጉዞ አነሳሽ ጉዳዮች (Motives) በዋናነት ኃይማኖታዊ ናቸው። እነዚህ ኃይማኖታዊ ጉዳዮች በተለያዩ ንዑስ ደረጃዎች እንደሚመደቡ Stoddard (1997፡56) ይገልጻል። እነሱም፡- የተሻለ ነገር ለማግኘት፣ ለማመስገን፣ ኃይማኖታዊ ትዕዛዝን ለመፈጸም፣ ንስሃ ለመግባት፣ ህግን ለማክበር፣ ክብር ለማግኘትና ለጽድቅ በሚል በሰባት ደረጃዎች ይከፍላቸዋል። የመንፈሳዊ

ጉዞ አነሳሽ ምክንያቶች መንፈሳዊ ስሜትን ለማርካት፣ የቡድንን ማንነትና ሕብርን ለመመስረት፣ ለፈውስ፣ ስጦታ ለመስጠት፣ ለንግድ፣ ለመዝናናት አልፎአልፎም ወንጀል ለመፈጸም እንደሆኑ Pankhurst (1994፡947-950) ይገልጻል።

ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረጉ የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞዎች የተለያዩ አነሳሽ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ የሚካሄዱ ናቸው። አነሳሽ ምክንያቶቹም መንፈሳዊ ተጓዦች በሕይወታቸው ማግኘት የሚመኙትን ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንዲሟሉላቸው ለመጠየቅ፣ የጠየቁት ነገር ሲሳካ ለማመስገን፣ ከሰሩት ኃጽያት ለመሰረይ፣ የሼኽ ሁሴንን ትዕዛዝ ለመፈጸም፣ ያለባቸውን ግዴታና ውዴታ ለመወጣት፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ክብርን ለመጎናጸፍ፣ ከሞት በኋላ ነፍሳቸው ገነት እንድትገባ ለመለመን፣ ከደረሰባቸው አካላዊና መንፈሳዊ ህመም ለመፈወስ፣ በመካነ ቅርሱ ለሚገኙ የኃይማኖት አባቶች፣ ነዋሪዎች ወይም በዓላትን ጠብቀው በመምጣት ምጽዋዕትን ለሚለምኑና እርዳታ ለሚፈልጉ ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎችን ለመስጠት፣ ለንግድ፣ ለጉብኝት፣ ማህበራዊ ደረጃን ከፍ ለማድረግ፣ የፖለቲካ ርዕዮትን ለማስፋፋት፣ የእርቅ ስርዓትን ለመፈጸምና የተለያዩ ወንጀሎችን ለመፈጸም በሚል የሚካሄዱ ናቸው።

በሁለቱ የሙዳ በዓላት ወቅት እስከ አምስት መቶ ሺሕ የሚገመት ሕዝብ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ጉዞ ያደርጋል። ወደ መካነ ቅርሱ የሚመጡ ሰዎች የተለያዩ አነሳሽ ምክንያቶች አሏቸው። እነዚህን የተለያዩ ምክንያቶች ካላቸው ባህርይ አንጻር መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ጉብኝትና ሕገ-ወጥ ተግባራት በሚል በስድስት መመደብ ይቻላል። በእነዚህ ምደባዎች መሰረት ተጓዦች ያላቸውን ጉዳዮች በተናጠል ቀጥለን እንመልከት።

### 6.2.1 መንፈሳዊ ጉዳዮች

በሙዳ በዓላትና በሌሎች ወቅቶች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚደረግ ጉዞ ካለው በርካታ ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው መንፈሳዊ ጉዳዮችን ለመከወን በሚል ነው። መንፈሳዊ ጉዳዮችን ለመፈጸም ወደ ስፍራው የሚመጡ ሰዎችን 'መንፈሳዊ ተጓዦች' በሚል መግለጽ ይቻላል። ወደ ስፍራው ከሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች አብዛኛዎቹ በሁለቱ የሙዳ በዓላት ወቅት የሚመጡ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በማንኛውም ወቅት ወደ ስፍራው ይሄዳሉ።

መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው የሚጓዙባቸው መንፈሳዊ ጉዳዮች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ በርካታ ጉዳዮች መካከል ከሕመም ለመፈወስ፣ ለመመረቅ፣ ለመለመን፣ ስለት ለማስገባት፣

በዓል ለማክበር፣ ለመቀደስ (ከኃጽያት ለመሰረይ)፣ ለመሳል፣ ሕልም ለማስፈታት፣ መልዕክት ለማድረስ፣ ትዕዛዝ ለመፈጸም፣ የቤተሰብን ውርስ ለማስቀጠል የመሳሰሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች በራሳቸው፣ በቤተሰባቸው አባላት፣ በቤተዘመዳቸውና በጓደኛቸው ላይ ከደረሰባቸው የጤና ችግር ለመፈወስና ጤነኛ ሕይወት ለመምራት ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦቹ ከሰው ልጅ በተጨማሪ በእንስሳቶቻቸውና በሰብላቸው ላይ የደረሰ የጤና ችግር እንዲለቃቸው ለመለመን ይመጣሉ፡፡ በጤና ችግር ምክንያት ወደ ስፍራው የሚመጡ ሰዎች የተለያየ ሕመም ያለባቸው ናቸው፡፡ ሕመማቸውም በአብዛኛው ክፉ እንደሆኑ በማሕበረሰቡ ውስጥ የሚታመንባቸው መንፈሶች (ሰይጣን፣ ቡዳ፣ ድግምት፣ አስማት ወዘተ.)፣ የውስጥ ደዌ ሕመሞች፣ የቆዳ ሕመሞች፣ የአዕምሮ ሕመሞች ወዘተ. ናቸው፡፡

በተለያዩ ሕመሞች የተጠቁ ሰዎች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ሲመጡ "ካለብን ችግሮች ሁሉ እንፈወሳለን" ብለው ያምናሉ፡፡ ማንኛውም ሰው ካለበት ችግር ለመፈወስ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ሲመጣ በዋናነት ሁለት ጉዳዮችን ማሟላት እንደሚገባው ይታመናል፡፡ እነሱም፤ አንደኛ፣ ወደ ስፍራው ሲመጣ እንደሚድን በሙሉ ልብ ማመን ሲሆን ሁለተኛው፣ ያለበትን ችግር በግልጽ ሰው ፊት መናገር ናቸው፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች በሕይወታቸው ጥሩ እድል እንዲገጥማቸው ለመመረቅ ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ ሰዎች በሕይወታቸው ማግኘት፣ መስራት ወይም መሆን የሚመኟቸው ፍላጎቶች እንዲሳካላቸው ለመመረቅ ይሄዳሉ፡፡ ሰዎች ከራሳቸው ግላዊ ምኞት በተጨማሪ ልጆቻቸውን፣ ሚስቶቻቸውን፣ ባሎቻቸውን፣ የቤተሰብ አባሎቻቸውን ወይም ሌሎች ግለሰቦችን ለማስመረቅ ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው በመሄድ ለሕይወታቸው ስጋት ከሆነ ችግር ለመዳን ልመና ያካሂዳሉ፡፡

ግለሰቦች በራሳቸው ልመና የሚያደርጉባቸው ወይም ለሌሎች ግለሰቦች በመናገር ልመና እንዲያደርግላቸው የሚጠየቅባቸው ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ግለሰባዊ፣ አካባቢያዊ፣ ክልላዊ ወይም አገራዊ ይዘት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በተለያዩ ደረጃዎች የተከሰቱ ችግሮች በቦታው ተነግረው ጸሎትና ልመና ከተካሄደባቸው መሉለሙሉ ይፈታሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

ግለሰባዊ ጉዳዮች የሚባሉት የጤና፣ የሀብት፣ የትዳር፣ የልጅ ወይም የቤተሰብ ሰላም እጦት ናቸው፡፡ አካባቢያዊ ይዘት ያላቸው ጉዳዮች የሚባሉት መንፈሳዊ ተጓዦቹ በመጡበት መንደር ያለ የጤና፣ የጸጥታ፣ የምርት እጥረት፣ የረሃብ ወይም የሰላም ችግሮች እንዲፈቱ በቦታው ለተገኘ ሕዝብ በማስረዳት ጸሎትና ልመና እንዲደረግ ይጠይቃሉ፡፡ ክልላዊና አገራዊ ችግሮች ደግሞ በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ የሰላም፣ የጸጥታ፣ የረሃብ፣ የዝናብ እጥረት፣ የወረርሽኝ፣ የእርስበርስ ጦርነት፣ የኃይማኖት ግጭት ወይም የመንፈሳዊ ቦታዎችና የቅዱሳን መካነ መቃብሮች ሀይማኖቱን በማይደግፉ አካላት የመፍረስ ችግሮች እንዲፈቱ በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ጉዳዩን በቦታው ለተገኘ ሕዝብ በማስረዳት ጸሎትና ልመና እንዲደረግ ይጠይቃሉ፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው በመሄድ ካለባቸው ችግሮች ማለትም ጤና የማጣት፣ ልጅ ያለመውለድ፣ ሀብት የማጣት፣ ሰላም የማጣትና ከሌሎች ችግሮች ከተፈወሱ ስለት እንደሚያስገቡ ቃል ይገባሉ፡፡ ስለት እንደሚያስገባ የሚሳለው ግለሰብ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአካል በመገኘት ወይም ወደ ስፍራው ሳይመጣ ባለበት ቦታ በመሆን ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ልመናዎች ሙሉለሙሉ ሲፈጸሙ ወይም እንደሚፈጸሙ ምልክት ሲያዩ እሰጣለሁ ብለው ቃል የገቡትን ስለት ይዘው በመምጣት ያስገባሉ፤ ምስጋናም ያቀርባሉ፡፡

ግለሰቦች ሰርቻለሁ ብለው የሚያምኑት ክፉ ስራ ካለ ወይም ሰው በመሆናቸው በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከሰሩት ኃጽያት እንዲሰረዩ ለመለመን ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ ወደ ስፍራው በመምጣትም ፈጣሪ ኃጽያታቸውን ይቅር እንዲላቸው፣ በሰሩት ኃጽያት ምክንያት በሕይወታቸው ውስጥ እየደረሰባቸው ካለው መከራ እንዲወጡ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ነፍሳቸው በገነት እንድትኖር ይለምናሉ፡፡ አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ ውስጥ ለ7 ጊዜያት ያህል የሼኽ ሁሴንን ገሞ ከዘየረ (ከጎበኘ) ትልቅ የሕይወት በረከትና የነፍስ ንጽሕና ያገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ ግለሰቡም በቤተሰቡና በአካባቢው ሰው ዘንድ ልዩ ክብርን ያገኛል፡፡[119] ይህም ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ (Rite of passage) መሸጋገሪያ ነው፡፡ በመሆኑም መንፈሳዊ ተጓዦች በሕይወት ዘመናቸው ቢያንስ ለ7 ጊዜ ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

---

[119] - ሼኽ ከሪም ቃሶና አቶ አብዱልፈታህ አህመድ፣ ጎባ፣ ጥር 15 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

በቅዱስ ቁርዓን 7 ገነቶች አሉ፡፡ በክርስትና 7 ሰማየሰማያት አሉ፡፡ በተመሳሳይም በግብጽ ሚት ገነት በ7 የተከፋፈለ ነው፡፡ 7 ቁጥር የምሉዕነት፣ የማጠናቀቅ፣ በመንፈስ ብቁና ሙሉ የመሆን ተምሳሌት ነው፡፡ በአገራችንም ሰው ከሞተ በኋላ በተለያዩ ወቅቶች የመታሰቢያ ዝክር ይደረግለታል፡፡ ከዝክሮች መካከል በ7ኛው ሙት ዓመት የሚደረገው መታሰቢያ የማሳረጊያ ነው፡፡ በመሆኑም 7 ቁጥር ልዩ መንፈሳዊ ትዕምርት አለው፡፡

በሌላ በኩል 7 የማይሰበርን ፍጹም ቃል ኪዳን ያመለክታል፡፡ አብርሃምና አቤሜሌክ ቃል ኪዳን ሲገቡ ሰባት ሰባት በጎች አቅርበው ነበር (ዘፍ፣ 21+27)፡፡ በሌላ በኩልም እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ያረፈው በ7ኛው ቀን ነው በመሆኑም 7 የፍጽምና፣ የእረፍትና የሰንበት ተምሳሌት ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎችም በሕይወት ዘመናቸው ለ7 ጊዜያት ያህል ወደ መካነ ቅርሱ መሄዳቸው በሼኽ ሁሴንና በእነሱ መካከል ያለውን ፍጹም ቃል ኪዳን ለማጠንከር፣ መንፈሳዊ ጉዟቸውን ምሉዕ ለማድረግና በሕይወታቸው ሙሉ በረከትን ለማግኘት ነው፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች በሕልም ምክንያት ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ ሕልም ሰዎችና ሼኽ ሁሴን የሚገናኙበት መንፈሳዊ መንገድ ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን ለግለሰቦች በሕልም በመገለጥ በቦታው ለተሰበሰቡ ሰዎች ሊደርስ የፈለጉትን መልዕክት በቦታው ሄዶ እንዲናገር፣ በስፍራው እንዲፈጸም የሚፈልጉትን ነገር እንዲፈጽም ወይም በሕልሙ ያየው ነገር ያለውን ትርጉም ለመረዳት የተለያዩ ሰዎች ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ የተወሰኑ መንፈሳዊ ተጓዦች ከጎሳ ወይም ከቤተሰብ የተቀበሉትን ውርስና ቅርስ (Legacy) ለማስቀጠል ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚከወኑ መንፈሳዊ ክወናዎች መካከል በአንድ ጎሳ አባላት ብቻ ወይም በአንድ ቤተሰብ አባላት ብቻ የሚከወኑ አሉ፡፡ እነዚህን መንፈሳዊ ክወናዎች ለመፈጸምና ጎሳው ወይም ቤተሰቡ በመከወን ያቆየውን መንፈሳዊ ስርዓት ለትውልድ ለማስተላለፍና ያለውን ውርስና ቅርስ ለማስቀጠል በሚል የጎሳው ወይም የቤተሰቡ አባላት ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡

## 6.2.2 ፖለቲካዊ ጉዳዮች

በሙዳ በዓላት ወቅት የተለያዩ የመንግስት አካላት፣ ቡድኖችና ግለሰቦች ያላቸውን የፖለቲካ አቋም ለመግለጽና በስፍራው የተገኘውን ሕዝብ ለመቀስቀስ በሚል ምክንያት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ይመጣሉ፡፡ የፖለቲካ አቋማቸውን ለመግለጽ የሚመጡ አካላትን የመንግስት አካላት፣

የተቃዋሚ ቡድኖችና ግለሰቦች በሚል በሶስት መክፈል ይቻላል። በዚህ ምደባ መሰረት የሙዳ በዓላትና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በመቀጠል እንመልከት፡

### 6.2.2.1 የመንግስት አካላትና ፖለቲካዊ ጉዳዮች

አገሪቷን በመንግስትነት የመሩ የፖለቲካ ሀይሎች በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከበሩ የሙዳ በዓላትን በልዩ ሁኔታ በመጠቀም ያላቸውን የፖለቲካ አቋም ሲገልጹ ቆይተዋል፤ አሁንም እየገለጹ ይገኛሉ። የሙዳ በዓላት ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች የሚመጡ በርካታ ቁጥር ያላቸው መንፈሳዊ ተጓዦች የሚሰበሰቡባቸው በመሆኑና ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች የሚመጣ ሕዝብ በአንድ ቦታ ተሰባስቦ መገኘቱ በቀላሉ መልዕክት ለማስተላለፍ ይረዳል።

ይህንን የሕዝቦች ስብስብ ተጠቅሞ የፖለቲካ አቋምን ማሳወቅ ያለውን ጠቀሜታ በመረዳት መንግስታት የተለያዩ የፖለቲካ አካላትን በመላክ የበዓሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ በተሰበሰበው ሕዝብ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ስሜት እንዲሰልሉ፣ ሕዝቡ ያለበትን ችግርና በመንግስት ላይ የሚያሰማውን ቅሬታ ለመረዳት ተጠቅመውበታል፤ አሁንም እየተጠሙበት ነው።የመንግስት አካላት ወደስፍራው በቋሚነት መምጣት የጀመሩትና በመንግስት ደረጃ ተመድበው በዓሉን እንዲካፈሉ መደረግ የተጀመረው በንጉስ ምኒልክ ዘመነ መንግስት እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ።[120]

ንጉስ ምኒልክ ማዕከላዊ መንግስታቸውን የማስፋፋትና በመንግስት ቁጥጥር ስር ያልዋሉ አካባቢዎችን ለማጠቃለል ዓላማ ነበራቸው። በዚህ ዓላማም ባሌን በማዕከላዊ የመንግስት አስተዳደር ስር አውለውታል። በራስ ዳርጌ ሳህለስላሴና በደጃዝማች ወልደገብረኤል የሚመራው የንጉስ ምኒልክ ጦር ባሌን ለመቆጣጠር ባቀደበት ወቅት ለስለላ የላኩት ቡሰሪ የተባሉ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይን ነው። እሳቸውም በድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ በዓል ላይ በመገኘት የሕዝቡን ስሜት እየሰለሉ ወደ ራስ ዳርጌ መረጃ ይልኩ ነበር።

ንጉስ ምኒልክ በአሁኑ ወቅት አርሲ፣ ባሌና ሐረርጌ በሚል ስያሜ በሚታወቁ ዞኖች ባደረጓቸው የመስፋፋት ሂደት ከፍተኛ ሕዝባዊ ተቃውሞ እንደደረሰባቸው ይታወቃል። ይህ ሕዝባዊ ተቃውሞም ወደ ጦርነት አመራ። ጦርነቱም በንጉስ ምኒልክ ጦር አሸናፊነት ተጠናቀቀ። ይህ ሁኔታ በሕዝቦችና በመንግስት ሀይሎች መካከል ከፍተኛ ቅራኔን እንዲፈጠር ምክንያት ሆነ።

---

120 - አቶ አብዱልናስር አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም።

በመሆኑም በመንግስት ጦር መያዛቸው ያስቆጫቸው ሀይሎች በተለያዩ ጊዜያት በመንግስት ጦርና በመንግስት ሹማምንት ላይ ጥቃት በመሰንዘርና ጦርነት በመክፈት የአጼ ምኒልክ መንግስት በአካባቢው የተረጋጋ ይዞታ እንዳይኖረው ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡

በወቅቱም የተፈጠረውን አለመረጋጋት፣ የሰላም እጦትና የእርስበርስ ጥላቻ ለመቅረፍ፣ የአካባቢውን ሕዝብ ኃይማኖት እንደሚያከብሩ ለማሳየት፣ ኃይማኖት የማስቀየር ዓላማ እንደሌላቸው ለማስገንዘብ እንዲሁም የተቃዋሚ ኃይሎችን መረጃ ለመሰለል የመንግስት ሹማምንት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን በመሄድ በዓላትን ከሕዝቡ ጋር በጋራ ያከብሩ ነበር፡፡ በወቅቱም የመንግስት ሹማምንት ወደ ስፍራው በመምጣት የመንግስትን የፖለቲካ አቋም ለሕዝቡ በማስረዳት፣ መልዕክቶችን በማስተላለፍና የስለላ ስራ በመስራት ይጠቀሙ ነበር፡፡

በራስ ዳርጌና በራስ ጎበና ከሚመራው የንጉስ ምኒልክ ጦር ጋር ለመዋጋት የተሰባሰበው የአርሲ የሕዝብ ጦርም የሼኽ ሁሴንን ስም ለቅስቀሳ እንደተጠቀሙበት Cerulli (1922) በሰበሰባቸው ግጥሞች ይገልጻል፡፡ የጦርነቱ ይዘት ሀይማኖታዊ ባይሆንም ሕዝቡን ለጦርነት ለመቀስቀስ የአርሲና የባሌ ጦር ሼኽ ሁሴንን እንደ ምልክት ተጠቅመውበታል፡፡ ሼኽ ሁሴንን እንደ ምልክት የተጠቀሙበት ዋናው ምክንያት በአካባቢው ጠንካራ መሰረት ያለው የእስልምና ኃይማኖት በመሆኑ፣ የእስልምና ኃይማኖትን መሰረት በማድረግ ከሸዋ ከመጣው የክርስቲያን መንግስት ጋር ለመዋጋት ቅስቀሳ ለማድረግ ነው፡፡ በአጼ ምኒልክ ጦር ሰራዊት በኩልም ጽላትን (ታቦትን) እንደ ምልክት መጠቀማቸው ይነገራል፡፡

በልጅ እያሱ ዘመነ መንግስት (1913-1916) በድሬ ሼኽ ሁሴንና በአካባቢው የሚኖሩ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ከሌላው ዘመን በተሻለ ለመንግስት ድጋፍ የሰጡበት ነበር፡፡ ለዚህም በዋናነት የልጅ እያሱ አስተዳደር ለእስልምና ኃይማኖት የተሻለ አመለካከት አለው በሚል ነው፡፡ በወቅቱም ከአርሲና ከባሌ የተውጣጡ ታዋቂ ሙስሊሞች ልጅ እያሱን በሐረር ጨርጨር ሄደው አናግረዋቸዋል፡፡ ይህ ቡድንም የተመራው በከቢር መንዛ ማሜ ነው (Ketebo, 1999፤22)፡፡ ቡድኑም ልጅ እያሱን በመደገፍ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅስቀሳ አካሂዷል፡፡ በዚህ ዘመን በአርሲና በባሌ በርካታ መስኪዶች በመገንባታቸው ልጅ እያሱ በእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ ነበራቸው፡፡

ልጅ እያሱ ከስልጣን በተነሱበት ወቅት በከቢር መንዛ የሚመራው የአርሲ ሙስሊሞች ቡድንና በሮባ ገርቢ የሚመራው የባሌ ሙስሊሞች ቡድን በጋራ የጅሃድ ጦርነት አውጀው ነበር፡፡

የጅሃዱም ስያሜ ‘አላሁ ዳዒሙ’ በመባል ይታወቃል (Ketebo, 1999፤22)። ‘ዳዒም’ የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ዘለዓለማዊነት ማለት ነው፡፡ ‘ዳዒሙ’ የአረብኛውን ቃል በመውሰድ ኦሮምኛዊ (Oromofication) በማድረግ የተፈጠረ ነው፡፡ የጅሃዱ ስያሜም ‘ለአላህ ዘለዓለማዊነት’ የሚል ትርጉም አለው፡፡ የዚህ ጅሃድ ዓላማ የክርስቲያን መንግስት እንደሆነ የሚያምኑትን አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንንን ከስልጣን ለማውረድና ልጅ እያሱን ድጋሚ ስልጣን ላይ ለማውጣት ነበር፡፡ ነገር ግን የራስ ሚካዔል ጦር በሰገሌ ከተሸነፈ በኋላ እንቅስቃሴው ቆመ፡፡

ልጅ እያሱ ከስልጣን በወረዱበት ወቅት ሕዝቡ የነበረበትን ቁጭት የሚገልጽና ከሼኽ ሁሴን ጋር የተገናኘ ቃል ግጥም መኖሩን Ketebo (1999፤24) ይገልጻል፡፡ ይኸውም፡-

Iyyaasiyoo kiyya abba xeenaa

Wonti takkaan natti haftee seenan

Wonti takkaan natti haftee qawe’ee

Worri awuseen akkanaanuun jawe’ee

ትርጉሙ፡-

የእኔ እያሱ አባ ጤና

ስላንተ የሚቆጨኝ አንድ ነገር አለ

ያጣሁት አንድ ነገር አለ፤ እሱም ጠመንጃ (መሳሪያ) ነው

ጠመንጃ (መሳሪያ) ብናጣ እንኳ ላንተ እንዋጋለን

የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች (ሰዎች) ዘንዶ ናቸው፡፡

ማለት ነው፡፡ ይህ ቃል ግጥም ሕዝቡ ለልጅ እያሱ የነበረውን ፍቅርና ድጋፍ የሚያሳይ ነው፡፡ በግጥሙ ሼኽ ሁሴን ሕዝቡን ረድተው ድል እንደሚያደርጉና የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች (ሰዎች) ዘንዶ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ በዚህ ግጥም የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች የሚለው የሼኽ ሁሴን ተከታዮች፣ አፍቃሪዎችና ወዳጆች ማለት ነው፡፡ ዘንዶ ደግሞ የእሳቸው ተከታዮች ያላቸውን ጀግንነት የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ግጥም የምንዋጋበት መሳሪያ ባይኖረንም የሼኽ ሁሴን ተከታዮች ጀግኖች በመሆናቸው ድሉ ለልጅ እያሱ ይሆናል የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡

የጣሊያን መንግስት አገራችንን ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም በወረረበት ወቅት ሕዝቡን ለመከፋፈል የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀም ነበር፡፡ ጣሊያን ከተጠቀማቸው የመከፋፈያ ስልቶች መካከል በኢትዮጵያ በነበሩት የመንግስት ስርዓቶች ወቅት ትኩረት አልተሰጣቸውም ለሚላቸው

ኃይማኖቶች የተሻለ ቦታ መስጠት ነበር፡፡ በዚህ ስልት መሰረትም የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ለሆኑ ወገኖች ልዩ ድጋፍ በመስጠት ኃይማኖታቸውን በነጻነት እንዲከተሉና በዓላትን በጋራ እንዲያከብሩ ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ ይህ የጣሊያን የፖለቲካ ስልት በወቅቱ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ላይ ይደርስ የነበረው የሀይማኖት ነጻነት እጦት እውነታን እንደመሳሪያ መጠቀሙን አመላካች ነው፡፡

ይህ የጣሊያን የፖለቲካ ስልት ውጤታማ እንዲሆን ትኩረት ከተደረገባቸውና ልዩ ድጋፍ ከተሰጣቸው ቦታዎች መካከል የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አንዱ ነው፡፡ ይህ አጋጣሚ በጣሊያን መንግስትና በመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ የጣሊያን ወራሪ ኃይልም በአካባቢው የተነሳበትን ሕዝባዊ ተቃውሞ ለመቆጣጠር፣ በኢትዮጵያ ላይ አመጣለሁ የሚለውን የለውጥ ዓላማ ለሕዝቡ ለማሳመን፣ ሕዝቡ የጣሊያንን መንግስት እንዲደግፍ እንዲሁም ወረራውን ለመመከት በአካባቢው ጫካ የገባውን የባሌ አርበኛ ጦርን እንዳይረዱ ቅስቀሳ ለማድረግ የሙዳ በዓላትን በልዩ መንገድ ይጠቀምበት ነበር፡፡

የጣሊያን መንግስት የድሬ ሼኽ ሁሴንን መካነ ቅርስ ልዩ ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት አድርጓል፡፡ ከጥረቶቹም መካከል በወቅቱ የድሬ ሼኽ ሁሴን ኢማም የነበሩት ኢማም መሃመድ ሰዒድ የባሌ ኢማም አንድርጎ መሾሙ አንዱ ነው፡፡ በጣሊያን መንግስትና በድሬ ሼኽ ሁሴን አስተዳዳሪዎች መካከል የተጀመረው መልካም ግንኙነት እየተጠናከረ በመምጣቱ የጣሊያን መንግስት ለመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች የአገር ጉብኝት ግብዣ አደረገላቸው፡፡ በግብዣው መሰረትም ኢማም መሃመድ ከሁለቱ የባሌ ሱልጣኔቶች መሪዎች ጋር ወደ ጣሊያን አገር ሮም ከተማ በመሄድ ከሞሶሎኒ ጋር ተገናኙ፡፡

ከጣሊያን ጉብኝት በኋላ በተደረገው ስምምነት ከጃራ ከተማ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ድረስ ያለውን የ60 ኪ.ሜትር ጥርጊያ የጠጠር መንገድ በጣሊያን መንግስት ወጪ ለመስራት የተደረገው ስምምነት አንዱ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ስምምነት ወደ ተግባር ለመለወጥ በሂደት ላይ እያለ የጣሊያን ወራሪ ኃይል አገሪቷን ለቅቆ በመውጣቱ የመንገድ ስራው እንደተቋረጠ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡[121]፡

[121] - አቶ ሱልጣን በክሪ፣ ሮቤ ከተማ፣ ጥር 15፣ 2008 ዓ.ም፡፡

የጣሊያን መንግስት የአካባቢውን የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ድጋፍ ለማግኘት መስጊዶችን በተለያዩ አካባቢዎች ይገነባ ነበር፡፡ ይህም ሕዝቡን ያስደሰተ ስራ በመሆኑ ሕዝቡም ለሼኽ ሁሴን ምስጋና ያቀረበበት ቃል ግጥም በወቅቱ እንደተነገረ Ketebo (1999፤33) ይገልጻል፡፡ ይኸውም፡-

Allahu maraam Sheek Huseen waa ima mootani hoo

Xichoo gibbi kaafiraa masgiida qootani hoo

ትርጉሙ፡-

የተከበርከው ሼኽ ሁሴን ያንተ ስልጣን ትክክል ነው

የክርስቲያን ስፍራ ሆና የቆየችውን ጢቾን የመስኪድ ማዕከል አደረካት፡፡

ማለት ነው፡፡ የጣሊያን መንግስት መስኪድ ካስገነባባቸው ከተሞች መካከል ጢቾ አንዷ ነች፡፡ ጢቾ በወቅቱ የአርሲ ዋና ከተማ ነበረች፡፡ ይህም የመስኪድ ግንባታ የሼኽ ሁሴን ትዕዛዝ እንደሆነና በዚህም ድርጊት ሕዝቡ ሼኽ ሁሴንን ያመሰገነበት እንደሆነ ግጥሙ ያሳያል፡፡

የመንግስት ሹማምንት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን በመሄድ በዓላትን የማክበር እንቅስቃሴ ከጣሊያን ወረራ በኋላ በነበረው የአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስትም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በአጼ ኃይለስላሴ መንግስትና በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አስተዳዳሪዎች መካከል ከአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በተሻለ ደረጃ ጠንካራ ግንኙነት እንደተፈጠረ ይነገራል፡፡[122] በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የነበሩ የአካባቢው ሹማምንቶች በሙዳ በዓላት ወቅት በስፍራው በመገኘት ከሕዝቡ ጋር በዓላቱን ያከብሩ ነበር፡፡

[122] - አቶ ከተማ አብደላ፣ ጎባ ከተማ፣ ጥር 8 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡



*ፎቶ፣ 16፡- አጼ ኃይለሥላሴ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን ሲጎበኙ። (ፎቶ ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የተገኘ)።*

በዚህ ግንኙነት መሰረትም በ1957 ዓ.ም. አጼ ኃይለስላሴ የባሌ ክፍለ ሀገርን በጎበኙበት ወቅት የድሬ ሼኽ ሁሴንን መካነ ቅርስ ጎብኝተዋል። ከላይ የቀረበው ፎቶ ግራፍ እንደሚያሳየው ከአጼ ኃይለስላሴ ፊት ለፊት የሚታዩት በወቅቱ የመካነ ቅርሱ ኢማም የነበሩት ኢማም መሃሙድ መሃመድ ናቸው። ኢማሙም በወቅቱ ኢማሞች ይለብሱት የነበረውን የክብር ልብስ፣ እጃቸው ላይ ያደርጉት የነበረውን የክብር አምባር አድርገው ስፍራውን ለንጉሱ ማስጎብኘታቸውን ፎቶግራፉ ያሳያል።

በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኝበት መሬት ለመንግስት የመሬት ግብር ገቢ እንዳይደረግ፣ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሚከበሩት የሙዳ በዓላት ወቅት የአውሮፕላን ትራንስፖርት መደበኛ መስመር ከአዲስ አበባ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን እንዲኖር፣ የአይሮፕላን ማረፊያ ሜዳ እንዲሰራ መፍቀዳቸው እንዲሁም ንጉሱ መካነ ቅርሱን በጎበኙበት ወቅት የተለያዩ አልባሳትን ይዘው በመምጣት ለድሬ ሼኽ ሁሴን ነዋሪዎችና ከአናጂና ቀበሌ በጥቂት ርቀት ላይ ለሚኖሩት የዱቤ ማህበረሰብ አባላት መስጠታቸው ይነገራል።

እነዚህ የንጉሱ ድርጊቶች በመንግስትና በመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲመሰረት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል። በ1956 ዓ.ም በተጀመረው የባሌ ገበሬዎች አመጽ ምክንያት የአካባቢው ሕዝብ፣ የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎችና በመንግስት መካከል የተመሰረተው

መልካም ግንኙነት ተቋረጠ፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የመንግስት አካላት ወደ ስፍራው በመሄድ የሚያካሂዱት የበዓል ተሳትፎ ሙሉለሙሉ ተቋረጠ፡፡

የአጼ ኃይለስላሴን መንግስት በመጣል በ1966 ዓ.ም. የደርግ መንግስት ተተካ፡፡ የደርግ መንግስት በሚያራምደው የሶሻሊስት ርዕዮተዓለም ነበር፡፡ በዚህ ርዕዮተዓለም አስተሳሰብ ሀይማኖት ማህበራዊ እድገትን፣ ምርታማነትን፣ አብዮትንና ለውጥን ወደ ኋላ የሚጎትት ነው ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም ለሀይማኖትና ለሀይማኖታዊ በዓላት እምብዛም ትኩረት አይሰጥም ነበር፡፡ ይህ አስተሳሰብ በድሬ ሼኽ ሁሴንን መካነ ቅርስ ላይ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡ በዚህ ርዕዮተዓለም መሰረት የድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ በዓላትን ከሕዝቡ ጋር ለማክበር የሚመጣ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ባይኖርም የወረዳው አስተዳዳሪዎች በበዓላቱ ወቅት በስፍራው ይገኙ ነበር፡፡

የደርግ መንግስት ስልጣን በያዘበት ወቅት የባሌ ገበሬዎች አመጽ ድጋሚ በመቀስቀሱ በመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎችና በመንግስት አካላት መካከል ተፈጥሮ የነበረው አነስተኛ ደረጃ ያለው መልካም ግንኙነት ተቋረጠ፡፡ በወቅቱ የመካነ ቅርሱ ኢማም የነበሩት ኢማም መሃሙድ መሃመድ የባሌ ገበሬዎች አመጽን ይመሩ ከነበሩት አመራሮች ጋር ግንኙነት ፈጥረዋል ተብለው በመጠርጠራቸው ምክንያት ወደ ሱማሊያ ሞቃዲሾ ተሰደዱ፡፡

ከእነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ ለኢማሙ ወደ ሱማሊያ መሰደድ ዋና ምክንያት በህዳር 5 ቀን 1970 ዓ.ም የተፈጠረ ድርጊት ነው (Østebo, 2015)፡፡ ይህም አንድ አይሮፕላን በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አይሮፕላን ማረፊያ ያርፋል፡፡ አይሮፕላኑም እንዳረፈ የአማጽያን ጦር አይሮፕላኑን በመክበብ የአይሮፕላኑን አብራሪና አንድ ኢንጂነርን ጠልፈው ወደ ሱማሊያ ወሰዷቸው፡፡ ይህ ድርጊት ለመንግስት ሪፖርት ተደረገ፡፡ የመካነ ቅርሱ ኢማም በድርጊቱ ላይ ተሳታፊ ባይሆኑም ይመለከታቸው ስለነበር በፍጥነት አካባቢውን በመልቀቅ ወደ ሱማሊያ ሸሹ፡፡ የሱማሊያ መንግስትም በሞቃዲሾ መኖሪያ ቤት በመስጠት በእንክብካቤ ተቀበላቸው፡፡

የኢማሙ ስደት ምክንያት በመካነ ቅርሱ የነበረው የኢማም የአስተዳደር መዋቅር ላይ ክፍተት ተፈጠረ፡፡ ይህንን ክፍተት መነሻ በማደረግ መንግስት በመካነ ቅርሱ አስተዳደር ውክልና ላይ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት አካሄደ፡፡ መንግስት የመካነ ቅርሱን የአስተዳደር ክፍተት ለመሙላት ከአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ መካከል በመምረጥ መካነ ቅርሱንና አካባቢውን በቀበሌና በገበሬዎች ማህበር መዋቅር መምራት ተጀመረ፡፡ ይህ ውሳኔ ለረጅም ዘመናት መካነ ቅርሱን የመሪነት

ስልጣን የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ የዘር ሃረግ ውርስ ከአባት ወደ ልጅ ይተላለፍ የነበረውን የኢማምነት አመራር አስቀረው። በተመሳሳይም ውሳኔው በሼኽ መሃመድ ቤተሰቦች፣ በሼኽ አባስ ቤተሰቦችና በሰኪናዎች መካከል የአመራር ስልጣኑን ለመያዝ ለሚደረግ ትግል በር ከፈተ።

በመካነ ቅርሱ ላይ የሚወሰን ውሳኔም ከቀበሌው አመራር አካላትና ከሕዝቡ ጋር በጋራ በመሆን መሰጠት ተጀመረ። ይህ የመካነ ቅርሱ የአስተዳር ስልጣንና አመራር ሂደትም በአሁን ጊዜም ተግባራዊ እየተደረገ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች የደርግ መንግስት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስንና ወደ ስፍራው የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦችን በጥንቃቄ እንዲመለከት አስገድዶታል። ይህ ቁጥጥርም በመካነ ቅርሱ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። ኢማም መሃሙድ ለ14 ዓመት በሱማሊያ ቆይተው የደርግ መንግስት በ1983 ዓ.ም. ስልጣን ሲለቅ ከስደት በመመለስ ከአናጂና ቀበሌ 100 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው የጊንር ከተማ መኖር ጀመሩ። ኢማሙም የደርግ መንግስት ስልጣን ከለቀቀ በኂላ የመካነ ቅርሱ ስልጣን እንዲመለስላቸው ጥያቄ አቅርበዋል። ነገር ግን ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ወደ ሞቃዲሾ ተመልሰው መኖር ጀመሩ። ኢማም መሃሙድ በ1996 ዓ.ም. በሞቃዲሾ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

የደርግ መንግስትን በትጥቅ ትግል በመጣል በ1983 ዓ.ም. ስልጣን ላይ የወጣው የኢሕአዴግ መንግስት በ1987 ዓ.ም አዲስ ህገ-መንግስት አወጣ። በዚህ ህገ-መንግስት መንግስትና ሐይማኖት የተለያዩ እንደሆኑና አንዱ በሌላው ላይ ጣልቃ እንደማይገባ በአንቀጽ 11 ደነገገ (የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት፣1987 ዓ.ም)። በዚህ አንቀጽ መሰረት የመካነ ቅርሱ አስተዳደር ከዚህ በፊት እንደነበረው በቤተሰብ የዘር ሃረግ በኢማምነት እንዲመራ የኢማም ቤተሰቦች ለመንግስት ጥያቄ አቅርበው ነበር። የመንግስት አካላት ጉዳዩን አይተው በ1997 ዓ.ም የመካነ ቅርሱ የኢማም ስልጣን እንዲቀጥል ወስነዋል። ውሳኔውም የኢማም መሃሙድ ልጅ ለሆኑት ኢማም ሙህይ አል-ዲን የኢማምነት ስልጣኑን የሚሰጥ ነው። ነገር ግን ይህ ውሳኔ በመካነ ቅርሱ መሪዎች መካከል ውዝግብ በማስነሳቱ እስካሁን ተፈጻሚ አልሆነም።

በኢሕአዴግ መንግስትና በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎች መካከል የጠበቀ ግንኙነት የተፈጠረው በ1997 ዓ.ም በተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ ወቅት ነው። ምርጫው ሊካሄድ 1 ወር ሲቀረው በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የንጹህ ውኃ መጠጥ ዝርጋታ ተመረቀ። የንጹህ

ውኃ ፕሮጀክቱንም በወቅቱ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ ጁነዲን ሳዶ በስፍራው በመገኘት መርቀዋል፡፡ እሳቸውም በሙዳ በዓል ወቅት በስፍራው በመገኘት የአካባቢው ሕዝብና ወደ ስፍራው የሚመጣው መንፈሳዊ ተጓዥ ኦሕዴድ/ ኢሕአዴግን እንዲመርጥ ከፍተኛ ቅስቀሳ አድርገው ነበር፡፡ በወቅቱም ከ30 በላይ የመንግስት መኪናዎች አቶ ጁነዲን ሳዶን አጅበው እንደመጡ መረጃ ሰጪዎቼ ያስታውሳሉ፡፡[123] ይህ ሁነት ለመንግስት ፕሮፓጋንዳ መካነ ቅርሱ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በኢሕአዴግ ዘመነ መንግስት የወረዳ፣ የዞን፣ የክልልና የፌዴራል ባለስልጣናት የሙዳ በዓልን ከሕዝቡ ጋር ለማክበር ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ በ2000 ዓ.ም. የኦሮሚያ ሚሊኒየም በዓል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በክልል ደረጃ ተከብሯል፡፡ የኦሮሚያ ሚሊኒየም በዓል በድሬ ሼኽ ሁሴን የተከበረው በሐጅ የሙዳ በዓል ላይ ነው፡፡ በሚሊኒየም በዓል ወቅትም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የመብራት አገልግሎት እንዲጀምር የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታና የቴሌ ኮምኒኬሽን ኔትወርክ ዝርጋታ ስራዎች ተሰሩ፡፡ በወቅቱ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ አባዱላ ገመዳ የመብራት ጄኔሬተር ለድሬ ሼኽ ሁሴን በስጦታ አበረከቱ፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች በመንግስትና በመካነ ቅርሱ መካከል መልካም ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በአመት ሁለት ጊዜ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅትም የተለያዩ የፌዴራል ባለስልጣናት፣ የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት፣ የባሌ ዞን አስተዳዳሪና የተለያዩ ሴክተር ቢሮ ኃላፊዎች በስፍራው ይገኛሉ፡፡ የመንግስት አካላትም በበዓሉ ወቅት በመገኘት የመንግስትን አቋም ይገልጻሉ፡፡ ከባሌ ዞን አስተዳደር ወክለው የመጡበትን የሴክተር ቢሮውን ስም በመግለጽ የገንዘብ ስጦታ ይሰጣሉ፡፡ ለመካነ ቅርሱ ሊሰሩት ያሰቡትን የስራ እቅድ ይገልጻሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎችና በመንግስት መካከል በአንጻራዊነት የተሻለ ግንኙነት አለ፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ወቅቶች በአገርና በአካባቢው በሚነሱ የፖለቲካ ችግሮች ምክንያት ከመንግስት ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚሻክርበት አጋጣሚዎች እንደነበሩ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡[124] ከእነዚህ አጋጣሚዎች መካከል በ1997 ዓ.ም. በተደረገው አገራዊ ምርጫ ምክንያት የተፈጠረው ረብሻ፣ ከምርጫው በፊት በተደጋጋሚ ለሙዳ በዓላት ይመጡ የነበሩ ከፍተኛ የፌዴራልና የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት ከምርጫው በኋላ ከስፍራው

[123] - አቶ ሀብታሙ ሰቦቃ፣ አቶ ከዲር ኢብራሂም፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 9 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡
[124] - አቶ ከዲር ሀምዛ፣ ሼኽ ጣሂር አወሉ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 28 ቀን 2009 ዓ.ም፡፡

መቅረታቸው እንዲሁም ከ2008 ዓ.ም. መጀመሪያ አንስቶ በኦሮሚያ ክልል የተፈጠረው የሕዝብ አመጽና የመንግስት ምላሽ በመንግስትና በመካነ ቅርሱ መካከል የነበረውን መልካም ግንኙነት በተወሰነ ደረጃ እንዲቀዛቀዝ ምክንያት ሆኗል (Østebo, 2015)።

በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከበሩ የሙዳ በዓላት በአጼ ምኒልክ፣ በአጼ ኃይለስላሴ፣ በደርግና በኢሕአዴግ መንግስታት የስልጣን ዘመን ልዩ የፖለቲካ ትኩረት ይሰጣቸዋል። በተለያዩ ወቅቶች አገሪቷን ባስተዳደሩ መንግስታትም ከፍተኛ የመንግስት አካላት ወደ ስፍራው በመምጣት በበዓላቱ ላይ ይገኛሉ። የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች በአገርና በአካባቢው በተከሰቱ ልዩ የፖለቲካ ሁነቶች ምክንያት ከመንግስት ጋር መልካም የሆኑ፣ በጥርጣሬ ላይ የተመሰረቱ፣ በመከባበር ላይ የተመሰረቱና የጋር ትብብርን የሚፈጥሩ ግንኙነቶችን ሲመሰርቱ ቆይተዋል። በአሁኑ ወቅትም እንደተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ በተለያየ ደረጃ በሚገኝ ግንኙነት ቀጥለዋል።

### 6.2.2.2 ተቃዋሚ ኃይሎችና ፖለቲካዊ ጉዳዮች

የመንግስት ተቃዋሚ ኃይሎች ያላቸውን የፖለቲካ ዓላማ ለሕዝቡ ለመግለጽ፣ በድብቅ መረጃ ለመለዋወጥና ለሕዝቡ ቅስቀሳ ለማድረግ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከበሩ የሙዳ በዓላትን ይጠቀማሉ። መንግስትን ለመቃወም ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች መካከል በዋናነት በጄኔራል ዋቆ ጉቱ የሚመራውና በታሪክ የባሌ የገበሬዎች አመጽ በሚል ስያሜ የሚታወቀው ይጠቀሳል። ይህ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ከሙዳ በዓላት ጋር ያለውን ግንኙነት በጥቂቱ ቀጥለን እንመልከት።

በ1956 ዓ.ም የተጀመረው የባሌ ገበሬዎች አመጽ የአጼ ኃይለስላሴን መንግስት በእጅጉ ከፈተኑ የሕዝብ አመጾች መካከል በዋናነት የሚጠቀስ ነው። ይህ አመጽ የ'ሶውራ' አመጽ በሚል ስያሜ ይጠራል። ሶውራ የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው አል- ትውራ (al-thawra) በመውሰድ ኦሮምኛዊ በማድረግ የተፈጠረ ነው። ትርጉሙም አብዮት፣ አመጽ፣ እምቢተኝነት ወይም አርበኝነት ማለት ነው (Østebo, 2014:9)። የአመጹ ምክንያቶች መካከል የግብር መጨመር፣ የአስተዳደር በደልና አካባቢው በ1892 በንጉስ ምኒልክ ጦር በማዕከላዊ መንግስት ስር በተጠቃለለበት ወቅት የመሬት ባላባትና የስልጣን ባለቤት የሆኑት ነፍጠኞች እንጂ ነባሩ ሕዝብ አይደለም የሚሉት ዋናዎቹ ናቸው።

እነዚህ ምክንያቶች በአካባቢው ሕዝብና በአስተዳዳሪ የመንግስት አካላት መካከል ልዩነትን በመፍጠሩ ወደ ግጭት አመራ፡፡ በሕዝብ በኩል የነበረው የተናጠል ተቃውሞ በሶውራ ጦር መሪዎች መመራትና መደራጀት ጀመረ፡፡ የግጭቱ ምክንያትና የአማጽያኑ ጥያቄ እየሰፋ ሄዶ በሱማሊያው የዚያድባሬ መንግስት ድጋፍ በማግኘት ባሌንና አካባቢውን ከኢትዮጵያ ግዛት በመገንጠል ወደ ሱማሊያ መቀላቀልና ታላቋን ሱማሌ የመመስረት ዓላማ ያዘ (Gebru, 1977፡293)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባሌን ከማዕከላዊ መንግስት ነጻ በማውጣት ራሷን ችላ እንድትገነጠል የሚል ዓላማም ይዞ እንደነበር ይነገራል፡፡[125] ይህ የሶውራ አመጽ በሱማሊያ አቦ ነጻ አውጪ ግንባር (SALF) ድጋፍ ያገኘ ነበር (Gebru, 1977)፡፡ የባሌ የገበሬዎች አመጽ ይመራ የነበረው በአካባቢው ተወላጆች ነው፡፡ የአመጹ ዋና መሪ ከሆኑ ግለሰቦች መካከል ጄኔራል ዋቆ ጉቱ፣ ጄኔራል ሁሴን ቡኔ፣ ኮለኔል አልዬ ጭሪ፣ ሀጂ አደም ጂሎ፣ ሀጂ ይሳቅ ዳዲና አቶ መሃመድ ገዳ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

የባሌ ገበሬዎች አመጽ ከተጠነሰሰበት ወቅት ጀምሮ የአመጹ መሪዎች ዓላማቸውን ለሕዝቡ ለማድረስ፣ የሕዝብ ብሶትና ጭቆና ምን ያህል የከፋ መሆኑን ለማስረዳት፣ ለጦርነት የሚሆን ቁሳዊና ሞራላዊ ድጋፍ ለማግኘትና የመንግስትን ሀይል ለመሰለል የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጉ ነበር፡፡ የአመጹ መሪዎች በተለያዩ ቦታዎች በመገኘት በሕዝቡ ላይ የቅስቀሳ ስራ ይሰሩ ነበር፡፡ መሪዎቹ ለቅስቀሳ ከሚመርጧቸው ቦታዎች መካከል የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሕዝቦች በአንድ ላይ ስለሚገኙ፣ ከሚመጡባቸው ስፍራዎች ያሉትን መረጃዎች ይዘው ስለሚመጡ፣ የሕዝብን ብሶትና የእነሱን የአመጽ ዓላማ በቀላሉ ለሕዝብ ማድረስ ስለሚችሉና ስፍራው ለመረጃ ልውውጥና ለምስጢራዊ የጦር እቅድ ውይይት አመቺ በመሆኑ ለአማጽያኑ ዋና ማዕከል በመሆን አገልግሏል፡፡

በወቅቱ የመካነ ቅርሱ ኢማም የነበሩት ኢማም መሃሙድ የአመጹን ዓላማ ስለሚደግፉ ለጦር መሪዎቹ ከፍተኛ ሽፋን ይሰጡ ነበር፡፡ ኢማሙም ለበዓል የሚመጣውን ሕዝብ አመጹን እንዲደግፍ ከፍተኛ ቅስቀሳ ያካሂዱ እንደነበር ይነገራል፡፡[126] የአመጹ መሪዎችም ለሕዝቡ ሊተላለፍ የሚፈልጉትን መልዕክት፣ የትግሉን ዓላማና የትግሉን የወደፊት ዕቅድ በመንፈሳዊ ሙዚቃዎች አማካኝነት በቀላሉ ይገልጹ ነበር፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ሳይሳካ በመቅረቱ ኢማሙን

[125] - ግራዝማች ኃይሌ ወልደሰንበት፣ ጎባ ከተማ፣ ጥር 9 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

[126] - ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 30 ቀን፣2008 ዓ.ም እና ግራዝማች ኃይሌ ወልደሰንበት፣ ጎባ ከተማ፣ ጥር 9 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ለስደት ዳረገ፣ በመካነ ቅርሱም የነበረውን የኢማምነት የቤተሰብ የስልጣን ውርስ እንዲቋረጥ ምክንያት ሆነ።

የባሌ ገበሬዎች አመጽ በወቅቱ በአገሪቱ ውስጥ ይንቀሳቀሱ ለነበሩ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መመስረትና መጠናከር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል ከድሬ ሼኽ ሁሴን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የነበራቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ENNLF) እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (OLF) በዋናነት ይጠቀሳሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ENNLF) በሼኽ ሁሴን መሃመድ (ሼኽ ሁሴን ሱራ) ደማስቆ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅት ነው (Sa’id, 2016)።

ይህ የፖለቲካ ድርጅት ከመመስረቱ በፊት ስያሜውንና የትግል አቅጣጫውን በሚመለከት ለመወሰን ስብሰባ ያደረጉት ቡድኖች በሁለት ሀሳብ ተከፈሉ። በአብዲ ጎዴ የሚመራው ቡድን ስያሜው ኦሮሞነታችንን የሚገልጽና ትግሉም የኦሮሞን ነጻነት ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ወሰነ። በሼኽ ሁሴን ሱራ የሚመራው ቡደን ደግሞ ስያሜው ሁሉንም ብሔር፣ ብሔረሰቦችን የሚወክልና ትግሉም ሁሉንም ሕዝብ ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ወሰነ። በሼኽ ሁሴን ሱራ የሚመራው ቡድን በሀሳብ በማሸነፉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ENNLF) በሚል ስያሜ ተመስርቶ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ወደ አገር ውስጥ መግባቱን Geda (1988፣134-136) እና Muhammad (2004፣151-157) ይገልጻሉ።

የዚህ ድርጅት መሪ የሆኑት ሼኽ ሁሴን ሱራ በባሌ ዞን ዋቤ አውራጃ ገንደ ሱራ በሚባል መንደር መወለዳቸውን Muhammad (2004) ሲገልጽ፣ Sa’id (2016) ደግሞ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መገኛ በሆነው አናጂና ቀበሌ መወለዳቸውን ይገልጻል። ሼኽ ሁሴን ሱራ በ15 ዓመት እድሜያቸው የኃይማኖታዊ ትምህርት ለመማር ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የትምህርት ማዕከል ገብተዋል። በመካነ ቅርሱም ለ8 ዓመት ኃይማኖታዊ ትምህርት ተምረዋል (Sa’id, 2016)።። ሼኽ ሁሴን ሱራ ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጋር ያላቸው የልጅነት ቀረቤታ ከፖለቲካ ትግል ሕይወታቸው ጋር በሁለት መንገድ ይያያዛል። አንደኛው፣ ለትጥቅ ትግል ጫካ በገቡበት ወቅት ለሙዳ በዓላት በመካነ ቅርሱ ለሚመጡ ሰዎችን ቅስቀሳ እንዲያደርጉ፣ ግለሰቦችን እንዲመለምሉና ገንዘብ እንዲያሰባስቡ አስችሏቸዋል።

ሁለተኛው፣ ሼኽ ሁሴን ሱራ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ስለተማሩ በስፍራው ለኃይማኖት ትምህርትም ሆነ ለሙዳ በዓላት ከመላው የአገሪቷ ክፍሎች የሚመጡ ብሔር ብሔረሰቦችን

የማየትና የማወቅ እድል እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ለዚህም ነው የድርጅታቸው ስያሜና የትግሉ ማዕከል መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብን የያዘ እንጂ በብሔር እና በኃይማኖት የተወሰነ ድርጅት እንዲሆን ያልፈለጉት፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና አካባቢው ያደገ፣ በማዕከሉ መንፈሳዊ ትምህርት የተማረ እንዲሁም ለሙዳ በዓል ወደ ስፍራው የሄደ ሁሉ አንድ የጋራ የሚያደርገው ባህርይ አለ፡፡ ይህም ከብሔርና ከኃይማኖት ወገንተኝነት አስተሳሰብ የጸዳ መሆን ነው፡፡ ይህ ባህርይ መካነ ቅርሱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያጎናጽፈው ጸጋ ነው፡፡

## 6.2.2.3 ግለሰቦችና ፖለቲካዊ ጉዳዮች

ለሙዳ በዓላት ወደ ስፍራው የሚመጣው ሕዝብ ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ወደ ስፍራው ከሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች መካከል የራሳቸውን የፖለቲካ አቋም ለማንጸባረቅና በያዙት የፖለቲካ አቋም መሰረት ሕዝቡን ለመቀስቀስ የሚመጡ የተወሰኑ ግለሰቦች አሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ገዢውን መንግስትን የሚደግፉ ወይም የሚቃወሙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በዓሉን ለማክበር ለተሰበሰበው ሕዝብ በተለያዩ መንገዶች የራሳቸውን የፖለቲካ አቋም ያንጸባርቃሉ፡፡ ከገዢው መንግስት ወገን የሆኑ ግለሰቦች ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ፈጣሪ የመረጠው መሆኑን፣ ልማታዊ መሆኑን፣ የሀይማኖት ነጻነት የሰጠ መሆኑንና የብሔር ማንነትን ያከበረ መሆኑን መግለጽ የተለመደ ነው፡፡ ግለሰቦቹም መንግስትን በማወደስና በመመረቅ ያላቸውን የፖለቲካ ወገንተኝነት ያንጸባርቃሉ፡፡

በተቃራኒው ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የሚቃወሙ ግለሰቦች መንግስት በብሔር መካከል መከፋፈልን እንደሚፈጥር፣ የእርስበርስ ግጭትን ሆነ ብሎ እንደሚያስነሳ፣ ወገኖችን እንደሚጨፈጭፍና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከስልጣን እንደሚነሳ ራዕይ እንደታያቸው መግለጽ የተለመደ ነው፡፡ ግለሰቦቹም መንግስትን በመርገምና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሼኽ ሁሴን ከስልጣን እንዲያስነሱላቸው በመለመን ያላቸውን የፖለቲካ ወገንተኝነት ያንጸባርቃሉ፡፡ የመንግስት ደጋፊዎችም ሆኑ ተቃዋሚ ግለሰቦች የፖለቲካ አቋማቸውን ለማንጸባረቅ የሚጠቀሙባቸው ስልቶች በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ስልቶች መካከል "ሼኽ ሁሴን ተናገር ብለው አዘውኝ ነው፡፡"፣ "በሕልም አይቼ ነው፡፡"፣ "ይህንን እንድናገር በፈጣሪ ታዝዤ ነው፡፡"፣ "ሼኽ ሁሴን አሳይተውኛል፡፡" የሚሉ አገላለጾች የተለመዱ ናቸው፡፡

### 6.2.3 ተቃዋሚ ኃይሎችና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች

ከጥቂት አመታት ወዲህ በአገራችን በእስልምና ኃይማኖት ስር የተፈጠሩ የሀይማኖት አስተምህሮ ንዑስ ክፍሎች ያላቸው ልዩነት ይፋ መሆን ጀምሯል፡፡ በዚህ የሀይማኖት አስተምህሮ ልዩነት ምክንያትም የተለያዩ ግጭቶች ተከስተዋል፡፡ ይህ የሀይማኖት ግጭት ከተስተዋለባቸው ስፍራዎች መካከል የአናጂና ቀበሌና አካባቢው አንዱ ነው፡፡ በአካባቢው የሚስተዋለው የአስተምህሮ ልዩነት በሁለት አካላት መካከል ጎልቶ ይታያል፡፡ እነዚህም አካላት የድሬ ሼኽ ሁሴንን አስተምህሮን የሚከተሉና የሰለፊያ አስተምህሮን የሚከተሉ ናቸው፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አስተዳዳሪዎች፣ የመካነ ቅርሱ ዙሪያ ነዋሪዎች፣ ወደ መካነ ቅርሱ የሚመጡ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ የሆኑ መንፈሳዊ ተጓዦች የሱፊዝም አስተምህሮ የሚከተሉ ናቸው፡፡ በመካነ ቅርሱ አካባቢ (ከዋናው የግምብ አጥር በግምት 500 ሜትር ርቀት ላይ) የሚኖሩ የተወሰኑ ግለሰቦች ደግሞ የሰለፊያ አስተምህሮ የሚከተሉ ናቸው፡፡

በእነዚህ ሁለት የሀይማኖት አስተምህሮዎች ልዩነት ምክንያት በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች የተለያዩ ግጭቶች ተከስተዋል፡፡ በግጭቱም ሳቢያ በሰው ሕይወት፣ በንብረትና በሀይማኖት ስፍራዎች ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች፣ የሰለፊያ አስተምህሮን የሚያራምዱ ግለሰቦች በአካባቢያቸው ያደረሱትን የሰው ሕይወት፣ የንብረትና የሀይማኖት ስፍራዎች የማፍረስ ጥፋት ለበዓል ለተሰበሰበው ሕዝቡ ይናገራሉ፡፡ ከሚኖሩበት አካባቢ በተጨማሪ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ለበዓል በሚመጡበት ወቅት በመንገድ ላይ ያደረሱባቸውን ችግሮች ይናገራሉ፡፡

በሀይማኖት አስተምህሮ ልዩነት ምክንያት የሚነሱ ችግሮችን መቋቋም የሚቻልበትን መንገድ፣ በሰለፊያና በሌሎች አስተምህሮ ተከታዮች የሚያነሱ ጉዳዮች የሀይማኖት መሰረቶች ትክክል አለመሆናቸው ለሕዝቡ ለማሳወቅና አስተምህሮውን ለማውገዝ የተለያዩ ቡድኖች ቅስቀሳ ያደርጋሉ፡፡ ለሀይማኖት ቅስቀሳና የሰለፊያን አስተምህሮን ለማውገዝ በሙዳ በዓል ወቅት የሀይማኖት መሪዎች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ ቡድኖቹም የሰለፊያን አስተምህሮ ያወግዛሉ፤ ሰለፊያዎችን ይረግማሉ፡፡

## 6.2.4 ማሕበራዊ ጉዳዮች

በሙዳ በዓላት ወቅት የተለያዩ ቡድኖችና ግለሰቦች የተለያዩ ማሕበራዊ ጉዳዮችን ለመፈጸም በሚል ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ይመጣሉ። በሙዳ በዓል ወቅት የሚከወኑ ማህበራዊ ጉዳዮች ካላቸው ባህርይ አንጻር ግጭት ለመፍታት፣ ጋብቻ ለመፈጸም፣ እርዳታ ለማሰባሰብ፣ ስጦታ ለመስጠትና መረጃ ለማስተላለፍ በሚል በአምስት መመደብ ይቻላል። እነዚህን ማሕበራዊ ጉዳዮች ያላቸውን ባህርይ በተናጠል ቀጥለን እንመልከት።

### 6.2.4.1 ግጭት መፍታት

በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ በድንበርተኛ ብሔሮች ወይም ጎሳዎች መካከል ግጭቶች ይነሳሉ። እነዚህ ግጭቶች ሰፍተው የከፋ ችግር ከመፍጠራቸው በፊት ማሕበረሰቡ ባለው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት መሰረት እንዲበርዱ ይደረጋል። ወደ ግጭት የገቡ ወገኖችም በሀይማኖት መሪዎች ወይም በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት እርቅ ይፈጽማሉ። ሁለቱ ታራቂዎች ከእርቅ በኋላ የግጭት መነሻ ምክንያቶችን በመፍታትና እርቅ በመፍጠር ወደ ሰላማዊ ኑሮ ይመለሳሉ።

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአካባቢው በሚገኙ ብሔሮች፣ ማህበረሰቦችና ጎሳዎች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች እርቅ የሚፈጽሙበት ስፍራ ነው። በማህበራዊ፣ በባህላዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በሌሎች ምክንያቶች የተነሱ ግጭቶች ተባብሰው ወደ ከፋ እልቂት ከማምራታቸው በፊት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሀይማኖት መሪዎችና የአገር ሽማግሌዎች መልዕክት በመላክ ሁለቱንም አካላት በቀነ ቀጠሮ ወደ ስፍራው ይጠራሉ።

የመካነ ቅርሱ መንፈሳዊ መሪዎችና የአገር ሽማግሌዎች የሚያቀርቡትን የእርቅ ጥሪ በማክበር የሁለቱም ታራቂ ወገን ተወካዮች ወደ ስፍራው ይመጣሉ። የመካነ ቅርሱን የሀይማኖት መሪዎችና የአገር ሽማግሌዎች የእርቅ ጥሪን አልቀበልም የሚል ወገን ይረገማል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ሁሉም ወገን ጥሪውን ተቀብሎ በቀጠሮው መሰረት ለእርቅ ተወካዮቹን ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ይልካል። የሀይማኖት መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች የግጭት ምክንያቶችን፣ አጥፊውን ወገንና የጥፋቱን መጠን በማጥናት አጥፊውን በመቅጣት፤ ተጎጂውን በመካስ ያስታርቃሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚካሄዱ የእርቅ ስርዓቶች የሚከወኑት በዓላት በሌሉባቸው ወቅቶች ነው፡፡ በእነዚህ ወቅቶች የተካሄዱ እርቆች የመጨረሻ ማሰሪያ የሆነውን የእርስበርስ የይቅርታ ቃል የሁለቱ ወገን ተወካዮች የሚያቀርቡት በሙዳ በዓላት ወቅት ነው፡፡ ሁለቱ ታራቂ ወገኖች ለበዓል በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ቀርበው የግጭቱን መነሻ ምክንያት ገልጸው ይቅርታ ይጠያየቃሉ፤ ይሳሳማል፡፡ ሕዝቡም ታራቂ ወገኖችን ይመርቃል፤ ያመሰግናሉ፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች በመካከላቸው ግጭት ተፈጥሮ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ እርቅ የፈጸሙ ብሔሮች፣ ማህበረሰቦችና ጎሳዎች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል የዱቤ ማሕበረሰብ እና የሀዲዶ ጎሳ፣ የሱዴ ጎሳ እና የአታባ ጎሳ፣ የአቦሰራ ጎሳ እና የቀጢባ ጎሳ፣ የሰብሮ ጎሳ እና የያብሰና ጎሳ፣ የኦቦራ ጎሳ እና የሲናና ጎሳ ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ ብሔሮች፣ ማህበረሰቦችና ጎሳዎች በተለያየ ወቅት በመካከላቸው የተከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት ዘላቂ ሰላማቸውን አስጠብቀዋል፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከእርቅ መፍጠሪያነት በተጨማሪ የሰላም ጥሪ የሚካሄድበት ስፍራ ነው፡፡ በአካባቢው የተፈጠረ ግጭት ካለ በእርቅ እንዲጠናቀቅ ይጠየቃል፡፡ ሰላም እንዲወርድ ይጸለያል፡፡ በ2007 ዓ.ም. ሚያዝያ ወር በሙዳ በዓል ላይ መረጃ ለመሰብሰብ በተገኘሁበት ወቅት ከጥቂት አመት በፊት በድንበር አካባቢ በሚገኙ የባሌ ዞን ነዋሪዎችና የሱማሌ ክልል ነዋሪዎች መካከል የተፈጠረው የድንበር ግጭት በሰላም እንዲፈታ ሲጠየቅና ሲጸለይ ሰምቻለሁ፡፡

## 6.2.4.2 ጋብቻ ማስፈጸም

ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን በሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ወቅት በሰዎች መካከል የእርስበርስ ትውውቅና ቀረቤታ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ትውውቅና ቀረቤታ ምክንያት በትዳር ለመተሳሰር የሚፈልጉ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በአጭር ጊዜ ቅውውቅ ትዳር መመስረት እንደሚችሉ ከተስማሙ፣ እዛው ጋብቻ ይፈጽማሉ፡፡ ሁለቱ ተጋቢዎች ለሙዳ በዓል ለተሰበሰበው ሕዝብ ሊጋቡ እንደተስማሙ ይገልጻሉ፡፡ ሕዝቡም ትዳራቸው እንዲሰምር ይመርቃቸዋል፤ የአዲስ ጎጆ መውጫና የኑሮ ማቋቋሚያ የሚሆን የገንዘብ ስጦታ ያዋጣላቸዋል፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት የሚፈጸም ጋብቻ ከሌላው ጊዜ የጋብቻ ስርዓት የተለየ የሚያደርጉት ሶስት ባህርያት አሉት፡፡ እነሱም፤ በሙሽራውና በሙሽሪት ወገን ሚዜ አለመኖር፣ ለሙሽሪት

ወይም ለቤተሰቦቿ የሚሰጥ ጥሎሽም ሆነ የሚገዛላት ልዩ አልባሳት አለመኖሩና የበዓሉ ስርዓት እንዳበቃ ሙሽራው ሙሽሪትን ወደ አገሩ ይዟት መሄድ መቻሉ ናቸው፡፡

### 6.2.4.3 እርዳታ ማሰባሰብ

በርካታ መንፈሳዊ ተጓዦች ከተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ለሙዳ በዓላት ይመጣሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ሲመጡ በሚኖሩበት አካባቢ፣ ወረዳ፣ ዞን ወይም ክልል የተከሰቱ ችግሮችን ለተሰበሰበው ሕዝብ ይናገራሉ፡፡ በበዓሉ ወቅት የሚነሱ አካባቢያዊ ችግሮች ድርቅ፣ ረሃብ፣ ወረርሽኝ፣ ጎርፍ፣ የእጸዋት በሽታ፣ የከብት በሽታ፣ ግጭት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ችግሩ ካለበት አካባቢ የመጡ ሽማግሌዎች ስለ ሁኔታው አስረድተው ሕዝቡ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ እንዲሰጥ ይጠይቃሉ፡፡ ሕዝቡም የአቅሙን ያህል የገንዘብና የአልባሳት እርዳታ ይሰጣል፡፡ ከሕዝቡ የተሰበሰበውን እርዳታ ችግሩን የገለጹ ሽማግሌዎች ይሰበስባሉ፡፡ የሰበሰቡትንም እርዳታ ይዘው ወደ መጡበት አካባቢ በመሄድ ለተጎዱ ወገኞች ያከፋፍላሉ፡፡ በመጋቢት ወር፣ 2008 ዓ.ም መረጃ ለመሰብሰብ በሙዳ በዓል ላይ በተገኘሁበት ወቅት ከጎባ ከተማ የመጡ ሽማግሌዎች በከተማው ከሳምንት በፊት የኮሌራ ወረርሽኝ መከሰቱን ገልጸው፣ ለተጎዶ ወገኖች እርዳታ ከሕዝቡ ሲሰበስቡ አይቻለሁ፡፡

### 6.2.4.4 ስጦታ መስጠት

ወደ መካነ ቅርሱ ከሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች መካከል በበዓሉ ላይ ለሚገኙ ሰዎች ስጦታ ለመስጠት በሚል ዓላማ የሚመጡ አሉ፡፡ ከደረሰባቸው ችግር ከወጡ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ካገኙ ስለት እንደሚያስገቡ ቃል የገቡ ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው ይመጣሉ፡፡ አልፎአልፎ ደግሞ የገቡት ስለት ባይኖርም በራስ ተነሳሽነት የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው የሚመጡ ሰዎች አሉ፡፡ በዓሉን ለማክበር ለተሰበሰበው ሰው ከሚሰጡ ስጦታዎች መካከል የገንዘብ ስጦታ፣ የከብት እርድ፣ የአልባሳትና የእህል ስጦታዎች ይጠቀሳሉ፡፡

ሰዎቹ ይዘው የመጡትን የገንዘብ፣ የአልባሳትና የእህል ስጦታዎች ለሕዝቡ ያከፋፍላሉ፡፡ ለእርድ የሚሆን ግመል፣ ከብት፣ በግ፣ ፍየልና ዶሮ በማምጣትና በማረድ ለበዓሉ የተገኙ ሰዎችን ያበላሉ፡፡ ይህ ስጦታ የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት፣ የወገን ደራሽ መሆንን ለመግለጽ፣

ማህበራዊ ክብርን ለማግኘት፣ ለመመረቅ፣ ለመባረክ፣ የእርስበርስ መረዳዳትን ለማጠናከርና ግንኙነትን ለማሳደግ ይጠቀማል።

### 6.2.4.5 መረጃ ልውውጥ

መንፈሳዊ ተጓዦች ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ወደ መካነ ቅርሱ ይመጣሉ። እነዚህ መንፈሳዊ ተጓዦች ከመጡበት አካባቢ ወይም ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ሲመጡ በመንገዳቸው ላይ ያጋጠማቸው አዲስ ነገር ካለ ለሕዝቡ መረጃ ይሰጣሉ። በሚሰጡት መረጃ መሰረት እንደ ጉዳዩ የአሳሳቢነት መጠን ጸሎት እንዲደረግላቸው፣ እርዳታ እንዲሰጣቸው፣ የመንግስት ድጋፍ እንዲሰጣቸው፣ ጥንቃቄ እንዲደረግ ወይም ሕዝቡ እንደ መረጃ እንዲወስደው ይጠይቃሉ።

መንፈሳዊ ተጓዦች በአካባቢያቸው ያለው ወይም በመንገድ ላይ ያጋጠማቸውን ጉዳይ ለሚመለከተው አካል በመግለጽ እንዲታወቅ ያደርጋሉ። በሙዳ በዓላት ወቅት በአካባቢያቸው እንዲሰራላቸው የሚፈልጉትን የመሰረተ ልማት ስራ በስፍራው ለሚገኙ የመንግስት ባለስልጣናት ይገልጻሉ። በአካባቢያቸው የተከሰተ ችግርን ለመንግስት አካላት ያሳውቃሉ። ከአካባቢያቸው ለረጅም ጊዜ የጠፋ ሰው ካለ ፎቶ ግራፉን ይዘው በመምጣት የሚያውቀው ሰው ካለ ይጠይቃሉ። በአካባቢያቸው የእህል ምርት ላይ የደረሰን ችግር ይገልጻሉ። በምርታቸው የገበያ ዋጋ ላይ የተከሰተ ችግር ካለ ይገልጻሉ።

በጥቅምት ወር 2007 ዓ.ም መረጃ ለመሰብሰብ በሙዳ በዓል ላይ በተገኘሁበት ወቅት ከገበያ ዋጋ አንጻር የመረጃ ልውውጥ ሲደረግ ሰምቻለሁ። ይህም ከጅማ ዞን የመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች የቡና ዋጋ መቀነሱን ገልጸው፣ የቡና ዋጋ እንዲሻሻል ሕዝቡ ጸሎት እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋል። ከጅማም ቡና ይዘው በመምጣት ስጦታ ሰጥተዋል። ይህ በበዓላት ወቅት የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦች በበዓሉ ላይ የተገኙ ሕዝቦች ስለተለያዩ አካባቢዎች ወቅታዊ ሁኔታ እንዲያውቁ፣ የእርስበርስ ግንኙነት፣ ትውውቅና መተሳሰብ እንዲፈጥሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

## 6.2.5 ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች

የሙዳ በዓላትን ለማክበር ከሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በተጨማሪ ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሚመጡ ግለሰቦች አሉ። የሙዳ በዓላትን ለማክበር ከተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ ስፍራው ስለሚመጣ በበዓላት ወቅት በስፍራው ከፍተኛ የንግድ

እንቅስቃሴ ይካሄዳል፡፡ በበዓላት ወቅት ለሚመጣው ሕዝብ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን፣ አልባሳትን፣ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን፣ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ያሉባቸውን ካሴቶችና ሲዲዎች፣ ምግቦችን፣ መጠጦችን፣ ቅመማቅመምን፣ ባህላዊ እቃዎችን ወዘተ. ለመሸጥ በአጎራባች ከተሞች የሚገኙ ነጋዴዎች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡

### 6.2.6 ጉብኝት

የሙዳ በዓላት የአከባበር ስርዓትን ለመመልከትና ስፍራውን ለመጎብኘት ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር ቱሪስቶች ይመጣሉ፡፡ ወደ ስፍራው የሚመጡ ጎብኚዎች በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎችን፣ ጥንታዊ የውኃ ኩሬዎችን፣ የተለያዩ ቅርጻቅርጽ ያለበትን ዋሻ፣ የሙዳ በዓላትን የአከባበር ስርዓቶችና የአካባቢውን ማህበረሰብ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች ይመለከታሉ፡፡ በመካነ ቅርሱ ለቱሪስት መስህብ የሚሆኑ በርካታ ቁሳዊ፣ ቃላዊና መንፈሳዊ ሀብቶች አሉ፡፡ ነገር ግን ስፍራውን ለመጎብኘት የሚመጡ ቱሪስቶች የሚያርፉበት ሆቴል ወይም ሎጅ ባለመኖሩ ሁሉም ቱሪስቶች የሚያርፉት በጊዜያዊነት በተዘጋጀላቸው ማረፊያ ቤት ነው፡፡ ይህ የቱሪስት ማረፊያ ቤት ለመካነ ቅርሱ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የተሰራ ቢሮ ነው፡፡

በስፍራው የእንግዳ ማረፊያ፣ የመብራት አገልግሎት፣ የንጹህ ውኃ አቅርቦት፣ ሆቴል፣ አመቺ ትራንስፖርትና አመቺ የመኪና መንገድ አይነት መሰረታዊ ልማቶች የሉም፡፡ የእነዚህ ዋና መሰረተ ልማቶች በመካነ ቅርሱ ባለመኖራቸው ወደ ስፍራው የሚመጣ ቱሪስት ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡

አብዛኛው ቱሪስት ወደ ስፍራው የሚመጣው በሙዳ በዓላት ወቅት ነው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት በስፍራው የሚገኝ ሕዝብ ቁጥር በርካታ በመሆኑ በቱሪስቶች ግላዊ ምቾት ላይ አልፎአልፎ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር በመረጃ ስብሰባዬ ወቅት ለመታዘብ ችያለሁ፡፡ ከእነዚህ ትዝብቶቼ መካከል በመስከረም ወር፣ 2008 ዓ.ም በሙዳ በዓል ወቅት ቱሪስቶች በሄሊኮፕተር ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ ሄሊኮፕተሯ እንዳረፈች ለበዓሉ የተሰበሰበው ሕዝብ ሄሊኮፕተሯን ለማየት ወደ አይሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ይሮጣል፡፡ ይህ የሕዝቡ ሁኔታ በሄሊኮፕተሯ ውስጥ ያሉትን ቱሪስቶች ለከፍተኛ ድንጋጤ ዳረጋቸው፡፡ በሁኔታው በመደናገጣቸውም ከሄሊኮፕተሯ መውረድ

በመፍራታቸው ወደ መጡበት በፍጥነት ለመመለስ ተገደዋል፡፡ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች በበዓላት ወቅት የተለመዱ እንደሆኑ መረጃ ሰጪዎቹ ገልጸውልኛል፡፡[127]

## 6.2.7 ሕገ-ወጥ ተግባራት

በበዓላት ወቅት በርካታ ሕዝብ ስለሚመጣ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሕገ-ወጥ ተግባራትን ለመፈጸም የሚመጡ ግለሰቦች አሉ፡፡ በስፍራው ከሚከናወኑ ሕገ-ወጥ ተግባራት መካከል የአልኮል መጠጥ ሽያጭ፣ የሺሻ ንግድ፣ ስርቆት፣ የወሲብ ንግድና የጦር መሳሪያ ሽያጭ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህን ተግባራት በመካነ ቅርሱ አካባቢ መፈጸም በጥብቅ የተከለከለ ቢሆንም አልፎአልፎ በድብቅ ይፈጸማሉ፡፡ ለእነዚህ ሕገ-ወጥ ተግባራት ተሳታፊ የሆኑ ግለሰቦችን ለመቆጣጠር የመካነ ቅርሱ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ የወረዳውና የቀበሌው አስተዳደር አካላት፣ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የኦሮሚያ ክልል ልዩ የፖሊስ ኃይልና የአናጂና ቀበሌ ነዋሪዎች ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

በእነዚህ አካላት ጥረትም ችግሩ ከአመት ወደ አመት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች በተለያዩ አካላት ሽፋን እንደሚሰጣቸው መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡[128] ሕገ-ወጥ ተግባራትን ሽፋን ከሚሰጡ አካላት መካከል መንፈሳዊ ተጓዦችን ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ይዘው የሚመጡ የአገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ሹፌሮችና ረዳቶች እንዲሁም ለንግድ የሚመጡ ግለሰቦች  በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## 6.3 የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ያለው ባህርይ

ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ በዓላትን ለማክበር የሚካሄድ መንፈሳዊ ጉዞ የራሱ የሆኑ ልዩ ባህርያት አሉት፡፡ መንፈሳዊ ጉዞዎች ካላቸው ባህርይ አንጻር በተለያዩ መስፈርቶች መመደብ ይቻላል፡፡ እነዚህን መስፈርቶች Stoddard (1997፡57) ከጉዞው ርቀት፣ ከጉዞው ድግግሞሽ፣ ከጉዞው የእንቅስቃሴ ሂደት፣ መንፈሳዊ ቦታው ከሚገኝበት መልክዓምድራዊ አቅጣጫ፣ የመንፈሳዊ ቦታው ጠቃሚነት፣ የመንፈሳዊ ተጓዦች አነሳሽ ምክንያትና ከመንፈሳዊ ተጓዦች ባህርያት በሚሉ መስፈርቶች በሰባት ይከፍላቸዋል፡፡

---

[127] - አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 10፣ 2008 ዓ.ም፡፡
[128] - ስማቸው እንዲገለጽ ፍቃደኛ ያልሆኑ መረጃ ሰጪ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 13፣ 2008 ዓ.ም፡፡

በእነዚህ የመክፈያ መስፈርቶች አንጻር የድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ያለው ባህርይ እንደ መንፈሳዊ ተጓዡ ማንነት የሚለያይ ነው፡፡ ይህም ለምሳሌ ተጓዡ ከሚነሳበት ቦታ፣ ወረዳ፣ ክልል ወይም አገር መሰረት በማድረግ ከርቀት አንጻር አካባቢያዊ፣ አገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ብለን በመስፈርት መለየት እንችላለን፡፡ ከድግግሞሽ አንጻር ደግሞ መንፈሳዊ ተጓዡ ወደ ስፍራው ከሚሄድበት አንጻር በተደጋጋሚ፣ በአመትና አልፎአልፎ በሚል፣ ከጉዞው እንቅስቃሴ ሂደት አንጻር በአንድነት ወይም በተመሳሳይነት፣ በክብና በቅደምተከተል በሚል መመደብ ይቻላል፡፡

Punkhurst (1994፡938-942) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አስር ቦታዎች ከሚካሄዱ መንፈሳዊ ጉዞዎች በመነሳት፣ ጉዞዎቹ ያላቸውን ባህርይ በአራት ይመድባቸዋል፡፡ ከእነዚህ ባህርያት መካከል የተለያየ ብሔር ያላቸውን ሰዎች በአንድ የሚሄዱበት፣ የፖለቲካ ድንበርን (የዓለምአቀፍ ወይም የአገር ድንበር) በመሻገር የሚሄዱበት፣ የተለያየ ኃይማኖት ያላቸው ሰዎች በአንድ የሚሄዱበት ናቸው፡፡ ከተለያየ ኃይማኖት፣ ብሔርና ቋንቋ ያላቸውና የኃይማኖትና የብሔር ድንበርን እንዲሁም ዓለምዓፍና አገራዊ ድንበርን በመሻገር ግለሰቦች በጋራ መንፈሳዊ ጉዞ ከሚያደርጉባቸው ቅዱስ ስፍራዎች መካከል አንዱ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መሆኑን Punkhurst (1994፡939) ይገልጻል፡፡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና፣ የክርስትና የዋቄፈና ኃይማኖት ወይም የሌላ ኃይማኖት ተከታዮች ለአምልኮ ይሄዳሉ፡፡

በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የተለያዩ የኃይማኖት ተከታዮችና የውጭ አገራት ዜጎች ወደ ድሬ መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ በኃይማኖት፣ በጾታ፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በዜግነት፣ በመደብና በሌሎች ምክንያቶች የተለያዩ ግለሰቦች በጋራ የሚያደርጉት ነው፡፡ ይህ ደግሞ መንፈሳዊ ጉዞው የተለየ ባህርይ እንዲይዝ ምክንያት ሆኗል፡፡ ባህርያቱም የተለያየ የኃይማኖት ዳራ ያላቸውን ኢትዮጵያውያንን በአንድ ስፍራ ያገናኛሉ፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያየ ብሔር ያላቸው ቡድኖች አንድ ላይ ያሰባስባሉ እንዲሁም ፓን-ኢትዮጵያን ያሳያሉ፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎችና ከአገር ውጪ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ ስፍራው ይመጣል፡፡ ይህም የተለያዩ የአገሪቷ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የውጭ አገር ዜጎች በአንድ ስፍራ እንዲገናኙ ያስችላል፡፡ ይህ ሁኔታም ለባህል

ልውውጥ፣ ለመረጃ ልውውጥ፣ ለእርስበርስ ትውውቅ፣ ለእርስበርስ መከባበርና የአገር አንድነት እሳቤ ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። የሙዳ በዓላትን ለማክበር የእስልምና፣ የክርስትና የዋቄፈና እንዲሁም ሌሎች የተለያየ የኃይማኖት ዳራ ያላቸው ግለሰቦች ወደ ስፍራው ይመጣሉ። ስፍራው የተለያየ የኃይማኖት ዳራ ያላቸው ግለሰቦች በጋራ መንፈሳዊ ስርዓት የሚፈጽሙበት በመሆኑ ልዩ ባህርይ እንዲኖረው አድርጎታል። ስፍራው የሁሉም ኃይማኖት ተከታዮች የጋራ ነው። ሼኽ ሁሴን የሁሉም እንደሆኑና ስማቸውን ለጠራ ሰው ሁሉ ደራሽ ናቸው ተብሎ ይታመናል።

ለሙዳ በዓል ወደ ስፍራው የሚመጣ ሕዝብ የተለያየ የኢኮኖሚ፣ የትምህርት፣ የስልጣን፣ የኃይማኖትና የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ያለው ነው። ይህ ልዩነት በመንፈሳዊ ተጓዦች መሃል ጎልቶ እንዳይወጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል። ሁሉም መንፈሳዊ ተጓዥ አቅሙ በፈቀደ መጠን ከሌሎች ሰዎች ጎልቶ እንዳይታይ፣ ያለው የኢኮኖሚ፣ የትምህርትና የስልጣን ደረጃ በሌሎች ሰዎች ላይ የስነ-ልቡና ተጽዕኖ እንዳይፈጥር በአለባበሱ፣ በአነጋገሩ ወይም በሌሎች መልኮች ጥረት ያደርጋል።

ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በአብዛኛው ተመሳሳይ አለባበስ፣ ድርጊትና ባህርይ እንዳላቸው በመስክ ቆይታዬ አስተውያለሁ። ይህ መሆኑ ምናልባት ከሌላው የመመሳሰል አስተሳሰብ የፈጠረው ስሜት እንደሆነ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል። ለበዓል የሚመጡ ሰዎች በጋራ ምግብ የመመገብ ግዴታ አለባቸው። ማንኛውም መንፈሳዊ ተጓዥ ብቻውን ምግብ እንዲበላ አይፈቀድም። ይህም አስተሳሰብ ሁሉም ያለውን ተካፍሎ እንዲበላ፣ የመከባበርና የመረዳዳት ስሜት እንዲኖር፣ የመካፈል ስሜት እንዲጎለብትና የእኩልነት ስሜት እንዲዳብር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

መንፈሳዊ ተጓዦችን በማሳፈር የሚጓዙ መኪናዎች ወደ ስፍራው ጉዞ ሲያደርጉ ወደ ድሬ እየሄዱ መሆናቸውን የሚገልጹ ልዩ ልዩ ምልክቶችን በማድረግ ነው። ከእነዚህ ምልክቶች መካከል በመኪናው ፊት ለፊት ላይ የፌዴራል ወይም የኦሮሚያ ክልል ሰንደቅ ዓላማን ወይም ሁለቱንም ሰንደቅ ዓላማዎች በአንድ ላይ በማድረግ ወይም በመኪናው አናት ላይ በእንጨት በማሰር እንዲውለበለብ በማድረግ ነው። ይህም ለበዓል እየሄዱ መሆናቸውንና ያሳፈሩት ተጓዥ ለመንፈሳዊ ጉዞ እንደሚሄድ ለመግለጽ ነው።

መንፈሳዊ ተጓዦችን ያሳፈረ መኪና ፊት ለፊቱ ላይ የደንቄ በትር ይሰካል፡፡ በመኪናም ይሁን በእግር ጉዞ ወደ ስፍራው የሚሄድ መንፈሳዊ ተጓዥ ሁሉ የደንቄ በትርን በእጁ ይይዛል፡፡ የደንቄ በትር የሼኽ ሁሴን ምልክት ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪነት ምልክት ነው፡፡ ደንቄ ልዩ መንፈሳዊ ኃይል ያለው በትር ነው፡፡ ደንቄ የወንድማማችነት ቃል ኪዳን ነው፡፡ የደንቄ በትር የሰላም ትዕምርት ነው፡፡ በጉዞ ወቅት ደንቄ እንደነጭ ባንዲራ የሰላም ተጓዥ ምልክት ነው፡፡ ተጓዡም የሰላም ተጓዥ መሆኑን ለመግለጽ ደንቄ ይይዛል፡፡ ይህን የደንቄ በትር የያዘ ግለሰብ ወይም በፊትለፊቱ ያደረገ መኪና የሰላም ተጓዥ ነው፡፡ በመሆኑም የደንቄ በትርን የያዘ ማንኛውም ግለሰብ የሚቃጣበት አደጋ የለም፡፡ የሚፈልገው ሁሉ ይደረግለታል፤ ልዩ እንክብካቤም ይቸረዋል፡፡




*ፎቶ፤17፣ ፊት ለፊቱ ላይ የደንቄ በትር የተሰካበትና ከላይ የሼኽ ሁሴን የቁልምጫ ስም የሆነውን "ባረ ባሌ" (የባሌው ባሕር) የሚል ጽሑፍ የለጠፈ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚጓዝ መኪና፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

መኪናዎቹ ወደ ድሬ ሲጓዙ ከመኪናቸው የድምጽ ማጉያ በከፍተኛ ድምጽ የሚያሰሙት የባሮ፣ የሹቢሳ፣ የአቶረራ፣ የሰርመዴና ሌሎች መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ሌላው የመለያ ምልክት ነው፡፡[129] መንፈሳዊ ተጓዦቹ ለሚቆዩባቸው ቀናት የሚሆን የእህል ዱቄት፣ ማብሰያ እንጨት፣ የማብሰያ ዕቃዎች፣ የስጦታ እህል፣ በግ፣ ፍየል፣ አልባሳት ይዘው ይመጣሉ፡፡ በመሆኑም ከደንቄ በትር፣ ከሰንደቅ ዓላማና ከመንፈሳዊ ሙዚቃ በተጨማሪ በመኪናው የእቃ መጫኛ ላይ

[129] - የእነዚህን መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ምንነትና ባህርይ በምዕራፍ 8 ተብራርተዋል፡፡

የሚጫኑ ዕቃዎች በራሳቸው ወደ ስፍራው የሚደረጉ ጉዞዎችን ከሌሎች ጉዞዎች መለያ መንገዶች ናቸው፡፡

በቡድን ተሰባስበው የመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ መካነ ቅርሱ መቃረባቸውን የሚያመልክት ዛፍ አለ፡፡ ይህ ዛፍ "ሐሎ ሐምዳ" በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡ ሐሎ ግራር ማለት ሲሆን፣ ሐምዳ ደግሞ ምስጋና ማለት ነው፡፡ የዛፉም ሙሉ ስም ምስጋና ማቅረቢያ ግራር ማለት ነው፡፡ ይህ የሐሎ ሐምዳ ዛፍ የሚገኘው ከመካነ ቅርሱ በግምት 4 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ነው፡፡ በእግር፣ በእንሰሳና በመኪና የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በሐሎ ሐምዳ ዛፍ በሚገኝበት ስፍራ ሲደርሱ "ፈጣሪ እንኳን በሰላም አደረስከን" በማለት የምስጋና ስግደት ("ሶላተል-ሹክር") ይሰግዳሉ ወይም "አልሐምዱሊላሂ" በማለት ለፈጣሪ ምስጋና ያቀርባሉ፡፡ ሐሎ ሐምዳ ወደ ቅዱስ ስፍራ የመግባት ምልክት ነው፡፡ ከዓለማዊ ሕይወት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት መሸጋገሪያ ድልድይ ነው፡፡ የገነት መግቢያ ምልክት ነው፡፡ እራስን ከዓለማዊነት ወደ መንፈሳዊነት የመቀየሪያ ድንበር ነው፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች በሐሎ ሐምዳ ስፍራ ደርሰው ከሰገዱ በኋላ የሰላሞ መንፈሳዊ ሙዚቃ ዜማን በሕብረት ማዜም ይጀምራሉ፡፡ የሰላሞ ዜማ በስፍራው መድረሳቸውን ለሼኽ ሁሴን የሚነግሩበት፣ በሼኽ ሁሴን ቅዱስ ስፍራ በሰላም በመድረሳቸው ደስታቸውን የሚገልጹበት፣ በሰላም በዓሉን እንዲያከብሩ የሚጠይቁበትና ሁሌም ከስፍራው እንዳይለዩ የሚለምኑበት ነው፡፡ ሰላሞ ሼኽ ሁሴንን የሚያወድስ ዜማ ነው፡፡ የሰላሞ የውዳሴ ዜማ በአንድ ከዋኝ መሪነት የሚቀርብ ነው፡፡ የዜማው መሪ የሰላሞ አንድ ስንኝ (መስመር) ብሎ ሲጨርስ ሌሎቹም ተቀብለው በጋራ መሪው ያለውን በከፍተኛ ድምጽ ይደግማሉ፡፡ የሰላሞ ዜማ ግጥም የሚከተለው ነው፡፡

Allahu maraa Sheikh Huseeni…. hooo
Aabbiyyo dhufne ufitti nu fudhadhaa
Hoo… hoo.. Sheikh Huseenni… hooo
Guutuu biyaa guutu walitti deebinee Sheikh Huseenihoo
Hoo… hooo Sheikh Huseeni….hooo
Allahu maraa Sheikh Huseeni….hooo

Ulfaatan ulfaata Sheikh Huseeni….hooo

Hoo … Hoo … Sheikh Huseeni….hooo

Allah maraa Sheikh Huseeni….hooo

Isini wayyuu namni keesan wayuu Sheikh Huseeni…. hooo.

ትርጉሙ፡-

አላህ ሆይ ለሼኽ ሁሴን ቸሩ ምህረትህን ለግሰው

አባታችን በስፍራዎ ደርሰናል፣ በጥሩ አቀባበል ተቀበሉን

ሆ… ሆ…. ሼኽ ሁሴኒ…..ሆ

ወደሀቅ ስፍራ ተመለስን ሼኽ ሁሴኒ….ሆ

ሆ…..ሆ….ሼኽ ሁሴኒ…..ሆ

አላህ ሆይ ለሼኽ ሁሴን ቸሩ ምህረትህን ለግሰው

አንተና ያንተ ተከታዮች የተመረጡ ናቸው ሼኽ ሁሴኒ….ሆ

በማለት በህብረት እያዜሙ ጉዟቸውን ወደ መካነ ቅርሱ ያደርጋሉ፡፡[130]

ለመንፈሳዊ ጉዞ ወደ ስፍራው የሚመጡ ሰዎች እንዳይፈጽሟቸው የሚከለከሉ ድርጊቶች አሉ፡፡ እነዚህ ክልክል የሆኑ ድርጊቶችም ወደ ስፍራው የሚካሄድ መንፈሳዊ ጉዞ መገለጫ ባህርያት ናቸው፡፡ እነዚህም ክልከላዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ማንኛውም መንፈሳዊ ተጓዥ በመካነ ቅርሱ ውስጥና አካባቢው ከትዳር አጋርም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር የወሲብ ግንኙነት መፈጸም ክልክል ነው፡፡ ለመንፈሳዊ ጉዞ ወደ ስፍራው የመጣ ሰው ግጭት (ጠብ) ውስጥ መግባት፣ የሰው ንብረት መስረቅ፣ አንዱ ሌላውን አለማክበርና መሰል ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን መከወን ክልክል ነው፡፡

አልኮልነት ያላቸው መጠጦችን መጠጣት፣ ይዞ መምጣት ወይም መሸጥ ክልክል ነው፡፡ የሺሻ እቃ ይዞ መምጣት ወይም ማጨስ ክልክል ነው፡፡ በመካነ ቅርሱ ሺሻ ማጨስ ቢከለከልም ሲጋራ ማጨስ ይፈቀዳል፡፡ የወር አበባ እያየች ያለች ሴትና በሰውነቱ ላይ ያልጠገገ ቁስል ያለበት ግለሰብ ወደ ገሞዎቹና በግምብ ወደ ታጠረው ግቢ መግባት ክልክል ነው፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ወድቆ የሚገኝን ማንኛውንም ገንዘብና ንብረት መውሰድ ክልክል ነው፡፡

---

[130] - በመካነ ቅርሱ ለሙዳ በዓል ከቀረበ መንፈሳዊ ሙዚቃ የተወሰደ፡፡

የጠፋ ንብረትን ያገኘ ሰው በግንብ በታጠረው መግቢያ ፊት ለፊት የሚገኝና ‘ቂልጡ ቶሂዳ’ በሚል ስያሜ በሚጠራ ትልቅ ዛፍ ስር የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡ ቂልጡ በኦሮምኛ ሾላ ማለት ነው፡፡ ቶሂዳ የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው ‘ቶሂድ’ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ፈጣሪ አንድ ነው እንደማለት ነው፡፡ ይህ የሾላ ዛፍ ስያሜውን ያገኘበት ምክንያት ሼኽ መሐመድ ቲልማ ቲልሞ በስፍራው በመጡበት ወቅት በስፍራው የሚኖርን ሕዝብ የአምላክን አንድነት ለማስተማር ሾላው ስር በመቆም “ቶሂድ- ቶሂድ -ቶሂድ” ይላሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ዛፉ ቂልጡ ቶሂዳ ተባለ፡፡[131] በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ የሚገኘው ቂልጡ ቶሂዳ የድሮው አርጅቶ ከወደቀ በኋላ፣ ከዛሬ 15 ዓመት በፊት በቦታው ላይ የተተከለ ነው፡፡



*ፎቶ 18፣ ወድቆ የተገኘ ዕቃ የሚቀመጥበት የቂልጡ ቶሂዳ ዛፍ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)*

የእስልምና ኃይማኖት በመካ ካዕባ አካባቢ በነብዩ መሐመድ አማካኝነት ከመስፋፋቱ በፊት የወደቀ እቃ የሚሰቀልበት የሾላ ዛፍ በስፍራው ይገኝ እንደነበር O’Leary (1927፡195) ይገልጻል፡፡ የሾላ ዛፉ ስያሜም “ዳት አንዋት” ይባላል፡፡ ትርጉሙም “የእቃ መስቀያ ዛፍ” ማለት ነው፡፡ በመካ ካዕባ አካባቢ ይገኝ በነበረው የሾላ ዛፍ መንፈሳዊ ጉዞ ይደረግበት እንደነበር፣ የእስልምና ኃይማኖት ሲስፋፋ ዛፉ መቆረጡንና ዛፉ በተቆረጠበት ስፍራ መስኪድ እንደተገነባ Ibn Ishaq (1955፡53) ይገልጻል፡፡

---

131 -ሼኽ መሐመድ ሼኽ ኢድሪስ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 26 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

በኢትዮጵያም የክርስትና ኃይማኖት ሲስፋፋ ቀደም ሲል የኃይማኖት ማዕከልና መንፈሳዊ ጉዞ ይደረግባቸው የነበሩ ዛፎች ተቆርጠው በምትካቸው ቤተክርስቲያናት መገንባታቸውን Doresse (1959፡22) ይገልጻል፡፡ ንጉስ ላሊበላ በአምባ ግሸን ተራራ ላይ የነበረና የማምለኪያ ስፍራ የነበረን ዛፍ ቆርጠው በምትኩ ቤተክርስቲያን እንደገነቡ፣ በአክሱም ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን መግቢያ ላይ ክርስቲያኖች የቆሸሹ ልብሶችን በንጹሕ ልብስ የሚቀይሩበትና የቆሸሸ ልብሳቸውን አስቀምጠው ወደ ቤተክርስቲያን የሚገቡበት የሾላ ዛፍ እንዳለ Doresse (1959) በማሳያነት ይገልጻል፡፡

የክርስትናም ሆነ የእስልምና ኃይማኖት በአገራችን ሲስፋፉ የመጀመሪያ ትኩረታቸው በአካባቢው ባለ ነባር ኃይማኖት መተግበሪያ የነበሩና የተከበሩ የእምነት ማዕከላት ናቸው፡፡ እነዚህ ማዕከላትን መቆጣጠርና ማውደም የአዲሱ ኃይማኖት ተቀናቃኝ የሆነ ኃይልን በቀላሉ ለማድከም ያስችላል፡፡ የነባሩን ኃይማኖት አሻራ በማጥፋት በአዲሱ ኃይማኖት መተካት ማህበረሰቡ በነባሩ ማዕከል ላይ የሚኖረውን ትውስታ ያጠፋል፤ የአዲሱን ኃይማኖት የበላይነትም ያረጋግጣል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኘውም የቁልጡ ቆሂዳ ዛፍ በስፍራው የእስልምና ኃይማኖት ሙሉለሙሉ ተቋርጦ በነበረበት ወቅት የአካባቢው ሕዝብ አምልኮ ይፈጽምበትና መንፈሳዊ ጉዞ ያደርግበት የነበረ ሊሆን ይችላል፡፡ ዛፉም በወቅቱ የነበረ አምልኮ ቅሪት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ የመካነ ቅርሱና የመንደሩ ምስረታ ዛፍን ማዕከል ያደረገ ('Tree centric') ነው ማለት ነው፡፡

ለዚህ መላምት ሌላው ማሳያ በመካነ ቅርሱ ከሚገኘው የቁልጡ ቆሂዳ ዛፍ በስተግራ በኩል ለብቻ በታጠረ ግቢ ውስጥ የሚገኝና ጀጀባ መውሊድ የሚባል ስፍራ አለ፡፡ ይህ ስፍራ የመውሊድ በዓል የሚከበርበት ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ የሚገኝና የመውሊድ በዓል በስሩ የሚከበርበት ትልቅ የቁልጡ ዛፍ አለ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች መካነ ቅርሱ መዳረሻ አካባቢ ባለ ሐሎ ሐምዳ ዛፍ ስር ይሰግዳሉ፣ ለሼኽ ሁሴን ምስጋና ማቅረብ ይጀምራሉ፡፡ በዛፍ ስር ስርዓተከበራዎችን መፈጸም በነባር ኃይማኖቶች እንጂ በእስልምና ኃይማኖት የተለመደ አይደለም፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚታየው በዛፎች አጠገብ የሚከወን ስርዓትና ዛፎች ያላቸው ልዩ ሚና ምናልባት የዋቄፈና ኃይማኖት ስርዓተከበራዊ ቅሪት መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡

# 7. ከሙዳ በዓል በፊት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች

የሙዳ በዓላት የሚከበሩባቸው ቀናት ከመድረሳቸው ቀደም ብሎ የተለያዩ ክዋኔዎች ይፈጸማሉ፡፡ እነዚህ የቅድመ ሙዳ የዝግጅት ክዋኔዎች የሚጀመሩት ከበዓሉ 6 ወር ቀደም ተብሎ ነው፡፡ እነዚህ ክወናዎች የተለያዩ ሲሆኑ የራሳቸው የሆነ ስርዓትና ቅደም ተከተል አላቸው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን ከሚካሄዱ ቅድመ ሙዳ ክወናዎች መካከል ሀሽ የማዘጋጀት፣ ሕንጻዎችን ሀሽ የመቀባት፣ ጀዋራ የማዘጋጀት፣ ደገሌዎችን የማሰናዳት፣ ደንቄ የማዘጋጀትና መንፈሳዊ ተጓዦችን የመቀበል ስርዓቶች ናቸው፡፡

Gluckman (1962፡4) "ስርዓተከበራዎች ቋሚና ዘልማዳዊ ቅርጾችን መሰረት በማድረግ በቡድን የሚተገበሩ ናቸው" ይላል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ እነዚህ ቅድመ ሙዳ ክወናዎች ሁል ጊዜ ቋሚ፣ ተደጋጋሚና በቡድን የሚከወኑ ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ እነዚህ የቅድመ ሙዳ ስርዓተከበራዎች በተናጠል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 7.1 የሀሽ አዘገጃጀት ስርዓት

ለሙዳ በዓል ቅድመ ዝግጅት ከሚከወኑ ስርዓተከበራዎች መካከል ሀሽ ማዘጋጀት አንዱ ነው፡፡ 'ሀሽ' የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን፣ ትርጉሙም ነጭ ማለት ነው፡፡ ሀሽ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎች የሚቀቡትና ነጭ ቀለም ያለው የኖራ ዱቄት ነው፡፡ የሙዳ በዓል የሚከበርበት ቀን ከመድረሱ ከ6 ወር በፊት የተለያዩ ኪነ-ህንጻዎችን ለማስዋብ የሚያገለግለውን የሀሽ ዱቄት የማዘጋጀት ስርዓት ይካሄዳል፡፡ የሀሽ ዱቄት የሚዘጋጀው በአመት አንድ ጊዜ ነው፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎችም ሀሽ የሚቀቡት ለሐጅ የሙዳ በዓል ብቻ ነው፡፡

ሀሽ የሚዘጋጀው ከእንጨትና ከድንጋይ ነው፡፡ ሀሽ ለማዘጋጀት የሚያገለግለው እንጨት 'ዶዶቲ' ይባላል፡፡ ለሀሽ ዝግጅት የሚያገለግለው ድንጋይ ቀላል ክብደት፣ ጠቃጠቆና ነጭ ቀለም ያለው ነው፡፡ ይህ ድንጋይ የሚገኘው በአይናገኜ ገደል ውስጥ ነው፡፡ ሀሽ የሚዘጋጅበት የራሱ ጊዜ አለው፡፡ ይህም የዛህራ ገልገላ ኀበና የሙዳ በዓል ካለፈ ከ10 እስከ 15 ቀናት በኋላ ነው፡፡ ገሞዎቹን ሀሽ የመቀባት ስርዓት የሚካሄደው የዛህራ በዓል በተከበራ በ6^ኛው^ ወር ላይ ለሚውለው የሐጅ በዓል ነው፡፡ የሀሽ ዝግጅቱ 6 ወር የሚፈጅ በመሆኑ ስራው የዛህራ ገልገላ ኀበና የሙዳ በዓል እንዳለፈ ይጀመራል፡፡

የዛህራ ገልገላ ጎበና የሙዳ በዓል ተከብሮ እንዳለፈ መስኪድ ላይ “በዚህ ቀን የሀሽ ስራ ይጀመራል፡፡” ተብሎ ለህዝቡ ይነገራል፡፡ የሀሽ ስራ የሚጀመረው ማክሰኞ እለት ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ማክሰኞ የሼኽ ሁሴን መታሰቢያ እለት በመሆኑ ነው፡፡ በሀሽ ዝግጅት ወቅት መጀመሪያ የሚሰራው ድንጋዩን ማዘጋጀት ነው፡፡ ከድንጋዩ ስራ ቀጥሎ የዶዶቲ እንጨት የማዘጋጀት ስራ ይሰራል፡፡ ድንጋዩን ለማዘጋጀት ማክሰኞ እለት ጠዋት የአናጂና ቀበሌና የአካባው ነዋሪ በግምብ አጥሩ ዋና መግቢያ ፊት ለፊት በሚገኘውና ዶቆ ከራ (Dhooqqoo karraa) በሚል ስያሜ የሚታወቀው ሰፊ ስፍራ ይሰባሰባል፡፡

የሀሽ ዝግጅትን ስራ የሚመሩትና ስራውን የሚከታተሉት በመካነ ቅርሱ እድሳት ላይ ሀላፊነት ያላቸው የኢማም ቤተሰቦች፣ የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎችና ከነዋሪዎች የተውጣጡ ኮሚቴዎች ናቸው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎችን ለማደስ፣ ሀሽ እንዲዘጋጅ ለማዘዝ፣ የሀሽ ዝግጅትን ለማስተባበርና ስርዓቱን ለመምራት የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ ልጅ የሆኑት የሼኽ ቡሽራ ቤተሰቦች ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ለሀሽ ዝግጅት ስራ አስተባባሪ እንዲሆኑ ከነዋሪዎች ኮሚቴ ይዋቀራል፡፡ የሼኽ ቡሽራ ቤተሰቦችም ከነዋሪው ከተመረጡ ኮሚቴዎች ጋር በመነጋገር የሀሽ ዝግጅት የሚጀመርበትን ቀን ወስነው ለህዝቡ ያሳውቃሉ፡፡

የሀሽ ዝግጅት በሚጀመርበት እለት በዶቆ ከራው ለተሰበሰበው ህዝብ በሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ መስኪድ ኢማም አማካኝነት ምረቃትና ዱዓ (ፀሎት) ይደረጋል፡፡ ኢማሙ ይህን ስራ ለመስራት በፍላጎት ስለመጡ፣ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎችን ለመጠበቅ በሚያደርጉት ስራ፣ መንፈሳዊ ተጓዦችን ተንከባክበውና አስደስተው በመመለሳቸው እንዲሁም በአካባቢው ሰው የተሰሩ ሌሎች መልካም ስራዎችን በማንሳት ህዝቡን ያመሰግናሉ፤ ይመርቃሉ፡፡ ለሚቀጥለው አመትም ከመሃላቸው ማንም ሰው ሳይለይ ለሀሽ ዝግጅት እንዲገናኙ፣ ለመጪው አመት አላህ በሰላምና በጤና እንዲያደርሳቸው፣ ያሰቡትን እንዲያሳካላቸው፣ የሼኽ ሁሴን ከራማ እንዳይለያቸው ኢማሙ ለህዝቡ ዱዓ ያደርጋሉ፡፡

የምርቃት ስርዓቱ እንደተጠናቀቀ የዶዶቲ እንጨት ዝግጅት የሚጀመርበትን ቀን ያሳውቃሉ፡፡ የኢማሙ ምርቃትና ዱዓ ከተጠናቀቀ በኋላ ህዝቡ ድንጋዩን ለማምጣት ወደ አይናገኜ ገደል ይሄዳል፡፡ ድንጋዩ የሚገኝበት የአይናገኜ ገደል ከዶቆ ከራው በግምት 3 ኪ.ሜትር ርቀት ሲኖረው መንገዱም ከፍተኛ ዳገትና ቁልቁለት ያለው ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ሁሉም ሰው መሄድ ስለማይችል አቅምና ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ብቻ ይሄዳሉ፡፡ በአብዛኛው ድንጋይ ለማዘጋጀት የሚሄዱት ወጣት ወንዶች ናቸው፡፡

ድንጋዩን ለመልቀም የሚሄዱ ሰዎች ግንባራቸው ላይ ጨርቅ ያስራሉ፡፡ ጨርቁም በሙዳ በዓል ወቅት የሼኽ ሁሴን ገሞ ጣሪያው ከተሸፈነበት በማውረድ በቀጫጭኑ በመቅደድ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ይህን ጨርቅ ግምባራቸው ላይ የሚያስሩት የሼኽ ሁሴንን በረከት ለማግኘት ነው፡፡ ድንጋዩን ለመልቀም ወደ አይናገኜ ገደል ሲሄዱና ድንጋዩን ይዘው ሲመጡ በህብረት ‹ሰላሞ› እያዜሙ ነው፡፡ ሰላሞ ሼኽ ሁሴንን የሚያወድስ ዜማ ነው፡፡ የሰላሞ የውዳሴ ዜማ በአንድ ከዋኝ መሪነት የሚቀርብ ነው፡፡ የዜማው መሪ የሰላሞ አንድ ስንኝ (መስመር) ብሎ ሲጨርስ ሌሎቹም ተቀብለው በጋራ መሪው ያለውን በከፍተኛ ድምጽ ይደግማሉ፡፡ የሰላሞ ዜማ ግጥም የሚከተለው ነው፡፡

Allahu maraa Sheikh Huseeni…. hooo

ትርጉሙ፡-

አላህ ሆይ ለሼኽ ሁሴን ቸሩ ምህረትህን ለግሰው፡፡

ሼኽ ሁሴኒ…..ሆ ማለት ነው፡፡

በአይናገኜ ገደል ውስጥ የሚገኘውን ድንጋይ አንድ ሰው በቀላሉ ሊሸከመው በሚችል መጠን ተፈልጦ ይዘጋጃል፡፡ ድንጋዩንም በሸክም ወደ ዋናው ግቢ ይዘው ይመጣሉ፡፡ መንገዱ ርቀት ያለውና አስቸጋሪ በመሆኑ ድንጋዩን በቀን ቢበዛ ለ3 ወይም ለ4 ዙር ማምጣት ቢቻል ነው፡፡ ከገደሉ ድንጋይ የማምጣት ስራ በአማካኝ 15 ተከታታይ ቀናትን ይወስዳል፡፡ ከገደሉ የመጣው ድንጋይ በአንድ ላይ ለመፍለጥ የሚያመች ቦታ ይሰበሰባል፡፡

በድሮ ጊዜ ድንጋይ ከአይናገኜ ገደል የመሰብሰብ ስራን የሚሰሩት በድሬ ሼኽ ሁሴን የቁርዓን ትምህርት ይማሩ የነበሩ ደረሳዎች (ተማሪዎች) ነበሩ፡፡ በወቅቱ የደረሳዎቹ ቁጥር በርካታ በመሆኑ በትንሽ ቀናት ውስጥ ድንጋዩን መሰብሰብ ይችሉ ነበር፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የደረሳዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ በህዝቡ ጉልበት ይሰበሰባል፡፡ ድንጋዩ በሰው ጉልበት የሚሰበሰብበት ምክንያት መንገዱ መኪና ለማስገባት አመቺ ባለመሆኑ ነው፡፡

ለሀሽ ዱቄት የሚሆነው ድንጋይ ከአይናገኜ ገደል ከተሰበሰበ በኋላ የዶዶቲ እንጨት የመቁረጥ ስራ ይጀመራል፡፡ የዶዶቲ እንጨት የሚገኘው ኩባዩ በሚባል ስፍራ ነው፡፡ ስፍራው ከዶቆ ከራው በግምት 20 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በእለቱም እንጨቱን የሚቆርጡ ሰዎች በዶቆ ከራው ይሰበሰባሉ፡፡ ስፍራው እርቀት ስላለውና መመላለስ ስለማይቻል አቅምና ፍላጎት ያላቸው ወንዶች ብቻ ይሄዳሉ፡፡ እንጨት ለመቁረጥ ለሚሄዱ ሰዎች ምርቃትና ዱዓ ይደረግላቸዋል፡፡

እንጨቱን ለመቁረጥ የሚሄዱ ሰዎችም በህብረት ሰላሞ እያሉ ይሄዳሉ፡፡ የዶዶቲ እንጨትን ለመቁረጥ በአማካኝ 20 ቀናት ይፈጃል፡፡ ስፍራው ርቀት ስላለውና መመላለስ ስለማይቻል ወደ ስፍራው የሚሄዱ ሰዎች ለእነዚህ ቀናት ያህል እዛው በመቆየት እንጨቱን ያዘጋጃሉ፡፡ ወንዶቹ እንጨቱን ለማዘጋጀት በሚቆዩባቸው ቀናት ምግብ የምታበስል አንድ ፍቃደኛ የሆነች ሴት አብራቸው ትሄዳለች፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎችም እንጨቱን ለማዘጋጀት ለሚሄዱ ሰዎች ቀለብ የሚሆን እህልና የትራንስፖርት መጪ በማዋጣት ይሰጣሉ፡፡ የዶዶቲ እንጨት ለማዘጋጀት የሄዱ ሰዎች እንጨቱን ለመኪና ጭነት በሚሆን መጠን ቆርጠው ያዘጋጃሉ፡፡ እንጨቱን አዘጋጅተው ሲጨርሱ በጭነት መኪና ወደከራው ያመጣሉ፡፡ ለሀሽ ዝግጅት የሚሆነው የዶዶቲ እንጨት በአማካኝ 8 ዙር (ባጃ) በትልቅ የጭነት መኪና ይጫናል፡፡ እንጨቱን ለማምጣት የሚሆን የመኪና ወጪ የሚሸፈነው በማህበረሰቡ ነው፡፡ ለአንድ ዙር የመኪና ጭነት በአማካኝ 800 ብር ይከፈላል፡፡

እንጨቱ ከመጣ በኂላ በደረጃ በደረጃ ይቆራረጣል፤ ድንጋዩም ይፈለጣል፡፡ ድንጋዩንና እንጨቱን የሚያዘጋጁት የሀሽ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ የሀሽ ዱቄት የሚዘጋጀው ድንጋዩናን እንጨቱን በአንድ ላይ በእሳት በማቃጠል ነው፡፡ በስፍራው ድንጋዩንና እንጨቱን ለማቃጠል የተዘጋጀ ጉድጓድ አለ፡፡ ይህ ጉድጓድ በግምት 3 ሜትር ጥልቀት ሲኖረው በሲሚንቶ የተገነባ ነው፡፡ በጉድጓዱ ውስጥ ድንጋዩ በመጠን በመጠኑ በደረጃ ይደረደራል፡፡ የድንጋዩ ደረጃም ትልቅ መጠን ያላቸው ድንጋዩች ከስር በማድረግ መሃል መሃል እንጨቱን በመደርደር ጉድጓዱ ይሞላል፡፡ የጉድጓዱ አናት በደቃቅ ድንጋይ ይሸፈናል፡፡

ጉድጓዱ በቁመቱ መሃል ላይ መስኮት መሰል ቀዳዳ አለው፡፡ በዚህ ቀዳዳ ነዳጅ (ጋዝ) ይጨመርበትና እሳት ይለኮስበታል፡፡ የተለኮሰውም እሳት በጉድጓዱ ውስጥ የተደረደረውን እንጨትና ድንጋይ ማቃጠል ይጀምራል፡፡ እንጨቱና ድንጋዩ ለተከታታይ 3 ወራት ያህል በእሳት ይቃጠላል፡፡ እሳቱ ሀይለኛ ሙቀት ስለሚፈጥር ወደ አካባቢው ሰውና እንስሳት እንዳይቀርቡ ዙሪያው በአጥር ይከለላል፡፡ ምክንያቱም ሰውና እንስሳ ወደ ጉድጓዱ ቢጠጉ የእሳቱ ነበልባልና ሙቀት ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል፡፡



*ፎቶ፣19፣ የሀሽ ዱቄት ማዘጋጃ ጉድጓድ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

ድንጋዩና እንጨቱ ለ3 ተከታታይ ወራት ከተቃጠለ በኋላ ዝናብ ሲዘንብ እሳቱ እየቀዘቀዘ ሄዶ መጨረሻ ላይ ሙሉለሙሉ ይጠፋል፡፡ እሳቱ ሲጠፋ የተቃጠለው ድንጋይና እንጨት ነጭ የኖራ ዱቄት ይፈጥራል፡፡ ይህ የኖራ ዱቄትም ሀሽ በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡ ድንጋዩና እንጨቱ ተቃጥለው ሀሽ እስከሚፈጥሩ ድረስ የሐጅ የሙዳ በዓል የሚከበርበት ቀን ይቃረባል፡፡

## 7.2 ሀሽ የመቀባት ስርዓት

የሐጅ የሙዳ በዓል ሊከበር 10 ቀናት ሲቀሩት ህንጻዎችን ሀሽ የመቀባት ስራ ይጀመራል፡፡ ሀሽ የሚቀባበት ቀን ለህዝቡ ቀደም ተብሎ ይነገራል፡፡ ሀሽ የመቀባት ስራ የሚጀመረው ማክሰኞ እለት ነው፡፡ በእለቱም ሁሉም ሰው በዶቆ ከራው ይሰበሰባል፡፡ በእለቱ ሁሉም ሰው አቅሙ የፈቀደውን ስጦታ ይዞ ይመጣል፤ ገንዘብ ይሰበሰባል፡፡ የሚሰበሰበውም ገንዘብ ለጫት፣ ለውኃ፣ ለቡና፣ ለእጣንና ለሰንደል መግዣ ያገለግላል፡፡ በዶቆ ከራ አነስተኛ ድግስ ይዘጋጃል፡፡ ምግብ በጋራ ከተበላ በኋላ ቡና ይጠጣል፡፡ የግብዣው ስርዓት እንዳለቀ ሰላሞ ይባላል፡፡ በዶቆ ከራው ላይ የተሰበሰበው ሰው በህብረት ሰላሞ እያለ ሀሽ የመበጥበጥ ስራ ይጀምራል፡፡

ሀሽ የመቀባት ስራ ጉልበት የሚጠይቅ በመሆኑ የሚሰሩት ወንዶች ብቻ ናቸው፡፡ በጉድጓድ ውስጥ ያለውን የሀሽ ዱቄት በሰፌድ እየተዛቀ በማውጣት ወደ በርሜል ውስጥ ይጨመራል፡፡ በርሜሉ ውስጥ ዱቄቱን በውኃ በመበጥበጥ ነጭ ቀለም ያለው ሀሽ ይዘጋጃል፡፡ በድሮ ጊዜ ዱቄቱን በውኃ የሚበጠብጡት በሼኽ ሁሴን ገሞ አጠገብ ለዚህ ስራ ተብለው በተዘጋጁ ክብ የድንጋይ ጉድጓዶች ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በበርሜል ስለሚበጠበጥ የድንጋይ ጉድጓዶቹ አገልግሎት አይሰጡም፡፡



*ፎቶ፡-20፤ በድሮ ጊዜ የሀሽ ዱቄት በውኃ ይበጠበጥበት የነበረ ግምብ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በርሜል ውስጥ የተበጠበጠው ሀሽ አነስተኛ መጠን ባላቸው እቃዎች እየተቀነሰ ህንጻዎቹ መቀባት ይጀምራሉ፡፡ ሀሽ የመቀባት ስራውን የሚያስጀምሩት የሼኽ መሀመድ ቲልማ ቲልሞ መስኪድ ኢማም ናቸው፡፡ ኢማሙ ለተሰበሰበው ህዝብ ምርቃትና ዱዓ ካቀረቡ በኋላ ‹ቢስሚላሂ› ብለው ይቀባሉ፡፡ ኢማሙ ስራውን ካስጀመሩ በኋላ ሁሉም ሰው ህንጻዎቹን መቀባት ይጀምራል፡፡



*ፎቶ፤ 21፤ ኢነሕንጻዎችን ሀሽ በመቀባት ስራ ላይ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎች ሀሽ የሚቀቡት የራሳቸውን ደረጃ በመጠበቅ ነው፡፡ ሀሽ የሚቀቡበትም ቀናት እንደደረጃቸው የተለያየ ነው፡፡ ኪነ-ህንጻዎቹን የመቀባት ስራ ማክሰኞ፣ ረቡዕና ሐሙስ ይከናወናል፡፡ በማክሰኞ እለት በመካነ ቅርሱ ካሉት ኪነ-ህንጻዎች መካከል መጀመሪያ የሚቀባው የሼኽ ሁሴን ገሞ ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን ገሞ የሚቀድምበት ምክንያትም ከሁሉም እሳቸው በክብር ስለሚበልጡ ነው፡፡ ሀሽ የመቀባት ስራ ማክሰኞ የሚጀመርበት ምክንያት ዕለቱ የሼኽ ሁሴን መታሰቢያ በመሆኑ ነው፡፡

የሼኽ ሁሴን ገሞን መቀባት የሚጀመረው ከላይ (ከአናቱ) ነው፡፡ ከእሳቸው ገሞ ቀጥሎ የእሳቸው ልጆች (የመሃመድ ተማምና የፋጡማ) ገሞዎች፣ የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ ገሞና የግቢው አጥር ይቀባል፡፡ እነዚህ ኪነ-ህንጻዎች ማክሰኞ እለት ተቀብተው ይጠናቀቃሉ፡፡ ረቡዕ የሚቀቡ ኪነ-ህንጻዎችም የራሳቸውን ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእለቱም መጀመሪያ የሚቀባው የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ ገሞ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ረቡዕ የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ የመታሰቢያ እለት በመሆኑ ነው፡፡ የእሳቸው ገሞ ተቀብቶ ካለቀ በኋላ ጎምቢሶዎች፣ ገንዳ መስኪዳና የሼኽ መሀመድ ሚልኪ ገሞ ይቀባሉ፡፡

ሀሙስ እለት መጀመሪያ የሚቀባው የሼኽ ሁሴን አባት የሼኽ ኢብራሂም መልካይ ገሞ ነው፡፡ ከአባታተው ገሞ ቀጥሎ የእናታቸው የአዮ ሽምሲያ፣ የሼኽ መሃመድ ሚስኪ፣ የሼኽ መሃመድ ሀጂ አህመድና የሼኽ ዑመር ሼኽ አልይ ገሞዎች ይቀባሉ፡፡ ገሞዎቹን ሀሽ የመቀባት ስርዓት ሲጠናቀቅ፣ አናታቸውን ጨርቅ የማልበስ ስራ ይከወናል፡፡ ከገሞዎቹ መካከል የሼኽ ሁሴን ገሞ ቀድሞ ጨርቅ ይለብሳል፡፡ የጨርቁ መልክ በአብዛኛው አረንጓዴ ነው፡፡ አረንጓዴ ቀለም የአበልቃሲም ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ገሞዎችን የማደስና የመንከባከብ ስራ የሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ግዴታ ነው፡፡ በዚህ ግዴታም ምክንያት ማህበረሰቡ ገሞው ያለውን የሕዋ ማዕከልነት ውክልና ያጠናክራል፡፡ ገሞው ባለው የሕዋ ማዕከልነትም የማህበረሰቡን ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ስነልቡናዊ ሁነቶች ይወስናል፡፡ የማህበረሰቡ አባላትም ገሞውን በማደሳቸውና በመንከባከባቸው ከፈጣሪ፣ ከሼኽ ሁሴን እንዲሁም ከአካባቢው ማህበረሰብ ግብረመልስ (Feedback) እናገኛለን ብለው ያምናሉ፡፡ ግለሰቦች ከፈጣሪና ከሼኽ ሁሴን የሚያገኙት ግብረመልስ ከችግራቸው መዳን፣ ከሕመማቸው መፈወስ፣ በሕይወታቸው ሊያሳኳቸው የሚመኙትን ነገር ማሳከት ወይም በአካባቢው ማህበረሰብ ምርቃትን፣ ምስጋናን ወይም ክብር ማግኘት ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ገሞዎች ራሳቸውን ማዕከል በማድረግ ግለሰብን፣ ማህበረሰብን፣ ሼኽ ሁሴንን እና ፈጣሪን በአንድ ቦታ ያገናኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ ገሞዎቹ በእነዚህ አራት አካላት መካከል የአራትዮሽ የግንኙነት ትስስር (Rectangular relationship) ይፈጥራሉ፡፡ ይህ የገሞዎቹ የአራትዮሽ ትስስር በተጨባጩ ቁሳዊ ዓለም (Physical world) እና በሜታምናባዊ ዓለም (Metaphysical world) መካከል ሕብር (Harmony) የመፍጠር ሚና እንዲኖራቸው ምክንያት ነው፡፡



*ፎቶ፣22፣ የሼኽ ኢብራሂም ገሞ አረንጓዴ ጨርቅ ሲያለብሱ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

ከላይ በፎቶግራፉ እንደሚታየው በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚገኙ ሁሉም ገሞዎች ቅርጻቸው የ"ፒራሚድ" ነው፡፡ ይህ አይነት የፒራሚድ ቅርጽ ያላቸው መካነ ቅርሶችና ቤተመንግስቶች በአፍሪካ በብዛት አሉ፡፡ ይህ የፒራሚድ ቅርጽ ያላቸው መካነ ቅርሶችና ቤተመንግስቶች በናይል ወንዝ አጠገብ በግብጽና በኑቢያ ከሚገኙ የፒራሚድ ግንባታ ቅርጽ የተወሰደ ሊሆን ይችላል፡፡ መካነ ቅርሶችን በፒራሚድ ቅርጽ መስራት የአፍሪካ የኪነሕንጻ ጥበብ መገለጫ ነው፡፡

በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ገሞዎች በወገባቸውና በአናታቸው ላይ ወጣ ወጣ ያሉ ጉጦች አሏቸው፡፡ የገሞዎቹ ጉጦች ከላይ በቀረበው ፎቶግራፍ ላይ በግልጽ ይታያሉ፡፡ እነዚህ ጉጦች ገሞዎቹ በሚታደሱበት፣ ሀሽ በሚቀቡበትና ጨርቅ በሚሸፈኑበት ወቅት ለመወጣጫ የሚያገለግሉ

መሰላሎች እንደሆኑ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡[132] መረጃ ሰጪዎቹ የጉጦቹ አገልግሎት እነዚህ መሆናቸውን ቢገልጹም ከዚህ አገልግሎት በተጨማሪ ልዩ ውክልና ያላቸው ይመስላል፡፡ ይህ ውክልናቸውም የገነት መግቢያ መሰላል ('Ladder to Heaven') ነው፡፡

የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች በስፍራው በሚገኙ የቅዱሳን መካነ መቃብር ላይ ወይም አርፈውበታል በተባለ ቦታ ላይ በተገነቡት የመታሰቢያ ገሞዎች አማካኝነት ከቅዱሳኑ ጋር ይገናኛሉ፡፡ በእነሱም የአማላጅነት ሚና ከሞት በኋላ ነፍሳቸው ወደ ገነት እንድትገባ አማኞች ይለምናሉ፡፡ ይህ የገነት ጉዞም በገሞዎቹ ላይ ባሉት የመወጣጫ ጉጦች ይመሰላል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦችና የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች በጉጦቹ መሰላል አማካኝነት ወደ ገነት ይሄዳሉ፡፡

## 7.3 ጀዋራ የማዘጋጀት ስርዓት

"ጀዋራ" (Jawaaraa) ለመድኃኒትነት የሚያገለግል ቅዱስ አፈር እንደሆነ ይታመናል፡፡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች የጀዋራ አፈርን ሰውነታቸውን በመቀባት፣ በመብላት፣ በዘምዘም (ጸበል) በጥብጠው በመጠጣት፣ ወደ ቤታቸው ወስደው በማስቀመጥ፣ ከብቶቻቸውን በመቀባት ወዘተ. ይጠቀሙበታል፡፡ ለመንፈሳዊ ተጓዦቹ የጀዋራ ቅዱስ አፈር ከህመማቸው ለመፈወስ፣ በረከት ለማግኘት፣ ጤናቸውን ለመጠበቅና ከሚያጋጥማቸው ችግር ለመጠበቅ እንደሚጠቅማቸው ያምናሉ፡፡ የሙዳ በዓል ሲቃረብ የጀዋራ አፈር ተቆፍሮ በገሞዎች ውስጥ ይቀመጣል፡፡ የጀዋራ አፈር የሚቆፈረው ቆርቃ ከሚባል ወንዝ ነው፡፡ የቆርቃ ወንዝ በመካነ ቅርሱ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ከዋናው የግምብ አጥር በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በግምት 3 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የጀዋራ አፈር በዱቄት መልክ፣ በአንኳር፣ በትንንሽ የድንጋይ መጠን እንዲሁም ከፍ ከፍ ባለ የድንጋይ ኮረት መጠን የሚገኝ ነው፡፡

የጀዋራ አፈርን ከቆርቃ ወንዝ የሚያመጡት ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ የጀዋራን አፈርን የመቆፈርና ተሸክሞ የማምጣት ስራ ለሴቶች ብቻ የተፈቀደበት ምክንያትም ስራው ብዙም ጉልበት የማይጠይቅ በመሆኑና የጀዋራ አፈርን ከስፍራው እንዲያመጡ በፈጣሪ የተፈቀደላቸው ሴቶች ብቻ መሆናቸው ነው፡፡[133] ሴቶቹ የጀዋራ አፈሩን ከቆፈሩ በኋላ በጀርባቸው ተሸክመው ያመጣሉ፡፡ ያመጡትንም የጀዋራ አፈር በገሞዎች ውስጥ ይበትኑታል፡፡ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ ገሞዎች መካከል የጀዋራ አፈር የሚበተነው በሼኽ ሁሴንና በሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ

[132] - ሼኽ ኢብራሂም ከዲር፣ አናጺና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 30 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

[133] - ወ/ሮ ቀመሪያ የሱፍ፣ ወ/ሮ ሀሊማ ዑስማንና ሼኽ ቃሲም ሐጂ አወል አናጺና ቀበሌ፣ ነሐሴ 30 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

ገሞዎች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ለመንፈሳዊ ጉዞ ወደ ስፍራው የሚመጡ ሰዎችና ነዋሪዎች ከእነዚህ ገሞዎች ውስጥ ያለውን የጀዋራ አፈር ይጠቀማሉ፡፡

የጀዋራ አፈርን ለመድኃኒትነት እንዲሆን ያደረጉት ሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ እሳቸውም "ይህ ጀዋራ ለሕመም መፈወሻ፣ ቅዱስ አፈር ይሁን፡፡" ብለው ለፈጣሪ ጸሎት አድርገው፤ ተፈቀደላቸው፡፡ ጸሎታቸው ሲፈቀድላቸው ከቆርቃ ወንዝ ሄደው የጀዋራን አፈር አመጡ፡፡ ያመጡትንም አፈር በገሞዎች ውስጥ እንዲቀመጥና ለመድኃኒትነት እንዲያገለግል አደረጉ፡፡[134] ሼኽ መሃመድ የጀዋራን አፈርን በገሞዎች ውስጥ ካደረጉ በኋላ 40 ጊዜ ቁርዓን ቀሩበት፡፡ ቁርዓንን 40 ጊዜ ከቀሩ በኋላ ምራቃቸውን በአፈሩ ላይ ተፉበት፡፡ ይህም አፈሩ ለመድኃኒትነት እንዲያገለግልና እንዲቀደስ ነው፡፡



*ፎቶ፣23፤ የጀዋራ ቅዱስ አፈር፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በፈጣሪ ፍቃድ፣ በሼኽ መሃመድ ጸሎት፣ ቁርዓን መቅራትና በእሳቸው ምራቅ የጀዋራ አፈር ቅዱስ አፈር ሆነ፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮም የጀዋራ አፈር ቅዱስ አፈር እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ ይህ የሼኽ መሐመድ መንፈሳዊ ድርጊት አንድን ቁስ ወደ መለኮታዊ ቁስነት የማሻገር (Cosmological transformation) ሂደት ነው፡፡ በዚህ የሽግግር ሂደት የእሳቸው ምራቅ ለአፈሩ መለኮታዊ ሽግግር ዋና ግብዓት (Cosmic Egg) ነው፡፡ በዚህ የምራቅ ግብዓት አማካኝነት አፈሩ ከነበረው ቀደምት ይዘት፣ ትርጓሜና አገልግሎት በመሻገር ወደ ሌላና አዲስ መንፈሳዊ አገልግሎት ተቀየረ፡፡

---

[134] - አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አንጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 26 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

የጀዋራ አፈር አመድማ መልክ ያለው ሲሆን፣ ሲቀመስ የጥፍጥና ባህሪ አለው። የጀዋራ ቅዱስ አፈር ማንኛውንም ሕመም እንደሚፈውስና ክፉ መናፍስትን እንደሚያባርር ይታመናል። አማኞቹ የጀዋራ አፈርን በመብላት፣ ሰውነትን በመቀባት፣ በዘምዘም በመበጥበጥና በሌሎች የተለያዩ መንገዶች ይጠቀሙበታል። ሁለቱ የሙዳ በዓላት የሚከበሩባቸው ቀናት ሲቃረቡ ለበዓል የሚመጡ ሰዎችና የአካባቢው ነዋሪዎች የጀዋራ አፈርን በቀላሉ እንዲያገኙ በገሞዎቹ ውስጥ ይበተናል። አፈሩ በገሞዎቹ ውስጥ ሲበተን የሚደረግ ጸሎት ወይም ቁርዓን የመቅራት ስርዓት የለም። ምክንያቱም የጀዋራ አፈር በሼኽ መሃመድ ጸሎት አንዴ የተቀደሰ እንደሆነ በመታመኑ ነው።

## 7.4 ደገሌ የማሰናዳት ስርዓት

በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚገኙና በባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብ የተሰሩ ቤቶች ‘ደገሌ’ ይባላሉ። ደገሌዎች ከሚሰሩበት ግብዐት፣ ከአገልግሎታቸውና ከንብረት ባለቤትነት አንጻር በተለያዩ መንገዶች ይከፈላሉ። ደገሌዎች ከሚሰሩበት ግብዐት አንጻር በሁለት ይከፈላሉ። አንደኛው፣ ግድግዳው ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ ነው። ሁለተኛው፣ ግድግዳው በድንጋይ የሚሰራ ነው። እነዚህ ሁለት አይነት ደገሌዎች ግድግዳቸው ቢለያይም የጣሪያቸው ቅርጽና የጣሪያቸው አሰራር ተመሳሳይ ነው። የደገሌ ቤት ጣሪያ ከእንጨትና ከአፈር የሚሰራና ጠፍጣፋ ቅርጽ ያለው ነው። አሰራሩም መጀመሪያ ረጃጅም እንጨቶች በአግድም ይደረደራሉ። በተደረደሩት እንጨቶች ላይ አፈርና ጠጠር ድንጋዮች ይደረግበትና በእኩል መጠን ይደመደማል።

አካባቢው ከፍተኛ ሙቀት ያለው በመሆኑ ነዋሪዎቹ የቀዘቀዘ አየር ቤታቸው ውስጥ እንዲኖር ለማድረግ የደገሌን ጣሪያ በአፈር ይሰራሉ። የዝናብ ውኃ የጣሪያውን አፈር በማለፍ ወደ ውስጥ እንዳይገባ የ“ገሬ” ቅጠል ይረበረብበታል። የገሬ ቅጠል ለበርካታ ዓመታት ሳይደርቅና ሳይበሰብስ የመቆየት ልዩ ባህርይ አለው። የገሬ ቅጠልና በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መካከል ተመሳስሎ ያለ ይመስላል። የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአስተምህሮ ልዩነት ምክንያት በርካታ ተቃዋሚዎች አሉት። እነዚህ ተቃዋሚዎች አጋጣሚና እድል ቢያገኙ መካነ ቅርሱን ከማጥፋት አይመለሱም። በሼኽ ሁሴንና በመካነ ቅርሱ ላይ ተቃዋሚዎች የሚያደርጉት ቅስቀሳ በጣም ጠንካራና አፍራሽ ነው።

መካነ ቅርሱ በውስጥም በውጪም ያሉበትን ተጽዕኖዎች ተቋቁሞ እስካሁን ቆይቷል። ይህ ባህሪው የዝናብ፣ የፀሐይና የአየር ጸባይ ተጽዕኖዎችን ተቋቁሞ ለበርካታ አመታት ሳይበሰብስ

ከሚቆየው የገሬ ቅጠል ባህርይ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በዚህ ተመሳስሎ የገሬ ቅጠል የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ተምሳሌት ይመስለኛል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን ከሚገኙ ደገሌዎች አብዛኛዎቹ ግድግዳቸው በእንጨትና በአፈር የተሰሩ ሲሆን ጥቂት ደገሌዎች ደግሞ ግድግዳቸው በድንጋይ የተሰራ ነው፡፡ በአካባቢው የሚገኙና የድንጋይ ግድግዳ ያላቸው ደገሌዎች ብዛት አነስተኛ ነው፡፡ እነዚህ ደገሌዎች ቀደም ባሉት አመታት የመካነ ቅርሱ ኢማሞችና ቤተሰቦቻቸው የሚኖሩባቸው ናቸው፡፡ የደገሌዎቹ ግድግዳም አሰራር ትልልቅ መጠን ያላቸው ድንጋዮችን በመደርደርና እርስበርስ በማያያዝ ነው፡፡ ደገሌዎቹ ሲሰሩም ድንጋዮቹን ለማያያዝ እንቁላል፣ የከብት ደምና የሀሽ ዱቄት በግብዐትነት በመጠቀም እንደተሰሩ ይነገራል፡፡[135]



*ፎቶ፡-24፣ የኢማሞች መኖሪያ የነበረና ግድግዳው በድንጋይ የተሰራን ደገሌ የሚያሳይ፡፡*
*(ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ የድንጋይ ደገሌዎች መካከል እስካሁንም አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት የተወሰኑት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ደገሌዎች መካከል ሰፊና የተለየ የእጅ ስራ ጥበብ የሚታይበት የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ ቤተሰቦች ነው፡፡ ይህ ደገሌ ከላይ በፎቶ ግራፍ የሚታየው ሲሆን ከ150 ዓመት በላይ እድሜ እንዳለው መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ፡፡[136] ይህ ደገሌ መካነ

[135] - ሼኽ ኢድሪስ ሐጂ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 11 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡
[136] - አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 26 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

ቅርሱ በኢማም ቤተሰቦች (ወረ-ኢማማ) በሚመራበት ወቅት ዋናው ኢማምና ቤተሰቦቹ ይኖሩበት ነበር፡፡ ይህ ደገሌ በአሁኑ ወቅትም ባለቤትነቱ የኢማም ቤተሰቦች ነው፡፡

ደገሌዎች ከአገልግሎቻቸው አንጻር በሁለት ይመደባሉ፡፡ አንደኛው፤ የአካባቢው ነዋሪዎች በቋሚነት የሚኖሩባቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው፤ ደግሞ በአመት ሁለት ጊዜ ለሚከበሩት የሙዳ በዓላት የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች የሚያርፉባቸውና ከበዓላት ወቅት ውጪ አገልግሎት የማይሰጡ ናቸው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን በጣም በርካታ ቁጥር ያላቸው ደገሌዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ደገሌዎች መካከል ነዋሪዎች ቋሚ የመኖሪያ አገልግሎት የሚሰጡት በቁጥር አነስተኛ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ደገሌዎች ከበዓላት ወቅት ውጪ አገልግሎት የማይሰጡና እስከ በዓል ተዘግተው የሚቆዩ ናቸው፡፡

ደገሌዎች ከንብረት ባለቤትነት አንጻር በሁለት ይመደባሉ፡፡ እነሱም፣ የግለሰብና የቡድን ናቸው፡፡ በግለሰቦች የሚሰሩ ደገሌዎች ባለቤትነታቸው የግለሰቡ ናቸው፡፡ የግለሰብ ደገሌዎች የሚሰሩት በግለሰቡ የግል መሬት ላይ ነው፡፡ ግለሰቦች ደገሌዎችን ለሁለት አገልግሎቶች ይገነባሉ፡፡ አንደኛው፣ ለቋሚ መኖሪያነት ሲሆን ለዚህ አገልግሎትም በሚገነቡ ደገሌዎች ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦች የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው፡፡ ሁለተኛው፣ ባላቸው ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ደረጃ ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጣቸውና ለሙዳ በዓላት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን በቋሚነት የሚመጡ ግለሰቦች ለማረፊያነት የሚሰሯቸው ናቸው፡፡ እነዚህን ደገሌዎች የሚሰሩ ግለሰቦች መሬቱን በግል በመግዛትና የቤቱን የግንባታ ወጪ በግል በመሸፈን ነው፡፡ የደገሌዎቹ ባለቤቶች የሙዳ በዓልን ለማክበር ወደ ቦታው ሲመጡ የሚያርፉባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ደገሌዎች ከሙዳ በዓላት ውጪ አገልግሎት የማይሰጡና ተዘግተው የሚቆዩ ናቸው፡፡

በቡድን የሚሰሩ ደገሌዎች ባለቤትነታቸው የቡድኑ ናቸው፡፡ ለሙዳ በዓላት ወደ ስፍራው በቋሚነት የሚመጡ ሰዎች በቡድን ሆነው ለማረፊያ የሚሆን ደገሌ ይገነባሉ፡፡ በቡድን ደገሌ የሚገነቡ ሰዎች ከአንድ አካባቢ የሚመጡ ወይም የአንድ ጎሳ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሰዎች በቡድን ሲመጡ በአንድ ቦታ ለማረፍ እንዲያመቻቸውና የማረፊያ ስፍራ እንዳይቸገሩ በሚል ገንዘብ አዋጥተው መሬት በመግዛት ወይም በስማቸው በተሰጣቸው መሬት ላይ ደገሌ ይገነባሉ፡፡ በድሮ ጊዜ በመካነ ቅርሱ በጎሳዎች ስም የተሰጡ መሬቶች ነበሩ፡፡ ይህም ሼኽ መሃመድና ሼኽ አባስ መካነ ቅርሱን ድጋሚ ባቋቋሙበት ወቅት ነው፡፡

በአካባቢው ለሚኖሩና ወደ ስፍራው በዋናነት ይመጡ ለነበሩ ጎሳዎች በስማቸው መሬት አከፋፍለዋል፡፡ በወቅቱም በባሌና በአርሲ የሚኖሩ ጎሳዎች በስማቸው መሬት ተሰጧቸዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የጎሳዎቹ አባላት ወደ ስፍራው መምጣት እንዳያቆሙና በመካነ ቅርሱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠርባቸው በሚል ነው፡፡ እያንዳንዱ ጎሳም በስሙ ደገሌ ይገነባል፡፡ በመካነ ቅርሱም የባሌ ደገሌ፣ የአርሲ ደገሌ፣ የዲድአ ደገሌ፣ የስልጤ ደገሌ፣ የሀላባ ደገሌ፣ የጅማ ደገሌ ወዘተ. በሚል ስያሜ የሚጠሩ ደገሌዎች ይገኛሉ፡፡ ለሙዳ በዓላት የሚመጡ የጎሳው አባላት በመሉ ባለቤትነቱ የጎሳቸው በሆነ ደገሌ ውስጥ ያርፋሉ፡፡ እነዚህ ደገሌዎች ከበዓላት ውጪ አገልግሎት የማይሰጡና ተዘግተው የሚቆዩ ናቸው፡፡

በሁለቱም የሙዳ በዓላት ወቅት በርካታ ቁጥር ያለው መንፈሳዊ ተጓዥ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ይመጣል፡፡ አብዛኞቹ መንፈሳዊ ተጓዦችም የሚያርፉት በደገሌዎች ውስጥ ነው፡፡ የበዓላቱ ቀናት ሲቃረቡ ነዋሪዎቹ ተሰባስበው መንፈሳዊ ተጓዦቹ የሚያርፉባቸውን ደገሌዎችን የማጽዳት ስራ ይሰራሉ፡፡ በሁለቱ የሙዳ በዓላት መካከል የ6 ወራት ልዩነት አለ፡፡ ለ6 ወራት ተዘግተው የነበሩ ቤቶች በሚከፈቱበት ወቅት የሚፈጸም መንፈሳዊ ስርዓት አለ፡፡ ይህ ስርዓትም በአካባቢው በሚታወቁ መንፈሳዊ ሰዎች ቤቱ ከመከፈቱ በፊት የሚያካሂዱት የጸሎት ስርዓት ነው፡፡

የደገሌው በር ከመከፈቱ በፊት እጣንና ሰንደል በማጨስ ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ ጸሎት የሚደርጉበት ምክንያትም ለበርካታ ቀናት ሰው ሳይገባበት ተዘግቶ በቆየ ቤት ውስጥ ክፉ መናፍስት ይኖራሉ ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ ተዘግቶ የቆየን ቤት ጸሎት ሳይደረግ ቢገባ በውስጡ ያሉት ክፉ መናፍስት ስለሚረበሹ በሚገባ ሰው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በጸሎት ሀይል በቤቱ ውስጥ የነበሩ መናፍስት ሙሉለሙሉ እንደወጡ ሲታመን የደገሌው በር በዝግታ ይከፈትና ይጸዳል፡፡

የሙዳ በዓላት በሚቃረቡበት ወቅት የድሬ ሼኽ ሁሴን ነዋሪዎች በቋሚነት የሚኖሩበትንና መንፈሳዊ ተጓዦች የሚያርፉበትን ደገሌ ያዘጋጃሉ፡፡ ለበዓላት ገሞዎች ሀሽ እንደሚቀቡ ሁሉ የደገሌዎችም ውስጣዊና ውጫዊ ግድግዳ 'አዱሌ' ይቀባል፡፡ አዱሌ የአፈር አይነት ሲሆን፣ 7 አይነት ቀለም አለው፡፡ የአዱሌ አፈር ቀለሞችም ነጭ፣ ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ደማቅ ቀይ፣ ቡኒ፣ ሽሯማና ወይን ጠጅ ናቸው፡፡ በታች በፎቶ ግራፍ ላይ እንደሚታየው ባህላዊ የደገሌ ቤቶች ጣሪያ በአፈር የተደመደመና ግድግዳቸውም በእንጨትና በጭቃ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ፎቶ ላይ የሚታዩ ደገሌዎች በአዱሌ አፈር ያሸበረቁ ናቸው፡፡ በቤቱ ግድግዳ ላይ የተቀቡት የአዱሌ

ቀለሞቹ ሽሯማ፣ ቀይ፣ ቢጫና ቡናማ ናቸው፡፡ ቀለሞቹም በዝግዛግ ቅርጽ የተቀቡና ለዐይን የሚማርኩ ናቸው፡፡



*ፎቶ፡-25፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኙና በጭቃ የተሰሩ የደገሌ ቤቶች የውጪ ግድግዳ በአዴሌ አፈር አሽብርቀው፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

የአዴሌ አፈር የሚገኘው በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አካባቢ ነው፡፡ ደገሌዎችን ለማስዋብ ከሚያገለግለው የአዴሌ አፈር በተጨማሪ የ‘ሹሬ’ አፈር ተቆፍሮ ይመጣል፡፡ የሹሬ አፈር ቀይ ቀለም ያለው ሲሆን በመካነ ቅርሱ አካባቢ ይገኛል፡፡ የደገሌ ግድግዳ በአግባቡ ከተጸዳ በኋላ መጀመሪያ የሹሬ አፈር በውኃ ተበጥብጦ ይቀባል፡፡ በሹሬ ቀይ ቀለም ላይ የአዴሌ ቀለም ተደርቦ ይቀባል፡፡ የሹሬ ቀይ ቀለም መጀመሪያ የሚቀባው የአዴሌ ቀለም በአግባቡ እንዲይዝና ውበት እንዲኖረው ነው፡፡ ነገር ግን ግድግዳው የሹሬ ቀለም ሳይቀባ የአዴሌ ቀለም ቢቀባ ግድግዳዉ ቀለሙን አይዝም፡፡ የደገሌው ግድግዳ የሹሬ ቀለም ተቀብቶ ሲደርቅ በላዩ ላይ የአዴሌ ቀለም ይቀባል፡፡ የአዴሌ አፈር ካሉት 7 አይነት ቀለሞች መካከል የሚፈልጉትን አይነት ቀለም በመምረጥ ይቀባሉ፡፡ ቀለሞቹንም በተለያየ ቅርስ በመቀባት ግድግዳው ውበት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

## 7.5 ደንቂ የማዘጋጀት ስርዓት

ደንቂ በድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ተጓዦችና በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ መንፈሳዊና ማህበራዊ ዋጋ ያለው በትር ነው። የደንቂ በትር ማህበራዊ ደረጃን መለያና ልዩ መንፈሳዊ ዋጋ ስላለው ወደ ድሬ የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች፣ ኡሌዎች፣ መንፈሳዊ መሪዎችና ገሪባዎች የደንቂ በትር ከእጃቸው አይለይም። የደንቂ በትር የሚዘጋጀው ከሙደጉሬ ተክል እንጨት ነው።

የሙደጉሬ ተክል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በተለያዩ ቦታዎች በብዛት የሚገኝ ነው። ተክሉ በተለያዩ ቦታዎች ቢገኝም ለደንቂ በትር የሚሆን እንጨት የሚቆረጠው በመካነ ቅርሱ ከሚገኘው ቀጨምሰሬ ተራራ ላይ ብቻ ነው። የሙደጉሬ ተክል በርካታ ቅርንጫፍ ያለው ሲሆን ቅርንጫፎቹም በአናታቸው ላይ የባላ ቅርጽ አላቸው። የተክሉ እንጨት በቀላሉ መተጣጠፍ የሚችል ነው። እንጨቱም በእርጥብነቱ እንደተቆረጠ የሚፈለገውን ቅርጽ እንዲይዝ በቀጭን ገመድ የባላዎቹን ጫፎች ወደ ውጪ በማጠፍ ይወጠራል። የተወጠረው እንጨትም ሲደርቅ የባላ ቅርጽ ይይዛል።

የደንቂ በትር በተለያየ መጠንና ውፍረት ይዘጋጃል። በአብዛኛው ረጅም፣ መካከለኛና አነስተኛ ቁመት ያላቸውና ውፍረትና ቅጥነት ያላቸው ደንቄዎች ይዘጋጃሉ። ደንቄዎች ባላቸው የውፍረትና የቁመት ልዩነት መሰረት አገልግሎታቸው የተለያየ ነው። ወፍራምና ረጅም ደንቄዎችን የሚይዙት 'ኡሌዎች' ናቸው። መካከለኛ ደንቄዎችን የሚይዙት 'ገሪባዎች' ናቸው። አነስተኛ ደንቄዎችን የሚይዘው ደግሞ በስፍራው ለአምልኮ የሚመጣው ማንኛውም መንፈሳዊ ተጓዥ ነው።

የደንቂ በትር መያዝ የተጀመረው በሼኽ ሁሴን ዘመን እንደሆነ ይነገራል። በእሳቸው ዘመን ስፍራው የሀይማኖት ተማሪዎች (ደረሳዎች) መማሪያ ማዕከል ነበር። በወቅቱም ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ለትምህርት ወደ ስፍራው የሚመጡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተከታትለው ይመረቃሉ። ትምህርታቸውን ተከታትለው ለጨረሱ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ስለማጠናቀቃቸው የሚገልጽ የደንቂ በትር ሽልማት ይሰጣቸዋል።

ይህ የደንቄ ሽልማትም ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ማጠናቀቃቸውን የሚገልጽ የትምህርት ማስረጃ ወረቀት (ሰርተፊኬት) ነው፡፡[137] በወቅቱ ትምህርቱን ያጠናቀቀና የደንቄ ሽልማትን ያገኘ ተማሪ በየትኛውም ቦታ ሄዶ ሀይማኖታዊ ትምህርት የማስተማርና የራሱን የሀይማኖት ማስተማሪያ ማዕከል ማቋቋም ይችል ነበር፡፡ የደንቄ በትር እንደትምህርት ማስረጃነት በማገልገል ለረጅም ጊዜ ቆይቷል፡፡ ይህ ታሪካዊ ሁነት የደንቄ በትር ለከፍተኛ ማህበራዊ ውክልና እንዲያገለግል አድርጎታል፡፡ ስፍራው በተለያዩ ምክንያቶች የሀይማኖት ትምህርት መስጫ ማዕከልነቱ ሲቋረጥ የደንቄ ማህበራዊ ውክልናም እየተለወጠና የተለያዩ ትርጓሜዎችን እየያዘ መጣ፡፡

በወቅቱም የደንቄ በትር ለተመራቂ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃ ከመሆኑም በተጨማሪ ሼኽ ሁሴንና የእሳቸው ተማሪዎች የደንቄ በትርን ለምርኩዝነት፣ መንገድ ሲሄዱ የሚዋጋ እሾህ ካላቸው ተክሎች ራሳቸውን ለመከላከል፣ ለፍየሎቻቸውና ለከብቶቻቸው ምግብ የሚሆን ቅጠል ከዛፍ ላይ ለማውረድ፣ የሶላት ውኃ መያዣ ቅልን ለማንጠልጠልና ሲደክማቸው ለመደገፍ ይይዙት እንደነበር ይነገራል፡፡[138]



*ፎቶ፡-26፤ አጥኚው በመስክ ስራ ወቅት የደንቄ በትር ይዞ (ፎቶ በአቶ ኑማን መሃመድ)፡፡*

---

[137] - ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ኡስማን፣ አቶ ኑማን መሃመድና አቶ መሃመድ ሰዒድ አህመድ፣ መጋቢት 26፣ 20008 ዓ.ም፡፡

[138] - ሼኽ ቃሲም ሼኽ አደም፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 26 ቀን 20008 ዓ.ም፡፡

የደንቁ በትር የወንድማማችነት (Fraternity) ምልክት ነው፡፡ ነዋሪው ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚመጣ እንግዳን የመቀበልና በቤታቸው የማሳረፍ ግዴታ አለባቸው፡፡ በመሆኑ ከዚህ በፊት ማረፊያ የሌለውና ለቦታው እንግዳ የሆነ ሰው የፈለገው ቤት ሄዶ ማደሪያ መጠየቅና የፈለገውን ጊዜ ያህል ቆይቶ መመለስ ይችላል፡፡ አንድ ግለሰብ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈሳዊ ጉዞ ሲያደርግ በእንግድነት በአንድ ግለሰብ ቤት ያርፋል፡፡ እንግዳው የመጣበትን መንፈሳዊ ጉዞ ጨርሶ ለመመለስ ሲያስብ እንግዳውን በቤቱ ተቀብሎ ያስተናገደው የቤቱ አባ ወራ ወይም እንግዳውን የተቀበለ የቤተሰቡ አባል ለማስታወሻ እንዲሆን የደንቁ በትር በስጦታ ይሰጠዋል፡፡ እንግዳውም አቅሙ የፈቀደውን ነገር ለቤቱ አባወራ ወይም ለተቀበለው ግለሰብ ይሰጣል፡፡

እንግዳው ወደ መኖሪያው ሲመለስ በስጦታ የተሰጠውን የደንቁ በትር በአግባቡ ደህና ቦታ ያስቀምጣል፡፡ በሌላ ጊዜም ግለሰቡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ሲመጣ ያንኑ ደንቁ ይዞ ይመጣል፡፡ በዚህ መልክ የተሰጠ ደንቁ በልዩ ጥንቃቄና አክብሮት የሚያዝ ነው፡፡ ግለሰቡ የተሰጠውን የደንቁ ስጦታ ባየ ቁጥር ስጦታውን የሰጠውን ግለሰብ ያስታውሳል፡፡ ይህ በመሆኑ የደንቁ በትር በሁለቱ ግለሰቦች መካከል የእርስበርስ ግንኙነት፣ ትውውቅ፣ ወንድማማችነት፣ ትብብርና መከባበር ለመመስረት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

በአሁኑ ወቅት የደንቁ በትር የተለያዩ ማህበራዊና መንፈሳዊ ተምሳሌቶች አሉት፡፡ ደንቁ የወንድማማችነት ተምሳሌት ነው፡፡ ደንቁን የያዘ ሰው የሰላም ሰው ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ደንቁም የሰላም ተምሳሌት ነው፡፡ ደንቁን የያዘ ሰው የሼኽ ሁሴን አፍቃሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ደንቁም የሼኽ ሁሴንና የእሳቸውን ፍቅር ተምሳሌት ነው፡፡ ደንቁን የያዘ ሰው ክፉ ነገር አይገጥመውም ተብሎ ይታመናል፡፡ ደንቁም የደህንነት ማረጋገጫ ነው፡፡

ደንቁ ከእነዚህ ተምሳሌቶች በተጨማሪ የሼኽ ሁሴን ወዳጆችን ከኃጽያት የሚያነጻ፣ ከበሽታ የሚፈውስና ከክፉ ነገር የሚጠብቅ እንደሆነ ይታመናል፡፡[139] በደንቁ ላይ የሼኽ ሁሴን መንፈስ ያርፍበታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም እሳቤ የደንቁ በትር እንጨት አይደለም፤ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎችንና ሼኽ ሁሴንን የሚያገኛኝ ድልድይ ነው፡፡ ነብዩ ሙሴ ባህሩን ለሁለት እንደከፈለበት በትር ሁሉ፣ የደንቁ በትርም ለሼኽ ሁሴን ወዳጆች መንፈሳቸውን ወደ ልዕልና ከፍ ማድረጊያ ነው፡፡

[139] - ሼኽ መሐመድ ሼኽ ሙሐሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

## 7.6 መንፈሳዊ ተጓዦችን የመቀበል ስርዓት

መንፈሳዊ ተጓዦች በተለያዩ የመጓጓዣ መንገዶች በመጠቀም ወደ ስፍራው ሲደርሱ የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች አቀባበል ያደርጉላቸዋል፡፡ በቡድን ተሰባስበው የመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በስፍራው ሲደርሱ የሰላሞ መንፈሳዊ ዜማን በሕብረት ያዜማሉ፡፡ የሰላሞ መንፈሳዊ ዜማ በስፍራው መድረሳቸውን ለሼኽ ሁሴን የሚነግሩበት፣ በሼኽ ሁሴን ቅዱስ ስፍራ በሰላም በመድረሳቸው ደስታቸውን የሚገልጹበት፣ በሰላም በዓሉን እንዲያከብሩ የሚጠይቁበትና ሁሌም ከስፍራው እንዳይለዩ የሚለምኑበት ነው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦቹ፡-

Allahu maraa Sheikh Huseeni…. hooo

ትርጉሙ፡-

አላህ ሆይ ለሼኽ ሁሴን ቸሩ ምህረትህን ለግሰው፡፡

ሼኽ ሁሴኒ…..ሆ ማለት ነው፡፡

ይህን በማለት የሰላሞ ዜማ በህብረት እያዜሙ ወደ ማረፊያ ቦታቸው ይሄዳሉ፡፡

ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በቋሚነት የሚያርፉበት የራሳቸው ደገሌዎች አሏቸው፡፡ ደገሌዎቹን በቡድን የሚመጡ ሰዎች በጋራ የሚሰሯቸው ቤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ደገሌዎች የቡድኑ የጋራ ሀብት ናቸው፡፡ በቡድን የሚመጡና ደገሌ የሌላቸው ሰዎች በቋሚነት የሚሰፍሩበት ቦታ አላቸው፡፡ በቋሚ ቦታቸው ላይ በእንጨትና በሸራ ፕላስቲክ ጊዜያዊ ዳስ ጥለው ያርፋሉ፡፡ የራሳቸው ደገሌ የሌላቸውና በቋሚነት የሚሰፍሩበት ቦታ የሌላቸው ግለሰቦች በአካባቢው ነዋሪዎች መኖሪያ ቤት ያርፋሉ፡፡ ወደ ስፍራው በተደጋጋሚ የሚመጣ ሰው ከነዋሪዎቹ ጋር በሚፈጥረው ትውውቅ ምክንያት በቋሚነት የሚያርፍበት ቤት ይኖረዋል፡፡

ለስፍራው እንግዳ የሆነ ግለሰብ በማንኛውም የግለሰብ ቤት ለሚፈልገው ያህል ጊዜ ማረፍና መቆየት ይችላል፡፡ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ "የአብዮን እንግዳ መቀበል በረከት ያስገኛል" ተብሎ ስለሚታመን መንፈሳዊ ተጓዡም ሆነ የአካባቢው ነዋሪ ወደ ስፍራው ለሚመጣ እንግዳ ልዩ ክብርና እንክብካቤ ይሰጣሉ፡፡ ሼኽ ሁሴን ለሰው ልጅ ሁሉ ልዩ ክብር እንዳላቸው ይነገራል፡፡ እንግዳንም በፍቅር መቀበል የእሳቸው ባህርይ እንደነበር ይነገራል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ እንግዳን በፍቅር የመቀበል ግዴታ ከሼኽ ሁሴን ሰብዕና ጋር ይገናኛል፡፡

የኮግኒቲቭ ሳይንስ ተመራማሪ የሆነው Boyer (1990) ሰዎች አምላካቸው ወይም ቅዱሳቸው የከወኑትን ድርጊትን እንደ ሞዴል በመውሰድና ድጋሚ በመተግበር ለሚኖራቸው የእርስበርስ ግንኙነት፣ መከባበር፣ መፈቃቀርና መረዳዳት አርዓያ እንደሚሆናቸው ይገልጻል፡፡ በመሆኑም በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎችና በመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ዘንድ የሚታየው የእንግዳ አቀባበል አስተሳሳብ ከፈጣሪና ከሼኽ ሁሴን መንፈስ ጋር የሚገናኙበት መሰላል ነው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው በሚመጡበት ወቅት የአካባቢው ነዋሪዎች እንግዶቹ የሚያርፉባቸውን ደገሌዎችና ቦታዎች የማጽዳት ስራ ይሰራሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦቹ በስፍራው ሲደርሱ ነዋሪዎቹ ‹እንኳን ደህና መጣችሁ› በማለት በፍቅር ይቀበሏቸዋል፡፡ ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡ ስለጉዟቸው ይጠያየቃሉ፡፡ በሰላም በመገናኘታቸው ፈጣሪንና ሼኽ ሁሴንን ያመሰግናሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእርስበርስ የሰላምታ አሰጣጥ መንገዶች ሁለት አይነት ናቸው፡፡ አንደኛው መንገድ ከንፈር ለከንፈር መሳሳም ነው፡፡ ይህ ሰላምታ እርስበርስ በጣም ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች የሚጠቀሙበት ነው፡፡ በዚህ የሰላምታ መንገድ ሰዎች እርስበርስ ያላቸውን ጥልቅ ወዳጅነትና ያላቸውን ልዩ ፍቅር ይገልጹበታል፡፡ ይህ አይነት የሰላምታ ልውውጥ ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ሰዎች ብቻ የሚጠቀሙት ነው፡፡ ሁለተኛው መንገድ አንዱ የሌላውን እጅ መሳም ነው፡፡ ይህ ሰላምታ የእርስበርስ ቀረቤታቸው እምብዛም ያልሆኑ ወይም አዲስ ለሚተዋወቁት ግለሰቦች እንዲሁም ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች የሚጠቀሙበት ነው፡፡ በመሆኑም በሁለት ተመሳሳይ ጾታ ባላቸው ግለሰቦች መካከል የሚደረግን የሰላምታ ልውውጥ መሰረት በማድረግ ግለሰቦቹ ያላቸውን ፍቅር፣ ወዳጅነትና ቀረቤታ ማወቅ ያስችላል፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን ነዋሪዎች በየበዓላቱ የተለያዩ እንግዶችን በቤታቸው ተቀብለው ያስተናግዳሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከዚህ በፊት ለበዓል የሚመጡት ቋሚ እንግዶች ሲሆኑ አልፎአልፎ አዳዲስ እንግዶች ይመጣሉ፡፡ ነዋሪዎቹ አዲስ እንግዳ ተቀብለው በሚያስተናግዱበት ወቅት ለማስታወሻና ለወንድማማችነት ማጠናከሪያ የደንቄ በትር ስጦታ በመስጠት ይሸኙታል፡፡ በመሆኑም በዓላት በሚቃረቡበት ወቅት የደንቄ በትር በማዘጋጀት አዲስ እንግዳን ይጠብቃሉ፡፡

## 8. በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ በዓላት በአመት ሁለት ጊዜ ይከበራሉ፡፡ የሙዳ በዓላት በሚከበሩባቸው ቀናትም የተለያዩ ስርዓተከበራዎች በተለያዩ የመካነ ቅርሱ ስፍራዎች ይከወናሉ፡፡ እነዚህ ስርዓተከበራዎች በተደጋጋሚና በቋሚነት የሚከወኑ ናቸው፡፡ Boyer (1990፡10) ሰው ስርዓተከበራዎችን በተደጋጋሚ የሚከውንበት ምክንያት ስርዓተከበራዎች ሀሳቦችን (Ideas) ስለሚገልጹና ሰዎች እነዚህ ሀሳቦች መጠበቅ አለባቸው ብለው ስለሚያስቡ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓተከበራዎችም የሚገልጹት ሀሳብ አለ፡፡ ይህንንም ሀሳብ መጠበቅና ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ ስርዓተከበራዎቹ ያላቸውን የአከዋወን ስርዓትና ቅደምተከተል በመጠበቅ ይከወናሉ፡፡

ማንኛውም ክወና ትርጉም እንዲኖረው አላባውያን ሊኖሩት ይገባል፡፡ የክወና አላባውያን የሚባሉት ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ትዕምርትና ማህበራዊ ኃይል ናቸው (Alexander, 2006፡32-37)፡፡ እነዚህ አላባውያን ከሌሉ ክወናው ሊተገበር አይችልም፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎች ላይ እነዚህ አራት የክወና አላባውያን አሉ፡፡ እነዚህንም አላባውያን መሰረት በማድረግ በመካነ ቅርሱ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች በዚህ ምዕራፍ ይቀርባል፡፡ ይህ ምዕራፍ በስድስት ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡ እነዚህ ክፍሎችም የሙዳ በዓላት የአጀማመር፣ የዋሬ፣ የዝክሪ፣ በከራ ጉዶና በቅጽር ግቢው ውስጥ የሚከወኑ፣ በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችና መንፈሳዊ ተጓዦችን የመሸኘት ስርዓት ናቸው፡፡

### 8.1 የሙዳ በዓላት የአጀማመር ስርዓተከበራዎች

Bauman (1992:45-48) የክወና ባህርያትን በሶስት ይመድባቸዋል፡፡ እነዚህም አንደኛው፣ ክወና በእቅድ የሚቀርብ መሆኑ ነው፡፡ በእቅዱም በሁለት አይነት ገደብ ሊከፈል ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የጊዜ ገደብ ነው፡፡ በዚህ ገደብ መሰረትም ክወናዎች በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በሚቀርቡበት ወቅት ቋሚ የሆነ የጊዜ እቅድ አላቸው፡፡ የክወናው የጊዜ ርዝማኔና የመከወኛ ወቅት ገደብ ያላቸውና የክወናው መጀመሪያና መጨረሻ በግልጽ የሚታወቅ ነው፡፡

የሙዳ በዓላትም ቋሚ በሆነ የጊዜ ገደብ በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ ናቸው፡፡ በዓላቱም መቼ ተጀምረው መቼ እንደሚያልቁ እንዲሁም የተለያዩ ክወናዎች በስንት ሰዓት ተጀምረው በስንት

ሰዓት እንደሚጠናቀቁ በግልጽ የታወቀ ነው፡፡ ሁለተኛው፤ የቦታ ገደብ ነው፡፡ በዚህ ገደብ መሰረትም የሙዳ በዓላት ክወናዎች የሚቀርቡት ውስን፣ ቋሚ ወይም የተደነገገ የመከወኛ ስፍራ ላይ ነው፡፡ የሙዳ በዓላት ክዋኔዎችም በመካነ ቅርሱ የተለያዩ ስፍራዎች በሚገኙ የመከወኛ ቦታዎች ይቀርባሉ፡፡

የሙዳ በዓላት ‘ሐጅ’ እና ‘ዛህራ ገልገላ ኅበና’ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሁለት በዓላት የአከባበር ስርዓቶች መካከል ያለው ልዩነት የበዓላቱ የአጀማመር ክወናዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህም ልዩነት የሐጅ የሙዳ በዓል የሚጀመረው በዕለቱ ጠዋት ላይ በሚካሄደው የሕብረት ሶላት (ስግደት) ስርዓት ነው፡፡ ለዛሕራ ገልገላ ኅበና የሙዳ በዓል ወቅት የሚካሄድ የሕብረት ስግደት የለም፡፡ የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል የሚጀምረው ማታ ጨረቃ ስትወጣ ነው፡፡ በዓሉ የሚጀምረውም ቁርዓን በመቅራት ነው፡፡ በሁለቱ የሙዳ በዓላት የአጀማመር ስርዓት ካለው ልዩነት በስተቀር የሚከወኑ ሌሎች ስርዓተከበራዎች በሙሉ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የሁለቱን የሙዳ በዓላት የአጀማማር ስርዓት ቀጥለን በተናጠል እንመልከት፡፡

## 8.1.1 የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል የአጀማመር ስርዓት

የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል የሚከበረው ማክሰኞ ዕለት ነው፡፡ በዓሉም የሚጀመረው ከምሽቱ 2 ሰዓት ገደማ ነው፡፡ በዓሉ ከመጀመሩ ጥቂት ሰዓታት አስቀድሞ ሁሉም መንፈሳዊ ተጓዥ ከዋናው የግምብ አጥር መግቢያ ፊት ለፊት በሚገኘው በዶቆ ከራ ሰፊ ስፍራ ላይ መሰባሰብ ይጀምራል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች በዕለቱ ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእንግድነት የመጡ ባለስልጣናትና የቢሮ ኃላፊዎች በዶቆ ከራ እንደተገኙ በዓሉ ይጀመራል፡፡

የዛሕራ ገልገላ ኅበና በዓል የሚጀመረው ቅዱስ ቁርዓን በመቅራት ነው፡፡ በዕለቱ ከቅዱስ ቁርዓን ሱራዎች (ምዕራፎች) መካከል የያሲን ሱራ (ሱራ፣ 36) ይቀራል፡፡ የያሲን ሱራ 83 ሀረጋት (Verse) ያሉት ሰፊ ክፍል ነው፡፡ በዕለቱ የሱራውን ሁሉንም ሀረጋት መቅራት ረጅም ጊዜ ስለሚወስድ፣ ከሱራው የተወሰኑትን ሀረጋት ብቻ መርጠው ይቀራሉ፡፡ በዕለቱ ቁርዓን የሚቀሩት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኃይማኖት ትምህርት የሚማሩ ደረሳዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ደረሳዎች በሕብረት በመሆን ቁርዓን ሲቀሩ፣ ስርዓቱን በበላይነት የሚመሩት በተለያየ ጊዜ የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ መስኪድ ኢማም የሆኑ የኃይማኖት አባት ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት መስኪዱን በዋናነት የሚመሩት ኢማም ሼኽ አብዱልቃድር ሼኽ መሃመድ ሳፊ ናቸው፡፡

ቁርዓን የመቅራት ስርዓት ሲጠናቀቅ የ"ሰለዋት" ስርዓት ይጀመራል። ሰለዋት የአረብኛ ቃል ሲሆን፣ ማወደስ የሚል ትርጉም አለው። በስርዓቱም አላህ፣ ነብዩ መሃመድ፣ ሼኽ ሁሴንና ሼኽ ሶፍዑመር ይወደሳሉ፤ ይመሰገናሉ።

## 8.1.2 የኢድ-አል-አድሃ (የሐጅ) በዓል የአጀማመር ስርዓት

በመካነ ቅርሱ የኢድ-አል-አድሃ (የሐጅ) በዓል የአከባበር ስርዓት የሚጀምረው ጠዋት በሚደረግ የሕብረት ስግደት ነው። በመካነ ቅርሱ የተገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች በዕለቱ ለሚካሄደው የሕብረት ስግደት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ሰውነቱን ታጥቦ፣ ንጹህ ነጭ ጀለብያ ልብስ ለብሶ፣ ኢማማ ለብሶ፣ ቆብ አናቱ ላይ አድርጎ፣ መስገጃ ምንጣፍ ይዞና ምስብሐ (መቁጠሪያ) ይዞ ወደ መስገጃ ስፍራ ይሄዳል። በመካነ ቅርሱ የሕብረት ስግደት የሚካሄደው በተለምዶ የአይሮፕላን ማረፊያ የሚባለው ቦታ ነው። የአውሮፕላን ማረፊያው ከከራ ጉዶ በግምት 500 ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሰፊ ቦታ ነው።

በዚህ ስፍራ የሕብረት ስግደት መሰገድ የተጀመረው በ1998 ዓ.ም ነው። ከዚህ ዓመት በፊት የአረፋ የሕብረት ስግደት ይሰገድ የነበረው በግምብ በታጠረው ግቢ ውስጥ በሚገኝ የመስገጃ ቦታ ነበር። ቦታውም ከጎምቢሶ አዮ ሀደ ገራዶ ፊት ለፊት በሚገኝ ሰፊ ሜዳ ላይ ነበር። የመንፈሳዊ ተጓዡ ሕዝብ ቁጥር ከአመት አመት እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት ቦታው በመጥበቡ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ እንዲዛወር ተደረገ። በሙዳ በዓል ወቅት ከሕዝብ በተሰበሰበ ገንዘብ የአይሮፕላን ማረፊያ በ2007 ዓ.ም ዙሪያው በሽቦና በቆርቆሮ አጥር ታጥሯል።

በሐጅ የሙዳ በዓል ወቅት በሕብረት የሚሰገድን ስግደት የሚሳተፈው የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ብቻ ነው። የክርስትና፣ የዋቄፈና ወይም የሌላ ኃይማኖት ተከታይ ወይም በተለያየ ምክንያት መስገድ የማይችል ግለሰብ ወደ ስግደቱ ቦታ በመሄድ ስርዓቱን ሊከታተል ይችላል። ከስር በቀረበው ፎቶ ግራፍ ላይ በቅርበት ቆሞ ስግደቱን ሲከታተል ከሚታየው ሕዝብ መካከል በአብዛኛው የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ያልሆነ ሲሆን፣ የተወሰነው ደግሞ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ሆኖ በተለያየ ምክንያት የማይሰግድ ነው።



*ፎቶ፡- 27፤ ለኢድ-አል-አድሃ በዓል የሕብረት ስግደት ሲካሄድ (ፎቶ በአጥኚው)።*

ሕዝቡ ወደ መስገጃ ስፍራው ለሶላት በሚሄድበት ወቅት በቡድን በቡድን በመሆን ለፈጣሪ የመወድስ ዜማ እያቀረበ ነው። ይህ መወድስ ተክቢራ ይባላል። በተክቢራውም

አላሁ አክበር

አላሁ አክበር ….

እያሉ ወደ መስገጃው ስፍራ ይሄዳሉ። አላሁ አክበር ማለት አላህ (ፈጣሪ) ክብር ይገባሃል ወይም ክብር ለአላህ እንደማለት ነው። ሕዝቡ በመስገጃው ስፍራ ከተሰባሰበ በኋላ የተክቢራ ስርዓት በኢማም መሪነት ይጀመራል። ተክቢራ የሚለው ቃል አረብኛ መጥራት፣ ማመስገን፣ ማወደስ እንደማለት ነው። ኢማሙ "አላሁ አክበር" ሲሉ ሕዝቡም እየተቀበለ "አላሁ አክበር" ይላል። የተክቢራ ስርዓት ሲጠናቀቅ የዳዕዋ ስርዓት ይጀመራል። ዳዕዋ፣ ትምህርት የማስተማር ሂደት ነው። የዳዕዋ ስርዓትን የሚመሩት ከተለያዩ አካባቢዎች በተጋባዥነት የመጡ የኃይማኖት አስተማሪ ምሁራን (ኡለማ) ናቸው። ተጋባዥ የኃይማኖት አስተማሪ ሆኖ የመጣ እንግዳ ከሌለ በመካነ ቅርሱ ታዋቂ የሆኑ የኃይማኖት አስተማሪዎች ስርዓቱን ሊመሩ ይችላሉ።

በዳዕዋ ስርዓት ወቅት ስለኢድ-አል-አድሃ በዓል አጀማመር ታሪክ፣ የነብዩ ኢብራሂም፣ የሐጋርና የእስማኤል የመንፈስ ቆራጥነትና ለፈጣሪ ያላቸው ታማኝነት፣ ሕዝቡ ሀይማኖቱን አጥብቆ እንዲይዝ አላህ በቁርዓን የተናገራቸው የቁርዓን ጥቅሶች፣ የነብዩ መሃመድ ታላቅነት፣ የኃይማኖቱ ትልልቅ ወልዮች መከበር እንዳለባቸው፣ የእነሱንም የመቃብር ስፍራ መዘየር

የነብዩ መሃመድ አስተምህሮ መሆኑን፣ እንደሼኽ ሁሴን ካሉ የፈጣሪ ሰዎች በረከት እንደሚገኝ፣ ስለኢድ-አል-አድሃ በዓል ምንነት፣ ስለበዓሉ በቁርዓን ላይ የቀረበው፣ ነብዩ መሃመድ ስለበዓሉ በሐዲስ ላይ የተናገሩት፣ ስለበዓሉ የአከባበር ስርዓት በሐዲስና በፊቅ ላይ የተገለጹ ጉዳዮችና የሰለፊያ አስተምህሮ ትክክል አለመሆኑን ያስተምራሉ፡፡

ሁሉም የመካነ ቅርሱ ነዋሪና መንፈሳዊ ተጓዥ አቅሙ የፈቀደውን ያህል የበግ፣ የፍየል፣ የግመል ወይም የከብት እርድ በማረድ በመኖሪያ ቤት የዑድሂያ ስርዓት እንዲፈጽሙ፣ ከእርዱም ላይ ለጎረቤት፣ ለዘመድ፣ ለደሃና ለጓደኛ የድርሻቸውን እንዲሰጡ፣ ሰደቃ እንዲያደርጉና ለደሃ እንዲያበሉ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይነገራል፡፡ የትምህርቱ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ለድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ እደሳና ጥበቃ የሚሆን ገንዘብ ይሰበሰባል፡፡ የትምህርቱና የገንዘብ ማሰባሰቡ ፕሮግራም ሲጠናቀቅ በኢማሙ መሪነት ሶላት (ስግደት) ይጀመራል፡፡ በስግደት ጊዜ ሁሉም ምዕመን ፊቱን ወደ መካ ቂብላ በሰሜን አቅጣጫ በማድረግ፣ ቀጥ ያለ መስመር በመስራትና እርስበርስ በጣም ሳይጠጋጉ ይደረደራሉ፡፡ ወንድና ሴት በተለያየ ቦታ በመሆን ይሰግዳሉ፡፡

የሶላት ስርዓተክዋኔ ሶስት ድርጊቶችን ይይዛል፡፡ እነሱም፡- ቀጥ ብሎ መቆም (ቂያም)፣ በአንደኛው የእግር መዳፍ ላይ መቀመጥ (ራካት) እና በጉልበት ተንበርክኮ በግምባር መሬት መንካት (ሱጁድ) ናቸው፡፡ እነዚህን ድርጊቶች ሲከወኑ በሰጋጆቹ አንደበት የሚባሉ የቁርዓን ጥቅሶች አሉ፡፡ ቀጥ ብለው ቆመው የሁለት እጅ አመልካች ጣትን በሁለቱ ጆሮዎች በመክተት 'አላሁ አክበር' ይላሉ፡፡ በእግር መዳፍ ላይ ሲቀመጡ ፋቲሃ ይቀራሉ፡፡ ፋቲሃ በቅዱስ ቁርዓን (ሱራ 1 ቁጥር 1-7) የሚገኝ የአላህን ታላቅነት የሚገልጽ ጥቅስ ነው፡፡ ፋቲሃን ቀርተው ሲጨርሱ 'አሜን' ይላሉ፡፡ ከፋቲሃ በመቀጠል ከቁርዓን የፈለጉትን ሱራ (ምዕራፍ) መርጠው ይቀራሉ፡፡ በአብዛኛው የተለመዱት ሱራ 112 ቁጥር 1-4 እና ሱራ 2 ቁጥር 225 ላይ ያሉት ጥቅሶች ናቸው፡፡ ትንሽ ጎንበስ ብለውና እጃቸውን በታፋ ላይ ደገፍ በማድረግ "አላሁ አክበር" የሚለውን ሶስት ጊዜ ይደግማሉ፡፡ ግምባርን መሬት በማስነካት እና ወደ ላይ ቀና በማለት "አላሁ አክበር" ይላሉ፡፡

ይህ የድርጊት ዙር (ራካት) የሚደጋገም ሲሆን ድግግሞሹ ሶላቱ እንደሚከወንበት ሰዓት ሁለት፣ ሶስት ወይም አራት ዙር ሊሆን ይችላል፡፡ የራካት ዙር ሲጠናቀቅ "ታሸሃሁድ" ይባላል፡፡ ታሸሃሁድ የእስልምና ኃይማኖት ዋና መልዕክት ሲሆን፣ የአላህን ብቸኛ አምላክነትና የነብዩ መሃመድን መልዕክተኛነት የሚገልጽ ነው፡፡ ታሸሃሁድን ቀርተው ሲጨርሱ አንዴ ወደ ቀኝ

አንዴ ወደ ግራ አቅጣጫ በመዞር ከጎናቸው ላለ ሰው ሰላምታ ያቀርባሉ፡፡ ይህ ሰላምታ ከጎን ሌላ ሰው ቢኖርም ባይኖርም የሚከወን ነው፡፡ ይህን የሶላት ስርዓት የሚመሩት ከሚሰግዱት ሰዎች ፊት ለፊት በሚሰግዱ ኢማም (መሪ) ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን ለአረፋ በዓል የሚከወንን የሶላት ስርዓት የሚመሩት በወቅቱ ያሉ የመስኪድ ኢማም ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢድ የሶላት ስርዓትን የሚመሩት ሼኽ አብዱልቃድር ሼኽ መሃመድ ሳፊ ናቸው፡፡ ሼኽ አብዱልቃድር ሼኽ መሃመድ ሳፊ በመካነ ቅርሱ የሚገኘው የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ መስኪድ ኢማም ናቸው፡፡

አንዳንድ ግለሰቦች በሶላት ወቅት ምስብሐ (መቁጠሪያ) በእጃቸው ይይዛሉ፡፡ የምስብሐ ጥቅም ግለሰቦች በቃላቸው የሚሉትን ስም፣ ቃል፣ ሀረግ ወይም አረፍተነገር ምንያህል ጊዜ እንዳሉ ለመቁጠር ነው፡፡ አንድ ስም ወይም ቃል አንዴ ሲሉ አንድ የምስብሐ ፍሬ በአውራ ጣታቸው ይቆጥራሉ፡፡ ምስብሐን መጠቀም በእስልምና፣ በክርስትና እና በጂው ሀይማኖቶች የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን የሚስባህ ፍሬ ቁጥር በየሀይማኖቶቹ የተለያየ ነው፡፡ በአብዛኛው በእስልምና ኃይማኖት የተለመዱት የምስብሐ ፍሬዎች ብዛት 99 ወይም 33 ናቸው፡፡ 99 የሆኑበት ምክንያትም የአላህን 99 የተለያዩ ስሞች ሲጠሩ ለመቁጠር ነው፡፡ አላህ 99 የተለያዩ ስሞች እንዳሉት በቅዱስ ቁርዓን (በሱራ 7 ቁጥር 180) ላይ ተገልጿል፡፡ የስግደት ስርዓት ሲጠናቀቅ "ቁጡባ" ይቀራል፡፡ ቁጡባ ስለኢድ-አል-አድሃ በዓል ምንነት፣ ታሪካዊ አመጣጥና በዕለቱ መደረግ ያለባቸውና መደረግ የሌለባቸውን ጉዳዮች የሚገልጽ መጽሐፍ ነው፡፡

የሶላት ስርዓት ሲጠናቀቅ ሕዝቡ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ሕዝቡ ወደ ቤቱ ሲመለስ በቡድን በቡድን በመሆን አላህን፣ ነብዩ መሃመድንና ሼኽ ሁሴንን የሚያወድሱ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን በጋራ እየከወነ ነው፡፡ በዕለቱ ሁሉም ሰው አቅሙ በፈቀደው መጠን በቤቱ የዕርድ መስዋዕት እንዲፈጽም ይጠበቅበታል፡፡ በዕለቱም እንደሰው የኢኮኖሚ አቅም የፍየል፣ የበግ፣ የከብት ወይም የግመል ዕርድ ይካሄዳል፡፡ የዕርድ መስዋዕት ማቅረብ በሁሉም ኃይማኖቶች የተለመደና ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው መንፈሳዊ ስርዓት ነው፡፡ የዕርድ መስዋዕት በሰው ልጅና በልዕለሰብዕ ኃይላት መካከል ግንኙነት የሚፈጥር ስርዓተከበራ ነው፡፡ የዕርድ መስዋዕት ለልዕለሰብዓዊ ኃይል ያለንን ልቡናዊ ታዛዥነትና ተገዥነት የምናሳይበት ውጫዊ ትዕምርት (An external symbol of dedication) ነው፡፡

ይህ ስርዓተከበራ የሚፈጸመው የተለያዩ ጉዳዮችን ምክንያት በማደረግ ነው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ከኃጽያት ለመንጻት፣ ከጥፋተኝነት ስሜት ለመገላገል፣ የተሻለ ነገር ለማግኘት፣ የታሰበው ነገር

እንዲሳካ፣ ቅጣትን ወይም ቁጣን ለማስቀረት፣ ዕርቅ ለመፍጠር፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠንከር፣ ልዕለሰብዕ ኃይሎችን ለማስደሰትና ከልዕለሰብዕ ኃይሎች ጋር ሕብር ለመፍጠር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በኢድ በዓል ዕለት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚኖሩና በዓሉን ለማክበር በስፍራው የተገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዕርድ የሚፈጽሙት እንደ ሌላው የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ሁሉ ኢብራሂም (አብርሃም) ልጁን በሚና ተራራ ላይ ለመሰዋት በተዘጋጀበት ወቅት አላህ በልጁ ምትክ የበግ ጥቦት እንዲሰዋ ማድረጉን ለማሰብ ነው፡፡ የኃይማኖቱ ተከታዮች ይህንን ድርጊት ከማሰብ ጎን ለጎን ከፈጣሪ ጋር ያላቸውን ቅርበት ለማጠናከር፣ ለፈጣሪ ያላቸውን ታማኝነት ለመግለጽ፣ ፈጣሪን ለማስደሰትና ከክፉ ነገር ለመጠበቅ በሚል የዕርድ ስርዓት ይፈጽማሉ፡፡

በእስልምና ኃይማኖት ለዕርድ መስዋዕትነት የሚቀርቡ እንስሳት በጥንቃቄ ይመረጣሉ፡፡ ለዕርድ የሚመረጡ እንስሳትም ዐይናቸው ያልጠፋ፣ አጥንታቸው ያልተሰበረ፣ ጆሯቸውና ጭራቸው ያልተቆረጠ፣ ቀንዳቸው ያልተሰበረና ጥርሳቸው ያልተሸረፈ መሆን አለበት (Iqabal, 2013፡27)፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚከበረው የኢድ-አል-አድሃ በዓል ከመድረሱ በፊት ከተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ ስፍራው ይመጣል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦችና የአካባቢው ነዋሪዎች ለእርድ የሚሆን ግመል፣ ከብት፣ ፍየል ወይም በግ በጥንቃቄ መርጠው ይገዛሉ፤ ያርዳሉ፡፡ ለበዓል የሚሆኑ የተለያዩ ምግቦችን ያዘጋጃሉ፡፡ ሁሉም አቅሙ በፈቀደ መጠን ለበዓል አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ምግቦች ያዘጋጃል፡፡

## 8.2 የዋሬ ስርዓተከበራ

"ዋሬ" (Waaree) የሚለው ቃል የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ በመካነ ቅርሱ ሶስት ጽንሰሃሳቦችን ይገልጻል፡፡ አንደኛው ስብሰባ (መሰባሰብ) ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው፣ በስብሰባው ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን ሲሆን፣ ሶስተኛ ደግሞ የመሰብሰቢያ ቦታው ነው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት በመካነ ቅርሱ የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በአንድ ላይ በመሰባሰብ የተለያዩ ስርዓቶችን ይፈጽማሉ፡፡ በመካነ ቅርሱ መንፈሳዊ ተጓዦች በጋራ የሚሰባሰቡበት ስፍራና ተሰባስበው የሚከውኑት ስርዓት በጥቅሉ ዋሬ ይባላል፡፡

በመካነ ቅርሱ የዋሬ ስርዓተከበራዎች የሚከወኑባቸው ስፍራዎች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም፡- አንደኛ፣ ዶቆ ከራ (Dhooqqoo karra) ሲሆን፣ የሚገኘው በግምብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ዋናው መግቢያ በር ፊት ለፊት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ዶቆ ድንኩሬ (Dhooqqoo Diinkuree) ሲሆን፣ የሚገኘው በድንኩሬ የውኃ ኩሬ አጠገብ ነው፡፡ በዶቆ ከራና በዶቆ ድንኩሬ የሚከወኑ የዋሬ ስርዓትከበራዎች የሚከወነው ቀንና ሌሊት (24 ሰዓት) ነው፡፡ እነዚህ ሁለት የዋሬ ስፍራዎች ላይ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡

በዋሬና በሌሎች የመካነ ቅርሱ ስፍራዎቸ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ከመጀመራቸው በፊት በመካነ ቅርሱ የተገኙ መንፈሳዊ ተጓዦች ሁሉ በዶቆ ከራ ዋሬ ላይ ይሰበሰባሉ፡፡ በዶቆ ከራ የዋሬ ስርዓተከበራ በጋራ ይጀመራል፡፡ በስፍራውም የተወሰኑ ስርዓተከበራዎች ከተከወኑ በኋላ በአንድ ላይ በስፍራው ተሰባስቦ የነበረው ሰው ወደሚፈልገው ስፍራ በመሄድ በተለያዩ ቦታዎች በሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ላይ መሳተፍ ይጀምራል፡፡

የዋሬ ስርዓተከበራ የሚጀመርበት ሰዓት በሁለቱ የሙዳ በዓላት ይለያያል፡፡ በሐጅ የሙዳ በዓል ወቅት የዋሬ ስርዓተከበራ የሚጀምረው በማለዳ የሚካሄደው የሕብረት ስግደት ከተጠናቀቀ በኋላ ነው፡፡ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ መንፈሳዊ ተጓዦች የሕብረት ስግደት ፈጽመም፣ በየቤታቸው ያዘጋጁትን የበዓል ምግብ ከቀመሱ በኋላ ወደ ዋሬ ስፍራዎች በመሄድ ክወናዎቹን ያካሂዳሉ፡፡ በሐጅ የሙዳ በዓል ወቅት የዋሬ ስርዓት የሚጀምረው ከረፋዱ 3 ሰዓት እስከ 4 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በዕለቱ የዋሬ ስርዓተከበራ ረፋድ ላይ ቢጀምርም፣ በይፋ መከበር የሚጀምረው ግን ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በዛሕራ ገልገላ ጎበና የሙዳ በዓል ወቅት የዋሬ ስርዓት የሚጀመረው ደግሞ ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

## 8.2.1 የዋሬ ስርዓተከበራ የአጀማመር ስርዓቶች

የሐጅ የሙዳ በዓል መከበር የሚጀምረው ማለዳ በሚካሄድ የሕብረት ስግደት መሆኑን፣ የዛሕራ በዓል ደግሞ ምሽት ላይ እንደሚጀምር ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የሁለቱ የሙዳ በዓላት አጀማመር መለያየትም፤ በበዓላቱ ወቅት የሚከወን የዋሬ ስርዓተከበራ የሚጀመርበት ሰዓት መለያየት ምክንያት ነው፡፡ በሁለቱ የሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወነው የዋሬ ስርዓት የሚጀምርበት ሰዓት ቢለያይም በይፋ የሚጀምርበትና ዋና ዋና ክወናዎች የሚከወኑበት ምሽት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለቱም በዓላት ወቅት የዋሬ ስርዓተከበራ በተመሳሳይ ሰዓትና

በተመሳሳይ የስርዓት ክወና ሂደት በይፋ ስለሚጀምር የዋሬ ስርዓት የአጀማመር ክወናዎችን በአንድ ላይ መመልከት ያስችላል፡፡

የዋሬ ስርዓት ክወና የሚጀመረው በዶቆ ከራ ላይ በሚገኝ የደረጃ መቀመጫ ቦታ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚገኙ ምህንድስናዎች መካከል በደረጃ የተሰሩ መቀመጫዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የደረጃ መቀመጫዎች የተለያዩ በዓላት በሚከበሩባቸው ቦታዎች ላይ የተገነቡ ናቸው፡፡ የደረጃ መቀመጫዎቹም የአምፊ ትያትር ማሳያ አይነት ቅርጽ ያላቸው ናቸው፡፡ በመካነ ቅርሱ 2 ቦታዎች ላይ እነዚህ የደረጃ መቀመጫዎች ተገንብተዋል፡፡ ቦታዎቹም ዶቆ ከራና ዶቆ ድንኩሬ በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ በበዓላት ወቅት ሕዝቡ በእነዚህ የደረጃ መቀመጫዎች ላይ በመቀመጥ የተለያዩ ስርዓተከበራዎችን ይከውናል፤ ሲከወኑ ይመለከታል፡፡ መቀመጫዎቹም በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ላይ በሼኽ መሃመድና በሼኽ አባስ እንደተገነቡ ይነገራል፡፡

በዓላቱን ለማክበር በመካነ ቅርሱ የተሰባሰቡ መንፈሳዊ ተጓዦች፣ ተጋባዥ እንግዶችና የአገር ሽማግሌዎች ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ በዶቆ ከራ የደረጃ መቀመጫ ስፍራ መሰባሰብ ይጀምራሉ፡፡ ሁሉም ሰው በዶቆ ከራ በተሰራው የደረጃ መቀመጫዎች ላይ ወይም መሬት ላይ በመቀመጥ ስርዓቱን ይታደማል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች፣ ተጋባዥ እንግዶችና የአገር ሽማግሌዎች በስፍራው ከተገኙ በኋላ የዋሬ ስርዓተከበራ ከምሽቱ 2 እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ይጀመራል፡፡



*ፎቶ 28፣ ዶቆ ከራ፤ የዋሬ ስርዓተከበራ መከወኛ ስፍራ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በዶቆ ከራ የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓቶችን የሚያስተባብሩ ግለሰቦች አሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በተለያየ ወቅት የአስተባባሪነት ኃላፊነት የተሰጣቸው ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት በዶቆ ከራ የሚከወነን ስርዓት የሚያስተባብሩት ሼኽ ከዲር ናቸው፡፡ ከዶቆ ከራ በተጨማሪ በየቦታው የሚካሄዱ ስርዓተከበራዎችን በኃላፊነት የሚመሩ መንፈሳዊ ግለሰቦችና የፕሮግራም መሪዎች አሉ፡፡ በስርዓተከበራዎች ላይ ልዩ ቦታ የሚሰጣቸው የኃይማኖት መሪዎች አምላክን ከሰው ልጅ ጋር የሚያገናኙ (Mediater) በምድር ላይ የአምላክ ተወካዮች እንደሆኑ Evans-Pritchard (1956፡292) ይገልጻል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች የአምላክ ተወካዮች ተደርገው ስለሚታዩም ይመስላል በመካነ ቅርሱ በሚገኙ መንፈሳዊ ተጓዦች ዘንድ ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል፡፡

በሁለቱም የሙዳ በዓላት ወቅት ምሽት ላይ የሚከወነው የዋሬ ስርዓተከበራ የሚጀምረው ቅዱስ ቁርዓን በመቅራት ነው፡፡ በዕለቱ ከቅዱስ ቁርዓን ሱራዎች (ምዕራፎች) መካከል የያሲን ሱራ (ሱራ፣ 36) ይቀራል፡፡ ከያሲን ሱራ መካከል የተወሰኑትን ሀረጋት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኃይማኖት ትምህርት የሚማሩ ደረሳዎች በጋራ በመሆን ይቀራሉ፡፡ እነዚህ ደረሳዎች በሕብረት በመሆን ቁርዓን ሲቀሩ፣ ስርዓቱን በበላይነት የሚመሩት በተለያየ ጊዜ የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ መስኪድ ኢማም የሆኑ የኃይማኖት አባት ናቸው፡፡ ቁርዓን የመቅራት ስርዓት ሲጠናቀቅ የ"ሰለዋት" ስርዓት ይጀመራል፡፡ በስርዓቱም አላህ፣ ነብዩ መሃመድ፣ ሼኽ ሁሴንና ሼኽ ሶፍዑመር ይወደሳሉ፤ ይመሰገናሉ፡፡

የሰለዋት ስርዓት እንደተጠናቀቀ የአገር ሽማግሌዎች ፕሮግራም ይጀመራል፡፡ በዚህ ፕሮግራም ከባሌና እና ከአርሲ የተመረጡ የአገር ሽማግሌዎች ከተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በመቆም ንግግር ያደርጋሉ፡፡ የአገር ሽማግሌዎች ቁጥር እንደሁኔታው ሁለት፣ ሶስት ወይም አራት ሊሆን ይችላል፡፡ የአገር ሽማግሌዎች የሚመረጡት ከባሌ ዞን እና ከአርሲ ዞን ሲሆን፣ በአዋቂነታቸው፣ በእድሜያቸው፣ በአገልግሎት ዘመናቸው፣ በስነምግባራቸው፣ በጎሳቸው ወይም በቤተሰባቸው (በዘራቸው) የሚመረጡ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መስፈርቶች በተጨማሪ በቤተሰብ ውርስ ሊመረጡ ወይም በመካነ ቅርሱ ቋሚ ደገሌ ካላቸው ጎሳዎች ወይም ቤተሰቦች መካከል አንጋፋ የሆኑት ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ የሙዳ በዓላትን የሚያስጀምሩ የአገር ሽማግሌዎች አንዴ ከተመረጡ በጣም ካልሸመገሉ ወይም ካልሞቱ በስተቀር አይቀየሩም፤ ቋሚ ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገር ሽማግሌነት የሚያገለግሉት ሐጂ ጆዋሮ (ከአርሲ)፣ ሐጂ ሻፊ (ከባሌ) እና

ሐጂ ኪሞ (ከአርሲ) ናቸው፡፡ የአገር ሽማግሌዎቹ የንግግር ይዘት በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው፡፡ ይዘቱም ስለሼኽ ሁሴን ገድል፣ ስለሕዝቡ መንፈሳዊነት፣ ስለመካነ ቅርሱ ሁኔታ፣ ስለበዓላቱ፣ በመካነ ቅርሱ፣ በአካባቢው ወይም እነሱ በመጡበት አካባቢዎች ስለተከሰቱ ችግሮች፣ በአካባቢው ስለተሰሩ የልማት ስራዎች እንዲሁም መፍትሄ ያስፈልገዋል ስለሚሉት ጉዳይ የሚገልጽ ነው፡፡

የአገር ሽማግሌዎች ባቀረቧቸው ጉዳዮች መሰረት መልካም ስራ የሰሩ ግለሰቦችን፣ የመንግስት አካላትንና መንግስትን ይመርቃሉ፡፡ ለመካነ ቅርሱ ወይም ለአካባቢው ጥሩ ስራ ሰርተዋል የተባሉ ግለሰቦች በስም በመጥራት፣ የሰሯቸውን ስራዎች በመግለጽ ይመርቃሉ፡፡ ግለሰቡም ሕዝቡ ፊት በመቆም ምርቃቱን ይቀበላል፡፡ መንግስት ሰላም ስለሰጠን፣ ልማት ስለሰጠን፣ በዓሉን በሰላም እንድናከብር ስላደረገን በሚል ይመረቃል፡፡



*ፎቶ 29፣ የዋሬ ስርዓተከበራ በዶቆ ከራ በሌሊት ሲከወን የሚያሳይ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

መልካም ስራ ሰርተዋል የተባሉ የመካነ ቅርሱ ሀላፊዎችና ሰራተኞች፣ የወረዳ፣ የዞን፣ የክልል፣ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በስም እየተጠሩና የሰሯቸው ስራዎች እየተገለጹ ይመረቃሉ፡፡ ስማቸው የተጠቀሱ የመንግስት መስሪያ ቤቶችንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመወከል የመጡ ኃላፊዎች ሕዝቡ ፊት በመቆም ምርቃቱን ይቀበላሉ፡፡ የአገር ሽማግሌዎች ጥፋት አጥፍተዋል ያሏቸውን ቡድኖች ይረግማሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚረግሟቸው ቡድኖች የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮችን ነው፡፡ በአገር

ሽማግሌዎች ለእርግማን ከሚያበቁ ጉዳዮች መካከል መስኪድ ማቃጠል ወይም ማፍረስ፣ ገሞ ማፍረስ፣ ደንቂ መስበርና ገሪባን መምታት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰቱ ችግሮች በአገር ሽማግሌዎች ትኩረት ተደርጎባቸው የሚቀርቡ ጉዳዮች ናቸው። በአብዛኛው ተደጋግመው የሚነሱ የአካባቢው ችግሮች የንፁህ መጠጥ ውኃ አለመኖር፣ መብራት አለመኖር፣ የመንገድ ችግር፣ የፀጥታ ችግር፣ የመጸዳጃ ቤት ችግር፣ በበዓላት ወቅት ስለሚከሰት የኮሌራ ወረርሽኝ እንዲሁም በበዓላት ወቅት የትራንስፖርት ዋጋ ታሪፍ መጨመር ናቸው። እነዚህን ችግሮች የሚመለከተው የዞን፣ የክልል ወይም የፌዴራል የመንግስት አካላት መፍትሄ እንዲሰጡ ይጠይቃሉ።

በተለያዩ አካባቢዎች ተከስተዋል ብለው ላቀረቧቸው የረሃብ፣ የድርቅ፣ የዝናብ እጥረት፣ የጦርነት፣ የወረርሽኝና መሰል ችግሮች ዱዓ (ፀሎት) ያደርጋሉ። ፀሎት የሚደረግባቸው በአናጂና ቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልል፣ በአገር እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ ችግሮችን ያካትታል። በመጨረሻም የአገር ሽማግሌዎቹ በዓሉን ለማክበር ለመጣው ሕዝብ፣ ለአካባቢው ነዋሪ፣ ለመንግስት፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ሕዝብ ሰላም፣ እድገትና ጤና ፈጣሪ እንዲሰጥ በመመረቅ ፕሮግራማቸውን ያጠናቅቃሉ።

የአገር ሽማግሌዎች ፕሮግራም ሲጠናቀቅ የካቢኔ ፕሮግራም ይጀመራል። የሙዳ በዓላት ወቅት ከወረዳ እስከ ፌዴራል ድረስ ያሉ ካቢኔዎች ይመጣሉ። ሁሉም ካቢኔዎች በዓላቱ በሚጀመሩበት ዕለት መገኘት አለባቸው። ካቢኔዎቹ ለሐጅ የሙዳ በዓል ማለዳ በሚደረገው የሕብረት ስግደት ላይ ለመገኘት በዋዜማው አናጂና ገብተው ያድራሉ። ለዛህራ ገልገላ ጎበና የሙዳ በዓል ደግሞ በዓሉ ምሽት ላይ የሚጀምር በመሆኑ በዕለቱ አናጂና መግባት አለባቸው። ለካቢኔዎች በዋሬው ስፍራ የክብር ቦታ ይዘጋጅላቸዋል። ለካቢኔዎች የሚዘጋጅላቸው የክብር ቦታ ቋሚ ሲሆን፣ ስፍራውም ከራ ዳባ ጎምቢሶ አጠገብ ነው። ከራ ዳባ ከግምብ አጥሩ ዋና መግቢያ ፊት ለፊት የሚገኝ ነው።

የካቢኔ ፕሮግራም ሲጀመር፣ በስፍራው የተገኙ ካቢኔዎች ሁሉም በሕዝቡ ፊት ይቆማሉ። የፕሮግራም አስተባባሪው የሁሉንም ካቢኔዎች ስምና የመጡበትን መስሪያ ቤት በመግለጽ ለሕዝቡ ያስተዋውቃቸዋል። የፕሮግራም አስተባባሪው ስለእነሱ፣ ስለመስሪያቤታቸውና ስለመንግስት መልካም ጎኖች እያነሱ ያመሰግናሉ፤ ያወድሳሉ። የፕሮግራም አስተባባሪው

አብዛኛውን ጊዜ በአሁኑ ወቅት ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ሲያወድሱ ይስተዋላል እንጂ ከመንግስት ጋር ሊያጋጭ የሚችል ነገር በፍጹም አያነሱም፡፡

በስፍራው የተገኙ ካቢኔዎች በመካነ ቅርሱና በአካባቢው ስለተሰሩ የልማት ስራዎች ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ መንግስት የሰራቸውን መልካም ስራዎች ይገልጻሉ፡፡ በመካነ ቅርሱና በአካባቢው ለወደፊት በዕቅድ የተያዙ ስራዎች ካሉ ይገልጻሉ፡፡ በአገር ሽማግሌዎች የተገለጹ ችግሮችን በሂደት ለመፍታት እንደሚሰሩና ለሚመለከተው የመንግስት አካል ሪፖርት እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ፡፡ በዞን፣ በክልል፣ በአገር ወይም በዓለምአቀፍ ደረጃ የተከሰቱ ችግሮች (ጦርነት፣ ወረርሽን፣ ድርቅ፣ ረሃብ ወዘተ.) ከተከሰቱ ጸሎት እንዲደረግ ይጠይቃሉ፡፡

በበዓላት ወቅት በስፍራው የኮሌራ ወረርሽን በአብዛኛው ይከሰታል፡፡ ከዞን ጤና ቢሮ የተወከለ አንድ ሰው ስለኮሌራ ወረርሽን ሕመምና ሕዝቡ ማድረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ያስተምራል፡፡ ከኮሌራ ወረርሽኝ በተጨማሪ ስለኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ፣ ስለወባ እንዲሁም በወቅቱ አሳሳቢ ስለሆኑ ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ለሕዝቡ ትምህርት ይሰጣል፡፡

ካቢኔዎችና የመንግስት ቢሮ ሀላፊዎች የመጡበትን ቢሮ በመግለጽ የገንዘብ ስጦታ ያበረክታሉ፡፡ አንድ መስሪያ ቤት ከ5,000 ብር እስከ 10,000 ብር ስጦታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በ2008 ዓ.ም. የዛህራ ገልገላ ጎበና በዓል ላይ የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ የ50,000 ብር የገንዘብ ስጦታ ሰጥቷል፡፡ ይህ ገንዘብም በመካነ ቅርሱ የመጸዳጃ ቤት ግንባታ የሚውል ነው፡፡ የቢሮ ተወካዮች የገንዘብ ስጦታ ከሰጡ በኋላ መስሪያ ቤታቸው በመካነ ቅርሱና በአካባቢው ሊሰራ ስላቀዳቸው የልማት ስራዎች ይገልጻል፡፡ የገንዘብ ስጦታው ስርዓት እንተጠናቀቀ ሁሉም ካቢኔዎች ሕዝብ ፊት በመቆም ይመረቃሉ፡፡ ወደ ክብር መቀመጫ ስፍራቸውም ይሸኛሉ፡፡

በዶቆ ከራ የሚካሄደው የካቢኔዎች ፕሮግራም እንደተጠናቀቀ ታዳሚው እንደፍላጎቱ ወደ ተለያዩ የመካነ ቅርሱ ስፍራዎች በየስፍራዎቹ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን ለመከታተል፣ ከዋኞችም መንፈሳዊ ክወናዎችን ለመከወን ይሄዳሉ፡፡ በዶቆ ከራ ላይ የሚካሄዱ ሌሎች የዋሬ ስርዓተከበራዎችን የሚከውኑና የሚከታተሉ ደግሞ እዛው ይቆያሉ፡፡



*ፎቶ፡-30፤ የዶቆ ድንኩሬ የደረጃ መቀመጫ ከፊል ገጽታ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በዶቆ ከራ የሚከናወነው የካቢኔ ፕሮግራም እንደተጠናቀቀ በመካነ ቅርሱ በተለያዩ ስፍራዎች የሚከወኑ ስርዓቶች ይጀምራሉ፡፡ የዋሬ ስርዓትም በዶቆ ከራ ከተጀመረ በኂላ የካቢኔ ፕሮግራም ሲጠናቀቅ የተወሰነው ሕዝብ ወደ ዶቆ ድንኩሬ የዋሬ ስፍራ በመሄድ ስርዓቱን ይከታተላል፡፡ በሁለቱ ስፍራዎች የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን የሚመሩ የፕሮግራም አስተባባሪዎችና ወንበራ (Wanbara) አሉ፡፡ ወንበራ የሚል የማዕረግ ስም የሚሰጣቸው የዋሬ ፕሮግራም ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ዋሬው መሃል በተዘጋጀላቸው ልዩ ቦታ ቆመው ወይም ቁጭ ብለው ዋሬን የሚመሩ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት የዶቆ ከራን ዋሬ በፕሮግራም አስተባባሪነት የሚመሩት ሼኽ ከዲር ሲሆኑ፣ የዋሬው ወንበራ ደግሞ ሼኽ ፈይሰል ናቸው፡፡ የዶቆ ድንኩሬን ዋሬ በፕሮግራም አስተባባሪነት የሚመሩት ሼኽ መሃመድ ሲሆኑ፣ የዋሬው ወንበራ ደግሞ ሼኽ ታጁ ናቸው፡፡ የዋሬ ፕሮግራም አስተባባሪዎች የሚመረጡት ባላቸው የመድረክ አመራር ችሎታና የማስተባበር አቅም ነው፡፡ የዋሬ ወንበራ በቤተሰብ ውርስ የሚገኝ ሹመት ነው፡፡

ሼኽ ፈይሰል የዋሬው ወንበራ የሆኑት ዋሬውን ይመሩ የነበሩት አባታቸው ሼኽ ዑመር ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኂላ ነው፡፡ ሼኽ ታጁም የድንኩሬን ዋሬ ወንበራ ሆነው መምራት የጀመሩት ዋሬውን ይመሩ የነበሩት አባታቸው ሀጂ ሀሰን ዳሞሌ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኂላ ነው፡፡ ወንበራዎች ጥቁር ካባ በመልበስ፣ አናታቸው ላይ የተለየ እጅ ስራ ያለው ቆብ

መሰል ነገር በማድረግና በዋሬ ስፍራ መሃል ላይ በቆመው ፕሮግራሙን ይመራሉ። የሚለብሱት ካባና ቆብ መሰል ነገር ከአባታቸው በውርስ የሚረከቡት ነው። እነዚህ አልባሳትም ያላቸውን ልዩ ማህበራዊ ደረጃና ስልጣን ያሳያሉ።

በዶቆ ከራና በዶቆ ድንኩሬ የሚካሄዱ የዋሬ ስርዓቶች ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህ ስርዓቶች ሲከወኑም በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ነው። ስርዓቶቹም የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና፣ የሂክማ ስርዓት፣ የአርጆማ ስርዓት፣ ስለት የማስገባት ስርዓት፣ የጪንጫ ስርዓት፣ የምረቃ ስርዓት፣ የእርግማን ስርዓት፣ የምህላ ስርዓትና የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና ናቸው። እነዚህ ክወናዎች ያላቸውን ባህርይ በተናጠል ቀጥለን እንመለከታለን።

## 8.2.2 የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚከወኑ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች መካከል አንዱ ነው። ባሮ (Baaroo) የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው ‹ባሕር› የተገኘ ሲሆን፣ በአርሲ ‘ባሕር’ ሼኽ ሁሴንን ለማወደስ የሚያገለግል ቃል እንደሆነ Jeylan (2005:34) ይገልጻል። ተከታዮቻቸው ሼኽ ሁሴንን ሲያወድሱ ‘ባሕረዎ’ (baahrawoo) ይሏቸዋል። ‘ባሕረዎ’ ማለት የአረብኛውን ባሕር የሚለውን ቃል ኦሮምኛዊ በማድረግ ‘ባሕር የሆኑ’ ለማለት ነው። ቃሉም ሼኽ ሁሴን ባሕር መሆናቸውን ይገልጻል። ባህር የሚለው ትዕምርት ሆደ ሰፊ፣ ቻይ፣ ታጋሽና ትዕግስተኛ የሚሉትን እሳቤዎች ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ነው።

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሼኽ ሁሴንን ለማወደስ በግጥም ቅርጽ የሚቀርብ ነው። በመንፈሳዊ ሙዚቃውም የሼኽ ሁሴንን ተዓምራት፣ ፈጥኖ ደራሽነት፣ ታጋሽነትና ሩሕሩሕነት ይገለጽበታል። በባሮ ከሼኽ ሁሴን በተጨማሪ ፈጣሪን፣ ነብዩ መሃመድን፣ ሼኽ ሶፍዑመርን፣ ሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒን በዋናነት ይወደሳሉ፤ ይለመናሉ። የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሼኽ ሁሴን ለሰዎች (ለግለሰቦች) የዋሉትን ውለታ፣ በክፉ ቀን እንዴት ፈጥነው እንደደረሱላቸው ይገልጹበታል። ከእነዚህ መንፈሳዊ ጉዳዮች በተጨማሪ በስፍራው ተከስተዋል ተብለው የሚታመኑ ሚቶችን፣ ታሪካዊ ሁነቶችን፣ የሼኽ ሁሴን ተከታዮች መከወን ስለሚገባቸው ስነምግባራዊ ጉዳዮች፣ ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች እንዲሁም ወደፊት የሚፈጸሙ ሁነቶችን (ትንቢቶችን) በባሮ ይገልጻሉ።

በመካነ ቅርሱ የተለያዩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ይከወናሉ። እነዚህም መንፈሳዊ ሙዚቃዎች የራሳቸው ልዩ ባህርያት አላቸው። የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃም የራሱ የተለዩ ባህርያት አሉት።

ከእነዚህ ባህርያት መካከል በአንድ ሰው ብቻ የሚከወን መሆኑ፣ ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስዱ ግጥሞች ያሉት መሆኑ፣ በሌሊት (ከምሽቱ 3 ሰዓት እስከ ንጋቱ 10 ሰዓት) ብቻ የሚከወን መሆኑ፣ በምንም አይነት የሙዚቃ መሳሪያ የማይታጀብ መሆኑ፣ በጭብጨባ የማይታጀብ መሆኑ፣ አንዱ ከዋኝ ለተወሰነ ጊዜ ባሮ ካለ በኋላ ሌላኛው ከዋኝ ተቀብሎት የሚቀጥል መሆኑ፣ አልፎአልፎ የባሮ ግጥሞች የወዲያው (Immediate) ፈጠራዊነት ባህርይ ያላቸው መሆኑ፣ በከፍተኛ እርጋታና በመንፈስ መመሰጥ የሚከወን መሆኑ፣ አድማጩም በከፍተኛ ተመስጦ የሚከታተለው መሆኑ፣ ታዳሚውም በተወሰኑ የግጥም አዝማቾችን ብቻ ከከዋኙ ጋር አብሮ ከማዜም በስተቀር የጎላ ተሳታፊ አለመሆኑ ናቸው፡፡

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ በዋሬ ስርዓት ወቅት እንዲሁም በቤት ውስጥ በሚከወን የሀድራ ስርዓት ላይ የሚቀርብ ነው፡፡ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም በአብዛኛው በኦሮምኛ ቋንቋ የሚቀርብ ነው፡፡ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ በኦሮምኛ ሲቀርብ በግጥሞቹ ውስጥ አልፎአልፎ የአማርኛ፣ የአረብኛ፣ የእንግሊዝኛ፣ የሱማልኛ እንዲሁም አንድን ቃል ከአንድ ቋንቋ (ከአረብኛ ወይም ከአማርኛ) በመውሰድ ኦሮምኛዊ ሆነው የተፈጠሩ ቃላትና ሀረጋት ይደባለቅበታል፡፡

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ መቼ እንደተጀመረ በትክክል አይታወቅም፡፡ የአጀማመር ታሪኩንም በሚመለከት ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡ እነሱም፡- አንደኛ፣ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ የተጀመረው ሼኽ ሁሴን ከዚህ ዓለም መለየታቸው እንደታወቀ፣ የእሳቸውን ታሪክና ስራዎች ለመግለጽ በሚል ነው፡፡[140] ሼኽ ሁሴን ከዚህ ዓለም ሲለዩ የእሳቸውን ታሪክና ስራዎች በባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጹት ሼኽ ሶፍ ዑመር እንደሆኑ ይነገራል፡፡[141] በተመሳሳይም Eliyas (2013:67) ባሮን የጀመሩት ሼኽ ሶፍ ዑመር እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ ሁለተኛ፣ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ከቅርብ አመታት ወዲህ የተጀመረ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡[142]

በዋሬ ስርዓት ላይ ባሮ የሚቀርበው የተለያዩ ስርዓቶች በሚከወኑበት ወቅት መሀል መሀል ላይ ነው፡፡ ባሮ የሚሉ ኡሌዎችም በዋሬ ስፍራ ላይ በተለያዩ ቦታዎች ይቀመጣሉ፡፡ አንዱ ኡሌ ተነስቶ ባሮ ይላል፡፡ አንዱ ኡሌ ባሮ እያለ ሲደክመው ሌላው ኡሌ ይቀበለዋል፡፡ ኡሌዎቹ አንዱ ከሌላው እየተቀበለ በየተራ ባሮ ይላሉ፡፡ ኡሌዎች እየተቀባበሉ ባሮ ማለት ከጀመሩ ስሜት

[140] - ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡
[141] - ሼኽ ቃሲም ሐጂ አወል፣ አናጂና ቀበሊ፣ ሚያዝያ 8፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡
[142] - አቶ ኑማን ሼኽ መሐሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 26፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ውስጥ እየገቡና ይበልጥ እየተመሰጡ ይሄዳሉ። በዚህም ሳቢያ አብዛኛውን ጊዜ በፕሮግራም አስተባባሪዎች ትዕዛዝ ክወናውን እንዲያቆሙ ሲገደዱ ይስተዋላል።

ኡሌዎች እየተቀባበሉ ለሰዓታት ያለማቋረጥ ባሮ ይላሉ። በነሐሴ፣ 2009 ዓ.ም በተከበረው የሐጅ የሙዳ በዓል ወቅት ሶስት ኡሌዎች እየተቀባበሉ 1 ሰዓት ከ31 ደቂቃ ከ36 ሰከንድ ያለማቋረጥ ባሮ ያሉት በመስክ ቆይታዬ ወቅት ከሰበሰብኳቸው የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች መካከል ረጅሙ ነው። በመረጃ ስብሰባዬ ወቅት በአንድ ሰው ብቻ ሲከወኑ ከሰበሰብኳቸው የባሮ መንፈሳዊ ግጥሞች መካከል ረጅሙ 22 ደቂቃ ከ50 ሰከንድ የፈጀውና በሀሰን ሙሳ የቀረበው ባሮ ይገኝበታል።[143]

ኡሌዎች የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሲያቀርቡ በዋሬ ላይ በተሰበሰበው ሕዝብ መሃል በመቆም፣ ወይም ከፍ ያለ ቦታ ላይ በመውጣት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ነው። ባሮ ሲሉም በቀኝ እጃቸው የደንቄን በትር በመያዝ፣ በትሩንም ወደፊት፣ ወደ ላይ፣ ወደ ጎን በቀስታ በማወዛወዝ፣ ትከሻቸው ላይ በማድረግ እንዲሁም የግራ እጅ አመልካች ጣታቸውን በግራ የጆሯቸው ቀዳዳ ውስጥ በመክተት ይከውናሉ። የተሰበሰበው ሕዝብ የግጥሙን አዝማች ከኡሌው ጋር በአንድ ላይ በመድገምና በማዜም፣ በጥሞና በማዳመጥ፣ በማልቀስ፣ የጭብጨባ ድጋፍና የተለያዩ ሽልማቶችን በመስጠት የባሮ ክወና ተሳታፊ ይሆናል።

---

[143] - ሀሰን ሙሳ የ60 ዓመት እድሜ እንዳላቸው የሚናገሩ ሲሆን፣ ድምጻቸው እጅግ የሚያምርና የተከበሩ ኡሌ ናቸው። ክወናውን ያቀረቡት በድንኩሬ ዋሬ ላይ ነው።



*ፎቶ 31፤ ኡሌ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃን በመካነ ቅርሱ ሲከወን። (ፎቶ፣ በአጥኚው)*

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም የተለያዩ ይዘቶች አሉት። እነዚህን ይዘቶች ስለሼኽ ሁሴን፣ ስለስነምግባር፣ ስለታሪክ፣ ስለወቅታዊ ጉዳዮችና ስለወደፊት ትንቢት የሚገልጹ በሚሉ በአምስት መመደብ ይቻላል። በባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ የሼኽ ሁሴን ተዓምራት፣ ታሪክና ባህርይ ይገለጽበታል። በግጥሙም የሼኽ ሁሴንን ፈጥኖ ደራሽነት፣ አባትነት፣ ሩሕሩሕነት፣ መድኃኒትነት፣ ከችግር አውጪነት፣ የቅርብ ዘመድነትና ሁሉንም እኩል እንደሚያዩ ይገለጻል።

ኡሌዎች በባሮ አማካኝነት ሼኽ ሁሴን ስለሰሯቸው ተዓምራት እንዲሁም ግለሰቦች በሕይወታቸው ከደረሱባቸው ችግሮች እሳቸው እንዴት ፈጥነው እንዳወጧቸው በግጥም ይገልጻሉ። በባሮ አማካኝነት በበዓሉ ላይ የተሰበሰበው ሕዝብ ጥሩ ምግባር መስራት እንዳለበት፣ ለሰው ልጅም ሆነ ለፍጡራን ሁሉ አዛኝ መሆን እንዳለበት፣ እርስበርስ መከባበር፣ መረዳዳትና መተሳሰብ እንደሚገባ፣ መካነ ቅርሱን በአግባቡ መጠበቅ እንደሚገባ፣ የሌላን ሰው ንብረት ማውደምና መውሰድ እንደሚያስቀጣ፣ ልጆች ወላጆችን ማክበር፣ ወላጆች ደግሞ ልጆችን መውደድ እንዳለባቸው ይገለጻል።

በባሮ አማካኝነት በአገር ደረጃና በአካባቢው ስለተከሰቱ ታሪካዊ ሁነቶች ይገለጻሉ። ታሪካዊ ሁነቶች የሚገለጹት ከሼኽ ሁሴን ከራማ ጋር ባላቸው ተያያዥነት ነው። ታሪካዊ ሁነቶቹ በአገር ደረጃ ወይም በአካባቢው የተከሰቱ ጦርነቶች፣ የድርቅ ችግር፣ ረሃብ ወይም ወረርሽኝ

ይታወሳሉ። በመካነ ቅርሱ አካባቢ ወይም በአገር ደረጃ የተከሰቱ ወቅታዊ ጉዳዮች በባሮ አማካኝነት ይገለጻሉ። ወቅታዊ ጉዳዮችም ለመካነ ቅርሱ፣ ለመንፈሳዊ ተጓዦች ወይም ለአገር አስጊ ወይም ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ሁነቶች ነው። ወደፊት በመካነ ቅርሱ፣ በአካባቢው ወይም በአገር ደረጃ ሊከሰቱ የሚችሉ ሁነቶችም በትንቢት መልክ በባሮ ይገለጻሉ።

እነዚህ ትንቢቶች በስፍራው የተገኙ መንፈሳዊ ተጓዦች እውነት እንደሆኑና በትክክልም ይከሰታሉ ብሎ ያምናል። በመሆኑም መንፈሳዊ ተጓዦቹ በባሮ አማካኝነት የሚገለጽ የወደፊት የአካባቢውና የአገር እጣ ፈንታ ለማወቅ በከፍተኛ ጉጉት ያዳምጣሉ። ባሮውን የሚከታተሉ ታዳሚዎች የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃን በከፍተኛ ስሜት ውስጥ በመግባትና በማልቀስ ያዳምጣሉ። ታዳሚዎቹ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም አዝማችን ከዋኙ ብሎ እንደጨረሰ በጋራ ይደግማሉ። ከባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም አዝማች መካከል አንዱ

Shiililaa yaa baahrawoo Hagasinnaa yaa baarahoo

Rabbii keessanii jedhaa Kottaatii nu ilaalaa

ትርጉሙ፡-

ሺሊላ ባሕር የሆኑት

ለአምላኮ ብለው መጥተው ይዩን።

የሚል ነው።[144] "ሺሊላ" የሚለው ቃል በተለያዩ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችና በመካነ ቅርሱ የተለያዩ ስርዓተከበራዎች በብዛት አገልግሎት ላይ ይውላል። ነገር ግን የቃሉን ትክክለኛ ትርጓሜና የምን ቋንቋ ቃል እንደሆነ ማወቅ አልቻልኩም። የቃሉ ምንጭ በትክክል ባይታወቅም ቃሉ ያለው አውዳዊ ትርጓሜ "በእርስዎ መጀን"፣ "እርስዎን አመሰገንኩኝ" ወይም "ለእርስዎ ሰገድኩኝ" እንደማለት ነው። ከዋኙ በሕዝቡ መሃል ሆኖ በእጁ የያዘውን የደንቄ በትር ወደ ፊት፣ ወደ ላይ፣ ወደ ጎን እያወዛወዘ፣ አካሉን ወዲህና ወዲያ እያወዛወዘ፣ ከጉልበቱ ሸብረክ እያለ በጥልቅ ስሜት ውስጥ በመሆን በሚያስረቀርቅ ድምጽ የባሮን መንፈሳዊ ሙዚቃ ያቀርባል። ታዳሚውም እጅግ ጥልቅ የሆነ ስሜት ውስጥ ይገባል።

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ በቅኝት መደቡ "ዶሪያን ፔንታቶኒክ ስኬል" የሚባለውን የድምፅ አደራደር የያዘ ነው። የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ስኬል በኖታ ምልክት የሚከተለው ነው።[145]

---

[144] - በመካነ ቅርሱ የሙዳ በዓል ሲከበር ከተሰነደ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ የተወሰደ።

[145] - በዚህ ጥናት የቀረቡ የመንፈሳዊ ሙዚቃ ስኬል በኖታ ምልክት የሰራልኝ አቶ ሰርፀፍሬ ስብሃት ነው።



የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሌሊት ሲከወን፣ የአካባቢውን ድቅድቅ ጨለማ ለማሸነፍ ትግል ላይ ያለችው ጨረቃ ትልቅና ሙሉ ክብ ቅርጽ ይዛ፣ በአበልቃሲምና በደደላ ተራራዎች መሃል ብርቱካናማ መልኳን ይዛ፣ የአካባቢውን የሌሊት ብርድ ለመቋቋም ጋቢ፣ ፎጣና አናት ላይ ጥምጣም አድርጎ በደረጃ በተሰራውና የአንፊ ትያትር መመልከቻ በሚመስለው ስፍራ ላይ የተቀመጠው ሕዝብ ብዛት አንድ ላይ ሕብር ሲፈጥር በስፍራው መገኘት ልዩ ስሜትን ይፈጥራል፡፡

የኡሌዎቹ የሚያስደምም ድምጽና ሕዝቡ በጋራ አንድ ላይ የሚያወጣው ከፍተኛ ድምጽ በአቅራቢያው ከሚገኙ የአበልቃሲምና የደደላ ተራራዎች ጋር ሲላተም፣ የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች የውዳሴ፣ የምስጋና፣ የአትርሱን የምልጃ ጥሪዎች በባሮ አመካኝነት ወደ ሰማየ ሰማያት ሄዶ ከአምላክ ዘንድ ሲደርስ፣ ከሼኽ ሁሴን ዘንድ ሲደርስ፣ ከሼኽ ሶፍ ዑመርና ከሌሎች ቅዱሳን ዘንድ ሲደርስ፣ ድምጻቸው ደርሶም የአይዟችሁ፣ የአለንላችሁ ምላሽ በስፍራው ሲደርስ በዐይነ ሕሊና ይታያል፡፡

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ የሚያቀርቡ ከዋኞች በአብዛኛው ቀደም ሲል በአዕሯቸው የያዟቸውን ግጥሞች በማስታወስ ነው፡፡ ይህ የትውስታ ሂደት (Memorization) በከዋኙ አዕምሮ ውስጥ ቀደም ሲል ቅርጽ ይዞ የተቀመጠና ቀደም ሲል በራሱ በከዋኙ ወይም በሌሎች ግለሰቦች ድረሳ (Composition) የተካሄደበትን ነገር ማቅረብ ነው፡፡ የከዋኙም ተቀዳሚ ስራ ቀደም ሲል በአዕምሮ ውስጥ ቅርጽ ይዘው የተቀመጡ አህዶችን ማስታወስ ነው፡፡ ትውስታ ለስነ ቃል (Verbal art) መሰረታዊ ሞተር ነው (Friedman, 1961፡114)፡፡ በአዕምሯዊ ትውስታ አማካኝነትም በቃል የሚከወኑና በጣም ረጃጅም ስንኝ ያላቸው ቃል ግጥሞችንና ባላዶች (Ballads) ማቅረብ ያስችላል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና ወቅት ኡሌዎች እጅግ ረጃጅም ስንኝ ያላቸው ግጥሞችን በተናጠል ወይም በቡድን በመቀባበል ይከውናሉ፡፡ በመስክ ስራ ያለማቋረጥ ለበርካታ ደቂቃዎች ባሮ ማለት የተለመደ እንደሆነ አስተውያለሁ፡፡ ከዋኞች ይህን ያህል ረጅም ግጥም እንዴት ማስታወስ ቻላችሁ? የሚል ጥያቄ ለኡሌዎች አቅርቤላቸው ነበር፡፡

የእነሱም መልስ ፈጣሪ የሰጣቸው ልዩ ጸጋ እንደሆነና ሼኽ ሁሴን ኡሌ ሆነው እሳቸውን እንዲያገለግሉ ስለፈለጉ ግጥሙን በአዕምሯችን ጨመሩልን የሚል ነው፡፡[146]

እነሱ እንዲህ ቢሉም በጣም ረጅም ግጥሞችን በአዕምሮ በመያዝ በቀላሉ ማስታወስ የሚያስችል የቃላዊ- ፎርሙላዊ ሞዴል (Oral-Formulaic Model) መኖሩን Finnegan (1977፣58-73) ትገልጻለች፡፡ በዚህ ሞዴል መሰረት የሚደጋገሙ ቃላትን፣ የስንኙን የመጀመሪያውን ቃል፣ ተመሳሳይነት ያላቸውን ሕብሮች (Metrical unity) በማያያዝና ቋሚ የአስተሳሰብ መዋቅርን (Fixed pattern of thought) በመጠበቅ ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ሞዴልም ቀደም ሲል በአዕምሮ ውስጥ ቅርጽ ይዞ የተቀመጠን መረጃ ፎርሙላዊ በሆነ መንገድ (Formulaic way) ማቅረብ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡

በዚህ ሞዴል መሰረት ለበርካታ ደቂቃዎች ያለማቋረጥ ቃል ግጥም የሚያቀርቡት ኡሌዎች ቀደም ሲል በራሳቸው ወይም በሌሎች የተደረሰን ቃል ግጥም በአዕምሮ ውስጥ በመያዝ ክወናቸውን ያቀርባሉ፡፡ በአዕምሯቸው ውስጥ የያዙትንም ቃል ግጥም በሚደጋገም ቃል፣ ስንኙ በሚጀምርበት ቃልና በስፍራው የሚገኝ ማህበረሰብ ባለው ቋሚ አስተሳሰብ መነሻ በማድረግ በአዕምሮ ውስጥ በሚሰሩት የሂሳብ ቀመር አማካኝነት በቀላሉ ማስታወስ ይችላሉ፡፡

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥሞች አልፎአልፎ በክወና ወቅት የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ግጥሞቹ የድንገታዊነትና የወዲያዊነት ባህርይ አላቸው፡፡ ባሮን የሚከውኑ ኡሌዎች ክወናውን ካቀረቡ በኋላ በድንገት ስለገጠሟቸው ግጥሞች ይዘትና ግጥሞቹ ምን ለማለት ፈልገው እንደገጠሙ (ግጥሞቹን በማስታወሻ ይዤ) ጠይቂያቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ኡሌዎቹ እነዚህን ግጥሞች ምን ይዘት እንዳላቸው አያውቁትም፡፡ ከይዘታቸው ባለፈም እነዚህን ግጥሞች ማለታቸውንም አያስታውሱም፡፡ አዳዲስ ግጥሞችን በድንገት የፈጠሩት ኡሌዎች ምን እንዳሉ የማያስታውሱበትም ምክንያት ግጥሞቹን የገጠሙት በተለየ የመንፈስ ደረጃ ውስጥ ስለሚገቡና ግጥሞቹ በእነሱ አንደበት ይቅረብ እንጂ በልዩና በልዕለሰብዓዊ ኃይል (Superhuman power) አማካኝነት የተገጠመ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡[147]

ድንገታዊ ፈጠራን በመጨመር አዲስ የባሮ ግጥም ሲደርሱ ቀደም ሲል ከተለመደው የክወና ሂደት ወደ አዲስ ይቀየራል፡፡ ይህም የክወና ለውጥ ይፈጥራል፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ

---

146 - ኡሌ መሐመድ እና ኡሌ አደም፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 27 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

147 - ኡሌ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 27 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡.

የሚከሰትን የክወና ለውጥ ሂደት Bauman and Briddgs (1990) በአዲስና በተሻሻለ የክወና አተያይ አንጻር ከአውዱ ውጪ፣ በአውዱ ውስጥና በአሀዱ ውስጥ ሂደቶች በሚል ይገልጿቸዋል፡፡ በክወና ወቅት ቀደም ሲል ከነበረው በተለየ የለውጥ ሂደት ሲከሰት ከዋኙና ታዳሚው ትኩረት የሚያደርገው በአውዱ ላይ እንጂ በአሀዱ ላይ አይደለም፡፡ ይህ አይነት የትኩረት ለውጥን ቦውማንና ብሪጅስ በአውዱ ውስጥ በሚል ይገልጹታል፡፡ ነገር ግን ታዳሚው የለውጡን ሂደት በአሀዱ ላይ እንጂ በአውዱ ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ አይነት የትኩረት ለውጥን ቦውማንና ብሪጅስ በአውዱ ውስጥ በሚል ይገልጹታል፡፡

እነዚህ የለውጥ ሂደቶች በመኖራቸውም ምክንያት Bauman (2004፡53-57) እንደሚለው በክወና ወቅት ታዳሚዎችና ከዋኞች ራሳቸውን የክወናው ማዕከል፣ ከማዕከሉ ውጪ፣ ድግመ-ማዕከል፣ አውዳዊነት፣ ከአውድ ውጪና ድግመ-አውድ ሂደት ውስጥ በመጨመር ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ክወናዎች ትርጉም እንዲኖራቸውና በከዋኙና በታዳሚው መካከል ተግባቦት እንዲፈጥሩ የክወናው አሀድ፣ አውድና፣ የክወናው ለውጥ እንዲሁም የለውጡ ሂደት ወሳኝ ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን በሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ወቅት አውዱ የሚፈጥራቸው አዳዲስ ክወናዎች በየጊዜው ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ አዳዲስ ክወናዎች ትርጉም የሚሰጡት ከዋኙና ታዳሚው ተግባቦት ሲፈጥሩ ነው፡፡ ተግባቦት እንዲፈጥሩም የሚቀርቡት ጉዳዮች ማህበረሰቡ ቀደም ሲል በሚያውቀውና በሚረዳው አውድ መነሻነት ነው፡፡ በኡሌዎችም የሚፈጠር አዳዲስ የባሮ ግጥሞች ነባሩን አውድ መሰረት አድርገው ድጋሚና በሌላ ቅርጽ የሚፈጠሩ ናቸው፡፡

## 8.2.3 የሂክማ ስርዓት

በዋሬ ላይ ከሚከወኑ ስርዓቶች መካከል አንዱ የሂክማ ስርዓት ነው፡፡ "ሂክማ" የአረብኛ ቃል ሲሆን፣ ምስጋና የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህ ስርዓት መንፈሳዊ ተጓዦቹ ከዚህ በፊት የነበረባቸውን ችግር ለሼኽ ሁሴን በመንገር፣ ከነበረባቸው ችግር መፈወሳቸውን፣ በስፍራው መጥተው የጀዋራ ቅዱስ አፈር ከተቀቡና ዘምዘም ከጠጡ በኋላ ከነበረባቸው የጤና ችግር መፈወሳቸውን፣ በስፍራው ደርሰው ከተመለሱ በኋላ ከነበረባቸው የገንዘብ፣ የሰላም፣ የጤንነት፣ የስኬት የመሳሰሉት ችግሮች መውጣታቸውን ተራ በተራ በመውጣት የሚገልጹበት፤ ምስጋና የሚያቀርቡበት ነው፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦቹ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ተራ በተራ በመቆም ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡ በሂክማ ስርዓት ወቅት ምስጋና አቅራቢዎች ለራሳቸው ከደረሰላቸው በተጨማሪ በቤተሰባቸው፣

በጓደኞቻቸውና በጎረቤቶቻቸው የደረሰላቸውን ይናገራሉ፡፡ ምስጋናቸውን የሚያቀርቡ ግለሰቦች ከዚህ በፊት ደርሶባቸው የነበረውን ችግር በግልጽ ማቅረብ ግዴታቸው ነው፡፡ ከነበረባቸው ችግር ተላቀው አሁን በምን ደረጃ ላይ እንደደረሱ በግልጽ የመናገርም ግዴታ አለባቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች በግልጽ መናገር ያለባቸው አንድም የሼኽ ሁሴንን ተዓምራትና ፈጥኖ ደራሽነት ለተሰበሰበው ሕዝብ ለማሳወቅ፣ አንድም የሚደብቁት ወይም መናገር ሲገባቸው ያልተናገሯቸው ቢኖሩ የሼኽ ሁሴንን ውለታ ማሳነስ ተደርጎ ስለሚታመን ነው፡፡

ሂክማውን የሚያቀርበው ግለሰብ በራሱ አንደበት ይናገራል፡፡ በራሳቸው አንደበት መናገር የማይፈልጉ ወይም መናገር ያልቻሉ ግለሰቦች ደግሞ ለፕሮግራም አስተባባሪዎች በመንገር ፕሮግራም አስተባባሪዎቹ ለሕዝቡ ይናገራሉ፡፡ ሂክማ ሲነገር በዋሬ ስፍራ ለተሰባሰበ ሰው ሁሉ እንዲሰማ በድምጽ ማጉያ (ማይክራፎን) ድምጽ ከፍ ተደርጎ ይነገራል፡፡ ሂክማውን የተናገረ ግለሰብ ሀሳቡን ሲጨርስ ይመረቃል፤ ወደ ፊትም ተመሳሳይ ችግር በሕይወቱ እንዳይከሰት ይጸለይለታል፡፡

ግለሰቡ ላይ የደረሰው አይነት ችግር በስፍራው በተሰበሰበ መንፈሳዊ ተጓዦችና በቤተሰባቸው ላይ እንዳይከሰት ሕዝቡ ይመረቃል፡፡ ግለሰቡም ሆነ ሕዝቡ ሲመረቅ በስፍራው የተሰበሰበ ሰው ሁሉ ‹አሜን› በማለት ምርቃቱን ይቀበላሉ፡፡ ግለሰቡን ሕዝቡ በቱፍታ እንዲመርቀው የፕሮግራም አስተባባሪው ይጠይቃል፡፡ ቱፍታ፣ ምራቅን ቱፍ-ቱፍ በማድረግ የሚከወን የምረቃ አይነት ነው፡፡ ሕዝቡም ግለሰቡን ሲመርቅ፣ ግለሰቡ አሜን በማለት ይቀበላል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሙዳ በዓላት ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ መስክ በነበርኩባቸው ወቅቶች እጅግ በርካታ ሂክማዎች ሲቀርቡ ሰምቻለሁ፡፡ ሂክማዎቹን የሚናገሩ ግለሰቦች ከደረሰባቸው የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የልጅ፣ የሰላምና የፍትህ እጦት፣ የድንገተኛ አደጋዎችና መሰል ችግሮች እንዴት ሼኽ ሁሴንን ለምነው፣ እንዴት የሼኽ ሁሴንን ስም ጠርተው፣ እንዴት ሼኽ ሁሴን ድረስልኝ ብለው ከችግራቸው እንደወጡ የሚገልጹ ናቸው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት በዶቀ ከራና በዶቀ ድንኩሬ የሚነገሩ ሂክማዎች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ እጅግ አሳዛኝ፣ በሰው ልጅ ላይ ይደርሳሉ ተብለው የማይገመቱና የሰው ልጅ ያደርጋቸዋል ተብሎ የማይገመት ክፉ ድርጊቶች የደረሰባቸው ግለሰቦች ከችግራቸው እንዴት ሼኽ ሁሴን እንዳዳኗቸው ይናገራሉ፡፡

በከዋኞች አማካኝነት በቃል የሚተላለፉ ታሪኮች (Stories) በአድማጮች ዘንድ በአግባቡ እንዲደርሱና የተፈለገውን መልዕክት እንዲያስተላልፉ የሚጠቀሟቸው የተለየዩ ስልቶች አሉ፡፡

እነዚህን ስልቶች የምናጠናባቸው መንገዶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መንገዶች መካከል Jafferson (1973) የፈጠረው አውዳዊ ተግባቦት መሰረት ያደረገ ታሪክ (Contexted occurrence of stories in conversation) መንገድ አንዱ ነው፡፡ የዚህ መንገድ ዋናው ትኩረት የአድማጭን አዕምራዊ ስሜት በመቆጣጠር የታሪኩ ተጋሪ የሚሆንበትን መተንነተን ነው፡፡ በትረካው ወቅትም አድማጩ በትረካው የሚሰማው ታሪክ የራሱ ታሪክ እንደሆነ እንዲያስብ፣ የራሱን ቀደምት የሕይወት ተመክሮውን በማስታወስ ከታሪኩ ጋር ማገናኘት፣ ታሪኩን በሙሉ ስሜትና የእኔ ገጠመኝ ነው በሚል ስሜት በትክክል አዳምጦ ለሌሎች እንዲያስተላልፍ ማድረግ ነው፡፡

በዚህ መንገድ አድማጩ ለሚቀርበው ታሪክ ረዳት-ከዋኝ (Co-producer) ሚና አለው፡፡ አድማጩ ይህንን ሚናውን የሚወጣው ታሪኩን በሚያዳምጥበት ወቅት የተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ነው፡፡ የአድማጩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችም ጭንቅላትን መነቅነቅ፣ አንገትን ወደ ላይ መሳብ፣ የሰውነት አቅጣጫን መቀየር፣ ዐይንን ዐይን ማየት፣ ጥያቄ ማቅረብ (ከዛ እንዴት ሆነ፣ ቀጥሎስ፣ እሺ አይነት አገላለጽ) የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እርግጥ Jafferson (1973) እነዚህን የሰውነት እንቅስቃሴዎች በምሳሌ ቢያመጣም፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎች አካባቢያዊና ባህላዊ ትርጓሜያቸው በየአካባቢው እንደሚለያዩ ከግምት ማስገባት ይኖርብናል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በተለያዩ ግለሰቦች ሂክማ ሲቀርብ ታዳሚው ሂክማውን ከልብ እንዲያዳምጥ የፕሮግራም መሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ሂክማውን ለመናገር ሕዝብ ፊት የሚቆም ግለሰብ ሂክማውን መናገር ከመጀመሩ በፊት፣ የፕሮግራም መሪው "የሼኽ ሁሴንን ተዓምር ሁላችሁም ስሙ"፣ "ለሼኽ ሁሴን ሂክማ ምስክር ናችሁ"፣ "ኡ-ኡ-ኡ-"፣ "አድማጡ-አድምጡ"፣ "ይኸው-ይኸው" የሚሉ አገላለጾችን በመጠቀም አድማጩ ለሂክማው ትኩረት እንዲሰጥና በጥሞና እንዲያዳምጥ ያደርጋሉ፡፡ ሂክማውን የሚናገረው ግለሰብ ታሪኩን ሲናገር መሃል መሃል ላይ የፕሮግራም መሪው በድምጽ ማጉያ ለሁሉም ሕዝብ እንዲሰማ አድርጎ ይናገራል፡፡

ግለሰቡ ሂክማውን ሲናገር የፕሮግራም መሪው "ጉድ ነው"፣ "አጃዒብ"፣ "አብዮ"፣ "ቢስሚላሂ"፣ "አላህ" የሚሉ አገላለጾች በመጠቀም፣ ሂክማውን ከልቡ እያዳመጠና የተራኪውን ግለሰብ ስሜት እየተጋራ ስለመሆኑ ምስክርነት ይሰጣል፡፡ አድማጩም ሂክማውን በጥሞና እንዲያዳምጥ ይጠቀምበታል፡፡ ታዳሚውም ተራኪው የሚያቀርበውን ታሪክ በጥሞና እያዳመጠ ስለመሆኑ ጭንቅላትን በመነቅነቅ፣ በእልልታ፣ በጭብጨባ፣ የጭንቀት ድምጽ በማውጣት፣

በጥልቀት በመተንፈስ፣ በማልቀስ፣ በመሳቅ ወይም የደስታ ስሜት በማሳየት የተራኪውን ስሜት ተጋሪነቱን ይገልጻል፡፡ ይህም ታዳሚው የሚሰማውን ሂክማ ከራሱ የሕይወት ተመክሮና ገጠመኝ ጋር በማያያዝ ታሪኩን የራሱ እንደሆነ እንዲሰማው ያደርጋል፡፡

ሂክማ በሚነገርበት ወቅት የተናጋሪውን ግለሰብ ንግግር በማቋረጥ ድንገት አንድ ኡሌ ብድግ ብሎ የተሰማውን ስሜት በባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሊገልጽ ይችላል፡፡ ኡሌውም ክወናውን ሲጨርስ ሌላ ኡሌ ተነስቶ ባሮውን ሊቀጥል ይችላል፡፡ ይህ ዓይነት ሁኔታ የሚስተዋለው እጅግ ስሜት የሚነኩ፣ በጣም የሚያሳዝኑ ወይም በጣም የሚያስደስቱ ሂክማዎች በሚነገሩበት ወቅት ነው፡፡ ግለሰቡ ሂክማውን ተናግሮ ሲጨርስ የፕሮግራም መሪው አድማጩ በእልልታ፣ በጭብጨባ ወይም በምርቃት ስሜቱን እንዲገልጽ ያደርጋል፡፡ በመጨረሻም የሂክማውን መጠናቀቅ ለመግጽና አድማጩ የሰማውን ሂክማ ከራሱ ሕይወት ጋር እንዲያገናኝ የፕሮግራም መሪው እንዲህ ይላል፡፡[148]

Hikmaan Sheekanaa Husen Kana dhagahee.

Yoo sirritti kadhatan nama dhagahu Sheekanaa Huseen itti.

Sheek Huseen namaaf birmatan.

Abbaan keenya abbaa gootottaati.

Kan rakkate huundaaf furtuu wanta hundaati

Sheek Huseen jeettii keenyaa.

ትርጉሙም፤

የሼኽ ሁሴን ሂክማ ይህ ነው፣ አድምጡ

ከልብ ሼኽ ሁሴንን ከለመኑ ሰውን ይሰማሉ፡፡

ሼኽ ሁሴን የተቸገሩትን ይረዳል፡፡

አባታችን የጀግኖች ሁሉ አባት (ጀግና) ነው፡፡

ለተቸገረ ሁሉ ደራሽ ነው፡፡

ሼኽ ሁሴን ለተቸገረ ጀታችን ነው፡፡

ማለት ነው፡፡ ይህን የሚሉትም ሂክማውን የሚያዳምጡ ሰዎች በሼኽ ሁሴን ላይ ያላቸውን እምነት እንዲያጠነክሩና ለሼኽ ሁሴን ሂክማም ምስክር እንዲሆኑ ነው፡፡ የሼኽ ሁሴንንም

---

[148] - በመካነ ቅርሱ ሲከወን ከመስክ ከተሰነደ መረጃ የተወሰደ፡፡

አዳኝነት ሙሉ ማረጋገጫ ለመስጠት ነው፡፡ በዚህ ማረጋገጫ ውስጥ ሼኽ ሁሴን በ"ጀት" ተመስለዋል፡፡ ጀት ፈጣን ነው፡፡ ሼኽ ሁሴንም ስንቸገር ፈጥነው ይደርሱልናል ለማለት ነው፡፡ የፕሮግራም መሪውም ሂክማ የተናገረውን ግለሰብ ሼኽ ሁሴን ይድረስልህ (Sheekanaa Huseen siif haa birmatan)፣ አብዮ ይተባበሩህ (Abiyyoon siif haa birmatan) ወዘተ. እያለ ይመርቀዋል፡፡

የፕሮግራም አስተባባሪው ሲመርቅ፣ ሂክማ አቅራቢውም ሆነ ታዳሚው ሁለቱን እጆች ወደፊት ወጣ አድርጎ፣ መዳፉን ዘርግቶ፣ ወገቡን ሰበር፣ አንገቱን ወደ መሬት ቀበር አድርጎና ምርቃቱን "አሜን" እያለ ይቀበላል፡፡ አንድ ግለሰብ ሲመረቅ በስፍራው የተሰበሰበ ሰው ሁሉ በጋራ አሜን የሚልበትም ምክንያት፣ "ምርቃቱ ሂክማውን ለተናገረው ግለሰቡ ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር ነው፡፡ እሱ የተመረቀው ነገር ለእኛም ይደርሳል፡፡" ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ይህም ታዳሚው የሂክማ ክወና ተመልካች ብቻ ሳይሆን ንቁ ተሳታፊም እንዲሆን አስችሎታል፡፡ በመካነ ቅርሱ በዚህ የክወና መንገድ መሰረት ፕሮግራም መሪው በሂክማ አቅራቢው፣ በሚቀርበው ሂክማና በታዳሚው መካከል የስሜት ትስስር ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡ የሂክማ ክወናም የታዳሚን አዕምሯዊ ስሜት በመቆጣጠር የታሪኩ ተጋሪና ታሪኩ የእኔ ነው የሚል ስሜት እንዲፈጠርበት ያደርጋል፡፡

## 8.2.4 የአርጆማ ስርዓት

"አርጆማ" (Arjooma) የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ ስጦታ ወይም እርዳታ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህ ቃል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ "ኒያ" ከሚለው ቃል ጋር በአቻዊነት ያገለግላል፡፡ "ኒያ" ካሉት የተለያዩ ትርጉሞች መካከል አንዱ ስጦታ መስጠት ማለት ነው፡፡ በስፍራውም እነዚህን ሁለት ቃላት በመቀያየር መጠቀም የተለመደ ነው፡፡

በመካነ ቅርሱ የሚሰጡ ስጦታዎች የራሳቸው ስርዓት አላቸው፡፡ ስጦታ የመስጠት ስርዓት የአርጆማ ስርዓት በሚል ይታወቃል፡፡ የአርጆማ ስርዓትም በዋሬ ስፍራ የተሰበሰበው መንፈሳዊ ተጓዥ ለተለያዩ አካላት ስጦታ የሚሰጥበት ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን ለተለያዩ አካላት የሚሰጡ ስጦታዎች አሉ፡፡ እነዚህን ስጦታዎች ለግለሰብ፣ ለማህበረሰብ፣ ለመካነ ቅርሱ፣ ለኡሌና ለደርጋ የሚሰጡ በሚሉ አምስት ምደባዎች መግለጽ ይቻላል፡፡ እነዚህ አምስት የስጦታ ምደባዎች ያላቸውን ባህርያት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ለግለሰብ የሚሰጥ ስጦታ፣ በተለያዩ ምክንያቶች እርዳታ ለሚፈልጉ ግለሰቦች የሚሰጥ ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ የሚሰጡ ስጦታዎች ካላቸው ባህርያት አንጻር በግለሰብ ላይ የደረሰ ችግርና

የጋብቻ በሚል በሁለት መመደብ ይቻላል፡፡ የተለያዩ ግለሰቦች የደረሰባቸውን ችግሮች ለተሰበሰበው ሕዝብ በግልጽ በመናገር እርጆማ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ፡፡ ሕዝቡም ግለሰቦቹ ደረሰብን የሚሉትን ችግር አድምጦ፣ አቅሙ የፈቀደውን ስጦታ ይሰጣል፡፡ ግለሰቦች የሚያቀርቧቸው ችግሮች ኢኮኖሚያዊ ናቸው፡፡ እነዚህ ችግሮች በግለሰቡ ሕይወት ውስጥ የቆዩ ወይም ድንገት የተከሰቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ድንገት ከሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መካከል ወደ መጡበት አገር ለመመለስ ለትራንስፖርት የሚከፍሉት ገንዘብ ማጣት በአብዛኛው የተለመደ ነው፡፡

የተሰበሰበው ሕዝብ ችግራቸውን ላቀረቡ ግለሰቦች አቅሙ የፈቀደውን ያህል የገንዘብ ወይም የአልባሳት ስጦታ ይሰጣሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለግለሰቦች ስጦታ ሲሰጥ ሰጪው በጥልቅ ሀዘኔታና በሙሉ ፍላጎት ነው፡፡ ግለሰቦቹ ስጦታ ሲሰጡ በጥልቅ ስሜት ውስጥ መሆናቸው በአብዛኛው የተለያ ክስተት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህም ክስተት አንድ ግለሰብ ችግሩን ሲናገር የሰማ ግለሰብ በሁኔታው በጣም በማዘኑ ምክንያት ለተለያዩ ወጪዎች ይሆነኛል ብሎ የያዘውን ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ የሚሰጥበት አጋጣሚ የተለመደ ነው፡፡ ያለውን ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ እንደሰጠ ተረድቶ ለሌላ ግለሰብ ከተናገረ ወይም ሁኔታውን ሲመለከት የነበረና የግለሰቡን ችግር የተረዳ ሌላ ግለሰብ ለግለሰቡ እዛው የገንዘብ ወይም የአልባሳት ስጦታ ይሰጣል፡፡

አንድ ግለሰብ በሰማው ችግር ጥልቅ ሀዘን ሲሰማው እራሱ የለበሰውን ጃኬት፣ ሱሪ፣ ሽሚዝ፣ ሹራብ ወይም ፎጣ ሕዝብ ፊት አውልቆ ይሰጣል፡፡ ግለሰቡ በስሜት ሆኖ የለበሰውን አልባሳት አውልቆ ሲሰጥ "ሌላ ተቀያሪ አልባሳት አለኝ?፣ ይህ አዲስ ነው፣ ይህን ብሰጥ ይሻላል ወይም ይህ ልብስ ለግለሰቡ ይሆነዋል?፡፡" የሚሉ ሀሳቦችና ጥያቄዎች በአዕምሯቸው በፍጹም አይመጣም፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የዋሬ ስርዓተከበራ ወቅት የለበሱትን ልብስ አውልቀው ችግሩን ለተናገረ ግለሰብ ስጦታ ሰጥተው እርቃናቸውን ወደ ተቀመጡበት ስፍራቸው የሚመለሱ ግለሰቦችን ማየት የተለመደ ነው፡፡ ለእነዚህ ግለሰቦች ደግሞ ሳያስቡት ሌላ ግለሰብ የለበሰውን ልብስ አውልቆ ይሰጣቸዋል፡፡ ልብሱን አውልቆ ለሰጠውም ግለሰብ ደግሞ ሌላ ግለሰብ የራሱን አውልቆ ይሰጣል፡፡ ይህ አይነት የስጦታ አሰጣጥ ሂደት መንፈሳዊ ተጓዦቹ ያላቸውን የእርስበርስ ፍቅር፣ ተደጋጋፊነት፣ ተስፋነትና አለኝታነት የሚያሳይ ነው፡፡

ከጥቂት አመታት በፊት ለሙዳ በዓላት የሚመጡ ባለፀጋዎች ተቀምጠው ወይም እቃ ጭነው የመጡባቸውን በቅሎዎች፣ አህዮች ወይም ግመሎች በመካነ ቅርሱ ለሚገኙ፣ የኃይማኖት

ትምህርት ለሚያስተምሩና በመንፈሳዊነት ብቻ ለሚኖሩ ሼኾች ሸልመው በእግራቸው ወደ መጡበት አገር ተመልሰው ይገቡ ነበር፡፡ ለምግብ ማብሰያነት ይዘው የመጡትን የማብሰያ ዕቃ እንዲሁም የለበሱትን አልባሳት አውልቀው በአካባቢው ለሚገኙ ደኃዎች ይሰጣሉ፡፡ በምትኩም ደኃዎቹ ይለብሱት የነበረን አልባሳት በመልበስ ወደ መጡበት አገር ተመልሰው ይገቡ ነበር፡፡ የዚህ አይነቱ የአርጆማ አሰጣጥ ስርዓት "ሳሬ" ይባላል፡፡ ይህ ስርዓትም ግለሰቦች ማግኘትንና ማጣትን፣ ጸጋንና ድህነትን፣ ማጌጥንና መታረዝን በእኩል እንዲያውቁት፣ ነፍስያን ከጉራና ከትዕቢት ለማጽዳትና ከፈጣሪ፣ ከነብዩ መሐመድና ከሼኽ ሁሴን በረከትን ለማግኘት የሚጠቅም እንደሆነ ይታመናል፡፡ በአሁኑ ወቅት የሳሬ ስርዓት እንደቀድሞው በተጠናከረ ደረጃ ባይከወንም፣ አሁንም አልፎአልፎ እንደሚፈጸም መረጃ ሰጪዎ ይገልጻሉ፡፡[149]

በግለሰብ ደረጃ የሚሰጡ ስጦታዎች ካላቸው ባህርያት መካከል አንዱ ጋብቻ ነው፡፡ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን በሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ወቅት በሰዎች መካከል የእርስበርስ ትውውቅና ቀረቤታ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ትውውቅና ቀረቤታ ምክንያት በትዳር ለመተሳሰር የሚፈልጉ ግለሰቦች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በአጭር ጊዜ ቅውውቅ ትዳር መመስረት እንደሚችሉ ከተስማሙ፣ እዛው ጋብቻ ይፈጽማሉ፡፡ ሁለቱ ተጋቢዎች በዋሬ ስፍራ ለተሰበሰበው ሕዝብ እዛው እንደተዋወቁና በጋብቻ ለመኖር እንደተስማሙ ይገልጻሉ፡፡ ሕዝቡም ትዳራቸው እንዲሰምር ይመርቃቸዋል፤ የአዲስ ጎጆ መውጫና የኑሮ ማቋቋሚያ የሚሆን የገንዘብና የቁሳቁስ ስጦታ ይሰጣቸዋል፡፡

ለማህበረሰብ የሚሰጥ ስጦታ፣ በአንድ አካባቢ በሚኖር ማህበረሰብ ላይ በደረሰ ችግር ምክንያት ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ ነው፡፡ በርካታ መንፈሳዊ ተጓዦች ከተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ለሙዳ በዓላት ይመጣሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ሲመጡ በሚኖሩበት አካባቢ፣ ወረዳ፣ ዞን ወይም ክልል የተከሰቱ ችግሮችን ለተሰበሰበው ሕዝብ ይናገራሉ፡፡ በአብዛኛው በአንድ አካባቢ በሚኖር ማህበረሰብ ላይ የሚደርስ ችግር ድርቅ፣ ረሃብ፣ ወረርሽኝ፣ ጎርፍ፣ የእጸዋት በሽታ፣ የከብት በሽታ ወይም ግጭት ሊሆን ይችላል፡፡ ችግሩ ካለበት አካባቢ የመጡ የአገር ሽማግሌዎች ስለ ሁኔታው አስረድተው ሕዝቡ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ እንዲሰጥ ይጠይቃሉ፡፡ ሕዝቡም የአቅሙን ያህል የገንዘብና የአልባሳት እርዳታ ይሰጣል፡፡ ችግሩን የገለጹ የአገር ሽማግሌዎች ከሕዝቡ የሚሰጠውን እርዳታ ይሰበስባሉ፡፡ የሰበሰቡትንም እርዳታ ይዘው ወደ መጡበት አካባቢ በመሄድ ለተጎዱ ወገኖች ያከፋፍላሉ፡፡

[149] - ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ለመካነ ቅርሱ የሚሰጥ ስጦታ፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለሚገኙ ኪነሕንጻዎች ማደሻ ወይም በመካነ ቅርሱ ውስጥ ለመስራት ለታቀደ የልማት ስራ የሚውል የገንዘብ እርዳታ ነው። የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች ሊሰሩት ያሰቡት የልማት ስራ ወይም የሚታደስ ኪነሕንጻ ካለ፣ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይገልጻሉ። ከዚህ በፊት በሕዝብ መዋጮ የተሰራ ስራም ካለ ይገልጻሉ። አስተዳዳሪዎቹ ለገለጹት የልማት ስራ እንዲውል ሕዝቡ አቅሙ የፈቀደውን ያህል የገንዘብ ስጦታ ይሰጣል። ለኡሌ የሚሰጥ ስጦታ፣ ለእነሱ የኑሮ መደጎሚያ የሚሰጥ ነው። ኡሌዎች በሚያቀርቧቸው መንፈሳዊ ሙዚቃዎች ምክንያት የተለየ ማህበራዊ ደረጃና አክብሮት ይሰጣቸዋል። በመሆኑም ለኡሌዎች የሚሰጥ የገንዘብ ስጦታ ለብቻ ይሰበሰባል። በስፍራው የተገኙ መንፈሳዊ ተጓዦችም ለኡሌዎች አቅማቸው የፈቀደውን ያህል የገንዘብ ስጦታ ይሰጣሉ። የተሰበሰበውንም ገንዘብ በስፍራው የተገኙ ኡሌዎች ይከፋፈሉታል።

ለደርጋ የሚሰጥ ስጦታ ደግሞ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ውስጥ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች የሚከፋፈል ነው። ለደርጋዎች በሚል የሚሰጥ የገንዘብና የአልባሳት ስጦታን በአስተባባሪዎች አማካኝነት ይሰበሰባል። የተሰበሰበው ገንዘብና አልባሳት፣ እርዳታውን ለመውሰድ ፍላጎት ላለው ደርጋ እንዲሁም የሙዳ በዓላት ካለፉ በኋላ በአካባቢው ለወራት ለሚቆዩ ገሪባዎች ይከፋፈላል።

ለመካነ ቅርሱ ደርጋዎች ከሚሰጡ ስጦታዎች መካከል አንዱ ወሬጋ (Wareegaa) ነው። "ወሬጋ" የሚለው የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም ስጦታ መስጠት ማለት ነው። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ወሬጋ አጠቃላይ ስጦታዎችን የሚገልጽ ቢሆንም፣ ቃሉ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውለው የእርድ ከብት ስጦታን ለመግለጽ ነው። በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያካሂዱ ግለሰቦች ወሬጋ ይዘው ይመጣሉ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የአናጂናን ሕዝብ መደገፍ የሚፈልጉ ግለሰቦች ወሬጋ ይልካሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን የደም መስዋዕት ማድረግ የተለመደ ነው። ለወሬጋ የሚታረደው ከብት ደሙ መሬት እንዲፈስ ይደረጋል። ይህ ደም ለረቂቅ መናፍስት የሚሰጥ መስዋዕት ነው። በደም መስዋዕትም ግለሰቡ ካለው ኃጽያት ይጸዳል፣ በአካባቢው ካለ መንፈስ ጋር ይታረቃል፣ ሕይወቱ ይሰምራል፣ ዘሩም ይበረክታል ተብሎ ይታመናል። በኢድ በዓል ዕለት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚኖሩና በዓሉን ለማክበር በስፍራው የተገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የደም መስዋዕት ይፈጽማሉ።

በመካነ ቅርስ የተገኙ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የደም መስዋዕቱን የሚፈጽሙት እንደ ሌላው የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ሁሉ ኢብራሂም (አብርሃም) ልጁን ለመሰዋት በተዘጋጀበት ወቅት አላህ በልጁ ምትክ የበግ ጠቦት እንዲሰዋ ማድረጉን ለማሰብ ነው፡፡ በክርስትና ኃይማኖትም የደም መስዋዕት ማቅረብ ክርስቶስ ለሰው ልጅ መዳን ሲል ያፈሰሰውን ደም ለማሰብ ነው፡፡ በዋቄፈና ኃይማኖትም የደም መስዋዕትነት ከልምላሜ (Fertility) እና ከዘር እርባታ (Procreation) ጋር የተያያዘ እንደሆነ Knutsson (1967፡59) እና Bartels (1990፡208) ይገልጻሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም ሆነ በእነዚህ ኃይማኖቶች ደም የሕይወት መሰረታዊ ኃይል (A life-force) ትዕምርት ነው፡፡ የደም መስዋዕትነትም የሰው ልጅ ከረቂቅ መናፍስት ጋር ግንኙነት መፍጠሪያ፣ የዕርቅ፣ የሰላም፣ የሕይወት መቀጠልና የመቀደስ ተምሳሌት ነው፡፡ ለአናጂና ነዋሪዎች የአገር ውስጥና የውጭ አገር ዜጎች ወሬጋ ይሰጣሉ፡፡ በ2009 ዓ.ም የኢድ የሙዳ በዓል ወቅት 6 የቱሪክ ዜጎች 4 ከብት ይዘው በመምጣት ወሬጋ ሲሰጡ በመስክ ቆይታዬ ወቅት አይቻለሁ፡፡ በዚሁ አመት ከባሌ ዞን ራይቱ ወረዳ ነዋሪ ሕዝብ የተሰበሰበ 8 ኩንታል የገብስ እህልና 3 ከብት እንዲሁም ከጉራጌ ዞን ማረቆ ወረዳ 2 ኩንታል የስንዴ እህል ለነዋሪው ወሬጋ ሲሰጡ አይቻለሁ፡፡

በመካነ ቅርሱ ወሬጋ መስጠት የተለያዩ እሳቤዎችን ይገልጻል፡፡ እሳቤዎቹም ግለሰቦችን መርዳት፣ እራስን ማስደሰት፣ ከፈጣሪና ከሼኽ ሁሴን በረከትንና ቅድስናን ለማግኘት ናቸው፡፡ በመሆኑም የወሬጋ ስርዓት ሰጪውን ግለሰብ፣ ስጦታውን ከሚቀበሉ ግለሰቦች፣ ከማህበረሰቡ፣ ከሼኽ ሁሴንና ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ነው፡፡ የአጋርነት መግለጫና መቅረጫ ቃልኪዳን ነው፡፡ ለወሬጋ የሚመጣ ከብትም በከራው ላይ ታርዶ ስጋው ይከፋፈላል፡፡ ስጋውን መመገብ የሚፈልግ ግለሰብም በከራው ላይ በመገኘት ይመገባል፡፡ ይህን አይነት የወሬጋ ስርዓት በተመሳሳይም በምዕራብ ኢትዮጵያ በሚገኙ የሜጫ ኦሮሞዎች በሚከውኑት የቃሉ ስርዓተከበራ ወቅት መኖሩን Knutsson (1967፡97) ይገልጻል፡፡

የወሬጋ ስርዓት የመለዋወጥ ውክልና (Symbolic exchange) ነው፡፡ ግለሰቦች ስጦታ የሚሰጡት እንዲሳካላቸው የጠየቁት ነገር ሲፈጸምላቸው ነው (Pankhurst, 1994፡935)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግለሰቦች ስጦታ ሲሰጡ፣ በምትኩ ምርቃት፣ ፈውስ ወይም ሌላ ችሮታ ፈልገው ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች በመካነ ቅርሱ ለሚኖሩ ግለሰቦች የሚሰጥ ወሬጋ፣ ለሰጪው አካል የአጸፋ ስጦታ

ያስገኝለታል። የአጸፋ ስጦታውም ምርቃት ወይም አክብሮት ሊሆን ይችላል። ወሬጋውን የተቀበለ አካልም የሚፈልገው ነገር እንዲሳካለት፣ ጤና እንዲሰጠው ወይም በአካባቢው ያለ የዝናብ፣ የድርቅ፣ የበሽታ ችግር ካለ ከዚህ ችግር እንዲወጡ ይመርቃቸዋል። በመካነ ቅርሱ ማንኛውም ግለሰብ የሚመርቀው ምርቃት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል። ነገር ግን የተወሰኑ ግለሰቦች የሚመርቁት ምርቃት ይበልጥ ዋጋ እንዳለው ይታመናል። እነዚህም ግለሰቦች በእድሜ የገፉ አዛውንቶች፣ ገሪባዎች፣ መናኞችና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበቁ ግለሰቦች ናቸው።

## 8.2.5 ስለት የማስገባት ስርዓት

በሼኽ ሁሴን የሚያምኑ ግለሰቦች ካለባቸው ችግር ለመፈወስ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ይሳላሉ። ግለሰቦቹ ስለት የሚሳሉት በመካነ ቅርሱ በአካል በመገኘት ወይም በሚኖሩበት ስፍራ ሆነው ነው። ግለሰቦች ካለባቸው የጤና፣ የኢኮኖሚ ወይም ሌሎች ችግሮች ለመዳን እንዲሁም በሕይወታቸው ማግኘት የሚፈልጉትንና የሚመኙትን ነገር ለማግኘት ሲፈልጉ፣ ሼኽ ሁሴን ከእነዚህ ችግሮች ከፈወሷቸው አቅማቸው የፈቀደውን ነገር ይዘው እንደሚመጡ ወይም በሰው እንደሚልኩ ስለት ይገባሉ።

ግለሰቦቹ ከነበረባቸው ችግር ሲፈወሱ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ሲያገኙ ቃል በገቡት መሰረት ስለታቸውን ይዘው ወደ ስፍራው ይመጣሉ ወይም በሰው ይልካሉ። ግለሰቦች ስለት አስገባለሁ ብለው የሚሳሉት የተለያዩ ነገሮችን ነው። ከእነዚህ መካከል የእርድ ከብት፣ ገንዘብ፣ ልብስ፣ ቡና፣ እህል፣ ጫት፣ እጣን፣ ሰንደል የመሳሰሉት የተለመዱ ናቸው። ግለሰቦች በስለት ምክንያት አመጣለሁ ብለው ቃል የገቡትን ከብት፣ ገንዘብ ወይም ሌሎች ነገሮችን ወደ ስፍራው ይዘው በመምጣት ስለታቸውን ያስገባሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የስለት አገባብ ሁኔታ ሁለት አይነት ነው። አንደኛው፣ ስለት የሚያስገባው ግለሰብ በመካነ ቅርሱ በቋሚነት የሚያርፍበት ቤት ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ደግሞ በመካነ ቅርሱ ቋሚ ማረፊያ ቤት የሌለው ነው። ስለት የሚያስገባው ግለሰብ በቋሚ የሚያርፍበት ቤት ካለው፣ ስለቱን ከማስገባቱ በፊት፣ ስለተሳለበት ነገር ለቤቱ ባለቤት (አባወራ) ይናገራል። ስለቱንም ይዞ መምጣቱን ይገልጻል። ግለሰቡ ይዞት የመጣውን ስለት ሲያስገባም የቤቱ ባለቤት አብሮት በዋሬው ስፍራ ላይ ይገኛል።

ስለት የገባው ግለሰብና የቤቱ ባለቤት አብረው ዋሬ ላይ ከተገኙ በኂላ፣ ምን ተቸግሮ ወይም ምን ፈልጎ ስለት እንደገባ፣ ስለት የገባው ግለሰብ እራሱ ወይም በቤቱ ባለቤት አማካኝነት በዋሬው ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይነገራል፡፡ ግለሰቡም "ስለቱ ደርሶልኝ ይህን ይዤ መጥቻለሁ፡፡" ይላል፡፡ ስለ ስለቱ የሚናገርለት የቤቱ ባለቤት ከሆነም "ስለቱ ደርሶለት ይህን ይዞ መጥቷል" ብሎ ይናገራል፡፡ በዋሬ ላይ የተሰበሰበው ሕዝብም "አብዮ እንኳን ስለትህን ሰሙህ፣ እንኳን ደስ አለህ፣ ወደፊትም ስለትህን ይስሙልህ፡፡" በማለት በአንድ ላይ ይመርቁታል፡፡ ግለሰቡም ምርቃቱን "አሜን" በማለት ይቀበላል፡፡

ግለሰቡ ይዞት የመጣውን ስለት ለቤቱ ባለቤት ያስረክባል፡፡ ቋሚ ማረፊያ ያለውና በዋሬው ስፍራ ከቤቱ ባለቤት ጋር በመሆን ስለቱን የተናገረ ሰው አመጣለሁ ብሎ ቃል የገባውን ነገር ይዞ ሲመጣ ለቤቱ ባለቤት ያስረክባል፡፡ በግለሰቡ የመጣውን ስለትም የቤቱ ባለቤት ለግሉ በመውሰድ ይጠቀምበታል፡፡ ግለሰቡ ለስለት ይዞ የመጣው የእርድ ከብት ከሆነ የቤቱ ባለቤት ከብቱን ወደ መኖሪያው ይወስደዋል፡፡ የቤቱ ባለቤት ከብቱ መቼ መታረድ እንዳለበት ይወስናል፡፡ ባለቤቱ በወሰነው ጊዜ ከብቱ ታርዶ የአካባቢው ሰው በጋራ ይመገባል፡፡ የቤቱ ባለቤት ለስለት የመጣውን የእርድ ከብት መሸጥም ሆነ ማርባት አይችልም፡፡ በመካነ ቅርሱ ቋሚ ማረፊያ ቤት የሌለው ግለሰብ ደግሞ የገባውን ስለት ሕዝቡ ፊት እራሱ ይናገራል፡፡ ሕዝቡም ስለቱ ስለተሰማለት ይመርቀዋል፡፡ ይዞት የመጣውን ስለት የፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ተቀብለውት በዋሬው ስፍራ ለሚገኙ ችግረኞች እዛው ያከፋፍሉታል፡፡ ግለሰቡ ለስለት ይዞት የመጣው የእርድ ከብት ከሆነም ታርዶ ስጋው ለሕዝቡ ይከፋፈላል፡፡

## 8.2.6 የጪንጫ ስርዓት

ጪንጫ ሽታ ማለት ነው፡፡ የጪንጫ ስርዓትም ለእርድ ከቀረበው ከብት ሽታውን መስዋዕት የማድረግ ክወና ነው፡፡ ግለሰቦች የከብት እርድ ይሳላሉ፡፡ ስለታቸው ሲደርስላቸው በስፍራው የከብት እርድ ያካሂዳሉ፡፡ ከስለት በተጨማሪም ግለሰቦች በፍላጎታቸው የእርድ ከብት ይዘው በመምጣት በስፍራው ያለውን ሕዝብ ያበላሉ፡፡ ለስለትም ይሁን ለስጦታ በሚታረድ ከብት ላይ የጪንጫ ስርዓት ይፈጸማል፡፡ ጪንጫ በስፍራው ከታረደው ግመል፣ በግ፣ ፍየል፣ በሬ ወይም ላም የተወሰኑት አካላትን በእሳት የማቃጠል ስርዓት ነው፡፡ ከእርድ ከብቱ አካላት መካከል ጭንቅላቱንና አራቱ ኮቴዎቹን በግራር እንጨት በተቀጣጠለ እሳት ያቃጥሉታል፡፡



*ፎቶ፣ 32፣ የጪንጫ ስርዓት በዶቆ ከራ ሲከወን የሚያሳይ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

በስፍራው የተገኘ ሰው የከብቱን ስጋ ይበላል። በስፍራው ከሰው ልጅ በተጨማሪ ረቂቅ መናፍስት አሉ ተብሎ ይታመናል። ረቂቅ መናፍስት የሚፈልጉት ስጋውን ሳይሆን ሽታውን ነው። በመሆኑም ጪንጫ የሚደረገው በስፍራው ለሚገኙ ረቂቅ መናፍስት ምግብ እንዲሆናቸው ነው። ጪንጫ የከራና የቤት በሚል በሁለት ይመደባል። ግለሰቡ ለስለት ይዞ የመጣውን የእርድ ከብት በከራ ላይ እንዲታረድ ከፈለገ፣ ቀደም ሲል ከራ ላይ አበላለሁ ብሎ ቃል ከገባ፣ ቋሚ የማረፊያ ቤት ከሌለው ወይም ለስጦታ በሚል ይዞ ከመጣ በከራ ስፍራ ላይ እንዲታረድ ይደረጋል። ከብቱም ከታረደ በኋላ የሚከወን የጪንጫ ስርዓት የከራ ጪንጫ ይባላል።

ቋሚ ማረፊያ ያለው ግለሰብ የእርድ ከብት ይዞ ሲመጣ ለቤቱ ባለቤት ያስረክባል። የቤቱ ባለቤት በሚወስነው ቀን ከብቱን በቤቱ አርዶ የአካባቢውን ሰው ያበላል። በመኖሪያ ቤት አካባቢ ከታረደው ከብት አካላት መካከል ጭንቅላቱና አራቱ ኮቴዎች በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ በእሳት ይቃጠላሉ። በመኖሪያ አካባቢ የሚከወን የጪንጫ ስርዓት የቤት ጪንጫ በሚል ስያሜ ይጠራል።

## 8.2.7 የምርቃ ስርዓት

ለመካነ ቅርሱና ለአካባቢው አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት እንዲሁም የተለያዩ ግላዊ ጉዳዮችቻቸውን ለተናገሩ ግለሰቦች ምርቃት ይሰጣቸዋል፡፡ በዋሬ ስርዓት ወቅት የሚቀርቡ ምርቃቶች ከሚመረቁ አካላት አንጻር የግለሰቦች፣ የመንግስት፣ የተቋማት፣ የማህበረሰብ፣ የሀገር፣ የእንስሳትና የእጸዋት በሚሉ ሰባት ምደባዎች መክፈል ይቻላል፡፡ እነዚህን ምደባዎች መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ምርቃቶችን ይዘት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በዋሬ ስርዓት ላይ የተለያዩ ግለሰቦች ይመረቃሉ፡፡ ግለሰቦቹ ለመካነ ቅርሱ ወይም ለአካባቢው አስተዋጽኦ ያደረጉ ወይም ግላዊ ጉዳዮቻቸውን የተናገሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለመካነ ቅርሱ እድሳት ወይም ለመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የቁሳቁስ ስጦታዎችን የሰጡ ወይም የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ የቢሮ ኃላፊዎችና ባለሀብቶች በግለሰብ ደረጃ ላደረጉት አስተዋጽኦ ይመረቃሉ፡፡ የበዓሉ አስተባባሪዎች የግለሰቦቹን ስም በመጥራት፣ በስፍራው ተገኝተው ከሆነም ሕዝቡ ፊት እንዲቆሙ በማድረግ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ለሕዝቡ ይገልጻሉ፡፡ ሕዝቡም ባደረጉት አስተዋጽኦ መደሰቱን ይገልጻል፡፡ ይመረቃሉ፡፡ የፕሮግራሙ አስተባባሪ ሲመርቅ፣ ሕዝቡም አስተባባሪው ያለውን ምርቃት በጋራ ይደግማል፡፡ በነሐሴ 26 ቀን፣ 2009 ዓ.ም በሙዳ በዓል ወቅት ሲከወን ከሰማኂቸው ምርቃት መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

| **የፕሮግራሙ አስተባባሪ** | **ሕዝቡ** |
|---|---|
| Waan naat gootaniif Abbiyoon isinii haa kennu | haa kenuu |
| (ላደረጋችሁት ነገር አብዮ ይስጣችሁ፡፡) | (ይስጣችሁ) |
| Kan qabdani irratti dabalee isinii haa kennu | haa kennuu |
| (ባላችሁ (ስልጣን ወይም ሀብት) ላይ ሼኽ ሁሴን ጨምሮ ይስጣችሁ፡፡) | (ይስጣችሁ) |
| Hamaa, waamyoo, dharticha irraa isinii haa eegu | haa eegu |
| (ከተንኮለኛ፣ ከምቀኛ፣ ከሸረኛ ይጠብቃችሁ፡፡) | (ይጠብቃችሁ) |
| Iji hamaarraa isinii haa eegu | haa eegu |
| (ከክፉ አይን ይጠብቃችሁ፡፡) | (ይጠብቃችሁ) |
| Fayyaa isinii haa kennu | haa kennu |
| (ጤናችሁን ይስጣችሁ፡፡) | (ይስጣችሁ) |

| | |
|---|---|
| Dhalli keessan haa barakatu | haa barakatu |
| (ዘራችሁ የተባረከ ይሁን።) | (ይባረክ) |

በማለት ይመርቃቸዋል። ተመራቂዎቹም ከወገባቸው ጎንበስ በማለትና የሁለቱንም እጃቸውን መዳፍ በመዘርጋት "አሜን" እያሉ ምርቃቱን ይቀበላሉ። ምርቃቱ ሲጠናቀቅም የዘረጉትን የእጃቸውን መዳፍ በመሳም ፊታቸውን ያባብሳሉ። ለመረጃ ስብሰባ በስፍራው በነበርኩበት የ2007 ዓ.ም የሙዳ በዓል ወቅት የአንድ ኢንዱስትሪ ባለቤት ለመካነ ቅርሱ በፀሐይ ብርሃን የሚሰራ መብራት (ሶላር) በስጦታ በመስጠታቸው ሕዝቡ ፊት ቀርበው ምርቃት ሲቀበሉ አይቻለሁ።

የተለያዩ ግለሰቦች በሕይወታቸው የገጠሟቸውን ችግሮች ለሕዝቡ በመናገር ከችግራቸው እንዲወጡና ሕዝቡ እንዲመርቃቸው ይጠይቃሉ። ግለሰቦቹ ደረሰብን የሚሉትን ችግር ምንም ሳይደብቁ በግልጽ የመናገር ግዴታ አለባቸው። በዋሬ ስርዓት ወቅት ግለሰቦች ከሚያነሷቸው ችግሮች መካከል የጤና፣ የገንዘብ፣ የልጅና የስራ እጦት በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ናቸው። ግለሰቦቹ ባቀረቧቸው ችግሮች መሰረት ይመረቃሉ። የፕሮግራሙ አስተባባሪ ሲመርቅ፣ ሕዝቡም አስተባባሪው ያለውን ምርቃት በጋራ ይደግማል። በነሐሴ 26 ቀን፣ 2009 ዓ.ም በመካነ ቅርሱ የሙዳ በዓል ሲከወን ከቀረቡ ምርቃት መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው።

| **የፕሮግራሙ አስተባባሪ** | **ሕዝቡ** |
|---|---|
| Sheek Huseen rakkoo kana keessaa isin haa baasu | haa baasu |
| (ሼኽ ሁሴን ከዚህ ችግር ያውጣችሁ።) | (ያውጣችሁ) |
| Rakkinni akkanaa isinitti hin deebi'in | hin deebi'in |
| (ተመሳሳይ ችግር ድጋሚ አይምጣባችሁ።) | (አያምጣባችሁ) |
| Kan yaaddan isiniif haa guutu | haa guutu |
| (ያሰባችሁት ይሳካላችሁ።) | (ያሳካላችሁ) |
| Rakkoo kana keessaa bahaatii nama galata dhiyeessu ta'aa | haa ta'aa |
| (ከዚህ ችግር ወጥታችሁ ለምስጋና የበቃችሁ ሁኑ።) | (ሁኑ) |

በማለት ይመርቋቸዋል። ግለሰቦች ደረሰብን ብለው የተናገሯቸው ችግሮች ከፍተኛና አሰቃቂ የሚሆኑበት አጋጣሚ አለ። እንደዚህ አይነት ችግሮች ሲነገሩ ሶስት ክወናዎች ይደረጋሉ። አንደኛው፣ ምራቅ መትፋት ነው። የፕሮግራም አስተባባሪው "ይኽ ችግር ከግለሰቡና ከእኛም እንዲርቅ ትፉ" በማለት ያዛል። ሕዝቡም ሶስት ጊዜ ምራቁን ወደ መሬት "አክ- እን- ትፍ" በማለት መሬት ላይ ይተፋል። ሁለተኛው፣ እጅን በአየር ላይ ማወራጨት ነው። የፕሮግራም አስተባባሪው "ይህ ችግር ከእኛ እንዲርቅ አባሩ።" በማለት ያዛል። ሕዝቡም ሶስት ጊዜ ሁለት እጁን በአየር ላይ ወደ ግራ ወደ ቀኝ በማወናጨፍ የማባረር ምልክት ያሳያል።

ሶስተኛው፣ በእጅ የራስን አካል ማጽዳት ነው። ነው። የፕሮግራም አስተባባሪው "ይህ ችግር ከእኛ እንዲርቅ አጽዱ።" በማለት ያዛል። ሕዝቡም ሶስት ጊዜ በሁለት እጁ የራሱን ሰውነት የመታጠብና ቆሻሻን ከሰውነት ላይ የማራገፍ ምልክት ያሳያል። በምራቅ መሬት መትፋት፣ እጅን ማወራጨትና በእጅ ሰውነትን ማጽዳት፣ የሰማነው ችግር ከግለሰቡ እንዲሁም ከእኛ አካባቢ እንዲወገድ፣ ድጋሚም እንዳይከሰት የሚል ትርጉም አለው። ሶስት ጊዜ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ችግሩ እንዳያዳግም ለማረጋገጥ ነው። ተመራቂ ግለሰቦችም ከደረሰባቸው ችግር እንዲፈወሱ የተሰጣቸውን ምርቃት "አሜን" በማለት ይቀበላሉ።

በዋሬ ስርዓት ወቅት ሰርቷቸዋል የሚሉትን የልማት ስራዎች በመግለጽ አገሪቷን በመምራት ላይ ያለውን መንግስት ይመርቃሉ። የፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ገዢው መንግስት በአጠቃላይ በአገር ደረጃ እንዲሁም በመካነ ቅርሱ አካባቢ ሰርቷል የሚሉትን ስራዎች ለሕዝቡ ይገልጻሉ። በአብዛኛው መንግስት ሰርቷቸዋል ብለው የሚያቀርቧቸው ጉዳዮች የመንገድ ግንባታን ማስፋፋት፣ የጤና ተቋማትን መገንባት፣ የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት ማስከበር፣ የሰለፊያ እንቅስቃሴን መቆጣጠር በተደጋጋሚ የሚነሱ ናቸው።

መንግስት እነዚህ ስራዎች በመስራቱ ይመረቃል። አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይመረቃል። በአካባቢው የሚኖር ሕዝብ ይመረቃል። መድኃኒት የሌላቸው በሽታዎች እንዲጠፉ ይመረቃል። በኦሮሚያና በሱማሊያ ክልል ሕዝቦች መካከል የተፈጠረው የድንበር ግጭት እንዲቆምና ሰላም እንዲሆን ይመረቃል። በስፍራው የተሰበሰበ ሕዝብ ይመረቃል። የፕሮግራሙ አስተባባሪ ሲመርቅ፣ ሕዝቡም "አሜን" በማለት ይቀበላል። ከምርቃቱ መካከል በመስከረም 11፣ 2008 ዓ.ም የሙዳ በዓል በመካነ ቅርሱ ከቀረቡ ምርቃቶች መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው።

Nageenyi bal’aan osoo ati hin galle si dura haa galu

Namni Anaajina dhufte marti galanni siif haa taatu

Biyyi ati dhufte, kaan illee nagaa haa taatu

Nageenya biyya keenya Itiyoophiyaa muluu nagaa haa taatu

Daardinbariin Itiyoophiyaa nagaa haa taatu

Orommoo fi Somaaleen naga haa taatu

Algaan mangistii naga haa taatu

Beelli haa badu

Dhukkubni baraa haa badu

Dhukkubni baraa haa badu

Dhukkubni marfeen sa’aafi namaa hin fayyisne haa badu

Gandi keessan ganda nagaa haa taatu

Roobni jannataa ammuma haa roobu

Anajinatti robe isin dura haa galu

Ifni rabbi as Anaajina jiru osoo ati hin galle si dura haa galu

Mootummaa fi uummaanni afaan tokko haa dubbatu

Mootummaa fi uummaanni haa galtuu.

ትርጉሙ፡-

እቤትህ ከመድረስህ በፊት ሰላም ቤትህ ይግባ

አክብራችሁ አናጂና የመጣችሁ ሁሉ የተከበራችሁ ሁኑ

የመጣችሁበትም ሆነ ሌላውም ቦታ ሰላም ይሁን

ኢትዮጵያ ሙሉ ሰላም ይሁን

የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ሰላም ይሁን

ኦሮሞና ሱማሌ ሰላም ይሁን

የመንግስታችን አልጋ (ስልጣን) ሰላም ይሁን

ረሃብ ይጥፋ

በሽታ ይጥፋ

የዘመኑ በሽታ ይጥፋ

መድኃኒት የሌለው የሰውም ሆነ የከብት በሽታ ይጥፋ

የመጣችሁበት ቀዬ ሰላም ይሁን

የገነት ዝናብ ይዝነብልን

አናጂና ዝናብ ዘንቦ፣ እናንተ ከመድረሳችሁ በፊት ቀዬአችሁ ላይ ይዝነብ

አናጂና ያለው የፈጣሪ ብርሃን ካንተ ቀድሞ እቤትህ ይግባ

የመንግስትና የሕዝብ ቃል አንድ ይሁን

መንግስትና ሕዝብ ይስማሙ።

በማለት ይመርቃሉ። በባሌ ዞን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የፌዴራል ወይም የክልል ተቋማት የገንዘብ ስጦታ ይሰጣሉ። የገንዘብ ስጦታውም ለመካነ ቅርሱ እደሳ፣ የሕዝብ መገልገያ ለሚሆኑ ግንባታዎች የሚውሉ ወይም ለአካባቢው ነዋሪዎች የሚከፋፈል ነው። ተቋማቱ ከገንዘብ በተጨማሪ የሕዝብ መገልገያ ቁሳቁሶችን ይሰጣሉ። የበዓሉ አስተባባሪዎች የተቋማቱን ስም ወይም ተቋማቱን የሚመሩ ግለሰቦችን ስም በመጥራት፣ በስፍራው ተገኝተው ከሆነም ሕዝቡ ፊት እንዲቆሙ በማድረግ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ለሕዝቡ ይገልጻሉ። ላደረጉት አስተዋጽኦም ይመረቃሉ። የፕሮግራሙ አስተባባሪ ሲመርቅ፣ ሕዝቡም አስተባባሪው ያለውን ምርቃት በጋራ ይደግማል። በመስከረም 11፣ 2008 ዓ.ም የሙዳ በዓል ላይ ከተከወኑ ምርቃት መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው።

| **የፕሮግራሙ አስተባባሪ** | **ሕዝቡ** |
|---|---|
| Hojji keessan haa baayatu | haa baayatu |
| (ስራችሁ የተባረከ ይሁን።) | (ይባረክ) |
| Biiron keesan ummataa haa galateeffamu | haa galateeffamu |
| (መስሪያ ቤታችሁ በሕዝብ የተመሰገነ ይሁን።) | (ይመስገን) |
| Aangon keessan haa guddatu | haa guddatu |
| (የእናንተም ስልጣን ይደግ።) | (ይደግ) |
| Sheek Huseen umriifi fayyaa isiniif haa kennu | haa kenuu |
| (ሼኽ ሁሴን እድሜና ጤና ይስጣችሁ።) | (ይስጣችሁ) |

በማለት ይመርቃሉ። መረጃ ለመሰብሰብ በስፍራው በነበርኩበት ወቅት የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለመካነ ቅርሱ የገንዘብና የቁሳቁስ ስጦታዎችን ሲያበረክቱ አይቻለሁ። በዋሬ ስርዓት ላይ የተለያዩ ማህበረሰቦች ይመረቃሉ። ማህበረሰብ የሚመረቀው ከማህበረሰቡ ጋር የተያያዙ ወቅታዊ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ነው። እነዚህ ወቅታዊ ሁኔታዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የተከሰቱ እንደ ድርቅ፣ ረሃብ፣ ግጭት፣ ወረርሽኝ የመሳሰሉት ችግሮች ናቸው። እነዚህ ችግሮች በአንድ አካባቢ ሲከሰቱ ከአካባቢው ወደ ስፍራው በሚመጡ የአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ለሕዝቡ ይነገራል፤ ሕዝቡም ማህበረሰቡ ከዚህ ችግር እንዲፈወስ ይመርቃል።

በማህበረሰቡ ውስጥ ከተከሰቱ ችግሮች በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ እርስበርስ ግጭት ገብተው፣ በቅርቡ በመካነ ቅርሱ የእርቅ ስርዓት የፈጸሙ ማህበረሰቦች ካሉ እርቅ በመፈጸማቸው፣ ሽማግሌ በማክበራቸው፣ ሰላም በመፈለጋቸውና እርቁን በመቀበላቸው ይመረቃሉ። በወቅቱ ግጭት ላይ ያሉ ማህበረሰቦች ካሉም ወደ እርቅ እንዲመጡ፣ በመሃላቸው ሰላም እንዲወርድና ሰላማዊ ሕይወት እንዲኖሩ ይመረቃሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እንዲኖር፣ ልማት እንዲኖር፣ ረሃብ፣ ድህነት፣ አለመረጋጋት እንዲጠፉ፣ የአገሪቷ ድንበር ሰላም እንዲሆን ይመረቃል። በአገሪቷ ውስጥ የሚገኙ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰላም እንዲሆኑ ይመረቃሉ። በአገሪቷ ውስጥ በወቅቱ የተፈጠረ ችግር ካለም፣ አገሪቷ ከችግሩ እንድትወጣ ይመረቃል።

እንደሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለመንፈሳዊ ጉዞ የሚመጣው አብዛኛው ሕዝብ ሕይወቱ የተመሰረተው በእርሻና በከብት እርባታ ነው። በመሆኑም የእንስሳትና የሰብል ደህንነት ለሕዝቡ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በመካነ ቅርሱም እንሰሳት ጤነኛ እንዲሆኑ፣ ምርታማ እንዲሆኑና እንዲረቡ ይመረቃሉ። ሰብሉም ምርታማ እንዲሆን፣ በዝናብ እጥረት እንዳይደርቅ፣ በቁር እንዳይመታና በሰብል በሽታ እንዳይጠቃ ይመረቃል። ሕዝቡም በሚያመርተው ሰብልና በሚያረባው እንስሳ የተሻለ ውጤት እንዲያገኝና ሕይወቱ እንዲሻሻል ይመረቃል። በመካነ ቅርሱ የተለያዩ አካላት ምርቃት ከተቀበሉ በኋላ በስፍራው የተገኘው ሕዝብ ጤና እንዲያገኝ፣ በሕይወቱ ደስተኛ እንዲሆን፣ የለመኑት ነገር ፈጥኖ እንዲደርስ፣ ከክፉ ችግር፣ ከምቀኛና ከሸረኛ እንዲጠበቁ ይመረቃሉ።

ሕዝቡም ምርቃቱን በጋራ "አሜን" በማለት ይቀበላል። ምርቃቱ የሚጠናቀቀው እርስበርስ ሰላምታ በመሰጣጣትና እርስበርስ በመዘያየር ነው። ሰላምታ አሰጣጡና አዘያየሩ አጠገብ ከተቀመጠ ሰው ጋር እጅ ለእጅ ወይም ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም ነው። ይህ የመሳሳም ሂደት

የምረቃ ስርዓቱ መጠናቀቁን ከመግለጽ በተጨማሪ ወደ ሌላ ክወና መሸጋገርን የሚያሳይ የክወና ቅየሳ (Performance turn) ድርጊት ነው፡፡

### 8.2.8 የእርግማን ስርዓት

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚከወኑ ስርዓቶች መካከል አንዱ እርግማን ነው፡፡ ሕዝቡ ወደ ስፍራው የሚመጣው ለጸሎትና ለምርቃት ነው፡፡ በስፍራው እርግማን ማካሄድ እጅግ አደገኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም በስፍራው የተገኘ ግለሰብ በተናጠልም ሆነ፣ ሕዝብ በጋራ የተራገመው ነገር በፍጥነት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በስፍራው እርግማን ማካሄድ የተለመደ አይደለም፡፡ በስፍራው እርግማን የተለመደ ባይሆንም አልፎአልፎ ይከወናል፡፡ በስፍራው የሚከወን እርግማን ከሚረገመው አካል አንጻር የግለሰብና የቡድን በሚሉ ሁለት ምደባዎች መክፈል ይቻላል፡፡ ግለሰቦች የሚረገሙበት ምክንያት በዋናነት በመካነ ቅርሱ መፈጸም የሌለባቸውና ክልክል የሆኑ ድርጊቶችን ፈጽመው ሲገኙ፣ በእምነቱ ልዩ ስፍራ በሚሰጣቸው ትዕምርቶች ላይ ጥፋት ሲያደርሱ ወይም ወደ ስፍራው በሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦች ላይ ጥቃት ሲያደርሱ ነው፡፡

በመካነ ቅርሱ በሚከወኑ ስርዓቶች ላይ ግለሰቦች ለመረገም የሚበቁባቸው ድርጊቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በአብዛኛው በስፍራው የስርቆት ወንጀል ሲፈጽሙ፣ የደንቁ በትር ሲሰብሩ፣ ገረባዎችን ሲመቱ፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው በሚመጡበት ወቅት ተጓዦች ላይ እንግልት ሲያደርሱ፣ ሼኽ ሁሴንና ሌሎች ቅዱሳንን ሲሳደቡ፣ ከታሪፍ በላይ ሂሳብ ሲያስከፍሉ፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው እንዳይሄዱ ቅስቀሳ ሲያደርጉ፣ በቤተሰባቸው፣ በጎረቤታቸው፣ በጓደኛቸው ወይም በስራ ባልደረባቸው ላይ በተደጋጋሚና ሆነ ብለው ጉዳት ሲያደርሱ እንዲሁም በበዓል ወቅት የመኪና ባለቤቶች ሕዝቡን ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን ይዞ አይሄድም በማለት ሲከለክሉ ነው፡፡ ግለሰቦች ከላይ የተገለጹትን ድርጊቶች ፈጽመው ሲገኙ፣ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ጸሎት ይደረግላቸዋል፡፡ ግለሰቦች ጥፋት እንዳያጠፉ በስፍራው ለተገኘ ሕዝብ ሲገለጽ፣ ሕዝቡም ባለማወቅና ባለማስተዋል የፈጸሙት ሊሆን እንደሚችል ከግምት በማስገባት ካሁን በኋላ ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጽሙ ጸሎት ያደርግላቸዋል እንጂ ወደ እርግማን አያመራም፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን "ፈጣሪ በአምሳያው የሰራውን የሰው ልጅ ቀርቶ ትንኝን መራገም አግባብ አይደለም፡፡" የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡ ይህ አስተሳሰብ የሚመነጨውም ሼኽ ሁሴን "በሰዎች ላይ

ዱአ አለማድረግና ሰዎች ሆነ ብለው ቢበድሉ እንኳን ከቂም በቀል መቆጠብ እንደሚገባ አስተምረዋል፡፡" ተብሎ መታመኑ ነው፡፡[150] በመሆኑም ሰዎች ባጠፉት ጥፋት ምክንያት በሰዎች ላይ ዱአ ማድረግና መራገም የሼኽ ሁሴን ተከታዮችና ወዳጆች በጣም የሚፈሯቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን እርግማን ማካሄድ በጣም ከባድ ነገር ነው፡፡ እርግማን 7ኛ ሰማይ ላይ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ሳይበድል ወይም ትንሽ ጥፋት አድርሷል ተብሎ አይረገምም፡፡

አንድ ሰው ምንም ነገር ሳይበድል መርገም በጣም ከባድ ነገር ነው፡፡ ሰውን ያለጥፋቱ መርገም፣ የተራገሙት ነገር ተመልሶ በራስ ላይ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት ሰዎች ከመራገማቸው በፊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ ግለሰቦቹ ከዚህ በፊት ከፈጸሙት ድርጊት አልቆጠብ ካሉ፣ በተደጋጋሚ የተለያዩ ችግሮችን ከፈጸሙና ድርጊታቸው ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ ከሆነ ሕዝቡ እንዲረግማቸው ይደረጋል፡፡ ግለሰቦች የሚረገሙት በቃል ነው፡፡ የፕሮግራም መሪው "ፈጣሪ ይይለት፣ ሼኽ ሁሴን እድሜውን ይቅጩት፣ ያሰበው አይሳካለት፣ ልመናው አይሰማ ወዘተ." በማለት ሲራገም፣ በስፍራው የተሰበሰበውም ሕዝብ የፕሮግራም መሪው የረገመውን እርግማን ተቀብሎ በአንድ ድምጽ ይደግማል፡፡

ከግለሰቦች በተጨማሪ ለተመሳሳይ ዓላማ የተደራጁ ቡድኖችም ይረገማሉ፡፡ ቡድኖች የሚረገሙት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ ጉዳት ለማድረስ ሲያቅዱ ወይም ሲንቀሳቀሱ፣ በሼኽ ሁሴን ተከታዮችና ወዳጆች ላይ አካላዊና አዕምሯዊ ጥቃት ሲፈጽሙ፣ በሼኽ ሁሴን ከራማ ላይ ሲያሾፉ፣ ሼኽ ሁሴንን ሲያንቋሽሹ፣ የሼኽ ሁሴን ከራማ የመረጣቸውና የተለየ መንፈሳዊ ኃይል የተሰጣቸውን ወልዮችንና ባለከራማዎችን ሲያዋርዱ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ገሞዎችና የአምልኮ ስፍራዎች ላይ ጥቃት ሲፈጽሙ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚረገሙ ቡድኖች የተለያየ ዓላማ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ቡድኖቹም የተመሰረቱበት ዓላማ ኃይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ ሊሆን ይችላል፡፡

በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ በተደጋጋሚ የሚረገመው የሰለፊያ አስተምህሮን የሚከተለው የእስልምና ኃይማኖት ቡድን ነው፡፡ የሰለፊያ አስተምህሮን የሚከተሉ ኃይማኖታዊ ቡድኖች የሼኽ ሁሴንን አስተምህሮ አይቀበሉም፣ የሼኽ ሁሴን ከራማን አይቀበሉም፣ ወደ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለአምልኮ መሄድ አይገባም፣ ሼኽ ሁሴንን ማመን የፈጣሪን አንድ አምላክነት ላይ

[150] - ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 26 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

ሽርክ (ተጋሪ) መፍጠር በመሆኑ በእሳቸው ማመን ስህተት ነው፣ የሼኽ ሁሴንን የቀብር ስፍራ መዘየር (መጎብኘት) አይገባም ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡

እነዚህን ድርጊቶች መፈጸም ከቁርዓንና ከሐዲስ ትዕዛዛት ውጪ በመሆኑ እስላማዊ አይደሉም ብለው ስለሚያምኑ፣ በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከወኑ መንፈሳዊ ድርጊቶችን አይቀበሏቸውም፡፡ በእነዚህና መሰል የኃይማኖት አስተምህሮ ልዩነት ምክንያት በሼኽ ሁሴን ተከታዮችና በሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች መካከል ቅራኔ አለ፡፡ በመሃላቸው ያለው ቅራኔ ተባብሶ ወደ ግጭት ያመራበት ወቅትም አለ፡፡ ይህ በመሆኑ የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ ለመካነ ቅርሱ፣ በስፍራው ለሚከበሩ ኃይማኖታዊ በዓላትና ለመንፈሳዊ ተጓዦች አስጊ እንደሆኑ ይታመናሉ፡፡ በአብዛኛው በመካነ ቅርሱ በሚከወን የዋሬ ስርዓተከበራ ላይ የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች በተለያዩ አካባቢዎች ጉዳት አድርሰዋል ተብሎ ክስ ይቀርብባቸዋል፡፡ እነዚህ ቡድኖች አጥፍተዋል የሚሉትን ጥፋቶች ለተሰበሰበው ሕዝብ በክስ መልክ ይነገራል፡፡ በስፍራው ከሚነገሩ ክሶች መካከል ገሪባ መትተዋል፣ ደንቄ ሰብረዋል፣ መስኪድ አፍርሰዋል፣ ገሞ አፍርሰዋል፣ ሼኽ ሁሴንን አዋርደዋል፣ ሰው ገድለዋል ወዘተ. የሚሉ ናቸው፡፡

ከተለያዩ አካባቢ የመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች እነዚህን ድርጊቶች በዚህ ክልል፣ በዚህ ወረዳ፣ በዚህ ቀበሌ ፈጽመዋል ብለው ክስ ያቀርባሉ፡፡ በእነዚህ ቡድኖች ላይ የሚቀርቡ ክሶች እውነት ናቸው? ወይስ ውሸት?፣ ተፈጽመዋል? ወይስ አልተፈጸሙም?፣ በሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች ወይስ በሌላ አካል የተፈጸሙ ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችም ሆነ ማጣሪያዎች አይደረግም፡፡ በእነዚህ ቡድኖች ተፈጽመዋል የተባሉ ድርጊቶች በሙሉ በሕዝቡ ዘንድ እውነተኛ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ቡድኖች ሕዝቡ በጋራ ይረግማል፡፡ ቡድኖችን ለመርገም የተለያዩ ድርጊታዊ ክወናዎች ይፈጸማሉ፡፡

የእርግማን መፈጸሚያ ክወናዎች አራት አይነት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ክወናዎች መካከል አንድ ክወና በአንድ እርግማን ወቅት ብቻ ሲከወን፣ አልፎአልፎ ግን በአንድ እርግማን ወቅት ሁለት የተለያዩ ክዋኔዎች ሊከወኑ ይችላሉ፡፡ የእርግማን ክወናዎቹ በጣም ከባድ ስለሆኑ ለግለሰብ እርግማን አይከወኑም፡፡ ግለሰቦች በቃል ብቻ ሲረገሙ፣ ቡድኖች ግን በድርጊታዊ ክወናዎች ይረገማሉ፡፡

በጣም ከባድ የሆኑትና ለቡድኖች ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ አራት የእርግማን ክወናዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ አንደኛ፤ ድንጋይ ከመሬት አንስቶ እርስበርስ ማጋጨት ነው፡፡ በስፍራው የተገኘ ሕዝብ ከመሬት በቀኝና በግራ እጆቹ ሁለት አነስተኛ መጠን ያላቸው ድንጋዮች (ጠጠሮች) እንዲያነሱ ይደረጋል፡፡ በእጆቻቸው ያነሷቸውን ድንጋዮች እርስበርስ ለማጋጨት ይዘጋጃሉ፡፡ የፕሮግራም መሪው “ያዛችሁ?” ሲል ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡ ድጋሚም የፕሮግራም መሪው “ያዛችሁ?” ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡ የፕሮግራም መሪውም “ምታ !!” የሚል ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ሕዝቡ የያዘውን ድንጋይ እርስበርስ ያጋጫል፡፡ የፕሮግራም መሪውም “ድገም” የሚል ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ ሕዝቡ ድንጋዮቹን ድጋሚ ያጋጫል፡፡ ሕዝቡም በፕሮግራሙ መሪ ትዕዛዝ የያዘውን ድንጋይ ሶስት ጊዜ ያጋጫል፡፡

ድንጋይ የማጋጨት ክወናዊ ትዕምርት “ይህን ያደረገ አካል እንደዚህ ይጋጭ፣ ጭንቅላቱ እንደዚህ ይፍረስ፡፡” የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ ሶስት ጊዜ መሆኑ እርግማኑ የተሟላ፣ ሙሉና ትክክል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በእጃቸው የያዙትን ድንጋይ ካጋጩ በኋላ ይረግማሉ፡፡ እርግማኑን የሚናገረው የፕሮግራሙ መሪ ሲሆን፣ እሱ ያለውን ሕዝቡ በአንድ ላይ ይደግማል፡፡ በነሐሴ 26 ቀን፣ 2009 ዓ.ም በሙዳ በዓል ወቅት ሲከወን ከተመለከትኩት እርግማን በአጭሩ የሚከተለው ነው፡፡

| **የፕሮግራሙ መሪው** | **ሕዝቡ** |
|---|---|
| Kan hamtuu nurratti yaadu dachiirra haa badu | haa badu |
| (ለእኛ ክፉ የሚያስብ ከምድር ይጥፋ፡፡) | (ይጣፋ) |
| Kan Abbiyyoo tufate haa tufatamu | haa tufatamu |
| (አብዮን የናቀ የተናቀ ይሁን፡፡) | (ይሁን) |
| Kan Abniyyoo dhiibe haa dhiibamu | haa dhiibamu |
| (አብዮን የገፋ ይገፋ፡፡) | (ይገፋ) |
| Dhakaa haa tahu | haa tahu |
| (ድንጋይ ይሁን፡፡) | (ይሁን) |
| Akka dhakaa kana haa waldhahu | haa waldhahu |
| (እንዲህ ድንጋይ ይጋጩ፡፡) | (ይጋጩ) |

Awwaalli isaani bakki hin beekamin hin beekamin

(መቃብራቸው አይታወቅ።) (አይታወቅ)

ሁለተኛ፤ የእጅ ባትሪ ወደ ሰማይ ማብራት ነው። በስፍራው የተገኘና የእጅ ባትሪ የያዘ ሰው የእጅ ባትሪውን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ያደርጋል። የፕሮግራም መሪው "ያዛችሁ?" ሲል ይጠይቃል። ሕዝቡም በአንድ ላይ "አዎ" ይላል። ድጋሚም የፕሮግራም መሪው "ያዛችሁ?" ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ይጠይቃል። ሕዝቡም በአንድ ላይ "አዎ" ይላል። የፕሮግራም መሪው "አብራ !!" የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ በስፍራው የተገኘና የእጅ ባትሪ የያዘ ሰው ሁሉ የባትሪውን ብርሃን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ያበራል። የፕሮግራም መሪው ያበሩትን የእጅ ባትሪ "አዙር" የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ ሁሉም በእጅ የያዘውን ባትሪ ሰማይ ላይ እንዳበራ ያሽከረክረዋል።

የእጅ ባትሪን በማብራት "ዐይናቸው ላይ እንዲህ ይብራ፣ ብርሃኑም ዐይናቸውን ያጥፋው፣ እንዲህ በእሳት ይቃጠሉ።" የሚሉ ትርጓሜዎች አሉት። ብርሃኑን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ማድረግ ደግሞ "ፈጣሪ ሆይ፣ ይህንን በደል ፈጽሟልና በብርሃን ፍጥነት እርምጃ ውሰድበት።" የሚል ትርጉም አለው። ባትሪ ሰማይ ላይ ማሽከርከር "ጠላት ዞሮ ዞሮ ውጤት አልባ ይሁን። ጠላት እንዲህ ይዙርበት። አሸናፊነቱ የእኛ ይሁን።" የሚሉ ትርጓሜዎች አሉት።[151] እርግማኑን የሚናገረው የፕሮግራሙ መሪ ሲሆን፣ እሱ ያለውን ሕዝቡ በአንድ ላይ ይደግማል። እርግማኑም በአጭሩ የሚከተለው ነው።

**የፕሮግራም መሪው** **ሕዝቡ**

Kan hamtuu nurratti yaadu dachiirra haa badu haa badu

(ለእኛ ክፉ የሚያስብ ከምድር ይጥፋ።) (ይጣፋ)

Kan Abbiyyoo tufate haa tufatamu haa tufatamu

(አብዮን የናቀ የተናቀ ይሁን።) (ይሁን)

Kan Abniyyoo dhiibe haa dhiibamu haa dhiibamu

(አብዮን የገፋ ይገፋ።) (ይገፋ)

Iji haa ifu haa ifu

151 - አቶ ኑማን መሃመድ፣ ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድና አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም።

(ዐይኑ ላይ እንዲህ ይብራ፡፡)　　　　　　　　　　(ይብራ)

iji ifaan haa badu　　　　　　　　　　haa badu

(ዐይኑ በብርሃን ይጥፋ፡፡)　　　　　　　　　　(ይጣፋ)

Akka baatirii kana itti haa maru　　　　　　　　　　haa maru

(እንደዚህ ባትሪ ይዙርባቸው፡፡)　　　　　　　　　　(ይዙርባቸው)



*ፎቶ፣ 33 የእጅ ባትሪ በማብራት እርግማን ሲፈጽሙ የሚያሳይ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

ሶስተኛ፤ የእጅን መዳፎች እርስበርስ በኃይል ማማታት ነው፡፡ በስፍራው የተሰበሰበ ሰው ሁለት እጁን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ይዘረጋል፡፡ የፕሮግራም መሪው “ዘረጋችሁ?” ሲል ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡ ድጋሚም የፕሮግራም መሪው “ዘረጋችሁ?” ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡ የፕሮግራም መሪው “ሰብስብ” የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ ሕዝቡም የዘረጋውን የእጅ መዳፍ ወደ ውስጥ በማጠፍና ወደ ውጪ በመዘርጋት የመሰብሰብ ምልክት ያሳያል፡፡ የፕሮግራም መሪው “ሰበሰባችሁ?” በማለት ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡ ድጋሚም የፕሮግራም መሪው “ሰበሰባችሁ?” ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡

የፕሮግራም መሪው “ፈትግ” ሲል፣ ሕዝቡ የእጆቹን መዳፎች እርስበርስ በፍጥነት ያፋትጋል፡፡ የፕሮግራም መሪው “ፈተጋችሁ?” በማለት ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡

ድጋሚም የፕሮግራም መሪው “ፈተጋችሁ?” ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ “አዎ” ይላል፡፡ ከዚህ በኋላ የፕሮግራም መሪው “ምታ” የሚል ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ሕዝቡም የእጆቹን መዳፎች እርስበርስ በኃይል ያማታል፡፡ የእጅ ምቱም ለሶስት፣ ለሰባት ወይም ለአስር ጊዜ በመቁጠር ይደጋገማል፡፡ መዳፎችን እርስበርስ በኃይል የማጋጨት ድርጊትና ግጭቱ የሚፈጥረው የጭብጨባ ድምጽ የሁሉም ሰው እኩል እንዲሆን ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ ሁሉም ሰው እኩል የማያጨበጭብ ከሆነ የፕሮግራም መሪው እርግማኑ ድጋሚ እንዲከወን ያዛል፡፡

ሕዝቡ የዘረጋውን የእጅ መዳፍ ወደ ውስጥ በማጠፍና ወደ ውጪ በመዘርጋት የመሰብሰብ ድርጊት የሚያሳየው ጥፋት ያጠፋውን ቡድን በእጅ መዳፍ ውስጥ ማስገባትና በቁጥጥር ስር ማዋልን የሚገልጽ ትዕምርት ነው፡፡ ሕዝቡ የእጆቹን መዳፎች እርስበርስ በፍጥነት የማፋተጉ ድርጊት በመዳፍ ውስጥ የገባውን ቡድን መጨፍለቅን፣ ማሸትንና ማስጨነቅን የሚገልጽ ትዕምርት ነው፡፡[152] የእጆችን መዳፎች እርስበርስ በኃይል ማማታት በቁጥጥር ስር ውሎ የታሸው ቡድን እንዲህ ይመታ፣ እንዲህ ይውደም የሚል ትርጉም አለው፡፡

የእጅ ምቱ ለ3፣ ለ7 ወይም ለ10 ጊዜ መከወኑ የራሱ ትርጉም አለው፡፡ 3 ቁጥር የምሉዕነት ተምሳሌት ነው፡፡ ምቱ 3 ጊዜ መሆኑ የተሟላ እርግማን ማድረግን ለማረጋገጥ ነው፡፡ 7 ቁጥር የቃልኪዳንና የፍጻሜ ተምሳሌት ነው፡፡ ምቱ 7 ጊዜ መሆኑ በእርግማኑ ምክንያት ለሚወሰድባቸው እርምጃ ውሳኔ መስጠትን የሚገልጽ ቃልኪዳን ነው፡፡ 10 ቁጥር የማይቋረጥ ረጅም ጊዜን የሚወክል ተምሳሌት ነው፡፡ ምቱ ለ10 ጊዜ መሆኑ ደግሞ እርግማኑ ቀጣይ፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ለዘለዓለም የጸና መሆኑን ለመግጽ ነው፡፡ እርግማኑን የሚናገረው የፕሮግራሙ መሪ ሲሆን፣ እሱ ያለውን ሕዝቡ በአንድ ላይ ይደግማል፡፡ እርግማኑም በአጭሩ የሚከተለው ነው፡፡

| **የፕሮግራም መሪው** | **ሕዝቡ** |
| --- | --- |
| Akkas haa walitii buhan | walttii buhan |
| (እንደዚህ እርስበርስ ይማቱ፡፡) | (ይማቱ) |
| Gurri isaanii haa duudu | haa duudu |
| (ጆሯቸው ይደንቁር፡፡) | (ይደንቁር) |

[152] - አቶ ኑማን መሃመድ፣ ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድና አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

| | |
|---|---|
| Afaani saanii walitti haa maxana | haa maxana |
| (አንደበታቸው እንዲህ ይጣበቅ፡፡) | (ይጣበቅ) |

አራተኛ፤ እጅን በትንፋሽ መጥረግ ነው፡፡ በስፍራው የተሰበሰበ ሰው ሁለት እጁን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ይዘረጋል፡፡ የፕሮግራም መሪው "ዘረጋችሁ?" ሲል ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ "አዎ" ይላል፡፡ ድጋሚ የፕሮግራም መሪው "ዘረጋችሁ?" ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡም በአንድ ላይ "አዎ" ይላል፡፡ የፕሮግራም መሪው "አብር" የሚል ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ሕዝቡም ወደ ላይ የዘረጋውን የእጅ መዳፍ ሰብሰብ በማድረግ ሁሉም ሰው ውስጥ እጁን በትንፋሹ እፍ- እፍ- እፍ ይላል፡፡ የእጅ መዳፍን በትንፋሽ እፍ- እፍ- እፍ ማለት ማስወገድን፣ መጥረግን ወይም ማባረርን የሚወክል ትዕምርት ነው፡፡ በዚህ ትዕምርት መሰረትም የሚረገመው ቡድን እንዲጠፋ ወይም እንዲወገድ ይደረጋል፡፡ ይህ እርግማን የሚረገመውን አካል ከምድረ ገጽ የሚያጠፋና የሚያወድም እንደሆነ ይታመናል፡፡

እነዚህ የእርግማን ክወናዎች ተከውነው ሲጠናቀቁ የማሳረጊያ ስርዓት ይፈጸማል፡፡ ስርዓቱም ፊርማ ነው፡፡ የፕሮግራም አስተባባሪው የእርግማን ክወናዎችን ሲያጠናቅቁ "ፊርም" በማለት ሕዝቡን ያዛል፡፡ ሕዝቡም በእጁ መሬት ላይ የመፈረም ምልክት ያሳያል፡፡ ይህ ፊርማ የእርግማኑ ማረጋገጫ ነው፡፡ ውሳኔን ማስተላለፊያ ነው፡፡ የተከፈተን የክስ ፋይል መዝጊያ ነው፡፡ የተሰጠው ቃል እንዳይታጠፍ ማረጋገጫ ማህተም ነው፡፡[153] ይህ የፊርማ ስርዓት የእርግማን ስርዓት ከመግለጽ በተጨማሪ ወደ ሌላ ክወና መሸጋገርን የሚያሳይ የክወና ቅየሳ ድርጊት ነው፡፡

## 8.2.9 የምህላ ስርዓት

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የምህላ ስርዓት የሚከወነው በአገር፣ በክልል፣ በዞን ወይም በመካነ ቅርሱ አካባቢ ችግር ሲከሰት ነው፡፡ ችግሩ የአገራት ጦርነት፣ የእርስበርስ ግጭት፣ የመንግስትና የሕዝብ ግጭት፣ በሽታ፣ ረሃብ፣ የዝናብ አጥረት ወይም ድንገተኛ ወረርሽኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ሕዝቡም ፈጣሪ ከችግሩ እንዲያወጣቸው፣ ሼኽ ሁሴን ችግሩን እንዲፈቱላቸው ይጸልያሉ፤ ይለምናሉ፡፡ በ2009 ዓ.ም በሙዳ በዓል ወቅት በአገር ደረጃ የተፈጠረውን የሰላም

---

[153] - አቶ ኑማን መሃመድ፣ ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድና አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

እጦትና በአካባቢው የተከሰተውን የዝናብ እጥረት ስጋት ፈጣሪ እንዲቀርፍላቸው የምህላ ስርዓት ሲከውኑ ተመልክቻለሁ፡፡

ምህላውን የሚያቀርበው የፕሮግራሙ አስተባባሪ ነው፡፡ ምህላውም በልመና፣ በጥያቄና በትንተና መልክ ይቀርባል፡፡ የፕሮግራሙ አስተባባሪ ምህላውን በጥያቄ መልክና በትንተና መልክ ሲያቀርብ፣ ተመልካቹ ``አዎ'' በማለት የፕሮግራም መሪውን ምህላ ያጸናል፡፡ የፕሮግራሙ አስተባባሪ ምህላውን በልመና መልክ ሲያቀርብ፣ ተመልካቹ ``አሜን'' በማለት የፕሮግራም መሪውን ምህላ ያጠናክራል፡፡ በወቅቱ ከቀረበው ምህላ መካከል የተወሰነውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

Gadaan gadaa salaamaa tii?

Gosaan naannummaa wal qooduun hin jiruu?

Walitti bu’uun hin jiruu?

Biyyi hundi nagayaa?

Oromoo fi Somaaleen waliin nagayaa?

Biheer, biheeresaboochiin hundi nagayaa?

Akkuma durii walitti siquu, waliin du’uu?

Giddun uummataa fi mangistii nagayaa?

Aalgaan mangistii nagayaa?

Mootummaan nu bulchu nagayaa?

Roobaan gallaa?

Rabbi biraamo?

Resuula rabbi biraamo?

Sheekena Huseen biraamo?

Yoo bokkan roobe jimaan lalisa.

Yoo bishaan hin jiraanne jimaan qama’amu illee garaa nama qaba.

Yoo roobni jiraate qanti oomishan biqila.

Yoo roobni jiraate margi biqilee loon wal horti gabatili.

Yaa Rabbi rooba nuuf roobsis !i

Yaa Rabbi dachee nuuf jiisi !

Roobni warqee, nadajii caalaa.

Yaa Rabbi rooba nuuf roobsisi !

ትርጉሙም፡-

ገዳው (ዘመኑ) ሰላም ነው?

በጎሳ፣ በብሔር መከፋፈል የለም?

እርስበርስ መጋጨት የለም?

አገር ሁሉ ሰላም ነው?

ኦሮሞና ሱማሌ እርስበርሳቸው ሰላም ናቸው?

ብሔር፣ ብሔረሰቦች ሰላም ናቸው?

እንደበፊቱ ይቀራረባሉ፤ አብረው ይሞታሉ?

በመንግስትና በሕዝብ መካከል ሰላም ነው?

የመንግስት አልጋ (ስልጣን) ሰላም ነው?

እኛን የሚያስተዳድር መንግስት ሰላም ነው?

በዝናብ እንግባ?

ከፈጣሪ ጋር (በዝናብ) እንገባለን?

ከረሱል (ነብዩ መሐመድ) ጋር (በዝናብ) እንገባለን?

ከሼኽ ሁሴን ጋር (በዝናብ) እንገባለን?

ዝናብ ካለ ጫት ይለመልማል፡፡

ውኃ ከሌለ የተቃመው ጫት ሆድ ይይዛል፡፡

ዝናብ ከሌለ የዘሩት ይደርቃል፡፡

ዝናብ ካለ ሳር በቅሎ ከብቶች ይረባሉ፣ ይደልባሉ፡፡

ፈጣሪ ሆይ ዝናብ አዝንብልን!

ፈጣሪ ሆይ መሬትን አርጥብልን!

ከወርቅም ከነዳጅም ዝናብ ይበልጣል፡፡

ፈጣሪ ሆይ ዝናብ አዝንብልን!

በማለት ለፈጣሪ፣ ለነብዩ መሐመድና ለሼኽ ሁሴን ምህላቸውን ያቀርባሉ። ይህ ምህላ በወቅቱ በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች በነበረው የዝናብ እጥረት ምክንያት ማሳ ላይ ያለ እህል እየደረቀ፣ ከብቶች እየሞቱ፣ ሰዎች በረሃብ እየተጠቁ በመሆኑ የተከናወነ ነው። በመካነ ቅርሱም አካባቢ የዝናብ እጥረት በመኖሩ የውኃ ኩሬዎች እየደረቁ ነበር። ይህ ወቅት እጅግ አሳሳቢ ነበር። በመረጃ ስብሰባዬ ወቅት ሕዝቡ ረጅም ሰዓት የፈጀ የዝናብ ልመና ምህላ ካካሄደ በኋላ፣ ሕዝቡ ምህላውን ሳይጨርስ ሰማይ በደመና ተሸፍኖ የተወሰነ ዝናብ ተንጠባጥቦ ተመለሰ። በዚህ ወቅት ከሕዝብ ይሰማ የነበረ የደስታ እልልታ ከፍተኛ ነበር። ይህ ክስተት በመረጃ ሰብሰባዬ ወቅት በጣም ካስገረሙኝ ገጠመኞቼ መካከል አንዱ ነው።

## 8.2.10 የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና

የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ በቡድን በመሆን የሚከወን ነው። በቡድን በመሆን ሲከውን አንድ የክወናው አቅራቢ በተሰበሰበው ሕዝብ መሃል ላይ በመቆም ወይም መሬት በመቀመጥ ክወናውን ያቀርባል። ታዳሚውም ከዋኙን መሃል በማድረግ፣ በክብ ቅርጽ በመሰባሰብና መሬት ቁጭ በማለት በየክወናው ተሳታፊ ይሆናል። ከዋኙ መንፈሳዊ ሙዚቃውን ሲያቀርብ፣ ታዳሚው የግጥሙን አዝማች በመድገም፣ እንደዜማው ስልት አንገትን ወደ ግራና ወደ ቀኝ በማወዛወዝና ከክወናው አቅራቢ ጋር አብሮ በማዜም ንቁ ተሳታፊ ይሆናል።

የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ በሁለት መንገድ ይቀርባል። አንደኛው፣ ያለምንም አይነት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን፣ ይህ በሙዳ በዓላት ወቅት በዋሬ ስርዓት ላይ የሚቀርብ ነው። ሁለተኛው፣ ደግሞ በከበሮና በጭብጨባ የሚከወን ሲሆን፣ ይህ በቤት ውስጥ በሚከወኑ ስርዓቶች ላይ የሚቀርብ ነው። ነው። ያለምንም የሙዚቃ መሳሪያ የሚቀርበው የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃው የዋሬ ስርዓተከበራ ሊጠናቀቅ ሲል የሚከወን ነው። በዋሬ ስርዓተከበራ የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ከንጋቱ 10 ሰዓት ገደማ ተጀምሮ እስከ 12 ሰዓት ድረስ ይከወናል። አልፎ አልፎም መንፈሳዊ ሙዚቃውን ቀን ላይ ሰዎች በቡድን በቡድን በመሆን ይከውናሉ።

የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ከዋኙ የሚለውን የግጥም አዝማችን ታዳሚው በጋራ በመደገም ይከውናል፡፡ የመንፈሳዊ ሙዚቃው የአዝማች ግጥም በአብዛኛው[154]

Allaahu maraam Nuur Huseen

Aannanii harmi keessan lachuu

Itti seenne gadaa gamachuu

ትርጉሙም፡-

አላሁ-መ-እርሐም ኑር ሁሴን

ሁለቱ ጡትዎ ወተት ነው

ወደ ደስታ ገዳ (ዘመን) ገባንበት

ማለት ነው፡፡ “አላሁ-መ-እርሐም ኑር ሁሴን” ማለት ‹‹አላህ ኑር ሁሴንን ይማር ወይም ይባርክ እንደማለት ነው፡፡ የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ከባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ጋር በሥልተ ምት (ሪትም) ከመለየቱ በስተቀር በሙዚቃዊ ቅኝቱ “ዶሪያን ፔንታቶኒክ ስኬል” ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ስኬል በኖታ ምልክት የሚከተለው ነው፡፡



በዋሬ ላይ የሚከወነው የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ በተረጋጋ ስሜትና ለፈጣሪ በሚደረግ ምልጃ አይነት ዜማ ስላለው፣ ቀልብን የማረጋጋትና ስሜትን በቀላሉ የመንካት ባህርይ አለው፡፡ በዚህም ባህሪው ይመስላል የመንፈሳዊ ሙዚቃው ከዋኝም ሆነ ታዳሚ በጥልቅ ስሜት ውስጥ በመግባት የሚከወነው፡፡

## 8.3 የዝክሪ ስርዓተከበራ

“ዝክሪ” የሚለው ቃል፣ “ዲክር” ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ነው፡፡ ቃሉም ሁለት እሳቤዎችን ይገልጻል (Renard, 2005፡198)፡፡ አንደኛው ፈጣሪን ማስታወስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከፈጣሪ ጋር ያለን ግንኙነት የሚገልጽ ነው፡፡ ዝክሪ ሁለት ጉዳዮችን እንደሚይዝ Jeylan (2016፡2) ይገልጻል፡፡ እነሱም፣ የእስላማዊ ኃይማኖት አገላለጽ ስልትንና የራስን የመንፈስ ደረጃ

[154] - በካሴት ከታተመ የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ የተወሰደ፡፡

ናቸው። የዝክሪ መሰረቱ አላህን ለማስታወስ፣ ለእሱ ያለን ጥልቅ ፍቅር (ታፋኩር) ለመግለጽ፣ የእሱን ልዕለ ኃያልነትና ትክክለኛነት ለሌሎች በማሳወቅ በስነምግባር (አክህላክ) የታነጹ ለማድረግ እንደሆነ Jeylan (2016፡2) Akhir and Sabjan (2015)ን በመጥቀስ ያብራራል። የዝክር ስርዓት ግጥምን፣ ግላዊ ወይም ቡድናዊ ዜማን (ሙዚቃን)፣ ቡድናዊ ውዝዋዜንና እንቅስቃሴን የሚይዝ ነው።

የዝክሪ ስርዓት በሱፊ የእስልምና ስርዓት ውስጥ የተለመደ እንደሆነ Renard (2005) ይገልጻል። በኢትዮጵያም የተለያዩ የእስልምና ኃይማኖት ማዕከላት የዝክሪ ስርዓተከበራ የተለመደ ነው። በሐረርጌ ሶስት አይነት የዝክሪ ስርዓት መኖሩን Jeylan (2016፡2) ይገልጻል። እነሱም በግለሰብ፣ በቡድንና በሱፊ ዑለማዎች ስም በተመሰረቱ የአምልኮ ቦታዎች ሕዝቡ በጋራ በመሰባሰብ የሚከውናቸው ናቸው። በወሎም  በተለያዩ ወቅቶች የሚከወኑ የዝክሪ ስርዓቶች መኖራቸውን Hussein (2001) እና Setargew (2017) ይገልጻሉ። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የተለያዩ የዝክሪ ስርዓተከበራዎች አሉ። እነሱም የሐጂ አደም፣ የሼኽ ዑመር፣ የአብሮኜ፣ የሼኽ ሁሴን፣ የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ፣ የመውሊድ፣ የአሹራ፣ የጁምዓና የዶውሪ ናቸው።

እነዚህ ዝክሪዎች በተለያዩ ወቅቶች የሚከወኑ ናቸው። እነዚህም ወቅቶች በሙዳ በዓላት ወቅትና ከሙዳ በዓላት ወቅት ውጪ በሚል መክፈል ይቻላል። በመካነ ቅርሱ የሚከወኑ እነዚህን ስርዓተከበራዎች ለመግለጽ ዝክሪና ሀድራ የሚሉ ቃላትን በመለዋወጥ መጠቀም የተለመደ ነው። የዝክሪ ስርዓት የሀድራና የዶውሪ ስርዓቶችን የሚያጠቃልል እሳቤ እንዳለው Renard (2005) ይገልጻል። ሀድራ የሚለው ቃል "ሑዱር" ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም በቡድን መሰባሰብ ወይም በጋራ መገኘት ማለት ነው። ዶውሪ ደግሞ በቡድን ክብ መስራት ማለት ነው። በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ የዝክሪ ስርዓቶች ሶስት ናቸው። እነሱም፣ የሐጂ አደም ሀድራ፣ የአብሮኜ ዝክሪና የዶውሪ ስርዓት ናቸው። እነዚህ ዝክሪዎች ያላቸውን ክወና በተናጠል ቀጥለን እንመልከት።

### 8.3.1 የሐጂ አደም ሀድራ ስርዓተከበራ

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚከወኑ ሀድራዎች መካከል አንዱ የሐጂ አደም ነው። ሐጂ አደም ከወሎ ወደ አካባቢው እንደመጡ ይነገራል። ሐጂ አደም ባለከራማ ናቸው። ይህ ዝክሪም በእሳቸው ስም እንዴት ሊሰየም እንደቻለ መረጃ ሰጪዎቹ "እሳቸው በሕይወት በነበሩበት ወቅት ቦረና የሚባል ጂኒ (ሰይጣን) ነበር። ይህ ቦረና ሰውን ይዞ ያሰቃይ ነበር። በቦረና የተያዙ ሰዎች

እሳቸው ዘንድ በመምጣት ይድኑ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ሀድራው በእሳቸው ስም ተሰየመ፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡[155] ሐጂ አደም በሕይወት በነበሩበት ወቅት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ውስጥ የሚያስተምሯቸው በርካታ ደረሳዎች ነበሩ፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት ለደረሳዎቻቸው፣ ለነዋሪዎችና ለመንፈሳዊ ተጓዦች የሚሆኑ ከ100 በላይ የእርድ ከብቶች ይዘው ይመጡ እንደነበር ይነገራል፡፡[156]

ሐጂ አደም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ዝክሪውን የመምራት ኃላፊነት ልጃቸው ሐጂ ተማም አደም ተረከቡት፡፡ እሳቸውም በሞት ሲለዩ ልጃቸው አዋሩዲን ተማም ስርዓቱን ተረክበው መምራት ጀመሩ፡፡ በአሁኑ ወቅትም የሐጂ አድም ዝክሪን የሚመሩት አዋሩዲን ተማም ናቸው፡፡ የሐጂ አደም ሀድራ የሚከወንበት የራሱ ቋሚ ስፍራ አለው፡፡ በስፍራው ላይም ሰፊ ቤት ተገንብቷል፡፡ የቤቱም ጣሪያ በቆርቆሮ የተሰራ ሲሆን፣ ዙሪያ አልፎአልፎ ከተተከሉ ቋሚ ከንቾች በስተቀር ግድግዳ የለውም፡፡ የቤቱ ግንባታ የተካሄደው ሐጂ አደም በሕይወት በነበሩበት ወቅት ነው፡፡



*ፎቶ፣ 34፣ የሐጂ አደም ሀድራ የመከወኛ ስፍራ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በሐጂ አደም ሀድራ የሚከወን መንፈሳዊ ሙዚቃ ሹቢሳ ይባላል፡፡ ሹቢሳ የሚለው ቃል የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም ጭፈራ ማለት ነው፡፡ ይህ መንፈሳዊ ሙዚቃ በደማቅ

---

[155] - ሼኽ ቃሲም ሼኽ አልይ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ህዳር1 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

[156] - ሼኽ ሰይፊዲን ሀጂ ዑስማን፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 29 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

ጭብጨባና በድቤ (በከበሮ) የታጀበ ነው፡፡ መንፈሳዊ ሙዚቃውም ጭፈራ መሰል የሰውነት እንቅስቃሴም አለው፡፡ የሀድራ ስርዓት የሚከወነው በምሽት ብቻ ነው፤ በቀን አይከወንም፡፡ ሀድራው መከወን የሚጀምረው ከምሽቱ 4 ሰዓት አካባቢ ሲሆን፣ የሚያበቃው ደግሞ ከሌሊቱ 9 ሰዓት ገደማ ነው፡፡ በሐጂ አደም ሀድራ ላይ የሚከወን የሹቢሳ መንፈሳዊ ሙዚቃ አቅራቢ የግጥሙን አዝማች ሲል፣ ታዳሚው አዝማቹን በጋራ ይደግማል፡፡ የመንፈሳዊ ሙዚቃው አዝማች በአብዛኛው ሁለት ነው፡፡[157] አንደኛው አዝማች፡-

Allaahu maraam Abbiyyo

Xaqallaloo kiyyahoo

Xaqallalii itti haaja kiyyahoo

ትርጉሙም፡-

አላሁ-መ-እርሐም አባቴ

የእኔ ጠባቂ

ሀጃችን (ችግራችን) በአንተ ይውጣ፡፡

ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው አዝማች ደግሞ፣

Salaamaleeykum Nuur Huseeniyyaa

Salaamaleeykum jiruu tiyyaa

Mandarri kee baalee gubbaa irraa

Kibirriini kee hin dhaamu nama irraa

ትርጉሙም፡-

አሰላሙ-አለይኩም የኔ ኑር ሁሴን

አሰላሙ-አለይኩም ሁሉ ነገሬ

መንደርክ በባሌ ከፍታ ላይ ነው

ያንተ ክብር (ፀጋ) ከሰው ላይ አይጠፋም፡፡

ማለት ነው፡፡ ሀድራው የሚጀመረው ነብዩ መሃመድን በሹቢሳ መንፈሳዊ ሙዚቃ በማወደስ ነው፡፡ ነብዩ መሃመድን ካወደሱ በኋላ ሼኽ ሁሴንን የሚያወድሱ የሹቢሳ ግጥሞች ይቀጥላሉ፡፡ ቀጥሎም ሼኽ ሶፍ ዑመርን ያወድሳሉ፡፡ የሹቢሳ መንፈሳዊ ሙዚቃ ቅኝቱ ‹‹ዶሪያን ፔንታቶኒክ

---

[157] - በሙዳ በዓል ወቅት ከተሰበሰቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች የተወሰደ፡፡

ስኬል" ሆኖ፣ ሙዚቃው ሲጀምር ግን አምስተኛውን የድምፅ ዲግሪ ይዞ ይነሳል። የሚጨርሰው ግን በሁለተኛው የድምፅ ዲግሪ ነው። በመሆኑም የሙዚቃ ባህሪው "ዶሪያን ፔንታቶኒክ ስኬል" ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ይቻላል። የሹቢሳ መነፈሳዊ ሙዚቃ ስኬል በኖታ ምልክት የሚከተለው ነው።



በዚህ ዝክሪ ላይ በክፉ መንፈስ የተያዙ ሰዎች ከሕመማቸው ለመፈወስ በብዛት ይመጣሉ። ዝክሪው እየደመቀ ሲሄድ ሕመምተኞቹን በመያዝ ዝክሪው በሚከወንበት ስፍራ መሃል ላይ ያስገቧቸዋል። ሕመምተኞቹም እላያቸው ላይ ያረፈው ክፉ መንፈስ በሹቢሳው አማካኝነት መረበሽ ይጀምራል። በዚህም ሳቢያ በክፉ መንፈስ የተያዙ ሕመምተኞች የሚያሰሙት ከፍተኛ ጩኸት፣ ማጓራት፣ ከስፍራው ለማምለጥ ሲሞክሩ ከአስታማሚዎቻቸውና ከሀድራው አስፈጻሚ ደረሳዎች ጋር የሚያደርጉት ትንቅንቅ፣ እንደ ጅብ መጮኽና እምብዛም ያልተለመዱ ድምጾችን ሲያወጡ መስማት በስፍራው የተለመደ ነው። ይኸ አይነት ሁኔታ ለሀድራው ወይም ለስፍራው አዲስ በሆነ ሰው ላይ ከፍተኛ የፍርሃት ስሜት የሚፈጥር ነው።

የሐጂ አደም ሀድራ የመሪነት ስልጣን በውርስ የሚተላለፍ ነው። ሀድራውን የመምራት ሀላፊነት ያለባቸው የእሳቸው ልጆችና ቤተሰቦቻቸው ብቻ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ሀድራውን በኃላፊነት የሚመሩት አዋሩድ ተማም ናቸው። የስርዓቱ መሪዎች ከአባት ወደ ልጅ ስርዓቱን የመምራት ውርስ ሲቀበሉ አብረው የሚወርሱት ጥቁር ካባ አለ። በአሁኑ ወቅት መሪ የሆኑት አዋሩድ በሀድራው መከወኛ መሃል ስፍራ ላይ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ጥቁር ካባቸውን በመልበስ አናታቸውንና ፊታቸውን በነጭ ጥምጣም በመሸፈን ይቆማሉ። እሳቸውም ሀድራው ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ በመቆም ስርዓቱን ይመራሉ።

በሀድራው ላይ የሚቀርበው የሹቢሳ መንፈሳዊ ሙዚቃ የግጥም ስልት፣ የሙዚቃ ምት፣ የሙዚቃ ቅኝትና የአጨፋፈር ስልት ከባሌ ባህላዊ ሙዚቃ ስልት ጋር ይመሳሰላል። ይህ ምናልባት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የባሌን ማህበረሰብ ባህል የመቅረጽ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል። ወይም የመካነ ቅርሱ ሹቢሳ ከማህበረሰቡ ነባር ባህል የተወሰደ ሊሆን ይችላል።

እነዚህ ሁለት የተለያዩ መላምቶች እንዳሉ ሆነው፣ ይህ ሀድራ የተጀመረው በሐጂ አደም የሕይወት ዘመን ነው።

ሐጂ አደም ይህንን ቦታ መቼ እንደመሰረቱ በትክክል አይታወቅም። Østebo (2015፡97) እሳቸው በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ መወለዳቸውን ይገልጻል። በአሁኑ ወቅት ሀድራውን ከሚመሩት የእሳቸው የልጅ ልጅ ካላቸው እድሜ እንዲሁም ኦስቴቦ ካቀረበው መረጃ በመነሳት ሀድራው የቅርብ አመታት ታሪክ እንዳለው መገመት ይቻላል። ሀድራው የተጀመረበት ዓመትም በግምት ከ70 አመት አይበልጥም። ይህ ከሆነ ደግሞ የሹቢሳ አጨፋፈር ስልትን ከባሌ ማህበረሰብ ነባር ባህል ውስጥ እንደወሰዱት ያመላክታል።

## 8.3.2 የአብሮኜ ዝክሪ

የአብሮኜ ዝክሪ የሚከወነው ከዶቆ ከራ በግምት 200 ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ቦታ ነው። ዝክሪው የሚከወነው በሙዳ በዓል ወቅት ለአንድ ቀን ብቻ በመሆኑ፣ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ይከወናል። የዝክሪው ክወና የሙዳ በዓላት በሚከበሩበት በመጀመሪያው ቀናት ከምሽቱ 5 እስከ 6 ሰዓት ባለው ጊዜ ተጀምሮ፣ ከ ሌሊቱ 7 ሰዓት እስከ 7፡30 ባለው ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል። የአብሮኜ ዝክሪ እሳት በማንደድ የሚከወን ነው። እሳት ለማንደድ የሚጠቀሙት ወፋፍራም የግራር እንጨቶችን ነው። እንጨት ማንደድ የሚጀምሩት ከምሽቱ 3 ሰዓት አካባቢ ነው። ክወናው በእሳቱ ዙሪያ ክብ በመሆን መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን ማቅረብና የተለያዩ መንፈሳዊ ድርጊቶችን መፈጸምን ይይዛል።

ሀድራውን የሚከውኑት፣ የሚያስፈጽሙትና በእሳቱ የመጀመሪያ ረድፍ ላይ በመሰለፍ ክብ የሚሰሩት የአብሮኜ ጎሳ አባላት ብቻ ናቸው። ከአብሮኜ ጎሳ አባላት ውጪ ሌላ ማንኛውም ሰው ስርዓቱን አይከውንም፤ በእሳቱ የመጀመሪያ ረድፍ ላይም መሰለፍ አይችልም። የአብሮኜ ጎሳ ከአርሲ ኦሮሞ አብይ ጎሳ ስር ከሚካተተው የቡላላ ንዑስ ጎሳ ስር የሚመደብ ነው (የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣1998 ዓ.ም፡215)። ጎሳው በአርሲ ዞን ገደብና ዲደአ በሚባሉ ቦታዎች እንዲሁም በባሌ ዞን ቆላማ አካባቢዎች የሚኖር ነው። ዝክሪው በሚከወንበት ስፍራ ላይ የተዘጋጀው የግራር እንጨት በደንብ ሲቀጣጠልና ከፍተኛ እሳት መፍጠር ሲጀምር ዝክሪው መከወን ይጀምራል። እሳት የማቀጣጠል ስርዓት “ዋዚዣ” ወይም “ዋሲሳ” በሚል ስያሜ ይጠራ



*ፎቶ፤ 32፣ የአብሮኚ ዝክሪ እሳት በማንደድ ሲከወን፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

ዝክሪው የሚጀምረው በስርዓቱ አስተባባሪ አማካኝነት ነብዩ መሐመድን በማመስገን ነው፡፡ ቀጥሎም ሼኽ ሁሴንን፣ አበል ቃሲምን፣ ሼኽ ሶፍ ዑመርን እንዲሁም ሌሎች ወልዮችን በማመስገን ስርዓቱን ይጀምራሉ፡፡ ዝክሪው ነብዩ መሐመድንና ወልዮችን በመጥራት ከተጀመረ በኋላ የዜከራ መንፈሳዊ ሙዚቃ መከወን ይጀመራል፡፡ የዜከራ መንፈሳዊ ሙዚቃ በጭብጨባ፣ በእልልታና በድቤ የታጀበ ነው፡፡ ድቤው የሚመታው በአጭር በትር (ዱላ) ነው፡፡ በዝክሪው ላይ ሁለት ድቤ መቺዎች በአንድ ላይ በስልት በመምታት የተለያየ ድምጽ እንዲያወጣ ያደርጉታል፡፡ ድቤውን ሲመቱ፣ ድቤውን መሬት በማስቀመጥ፣ በእጅ በማንጠልጠል፣ በእግር መሃል በመጨመር እንዲሁም እግር መሃል በመጨመር ሁለቱንም እግሮች ወደ ላይ በመስቀልና በጀርባ መሬት ላይ በመተኛት በተለያየ ስልትና ውብት ባለው መልኩ ይጫወታሉ፡፡

መንፈሳዊ ሙዚቃው የሚከወነው አንድ ከዋኝ ግጥሞቹን ሲያቀርብ ሌላው ሰው በጋራ የግጥሙን አዝማች በመድገም፣ በማጨብጨብና በእልልታ ያጅቡታል፡፡ የዝክሪው ከዋኞችም ከፊት ለፊት መስመር ወደ መሃል ተራ በተራ በመግባት የተወሰኑት እሳቱን ከቀኝ ወደ ግራ በመዞር መንፈሳዊ ሙዚቃውን ይከውናሉ፡፡ የዜከራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም አዝማች ይደጋገማል፡፡ ከዋኙም ከግጥሙ የተወሰነ ካዜመ በኋላ ተቀባዮች አዝማቹን በጋራ በማለት ይደግማሉ፡፡[158] የዜከራ መንፈሳዊ ሙዚቃ አዝማች፡-

[158] - በሙዳ በዓል ወቅት ከተሰበሰበ መንፈሳዊ ሙዚቃ የተወሰደ፡፡

Makoole makoo barcumaan irraa techaa warqii keessaa janoo garbbii

Makoole makoo dhufanee ganda keessaan bulee ya malikofanuu nalee

Sofuu-marole jetii aritii aschokaayii kiya kotuu dafiitii

ትርጉሙም፡-

መኮሌ መኮሌ ጃኖ ገርቢ የተቀመጣችሁበት በርጩማ ውስጡ ወርቅ አለ

መኮሌ መኮሌ በእናንተ ደጅ መጥተን አድረናል ይቅናን

ሶፍዑመር የኔ ጀት በአስቸኳይ ድረስልኝ፡፡

የሚል ነው፡፡ "መኮሌ" የሚለው ቃል መኮ የሚለውን ስም በቁልምጫ መጥራት ነው፡፡ አዮ መኮ የሼኽ ሶፍ ዑመር ልጅ ናቸው፡፡ "ጃኖ ገርቢ" የሚለው ቃል በአርሲዎች ዘንድ ሼኽ ሁሴን በቁልምጫ የሚጠሩበት ስያሜ ነው፡፡ ትርጉሙም ጃኖ ያለበሰህ አድባር እንደማለት ነው፡፡ ይህ አይነት የድቤ አመታት ስልት፣ የዜከራ ግጥምና ዜማ በሼኽ ሶፍ ዑመር መካነ ቅርስ ከሚከወንና ሼኽ ሶፍ ዑመርን ከሚያወድሱበት "ዋሪዳ" ከተሰኘ መንፈሳዊ ሙዚቃ ጋር ተቀራራቢ ያደርገዋል፡፡

የዜከራ መንፈሳዊ ሙዚቃ በሥልተ ምት (Rythm) ዓይነት ሊቀመጥ የሚችል ሲሆን፣ በመሠረታዊነት የድቤ አመታት ላይ የምናዳምጠው የአመታት ቀመር ነው፡፡ የድቤው አመታት ቀመር ከዜማው ጋር አንድ ላይ ሲሄድ ይህንን የሚመስል የስኬል ኖታ መልክ ይይዛል፡፡



ዝክሪው እየሞቀ ሲመጣ፣ ተሳታፊው በመንፈሳዊ ኃይል መሞላት ይጀምራል፡፡ በዚህን ወቅት ቀድሞ የነበራቸው ስሜት እየተቀየረ የመኮሳተር፣ ፊትን የማጨማደድ፣ ዐይንን የማፍጠጥ፣ የመጨነቅ፣ የመጮኽ፣ የማጓራትና በፍጥነት ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ ድርጊቶችን መፈጸም ይጀምራሉ፡፡ በዚህን ወቅት ጭብጨባው፣ እልልታውና ውዝዋዜው ይደምቃል፡፡ ከዋኞቹ በመንፈስ ሲሞሉ ለመታደምና በዐይን ለማየት የሚከብዱ በጣም አስፈሪና መንፈስን የሚረብሹ ድርጊቶችን ይፈጽማሉ፡፡

እነዚህ ድርጊቶችም ከፍተኛ የእሳት ነበልባል በሚፈጥሩት ወፋፍራም የግራር ፍም ላይ በባዶ እግራቸው እሳቱን መርገጥና እሳቱ መሃል መቆም ናቸው፡፡ በዚህን ወቅት ፍም የሚነደው

እሳት መሃል ወደ ላይ ይበተናል፡፡ ልብሳቸውን በማውለቅ ወይም ልብሳቸውን እንደለበሱ ከሚነደው እሳት ላይ ይንከባለላሉ፡፡ ከሚነደው እሳት መሃል ፍም ከሰል በእጃቸው በማንሳት በመዳፋቸው ወደ ላይ፣ ወደ ላይ በማንቀርቀብ ትርዒት መሰል ድርጊት ይከውናሉ፡፡ በጣም ፍም የሆነ ከሰል በአፋቸው ውስጥ በመክተት ይጎርሱታል፡፡

ከዋኞቹ የሚነደውን እሳት በእግራቸው ሲረግጡም፣ እሳት ላይ ሲንከባለሉ፣ በእጃቸው ፍም ከሰል ሲያንቀረቅቡም ሆነ ፍም ከሰል አፋቸው ውስጥ ሲከቱ ምንም አይነት አደጋ በሰውነታቸው ላይ አይከሰትም፡፡ በእሳቱ ላይ ከሚፈጽሟቸው ድርጊቶች በተጨማሪ አልፎ አልፎ እጅግ አስፈሪ ድርጊቶችንም ይከውናሉ፡፡ እነዚህም ድርጊቶች ስለት ያለው ቢላዋ ወይም ጩቤ ወደ አፋቸው ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ማስገባት እንዲሁም ስለት በምላሳቸው መሃል ማሳለፍ ናቸው፡፡ ከዋኞቹ እነዚህን በጣም አደገኛ ድርጊቶች በሚከውኑበት ወቅትም ሆነ ድርጊቶቹን ከከወኑ በኋላ ምንም አይነት አካላዊ ጉዳት አይደርስባቸውም፡፡

የአብሮኼ ዝክሪ በመካነ ቅርሱ ከሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ሁሉ የተለየ ባህርይ አለው፡፡ ይህ ልዩ ባህሪው የመነጨው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው፣ የክዋኔው ዋና ባህርይ የሰው ልጅ በተፈጥሯዊ ሁነት ሊፈጽማቸው የማይችሉ ልዕለ ሰብዓዊ ክዋኔዎች የሚፈጸምበት መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው፣ ስርዓተከበራው የሀገረሰባዊ እምነት (Superstition) ድርጊቶች እንዴት በእስላማዊ ባህል ውስጥ በውሕደት እንደሚቆዩና የእስላማዊ ባህል በስፋት ባለበት ሁኔታ እንዴት በተውጦ (Acculturation) ውስጥ ሊቆይ እንደቻለ የሚያሳይ መሆኑ ነው፡፡

በዝክሪው ላይ የሚከወኑ የሀገረሰባዊ እምነት ድርጊቶች በእስልምና እንደኃይማኖታዊ ድርጊት፣ ዕውቀትም ሆነ ስልጣኔ አይቀበላቸውም፡፡ ድርጊቶቹን እስልምናው ባይቀበላቸውም በስፍራው የራሳቸው በሆነና በተለየ ቦታ ይከወናሉ፡፡ ይህ ክወናም በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሀገረሰባዊ እምነት ድርጊቶች ከኃይማኖታዊ ድርጊቶች ጋር እንዴት ተዋሕደው እንደሚገኙ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

የአብሮኼ ዝክሪ ላይ የሚሳተፈው ሰው ቁጥር አነስተኛ ነው፡፡ በክወናው ላይም የሚሳተፉት የአንድ ጎሳ አባላት ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ክወና የአብሮኼ ጎሳ አባላት ብቻ ለምን ሊከውኑት እንደቻሉ መረጃ ሰጪዎቹ "ለእነሱ የተሰጠ ችሎታ ነው፡፡" የሚል መልስ ነው የሰጡኝ፡፡[159] ይህን እሳቤ የስነልቡና ባለሙያ የሆነው Skinner (1948፣168-172) የሀገረሰባዊ እምነቶች ድርጊት

---

[159] -ሼኽ ቃሲም ሐጂ አወል፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

የጥቂት ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ማህበረሰቦች ብቻ የሚኖራቸው ልዩ መለያና ተፈጥሯዊ ችሎታ (Innate quality) እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ከመረጃ ሰጪዎቼና ከ Skinner (1948) ሀሳብ የአብሮኼ ጎሳ አባላት እንዳላቸው አይነት ልዩ ችሎታዎች በሰው ልጅ የተፈጥሮ ሂደት ውስጥ ለጥቂቶች ብቻ የሚሰጥ ተፈጥሯዊ ስጦታ ሲሆን፣ አብሮኼዎቹም ይህንን ችሎታ ያገኙት በተፈጥሮ በመመረጥ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጎሳዎች በጥልቀት ቢጠኑ በተፈጥሮ ከመመረጥ ይልቅ፣ ይህንን ችሎታ ሊማሩ ያስቻላቸው አንድ ልዩ አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡

በተለያዩ የዓለም አገራት የተለየ ችሎታ ያላቸው የተወሰኑ ምስጢራዊ ማህበረሰቦች (Secret Societies) አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል፣ በአውሮፓ የጂብሲ ጎሳ እንዲሁም በአፍሪካ የኦግባኒ ጎሳ በናይጀሪያ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ጎሳዎች በዘር የሚወርሱት ልዩ መንፈሳዊ ጸጋ አላቸውና ሰውን የመጉዳትም ሆነ የመጥቀም ችሎታ አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በአገራችንም በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰው ላይ ጥሩም፣ መጥፎም የሚሰሩ "ደብተራዎች"፣ በቤንች ብሔረሰብ ዝናብና ጸሐይን የሚቆጣጠሩ የ"ቲያት" ጎሳ፣ በዘይሴ ብሔረሰብ መብረቅን መቆጣጠር የሚችሉ የ"ማልዝ" ጎሳ፣ በኦሮሞ ብሔረሰብ ዝናብ ማቆም የሚችሉ "ጫሞሺቶች" እና "ማሊማዎች" ይጠቀሳሉ (ሰሎሞን፣2007ዓ.ም፣197)፡፡ በተለያዩ የዓለም አገራት እንደሚገኙ ምስጢራዊ ማህበረሰቦች ሁሉ፣ በድሬ ሼኽ ሁሴንም የዝክሪ ስርዓት የሚፈጽሙት የአብሮኼ ጎሳዎች የተለዩና ልዕለ ሰብዓዊ ክወናዎችን መፈጸም የሚችሉ ምስጢራዊ ማህበረሰቦች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

የእስልምና ኃይማኖት ተቀዳሚ አላማ የእስልምናን ትክክለኛ እሳቤ ማስረጽና ሀገረሰባዊ እምነቶችን ማስወገድ እንደሆነ Saheed (2009፡191) ይገልጻል፡፡ ለዚህም በሳዑዲ አረቢያ- መካና አካባቢው የነበሩ የተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነቶችና የእምነቶቹ የማምለኪያ ስፍራዎች በነብዩ መሐመድና በተከታዮቻቸው ወድመዋል፡፡ በአገራችን የእስልምናም ሆነ የክርስትና ኃይማኖቶች የመስፋፋት ታሪክ ሀገረሰባዊ እምነቶችን፣ ሀገረሰባዊ ኃይማኖቶችን እንዲሁም የማምለኪያ ስፍራዎችን በማውደም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ የኃይማኖቶቹ ታሪክ እንዳለሆኖ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሀገረሰባዊ እምነት ድርጊቶች እስካሁን ይከወናሉ፡፡

በስፍራው በነበረኝ የመስክ ቆይታዬ ወቅት በመካነ ቅርሱ እነዚህ ድርጊቶች እንዴት ሊከወኑ ቻሉ? ወይም እስካሁን እየተከወኑ እንዴት ቆዩ? የሚሉ ጥያቄዎች ወደ አዕምሮዬ ይመጣሉ፡፡

እነዚህ ድርጊቶች በስፍራው እየተከወኑ ሊቆዩ የቻሉት በሶስት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። አንደኛው፣ በኮግሚቲቭ ንድፈሃሳብ መሰረት የሰው ልጅ አዕምሮ ከተፈጥሮ በላይ ነው። የሰው ልጅም የሚያምነው ነገር በጽሑፍ ከሰፈሩ ወይም ካልተጻፉ ሕግጋት በላይ ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ የሚያምነው የእስልምና፣ የክርስትና ወይም የሌላ ኃይማኖት የሚያዘው እንዲህ ነው፤ የእምነት ህጉ እንዲህ ነው፤ ቅዱስ ቁርዓን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሌላ ላይ የተጻፈው እንዲህ በመሆኑ፣ እንዲህ አታድርግ ከሚሉ መሰል ቀኖናዊ ህግጋቶች ውጪ ነው። የሰው ልጅ አዕምሯዊ ተፈጥሮና እምነት ከእነዚህ "አድርግና አታድርግ" ማዕቀፍ በላይ ነው።

ሁለተኛው፣ በአገራችን የእስልምናም ሆነ የክርስትና ኃይማኖት ሲስፋፉ በአካባቢው ካለ ሀገረሰባዊ እምነት ጋር ትግል በማድረግ ነው። በትግሉም ሲያሸንፉ የራሳቸውን ሙሉ ባህርይ በሀገረሰባዊ እምነቱ ላይ በመጫን፣ የእምነቱን አሻራ ሙሉለሙሉ ያጠፉሉ። በትግሉ ሲሸነፉ በሀገረሰባዊ እምነት ይዋጡና እራሳቸው ይጠፉሉ። በትግሉ እኩል ኃይል ኖሯቸው አሸናፊም ተሸናፊም ሲጠፉ ሁለቱም እኩል ይቆያሉ። ይህ የእኩሌታ (Accomodation) ሁነት በኃይማኖቶች ውስጥ ሀገረሰባዊ እምነት፣ በሀገረሰባዊ እምነት ውስጥ ደግሞ ኃይማኖት የእርስበርስ ተጽዕኖ ይፈጥራሉ። የእርስበርስ ተጽዕኖው ደግሞ የሁለቱም ክወናዎች የውሕደት ባህርይ እንዲይዝ ምክንያት ይሆናል። የውሕደቱ መገለጫም ልክ አንደ አብሮኜ ዝክሪ በማዕከሉ የራሱን ክወና፣ ግዛት፣ የመከወኛ ቦታ፣ የተለዩ ባለሙያዎችንና ዕወቅናን ይዞ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ይከወናል።

ሶስተኛ፣ ሀገረሰባዊ ክወናዎች በአንድ ወቅት በተለያዩ አካባቢው በስፋት የነበራቸው ክወና እየቀነሰ ይሄዳል። ክወናቸው ሲቀንስም ሕልውናቸው እየጠፋ ይሄዳል። ክወናዎቹም በሂደት ያላቸውን ሕልውና ለመጠበቅ አንድ ጥግ (Corner) ይዘው ይሸሸጋሉ። የአብሮኜ ዝክሪ በአንድ ወቅት በተለያዩ አካባቢዎች ሲከወን ቆይቶ በአሁን ላይ የተዳከመ ሊሆን ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለሀድራው የመሸሸጊያ ጥግ ሆኖታል። በስፍራውም የሚከወነው ሀድራ ከዚህ በፊት የነበረውን ሕልውና የሚያስቀጥልበትና ያለውን የክወና ቅሪት የሚጠብቅበት ነው።

በመካነ ቅርሱ የሚከወኑት የሐጂ አደም ሀድራና የአብሮኜ ዝክሪ የተለየ ባህርይ አላቸው። የዝክሪ ክዋኔ በዋናነት ከእርኩስ መንፈስ (ጂኒ) ጋር የተያያዘ ነው። የሐጂ አደም ዝክሪ እርኩስ መንፈስን ማስወጣት ነው። የአብሮኜ ዝክሪ ደግሞ በተለየ መንፈሳዊ ኃይል በመሞላት

ልዕለሰብዓዊ ድርጊቶችን መፈጸም ነው፡፡ የእነዚህ ዝክሪዎች ክወና፣ እሳቤና ድርጊት በስፍራው ነባር ከሆኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች ጋር የተፈጠረ ውሕደት ሊሆን ይችላል፡፡

## 8.3.3 የዶውሪ ስርዓት

"ዶውሪ" በቡድን በመሰባሰብ ክብ መስራት ማለት ነው፡፡ ዶውሪ የጸሎት ስርዓት ነው፡፡ የዶውሪ ስርዓት በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚከወን ነው፡፡ ይህ ስርዓት ከሌሎች ስርዓቶች ልዩ የሚያደርገው በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በአንድ ቤት ተሰባስበው ጫት እየቃሙ ጸሎት የሚያደርጉበት ሲሆን፣ ምንም ጩኸት፣ መንቀዥቀዥ እንዲሁም ድምጽን በጣም ከፍ አድርጎ ማውራት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ ስርዓቱ እጅግ የተረጋጋና በከፍተኛ የተመስጦ ስሜት የተሞላ ነው፡፡ በዶውሪ ወቅት ለሚከወን የጸሎት ክዋኔ ጫት ዋና ግብዐት ነው፡፡ በመካነ ቅርሱ ጫት መቃም ይበረታታል፡፡ ጫት መቃም ከድካም፣ ከድብርትና ከእንቅልፍ ስሜት ስለሚታደግ ሰዎች ጠንክረው ጸሎት እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ዶውሪ ረጅም ሰዓት የሚፈጅ የጸሎት ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ረጅም የጸሎት ስርዓት ወቅት ሰዎች ያለመድከምና ያለመሰልቸት ጸሎት እንዲያደርጉ ጫት ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡

በዶውሪ ስርዓት ወቅት ግለሰቦች ተሰባስበው የግላቸውንም ሆነ በአገር ጉዳይ ላይ ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ ስርዓቱ ከሰዓት በኋላ ወደ 9 ሰዓት አካባቢ የሚጀመር ሲሆን፣ በአብዛኛው የሚጠናቀቀው ከንጋቱ 10 ሰዓት አካባቢ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰዓታት መካከል በእኩለ ሌሊት አካባቢ ያሉ ሰዓታት ልዩ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ በእነዚህ ሰዓታት የፈጣሪ በር ክፍት እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በእነዚህ ሰዓታት ወቅት የሚደረግ ጸሎት፣ ምርቃት ወይም እርግማን የፈጣሪን ፈጣን ምላሽ ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

በዶውሪ ስርዓት ወቅት በአብዛኛው የሚከወነው መንፈሳዊ ሙዚቃ አቶረራ ነው፡፡ የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ከሌሎች መንፈሳዊ ሙዚቃዎች የተለየ የሚያደርጉት ባህርያት አሉ፡፡ ከእነዚህም ባህርያት መካከል የመንፈሳዊ ሙዚቃው ግጥም ስንኞች በመጨረሻ ፊደላት የተለያዩ በመሆናቸው ግጥሙ ቤት አይመታም፡፡ የግጥሞቹ ይዘትም የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን የሚዳስስ ነው፡፡ ርዕሰጉዳዮቹም ስለፍቅር፣ ስለሀገር፣ ስለሂክማ፣ ስለሰው ልጅ ባህርይ፣ ስለፖለቲካ እንዲሁም ስለራሱ (አቶረራውን ስለሚከውነው ግለሰብ) ገጠመኝ የያዙ ናቸው፡፡ በአንድ

የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ውስጥ ከአዝማቹ በስተቀር ሌላው ግጥም አይደገምም፡፡ በአብዛኛው የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም አዝማች የሚከተለው ነው፡፡[160]

Abbaa kiyaahoo

Nalaalaa jaalalloo jaallattanii jedhaa

Baahira dheeraa kiyyaa baahira dheeraa.

ትርጉሙም፡-

አባቴ

ተወዳጃችን ይዩኝ፣ ወዳችኒላሁ በሉ

ሰፊው ባሕር የእኔ ሰፊ ባሕር

የሚል ነው፡፡ የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ የ"ዶሪያን ፔንታቶኒክ" ስኬልን መሠረት አድርጎ የሚጫወቱት ነው፡፡ የዚህ መንፈሳዊ ሙዚቃ ስኬል በኖታ ምልክት የሚከተለው ነው፡፡



የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ከሌላው የተለየ የሚያደርገው ሌላው ባህሪው ከዋኙ ሙዚቃውን ሲያቀርብ አድማጩ አብሮት አይልም፡፡ አዝማቹንም አይቀበለውም፡፡ አድማጩ የሚሳተፈው ክወናው ሲቀርብ "ይገርማል"፣ "አባቴ"፣ "እንዲህ ነው" አይነት የድጋፍና የስሜት መግለጫ ቃላት በመጠቀም እንዲሁም አንገታቸውን ከግራ ወደ ቀኝ በቀስታ በማወዛወዝ ነው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች ክወናውንም ከልባቸው እያዳመጡና የክወናው ንቁ ተሳታፊ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡

## 8.4 በከራ ጉዶ እና በቅጽር ግቢው ውስጥ የሚከወኑ ስርዓቶች

በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ የሼኽ ሁሴን ገሞ፣ የልጆቻቸው (የመሐመድ ተማምና የፋጡማ) ገሞዎች፣ የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ ገሞ፣ የሼኽ ዑመር ገሞ፣ የሀሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ፣ የአዮ ሀደ ገራዶ ጎምቢሶና የሼኽ ቡሽራ ጎምቢሶ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ኪነሕንጻዎች በተጨማሪ የመቃብር ስፍራ አለ፡፡ በዚህ ስፍራ የአናጂና ቀበሌ ነዋሪዎች፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ጉዞ ለማድረግ መጥተው ሕይወታቸው እዛው ያለፈ

---

[160] - በሙዳ በዓል ወቅት ከተሰበሰቡ የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥሞች የተወሰደ፡፡

እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች በስፍራው መንነው የሚኖሩ ሰዎች ከዚህ ምድር በሞት ሲለዩ የሚቀበሩበት ነው፡፡

የመቃብር ስፍራው በርካታ ቁጥር ያላቸው አስክሬኖች ያረፈበት ነው፡፡ አስክሬኖች ባረፉባቸው ቦታዎች ላይ ትልቅና ጠፍጣፋ ወጥ ድንጋይ በቀብሩ አናት ላይ ይተከላል፡፡ በስፍራው የተተከሉ የቀብር ምልክት ድንጋዮች (Megalithic) መካከል የተወሰኑት ረጅም እድሜ እንዳላቸው ያመላክታሉ፡፡



*ፎቶ፤35. በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኝ የመቃብር ስፍራ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ ውስጥ በሚገኝ የመቃብር ስፍራ ላይ ለመለያነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ምልክቶች አሉ፡፡ እነዚህም ምልክቶች በመቃብሩ ራስጌ ላይ ትልልቅና ወጥ የተፈለጡ ድንጋዮችን መትከል፣ ሀውልት መሰል የድንጋይ ካብ መቃብሩ ላይ መስራት፣ መቃብሩ ዙሪያውን በጠፍጣፋና በትልልቅ ወጥ ድንጋዮች ማጠር እንዲሁም የግራር ተክሎችን በመቃብሩ ግርጌ መትከል ናቸው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት በመካነ ቅርሱ በሚገኘውና በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ (ፎና) ዋና የመግቢያ በር ላይ እንዲሁም በቅጽር ግቢው ውስጥ በሚገኙ ስፍራዎች የተለያዩ ስርዓቶች ይከወናሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች የግቢውን ዋና የመግቢያ በርን (ከራ ጉዶን) የመሳለም፣ ገሞዎችን የመሳለም፣ ዘምዘም የመጠጣትና የመታጠብ ስርዓት፣ ጀዋራ የመቀባት ስርዓት እንዲሁም ስለት የመሳል ስርዓት ናቸው፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ያላቸውን ባህርይ በተናጠል ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## 8.4.1 የግቢውን ዋና የመግቢያ በር የመሳለም ስርዓት

መንፈሳዊ ተጓዥም ሆነ አካባቢውን ለመጎብኘት የሚመጣ ማንኛውም ግለሰብ በግንብ ወደ ታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ክልከላ የሚደረጉባቸው ሁኔታዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። እነዚህ ክልከላዎች ጫማ አድርጎ መግባት፣ የወር አበባ እያየች ያለች ሴት መግባት፣ ወደ መካነ ቅርሱ ከመምጣቱ ከሶስት ቀን ወዲህ ወሲብ ያደረገ ሰው መግባት፣ ሴቶች ሱሪ ለብሰው መግባት፣ ሴቶች ጸጉራቸውን ሳይሸፍኑ መግባት፣ ያልጠገገ ቁስል በአካሉ ላይ የሚገኝ እንዲሁም ቂም በቀል በልብ ይዞ መግባት በፍጹም ክልክል ነው። ለመንፈሳዊ ጉዞ የመጣ ማንኛውም ግለሰብ በግንብ ወደ ታጠረው ቅጽር ግቢ ለመግባት ክልከላ የተደረገባቸውን ጉዳዮች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ወደ ግቢው መግባት ይችላል።

ማንኛውም ግለሰብ ወደ ግቢው ከመግባቱ በፊት ጫማውን የማውለቅ ግዴታ አለበት። ወደ ግቢው ጫማ ተደርጎ የማይገባው ስፍራው የተቀደሰ በመሆኑ ለቦታው ክብር ለመስጠት ነው። ግለሰቡ ጫማውንም ካወለቀ በኋላ፣ የግቢውን ዋና መግቢያ በር (ከራ ጉዶ) ይሳለማል። የግቢውን ዋና በር በግራና በቀኝ የሚገኙ የበሩን ምሰሶዎች በመሳም፣ መሬት ላይ በመንበርከክ በግንባር መሬቱን በመንካትና በመሳም የመሳለም ስርዓት ይፈጽማል። መንፈሳዊ ተጓዦች የበሩን ምሰሶዎችና መሬቱን የሚሳለሙት ስፍራው የተቀደሰ በመሆኑ ከስፍራው በረከት ለማግኘት ነው።

መንፈሳዊ ተጓዦች በግምብ ወደታጠረው ግቢ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት የመሳለም ስርዓት ይፈጽማሉ። ከዚህ ስርዓት በኋላ ለስለት ወይም ለስጦታ በሚል ይዘው የሚመጡትን ሰንደልና ጧፍ በመግቢያው በር ላይ በመሰካት በክብሪት ለኩሰው ያቀጣጥሉታል። እጣን፣ ከርቤና ሉባንጃ ጊርጊራ ወይም ከሰል ማንደጃ ላይ በማድረግ ያጨሳሉ። አልፎ አልፎ ሽቶ የሚረጩም አሉ። ይህን የሚያደርጉትም ስፍራው የተቀደሰ በመሆኑ ልዩ መዐዛ በአካባቢው እንዲኖር ነው። ከዚህም ባለፈ ሰንደል፣ እጣን፣ ሽቶ ወይም ሌሎች ጥሩ መዐዛ ያላቸውን ነገሮች በአካባቢው ለሚገኝ ቅዱስ መንፈስ መስዋዕት ለማቅረብ ነው። መስዋዕቱም ለመንፈሶቹ የሚደርሰው በሽታ ነው። ሽታ የሰው ልጅ ከረቂቅ መንፈስ ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት አንዱ የመገናኛ ድልድይ ነው። ሰንደል፣ እጣን፣ ሽቶና መሰል ቁሶችን በቤተ አምልኮዎችና አካባቢያቸው ማጨስ በክርስትና፣ በእስልምና እንዲሁም በሌሎች ኃይማኖቶችና እምነቶች ስርዓተ አምልኮ ውስጥ የተለመደ ነው።

በስፍራው የሚመጡ አንዳንድ መንፈሳዊ ተጓዦች የመግቢያ በሩን የግራና ቀኝ ምሰሶዎች ቅቤ ይቀባሉ፡፡ ብዙም የተለመደ ባይሆንም አልፎ አልፎ ደግሞ በሩን ደም ይቀቡታል፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚኖሩ የበዓሉ አስተባባሪዎች በሩን ቅቤና ደም የመቀባት ስርዓት አግባብ እንዳልሆነ በመግለጽ ስርዓቱ እንዳይካሄድ ይከለክላሉ፡፡ አስተባባሪዎቹ ድርጊቱን የሚከለክሉት የበሩን ውበት እያበላሸ ነው፣ ሰዎች በሩን ሲሳለሙ ቅቤውና ደሙ ሰውነታቸውን ያበላሻቸዋል እንዲሁም ይህን ድርጊት መፈጸም የ"ባዕድ አምልኮ" ተምሳሌት በመሆኑ ክልክል እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡[161]

ይህን ድርጊት የበዓሉ አስተባባሪዎችና አንዳንድ የበዓሉ ተሳታፊዎች "ፉቅራ" እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ፉቅራ ማለት ሀይማኖቱ የማይፈቅደውን ድርጊት መፈጸም ነው፡፡ ነገር ግን ግለሰቦች በራሳቸው ፍላጎት፣ በረከት ለማግኘት በሚል በሩን ቅቤ የመቀባት ድርጊት በየጊዜው ሲፈጽሙ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ደም የመቀባት ስርዓት ይፈጽማሉ፡፡ የማምለኪያ ስፍራዎችን ደምና ቅቤ የመቀባት መንፈሳዊ የመስዋዕት ስርዓት በዋቄፈና ኃይማኖት የተለመደ ነው፡፡

## 8.4.2 ገሞዎችን የመሳለም ስርዓት

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ 10 ገሞዎች አሉ፡፡ እነዚህ ገሞዎች በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥና ከቅጽር ግቢው ውጪ የሚገኙ ናቸው፡፡ ከቅጽር ግቢ ውጪ 5 ገሞዎች የሚገኙ ሲሆን ገሞዎቹም የሼኽ ኢብራሂም መልካይ፣ የአዮ ማኪዳ፣ የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ፣ የሼኽ መሃመድ ሚስኪና የሼኽ መሃመድ ሀጂ አህመድ ናቸው፡፡ በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ ደግሞ 5 ገሞዎች ይገኛሉ፡፡ በቅጽር ግቢው መሃል ላይ እራሱን የቻለና ዙሪያው በግንብ የታጠረ ግቢ ይገኛል፡፡ በዚህ ተጨማሪ የግንብ ቅጽር ውስጥ 3 ገሞዎች ይገኛል፡፡ ገሞዎቹም የሼኽ ሁሴንና የልጆቻቸው (የመሐመድ ተማምና የፋጡማ) ናቸው፡፡ ግቢው መሃል ላይ ከሚገኘው ተጨማሪ ቅጽር ግቢ ውጪ የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒና የሼኽ ዑመር ገሞዎች ይገኛሉ፡፡

[161] - ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 9 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡



*ፎቶ፣ 36፣ ዙሪያው በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኘውና በውስጡ የሼኽ ሁሴንና የልጆቻቸው (የመሐመድ ተማምና የፋጡማ) ገሞዎች የሚገኙበት ቅጽር ግቢ ውጫዊ ገጽታ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

መንፈሳዊ ተጓዦች ከእነዚህን ገሞዎች መካከል የተወሰኑትን ይሳለማሉ። ከቅጽር ግቢ ውጪ ከሚገኙ ገሞዎች መካከል የሼኽ ኢብራሂም መልካይንና የአዮ ማኪዳን ገሞዎች ይሳለማሉ። በቅጽር ግቢ ውስጥ ከሚገኙ ገሞዎች መካከል መንፈሳዊ ተጓዦች የሚሳለሚቸው የሼኽ ሁሴንን ገሞና የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒን ገሞ ነው። በቅጽር ግቢ ውስጥ ከሚገኙና መንፈሳዊ ተጓዦች ከሚሳለሚቸው 2 ገሞዎች መካከል መንፈሳዊ ተጓዦች በመጀመሪያ የሚሳለሙት የሼኽ ሁሴንን ገሞ ነው። የሼኽ ሀሴን ገሞ የ383 አመት እድሜ እንዳለው ይነገራል። ይህ ገሞ የኪነ-ህንጻ ዲዛይኑና ትልቀቱ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ገሞዎች የተለየ ያደርገዋል። ገሞው 45 ሜትር ርዝመት፣ 35 ሜትር ስፋትና 3 ሜትር ከፍታ አለው።

ገሞው ውስጡ ክፍት ሲሆን፣ 7 ወፋፍራም ምሰሶዎች አሉት። ይህ ገሞ ‹ከራ ሀሮ ሉኩ› እና ‹ከራ ጀጀባ› በሚል ስያሜ የሚጠሩ 2 መግቢያ በሮች አሉት። የገሞው መግቢያ በር አናት ላይ መስኮት መሰል ቀዳዳ አለ። በዚህ ቀዳዳ ውስጥ አነስተኛ መጠን ያለው ክብ ድንጋይ ይገኛል። ሰዎች ወደ ገሞው ከመግባታቸው በፊትም በቀዳዳ ውስጥ እጃቸውን በማሾለክ፣ በውስጡ በሚገኝ ክብ ድንጋይ ድምጹን ከፍ በማድረግ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ያንኳኳሉ። ይህ ክብ ድንጋይ ከሳዑዲ አረቢያ መካ የመጣ እንደሆነ ይነገራል።[162]

---

[162] - ሼኽ አህመድ ሐጂ ሙሐሙድ፣ አናጂና ሚያዝያ 29 ቀን፣ 2008 ዓ.ም።



*ፎቶ፣ 37፣ በሼኽ ሁሴን ገሞ መግቢያ በር አናት ላይ የሚገኝ የክብ ድንጋይ ማስቀመጫ መስኮት መሰል ቀዳዳ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

ወደ ገሞው ውስጥ ከመግባቱ በፊት ድንጋይ የሚንኳኳበት ምክንያት በገሞው ውስጥ እንደሚኖር ለሚያምኑት የሼኽ ሁሴን መንፈስ መምጣታቸውን ለመግለጽ፣ ድንጋዩ ከመካ የመጣ እንደሆነ የሚታመን በመሆኑ፣ ድንጋዩን መንካት ሳዑዲ አረቢያ መካ ለሐጂ መንፈሳዊ ጉዞ ከመሄድ እኩል እንደሆነ ስለሚታመን፣ መካ እንደሄዱ እንዲሰማቸው፣ በገሞው ውስጥ ሰው ካለም ሰው መምጣቱን ለማሳወቅ እንዲሁም ገሞው ውስጥ ሴቶች ካሉ ሰው መምጣቱን አውቀው ጸጉራቸውን እንዲሸፍኑ ለማሳወቅ በሚል ነው።



*ፎቶ፣38፣ በሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ ሲጸለይ የሚያሳይ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

መንፈሳዊ ተጓዦች ድንጋይ አንኳክተው ወደ ጎሞው ከገቡ በኋላ በውስጥ ሰንደልና እጣን ያጨሳሉ። በውስጡም አለ ተብሎ በሚታመነው በሼኽ ሁሴን መካነ መቃብርን፣ በውስጡ የሚገኙ ምሰሶዎችንና የውስጥ ግድግዳውን ይሳለማሉ። በገሞው ውስጥም ይጸልያሉ። በገሞው ውስጥ መሃል ላይ የሼኽ ሁሴን መካነ መቃብር እንደሆነ የሚታመን ስፍራ አለ። ስፍራው ከመሬት በግምት 1 ሜትር ከፍታ ያለው ግንባታ አርፎበታል። መንፈሳዊ ተጓዦቹም የሼኽ ሁሴንን መካነ መቃብር ከቀኝ ወደ ግራ በመዞር ሼኽ ሁሴንን ይዘይራሉ። መንፈሳዊ ተጓዦች ሼኽ ሁሴንን ዘይረው ሲጨርሱ ከገሞው ይወጣሉ። ከገሞው ወደ ውጪ ሲወጡም የራሱ የሆነ የአወጣጥ ስርዓት አለው። ይህም ፊታቸውን ወደ ገሞው ውስጥ በማዞርና ጀርባቸውን ወደ መውጫው በር በማዞር ወደ ኋላ ይወጣል። ከገሞው በጀርባ ተዙሮ ወደ ኋላ የሚወጣበት ምክንያት ለሼኽ ሁሴን ጀርባ መስጠት አይገባም ከሚል አክብሮታዊ አመለካከት ነው።



*ፎቶ፣ 39፣ መንፈሳዊ ተጓዦች የአዮ ሸምሲያ (የሼኽ ሁሴን እናት) ገሞን ተሳልመው፣ ከውስጥ ወደ ውጭ ወደ ኋላ ሲወጡ የሚያሳይ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

መንፈሳዊ ተጓዦች የሼኽ ሁሴን ገሞን ከዘየሩ በኋላ በመቀጥል የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒን ገሞ ይዘይራሉ። የሼኽ አብዱልቃድር ገሞ ውስጡ ክፍት ሲሆን፣ አንድ የመግቢያ በር አለው። ሰዎች በገሞው ውስጥም በመግባት ጸሎት ያደርሳሉ፣ የሼኽ አብዱልቃድር ከረማ እንዲላመናቸው ይጠይቃሉ። በቅጽር ግቢ ውስጥ ያሉትን ገሞዎች ዘይረው ከጨረሱ በኋላ ከቅጽር ግቢ ውጪ የሚገኙትን የሼኽ ኢብራሂም መልካይንና የአዮ ሸምሲያን ገሞዎች ይሳለማሉ። እነዚህ ሁለት ገሞዎች ውስጣቸው ክፍት ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው አንድ የመግቢያ በር አላቸው።

## 8.4.3 ዘምዘም የመጠጣትና ሰውነትን የማሻሸት ስርዓት

በመካነ ቅርሱ 9 የውኃ ኩሬዎች ይገኛሉ። በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ ደግሞ 1 የውኃ ኩሬ አለ። ከእነዚህ የውኃ ኩሬዎች መካከል ለጸበልነት ብቻ የሚያገለግለው የሀሮ ሉኩ የውኃ ኩሬ ነው። ሌሎቹ የውኃ ኩሬዎች ለመጠጥ፣ ለንጽሕና መጠበቂያ፣ ለምግብ ዝግጅትና ለእንስሳት መጠጥ ያገለግላሉ። ሁሉም የውኃ ኩሬዎች በአመት ውስጥ በአካባቢው ዝናብ በሚጥልባቸው ጥቂት ወራት አማካኝነት ውኃ ይጠራቀምባቸዋል።

የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎችም ሆኑ ለበዓል ወደ ስፍራው የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች ከእነዚህ ኩሬዎች ለመጠጥ፣ ለንጽሕና፣ ለምግብ ዝግጅትና ለተለያዩ ጉዳዮች ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ለመጠጥና ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉት የውኃ ኩሬዎች ንጽህናቸውን ያልጠበቁና ለብልሽት የተዳረጉ በመሆናቸው የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎችና መንፈሳዊ ተጓዦች ለተለያዩ ውኃ ወለድ በሽታዎች ይዳረጋሉ፡፡ ይህንንም ችግር በጊዜያዊነት ለመቅረፍ በሙዳ በዓላት ወቅት የኩሬውን ውኃ ሲጠቀሙ የውኃ አጋር (የውኃ ማከሚያ ኬሚካል) እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡

ለጸበልነት የሚያገለግለው የውኃ ኩሬ ሀሮ ሉኩ ሲሆን፣ በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ ጸበል "ዘምዘም" ተብሎ ይጠራል፡፡ የሀሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ በግምት ከ5 እስከ 8 ሜትር ጥልቀትና 20 ሜትር በ20 ሜትር ስፋት አለው፡፡ ይህን ኩሬ ያስገነቡት ሼኽ ሁሴን እራሳቸው እንደሆኑ ይነገራል፡፡ የሀሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ በዝናብ ወቅት ከሚጠራቀመው የዝናብ ውኃ የሚያገኝ ነው፡፡ ኩሬው በ 9 አመት አንዴ መጠኑ እጅግ አነስተኛ እንደሚሆን ይነገራል፡፡ ይህም እንዲሆን የሼኽ ሁሴን ቃል ኪዳን እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመጀመሪያ ዙር የመስክ ቆይታዬ ወቅት (ከጥቅምት 28 እስከ ህዳር 2 ቀን 2007 ዓ.ም) የሀሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ ሙሉ ለሙሉ ደርቋል ሊባል በሚያስብል ደረጃ መጠኑ ቀንሶ ነበር፡፡

የኩሬው የውኃ መጠን የቀነሰበት ወቅት ከሙዳ በዓል ውጪ በመሆኑ እንዲሁም ልክ 9 አመቱ ላይ ስለነበር አጋጣሚው እምብዛም ስጋት የፈጠረ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ለመጠጥነት የሚያገለግሉ ሌሎች የውኃ ኩሬዎችም መጠናቸው በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰበት ወቅት በመሆኑ በነዋሪው ዘንድ ከፍተኛ ስጋት ተፈጥሮ ነበር፡፡ ከዚህ ችግርም እንዲወጡ የጸሎትና የምህላ ቀጠሮ ከ15 ቀን በኋላ እንደተያዘ መረጃ ሰጪዎቼ በወቅቱ ገልጸውልኝ ነበር፡፡ ከጸሎቱና ከምህላው በኋላ በአካባቢው በአንድ ቀን ለተከታታይ ሰዓታት በጣለው ከፍተኛ ዝናብ ምክንያት የውኃ ኩሬዎቹ እንደሞሉ መረጃ ሰጪዎቼ በስልክ ገልጸውልኛል፡፡



*ፎቶ፣40፣ የሆሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ መጠኑ በ 9 አመት አንዴ በሚቀንስበት ወቅት፡፡*
*(ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ሲመጡ ዘምዘም ይጠቀማሉ፡፡ ዘምዘም የሰው ልጅን፣ እንሰሳትንና እጽዋትን ከተለያዩ በሽታዎች ይፈውሳል፣ ከመኖሪያ ቤትና ከአካባቢው ክፉ መናፍስትን ያርቃል፣ በኑሮ ላይ ረድዔትና በረከት ያጎናጽፋል፣ ሕይወትን ስኬታማ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ወደ ስፍራው የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በውኃ መያዣ ጀሪካኖችና የፕላስቲክ ዕቃዎች ዘምዘም በመቅዳት ወደ መኖሪያ ቤታቸው ይወስዳሉ፡፡ ዘምዘሙን በዕቃ ወደ መኖሪያ ቤት ከመውሰድ በተጨማሪ በስፍራው ዘምዘሙን ይጠጣሉ፤ ሰውነታቸውንም ያሻሻሉ፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች ዘምዘም በሁለት መንገድ ይጠቀማሉ፡፡ እነሱም፣ አንደኛው ግለሰቦቹ ራሳቸው ዘምዘሙን መጠጣትና ሰውነትን ማሻሸት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በሌላ ሰው አማካኝነት ዘምዘም መጠጣትና ሰውነትን ማሳሸት ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ቀደም ሲል የመጡና እንግዳ ካልሆኑ ብቻቸውን ሄደው ዘምዘም ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ለስፍራው እንግዳ ከሆኑ፣ በእንግድነት በመኖሪያ ቤቱ የተቀበላቸው የቤቱ አባወራ ወይም እማወራ ይዘዋቸው ወደ ኩሬው ይሄዳሉ፡፡ እንግዳው ወንድ ከሆነ የቤቱ አባወራ ይዘው ሲሄዱ፣ እንግዳዋ ሴት ከሆነች ደግሞ የቤቱ እማወራ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ የቤቱ አባወራ ወይም እማወራ እንግዶቹን ወደ ጸበሉ ይዘው ከሄዱ በኋላ በእጃቸው መዳፍ ጸበሉን በመጨለፍ መጀመሪያ እራሳቸው ይጠጣሉ፡፡ ቀጥሎ በእጃቸው በመጨለፍ እንግዳው ከእጃቸው ላይ

ይጠባል፡፡ በእጅ በመጨለፍ የማጠጣት ሂደት ለሶስት ጊዜ ያህል ይደጋገማል፡፡ ቀጥሎ ጸበሉን በእጅ በመጨለፍ የእንግዳውን ግንባር፣ ማጅራት፣ አንገትና ደረትን ይቀባሉ፡፡



*ፎቶ፣ 41፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ከሀሮ ሉኩ ኩሬ ዘምዘም ሲቀዱ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

የሀሮ ሉኩ የውኃ ኩሬ ከሌሎች የአካባቢው ኩሬዎች በተለየ የፈዋሽነት ኃይል ያለው ዘምዘም ተደርጎ የተወሰደበት አራት ምክንያቶች እንዳሉ መረጃ ሰጪዎቼ በቡድን ውይይት ወቅት ገልጸውልኛል፡፡[163] እነዚህም ምክንያቶች አንደኛው፣ ሼኽ ሁሴን ይህ ውኃ መፈወሻ ይሁንላችሁ ብለው ስለመረቁት እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን የውኃ ኩሬውን በመንፈሳቸው ቀድሰውና ባርከው ለሰው ልጅ፣ ለእንስሳትና ለእጽዋት ለተለያዩ በሽታዎች ፈውስ እንዲሁም የክፉ መናፍስት ማባረሪያ ይሆን ዘንድ የመረጡት ነው፡፡ በመሆኑም ኩሬው የተቀደሰ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ሁለተኛው፣ የአካባቢው ነዋሪዎችና በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ግለሰቦች የኢድ በዓልን ለማክበር ወደ ሳዑዲ አረቢያ ሐጅ ያካሂዳሉ፡፡ ሐጅ ሄደው ሲመለሱም በመካ ከሚገኘው የዘምዘም ኩሬ በዕቃ የተወሰነ ዘምዘም ይዘው በመምጣት በሀሮ ሉኩ የውኃ ኩሬ ውስጥ ስለሚጨምሩ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ሶስተኛው፣ የአገልግሎት ጊዚያቸውን የጨረሱና ያረጁ ቅዱስ ቁርዓኖች በኩሬው ውስጥ ስለሚጣሉ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም ቅዱስ ቁርዓን

[163] - ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7 ቀን፣ 2007 ዓ.ም፡፡

የተቀደሰና የፈጣሪ ቃል የያዘ በመሆኑ፣ መጻሕፉን በኩሬ ውስጥ መጨመር የኩሬውን ውኃ ወደ ቅዱስነት ይቀይረዋል ከሚል እምነት ነው፡፡

አራተኛው፣ በሼኽ ሁሴን ስለት የተወለደ ልጅ የመጀመሪያውን ጸጉር ሲላጭ፣ ጸጉሩ በኩሬው ውስጥ ስለሚጨመር እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ግለሰቦች በተለያዩ ምክንያቶች ልጅ መውለድ ሳይችሉ ሲቀሩ ወይም የመጀመሪያ ልጃቸው እንዲሆንላቸው የሚፈልጉትን ጾታ (ወንድ ወይም ሴት ልጅ) እንዲያገኙ ለሼኽ ሁሴን ይሳላሉ፡፡ በስለት የተወለዱት ልጆች ጸጉራቸውን እስከ 7 ዓመት እድሜያቸው ድረስ አይላጩም፡፡ ልጆቹ እስከ 7 ዓመታቸው ድረስ ጸጉራቸው ጉድሮ (‘ድሬድ’) ይሆናል፡፡ ልጆቹ 7 ዓመት ሲሆናቸው ቤተሰቦቻቸው ቀደም ብለው ስለት በገቡት መሰረት ጸጉራቸው ይላጫል፡፡ ቤተሰቦቹ ስለት በገቡበት መሰረት ሲባል ቀደም ሲል ልጅ ለመውለድ ሲሳሉ ጸጉሩን በ7 ዓመቱ በመካነ ቅርሱ አስላጫለሁ ወይም ባለበት ቦታ አስላጫለሁ ብለው ስለት ይገባሉ፡፡

ልጆቹ በመካነ ቅርሱ መጥተው ጸጉራቸውን የሚላጩ ከሆነ፣ ጸጉራቸውን የሚላጨው ቤተሰቦቻቸው የሚያርፉበት ቤት ባለቤት ነው፡፡ ልጁ ወንድ ከሆነ የቤቱ አባወራ ሲላጫቸው፣ ሴት ከሆነች ደግሞ የቤቱ እማወራ ትላጫታለች፡፡ በስለታቸው መሰረትም ልጅ ከወለዱ በኋላ የልጆቹ የመጀመሪያ ጸጉር ከተላጨ በኋላ ተሰብስቦ በሀሮ ሉኩ ኩሬ ውስጥ ይጨመራል፡፡ በልጆቹ ጸጉር አማካኝነት የኩሬው ውኃ ወደ ቅዱስነት ይቀየራል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 8.4.4 ጀዋራ የመቀባት ስርዓት

የሙዳ በዓል ሲቃረብ የጀዋራ አፈር ተቆፍሮ በገሞዎች ውስጥ ይቀመጣል፡፡ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ ገሞዎች መካከል የጀዋራ አፈር የሚበተነው በሼኽ ሁሴንና በሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ ገሞዎች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ አማኞቹ የጀዋራ አፈርን በተለያዩ መንገዶች ይጠቀሙበታል፡፡ አንደኛው፣ ሰውነትን መቀባት ነው፡፡ ሰዎች የተለያየ የሰውነት ክፍላቸው ላይ ሕመም ሲያጋጥማቸው የታመመውን አካል በጀዋራ አፈር ይቀቡታል፡፡ ሁለተኛው፡- የጀዋራ አፈርን መብላት ነው፡፡ ሰዎች ከሕመም ለመፈወስ ወይም በረከትን ለማግኘት የጀዋራ አፈርን ይበላሉ፡፡ አፈሩም የተቀደሰ በመሆኑ ከችግር ያድነናል፣ በረከትም እናገኛለን ብለው ያምናሉ፡፡

ሶስተኛው፣ የጀዋራን አፈር በዘምዘም ጸበል በመበጥበጥ መጠጣት ወይም መታጠብ ነው፡፡ ጀዋራን በዘምዘም በጥብጠው የሚጠጡትም ከውስጥ ደዌ (ሕመሞች) ለመፈወስ ሲሆን የሚታጠቡትም በሰውነት አካል ላይ ከተከሰተ ሕመም ለመዳን ነው፡፡ አራተኛው፣ የጀዋራ

አፈርን ወደ መኖሪያ ቤት በመውሰድ ምቹ ቦታ ማስቀመጥ ነው፡፡ የጀዋራ አፈር መኖሪያ ቤት ውስጥ ከተቀመጠ ክፉ መናፍስት ከአካባቢው ይርቃሉ፣ በቤቱ ውስጥ ሰላም፣ ጤናና በረከት ይኖራል ተብሎ ይታመናል፡፡

አምስተኛው፣ የጀዋራን አፈር በዘምዘም ጸበል በመበጥበጥ መኖሪያ ቤትን፣ ግቢውን፣ የእንስሳት ማደሪያን፣ እንስሳትን፣ የእህል ጎተራን፣ የምግብ ማብሰያ እቃዎችን፣ የእህል አዝመራን መርጨት ነው፡፡ ይህም በመኖሪያ ቤትና አካባቢው ክፉ መናፍስት እንዳይቀርቡ ያደርጋል በሚል እምነት ነው፡፡ እህል በረከት እንዲኖረውና ከሰላቢ መንፈስ ለመከላከል በሚል የምግብ ማብሰያ እቃዎች ላይ ይረጫል፡፡ የእህል አዝመራ ፍሬ እንዲያፈራ፣ ጥሩ ምርት እንዲያስገኝ፣ የተለያዩ ነፍሳት እንዳያበላሹት፣ ከቡዳ (ክፉ ዐይን) ለመከላከል በአዝመራው ላይ ይረጫል፡፡ ከማሳ የተሰበሰበውም እህል በረከት እንዲኖረው፣ ከተባይና ከሌሎች አደጋዎች ለመከላከል በእህል ጎተራ ውስጥ ይረጫል፡፡ እንስሳት ጤነኛ እንዲሆኑ፣ እንዲረቡ፣ ከቡዳ ዐይን እንዲጠበቁ በእንስሳቱ አካል ላይና በማደሪያቸው ውስጥ ይረጫል፡፡



*ፎቶ፣ 42፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ሰውነታቸውን ጀዋራ (ቅዱስ አፈር) ተቀብተው፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

መንፈሳዊ ተጓዦች የጀዋራ ቅዱስ አፈርን በሁለት መንገድ ይጠቀማሉ፡፡ እነሱም፣ አንደኛው፣ ግለሰቦቹ ራሳቸው ጀዋራውን መብላት፣ በዘምዘም በጥብጦ መጠጣትና ሰውነትን መቀባት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በሌላ ሰው አካማኝነት ጀዋራን መብላትና ሰውነትን መቀባት ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ቀደም ሲል የመጡና እንግዳ ካልሆኑ ብቻቸውን ሄደው

የጀዋራ አፈርን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ለስፍራው እንግዳ ከሆኑ፣ በእንግድነት በመኖሪያ ቤቱ የተቀበሏቸው የቤቱ አባወራ ወይም እማወራ ይዘዋቸው ወደ ገሞዎቹ ይሄዳሉ፡፡ እንግዳው ወንድ ከሆነ የቤቱ አባወራ ይዘው ሲሄዱ፣ እንግዳዋ ሴት ከሆነች ደግሞ የቤቱ እማ ወራ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ የቤቱ አባወራ ወይም እማወራ እንግዶቹን ወደ ገሞዎቹ ይዘው ከሄዱ በኋላ በእጃቸው መዳፍ ላይ ጀዋራውን በማድረግ መጀመሪያ እራሳቸው በምላሳቸው ይልሱታል፡፡ ቀጥሎ በእጃቸው መዳፍ ላይ በማድረግ እንግዳው ከእጃቸው ላይ በምላሱ እንዲልስ ያደርጋሉ፡፡ ቀጥሎ ጀዋራውን በእጅ ላይ በማድረግ የእንግዳውን ግንባር፣ ማጅራት፣ አንገትና ደረትን ይቀባሉ፡፡

## 8.4.5 ስለት የመሳል ስርዓት

ግለሰቦች በሕይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸው በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ ችግሮች መካከል የጤና እክል፣ የሀብት እጦት፣ የደስታ እጦት፣ የልጅ እጦት፣ የበረከት እጦት፣ የማህበራዊ ግንኙነት ችግር የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ግለሰቦቹ በሕይወታቸው ከሚያጋጥሟቸው መሰል ችግሮች ለመዳን ወይም ወደ ፊት በሕይወታቸው ውስጥ ማሳካትና ማግኘት የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት በሼኽ ሁሴን ስም ስለት ይሳላሉ፡፡ ግለሰቦቹም ከደረሰባቸው ችግር ለመዳን ወይም የሚፈልጉትን ለማግኘት ሼኽ ሁሴንን ይለምናሉ፡፡ የለመኑት ነገር እንዲሳካላቸውም ስለት ይገባሉ፡፡

አማኞች በሼኽ ሁሴን ስም በተለያዩ መንገዶች ስለት ይገባሉ፡፡ እነዚህም መንገዶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው፣ አማኙ በሚኖርበት ስፍራ ሆኖ ስለት ሊገባ ይችላል፡፡ ሁለተኛው ድግሞ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ተገኝቶ ስለት ሊገባ ይችላል፡፡ አንድ አማኝ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ተገኝቶ ስለት ሲገባ የተለያዩ ስርዓተክዋኔዎችን ይከውናል፡፡ ክወናዎቹም አማኙ ስለት የሚገባበት ጉዳይና ግለሰቡ ከዚህ በፊት ወደ ቦታው የመምጣት ልምድ ጋር የተገናኘ ነው፡፡

ግለሰቡ በመካነ ቅርሱ የመጣው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ያረፈበት ቤት ባለቤት ጋር በመሆን ወደ ሼኽ ሁሴን ገሞ በመሄድ ስለት ይገባል፡፡ ግለሰቡ የሚያሳስበው ወይም የሚፈልገውን ጉዳይ ለቤቱ ባለቤት በመንገር ስለት ይገባል፡፡ የቤቱ ባለቤትም የግለሰቡ ስለት እንዲሰምር ጸሎት ያደርግለታል፡፡ ግለሰቡ ከዚህ በፊት ወደ ስፍራው የመጣ ከሆነ ብቻውን ወደ ሼኽ ሁሴን ገሞ በመሄድ ስለቱን ሊሳል ይችላል፡፡ የስለት የመሳል ስርዓት ግለሰቡ እንደሚሳለው ጉዳይ

ይለያያል። የግለሰቡ ችግር፤ የጤና፣ የሀብት፣ የበረከት፣ የሰላም፣ የደስታ የመሳሰሉት ከሆነ በአብዛኛው በሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ ገብቶ የሼኽ ሁሴንን ከዘየረ በኋላ የእሳቸው የመቃብር ስፍራ እንደሆነ በሚታመነውና ቁመቱ በግምት 1 ሜትር ከፍታ ባለው 4 ማዕዘን የግንብ ግንባታ ላይ እጁን አሳርፎና ግንባሩን በግንቡ ላይ ደፍቶ የሚፈልገውን ነገር ይጠይቃል፤ ስለት ይሳላል።

የግለሰቡ ችግር፣ የልጅ እጦት ችግር ከሆነ የተለየ ስለት የመሳል ስርዓት አለ። ይኸውም በተለያዩ ምክንያቶች ልጅ መውለድ ያልቻሉ ግለሰቦች፣ ልጅ ለመውለድ አለመቻላቸውንና ስለት እንደሚገቡ ለሚያርፉበት ቤት ባለቤት፣ በከራ ወይም በድንኩሬ ዋሬ ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይናገራሉ። ግለሰቡ ለቤቱ ባለቤት የተናገረ ከሆነ ከቤቱ ባለቤት ጋር በመሆን ወደ ሼኽ ሁሴን ገሞ ሄዶ ይመረቃል። በዚህ ወቅት ግለሰቦቹን የሚመርቀው የቤቱ ባለቤት ነው። ግለሰቡ ሕዝብ ፊት በከራ ወይም በድንኩሬ ዋሬ ላይ የተናገረ ከሆነ፣ በስፍራው ፕሮግራሙን የሚመሩ ግለሰቦች ጋር በመሆን በሼኽ ሁሴን ገሞ በመሄድ ይመረቃል። በዚህ ወቅት ግለሰቦቹን የሚመርቀው የስፍራው ፕሮግራም አስተባባሪ ግለሰብ ነው።

ግለሰቦቹ ከቤቱ ባለቤት ወይም ከፕሮግራም መሪ ጋር በመሆን ወደ ሼኽ ሁሴን ገሞ ይሄዳሉ። በቤቱ ባለቤት ወይም በዋሬ ስርዓት ፕሮግራም መሪ ግለሰቡ ይመረቃል። የምርቃቱ ሂደትም ግለሰቡ በሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ ገብቶ መሬት እግሩን ዘርግቶ/ እግሯን ዘርግታ እንዲቀመጥ/ እንድትቀመጥ ይደረጋል። የቤቱ ባለቤት ወይም የፕሮግራሙ መሪ ከሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ ከተበተነው የጀዋራ አፈር የተወሰነ በእጁ በማንሳት የግለሰቡን ፊት፣ አንገት፣ ትከሻ፣ ደረት፣ ሆድና ጭን ይቀባል። ግለሰቡ መሬት በእጅና በእግሩ ጉልበት እንዲንበረከክ ይደረጋል። መራቂውም የግለሰቡን ጀርባ፣ ጭን፣ ሆድና ደረት ጠንከር አድርጎ እያሸ ጸሎት ያደርግለታል። በዚህ መንገድ የተመረቀ ግለሰብ በአመቱ ልጅ እንደሚወልድ ሙሉ ለሙሉ ይታመናል። በስለት የተወለደ ልጅም ለ7 ዓመት ያህል ጸጉሩን አይላጭም። 7 ዓመት ሲሞላው ጸጉሩ ተላጭቶ በሆሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ ውስጥ ይጨመራል።

በስለት የተወለዱ ልጆች ጸጉራቸውን ለ7 ዓመት ጉድሮ የሚያደርጉበት ምክንያት ሼኽ ሁሴን ጸጉራቸውን የተላጩት በ7 ዓመታቸው ስለሆነ ነው። ሼኽ ሁሴን 7 ዓመት ሲሆናቸው ጸጉራቸውን የላጨው አበልቃሲም እንደሆኑ ይታመናል። በእለቱም አበልቃሲም ጸጉራቸውን ሊላጭ ሲመጣ በአካባቢው ውኃ አልነበረም። አበልቃሲምም በያዙት በትር መሬቱን ወግተው ውኃ አፈለቁ፣ ባፈለቁትም ውኃ የሼኽ ሁሴንን ጸጉር ላጩ። ሼኽ ሁሴን ለመጀመሪያ ጊዜ

ጸጉራቸውን የተላጩበት ስፍራ "ጀበል አባስ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ስፍራው በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ አጠገብ የሚገኝ ነው፡፡

አንድ ህጻን ከተወለደ በኋላ መጀመሪያ ያደገን ጸጉር መላጨት በተለያዩ ማህበረሰቦች ልዩ ትርጓሜ ይሰጠዋል፡፡ በልጁ የሕይወት ዑደት (Rite of passage) ውስጥ የተለየ ስፍራ አለው፡፡ ማህበረሰቡ እንደ ባህሉ የህጻኑ የመጀመሪያ ጸጉር ከተላጨ በኋላ በመኖሪያ ቤት ውስጥ፣ በመኖሪያ ቤት ደጃፍ ወይም በእርሻ ማሳ ውስጥ ጉድጓድ ተቆፍሮ ጸጉሩ ይቀበራል፡፡ ወይም በጨርቅ ተጠቅልሎ በመኖሪያ አካባቢ ባለ ትልቅ ዛፍ ላይ ይታሰራል፡፡ ይህ የሚደረገውም የህጻኑ የወደ ፊት ሕይወቱ የስኬት እንዲሆን፣ ጤነኛ እንዲሆንና እድሜውም እንዲረዝም በሚል ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም በስለት የተወለደ ልጅም 7 ዓመት ሲሞላው ጸጉሩ ተላጭቶ በሀሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ ውስጥ የሚጨመረው በልጁ ጸጉር ላይ ቅዱስ መንፈስ ያርፍበታል፣ ጸጉሩም የተቀደሰ ነው ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ በሀሮ ሉኩ ውስጥ ሲጨመርም፣ ውኃውን ወደ ቅዱስነት ይቀይረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ 7 ቁጥር የምሉዕነት፣ የማጠናቀቅ፣ በመንፈስ ብቁና ሙሉ የመሆን ተምሳሌት ነው፡፡ በሼኽ ሁሴን ስም በስለት የተወለዱ ልጆችም በመንፈስ ብቁና ምሉዕ የሚሆኑት በ7 ዓመታቸው ነው፡፡

## 8.5 በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ ስርዓቶች

የአይናገኜ ገደል ከዋናው የግምብ አጥር በግምት 3 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የአይናገኜ ገደል ሼኽ ሁሴን ለ40 ዓመታት ጸሎት ያደረጉበት ስፍራ ነው፡፡ ገደሉ በመካነ ቅርሱ ሜዳማ ስፍራና በቀጨምሰሬ ተራራ መሃል ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በገደሉ ውስጥ የአይናገኜ ወንዝ ይገኛል፡፡ ሼኽ ሁሴን በዚህ ገደል ውስጥ ከሰው ተሰውረው በዱር ቅጠሎችን እየተመገቡና ጨው በውኃ በጥብጠው እየጠጡ በጸሎት ኖረዋል፡፡

ገደል ወይም ሸለቆ በአረብኛው "ካውታሃር" ከሚለው ቃል ትርጓሜ ጋር ይቀራረባል፡፡ ገደል የገነት ወንዝ ተምሳሌት ነው፡፡ ገደል የዳግም ሕይወት (ምጽዓት) ቀን ውክልና ነው፡፡ እንደ Smith and Haddad (1981፣80) አገላለጽ በነባር የእስልምና ባህል እሳቤ ገደል ገነት ከመግባት በፊት እራስን የማጽጃ፣ የመቀደሻና ንስኃ የመቀበያ ስፍራ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሼኽ ሁሴንም በምድራዊ ሕይወታቸው ፍጻሜ አካባቢ ለ40 ዓመታት ያህል በአይናገኜ ገደል ውስጥ የኖሩት ወደ ገነት ከመሄዳቸው በፊት እራሳቸውን ለማጽዳት፣ ለመቀደስና ንስኃን ለመቀበል ነው፡፡

በአይናገኜ ገደል ርዝመቱ በትክክል የማይታወቅ ዋሻ፣ የኃጽያት ማረጋገጫ መስኮት መሰል ሁሉቃዎች (መሹለኪያዎች)፣ ሼኽ ሁሴን ይሰግዱበት የነበረ ሰፊና ጠፍጣፋ ድንጋይ፣ ሼኽ ሁሴን በስፍራው ጸሎት በሚያደርሱበት ወቅት እሳቸውን ለመብላት የመጡ አውሬዎች ወደ ድንጋይነት እንደተለወጡ የሚታመኑ የእንስሳት ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ድንጋዮች፣ ሼኽ ሁሴን ረግመዋቸው ወደ ድንጋይነት የተቀየሩ ሰዎች እንደሆኑ የሚታመኑና የሰው ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ድንጋዮች ይገኛሉ፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት ወደ መካነ ቅርሱ የመጣ መንፈሳዊ ተጓዥ ወደ አይናገኜ ገደልም ይሄዳል፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ አይናገኜ ገደል በመሄድ የተለያዩ ስርዓቶችን ይፈጽማሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ሶስት ናቸው፡፡ እነሱም በሁሉቃ ውስጥ የመሹለክ፣ በዋሻ ውስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ውኃን መጠጣትና ሰውነትን መቀባት እንዲሁም ወደ ገደሉ ውስጥ ጠጠር የመወርወር ስርዓቶች ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች በአይናገኜ ገደል በሚገኝ ሁሉቃ ውስጥ ይሾልካሉ፡፡ የሁሉቃ ዋሻ በአይናገኜ ገደል ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ሁሉቃ የሚለው ቃል ኦሮምኛ ሲሆን ትርጉሙም መሹለኪያ ማለት ነው፡፡ ይህ ዋሻ 2 መግቢያ በሮችና 2 መስኮት መሰል ሁሉቃዎች (መሹለኪያዎች) አሉት፡፡ የዋሻው ሁለቱ ሁሉቃዎች የተለያየ መጠን ያላቸውና ጠባቦች ናቸው፡፡ አንደኛው ሁሉቃ በአንጻራዊነት ትንሽ ሰፋ ያለ ሲሆን ሁለተኛው፣ በጣም ጠባብ ነው፡፡



*ፎቶ፣ 43፤ አጥኚው የኃጢያት መፈተሻና ማረጋገጫ ሁሉቃዎች በመሹለክ ራሱን ሲፈትሽ የሚያሳይ። (ፎቶ በአቶ መሃመድ ሰዒድ አህመድ)።*

በዋሻው ሁለቱ ሁሉቃዎች መሃል መሹለክ የቻለ ሰው ኃጢያት የሌለበት እንደሆነ ይታመናል። ኃጢያት ያለበት ሰው በሁሉቃዎቹ መካከል እየሾለከ እያለ፣ ቀዳዳው በራሱ ጊዜ በመጥበብ ያጣብቀዋል፤ ስለሆነም መሹለክ አይችልም ተብሎ ይታመናል። ይህ በሁሉቃው ላይ የሚነገር ሚት በመንፈሳዊ ተጓዦች ዘንድ ከፍተኛ ታማኝነት ስላለው ወደ ስፍራው የሚሄድ ሰው ሁሉ በሁሉቃው ውስጥ በመሹለክ ከኃጢያት ነጻ ስለመሆኑ ወይም ኃጢያተኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይወስዳል። በሁሉቃዎቹ በመሹለክ ራስን ከኃጢያት ነጻ መሆን ወይም አለመሆንን ከሚፈትኑ ነገሮች መካከል የመሹለኪያው ቀዳዳ ጥበትና የድንጋዩ የማዳለጥ ባህርይ ይጠቀሳሉ። በሁሉቃ ውስጥ የመሹለክ ሂደት ከኃጢያት መኖር ወይም አለመኖር ባለፈ የሚሾልከው ግለሰብ ያለውን የአካል ብቃት፣ ትኩረትና የመሹለክና ድንጋዩ ሳያዳልጠው የመውረድ ስልትን ማወቅ ይጠበቅበታል።

በዚህ ዋሻ ውስጥ ምንጩ የማይታወቅና የማያቋርጥ የውኃ ጠብታ አለ። ይህን ጠብታ መንፈሳዊ ተጓዦች በምላሳቸው በመቅመስና ሰውነታቸውን በመቀባት ይጠቀሙበታል። ይህ የውኃ ጠብታም ከተለያዩ በሽታዎች የሚፈውስ የሼኽ ሁሴን ጸበል እንደሆነ ይታመናል። ይህ የውኃ ጠብታ እጅግ በቀስታ የሚንጠባጠብ ሲሆን፣ መልኩ ወደ ግራጫነት የሚያደላ ነው። ውኃውን በእጅ ሲነኩት ከትክክለኛ ውኃ በተለየ የመወፈር ባህርይ አለው። ይህ የውኃ መሰል

ጠብታ መንፈሳዊ ተጓዦች የ"ሼኽ ሁሴን ወተት" በሚል ስያሜ ይጠሩታል፡፡ ይህም ስያሜ በአይናገኜ ዋሻ "ወተት ከድንጋይ ውስጥ ይመነጫል፡፡" ተብሎ እንዲታመን ምክንያት ሆኗል፡፡

በአይናገኜ ገደል በግምት 30 ሜትር ርቀት ባለው ጥልቀት ስር በሚገኝ ስፍራ ላይ ሰፊና ጠፍጣፋ ድንጋይ አለ፡፡ ይህ ድንጋይ ሼኽ ሁሴን ይሰግዱበት እንደነበር ይነገራል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ አይናገኜ ገደል ሲመጡ ድንጋዩ ከሚገኝበት ጥልቀት የተነሳ ይህንን ድንጋይ በእጃቸው መንካትና እላዩ ላይ መስገድ አይችሉም፡፡ በመሆኑም ከመሬት ጠጠር ያነሱና ጠፍጣፋው መስገጃ ወደሚገኝበት አቅጣጫ ወደ ገደል ይወረውራሉ፡፡ ጠጠር ወደ ገደል ውስጥ የሚወረውሩበት ምክንያትም ወደ ስፍራው በአካል መሄድ ስለማይችሉ፣ በጠጠሩ አማካኝነት ወደ ስፍራው መድረሳቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ጠጠሩ የእነሱ ወካይ ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑም ስፍራው ላይ በአካል እንደደረሱ ይቆጠራል፡፡



*ፎቶ፣ 44፣ ሼኽ ሁሴን ይሰግዱበት እንደነበር የሚነገርና ጠጠር የሚወረወርበት ጠፍጣፋና ክብ ቅርጽ ያለው ድንጋይ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡*

አንዳንድ አጥኚዎች ይህን ድንጋይ ወደ ገደል የመወርወር ስርዓት በሐጅ ለመንፈሳዊ ጉዞ ወቅት በሳዑዲ አረቢያ ከሚከወን የድንጋይ መወርወር ስርዓት ጋር ያመሳስሉታል፡፡ የሳዑዲ-አረቢያ መካ መንፈሳዊ ተጓዦቹ በ10ኛው ቀን ጠዋት በሚና ተራራ ሲደርሱ 7 አነስተኛ ጠጠሮችን ከመሬት አንስተው ወደ ጁምራት-አል-አቀባ፣ ጁምራት-አል-ኡላና ጁምራት አል-ዋስታ የመታሰቢያ ሐውልቶች ይወረውራሉ (Galwash, 1966:46-54)፡፡ እነዚህ የመታሰቢያ ሐውልቶች

የሰይጣን ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ነብዩ ኢብራሂም ልጁን ለመሰዋት ወደ ስፍራው በሚሄድበት ወቅት ሰይጣን መንገድ ላይ አግኝቶት ይህንን መስዋዕት ማድረግ እንደሌለበት የመከረውን ምክር በማሰብ ወደ ሐውልቶቹ ጠጠሮች ይወረወራሉ፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦቹ ጠጠር የሚወረውሩት በፈጣሪ ስም ሰይጣንን እንደሚያወግዙ፣ እንደሚጠሉና የሰይጣንን ምክር እንደማይቀበሉ ለመግለጽ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ድንጋይ የሚወረወረው ሼኽ ሁሴን ወደ ሰገዱበት ስፍራ መድረሳቸውንና እሳቸው በሰገዱበት ድንጋይ ላይ መስገዳቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የድንጋዩ ተምሳሌት የሳዑዲ አረቢያ-ሚና ድንጋይ ሰይጣንን መምቻ መሳሪያ ሲሆን፣ በድሬ ደግሞ ከሼኽ ሁሴን ጋር የመገናኛ መሳሪያ ትዕምርት ነው፡፡ በድንጋዩ አማካኝነት መንፈሳዊ ተጓዦች ከሼኽ ሁሴን የመስገጃ ቦታና ከሼኽ ሁሴን መንፈስ ጋር ይገናኛሉ፡፡

## 8.6 መንፈሳዊ ተጓዦችን የመሸኘት ስርዓት

የሙዳ በዓላትን ለማክበር ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ወደ ስፍራው የመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች፣ የበዓሉ ስርዓት ሲጠናቀቅ ወደ መጡበት አካባቢ ይመለሳሉ፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ መጡበት ስፍራ ሲመለሱ የሽኝት ስርዓት ይከናወንላቸዋል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ መጡበት ስፍራ በሰላም እንዲገቡ፣ ያሰቡት እንዲሳካላቸው፣ ምኞታቸው (ሀጃቸው) እንዲፈጸምላቸው፣ በስድስተኛው ወር በሚከበረው የሙዳ በዓል ተሳክቶላቸው እንዲመጡ፣ በሰላም ድጋሚ እንዲገናኙ ይመራረቃሉ፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦቹ ያረፉበት ቤት ባለቤት ይዘውት የሚሄዱት የጀዋራ አፈርና የዘምዘም ጸበል ይሰጣቸዋል፡፡ ተጓዦቹም ወደ ስፍራው የመጡት ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የደንቁ በትር ማስታወሻ ይሰጣቸዋል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦቹም ለቤቱ ባለቤት የገንዘብ፣ የአልባሳት፣ የቁሳቁስ ወይም ለስንቅ ይዘው ከመጡት እህል የተረፋቸውን ስጦታ ይሰጣሉ፡፡ የቤቱ ባለቤትም ስጦታውን በመቀበል ይመርቃቸዋል፣ ሽቶ ይቀባቸዋል፡፡ ሽቶ መቀባት የደስታ ስሜትንና ቅድስናን የሚገልጽ ነው፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮችን በመጠቀም ወደ መጡበት ስፍራ ይመለሳሉ፡፡ በመኖሪያ ስፍራቸው ሲደርሱም፣ ከመካነ ቅርሱ ይዘውት የመጡትን ጀዋራ በዘምዘም ጸበል በመበጥበጥ በመኖሪያ ውስጥ፣ በእርሻ ማሳ ላይ፣ በእንስሳ መኖሪያ ውስጥ

ይረጫሉ። ይህም ድርጊት በአካባቢው ያለውን ክፉ መንፈስ ያባርራል፣ በቤተሰብ አባል፣ በእንስሳትና በእጽዋት ላይ ያለ ሕመም ይጠፋል፤ ሙሉ ጤነኛም ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። የዘምዘም ጸበልን ለቤተሰብ አባላት ያጠጣሉ፤ የጀዋራ ቅዱስ አፈርንም ሰውነታቸውን ይቀባሉ። ጀዋራውን በዘምዘም በጥብጠው ያጠጣሉ።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያካሂዱ ተጓዦች የሚሰጣቸው የተለየ ማህበራዊ ክብርና ማዕረግ የለም ። ነገር ግን የሼኽ ሁሴን አፍቃሪ የሆኑና በተለያዩ ምክንያቶች ለሙዳ በዓል ወደ መካነ ቅርሱ መሄድ ያልቻሉ ግለሰቦች፣ በስፍራው ደርሰው የመጡ መንፈሳዊ ተጓዦችን በልዩ ሁኔታ ይቀበሏቸዋል። በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ መካነ ቅርሱ ደርሶ የመጣ ግለሰብ በቦታው ላይ በመድረሱ ብቻ ቅድስና አግኝቷል ተብሎ ይታመናል።

በስፍራው ደርሶ የመጣ ግለሰብ በሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ያለው በረከት በለበሰው ልብስ፣ በአካሉ ላይ፣ ይዞት በሄደው ማንኛውም ቁስ ላይ ያርፋል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም በተለያዩ ምክንያቶች ለሙዳ ወደ ስፍራው መሄድ ያልቻሉ ግለሰቦች፣ በስፍራው ደርሶ የመጣ ግለሰብ የለበሰውን ልብስ ከማጠቡ፣ ሰውነቱን ከመታጠቡና ይዞ የሄደውን ቁስ ከማጽዳቱ በፊት እንዲያገኙት ይመኛሉ፤ ይጥራሉ። ግለሰቡንም ሲያገኙት በልብሱ፣ በአካሉና በቁሶቹ ላይ ካረፈው በረከት ለመቋደስ አካሉን፣ ልብሱንና ቁሱን በእጃቸው በማሻሻሸት፣ ባሻሹበት እጅ የራሳቸውን አካል መልሰው በማሻሸት የበረከቱ ተቋዳሽ ይሆናሉ። ይህ ድርጊት በረከትን መካፈልና ግለሰቡም በስፍራው ደርሶ እንደተመለሰ እንዲሰማው የሚያደርግ ነው።

የሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይ መገኘት ትልቅ የሕይወት ስኬት ተደርጎ ይታመናል። ግለሰቦቹም ከአቅማቸው በላይ የሆነ ችግር ካልገጠማቸው በስተቀር ወደ መካነ ቅርሱ በየስድስት ወሩ ይሄዳሉ። ወደ መካነ ቅርሱ ለ7 ጊዜ ያህል መሄድ ትልቅ በረከትን ያስገኛል፣ ከሼኽ ሁሴን ጋር ያለን ቃልኪዳን ያረጋግጣል ተብሎ ይታመናል። በዚህም ምክንያት አብዛኛው መንፈሳዊ ተጓዥ ለ7 ጊዜ ያህል ወደ መካነ ቅርሱ ለመሄድ ጥረት ያደርጋል። ከሙዳ በዓል የተመለሰ ግለሰብ ለቀጣይ ስድስት ወር ለሚካሄደው የሙዳ በዓል ዝግጅት ያደርጋል። ዝግጅቱም በግለሰብ ወይም በቡድን ለሚደረግ ጉዞ ገንዘብ የማጠራቀም፣ የስንቅና በመካነ ቅርሱ ለሚኖሩ ግለሰቦች የሚሆን እህል የማጠራቀም ስራ ይሰራሉ።

# 9. በሙዳ በዓላት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች እና ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች

በዚህ ምዕራፍ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት፣ በመካነ ቅርሱ፣ በመንፈሳዊ ጉዞና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጫና የፈጠሩና በአሁኑ ወቅትም እየፈጠሩ የሚገኙ ሁነቶችንና የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች እንዲሁም በተለያዩ ወቅቶች የተከሰቱና ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች ይቀርባል።

## 9.1 በሙዳ በዓላት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች

በሙዳ በዓላት፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በመንፈሳዊ ጉዞዎች ላይ የሚስተዋሉ በርካታ ተግዳሮቶች አሉ። እነዚህ ተግዳሮቶች ካላቸው ባህርይ አንጻር የመካነ ቅርሱ ተቃዋሚዎች አስተምህሮ መስፋፋት፣ የትምህርት መስፋፋት፣ የኑሮ ውድነት ማሻቀብ፣ የዶዶቲ ተክል መራቆት፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መስፋፋት፣ የንግድ እንቅስቃሴዎች፣ የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ፣ ለመካነ ቅርሱ የሚደረግ ጥንቃቄ መላላት፣ የመሰረተ ልማቶች አለመሟላት፣ የተለያዩ አካላት ያላቸው የግል ፍላጎት በሚል ተመድበዋል። እነዚህን ተግዳሮቶች በተናጠል ቀጥለን እንመልከት።

### 9.1.1 የመካነ ቅርሱ ተቃዋሚዎች አስተምህሮ መስፋፋት

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በርካታ ወዳጆች እንዳሉት ሁሉ በርካታ ተቃዋሚዎችም አሉት። ከተቃዋሚዎቹ መካከል የክርስትና ኃይማኖት ክፍሎች፣ የዋቄፈና ኃይማኖት፣ የሰለፊያ የእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ ናቸው። እነዚህ የኃይማኖት ክፍሎች በሼኽ ሁሴን፣ በመካነ ቅርሱ፣ በሙዳ በዓላትና በመንፈሳዊ ተጓዦች ላይ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት ከፍተኛ ነው። የክርስትና ኃይማኖት ክፍሎችና የዋቄፈና ኃይማኖት ተከታዮች ባላቸው የአስተምህሮ ልዩነት ምክንያት ሊኖራቸው የሚችለው አሉታዊ አመለካከት ይጠበቃል። ምክንያቱም በኃይማኖቶች መካከል ልዩነት ከሌለ አንዱ ከሌላው የሚለይበት መሰረታዊ ማዕቀፍ ሊኖር አይችልም። እነዚህ የኃይማኖት ክፍሎች ከድሬ ሼኽ ሁሴን ጋር ቅራኔ ቢኖራቸውም ወደ ግጭትና የከረረ አለመግባባት ውስጥ የገቡበት የታሪክ አጋጣሚ እስካሁን የለም።

የሰለፊያ የእስልምና አስተምህሮ ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጋር ያለው የአመለካከት ልዩነትም በሌሎች ኃይማኖት ክፍሎች መካከል እንዳለው፣ ልዩነት መኖሩ የሚጠበቅ ነው።

ነገር ግን የሰለፊያ አስተምህሮ በሸኽ ሁሴንና በመካነ ቅርሱ ላይ ካለው ልዩነት ባለፈ ወደ ግጭትና መካነ ቅርሱን ለማውደም የሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ የመግባት ሂደት እንደነበረው መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ ይህ የሁለቱ ግጭት ካለፉት አርባ አመታት ጀምሮ የነበረና፤ አሁንም ያለ ነው፡፡ የሰለፊዝም የእስልምና አስተምህሮን የጀመሩት ሼኽ ሙሐመድ ኢብን አብደ አል- ወሐብ (1703-1791) ናቸው፡፡ ይህ አስተምህሮ አብይ የእስልምና ክፍል አንዱ ከሆነው ሱኒ ስር ከሚገኙ ንዑስ ክፍሎች መካከል በሐንባሊ ስር የሚመደብ ነው፡፡

ይህ አስተምህሮ መሰረቱ ቅዱስ ቁርዓን በተጻፈበትና በቀጥታ መተርጎም አለበት እንዲሁም ለእስልምና ሕግና ተግባራት የነብዩ መሐመድ ሱና ብቻ መርሕ መሆን አለበት፣ ለወልዮችና ለነብያት ከፍያለ ፍቅርና አክብሮት መስጠት ከአላህ ጋር ሽርክ (ማጋራት) ይፈጥራል የሚሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በመንፈሳዊ ተጓዦች የሚዘየሩ (የሚጎበኙ) መካነ ቅርሶች፣ የቅዱሳን መካነ መቃብሮችና ሌሎች ቦታዎች እንዲወድሙ ድጋፍ ያደርጋል (Gulevich, 2004)፡፡

የሰለፊያ እንቅስቃሴ በባሌ ዞን የተጀመረው በ1963/4 በሼኽ መሐመድ-አሚን ጫፋ ነው፡፡ (Østebo, 2009)፡፡ ከእሳቸው በመቀጠል አስተምህሮቱ በስፋት መሰረት መያዝ የጀመረው የ"80ዎቹ ጉዞ" በመባል በሚታወቀው የሳዑዲአረቢያ የትምህርት እድል ምክንያት ነው፡፡ በዚህ ጉዞ ምክንያት ሳዑዲአረቢያ ከሄዱት መካከል ሼኽ አቡበከር መሐመድ በ1969 ወደ ባሌ ዞን በመመለስ የሰለፊያን አስተምህሮ በማስፋፋታቸው ነው፡፡ ከዚህን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ግለሰቦች አማካኝነት የሰለፊያ አስተምህሮ በባሌ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ተስፋፋ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም የሚከወኑ መንፈሳዊ ድርጊቶች፣ ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ፣ አማኞች በሼኽ ሁሴን ላይ ያላቸው እሳቤና መካነ ቅርሱ በራሱ በሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮችና አራማጆች ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሼኽ አቡበከር በ1971 በአርብ የጁምዓ ዕለት በመስኪድ በተሰበሰበ ሕዝብ ፊት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ ጉዞን፣ የሙዳ በዓልን እንዲሁም ለአውሊያ የሚሰጥ ክብርን በይፋ ተቃወሙ፡፡ በዚህን ወቅት የሼኽ አቡበከርን ሀሳብ በሚደግፉና የእሳቸውን አዲስ የሰለፊያ አስተሳሰብ በሚቃወሙ መካከል ከፍተኛ ልዩነት ተፈጠረ፡፡ በዚህ ልዩነትም በአካባቢው የተከበሩ ግለሰቦችና የሀገር ሽማግሌዎችም ተሳታፊ ሆኑ፡፡ የሼኽ አቡበከርን አዲስ አስተምህሮ የመቃወምና ወደ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞን የሚደግፈው ቡድን ከሕዝቡ ከፍተኛ ተቀባይነት ነበረው፡፡

በወቅቱ በሁለቱ አካላት መካከል ልዩነቶች እየሰፋ በመምጣቱ ወደ ዛቻና ማስፈራራት አልፎተርፎም ወደ ክስ አመራ፡፡ በዚህም ምክንያት ሁለቱን አካላት ለማወያየት በ1972 በጎባ ከተማ ስብሰባ ተዘጋጀ፡፡[164] ስብሰባውንም የመሩት የጄነራል ጃገማ ኬሎ (በወቅቱ የባሌ ገዥ የነበሩት) ምክትል የሆኑት ፊታውራሪ ቦክራ ገብረመድህን፣ የጎባ ከተማ አስተዳዳሪ ቀኛዝማች አድማሱ፣ የወለሼ ጎሳ ባላባት ቀኛዝማች መሐመድአሚን ሼሞና ከዶዶላ የመጡት አባ ጀበል ጣሂሮ ናቸው፡፡

በስብሰባው ላይም የሰለፊያን እንቅስቃሴ ከሚቃወሙ ግለሰቦች መካከል ከሐጂ አደም ሳዶ፣ ሐጂ መሐመድ ሐርሰዲ፣ ሼኽ ጁነይዲን አቦራ፣ ሼኽ መሐመድ ሁሴን አባቡሌ፣ ሼኽ አብዱልቃዲር ማሜ ቡኔ፣ ሼኽ ከዲር አብዱልቃዲር ቂቶ፣ ሼኽ አብዱልገፋር ሻፊሌና ሼኽ ኢድሪስ ቲልሞ የተባሉ ይገኙበታል፡፡ የሼኽ አቡበከርን አስተምህሮ ከሚደግፉ ታዋቂ ግለሰቦች መካከል ሼኽ አብዱልቃዲር ሲዶ፣ ሼኽ ከዲር ሼክመራ፣ ሼኽ መሐመድአሚን ጫፉ፣ ሐጂ ከዲር አደም፣ አቶ አህመዶ ከቢር ፋቂህና ሐጂ ኮርሜ ኪሞ ይገኙበታል፡፡ ስብሰባውም በሁለቱ አካላት መካከል ምንም መግባባት ሳይደረግ ተጠናቀቀ፡፡

ከዚህ ስብሰባ በኋላ በሁለቱ አካላት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋና የሰለፊያ አስተምህሮም እየተጠናከረ ሄደ፡፡ የሰለፊያ አስተምህሮም በገንዘብና በሰው ኃይል እየተጠናከረ ሲመጣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ፣ በሙዳ በዓላትና በመንፈሳዊ ተጓዦች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እየበረታ ሄደ፡፡ በዚህም የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች ዘንድ ሼኽ ሁሴን፣ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና ሙዳ የተወገዙ ሆኑ፡፡ ይህ ሁኔታ እየሰፋ ሄዶ በቤተሰብ መካከል መከፋፈልን፣ በጓደኛ መካከል መለያየት ፈጠረ፡፡ ከእነዚህም ባለፈ ወደ እርስበርስ ግጭትና የነፍስ ማጥፋት ደረጃ ደረሰ፡፡[165]

ይህ የአስተምህሮ ልዩነት እየሰፋ በመሄዱ በ1998 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም በድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ተጓዦችና በሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች መካከል ግጭት ተፈጥሮ የሰው ሕይወት ጠፋ፡፡[166] ግጭቶቹ የተከሰቱት ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ ተነስቶ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን በሚያደርሰው የመኪና መንገድ ላይ ባሉ የወረዳ ከተሞች ላይ ነው፡፡ ከዚህ የመኪና መስመር ባለፈም በተለያዩ አካባቢዎች ተመሳሳይ ግጭቶች ይከሰታሉ፡፡

---

[164] - በስብሰባው ላይ የተገኙ ግለሰቦችንና በስብሰባው ላይ ስለተነሱ ጉዳዮች Østebo (2015፡152-155) በዝርዝር አቅርቧል፡፡

[165] - አቶ መሐመድ ሰዒድ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 29፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[166] - ሼኽ አህመድ ሐጂ ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 9 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

በአሁኑ ወቅት ድሬ ሼኽ ሁሴን በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይ ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች በመምጣት በስፍራው የሚገኙ አማኞች በወረዳቸው፣ በመንደራቸውና በቤተሰባቸው ውስጥ የሰለፊያ አስተምህሮ ተከታዮች አድርሰውብናል የሚሉትን ጉዳቶች መስማት የተለመደ ነው፡፡ በሙዳ በዓል ወቅት ከሚነገሩ የሰለፊያ ጉዳቶች መካከል የመስኪድ ማቃጠል፣ የአውሊያን ገሞዎች ማፍረስ፣ ሰው መግደል፣ ሰው መደብደብ፣ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦችን መሳደብ፣ መዝረፍ፣ የሼኽ ሁሴን ተከታዮች ምልክት የሆነውን የደንቄን በትር መስበር፣ ገሪባዎችን መምታት፣ በሙዳ በዓል ወቅት የትራንስፖርት ስምሪት ቢሮ ካወጣው ታሪፍ በላይ የትራንስፖርት ገንዘብ መጠየቅ፣ የመኪና ባለቤቶች የእኔ መኪና ወደ ድሬ አይሄድም ብለው ማስቀረት፣ ከቤተሰብ አባላት መካከል ወደ ድሬ እንዳይሄዱ መከልከል የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት ሰለፊያ አደረሰብን ከሚሉት ጉዳቶች በተጨማሪ በመካነ ቅርሱና የሙዳ በዓላትን ለማክበር በተሰበሰበ ሕዝብ ላይ ጉዳት ለማድረስ ብለው የሚመጡ እንዳሉ በስፋት ይነገራል፡፡ መረጃ ሰጪዎቼ አይተናል፣ ሰምተናልም ብለው ስለዚህ ጉዳይ ብዙ መረጃዎችን ነግረውኛል፡፡ ሁሉም የሚያምኑት ግን በአንድ ነው፡፡ "በዚህ ቦታ ማንም ጥቃት ለመሰንዘር አቅም የለውም፣ ሼኽ ሁሴን እጅ እግሩን ይዘውት ሕዝብ ፊት ያጋልጡታል፡፡" የሚል ነው፡፡ ጥቃት ለመፈጸም የመጣ ግለሰብም በራሱ ጊዜ "እንዲህ ላደርግ ነበር አቃተኝ"፣ "እንዲህ ላደርግ ስል አንድ ሽማግሌ በህልሜ አስፈራራኝ"፣ "እንዲህ ላደርግ ተልኬ መጥቼ እንቅልፍ ሁለት ቀን ጣለኝ" ይላል የሚሉ አገላለጾች የተለመዱ ናቸው፡፡

ይህንን ወንጀል ሊፈጽም የነበረ ግለሰብ ለምን በህግ አታስቀጡም? የሚል ጥያቄ ለመረጃ ሰጪዎቼ በቡድን ውይይት ወቅት ጠየኳቸው፡፡ የሁሉም መልስ አንድ ነው፡፡ እንዲህ የሚል፤

> በበዓላት ወቅት የሚመጡ የጥበቃ ኃይሎች ይይዙትና ለእኛ አስረክቡን ይላሉ፡፡ እኛ ግን አናስረክበውም፡፡ ምክንያቱም ወንጀለኛውን የያዘው ሼኽ ሁሴን ነው፡፡ በሕዝብ ፊትም እንዲህ ላደርግ ነበር ብሎ እንደዲናዘዝ ያደረገው ሼኽ ሁሴን ነው፡፡ ሰውዬውን እጅ ከፍንጅ የያዘው ሼኽ ሁሴን እንጂ የጥበቃ ኃይል አይደለም፡፡ ስለዚህ ሕዝብ ፊት በራሱ አንደበት ወሐቢያን እንዲረግም፣ትምህርቱ ስህተት ነው እንዲል፣ የሼኽ ሁሴንን ትልቅነት እንዲመሰክር አድርገን በሰላም ወደ አገሩ እንዲመለስ መርቀን እንሸኘዋለን፡፡[167]

[167] - ሼኽ አህመድ ሼኽ ከዲር፣ ሼኽ መሐመድ ሐጂ አብዱልቃድር፣ ሼኽ መሐመድ ሐጂ መሐሙድ፣ አናጂና፣ መጋቢት 29 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት የሰለፊያ አስተምህሮንና ተከታዮቹን መርገም የተለመደ ነው። የሰለፊያ ተከታይ ከምደረ ገጽ እንዲጠፋ በባትሪ ይረገማል፣ በድንጋይ ይረገማል፣ በጭብጨባ ይረገማል፣ በፊርማ ይረገማል፣ በትንፋሽ ይረገማል። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለሚመጡ የሼኽ ሁሴን ወዳጆች ትልቁ ጠላት ሰለፊያ ነው። የእነሱ ትልቅ ጠላት የሆነ ኃይል በመካነ ቅርሱና በአማኙ ላይ ጥቃት ሊፈጽም መጥቶ ሲያዝ ግን እርምጃ ልውሰድ ብሎ በስሜት የሚውረገረግ ሰው የለም። የሁሉም ሰው መልስ "ሼኽ ሁሴን አጋልጠውታል፣ በሰላም ወደ መጣበት ይመለስ።" የሚል ነው። ይህን መልስ መስማት የተለያዩ ጉዳዮችን ያሳያል። አንድም መንፈሳዊ ተጓዦች በሼኽ ሁሴን ላይ ያላቸው ፍጹም እምነት፣ አንድም ሊጎዳህ የመጣን በፍቅር የመመለስ የአሸናፊ ስብዕናን ነው። ይህ አይነት የሰለፊያ ድርጊት የሌላውን እምነት የመጫን፣ ልዩነትን ያለመቀበልና ማንም ሰው የፈለገውን እምነትና ኃይማኖት የመከተል ሰብዓዊ መብትን የመገርሰስ ፍላጎት ይመስላል።

## 9.1.2 የትምህርት መስፋፋት

በአናጂና ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ከ1ኛ እስከ 9ኛ ክፍል የሚያስተምር አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት አለ። የአካባቢው ተማሪዎች መደበኛ ትምህርታቸውን እስከ 9ኛ ክፍል ድረስ ከተማሩ በኋላ የ10ኛ ክፍልና የመሰናዶ ትምርታቸውን ለመጨረስ ወደ ጃራ፣ ጊንር፣ ጋሰራና ወይም ወደ ሌሎች አጎራባች የወረዳ ከተሞች ይሄዳሉ። እነዚህ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ ሌሎች አካባቢዎች በመሄዳቸው ምክንያት ከቤተሰብና ከመካነ ቅርሱ ጋር ያላቸው ቁርኝት እየላላ እንዲሄድ አድርጓል።

የሙዳ በዓላት ሲቃረቡ ኪነሕንጻዎቹን የማደስ ስራ ላይ ለሀሽ ዝግጅት የድንጋይ ፈለጣ፣ የእንጨት ቆረጣ፣ ድንጋዩንና እንጨቱን ከመገኛ ስፈራቸው ወደ መካነ ቅርሱ ይዞ በሸክም ወይም በመኪና ማምጣት እንዲሁም ሕንጻዎችን ሀሽ መቀባት ከፍተኛ የሰው ጉልበት ይጠይቃል። በመሆኑም በርካታ ቁጥር ያለው ወጣት ያስፈልጋል። ወጣቱ ለትምህርት በሚል ከአካባቢው በመራቁ የሰው ኃይል እጥረት ያጋጥማል። ይህ መሆኑ ደግሞ ሀሽ የመቀባት ስራ መከናወን ባለበት ቀን መጨረስ አይቻልም።

የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች እድሜያቸው ለሁለተኛ ደረጃ ትምርት ሲደርስ ከአካባቢው በመራቃቸው ምክንያት በሙዳ በዓላት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ፣ በቤተሰባቸው የሚከወነውና ለመንፈሳዊ ጉዞ ወደ ስፍራው የሚመጡ ግለሰቦችን የመቀበልና የማስተናገድ ባህልን፣ በመካነ

ቅርሱ በሚገኙ ኪነሕንጻዎች፣ የውኃ ኩሬዎችና ልዩ መንፈሳዊ ዋጋ ያላቸውን ቦታዎችን የመንከባከብና የመቆጣጠር ስሜት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ሊሄድ ይችላል። ይህ መሆኑ በራሱ በመካነ ቅርሱና በሙዳ በዓላት ላይ እንደ ተግዳሮት ይወሰዳል።

## 9.1.3 የኑሮ ውድነት ማሻቀብ

በመካነ ቅርሱ የሚኖሩ ግለሰቦችና በመንፈሳዊ ተጓዦች መካከል የቃልኪዳን ስምምነት አለ። ይህ ስምምነትም ነዋሪዎቹ አካባቢውን እንዲጠብቁ፣ እንዲንከባከቡና በበዓላት ወቅት እንግዶችን እንዲያስተናግዱ፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ደግሞ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሙዳ በዓላት ወደ ስፍራው ሲመጡ የነዋሪዎቹን የስድስት ወር ቀለብ እንዲችሉ ነው። ይህ የቃልኪዳን ስምምነት ለረጅም ዘመናት ቀጥሏል፤ አሁንም እንደቀጠለ ይገኛል።

የቃልኪዳን ስምምነቱ በየጊዜው በሚከሰት የዋጋ ግሽፈትና የምርት እጥረት ምክንያት የኑሮ ውድነት እያሻቀበ በመሄዱ ፈተና ላይ እየወደቀ ነው። መንፈሳዊ ተጓዦች ካለው የኑሮ ውድነትና ድህነት ከአመት አመት እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት ከዚህ በፊት ለነዋሪዎቹ ያደርጉት የነበረውን የቀለብ ሰፈራ ስራ እንዲቀንሱ ወይም ሙሉለሙሉ እንዲተዉ ያስገድዳቸዋል። የኑሮ ውድነት ማሻቀብ በነዋሪዎቹ፣ በመንፈሳዊ ተጓዦች፣ በመካነ ቅርሱና በሙዳ በዓላት ላይ ተግዳሮት ፈጥሯል።

የኑሮ ውድነት ማሻቀብ ከነዋሪዎች አንጻር ያለው ተግዳሮት በርካታ ነው። የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ከዚህ በፊት ከመንፈሳዊ ተጓዦች ይመጣላቸው የነበረ ቀለብ በመጠኑ እየቀነሰ ወይም የነዋሪዎቹ የቤተሰብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ አልዳረስ እያለ ወይም መንፈሳዊ ተጓዦች ቀለብ ይዘው መምጣት ሙሉለሙሉ በማቋረጥ ለከፋ ድህነት ወይም ለረሀብ ሊጋለጡ ይችላሉ። በመካነ ቅርሱ አንዳንድ ነዋሪዎች ያለባቸውን ድህነት በቀላሉ መለየት ይቻላል።

የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች በድህነት በተጠቁ ቁጥር የራሳቸውን አማራጮች መውሰድ ይጀምራሉ። እርምጃዎቹም ለስራ ፍለጋ ወደ ሌሎች ከተሞች መሄድ፣ ለመካነ ቅርሱ የነበራቸው ተቆርቋሪነት መቀነስ ወይም አቅማቸው በፈቀደ መጠን በስፍራው ሌሎች ስራዎችን መስራት መጀመር ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ መሆኑ የሙዳ በዓላት ሲዳረሱና በበዓላት ወቅት እንግዶችን ለመቀበል የሚሰሩ ስራዎች በአግባቡ እንዳይሰሩ ችግር እየፈጠረባቸው ነው።

### 9.1.4 የዶዶቲ ተክል መራቆት

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኙ ገሞዎች በአመት አንድ ጊዜ ሀሽ ይቀባሉ። ሀሽ የሚዘጋጀውም ከዶዶቲ እንጨትና ከድንጋይ ነው። የዶዶቲ እንጨት የሚገኘው ኩባዩ በሚባል ስፍራ ነው። ስፍራው ከዶቆ ከራው በግምት 20 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። እንጨቱን ለማምጣት የሚሆን የመኪና ወጪ የሚሸፈነው በማህበረሰቡ ነው። ለሀሽ የሚሆን የዶዶቲ እንጨትን ማዘጋጀት ሁለት ተግዳሮቶችን ፈጥሯል። አንደኛው፣ ለእንጨቱ ማጓጓዣ የሚሆን የገንዘብ ወጪ እጅግ በርካታ ነው። ለአንድ ዙር የመኪና ጭነት በአማካኝ 800 ብር ይከፈላል። ለአንድ ጊዜ ሀሽ የማዘጋጀት ስራ በአማካኝ 8 ዙር (ባጆ) መኪናው ይመላለሳል። ይህ ማለት ለአንድ ጊዜ 6,400 ብር ወጪ ይደረጋል። እንጨቱን ለመቁረጥ የሚሄዱ ሰዎች ቁጥር በርካታ ነው። እንጨቱ የሚቆርጡ ሰዎች በስፍራው ለ20 ቀናት ይቆያሉ። ለሰዎቹ የሚሆን ቀለብ የሚያዋጣው የመካነ ቅርሱ ነዋሪ ነው።

ይህ የማህበረሰቡ አስተዋጽኦ መካነ ቅርሱን ከመጠበቅና ከመንከባከብ አንጻር ትልቅ ጸጋ ነው። ከቅርስና ባህል ጥበቃ አንጻር አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው። ይህ መሆኑም ሊበረታታ የሚገባው ነው። ነገር ግን ይህ ጸጋ በአሁኑ ወቅት ካለው የኑሮ ውድነትና የማህበረሰቡ ድህነት መጨመር በሀሽ ዝግጅት ላይ ያለው ሚና ሊቀንስ ይችላል። ይህ ደግሞ ለወደፊት አስጊ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። ሁለተኛው፣ ለሀሽ ዝግጅት የሚያገለግለው የዶዶቲ እንጨት በድሮ ጊዜ በአካባቢው በስፋት የሚገኝ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እየተመናመነ ከመካነ ቅርሱ የድንበር ክልል እያለፈ ነው። ይህ ተክል የተለየ የሚያደርገው አንዴ ከተቆረጠ ድጋሚ የማይበቅል መሆኑ ነው። ይህ የተክሉ ባህሪና ለሀሽ ዝግጅት በርካታ እንጨት በየአመቱ መቆረጡ ተክሉ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አካባቢው ሙሉለሙሉ ሊጠፋ ይችላል የሚል ስጋት አለ።

### 9.1.5 የቴክኖሎጂ ውጤቶች መስፋፋት

በተለያዩ ወቅቶች የሚፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አሉ። እነዚህ የቴክኖጂ ውጤቶች በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ በዓላት ወቅት የተለያዩ ተግዳቶችን እየፈጠሩ ነው። ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መካከል ተንቀሳቃሽ የእጅ ስልክ፣ ሚሞሪ ካርድ፣ የድምጽ ማጉያ (ሞንታርቦ) እና የሙዚቃ ማቀናበሪያ ስቱዲዮዎች መስፋፋት ይጠቀሳሉ። እነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሙዳ በዓል ወቅት የፈጠሩትን ተግዳሮት በተናጠል እንመልከት።

በሙዳ በዓል ወቅት በርካታ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ በመካነ ቅርሱ በተለያዩ ስፍራዎች ስርዓተከበራዎች ይከወናሉ፡፡ እነዚህ ስርዓከበራዎች ሲከወኑ መንፈሳዊ ተጓዦች ይታደሚቸዋል፡፡ በዚህ ወቅት መንፈሳዊ ተጓዦቹ በሚይዟቸው ተንቀሳቃሽ የእጅ ስልኮች የሚደረግ ጥሪን እዛው ባሉበት ሆነው መቀበልና ማውራት እንዲሁም በሚይዙት ስልክ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን በድምጽና በምስል መቅዳት ከፍተኛ ተግዳሮት እየፈጠሩ ናቸው፡፡

ይህም በስፍራው የተለያዩ ስርዓተከበራዎችን የሚፈጽሙ ሰዎችን ስሜት ይረብሻል፡፡ ስርዓተከበራዎቹን የሚፈጽሙ ሰዎች በስሜት ውስጥ ሆነው ክወና በሚያቀርቡበት ወቅት በስልክ ማውራት፣ ከእጅ ስልክ የሚወጣና ከፍተኛ የብርሃን ኃይል ያለው ጨረር በመልቀቀቅ ፎቶግራፍ ለማንሳትና ቪዲዮ ለመቅረጽ መጣር አንዱ ተግዳሮት ነው፡፡ ከዋኞች ክወናቸውን በሚያቀርቡበት ወቅት ድምጻቸውን በመቅረጸ ድምጽ ወይም ምስላቸውን በፎቶና በቪዲዮ ለማስቀረት በመፈለግ ከዋኞቹን እየተከተሉ፣ የሞባይል ስልካቸውን በከዋኞቹ ፊት ላይ መደንቀር፣ ወደ አፋቸው ማስጠጋት ሌላው ተግዳሮት ነው፡፡

እነዚህ ድርጊቶች በአንድ በኩል ከዋኞች ከስሜት እንዲወጡና እንዲረበሹ በማድረግ ከክወናቸው ሲያደናቅፉ በብዛት ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ግለሰቦች ካለፍላጎታቸውና ፍቃዳቸው ውጪ ድምጻቸውና ምስላቸው እንዲያዝ ያረጋል፡፡ ይህም ድርጊት የግለሰቦችን ሰብዓዊ መብትና ነጻነት የሚጋፋና የሚጥስ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ድርጊቶች የከዋኞቹ መብት በመጣስ በመካነ ቅርሱ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች በነጻነትና በስሜት እንዳይከወኑ ተጽዕኖ ይፈጥራሉ፡፡

በመካነ ቅርሱ የሚከወኑ የባሮ፣ የሰርመዴ፣ የሹቢሳና ሌሎች መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በሚሞሪ ካርድ ላይ በመጫን በሞባይል በስፋት ይደመጣሉ፡፡ እነዚህ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በሚሞሪ ካርድ በቀላሉ መጫን መቻላቸው በሁሉም ግለሰብ ዘንድ በቀላሉ እንዲገኙና እንዲደመጡ ሆኗል፡፡ ይህ መሆኑ በራሱ ጥሩ ጎን አለው፡፡ ነገር ግን እነዚህን መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በመካነ ቅርሱ የተለያዩ ስርዓተከበራዎች በሚከወኑባቸው ስፍራዎች አካባቢ በከፍተኛ ድምጽ የማስጮህ ድርጊት ይፈጸማል፡፡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎቹ በከፍተኛ ድምጽ በመለቀቃቸው ምክንያት ስርዓተከበራዎቹ በሚፈጸሙባቸው ቦታዎች ድረስ ይሰማሉ፡፡ ይህም ድርጊት ስርዓተከበራዎችን የሚከታተሉና የሚከውኑ ግለሰቦችን ይረብሻል፡፡

በተመሳሳይ እነዚህ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በድምጽ ማጉያ (ሞንታርቦ) አማካኝነት ይለቀቃሉ፡፡ በድምጽ ማጉያ አማካኝነት ከመንፈሳዊ ሙዚቃዎች በተጨማሪ ከጤና ቢሮ የሚሰጡ የጤና

አጠባበቅ ትምህርቶችና የንግድ ማስታወቂያዎች አልፎአልፎም ይለቀቃሉ፡፡ የድምጽ ማጉያ መሳሪያው ከፍተኛ ድምጽ የመልቀቅ ባህርይ ስላለው በአካባቢው አላስፈላጊ ድምጽ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በሚሞሪ ካርድና በድምጽ ማጉያ የሚለቀቁ ድምጾች በአካባቢው አላስፈላጊና መጠኑ ባለፈ ድምጽ እንዲበከል ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ድርጊት መንፈሳዊ ተጓዡ፣ መንፈሳዊ ስርዓተከበራ ከዋኙና ስርዓተከበራውን የሚከታተሉ ሰዎችን በከፍተኛ ደረጃ ይረብሻል፡፡ በመሆኑም አካባቢው ለአላስፈላጊ የድምጽ ብክለት እየተዳረገ ነው፡፡

በከተሞች ውስጥ የሙዚቃ ማቀናበሪያ ቤቶች እየተስፋፉ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የባሮ፣ የሰርመዴ፣ የሹቢሳና ሌሎች መንፈሳዊ ሙዚቃዎች በካሴትና በሲዲ በስፋት እንዲታተሙና ለሕዝቡ እንዲሰራጩ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ መሆኑ የራሱ ጥሩ ጎን አለው፡፡ ነገር ግን እነዚህ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን የሚያወጡ ግለሰቦች አንዳንዶቹ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኡሌ ማዕረግ ስርዓት መሰረት እውቅና ያልተሰጣቸውና ማንነታቸው የማይታወቅ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ነባሩን የድሬ ባህል የሚጋፉ፣ መንፈሳዊ ሙዚቃዎቹ ያላቸውን ትክክለኛ ዜማ፣ ቅኝት፣ ክወና እንዲሁም የኃይማኖትን መንፈስ በትክክል ያልያዙ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ከመንፈሳዊ ሙዚቃዎቹ መካከል ባሮ ምንም አይነት የሙዚቃ መሳሪያና ጭብጨባ የሌለው ነው፡፡ ይህ የባሮን ባህሪን ባልተከተለ መንገድ በሙዚቃ መሳሪያ መከወን ይስተዋላል፡፡ በድቤ ድምጽ  ድምጽና በጭብጨባ የሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን በኪቦርድና በሌሎች ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በማጀብ ማቅረብ እንዲሁም የተሻለ እንዲሆን በሚል በኮምፒውተር በታገዘና በሚረብሽ ድምጽ ማቅረብ ይስተዋላል፡፡ ይህ ሁኔታም በመንፈሳዊ ሙዚቃዎች ክወና፣ ይዘት፣ ባህርይ፣ ከትውልድ ትውልድ ባለው ተስተላልፎ እንዲሁም የኡሌዎቹን የፈጠራ መብት የሚጋፋ ድርጊት ነው፡፡ ይህም ድርጊት በመካነ ቅርሱ ልዩ እሴቶች ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ፈጥሯል፡፡

### 9.1.6 የንግድ እንቅስቃሴዎች

በሙዳ በዓላት ወቅት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ሕዝብ ወደ ስፍራው ይመጣል፡፡ ሕዝቡም የሚጠቀማቸውን ምግብ፣ መጠጥ፣ አልባሳት፣ ቅመማቅመምና ሌሎች ጉዳዮች ለመሸጥ ከመካነ ቅርሱ ቅርብ ርቀት ላይ ከሚገኙ የወረዳ ከተሞች በርካታ ቁጥር ያላቸው ነጋዴዎች ይመጣሉ፡፡ በስፍራው በሚካሄድ የንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት ከነጋዴዎቹ በሚሰበሰብ ቀረጥ መካነ ቅርሱ፣

ቀበሌው፣ ወረዳውና ዞኑ የገቢ ምንጭ ያገኛል። ለነጋዴውም የገቢ ምንጭ፣ በስፍራው ለመጣ ሕዝብም ግልጋሎት በመስጠት ከፍተኛ ጥቅም እያስገኘ ነው።

በስፍራው የሚከወን የንግድ እንቅስቃሴ ለመካነ ቅርሱም ሆነ ለሙዳ በዓላት ያለው ጠቀሜታ እንዳለው ሁሉ የራሱ ተግዳሮትም አለው። የንግድ እንቅስቃሴው ከፈጠራቸው ተግዳሮቶች መካከል ለንግድ በማይፈቀድና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ የሚውል የመካነ ቅርሱ ማዕከላዊ ክልል (Core zone) ውስጥ የንግድ ስራ መስራት፣ ነጋዴዎች ያመጡትን ዕቃ ለማሻሻጥ በመኪና ከስፍራ ስፍራ በመዞር ወይም በአንድ ስፍራ በመሆን ከፍተኛ ድምጽ ባለው የድምጽ ማጉያ ማስተዋወቅ፣ በስፍራው የማይፈቀዱ የሺሻና የአልኮል መጠጦችን መሸጥ እንዲሁም የወሲብ ንግድ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

በስፍራው የማይፈቀዱ የሺሻና የአልኮል መጠጦችን መሸጥ እንዲሁም የወሲብ ንግድ ሊስፋፉ የቻሉበት ዋናው ምክንያት በሙዳ በዓላት ወቅት መንፈሳዊ ተጓዦችን ይዘው የሚመጡ የአገር አቋራጭ፣ መካከለኛና አነስተኛ የሕዝብ ትራንስፖርት መኪና ሹፌሮችና ረዳቶች፣ ስፍራውን ለመጎብኘት የሚመጡ ግለሰቦችና ለንግድ የሚመጡ ግለሰቦች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ ነው። እነዚህ ግለሰቦች ወደ ስፍራው የሚሄዱት ለመንፈሳዊ ጉዳይ ባለመሆኑ ለመካነ ቅርሱም ሆነ ለስፍራው መንፈሳዊነት ዋጋ አይሰጡም። በመሆኑም በስፍራው የሚስተዋሉ እነዚህ አላስፈላጊ የንግድ እንቅስቃሴዎች መካነ ቅርሱ ያለውን መንፈሳዊ ዋጋ የሚያራክሱ፣ የሙዳ ክወናዎችን የሚረብሹና የቅርሱን ሕልውና የሚያናጉ ናቸው።

የደንቄ በትር በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ፣ በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎችና በሙዳ በዓላት ወቅት ልዩ መንፈሳዊና ማህበራዊ ውክልና አለው። ከጥቂት አመታት በፊት የደንቄ በትር የሚቆረጠው ከቀጨምስሬ ተራራ ላይ ብቻ ነው። በትሩንም የሚያዘጋጀው የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ሲሆኑ፣ በእንግድነት ለሚመጡ ግለሰቦች የወንድማማችነት ማጠናከሪያ በሚል የሚሰጡት ስጦታ ነው። በአሁኑ ወቅት የደንቄ በትርን ከየትኛውም ቦታ በመቁረጥና በማዘጋጀት ወጣቶች በአነስተኛ የገንዘብ መጠን ይሸጣሉ። ይህም ድርጊት የአካባቢው ነዋሪ ወጣቶች በትሩን ሸጠው ገንዘብ ለማግኘት ካላቸው ፍላጎት የመነጨ ነው። ወጣቶች ገቢ ማግኘታቸው መልካም ነገር ቢሆንም የደንቄ በትር ያለውን ማህበራዊና መንፈሳዊ ዋጋ እየቀነሰ እንዲሄድ ያደርገዋል። ይህም ለውጥ በአካባቢው የንግድ እንቅስቃሴ ከመስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው።

### 9.1.7 የስልጣን ይገባኛል ሽኩቻ

የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች (ደርጋዎች) ባላቸው ማህበራዊ አደረጃጀቶች መሰረት ለቅርሱ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋሉ፡፡ የተለያዩ ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን ይመራሉ፡፡ ለሙዳ በዓላት የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓገኞችን ያስተናግዳሉ፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚኖሩ ደርጋዎች ቤተሰባዊነትን መሰረት ያደረገ ማህበራዊ አደረጃጀቶች ቢኖሩም እርስበርስ ያላቸው ቅርርብ ከፍተኛ ነው፡፡ የመካነ ቅርሱ ደርጋዎች እርስበርስ ቅርርብ ቢኖራቸውም "የኢማምነት ስልጣን ይመለስልን" የሚል ጥያቄ በሚያነሱት የሼኽ መሃመድ ቤተሰቦችና የኢማምነት ስልጣንን መመለስ በሚቃወሙ የሼኽ አባስ ቤተሰቦችና ሰኪናዎች መካከል አልፎአልፎ አለመግባባት ይከሰታል፡፡

በአሁኑ ወቅት የሚከሰቱ አለመግባባቶች የሼኽ መሃመድ ቤተሰብ የሆኑት ኢማም ሙሀይ አል-ዲን የመካነ ቅርሱ ኢማም መሆን አለባቸው የሚል ነው፡፡ ከእነዚህ አለመግባባቶች መካከል በ1999 ዓ.ም በሼኽ መሃመድና በሼኽ አባስ ቤተሰቦች መካከል የተነሳው ይጠቀሳል፡፡ ይህ አለመግባባትም ወደግጭት አምርቶ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ፡፡

በእነዚህ ቤተሰቦች መካከል ያለው የስልጣን ሽኩቻና አልፎአልፎ የሚከሰት ግጭት በመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች ዘንድ ያለው አንድነት እንዲላላ፣ መካነ ቅርሱ የግል ጥቅም ማስጠበቂያ፣ የኃብት ማመንጫና የግል ክብር መጠበቂያ ተደርጎ እንዲታሰብ፣ ወደ ስፍራው የሚመጣ መንፈሳዊ ተጓገኞችንና የመንግስት ባለስልጣናትን በማግባባት የአንዱ ቡድን ደጋፊ እንዲሆኑ፣ አጥኚዎች የመካነ ቅርሱን ታሪክ ሲያጠኑ በአንድ ቤተሰብ በኩል ያለውን ታሪክና ሚና እንዲያጎሉ በማድረግ አጥኚዎች ነጻና ገለልተኛ እንዳይሆኑ ጫና ማሳደርና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮችን ፈጥሯል፡፡ ይህ አለመግባባት እስካሁን በመካነ ቅርሱ አካላዊ ገጽታ ላይ ያደረሰው ጉዳት ባይኖርም ወደፊት ችግር ሊፈጥር የሚችልበት እድል ሊኖር ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ የስልጣን ይገባኛል ሽኩቻ በመካነ ቅርሱ፣ በሙዳ በዓላት፣ በመንፈሳዊ ተጓገኞችና በአጥኚዎች ላይ የራሱን ተግዳሮት ፈጥሯል፡፡

### 9.1.8 ለመካነ ቅርሱ የሚደረግ ጥንቃቄ መላላት

በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት ወደ መካነ ቅርሱ የሚመጣው የሕዝብ ቁጥር እስከ አምስት መቶ ሺኽ የሚገመት ነው፡፡ የሕዝብ ብዛቱም ከዓመት ወደ አመት እየጨመረ መሆኑን ከመረጃ ሰጪዎቹ ባገኘሁት መረጃና በተለያዩ ወቅቶች በመስክ ቆይታዬ ወቅት አስተውያለሁ፡፡ የሕዝብ ቁጥር መጨመር የራሱ ጥሩ ጎን ቢኖረውም ከመካነ ቅርሱ

የወደፊት ሕልውና አንጻር ተግዳሮት የሚፈጥር ነው፡፡ በስፍራው የሚመጣው ሕዝብ ሼኽ ሁሴንን፣ ሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒን፣ ሼኽ ኢብራሂምንና ሌሎችን ለመዘየር ወደ ገሞዎች ውስጥ ይገባል፡፡ በአንድ ጊዜ ወደ ገሞዎቹ የሚገባው ሕዝብም ቁጥር በርካታ ነው፡፡ ይህ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብም በገሞዎቹ ውስጥ ለረጅም ሰዓታት ይቆያል፡፡ ይህ ድርጊት ወደ ፊት በመካነ ቅርሱ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦችን አሳፍረው የሚመጡ ከፍተኛ አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሺያና አነስተኛ መጠን ያላቸው መኪናዎች እንዲሁም ለንግድ እንቅስቃሴ የሚያገለግሉ መኪናዎች ለሙዳ በዓላት ወቅት ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት አገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት መኪናዎች የሚቆሙበት መናኸሪያ ስላለ እዛ ይቆማሉ፡፡ መኪኖችም የመካነ ቅርሱን ድንበር እንዳያልፉ በባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች፣ በነሪዎችና በጥበቃ ኃይሎች ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ ነገር ግን አነስተኛ መጠን ያላቸው የንግድ፣ የቤትና የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች ወደ መካነ ቅርሱ ድንበር በማለፍ የሚቆሙበት ወይም በድንበሩ ውስጥ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

መኪናዎቹ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ምክንያት በመሬቱ ላይ ንዝረት ይከሰታል፡፡ የንዝረቱ መጠን እየጨመረና እየተደጋገመ በሄደ ቁጥር መካነ ቅርሱ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ ይህ መሆኑ በመካነ ቅርሱ የወደ ፊት ሕልውና ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡ መካነ ቅርሱ፣ የሙዳ በዓላትና መንፈሳዊ ጉዞዎች ቀጥተኛ ተያያዥነት አላቸው፡፡ የመካነ ቅርሱ ሕልውና ችግር ገጠመው ማለት የሙዳ በዓላትና መንፈሳዊ ጉዞው ችግር ገጠመው ማለት ነው፡፡

## 9.1.9 የመሰረተ ልማቶች አለመሟላት

በሙዳ በዓላት ወቅት በርካታ ሕዝብ ወደ ስፍራው ይመጣል፡፡ ለሙዳ በዓላት የሚመጣው ሕዝብ እንዳለ ሆኖ በስፍራው በቋሚነት የሚኖሩ ሕዝብ አለ፡፡ በስፍራው ለነዋሪዎችም ሆነ ለሙዳ በዓል ተጓዦች የሚያገለግል የመጸዳጃ ቤት፣ የንፁሕ መጠጥ ውኃ፣ የመብራት፣ የስልክ ኔትወርክ፣ የምግብ ቤት፣ የማረፊያ ቤት፣ የመንገድና መሰል መሰረታዊ ልማቶች አልተሟሉም፡፡ እነዚህ መሰረተልማቶች ለመካነ ቅርሱ፣ ለነዋሪዎችና ለመንፈሳዊ ተጓዦች ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

የእነዚህ መሰረተልማቶች ጥቅም የተለያየ መሆን፣ ሁሉም ጠቃሚዎች መሆናቸውና የአንዱ አለመኖር የራሱ ችግር ስለሚፈጥር አንዱን ከሌላው ማወዳደር ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን

በአንጻራዊነት የንጹሕ መጠጥ ውኃ፣ የመብራትና የመጸዳጃ ቤት ሙሉለሙሉ ወይም በበቂ ደረጃ አለመኖር ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩ እንደሆነ በመስክ ቆይታዬ ወቅት አስተውያለሁ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በ2000 ዓ.ም በተከበረው የኦሮሚያ ሚሊኒየም በዓል ምክንያት በመካነ ቅርሱ የንጹሕ የመጠጥ ውኃ፣ የመብራትና የስልክ ኔትውርክ ዝርጋታ ስራ ተሰርቷል፡፡ በወቅቱም የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎችና የሙዳ በዓል ተሳታፊዎች የእነዚህ መሰረተልማቶች ተጠቃሚ ሆነ፡፡ የሚያሳዝነው ነገር በዓሉ በስፍራው ተከናውኖ በተጠናቀቀ ማግስት የውኃው፣ የመብራቱ ሆነ የስልክ ኔትወርክ አገልግሎቶች ሙሉለሙሉ ተቋረጡ፡፡ በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ የንጹሕ መጠጥ ውኃ፣ የመብራትና የስልክ ኔትወርክ አገልግሎቶች የሉም፡፡

በመካነ ቅርሱ የንጹሕ መጠጥ ውኃ ባለመኖሩ ነዋሪዎችና የሙዳ በዓል መንፈሳዊ ተጓዦች በጣም ይቸገራሉ፡፡ ይህንን ችግራቸውን ለመቅረፍ ገንዘብ ያለው ሰው ታሽጎ የሚሸጡ ውኃን ለመጠጥ ይጠቀማል፡፡ ገንዘብ የሌለው ሰው ደግሞ በስፍራው በሚገኙ ኩሬዎች ውስጥ በዝናብ ምክንያት የሚጠራቀምን ውኃ ለመጠጥነት ይጠቀማል፡፡ አብዛኛዎቹ ነዋሪዎችና መንፈሳዊ ተጓዦች በኩሬዎቹ የተጠራቀመውን ውኃ ለመጠጥ፣ ለምግብ ማብሰያነት፣ ለልብስ እጥበት፣ ለእንስሳት መጠጥ፣ ለግልና ለአካባቢ ንጽሕና መጠበቂያ ይጠቀሙበታል፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት ነዋሪዎቹና መንፈሳዊ ተጓዦቹ የኩሬዎቹን ውኃ ሲጠቀሙ በመካነ ቅርሱ ጤና ጣቢያ፣ በወረዳ ጤና ጽ/ቤትና በዞን ጤና ቢሮ ባለሙያዎች አማካኝነት ውኃውን አፍልተው እንዲጠቀሙ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ከትምህርቱም ባለፈ የአካባቢ ጸጥታ ጥበቃ ዘርፍ ባለሙያዎችን በማሰማራት የውኃ ማከሚያ ኬሚካል እንዲታደል ያደርጋሉ፡፡ የአካባቢ ጸጥታ ጥበቃ ዘርፍ ባለሙያዎችም በውኃ ኩሬዎቹ አጠገብ በመገኘት እያንዳንዱ ግለሰብ ውኃ ከኩሬዎቹ ቀድቶ እንደጨረሰ የውኃ ማከሚያ ኬሚካል በውኃ መያዣው ውስጥ በመጨመር ሕዝቡ በውኃ ወለድ በሽታዎች እንዳይጠቃ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡



*ፎቶ 45፣ ለመጠጥና ለተለያየ አገልግሎት የሚውለው የድንኩሬ የውኃ ኩሬ። (ፎቶ በአጥኚው)።*

ይህ ውኃን የማከም ጥረት እንዳለሆኖ በኩሬዎቹ የሚገኘው ውኃ ንፅሕናውን ያልጠበቀና ለረጅም ወራት የተጠራቀመ በመሆኑ በአልጌ ተክል የተሸፈነ መሆኑ፣ የውኃ መጠን መቀነስና አልፎአልፎም መድረቅ፣ እንሰሳት ወደ ኩሬው መቅረብ፣ ከኩሬዎቹ ውኃ መጠጣት፣ በውኃው ውስጥ መግባትና በውኃው ውስጥ መጸዳዳት፣ አንዳንድ ግለሰቦች በውኃ ኩሬዎቹ አጠገብ ልብስ ማጠብና፣ ሰውነትን መታጠብና የውኃ ማከሚያ ኬሚካል (ውኃ አጋር) የሚጨምሩ ግለሰቦች ቀንም ሆነ ሌሊት በስፍራው አለመገኘት እንዲሁም በቂ የመጸዳጃ ቤቶች አለመኖር በሚፈጥሩት ችግር ምክንያት ተላላፊ የውኃ ወለድ በሽታዎች በሙዳ በዓል ወቅት በስፋት ይከሰታሉ።

በውኃ ወለድ ተላላፊ በሽታ የተጠቃ ግለሰብ በሚፈጥረው የጥንቃቄ ጉድለትና ፈጥኖ ሕክምና ባለመውሰድ ምክንያት በሙዳ በዓል ወቅት የኮሌራ ወይም የአተት (አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት) በሽታ ወረርሽኝ በስፋት ይከሰታል። በወረርሽኝ ሳቢያም በየጊዜው በርካታ ሰዎች ለሕልፈት ተዳርገዋል፤ አሁንም እየተዳረጉ ነው።

የኮሌራ ወረርሽኝ በሽታ በዓል ወቅት በተለያዩ ዓመታት ተከስቷል። ከእነዚህ ዓመታት መካከል እ.ኤ.አ 1976 አንዱ እንደሆነ Braukämper (1977:126) ይገልጻል። በዚህ ወቅት በመካነ ቅርስ በተከሰተ የኮሌራ ወረርሽ ምክንያት ወደ 3,000 የሚገመት ሕዝብ ሕይወቱ ማለፉን Braukämper (1977) ገልጿል። በዚህ ወቅት የተከሰተው የኮሌራ ወረርሽኝ እጅግ ብዙ ሕዝብ ያለቀበት ነው። ይህ ወቅት የ‹‹ኮሌራው ዘመን›› በሚል ይታወቃል። በአሁኑ ወቅትም ያንን ጊዜ ለመግለጽ፣ በመካነ ቅርሱ የተፈጠሩ ታሪኮችን ለመግለጽ የ‹‹ኮሌራው ዘመን›› ወቅት፣

የ"ኮሌራው ዘመን" ካለፈ በኋላ የሚሉ አገላለጾች የተለመዱ ናቸው። የኮሌራው ወረርሽኝ ክስተትም ለአካባቢው ነዋሪና ለመንፈሳዊ ተጓዦች የጊዜ መለያና የታሪክ ማስታወሻ ምክንያት ሆኗል።

የኮሌራ ወረረሽን በቅርብ አመታትም ተከስቶ በርካታ ሰዎችን ለሕልፈት ዳርጓል። ከእነዚህ ዓመታት ውስጥ በ1992 ዓ.ም፣ በ1999 ዓ.ም፣ በ2002 ዓ.ም እና በ2006 ዓ.ም እንደተከሰተና የበርካታ ሰው ሕይወት እንዳለፈ መረጃ ሰጪዎቼ ይገልጻሉ።[168] በመስከረም፣ 2008 ዓ.ም በተከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት አነስተኛ መጠን ያለው የኮሌራ ወረርሽኝ ተከስቶ የ3 ሰው ሕይወት አልፏል። በመጋቢት፣ 2008 ዓ.ም በተከበረው የሙዳ በዓል ወቅት በተከሰተ የኮሌራ ወረርሽኝ የ21 ሰው ሕይወት አልፏል። በእነዚህ ዓመታት የኮሌራ ወረርሽኝ ሲከሰትና በጣም አሳሳኝ ሁኔታ ሲፈጠር እኔ ለመስክ ስራ በስፍራው ነበርኩኝ።

በነሐሴ፣ 2009 ዓ.ም በተከበረው የሙዳ በዓል ላይ የኮሌራ በሽታ ይከሰታል ተብሎ በእጅጉ ተፈርቶ እንደነበር ለመስክ ስራ በመካነ ቅርሱ በነበርኩበት ወቅት አስተውያለሁ። ለዚህም ስጋት መነሻው በመካነ ቅርሱ ዙሪያ በሚገኙ የባሌ፣ የሐረርና የአርሲ ወረዳዎችና በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች የኮሌራ ወረርሽኝ በመከሰቱ ነው። በወቅቱ ወረርሽኝ ይከሰታል ተብሎ ቢፈራም፣ ሳይከሰት በዓሉ በሰላም ተከብሯል። በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከሰትን የኮሌራ ወረርሽኝን ለመከላከል ከባሌ ዞን ጤና ጥበቃ ቢሮ በልዩ ዝግጅትና የጤና ባለሙያዎች ግብረ ኃይል በማቋቋም ወደ መካነ ቅርሱ ይልካል። ግብረ ኃይሉም ከድሬ ሼኽ ሁሴን የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ትልልቅ ደንኳኖችን በመትከል፣ መድኃኒቶችን በማሟላት፣ የውኃ አጋር በማደልና በውኃ መያዣ እቃዎች ውስጥ በመጨመር ከፍተኛ የዘመቻ ስራ ይሰራሉ።

በስፍራው ያለውን የመጠጥ ውኃ ችግር ለመቀነስ በባሌ ዞን የውኃና ፍሳሽ ቢሮ ግብረኃይል በማቋቋም ቅርበት ካላቸው ከተሞች ንጹህ የመጠጥ ውኃ በቦት መኪናዎች በማምጣት ለሕዝቡ ያድላል። በአካባቢው የመጸዳጃ ቤት እጥረት በመኖሩ ነዋሪዎችንና መንፈሳዊ ተጓዦችን ለጤና ችግር ዳርጓል። ይህን ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች በሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ጥቂት መጸዳጃ ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ይህም በአካባቢው የሚከሰተውን የጤና ችግር ለመቀነስ ቢጠቅምም፣ የመጸዳጃ ቤቶች ቁጥር አነስተኛ መሆንና ያሉትንም በአግባቡ አለመጠቀም አሁንም ችግር እየፈጠረ ነው።

---

[168] - አቶ ኑማን ሼኽ መሐመድ፣ አቶ መሐመድ ሰዒድ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 30 ቀን፣ 2008 ዓ.ም።

## 9.1.10 የተለያዩ አካላት ያላቸው የግል ፍላጎት

የተለያዩ የኃይማኖት ክፍሎች ባላቸው የአስተምህሮ ልዩነት ምክንያት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በሙዳ በዓላት ላይ አሉታዊ አመለካከለት አላቸው፡፡ ይህ አመለካከትም የራሱን ተግዳሮት እንደፈጠረ ቀደም ሲል አይተናል፡፡ እነዚህ አካላት ያላቸውን አሉታዊ አመለካከለት በሙዳ በዓላት ላይ ለማንጸባረቅ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች መካከል በኢትዮጵያ እስልምና ጽ/ቤት (መጅሊስ) ውስጥ በሚሰሩ የሰለፊያ አስተምህሮ አራማጆችና በሌሎች አካላት አማካኝነት በመካነ ቅርሱ አዳዲስ መስኪዶችን በመገንባት፣ የኃይማኖት መምህራንን በመላክና የኃይማኖት መጽሐፍትን በስጦታ በመስጠት እነሱ የሚፈልጉት አስተምህሮ እንዲስፋፋ ጥረት የማድረግ እንቅስቃሴ አለ፡፡ ለዚህ እንቅስቃሴ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ 15 መስኪዶች መካከል 4ቱ በእነዚህ አካላት አማካኝነት ከአስር ዓመት ወዲህ መገንባታቸው አንዱ ማሳያ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቼ ይገልጻሉ፡፡[169]

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎች የሙዳ በዓልን የኦሮሞ ብሔር ባህላዊና ኃይማኖታዊ ስርዓት አድርገው እንደሚወስዱት መረጃ ሰጪዎቼ ይገልጻሉ፡፡[170] በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከበሩ የሙዳ በዓላትን የራስን ፍላጎትና ማንነት ለመጫን የሚደረግ ጥረት የራሱን ተግዳሮት ፈጥሯል፡፡ ይህ አይነት አመለካከት በመካነ ቅርሱ ላይ ጥናት ባደረጉ አንዳንድ ምሁራን ስራ ውስጥ በግልጽ ይታያል፡፡ ይህ አመለካከትም የሙዳ በዓልን በራሱ ያለው ባህርይ እንዳይጠና ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከሰት የኮሌራ ወረርሽን አለ፡፡ የወረርሽኙ መከሰቻ ምክንያቶች መካከል አንዱ ንጹህ የመጠጥ ውኃ በአካባቢው አለመኖር ነው፡፡ በባሌ ዞን የጤና ቢሮ ባለሙያዎች አማካኝነት ሕዝቡ የሚጠጣውን የኩሬ ውኃ በኬሚካል የማከም ስራ ይሰራል፡፡ ውኃ የማከም ስራ በሚሰሩ አንዳንድ የዞን የጤና ቢሮ ባለሙያዎች በሙዳ በዓላት ወቅት የራሳቸውን የግል ፍላጎት የሚገልጹ ድርጊቶችን ይፈጽማሉ፡፡ ከእነዚህ ድርጊቶች መካከል የሀሮ ሉኩን ዘምዘም አትጠጡ ወይም የውኃ አጋር ጨምሩበት የሚሉ ቅስቀሳዎች እንደሆኑ መረጃ ሰጪዎቼ

---

169 - አቶ አብልዱናስር አህመድ፣ መጋቢት 29፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

170 - አቶ ነስሩዲን ሼኽ ቃሲም፣ መስከረም 9 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ይገልጻሉ፡፡[171] የሀሮ ሉኩ የውኃ ኩሬን ውስጥ የሚገኘውን ዘምዘም (ቅዱስ ውኃ) የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎችና መንፈሳዊ ተጓዦች ከተለያዩ ሕመሞች እንዲፈውሳቸው ይጠቀሙበታል፡፡

ይህን ዘምዘም በውኃ ማከሚያ ኬሚካል በመጨመር መንፈሳዊ ተጓዦችና ነዋሪዎች እንዲጠጡ ማሰብ፣ መምከርም ሆነ በድርጊቱ መሳተፍ አንድም የሰዎቹን እምነት ማንቋሸሽ ሲሆን፣ አንድም የግል ፍላጎትንና አጀንዳን ለማስፈጸም መጣር ነው፡፡ በደርግ ዘመን በዘምዘም ውስጥ የውኃ ማከሚያ ኬሚካል ለመጨመር የተደረገውን ሙከራ አይቻለው የሚሉትን ልዩ ገጠመኝ መረጃ ሰጪዬ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> በደርግ ዘመን ነው፡፡ በሙዳ በዓል ወቅት የውኃ ወለድ በሽታ ይከሰታል፡፡ ይህንን በሽታ ለመከላከልም በዶ/ር አዳነ የሚመራ የጤና ጥበቃ ቡድን ከጎባ ከተማ ሆስፒታል ይመጣል፡፡ ቡድኑም ሕዝቡ የውኃ አጋር ኪኒን እንዲጠቀም ይወስናል፡፡ ዶ/ር አዳነ ሕዝቡ ለጸበል በሚጠቀምበት ሀሮ ሉኩ ውስጥ ሊጨምር ሲል፣ ምን ይውሰደው፣ ወዴት ይሂድ ሳይታወቅ ይጠፋል፡፡ በአካባቢው ቢፈለግ ቢፈለግ ይጠፋል፡፡ በሳምንቱ ኢተያ (በአርሲ ዞን ውስጥ የሚገኝና ከመካነ ቅርሱ በግምት 320 ኪ.ሜትር ርቀት ያለው ከተማ ነው፡፡) ተጥሎ ተገኘ፡፡ እሱም መንፈስ እንደወሰደው ተናገረ፡፡ ዶ/ር አዳነ ኢተያ በተገኘ በሳምንቱ ሞተ፡፡[172]

ይህን መሰል ድርጊቶች ማህበረሰቡ ሳይታወቅ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት የሚደረግ ጥረትን ያሳያል፡፡ ይህ ገጠመኝም አንድም፣ ማህበረሰቡ ያለውን ባህል፣ ኃይማኖትና እምነት መሰረት በማድረግና በማክበር እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላትን በማሳተፍ የአካባቢውን ችግር መፍታት እንደሚገባ ያሳያል፡፡ አንድም፣ ተመሳሳይ ድርጊት በሚፈጽሙ ግለሰቦች ላይ ከፍተኛ አደጋ እንደሚደርስባቸው በመግለጽና በኩሬው የሚገኘውን ዘምዘም ያላከበረ ክፉ ነገር ይደርስባቸዋል ተብሎ እንዲታመን አስተዋጾ ያደርጋል፡፡

---

171 - አቶ ኑማን ሼኽ መሐመድ፣ ጥቅምት 29 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

172 - አቶ አብዱልናስር አህመድ፣ መጋቢት 29፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

## 9.2 በሙዳ በዓላት ላይ ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶች

የሙዳ በዓላት መቼ፣ ለምን እና እንዴት መከበር እንደተጀመሩ የተለያዩ መላምቶች እንደሚቀርቡ በምዕራፍ ሁለት ተመልክተናል። ስለሙዳ በዓላት አጀማመር ከሚቀርቡ ከእነዚህ መላምቶች ውስጥ ትክክለኛው ምክንያት በግልጽ አይታወቅም። በአሁኑ ወቅት በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩት የሙዳ በዓላት የመጀመሪያው የኢድ በዓልን ምክንያት በማድረግ የሚከበር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የሼኽ ሁሴንን የውልደት ቀን ለማሰብ የሚከበር ነው።

የሙዳ በዓል መቼ እንደተጀመረ በትክክል አይታወቅም። በመሆኑም በሙዳ በዓላት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶችን በትክክል ለመግለጽ አዳጋች ነው። ይህ አዳጋችነት እንዳለሆኖ በሙዳ በዓላት ላይ ለውጥ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁነቶችን በመካነ ቅርሱ ላይ ለውጥ ከፈጠሩ ሆነቶች ጋር በማያያዝ መተንተን አንዱ መንገድ ነው። ይህ መንገድ በቅርሱና በአካባቢው ላይ የተከሰቱ ሁነቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሙዳ በዓላት ጋር ይገናኛሉ የሚል ሃሳብን መነሻ በማድረግ ነው። በዚህ መነሻነት በሙዳ በዓል ላይ ለውጥ የፈጠሩ ሁነቶችን ቀጥለን እንመልከት።

### 9.2.1 የመካነ ቅርሱ የቦታ ለውጥ

ሼኽ ሁሴን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስገነቡት የባላ መስኪድን ነው። በዚህ መስኪድም በርካታ ተማሪዎችን አስተምረውበታል። የተለያዩ መንፈሳዊ ድርጊቶችን ፈጽመዋል። የሙዳ በዓል አጀማመር ላይ ከሚነገሩ መላምቶች መካከል፣ ከሼኽ ሁሴን ዘንድ በቋሚነት ተቀምጠው ለሚማሩ ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸው ስንቅ ይዘውላቸው በዓመት ሁለት ጊዜ ወደ ስፍራው ከሚያደርጉት ጉዞ እና ሼኽ ሁሴን የተወለዱበትን ቀን ከማሰብ ጋር የሚያያዙ ናቸው። በዚህ መላምት መሰረት የሙዳ በዓል መነሻ የሆኑ ድርጊቶች በወቅቱ ይከወኑ ነበር። ምክንያቱም በባላ መስኪድ በርካታ ተማሪዎች ይማሩ ስለነበር ነው። ይህ ደግሞ በወቅቱ የሙዳ በዓልን የሚመስል የመሰባሰቢያና የመገናኛ ወቅቶች እንደነበሩ መገመት ያስችላል።

ሼኽ ሁሴን የባላ መስኪድን ለቀው የዙቅጡም መስኪድን ገነቡ። በዚህም ምክንያት የኃይማኖት ማዕከሉን ከባላ መስኪድ ወደ ዙቅጡም መስኪድ አካባቢ እንዲቀየር ሆነ። የባላ መስኪድ ከድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ 9 ኪ. ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ሼኽ ሁሴን ለምን የባላ መስኪድን በመተው የዙቅጡምን መስኪድ እንደገነቡ በትክክል አይታወቅም። የባላና የዙቅጡም መስኪዶች መቼ እንደተገነቡ በትክክል ባይታወቅም፣ በቃል የሚነገሩ ታሪኮችን መሰረት በማድረግ የባላ

መስኪድ ከተገነባ 980 አመት እንደሆነው ይገመታል፡፡ የዙቅጡም መስኪድ ደግሞ ከተገነባ 950 አመት እንደሆነው ይገመታል፡፡

በእነዚህ ግምቶች መነሻነት ሼኽ ሁሴንና ተከታዮቻው የባላ መስኪድን ለ30 ዓመታት ያህል ተጠቅመውበታል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥም ስፍራው ለሙዳ በዓል መጀመር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ተከውነውበት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሼኽ ሁሴን ማዕከላቸውን ከባላ ወደ ዙቅጡም መስኪድ ሲቀይሩ የሙዳ በዓላት ይከበርበት የነበረው ስፍራም ከባላ ወደ ዙቅጡም መስኪድ መገኛ አካባቢ ተቀይሯል ማለት ነው፡፡ ይህ መሆኑ ምናልባት በሙዳ በዓል ላይ ለውጥ ከፈጠሩ ምክንያቶች መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

## 9.2.2 የሼኽ ሁሴን ውልደትና ሕልፈት

የሙዳ በዓላት አጀማመር ላይ ከሚነገሩ መላምቶች መካከል ሼኽ ሁሴን የተወለዱበትንና የሕልፈታቸውን ቀናት ከማሰብ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን በየካቲት ወር ማክሰኞ ዕለት እንደተወለዱና በነሐሴ ወር ማክሰኞ ዕለት እንዳረፉ ይታመናል፡፡ የእሳቸውን የውልደትና የሕልፈት ቀናትን ለማሰብም በአመት ሁለት ጊዜ ወደ ስፍራው ይኬድ ነበር፡፡ ይህ ጉዞም ተጠናክሮ ለሙዳ በዓላት መከበር ምክንያት እንደሆነ ይነገራል፡፡ በዚህ መላምት መነሻነት የሼኽ ሁሴን ውልደት ለመካነ ቅርሱ መመስረት፣ መጠናከርና የሙዳ በዓልም በስፍው እንዲከበር መሰረት የጣለ ነው፡፡

የሼኽ ሁሴን ሕልፈት የሙዳ በዓል እንዲጀመርና በአሁኑ ወቅት በሙዳ በዓላት ለሚከወኑ የተለያዩ ስርዓተከበራዎችና መንፈሳዊ ሙዚቃዎች መጀመር ምክንያት ሆኗል፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት የሼኽ ሁሴን የመቃብር ስፍራ እንደሆነ በሚታመነው ቦታ የተገነባን ገሞን መዘየር እንዲሁም ስፍራው የእሳቸው መንፈስ አለበት ተብሎ እንዲታመን ምክንያት ሆኗል፡፡ የሼኽ ሁሴን ሕልፈት በተሰማ ወቅት፣ የእሳቸው የቅርብ ወዳጅ የነበሩት ሼኽ ሶፍዑመር የእሳቸውን መንፈሳዊነት፣ ተዓምራት፣ ስነ-ምግባርና ሰብዕና በዜማ መልክ ለአፍቃሪዎቻቸው እንዳቀረቡ ይነገራል፡፡

ይህ የሼኽ ሶፍዑመር ዜማ በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ የሚቀርበው የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃም የሼኽ ሁሴን ሕልፈትን ምክንያት በማድረግ የተጀመረ እንሆነ የሚታመንና እስካሁንም በሙዳ በዓላት ላይ የሚከወን ነው፡፡ ከሼኽ ሁሴን

ውልደትና ሕልፈት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ጉዳዮች የሙዳ በዓላት እንዲጀመሩና በበዓላቱ ላይ ለተፈጠሩ ለውጦች መነሻ ምክንያት ከሆኑ ሁነቶች መካከል በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## 9.2.3 መካነ ቅርሱ የነባር ሕዝቦች የኃይማኖት ማዕከል መሆን

ከሼኽ ሁሴን ሕልፈት በኋላ የኃይማኖት ማዕከሉን ልጃቸው ኑርላህ አህመድ ተረክበው ይመሩ ነበር። በኑርላህ አህመድ ዘመን በአካባቢው ከፍተኛ ረሃብ ተከስተ።[173] በረሃቡም ምክንያት በስፍራው ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች አካባቢውን ጥለው ወደ ትውልድ አገራቸው ተመለሱ። ተማሪዎቹም ወደ ትውልድ አገራቸው በመመለሳቸው ስፍራው የትምህርት ማዕከልነቱ ሙሉለሙሉ ተቋረጠ። በረኃብ ምክንያት የመካነ ቅርሱ የኃይማኖት ማዕከልነት ለ400 ዓመታት ያህል ተቋረጠ።

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ መካነ ቅርሱ የነበረው አገልግሎትና ታሪክ በትክክል አይታወቅም። በእነዚህ ዓመታት መካነ ቅርሱ የነበረበት ሁኔታ በትክክል ባይታወቅም ስፍራው በአካባቢው የነበሩ ሕዝቦች ይዞታና የኃይማኖት ማዕከል እንደነበር ይነገራል። እነዚህ ነባር ሕዝቦች ከሼኽ ሁሴን ውልደት በፊት በአካባቢው እንደነበሩም ይገመታል።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አካባቢና በባሌ ዞን በሚገኙ አጎራባች አካባቢዎች የዋቄፈና፣ የእስልምናና የክርስትና ኃይማኖቶች ከመስፋፋታቸው በፊት የተለያዩ ሕዝቦች ይኖሩ ነበር። እነዚህ ሕዝቦች በወቅቱ ምን አይነት ኃይማኖት ይከተሉ እንደነበር በግልጽ ባይታወቅም የራሳቸው ኃይማኖት እንደነበራቸው ግን መገመት ይቻላል። በአካባቢው የሚገኙ ዋና ዋና ኃይማኖቶች ከመስፋፋታቸው በፊት የነበሩ ሕዝቦች እነማን እንደነበሩ የሚገልጹ በቂ ጥናቶች የሉም። ነገር ግን የተወሰኑ ጥናቶች በአካባቢው የተለያዩ ሕዝቦች ይኖሩ እንደነበር ፍንጭ ይሰጣሉ።

በኢትዮጵያ ደቡባዊ ጠረፍና በስምጥ ሸለቆ ዝቅተኛና ከፍተኛ ቦታዎች በጥንት ዘመን በተለያዩ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደቡ ቋንቋዎች የሚነገሩበት ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ቋንቋዎች በአሁኑ ወቅት ጠፍተዋል (Østebo, 2012:46)። በወቅቱ በአካባቢው ይነገሩ የነበሩ ቋንቋዎች በሴሜቲክና በኩሽቲክ የቋንቋ ቤተሰቦች የሚመደቡ ናቸው። ከሰሜቲክ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ቋንቋ

[173] - አቶ አብዱልናስር አህመድ፣ መጋቢት 29 ቀን፣ 2008 ዓ.ም።

ይናገሩ የነበሩት ሀበሻ[174]፣ ዛንጅና ሀርላ በሚሉ ስያሜዎች የሚታወቁ ሕዝቦች ናቸው (Taddesse, 1977: 134)።

"ሀበሻ- ሀበሽት" የተሰኘው የሕዝብና የአካባቢ ስያሜ ጥንታዊያን ግብጾች በቅድመ ክርስትና ከሶስት ሺሕ ዘመናት በፊት መዝግበውት የተገኘና ግዙፍ ቋጥኞች፣ ትክል ድንጋዮችና ሐውልች በሚስተዋሉበት የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ አካባቢ መጠሪያነት ሲሆን ስያሜው የአካባቢውን ነባር ሕዝቦች በሙሉ መጠሪያ ነበር (ብሩ፣2008 ዓ.ም፡109-110)። "ዛንጅ" የተሰኘው ስያሜ ፐርሺያዊያን ለደቡብ ምስራቅ አፍሪካ ምድርና በአካባቢው ለሚኖሩ ለነባር ሕዝቦች የሰጡት ስያሜ ሲሆን፣ "ጥቁር" የሚል መልዕክት ያለው ስያሜ እንደሆነ ብሩ (2008 ዓ.ም፡275-276) ይገልጻል።

የሀርላ ሕዝብ በሐረርና በባሌ ውስጥ ይኖሩ እንደነበር የሚገልጹ ጥቂት ማስረጃዎች አሉ። ሐርላዎች በግንባታ ስራ የታወቁ እንደነበር ይነገራል። የሀርላዎች ግንባታ እንደሆኑ ከሚነገሩት መካከል በሐረር የሚገኝ የሐርላዎች መስኪድ ፍርስራሽ ሕንጻ አለ (Chernet, 1990፡315)። በ2009 ዓ.ም በድሬደዋ ከተማ አካባቢ ደንገጎ በሚባል ስፍራ በ8ኛው መቶ ክ/ዘመን በሀርላዎች የተገነባ ኪነሕንጻ በቁፋሮ ተገኝቷል። ይህ ግኝት ሕዝቡ የነበረውን የሕንጻ ሙያና የአኗኗር ሁኔታ ጠቋሚ ነው።

የሀርላ ሕዝብ በባሌ ዞን ውስጥ ይኖር እንደነበር ከሚያሳዩ ማስረጃዎች መካከል ኦዳ ሮባ በሚባል ቦታ ሀርላዎች እንደሰሯቸው የሚነገር ፍርስራሽ የኪነህንጻ ቅሪቶች መኖራቸውን Østebo (2012:47) ይገልጻል። ሼኽ ሁሴን እንዳስገነቧቸው የሚነገረውን የባላና የዙቅጡም መስኪዶች ሀርላዎች በባለሙያነት በመሳተፍ እንደገነቡት ይነገራል።[175] በአሁኑ ወቅትም በመካነ ቅርሱ አካባቢ በሀርላ ሕዝቦች እንደተገነቡ የሚነገር የኪነሕንጻ ፍርስራሾች አሉ። ከእነዚህ በተጨማሪ የመካነ ቅርሱ መገኛ ከሆነው ጎሎልቻ ወረዳ አጎራባች በሆኑት የቤልቱና የራይቱ ወረዳዎች ውስጥ በሀርላ ሕዝቦች እንደተገነቡ የሚነገሩ ፍርስራሽ ኪነ ሕንጻዎች አሉ።

በኩሽቲክ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ቋንቋ የነበራቸው ሕዝቦች በባሌና አካባቢው ይኖሩ ነበር። ከእነዚህ ሕዝቦች መካከል ሱማሌ፣ ሀዲያና ሲዳማ እንደሆኑ Taddesse (1977) እና Braukämper (2004) ይገልጻሉ። ከእነዚህ ሕዝቦች መካከል በባሌ ዞን ቀደምት ነዋሪዎች ሲዳማዎች እንደነበሩ

---

[174] -ሀበሻ ራሳቸውን የቻሉ ሕዝቦችን የሚገልጽ ስያሜ ነው። ይህ ስያሜ በኢትዮጵያ ሀበሻ በሚል ይጠሩ ከነበሩ ሕዝቦች ጋር መገናኘት አለመገናኘቱ ጥናት የሚጠይቅ ነው።

[175] - አቶ ኑማን ሼኽ መሐመድና አቶ መሐመድ ሰዒድ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም።

Trimingham (1952:67)፣ Cerulli (1971:412) እና Merid (1971:47) ይገልጻሉ፡፡ በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ይኖሩ የነበሩት ቀደም ሕዝቦች ሀርላ፣ ኢቱ፣ ዋው፣ ጋርጃዳ፣[176] ጋዱላና ከረዩ ነበሩ (Areba and *et al*, 2003:14)። በሼኽ ሁሴን ላይ ከሚነገሩ ሚቶች መካከል የኢቱና የሀርላ ሰዎችን በመርገም ወደ ድንጋይነት እንደለወጧቸው ይነገራል፡፡ ይህ ሚት የኢቱና የሀርላ ሕዝቦች በአካባቢው ይኖሩ እንደነበር ጥቆማ ይሰጣል፡፡

ከ16ኛው መቶ ክ/ዘመን የኦሮሞ እንቅስቃሴ በፊት በአናጂና ቀበሌና አካባቢው የኦሮሞ ሕዝብ ይኖር እንደነበር የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መረጃዎች መካከል አንደኛ፣ የሼኽ ሁሴን እናት የሆኑት ሽምሲያ በባሌ ዞን ጊንር ወረዳ የተወለዱ ኦሮሞ ናቸው የሚል ነው (Gemechu, 2013:68)። አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቼም በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ፡፡[177] ሁለተኛ፣ የሼህ ሁሴን ቤተሰቦች ወደ ስፍራው በመጡበት ወቅት በስፍራው ዋው፣ ጋርጃዳ፣ ጋዱላና ከረዩ የተባሉ የኦሮሞ ጎሳዎች ይኖሩ ነበር (Areba and *et al*, 2013:14)።

ሶስተኛ፣ ሼኽ ሁሴን አስተምረዋቸው በመጀመሪያ እስልምናን የተቀበሉት የአካባቢው ነዋሪዎች ‘ፓኒጋል’ የተባሉ የኦሮሞ ጎሳዎች መሆናቸውን Feyisa (1998:157) Paulitschike (1889)ን በመጥቀስ ይገልጻል፡፡ አራተኛ፣ ሼኽ ሁሴን ስፍራውን ወደ ኃይማኖታዊ ስፍራ ሲቀይሩት የቦታው ባለቤት የነበረው ድሬ እንደነበር ይነገራል፡፡ የሰውዬው ስም እንዳይጠፋ በሚል ሼኽ ሁሴን ስፍራውን ድሬ ብለው መሰየማቸው ይነገራል፡፡ ድሬ የሚባለው ሰው በአካባቢው ይኖር የነበረ የአርሲ ኦሮሞ ጎሳ ተወላጅ መሆኑን መረጃ ሰጪዎቼ ገልጸውልኛል፡፡[178]

አምስተኛ፤ ሼኽ ሁሴን የኢቱ ጎሳ አባላትን በመርገም ወደ ድንጋይነት መለወጣቸውን የሚገልጽ ሚት አለ፡፡ በኦሮሞ ሚት መሰረት 10 የኦሮሞ አብይ ጎሳዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ ኢቱ እና ሁምባና ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም ኢቱ በአርሲ፣ በሐረርና በከረዩ የሚገኝ የኦሮሞ ጎሳ ስያሜ ነው፡፡ ስድስተኛ፣ ሼኽ ሁሴን እራሳቸው የኦሮሞ ብሔር ተወላጅና በወቅቱ የገዳ አባል እንደነበሩ Hussein (2008 ዓ.ም፡43) ይገልጻል፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና ኃይማኖት ማዕከልነቱ ሲቋረጥ፣ በአካባቢው ነባር ሕዝብ የኃይማኖት ማዕከል ሆነ፡፡ በኦሮሞ ብሔር ኃይማኖት ከባሌ ዞን መደወላቡ አካባቢ

---

176 - ጋርጃዳ፣ የጉጂ ኦሮሞ ሌላ ስም ነው፡፡
177 - አቶ ዑስማን ከዲር፣ ሼኽ ሰይፈዲን ሐጂ ኡስማን፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 29፣ 2007 ዓ.ም፡፡
178 - አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ ሼኽ አልይ ሼኽ መሃመድና አቶ ዑስማን ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ ጥቅምት 29፣ 2007 ዓ.ም፡፡

በስምንት ዓመት አንዴ ይደረግ የነበረው የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን እንዲካሄድ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ማዕከሉ ድጋሚ ሲቋቋም፣ የዋቄፈና ኃይማኖት የሙዳ ጉዞ ሲዳከምና እስልምና ኃይማኖት በአካባቢው ሲጠናከር፣ አንዳንዶቹ ወደ መደወላቡ የሚደረገውን መንፈሳዊ ጉዞ ሲቀጥሉ አንዳንዶች ደግሞ መንፈሳዊ ጉዞ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ማድረግ መጀመራቸው Temam (2002፡13)፣ Umer (2006፡60)፣ Abbas (2014፡179) እና Mohamed (2015፡36) ይገልጻሉ፡፡

በዚህም ምክንያት በሙስሊም ኦሮሞዎች ዘንድ ወደ ሼኽ ሁሴን የሚደረግ ጉዞ የአባ ሙዳ ጉዞ ቀጣይ ተደርጎ መታሰብ እንደጀመረ Trimingham (1952፡256) ይገልጻል፡፡ ከእነዚህ መረጃዎች በተለየ ደግሞ ሼኽ ሁሴን ከቅዱስ ተክለኃይማኖት ጋር መገናኘታቸውን ዳንኤል (1984 ዓ.ም፣2) ይገልጻል፡፡ እንዲሁም መካነ ቅርሱ አቡነ አኖሪዎስ ትልቁ የመሰረቱት ገዳም እንደነበር ዳንኤል (2006 ዓ.ም፡336) ይገልጻል፡፡

ከላይ ከቀረቡ ሀሳቦች በመነሳት በባሌ ዞን ውስጥ እንዲሁም በአናጂና ቀበሌና አካባቢው ይኖሩ የነበሩ ነባር ሕዝቦች ሀርላ፣ ዛንጅ፣ ሀበሻ፣ ሲዳማ፣ ሀዲያ፣ ሱማሌ፣ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ኢቱ፣ ዋው፣ ጋዱላ፣ ጋርጃዳ፣ ከረዩ፣ ፓኒጋል እንዲሁም አረቦች (የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦችን ጨምሮ) ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ ምናልባት ትክክለኛ ታሪክ ከሆነ እነዚህ እያንዳንዳቸው ሕዝቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሼኽ ሁሴን፣ ከእሳቸው ተማሪዎች ወይም ከመካነ ቅርሱ ጋር በአንድም ወይም በሌላም መንገድ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ ይህ ከሆነ በመካነ ቅርሱ ላይ የራሳቸውን አሻራ እንዲያሳርፉ ምክንያት ነው፡፡ ምናልባትም እንደነዚህ አይነት ታሪካዊ አጋጣሚዎች በመከሰታቸው ይመስላል በሙዳ በዓል ላይ የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓተከበራዎች የውሕደት ባህርይ እንዲኖራቸው ምክንያት የሆነው፡፡

## 9.2.4 የመካነ ቅርሱ የኃይማኖት ማዕከልነት ድጋሚ መጠናከር

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ለ400 ዓመታት ያህል ተቋርጦ የነበረው የእስልምና ኃይማኖት ማዕከልነቱ በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ላይ ድጋሚ ተጠናከረ፡፡ ለማዕከሉ ድጋሚ መጠናከር ዋናው ምክንያት ሼኽ መሐመድ ቲልማ ቲልሞንና ሼኽ አባስን በ1790ዎቹ የሐረሩ ንጉስ አሚር አብዱል ሽኩር (1783- 1794) ወደ አናጂና በመላካቸው ነው Braukämper (2004:138)፡፡ ሼኽ መሐመድና ሼኽ አባስ በአሁኑ ወቅት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ

የሚገኙትን የተለያዩ ኪነሕንጻዎች በመገንባትና የተለያዩ ስርዓቶችን በመጀመር ስፍራው ድጋሚ የእስልምና ኃይማኖት ማዕከል እንዲሆን አድርገዋል።

እነሱም ወደ ስፍራው መጥተው በርካታ ገሞዎችን፣ መስኪዶችና ጎምቢሶዎችን ገንብተዋል። በወቅቱ የገሞዎቹን ዲዛይን የሰሩትና ግንባታውን በበላይነት ይቆጣጠሩ የነበሩት ሀዲስ የተባሉ ባለሙያ እንደሆኑ ይነገራል። ከሼኽ መሐመድና ከሼኽ አባስ ጋር በመሆን ኪነሕንጻዎቹን የገነቡ በርካታ የአካባቢው ሰዎች አሉ።

## 9.2.5 አንዳንድ የሙዳ ስርዓተከበራዎች መጀመር

ሼኽ መሐመድ ከኪነሕንጻ ግንባታዎች በተጨማሪ በመካነ ቅርሱ የኢማም አስተዳደር በመመስረት፣ ለአምስት ልጆቻቸው የተለያየ የኃላፊነት ስልጣን በመስጠት፣ የጀዋራ ቅዱስ አፈርን እንዲቀደስና ለመድኃኒትነት እንዲያገለግል ማድረጋቸው ይነገራል። ሼኽ መሐመድና ሼኽ አባስ የድሬ ሼኽ ሁሴንን መካነ ቅርስ ድጋሚ በማቋቋማቸው ምክንያት የመካነ ቅርሱ አስተዳደር፣ የአካባቢውን ኪነሕንጻዎች ግንባታና የጀዋራ ቅዱስ አፈርን ለመንፈሳዊ ተጓዦች መፈወሻ በማድረግ የሙዳ በዓልና ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ቅርጽ እንዲይዝና እንዲጠናከር መሰረት ጥለዋል። ለዚህ አስተዋጾም በስማቸው የተሰየሙ መስኪዶችና አንድ አደባባይ በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ ይገኛሉ።

ከ19ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ሐጂ አደም በክፉ መንፈስ የተያዙ ግለሰቦችን የመፈወስ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት ጀመሩ። በዚህም አገልግሎታቸው ምክንያት በመካነ ቅርሱ የራሳቸውን ሀድራ በስፍራው ጀመሩ። ሀድራው ከተጀመረ በግምት 70 አመት ይሆነዋል። ይህም አጋጣሚ በመካነ ቅርሱ አዲስ ሀድራ እንዲጀመር፣ አዲስ የሹቢሳ መንፈሳዊ ሙዚቃ እንዲጀመርና አዲስ የሀድራ ስርዓተከበራ እንዲጀመር ምክንያት ሆኗል። የዛሬ 50 ዓመት ገደማ የመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ ዙሪያ አጥር መገንባቱ፣ በአጥሩ ዋና የመግቢያ በር (ከራ ጉዶ) እና በድንኩሬ ላይ የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓተከበራዎች እንዲጀመሩ ምክንያት ሆኗል። ይህም አጋጣሚ በመካነ ቅርሱ በሙዳ በዓላት ወቅት አዲስ ስርዓተከበራዎች ከመጀመር አንጻር የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

በሙዳ በዓላት ላይ ካለፉት 10 አመታት ወዲህ የተጀመሩ አዳዲስ ስርዓተከበራዎች አሉ፡፡ እነዚህ ስርዓተከበራዎችም የዳካ ዳባ ዋሬና የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃ ናቸው፡፡[179] በሙዳ በዓል ወቅት የዋሬ ስርዓት የሚከወንባቸው ቦታዎች በዶቆ ከራና በዶቆ ድንኩሬ ስፍራዎች ነበር፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ የዳካ ዳባ ዋሬ ተጀምሯል፡፡ ይህ ዋሬ የሼኽ ጃርሶ ዋሬ በሚል ስያሜም ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ዋሬው የሚከወነው በመካነ ቅርሱ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ላይ ባለ ሜዳ ላይ ነው፡፡ ዋሬው የሚከወነው ቀን ቀን ብቻ ነው፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ የተጀመረው ሌላው ስርዓተከበራ የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃን በሙዳ በዓላት ወቅት መከወን ነው፡፡ የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃ በመካነ ቅርሱ የመውሊድ በዓል ሲከበር የሚቀርብ እንጂ በሙዳ በዓላት ላይ አይታወቅም ነበር፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ በሙዳ በዓላት ወቅት ምሽት ላይ በዶቆ ከራ ዋሬ ፊት ለፊት በሚገኝ ሜዳ ላይ የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃ መከወን ተጀምሯል፡፡ የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃ የሚከውኑ ግለሰቦችም በመጽሐፍ (በኪታብ) ላይ የተጻፈን የኦሮምኛ የመንዙማ ግጥምን በማንበብ በህብረት በዜማ ያቀርባሉ፡፡ የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም አዝማች የሚከተለው ነው፡፡[180]

Sallala Allah Mohammed

Saydi sallala Allah Mohammed

Saydi Allah Mohammed.

ትርጉሙም፤-

መሐመድ (ነብዩ) እንወድዎታለን፣ አላህ ወዶዎታልና፡፡

መሐመድ (ነብዩ) እናከብሮዎታል፣ አላህ አክብሮዎታልና፡፡

ማለት ነው፡፡ የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃ ቅኝት "ትዝታ ሜጀር" ነው፡፡ የመንፈሳዊ ሙዚቃው ስኬል በኖታ ምልክት የሚከተለው ነው፡፡



በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃን የሚያቀርቡ ግለሰቦች በአብዛኛው ገሪባዎች ናቸው፡፡ የገሪባዎችን መንዙማ ከቅርጽ፣

[179] - ሼኽ መሐመድ ሼኽ ኢድሪስ፣ ሼኽ ኢብራሂም ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 28 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡
[180] - በመካነ ቅርሱ የመንዙማ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሲከወን የተወሰደ፡፡

ከአገልግሎትና ከይዘት አንጻር Berhanu (2016) አጥንቷል፡፡ በጥናቱም የገሪባዎች መንዙማ ከቅርጽ አንጻር በዜማ፣ በድግግሞሽና በምት የሚቀርብ ቃላዊ ግጥም መሆኑን፣ ከአገልግሎት አንጻር ለጸሎት፣ ለምርቃትና ለውደሳ የሚቀርብ መሆኑን እንዲሁም ከይዘት አንጻር አላህን፣ ነብዩ መሐመድንና ሼኽ ሁሴንን የሚያወድሱበት እንዲሁም በአብዛኛው ኃይማኖታዊ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

## 9.2.6 የጣሊያን ወረራ

የጣሊያን መንግስት አገራችንን በወረረበት ወቅት ሕዝቡን ለመከፋፈል የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀም ነበር፡፡ ጣሊያን ከተጠቀማቸው የመከፋፈያ ስልቶች መካከል በኢትዮጵያ በነበሩት የመንግስት ስርዓቶች ወቅት ትኩረት አልተሰጣቸውም ለሚላቸው የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ለሆኑ ወገኖች ልዩ ድጋፍና የተሻለ ቦታ መስጠት ነበር፡፡ ይህ የጣሊያን የፖለቲካ ስልት ውጤታማ እንዲሆን ትኩረት ከተደረገባቸውና ልዩ ድጋፍ ከተሰጣቸው ቦታዎች መካከል የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አንዱ ነው፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅትም ባሌ በሁለት ኮሚሳራትና በስድስት ዲስትሪክት ተደራጀ፡፡ ስድስቱ ዲስትሪክቶች መካከል ሼኽ ሁሴን አንዱ ነበር (Mindaye, 2005፡72)፡፡

በወቅቱ የድሬ ሼኽ ሁሴን ኢማም የነበሩት ኢማም መሃመድ ሰዒድ ደግሞ የባሌ ኢማም በመሆን ተመረጡ፡፡ በጣሊያን መንግስትና በድሬ ሼኽ ሁሴን አስተዳዳሪዎች መካከል የተጀመረው መልካም ግንኙነት እየተጠናከረ በመምጣቱ የጣሊያን መንግስት ለድሬ ሼኽ ሁሴን አስተዳዳሪዎች ወደ ጣሊያን አገር ሮም ከተማ ለአገር ጉብኝት ሄዱ፡፡ ከጣሊያን ጉብኝት በኋላ በተደረገው ስምምነት ከጻራ ከተማ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ድረስ ጥርጊያ የጠጠር መንገድ በጣሊያን መንግስት ወጪ ለመስራት የተደረገው ስምምነት አንዱ ነበር፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅት የድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ በዓል በጣሊያን መንግስት ደረጃ እውቅና ተሰጥቶት ነበር፡፡ በበዓላት ወቅትም የራይቱና የሱዴ ሱልጣኔት መሪዎች እራሳቸው በመካነ ቅርሱ ይገኙ ነበር፡፡

ይህ በጣሊያን ወራሪ ኃይልና በመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች መካከል የተጀመረው ወዳጅነት የሙዳ በዓላትን ለማክበር ወደ መካነ ቅርሱ የሚሄዱ ሰዎችን በሁለት ጎራ ከፈለ፡፡ አንደኛው ጎራ የጣሊያንን ወረራ ከሚደግፉት የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች ጋር ወገነ፡፡ ሁለተኛው ጎራ ደግሞ የጣሊያንን ወረራ የሚቋወምና የመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎችን ድርጊት የሚቃወም ነበር፡፡

ይህ የሁለት ጎራ ሙግት በሙዳ በዓላት ወቅት በሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ላይም መንጸባረቅ ጀመረ፡፡ ከእነዚህ ነጸብራቆች መካከል የጣሊያንን ወረራ የሚደግፈው ጎራ በሙዳ በዓላት ወቅት የሞሶሎኒ መንግስት አገሪቱን መግዛት ያለውን ጥቅም በመግለጽ፣ ለሞሶሎኒ የጣሊያን መንግስት ምርቃት ይሰጡ እንደነበር ይነገራል፡፡[181]

ይህንን ድርጊት የሚቃወመው ሁለተኛው ጎራ በግልጽ ድርጊቱን መቃወም ባይችልም በስውር ገንዘብና ሌሎች ቁሳቁሶችን በመሰብሰብ የጣሊያንን ወራሪ ኃይል ለመታገል ጫካ ለገባው የባሌ አርበኞች ጦር ይልክ ነበር፡፡ ይህ አጋጣሚ በአንድ ልብ፣ በጋራ ስሜትና በወንድማማችነት ፍቅር ወደ መካነ ቅርሱ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያድርግን ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀሳብና በዓላማ እንዲፋፈል ምክንያት እንደሆነ ይነገራል፡፡ የጣሊያን ወረራ መንፈሳዊ ተጓዦችን ፍላጎት ለሁለት በመክፈል የፈጠረው አጋጣሚ በሙዳ በዓላትና በመንፈሳዊ ጉዞ ላይ ለውጥ ከፈጠሩ አብይ ሁነቶች መካከል ይጠቀሳል፡፡

## 9.2.7 አጼ ኃይለሥላሴ መካነ ቅርሱን መጎብኘታቸው

በአጼ ኃይለሥላሴ መንግስትና በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አስተዳዳሪዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንደነበር ይነገራል፡፡ በወቅቱ የነበሩ የአካባቢው ሹማምንቶች በሙዳ በዓላት ወቅት በስፍራው በመገኘት ከሕዝቡ ጋር በዓላቱን ያከብሩ ነበር፡፡ በዚህ ግንኙነት መሰረትም በ1957 ዓ.ም. አጼ ኃይለሥላሴ የባሌ ክፍለ ሀገርን በጎበኙበት ወቅት የድሬ ሼኽ ሁሴንን መካነ ቅርስ ጎብኝተዋል፡፡ በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኝበት መሬት ለመንግስት ከሚገባ የመሬት ግብር ነጻ እንዲሆን፣ በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት የአውሮፕላን ትራንስፖርት መደበኛ መስመር ከአዲስ አበባ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን እንዲኖርና የአይሮፕላን ማረፊያ ሜዳ እንዲሰራ ፈቀዱ፡፡ ንጉሱ መካነ ቅርሱን በጎበኙበት ወቅት የተለያዩ አልባሳትን ይዘው በመምጣት ለድሬ ሼኽ ሁሴን ነዋሪዎችና በአካባቢው ለሚኖሩ የዱቤ ማህበረሰቦች ስጦታ ሰጥተዋል፡፡

እነዚህ የንጉሱ ድርጊቶች በመንግስትና በመካነ ቅርሱ አስተዳዳሪዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲመሰረት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ከግንኙነቱ ባለፈም የሙዳ በዓላትን ለማክበር የሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦች ከአዲስ አበባ እስከ ድሬ በአውሮፕላን መሄድ ጀመሩ፡፡ ይህ አጋጣሚ የሙዳ መንፈሳዊ ጉዞ በመንግስት ደረጃ እውቅና እንዲያገኝና ተጓዦች በቀላሉ ወደ

[181] - ሼኽ መሐመድ ሐጂ አብዱልቃዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ መጋቢት 29 ቀን፣ 2008 ዓ.ም፡፡

ስፍራው እንዲሄዱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የንጉሡ መካነ ቅርሱን መጎብኘትና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ፍቃድ መስጠታቸው በሙዳ በዓላት ላይ አወንታዊ ለውጥ ከፈጠሩ ሁነቶች መካከል አንዱ ነው።

## 9.2.8 የባሌ ገበሬዎች አመጽ

በ1956 ዓ.ም የተጀመረው የባሌ ገበሬዎች አመጽ የደርግ መንግስት ስልጣን ላይ በወጣበት ወቅትም እንደቀጠለ ነበር። በወቅቱም የባሌ ገበሬዎች አመጽ መሪዎች በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና አካባቢው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር። የባሌ ገበሬዎች አመጽ በመካነ ቅርሱ የአስተዳደርና የሙዳ በዓላት አከባበር ላይ በሁለት ምክንያቶች ለውጥ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። እነሱም፣ አንደኛው፣ በመካነ ቅርሱ የተፈጸመው አውሮፕላን የመጥለፍ ድርጊት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የሶውራ ጦር ለሁለት መሰንጠቅ ነው። እነዚህ ታሪካዊ ሁነቶች ከመካነ ቅርሱና ከሙዳ በዓላት አንጻር እንዴት የለውጥ መንስኤዎች እንደሆኑ ቀጥለን እንመልከት።

በባሌ ገበሬዎች አመጽ ወቅት መካነ ቅርሱን ያስተዳድሩ የነበሩት ኢማን መሃሙድ መሃመድ ሰኢድ ነበሩ። በህዳር 5 ቀን 1970 ዓ.ም በመካነ ቅርሱ ያረፈ አንድ አይሮፕላን በአማጽያን ጦር ቁጥጥር ስር ይገባል። የአማጽያን ጦር አይሮፕላኑን በመጥለፍ ወደ ሱማሊያ-ሞቃዲሾ ወሰዱ። የመካነ ቅርሱ ኢማም በድርጊቱ ላይ ተሳታፊ ባይሆኑም ይመለከታቸው ስለነበር በፍጥነት አካባቢውን በመልቀቅ ወደ ሱማሊያ ሞቃዲሾ ተሰደዱ። የኢማሙ ስደት ምክንያት በመካነ ቅርሱ የነበረው የኢማም ቤተሰብ የአስተዳደር መዋቅር ላይ ክፍተት ተፈጠረ።

ይህንን ክፍተት መነሻ በማደረግ መንግስት በመካነ ቅርሱ አስተዳደር ውክልና ላይ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት አካሄደ። መንግስት የመካነ ቅርሱን የአስተዳደር ክፍተት ለመሙላት ከአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ መካከል በመምረጥ መካነ ቅርሱንና አካባቢውን በቀበሌ ገበሬዎች ማህበር መዋቅር መምራት ተጀመረ። ይህ ውሳኔ ለ200 አመታት መካነ ቅርሱን የመሪነት ስልጣን የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ የዘር ሃረግ ውርስ የነበረውን የኢማምነት አመራር አስቀረው። በተመሳሳይም ውሳኔው በሼኽ መሃመድ ቤተሰቦች፣ በሼኽ አባስ ቤተሰቦችና በሰኪናዎች መካከል የአመራር ስልጣኑን ለመያዝ ለሚደረግ ትግል በር ከፈተ።

እነዚህ ሁኔታዎች የደርግ መንግስት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስንና ወደ ስፍራው የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦችን በጥንቃቄ እንዲመለከት አስገድዶታል። በዚህም ሳቢያ በመካነ ቅርሱ

በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። ከእነዚህ ተጽዕኖዎች መካከል የአካባቢውን የሚሊሻ ጦርና የጸጥታ አስከባሪ ኃይሎችን በሙዳ በዓላት ወቅት ማሰማራት፣ ጸረ-መንግስት አቋም ያላቸውን ግለሰቦች መከታተልና በቁጥጥር ስር ማዋል እንዲሁም በሙዳ በዓላት ወቅት በመካነ ቅርሱ አቅራቢያ ጊዜያዊ የፍተሻ ጣቢያ በማቋቋም መንፈሳዊ ተጓዦችን መፈተሽ ተጀመረ።[182]

በወቅቱ የመካነ ቅርሱ ኢማምነትም ስልጣን በመቋረጡ ምክንያት በሙዳ በዓላት ላይ በኢማሞችና በቤተሰቦቻቸው ይፈጸም የነበረው ምርቃት፣ የበዓል የመክፈቻ ንግግርና የኢድ ዕለት የሚካሄድን የህብረት ስግደት መምራት ተቋረጠ። እነዚህ ድርጊቶችም አዲስ በተሾሙ አካላት መከወን ተጀመሩ። በመካነ ቅርሱ የነበረው የአስተዳደር መዋቅርና የኃይል አሰላለፍ መስመር ተለወጠ። በዚህም ሳቢያ የኢማሙ ስርዓት መቀጠል አለበት በሚሉና መቀጠል የለበትም በሚሉ ሁለት አስተሳሰቦች ተፈጠሩ። እነዚህ ሁለት ተጻራሪ አስተሳሰቦችም የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎችንና መንፈሳዊ ተጓዦችን ለልዩነት ዳረገ። ይህ ልዩነት ከዚህን ጊዜ አንስቶ እስከ አሁንም ድረስ ለግጭት ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም የአውሮፕላን ጠለፋ ድርጊት በወቅቱ በመካነ ቅርሱ በተከበሩ የሙዳ በዓላት እንዲሁም ከዛን ጊዜ ጀምሮ እስካሁንም በሚከበሩ በዓላት ላይ ለውጥ ከፈጠሩ ሁነቶች መካከል አንዱ ነው።

በ1956 ዓ.ም የተጀመረው የባሌ ገበሬዎች አመጽ የአጼ ኃይለስላሴን መንግስት በእጅጉ ከፈተኑት የሕዝብ አመጾች መካከል በዋናነት የሚጠቀስ ነው። ይህ አመጽ የ'ሶውራ' አመጽ በሚል ስያሜ ይጠራል። የባሌ የገበሬዎች አመጽ ይመሩ የነበረው በአካባቢው ተወላጆች ነው። መሪዎቹ የአካባቢው ተወላጆች ቢሆኑም የሶውራ አመጽ በሱማሊያ አቦ ነጻ አውጪ ግንባር (SALF) ድጋፍ ያገኝ እንደነበር ይነገራል። የአመጹ መሪዎች በተለያዩ ቦታዎች በመገኘት በሕዝቡ ላይ የቅስቀሳ ስራ ይሰሩ ነበር። መሪዎቹ ለቅስቀሳ ከሚመርጧቸው ቦታዎች መካከል የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በዋናነት ይጠቀሳል።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሕዝቦች በአንድ ላይ ስለሚገኙ፣ የአመጽ ዓላማቸውን በቀላሉ ለሕዝብ ማድረስ ስለሚችሉ፣ ስፍራው ለመረጃ ልውውጥና ለምስጢራዊ የጦር እቅድ ውይይት አመቺ በመሆኑ ለአማጽያኑ ዋና ማዕከል በመሆን አገልግሏል። በወቅቱ የመካነ ቅርሱ ኢማም የነበሩት ኢማም መሃሙድ

---

[182] - ሼኽ አህመድ ሼኽ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ መስከረም 11 ቀን፣ 2008 ዓ.ም።

የአመጹን ዓላማ ስለሚደግፉ ለጦር መሪዎቹ ከፍተኛ ሽፋን ይሰጡ ነበር። ኢማሙም ለበዓል የሚመጣውን ሕዝብ አመጹን እንዲደግፍ ከፍተኛ ቅስቀሳ ያካሂዱ እንደነበር ይነገራል።[183]

በሱማሊያው የዚያድባሬ መንግስት በሱማሊያ አቦ ነጻ አውጪ ግንባር በኩል ለሶውራ ጦር ድጋፍ በመስጠቱ ምክንያት ባሌንና አካባቢውን ከኢትዮጵያ ግዛት በመገንጠል ወደ ሱማሊያ መቀላቀልና ታላቋን ሱማሌ የመመስረት ስውር ዓላማ ይፋ መሆን ጀመረ። በዚህን ምክንያት በሶውራ ጦር ውስጥ አለመግባባት ተፈጠረ። ጦሩም የባሌ ደገኞችና የባሌ ቆለኞች በሚል ለሁለት ቡድን ተከፈለ።[184] የባሌ ደገኛ ቡድን የተባለው በደጋማው የባሌ አካባቢዎች (ጎባ፣ ሮቤ፣ አጋርፋ፣ ጋሰራና ሌሎች ወረዳዎች) ተወላጅ የሆኑ የጦሩ አባላት ሲሆኑ፣ ይህ ቡድን "እኛ ኦሮሞዎች እንጂ ሱማሌዎች አይደለንም። የምንታገለው ለኦሮሞ እንጂ ለሱማሊያ አይደለም።" የሚል አቋም ያለውና የዚያድባሬን ሀሳብ የሚቃወም ነው።

የባሌ ቆለኛ ቡድን የተባለው በቆላማው የባሌ አካባቢዎች (ራይቱ፣ ሰዌና፣ ዳዌ ሰረር፣ ዳዌ ቀቾንና ሌሎች ወረዳዎች) ተወላጅ የሆኑ የጦሩ አባላት ሲሆኑ፣ የዚያድባሬን ታላቋ ሱማሌን የመመስረት ሀሳብ የሚደግፍ ነው።[185] በልዩነቱ ምክንያት የሶውራ ጦር ለሁለት ተበተነ። የባሌ ደገኛ ቡድን የተወሰነው ለመንግስት ጦር እጅ እየሰጠና ይቅርታ እየጠየቀ ወደ ትውልድ መንደሩ ተመለሰ። የባሌ ቆለኛ ቡድን ደግሞ የሶውራ ጦርን እንቅስቃሴ ቀጠለ። በዚህ ልዩነት ምክንያት ለሶውራ ጦር ከፍተኛ ድጋፍ የነበራቸው ታዋቂ ግለሰቦች ጦሩን መልቀቅ፣ መረጃ ማውጣት፣ ዓላማውን በማንቋሸሽ የሕዝብ ድጋፍ እንዳይኖረውና እንዲጠላ እንዲሁም ከመንግስት ጦር ጋር በመተባበር መምታት ጀመሩ። በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት በተሰበሰው ሕዝብ ፊት የዚያድባሬ መንግስትን ዓላማ በይፋ መቃወም ተጀመረ።

ከዚህ በፊት በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ወቅት ሕዝቡ ለሶውራ ጦር ማጠናከሪያ ይሰበስበው የነበረው መዋጮ እንዲቋረጥ በይፋ መቃወም ተጀመረ። ይህንን ተቃውሞ በመካነ ቅርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ ያሰሙት ቃዲ አሕመድ ኢማማ ናቸው። ቃዲ አሕመድ ኢማማ በወቅቱ ለሙዳ በዓል የሚካሄድን የከራ ጉዶ የዋሬ ስርዓተከበራን በበላይነት የሚመሩ ነበሩ።

183 - ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ አናጂና ቀበሌ፣ የካቲት 6፣ 2009 ዓ.ም። ግራዝማች ኃይሌ ወልደሰንበት፣ ጎባ ከተማ፣ ጥር 9 ቀን 2008 ዓ.ም።
184 - አቶ በሪሶ ነገዎ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 8 ቀን፣ 2007 ዓ.ም።
185 - ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም።

በጦሩ ለሁለት መሰንጠቅ ምክንያት የሶውራ ጦር በደጋማው አካባቢዎች ጥቃት መሰንዘር ጀመረ። የጥቃቱም ማዕከል ከሆኑ ስፍራዎች መካከል የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ አንዱ ነበር።[186] በከፍተኛ ደረጃ የታጠቀ የሶውራ ጦር ኃይል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በአካባቢው በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ ተከታታይ ጥቃት ሰነዘረ። በጥቃቱም በርካታ የሰው ሕይወት ጠፋ፤ ንብረትም ወደመ። የሶውራ ጦር የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስንና አካባቢውን ሲቆጣጠር አቅም ያለው ሰው ወደ ጃራና ወደ ጋሰራ ከተሞች ሲሸሽ፣ አቅም የሌላቸው ደግሞ ከመካነ ቅርሱ በግምት 3 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው የአይናገኚ ገደል ተደበቁ።[187]

የሶውራ ጦር አካባቢውን ሲያጠቃ በአይናገኚ ገደል ተደብቀው የነበሩ መረጃ ሰጪዎቼ በቤተሰቦቻቸው ላይ የደረሰው የሞትና የመቁሰል አደጋን፣ የከብቶቻቸው መዘረፍን፣ የእህል ማሳቸው መቃጠልን፣ የቤታቸውና ቤታቸው ውስጥ ያለ ንብረት መዘረፍንና መቃጠልን የሚናገሩበት አንደበትና የሚሰማቸው ኃዘን፣ ድርጊቱ ከዛሬ ሀምሳ አመት በፊት ሳይሆን፣ ከዛሬ ሀምሳ ቀን በፊት የተፈጸመ ይመስላል።

በመንግስት ጦርና በደጋ ባሌዎች የጋራ ትብብር የሶውራ ጦርን እንቅስቃሴ መግታትና ጦሩ የያዛቸውን ቦታዎች ማስለቀቅ ተቻለ። በአይናገኚ ገደል ለ15 ቀናት ያህል ተደብቀው የነበሩ ግለሰቦችም ነጻ ወጡ። ይህ ድርጊት ከተፈጸመ ከጥቂት ወራት በኋላ በተከበረው የሙዳ በዓል ላይም የሶውራ ጦር መንገድ በመዝጋት ወደ ስፍራው የሚሄዱ መንፈሳዊ ተጓዦችን ማጥቃት ጀመረ። የሶውራ ጦር የዘጋው መንገድ መካነ ቅርሱን ከአጎራባች የሐረር፣ የሱማሌና የባሌ ወረዳዎች ጋር የሚያገናኘውን ነው። ጦሩም መንገድ በመዝጋት ከእነዚህ አካባቢዎች ወደ ስፍራው የሙዳ በዓልን ለማክበር የሚሄዱ ግለሰቦችን እንዳያልፉ አደረገ።

የሶውራ ጦር መንገድ ዘግቶ መንፈሳዊ ተጓዦችን አላሳልፍም ባለበት የሙዳ በዓል ላይ አንድ ልዩ ክስተት ተፈጠረ። ይህ ክስተትም የተፈጠረው የሶውራ ጦርን ለመጀመሪያ ጊዜ የተቃወሙት ቃዲ አሕመድ ኢማማ ናቸው። ቃዲ አሕመድ በከራ ጉዶ ዋሬ ስርዓተከበራን ለመታደም በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት የሱማሊያ መንግስትን፣ ፕሬዚዳንት ዚያድባሬንና የሶውራ ጦርን የሚቃወም ንግግር በይፋ አሰሙ። ንግግራቸውን ሲጨርሱም የለበሱትን ነጭ ጀለቢያ

---

[186] - አቶ መሐመድ ሰዒድ አህመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 25 ቀን 2009 ዓ.ም።
[187] - አቶ መሐመድ ሼኽ ሙሐሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም።

አንገት ማስገቢያ ግራና ቀኝ በእጃቸው ያዙ፡፡ "ከዛሬ ጀምሮ ሱማሊያ እንደዚህ ትቀደድ!!" በማለት የለበሱትን ጀለቢያ ከላይ ወደ ታች እላያቸው ላይ ቀደዱት፡፡[188]

በመካነ ቅርሱ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይ የተለያዩ አካላት ይረገማሉ፡፡ ነገር ግን በቃዲው የተካሄደው ይህ አይነት እርግማን ተደርጎ አይታወቅም፡፡ ይህ አይነት እርግማን ከዚያ ወቅት በፊትም ሆነ ከዚያ ወዲህ በመካነ ቅርሱ ተካሂዶ አይታወቅም፡፡ በወቅቱ በስፍራው የነበረ ሕዝብ በታላቅ ስሜት በእልልታና በጭብጨባ እርግማኑን እንደደገፈ መረጃ ሰጪዎቹ ያስታውሳሉ፡፡[189] ይህ ድርጊት ከተፈጸመ ከአመታት በኋላ የዚያድባሬ መንግስት ወደቀ፤ ሱማሊያ ተበተነች፡፡

ሱማሊያ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን መንግስቱም መንግስት፣ አገሩም አገር ሳይሆን እንደተበተነ አለ፡፡ ሱማሊያ ለዚህ እጣፈንታ የተዳረገችው በቃዲው እርግማን እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ያምናሉ፡፡[190] ከባሌ ገበሬዎች አመጽ ጋር የተያያዙት እነዚህ ክንውኖች በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በሚከወኑ የሙዳ በዓላት ላይ ለውጥ ከፈጠሩ ሁነቶች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

### 9.2.9 ለመካነ ቅርሱ ትኩረት መሰጠት መጀመር

የተለያዩ አካላት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ ትኩረት አላቸው፡፡ እነዚህ አካላት ከራሳቸው ፍላጎት በመነሳት ያላቸውን ትኩረትም በተለያዩ ወቅቶች ገልጸዋል፡፡ ከእነዚህ አካላት መካከል የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ የተባበሩት መንግስታት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅት ዩኒስኮ (UNESCO)፣ የመንግስት ባለስልጣኖች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ የፌዴራል፣ የኦሮሚያ ክልልና የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎችና የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን የቱሪስት መዳረሻ ማዕከል ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጥረትም ወደ መካነ ቅርሱ በሚሄድ መንገድ ላይ በሚገኙ ከተሞና የመንገድ መታጠፊያና መለያያ ቦታዎች የመካነ ቅርሱን ፎቶግራፍ በትልልቅ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች (ቢልቦርድ) የመትከል ስራና በመካነ ቅርሱ ላይ የኢንቨንተሪ ጥናቶች ማካሄድ ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህም ምክንያት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀደምት ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ ጁነዲን ሳዶና አቶ አባዱላ ገመዳ የሙዳ በዓላትን በመካነ ቅርሱ በመገኘት ማክበር ጀመሩ፡፡ በወቅቱም የክልሉ ፕሬዚዳንቶችም ለድሬ ሼኽ ሁሴን የመብራት ጄኔሬተርና የገንዘብ ስጦታ

---

188 - ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 26 ቀን 2009 ዓ.ም፡፡

189 - ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ መሐመድ፣ ሼኽ ሙሃመድ ሼኽ ኢድሪስና አቶ መሐመድ ሼኽ መሐሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ነሐሴ 26 ቀን 2009 ዓ.ም፡፡

190 - ሼኽ ኢብራሂም ሼኽ መሐመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ሚያዝያ 7 ቀን 2007 ዓ.ም፡፡

ሰጥተዋል፡፡ በ1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኢምባሲ ለመካነ ቅርሱ ማሳደሻ 25,600 ዶላር የገንዘብ ስጦታ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ገንዘብም በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ የውስጥ ለውስጥ መንገድን ጥርብ ድንጋይ የማንጠፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

በ2000 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ ተከብሯል፡፡ የሚሊኒየም በዓልን በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም በክልል ደረጃ አክብሯል፡፡ የኦሮሚያ ክልል የሚሊኒየምን በዓል በክልል ደረጃ ያከበረው በባሌ ዞን ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነው፡፡ በዓሉ የተከበረውም ከሐጅ የሙዳ በዓል ጋር በጥምረት ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኦሮሚያ ክልል ሚሊኒየም መከበሩ በሙዳ በዓል፣ በመካነ ቅርሱና በመንፈሳዊ ጉዞው ላይ የተለያዩ ለውጦች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

የሚሊኒየም በዓል በመካነ ቅርሱ እንዲከበር ከተወሰነበት ጊዜ አንስቶ በክልሉና በዞኑ የተለያዩ የልማት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከእነዚህ የልማት ስራዎች መካከል ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ እስከ ድሬ ሼኽ ሁሴን ያለው የመኪና መንገድ ታድሷል፡፡ ይህ መሆኑም ለሙዳ በዓል ወደ ስፍራው የሚሄዱ የሕዝብ ማመላለሻና የቤት መኪናዎች ቁጥር እንዲጨምር አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ስራ ተሰርቷል፡፡ የንፁሕ መጠጥ ውኃ መስመር ዝርጋታ ስራ ተሰርቷል፡፡ የስልክ ኔትወርክ መስመር ዝርጋታ ተከናውኗል፡፡ በወቅቱ የእነዚህ መስመሮች ዝርጋታ በመከናወኑ የመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች የመብራት፣ የውኃና የስልክ ኔትወርክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ከዚህ በፊት በጄኔሬተር ከሚገኝ የኤሌክትሪክ ኃይል አማካኝነት በምሽት የሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎች ይከወኑ ነበር፡፡ በሚሊኒየም በዓል ምክንያት በምሽት የሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎች ለመጀመሪያ ጊዜ  በቀጥታ ከኤሌክትሪክ መስመር በሚገኝ ኃይል ተከውነዋል፡፡

በሚሊኒየም በዓል ምክንያት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ነዋሪዎችና መንፈሳዊ ተጓዦች ለመጀመሪያ ጊዜ በቧንቧ መስመር አማካኝነት ንጹህ የመጠጥ ውኃን በመጠቀም የሙዳ በዓልን አከበሩ፡፡ የስልክ ኔትወርክ ዝርጋታም በመካሄዱ የሙዳ በዓልን የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነው አከበሩ፡፡ ለሚሊኒየሙ ዘመናዊ የጤና ጣቢያ ተገንብቶ በመካነ ቅርሱ ስራ ጀመረ፡፡ የሚሊኒየም በዓል ለመካነ ቅርሱ መሰረተ ልማት መሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበረከተ፡፡ የመሰረተ ልማት ስራው ጥሩ ሆኖ ሳለ የሚያሳዝነው በዓሉ ተከብሮ በተጠናቀቀ ማግስት የመብራት፣ የውኃና የሞባይ ስልክ ኔትወርክ አገልግሎት ሙሉለሙሉ መቋረጡ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በመካነ ቅርሱ የመብራት፣ የውኃና የስልክ አገልግሎት የለም፡፡

በመካነ ቅርሱ የሚሊኒየም በዓል በተከበረበት ወቅት የፌዴራልና የክልል ባለስልጣናትና የቢሮ ኃላፊዎች ተገኝተው የሙዳ በዓልን ከሕዝቡ ጋር አብረው አክብረዋል፡፡ በስፍራው በዓሉ ሲከበርም በኦሮሚያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የቀጥታ የአየር ስርጭት ሽፋን አግኝቷል፡፡ በዚህ የሚዲያ ሽፋን አማካኝነትም አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ ስለ መካነ ቅርሱ ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ ይህ አጋጣሚም የሙዳ በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ ሰፊ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋንና የቀጥታ የአየር ስርጭት አግኝቶ እንዲከበር ምክንያት ሆኗል፡፡

የሐጅ የሙዳ በዓል ከዛሀራ ገልገላ ጎበና የሙዳ በዓል የሚለየው ጠዋት ላይ በሚሄደው የህብረት ስግደት ነው፡፡ ቀደም ሲል ይህ የህብረት ስግደት ይካሄድ የነበረው በግንብ በታጠረው ግቢ ውስጥ ነበር፡፡ የሚሊኒየም በዓል አካባቢ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ ቦታው መጥበብ ጀመረ፡፡ በዚህም ምክንያት የህብረት ስግደት የሚካሄድበትን ስፍራ በመቀየር በመካነ ቅርሱ አካባቢ የሚገኘውና አውሮፕላን ማረፊያ በሚባለው ሰፊ ሜዳ ላይ እንዲሰገድ ተደረገ፡፡ በሚሊኒየም በዓል ወቅትም የህብረት ስግደት በአይሮፕላን ማረፊያ ስፍራ ተከውኗል፡፡ ይህ አጋጣሚ በሙዳ በዓል ስርዓተክወናዎች ከሚከወኑበት ቦታ አንጻር ለውጥ እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል፡፡

ከ2000 ዓ.ም ወዲህ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን በተባበሩት መንግስታት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅት (UNESCO) በዓለም የቅርስ መዝገብ ዝርዝር ውስጥ የማስመዝገብ ጥረት መደረግ ተጀመረ፡፡ በዚህ ጥረትም የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፣ የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮና የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በጋራ የተለያዩ አውደ ጥናቶች፣ የኢንቬንተሪ ስራዎች፣ የመካነ ቅርሱን ድንበር የማካለል፣ የካርታ ስራዎችና የዶክመንተሪ ፊልም ስራ በስፋት ተሰርተዋል፡፡ ይህም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና የሙዳ በዓል ትኩረት እንዲሰጣቸው ምክንያት ሆኗል፡፡

# 10. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "በባሌ ዞን ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሙዳ ስርዓተከበራ፣ ውሕደትና መንፈሳዊ ጉዞ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ነው። የጥናቱ አብይ ዓላማ የሙዳ በስርዓተከበራዎችንና መንፈሳዊ ጉዞዎችን መተንተን ነው። የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በባሌ ዞን በጎሎልቻ ወረዳ፣ በአናጂና ቀበሌ የሚገኝ ነው። መካነ ቅርሱን የመሰረቱት ሼኽ ሁሴን ሼኽ ኢብራሂም መልካይ ናቸው። ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርሱ በሚገኝበት አናጂና ቀበሌ እንደተወለዱ ይታመናል። የሼኽ ሁሴን የውልደት ዘመን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች ቢኖሩም፣ ይህ ጥናት በ12ኛው መቶ ክ/ ዘመን አጋማሽ እንደተወለዱ ያሳያል። ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት በርካታ ተማሪዎችን መንፈሳዊ ትምህርት በመካነ ቅርሱ አስተምረዋል። በወቅቱም የራሳቸው አስተምህሮ እንደሆነ የሚታመን "ሁሴኒያ" የተሰኘ የሱፊዝም ስርዓት እንደነበራቸው ጥናቱ ያመለክታል።

ሼኽ ሁሴን በአናጂና ቀበሌና አካባቢው የተለያዩ ኪነህንጻዎችን በመገንባት፣ የኃይማኖት ማስተማሪያ ተቋም በመመስረትና ሰፋፊ እርሻ ተግባራዊ በማድረግ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በአካባቢው አስተዋውቀዋል። ይህም የባሌ ዞን ከሌሎች አጎራባች የደቡብ ምስራቅ የአገሪቷ አካባቢዎች በተለየ አዳዲስ ስልጣኔዎች የተስፋፉበትና ቀደምት የእስልምና ኃይማኖት ማዕከል እንዲሆን አስችሎታል። ይህ ሁኔታም መካነ ቅርሱ የሚገኝበት የአናጂና ቀበሌና አካባቢው የአገራችንን ቀደምት ስልጣኔ ማሳያ እንዲሆንና በወቅቱ አገሪቷ ደርሳበት የነበረውን የእድገት ደረጃ የሚያሳይ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

የሼኽ ሁሴን ሰብዕናን በሚመለከት ከአፍቃሪዎቻቸውና ከተቃዋሚዎቻቸው አንጻር የተለያዩ እሳቤዎች እንዳሉ ጥናቱ አሳይቷል። ሼኽ ሁሴን ከአፍቃሪዎቻቸው አንጻር በፈጣሪ የተመረጡ ቅዱስ፣ ልዩ የፈጣሪ ጸጋ ያላቸው፣ ለሰው ልጅ አማላጅና አዳኝ፣ ለዘለዓለም ሕያው፣ የፍጡራን ሁሉ አባት፣ በኃይማኖትና በመንፈስ ጽኑ፣ ፍጡር ሁሉ የሚያከብራቸውና የሚታዘዛቸው፣ እሳቸውን የናቀ ወይም ሊጎዳ ያሰበ እጅግ ከባድ ቅጣት እንደሚቀጣ፣ የሰው ስጋ ለብሰው በአካል እንደሚመጡ፣ ከግለሰቦች ጋር መልዕክት እንደሚለዋወጡና የመንፈስ ልዕልናቸው እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል። እነዚህም እሳቤዎች በእሳቸው ላይ በሚነገሩ ሚቶች፣ ተዓምራትና ለእሳቸው መወድስ በሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች አማካኝነት ተገልጸዋል። እሳቤዎቹም በቁጥር፣ በትረካ፣ በምልክት፣ በሚታዩ መልክዓምድራዊ ቅርጾችና መንፈሳዊ ኃይል

ባላቸው የቁልምጫ ስሞች አማካኝነት የነገረ ፍጥረት፣ የነገረ ህላዌና የነገረ ተልዕኮ አዕምሯዊ ትርጓሜን እንደሚፈጥሩ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በሼኽ ሁሴን ላይ የሚንጸባረቁት እሳቤዎች በፈጣሪ (በአምላክ) ላይ ከሚንጸባረቁ እሳቤዎች ጋር የውሕደት ባህርይ ይታይባቸዋል፡፡ ውሕደቶቹም አቻ ያልሆኑ አካላትን በእኩል መመልከትና የአንድ አካልን ባህርይ ለሌላ መስጠት ናቸው፡፡ የእሳቤዎቹ ውሕደትም ከኮግኒቲቭ ንደፈሃሳብ አንጻር አምላክ የሚገለጸው እንደሰው ልጅ አዕምሯዊ ግንዛቤ፣ አዕምሯዊ ጠቀሜታና ለሰውነት ባለው ቅርበት ነው፡፡ በዚህ አሳቤ መሰረት ለሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ሼኽ ሁሴን በዕለትተዕለት ችግራቸው ደራሽና ከክፉ ነገር ጠባቂ እንደሆኑ ያምናሉ፡፡

በኮግኒቲቭ ንድፈሳሃሳብ እሳቤ መሰረት በአንድ አካል ላይ ያለው የታድጎት እሳቤ በከፍተኛ ደረጃ ሲያድግና አዕምሯዊ ማዕከልነት ሲይዝ የአምላክነት ባህርይ ይላበሳል፡፡ ለዚህም ሼኽ ሁሴን በአማኞቻቸው ዘንደ ባላቸው የታድጎት ሚና የአምላክነት ውክልና እንዲይዙና የእሳቸው ባህርይ ከአምላክን ባህርይ ጋር ውሕደት እንዲፈጥር ምክንያት እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በተቃራኒው ሼኽ ሁሴን ከተቃዋሚዎቻቸው አንጻር የሞቱና ምንም መንፈሳዊ ጥቅም የሌላቸው እንደሆኑ መታመኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ ያለው የቦታ እሳቤ ከእሳቸው አፍቃሪዎችና ተቃዋሚዎች አንጻር የተለያየ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከአፍቃሪዎቻቸው አንጻር ቦታው እጅግ የተከበረና የተቀደሰ እንደሆነ ይታመናል፡፡ መካነ ቅርሱ ከሚገኝበት የመልከዓምድርና የኪነህንጻዎቹ ዲዛይን ባህርያት በመነሳት የሰማያዊው የዔደን ገነት ቅርጽ ያለውና በምድር ላይ ያለ የገነት አምሳያ ተደርጎ እንዲታሰብ ምክንያት መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ መካነ ቅርሱና በስፍራው የሚገኙ ኪነህንጻዎች ወደ ስፍራ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርግ ግለሰብን፣ በአካባቢው የሚኖር ማህበረሰብን፣ ሼኽ ሁሴንንና ፈጣሪን በአንድ በማገናኘት በተጨባጩ ቁሳዊ ዓለምና በሜታ ምናባዊ ዓለም መካከል ሕብር እንዲኖር በማድረግ የአራትዮሽ የግንኙነት ትስስር እንደፈጠሩ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በዚህ ሚናም ስፍራው የመንፈስ የኃይል ስበት ማዕከልና የዓለምን ስርዓት አቅፎ የያዘ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

በትዕምርታዊ ንድፈሃሳብ መሰረት ቦታ ልዩ ትርጉም፣ ውክልና፣ ዋጋና መልዕክት አለው፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም በሼኽ ሁሴን አፍቃሪዎች ዘንድ ልዩ መንፈሳዊ ኃይል ያለው፣ በፈጣሪ የተመረጠና በስፍራው መገኘትም ቅድስናን የሚያስገኝ እንደሆነ መታመኑን ጥናቱ

ያሳያል፡፡ ይህ የቦታው ልዩ ዋጋና ውክልና መሰረት ያደረገው የአማኙን ግንዛቤ፣ ስሜት. ዕይታና ልምድ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በተቃራኒው ስፍራው ከሼኽ ሁሴን ተቃዋሚዎች አንጻር የተለያየ እሳቤ አለው፡፡ ስፍራው ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ወገን ቀደም ሲል በአቡነ አኖሪዎስ የተመሰረተ የክርስቲያን ገዳም ነበር የሚል ሀሳብ ሲኖር፣ ከሰለፊያ የእስልምና አስተምህሮ አራማጆች ወገን ደግሞ ስፍራው ምንም ጥቅም የሌለውና መውደም ያለበት እንደሆነ መታመኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

መካነ ቅርሱ በሚገኝበት የአናጂና ቀበሌና አካባቢው ቋሚ ነዋሪዎች አሉ፡፡ ሁሉም ነዋሪዎች የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ናቸው፡፡ በአካባቢው የእስልምና ኃይማኖት በ8[ኛው] መቶ ክ/ዘመን የተዋወቀ ቢሆንም በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋውና የተጠናከረው በ12[ኛው] መቶ ክ/ዘመን በሼኽ ሁሴን አማካኝነት ነው፡፡ በወቅቱም ሼኽ ሁሴን መስኪዶችን በመገንባትና የኃይማኖት ማስተማሪያ ማዕከል በመመስረት የእስልምና ኃይማኖት በአካባቢው አስፋፍተዋል፡፡

በእስልምና ኃይማኖት ስር የሚካተቱ የተለያዩ አስተምህሮዎች በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ እንደፈጠሩ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ተጽዕኖ የፈጠሩ አስተምህሮዎችም የሱፊዝም፣ የሺዓት፣ የኦርቶዶክስ፣ የፖፑላርና የሰለፊያ ናቸው፡፡ የአስተምህሮዎቹ ድርጊቶችና ስርዓቶች በመካነ ቅርሱ በሚከወኑ የሙዳ በዓላት፣ መንፈሳዊ ጉዞ፣ የመካነ ቅርሱ አስተዳደርና በሚከወኑ ሌሎች ኃይማኖታዊና ማህበራዊ ስርዓተከበራዎች ላይ እንደሚንጸባረቅ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በተለየዩ ወቅቶች የተለያዩ የእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮዎች በፈጠሩት ተጽዕኖ በመካነ ቅርሱና በሙዳ በዓላት ላይ የውሕደት ባህርይ በስፋት እንዲንጸባረቅ ምክንያት እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

በአናጂና ቀበሌና አካባቢው የሚኖሩ ማህበረሰቦች ኢኮኖሚ በንግድ፣ በእርሻ፣ በአስጎብኚነትና በልመና ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ማህበረሰቡ ደርጋ፣ ኡሌ፣ ገሪባና መናኝ በሚሉ አራት ማህበራዊ አደረጃጀቶች ይመደባል፡፡ ከእነዚህ አደረጃጀቶች መካከል ደርጋ በቤተሰብ የዘር ሃረግ የተመሰረተና ቋሚ ነዋሪዎችን የሚገልጽ ነው፡፡ የኡሌ፣ የገሪባና የመናኝ ምደባዎች ግለሰቦቹ ባላቸው ልዩ ችሎታና ባህርይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በእነዚህ ማህበራዊ ምደባዎች መሰረትም ነዋሪዎች በመካነ ቅርሱና በሙዳ ስርዓተከበራዎች ላይ የተለያየ ሚና እንዳላቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡

የሙዳ በዓላት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩና በመታሰቢያ ስርዓት ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ የሙዳ በዓላት ሐጅና ዛሕራ ገልገላ ኀበና በሚሉ ስያሜዎች

ይታወቃሉ። በበዓላቱ ወቅት እስከ አምስት መቶ ሺሕ የሚገመት ሕዝብ በስፍራው ይገኛል። መንፈሳዊ ተጓዦችም የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮችን በመጠቀም ወደ ስፍራው ይሄዳሉ። ወደ መካነ ቅርሱ የሚጓዙ ግለሰቦች የተለያየ አነሳሽ ጉዳዮች አሏቸው። እነዚህ አነሳሽ ጉዳዮች መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ጉብኝትና ሕገወጥ ተግባራት እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል።

በሙዳ በዓላት ወቅት በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚኖሩ የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የውጪ አገር ዜጎች እንዲሁም የእስልምና፣ የክርስትና፣ የዋቄፈናና የሌሎች ኃይማኖት ተከታዮች ወደ መካነ ቅርሱ መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ። መንፈሳዊ ጉዞው በኃይማኖት፣ በጾታ፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በዜግነት፣ በመደብና በሌሎች ምክንያቶች የተለያዩ ግለሰቦች በጋራ የሚያካሂዱት ነው። ይህ ልዩ ባህሪውም ለባህልና ለመረጃ ልውውጥ፣ ለእርስበርስ ትውውቅና መከባበር እንዲሁም የአገር አንድነት አሳቤ ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህ ልዩ ባህሪው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ኢትዮጵያዊያንን በአንድ የሚያገናኝ ነው። ይህ መሆኑም በልዩነት ውስጥ አንድነትን የሚያንጸባርቅና የፓን-ኢትዮጵያን እሳቤ መሰረት የጣለ የአገራችን ልዩ ስፍራ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል።

ሼኽ ሁሴን በአፍቃሪዎቻቸው ዘንድ ያላቸው ሰብዕናዊ እሳቤና መካነ ቅርሱ ተመሳሳይ ባህርይ እንዳላቸው ጥናቱ ያሳያል። ሼኽ ሁሴን አቃፊ፣ ደጋፊ፣ ሰብሳቢያና የአንድነት ሻምፒዮን ናቸው እንጂ ገፊ፣ አግላይ፣ ነጣይና መራጭ አይደሉም። መካነ ቅርሱም የሁሉም ፍጡር መሰብሰቢያ ነው። በመሆኑም ሼኽ ሁሴን የመካነ ቅርሱ፤ መካነ ቅርሱ ደግሞ የሼኽ ሁሴን አምሳያ ናቸው። ይህ የሁለትዮሽ ባህሪያዊ ትስስር በሼኽ ሁሴንና በመካነ ቅርሱ ላይ በሚነገሩ ሚቶች፣ በሚቀርቡ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች፣ ልዩ ውክልና ባላቸው ትዕምርቶችና በአካባቢው መልከዓምድራዊ አንድምታ እንደሚንጸባረቁ ጥናቱ አሳይቷል።

የሙዳ በዓላት የሚከበሩባቸው ቀናት ከመድረሳቸው ቀደም ብሎ የተለያዩ ስርዓተከበራዎች ይከወናሉ። እነዚህ ስርዓተከበራዎችም የሀሽ ዱቄት ዝግጅት፣ የተለያዩ ኪነህንጻዎችን ሀሽ መቀባት፣ የጀዋራ ቅዱስ አፈር ማዘጋጀት፣ የደንቄ በትር ማዘጋጀትና የእንግዳ ማረፊያ ደገሌን ማሰናዳት እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል። እነዚህ ስርዓተከበራዎችም እያንዳንዳቸው የሚከወኑበት ወቅት፣ ስርዓት፣ ቅደምተከተልና የራሳቸው ከዋኞች እንዳላቸው ጥናቱ በዝርዝር አቅርቧል። የበዓላቱ ቀናት ሲቃረቡም መንፈሳዊ ተጓዦችን ለመቀበል የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓቶች መኖራቸውን ጥናቱ ያሳያል።

በሐጅና በገልገላ ጎበና የሙዳ በዓላት ወቅት የተለያዩ ስርዓተከበራዎች ይከወናሉ። እነዚህ ስርዓተከበራዎች የዋሬ፣ የዝክሪ፣ በከራ ጉዶና በቅጽር ግቢው ውስጥ የሚከወኑና በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል። በመካነ ቅርሱ በተለያዩ አካባቢዎች በሚከወኑ ስርዓተከበራዎች በስራቸው በርካታ ስርዓቶችን አጠቃለው እንደሚይዙ፣ እያንዳንዳቸው የሚከወኑበት ቋሚ ጊዜ፣ ቦታና የራሳቸው ከዋኞች እንዳላቸው በጥናቱ በዝርዝር ቀርቧል። በሁለቱ የሙዳ በዓላት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ በበዓላቱ የአጀማመር ሂደት ላይ ልዩነት መኖሩን ጥናቱ አሳይቷል።

ክወና እንዲቀርብ መሰረታዊ ጉዳዮች መቼት፣ አሀድ፣ ትረካ፣ መልዕክት፣ ሕግና ማዕቀፍ ናቸው። በመካነ ቅርሱ የሚቀርብ እያንዳንዱ ክወናም የመከወኛ ጊዜ፣ ቦታ፣ የሚቀርብ አሀድ፣ በከዋኝና በታዳሚ መካከል ተግባቦት የሚፈጥርና መልዕክት የሚያስተላልፍ፣ የራሱ የአከዋወን፣ የአፈጻጸምና የአተገባበር ሕግና ማዕቀፍ አለው። እነዚህ ጉዳዮች በጊዜ ሂደት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለመዱና የታወቁ ናቸው። በጥናቱም ስርዓተከበራዎቹ ያላቸውን የክወና ቅደም ተከተል፣ በክወናው መልዕክት፣ የክወናው መዋቅር፣ ለክወናው ትርጉም የሚሰጡ ጉዳዮችና ትርጓሜዎች፣ በታዳሚውና በከዋኝ ላይ የሚፈጠሩ የስሜት ለውጦች በጥናቱ ተብራርተው ቀርበዋል።

በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ለመንፈሳዊ ተጓዦች መንፈሳዊ እሴትን፣ የመንፈስ ለውጥን፣ የምሉዕነት ስሜትንና እርካታን የሚያጎናጽፉ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል። የሙዳ በዓላት ከተጠናቀቁ በኋላ መንፈሳዊ ተጓዦች በየአካባቢያቸው የሚፈጽሟቸው ስርዓቶች አሉ። ይህም መሆኑ የሙዳ በዓላት ስርዓቶች በየስድስት ወራት የሚደጋገሙ፣ የክብ ቅርጽ መልክ የሚይዙ፣ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚያሸጋግሩና የሕይወት ዑደት ስርዓትን የተከተሉ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል።

በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስምንት አይነት መንፈሳዊ ሙዚቃዎች አሉ። እነዚህ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች የተለያየ ዜማ፣ የመከወኛ ጊዜና ቦታ፣ ግጥም፣ የአጨዋወት ስልትና ቅኝት አላቸው። መንፈሳዊ ሙዚቃዎቹ የተለያዩ ባህሪ ቢኖራቸውም፣ በሙዚቃ ስኬል አጠቃቀም ትዝታ ሜጀርና ዶሪያን ፔንታቶኒክ ስኬል መሰረት ያደረጉ ናቸው። መንፈሳዊ ሙዚቃዎቹ ከእነዚህ ሁለት የሙዚቃ ቅኝቶች በይበልጥ ለዶሪያን ፔንታቶኒክ ስኬል ያደሉ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል።

በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች የውሕደት ባህርይ እንደሚስተዋልባቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በመካነ ቅርሱ የተለያዩ ብሔሮች፣ ጎሳዎችና ማህበረሰቦች፣ የተለያዩ አብይ ኃይማኖቶችና የኃይማኖት አስተምህሮዎች እንዲሁም ሀገረሰባዊ እምነቶች በተለያዩ ወቅቶች ተጽዕኖ ፈጥረውበታል፡፡ ይህ ተጽዕኖም በበዓላቱ ወቅት በሚከወኑ ስርዓቶች ውሕደት እንዲፈጠር ምክንያት እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ውሕደት ከተለያዩ ነገሮች የሚፈጠር ቢሆንም አዲስ የባህል ቅርጽ መፍጠር ሳይሆን፣ የተለያዩ መንፈሳዊና ቁሳዊ ግብዐቶችን በመውሰድ ነባሩን ባህል በአዲስ አውድ መግለጽ ነው፡፡

በሙዳ በዓል ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችም ከተለያዩ ኃይማኖቶች፣ እምነቶችና ባህሎች የወሰዳቸውን መንፈሳዊና ቁሳዊ ግብዐቶች በአዲስ ቅርጽና በአዲስ አውድ የሚቀርቡባቸው ናቸው፡፡ ይህም ስርዓተከራዎቹ የተለያዩ ግብዐቶችን በአውድ በማዋሃድና በመግለጽ አዲስና የራሳቸው ልዩ መልክ ያላቸው እንዲሆኑ ማስቻሉን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በሙዳ በዓላት፣ በመንፈሳዊ ጉዞ፣ በሼኽ ሁሴንና በመካነ ቅርሱ ላይ የሚታዩ የውሕደት ባህርያት በኮግኒቲቭ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው፡፡

የሙዳ በዓላት ለረጅም ዓመታት በመካነ ቅርሱ ሲከወኑ ቆይተዋል፡፡ በእነዚህ ረጅም ዓመታትም በስርዓተከበራዎቹ ላይ የተለያዩ ለውጦች ተከስተዋል፡፡ ለውጦቹም የመካነ ቅርሱ የቦታ ለውጥ፣ የሼኽ ሁሴን ውልደትና ሕልፈት፣ መካነ ቅርሱ የነባር ሕዝቦች የኃይማኖት ማዕከል መሆኑ፣ የመካነ ቅርሱ የኃይማኖት ማዕከልነት ድጋሚ መጠናከር፣ አንዳንድ ስርዓተከበራዎች መጀመር፣ የጣሊያን ወረራ፣ አጼ ኃይለሥላሴ መካነ ቅርሱን መጎብኘት፣ የባሌ ገበሬዎች አመጽና ለመካነ ቅርሱ ትኩረት መሰጠት መጀመር እንደሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ እነዚህም በመካነ ቅርሱ፣ በሙዳ በዓላት ክወና፣ በመንፈሳዊ ጉዞና በመንፈሳዊ ተጓዦች ላይ ወቅታዊና ዘለቄታዊ ለውጦች መከሰታቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡

በሙዳ በዓላት ላይ የሚስተዋሉ የተለያዩ ተግዳሮቶች አሉ፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶችም የመካነ ቅርሱ ተቃዋሚዎች አስተምህሮ መስፋፋት፣ የትምህርት መስፋፋት፣ የኑሮ ውድነት ማሻቀብ፣ ለሀሽ ዱቄት ዝግጅት የሚያገለግለው የዶዶቲ ተክል መራቆት፣ የቴክኖሎጂ መስፋፋት፣ የንግድ እንቅስቃሴ፣ በመካነ ቅርሱ ላይ የስልጣን ይገባኛል ሽኩቻ፣ ለመካነ ቅርሱ የሚደረግ ጥንቃቄ መላላት፣ የመሰረተ ልማቶች አለመሟላትና የተለያዩ አካላት ያላቸው የግል ፍላጎት እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶች በተለያዩ ወቅቶች እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ወቅታዊና ዘለቄታዊ ችግሮች እየፈጠሩ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

# የይሁንታ ሀሳቦች

በዚህ ጥናት ከቀረቡ መረጃዎችና ከተገኙ ግኝቶች፣ የመስክ ተመክሮዎች፣ በመካነ ቅርሱና በሙዳ በዓላት ላይ ተግዳሮት ከፈጠሩ ሁነቶች በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

- በሙዳ በዓላት በኃይማኖት፣ በጾታ፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በዜግነት፣ በመደብና በሌሎች ምክንያቶች የተለያዩ ግለሰቦች በጋራ የሚያከብሩት ነው፡፡ ይህ ልዩ ባህሪውም ለባህል ልውውጥ፣ ለመረጃ ልውውጥ፣ ለእርስበርስ ትውውቅና መከባበር እንዲሁም የአገር አንድነት አሳቤ ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህ መሆኑም በልዩነት ውስጥ አንድነትን የሚያንጸባርቅና የፓን- ኢትዮጵያን እሳቤ መሰረት የጣለ የአገራችን ልዩ ስፍራ ነው፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና መሰል ባህሪይ ያላቸው ሌሎች የአገራችን ስፍራዎች የአንድነት ሕብር ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የአንድነት ሕብር ተምሳሌት የሆነውን የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ይበልጥ ለማወቅና ለሌሎች ለማስተዋወቅ በተለያዩ አካላት ጥናትና ምርምሮች መሰራት አለባቸው፡፡
- የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የአንድነት፣ የውሕደትና የሕብረት ተምሳሌት ነው፡፡ የእኩልነት፣ የመከባበርና የመደመር አርማ ነው፡፡ ይህ ጥናት የኢትዮጵያዊያንን የአንድነት ረቂቅ ማህበራዊ ስሪትና የአገሪቷን ልዩ ገጽታ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በባህል፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካና በልማት ላይ ለሚዘጋጁ አገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ፖሊሲዎች በግብዐትነት ይጠቅማል፡፡ የፖሊስ አውጭና አስፈጻሚ አካላትም፣ በመካነ ቅርሱና አካባቢው የልማት ስራ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህንን ጥናት በግብዐትነት መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡
- መካነ ቅርሱ በተለያዩ መንፈሳዊ፣ ቁሳዊና ቃላዊ ሀብቶች የበለጸገ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በስፍራው የተጠኑ ጥቂት ጥናቶች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ በመካነ ቅርሱ ያሉ ሀብቶችን ለመግለጽ በሚል ይመስላል፣ የኢንቨንተሪ መልክ ያላቸውና ጥልቀት የሌላቸው ናቸው፡፡ በሙዳ ስርዓተከበራ ላይ ያተኮረው ይህ ጥናትም ቢሆን ካለው ወሰን በመነሳት ያልተዳሰሱ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ በመሆኑም በስፍራው የሚገኙ መንፈሳዊ፣ ቁሳዊና ቃላዊ ሀብቶች በተለያዩ አጥኚዎች በጥልቀት መጠናትና መሰነድ ይኖርባቸዋል፡፡

- ለሙዳ በዓላት ቅድመ ዝግጅት ኪነህንጻዎችን ሀሽ የመቀባት ስርዓት በአመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል። በአሁኑ ወቅት ለሀሽ ዝግጅት የሚያገለግለው የዶዶቲ ተክል ከመካነ ቅርሱ ክልል እየተመናመነ ነው። ይህ ተክል እንዲመናመን ምክንያት የሆነው በአንድ ጊዜ በርካታ መጠን ያለው የዶዶቲ ተክል ለሀሽ ዝግጅት ስለሚመነጠርና ተክሉ አንዴ ከተቆረጠ ድጋሚ ስለማይጸድቅ ነው። ይህ ደግሞ ከቅርብ አመታት በኋላ በሀሽ ዝግጅት ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል። ከችግሩ ለመዳን መፍትሄው የተክሉን ችግኝ ማርባትና በመካነ ቅርሱ ክልል መትከል ነው። ይህም ስራ በሚመለከተው አካል መሰራት ይኖርበታል።
- የተለያየ የኃይማኖት አስተምህሮ የሚከተሉና የመካነ ቅርሱ ተቃዋሚ የሆኑ አካላት አሉ። እነዚህ አካላት ለመካነ ቅርሱ፣ ለሙዳ በዓላትና ለመንፈሳዊ ተጓዦች ስጋት ናቸው። የኃይማኖት ልዩነት ተፈጥሯዊና የሚጠበቅ ነው። ነገር ግን ያለን የኃይማኖት አስተምህሮ ልዩነት በመጠቀም የሌላውን አካል ኃይማኖት በኃይል ለመጨፍለቅና በአማኙ ላይ ጉዳት ማድረስ ኢ-አማኝነትና ልዩነት ተፈጥሯዊ መሆኑን የማይቀበል ጽንፈና አመለካከት ነው። በመሆኑም የሚመለከተው የመንግስት አካል የኃይማኖት ልዩነት መኖር ተፈጥሯዊ፣ የአማኙ ሰብዓዊ መብትና የአገር ውበት መሆኑን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት ይኖርባቸዋል።
- የሙዳ ስርዓተከበራና መካነ ቅርሱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው። ሙዳ የሚኖረው መካነ ቅርሱ ሲኖር ነው። በአሁኑ ወቅት በመካነ ቅርሱ ላይ ውድመት የሚያደርሱ የተለያዩ ድርጊቶች ይፈጸማሉ። ከእነዚህ መካከል አሁን ላይ አሳሳቢ የሆነው ከባድና ቀላል ተሽከርካሪ መኪናዎች ወደ መካነ ቅርሱ ቅጽር መግባት ወይም መጠጋት ነው። ይህ ድርጊት በመካነ ቅርሱ ላይ አደጋ ከመፍጠሩ በፊት የሚመለከታተቸው አካላት ቁጥጥር ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የኃይማኖት ማዕከል ነው። መንፈሳዊ ቦታ ነው። የታሪክ፣ የእምነትና የባህል መሰረት ነው። እነዚህን የመካነ ቅርሱን መሰረታዊ መገለጫዎች የሚፈታተኑና በሙዳ በዓል ወቅት ችግር እየፈጠሩ የሚገኙ ድርጊቶች ይከወናሉ። ደርጊቶቹም ከተፈቀደው ቦታ ውጭ በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ ውስጥና አካባቢው ንግድ መነገድ፣ አካባቢውን በአላስፈላጊ የድምጽ ብክለት መረበሽ፣ በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠቀም በመካነ ቅርሱ የሚከወኑ ስርዓቶችን ለመሰነድ መሞከርና መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን ስርዓቱን ባልጠበቀ መልኩ ማሰራጨት፣ ክልክል

የሆኑ ነገሮችን መሸጥና የማይፈቀዱ ድርጊቶችን መፈጸም ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በስርዓተከበራው፣ በከዋኙና በታዳሚው ላይ ችግር እየፈጠሩ በመሆኑ የሚመለከተው አካል ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- በሙዳ በዓላት ወቅት ከተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋል፡፡ ለመንፈሳዊ ተጓዦችም ሆነ ለመካነ ቅርሱ ነዋሪዎች የሚጠቅሙ የንጹህ መጠጥ ውኃ፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የመጸዳጃ ቤት፣ የመንገድና መሰል መሰረተ ልማቶች የሉም፡፡ የእነዚህ መሰረተ ልማቶች አለመሟላት ሕዝቡን ለከፍተኛ እንግልት የዳረጉና ለሕይወት ሕልፈት መንስኤ የሆኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚመለከተው አካል መሰረተ ልማቶችን በፍጥነት ማሟላት ይኖርበታል፡፡
- የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአገራችን ከሚገኙ የቱሪስት መስህቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ መስህብ በተለይ በአገራችን ካሉት እስላማዊ የቱሪስት ማዕከላት ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ በመካነ ቅርሱ የቱሪስዝም ልማትን ማሳደግ የአካባቢውንና የዞኑን ነዋሪዎች ኑሮ ከማሻሻሉም በተጨማሪ ለአገር ትልቅ ገቢ ያስገኛል፡፡ በመሆኑም መካነ ቅርሱ በተጠናከረ ደረጃ በማስተዋወቅና መሰረታዊ ልማቶችን በማሟላት ለቱሪዝም ልማት የሚውልበት መንገድ መጠናከር ይኖርበታል፡፡
- የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) በዓለም የቅርስ መዝገብ ዝርዝር ውስጥ የማስመዝገብ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህ ስራ በተለያዩ ምክንያቶች ለበርካታ አመታት በመዘግየቱ የሚጠበቀውን ያህል ስራ አልተሰራም፡፡ በመሆኑም ቅርሱን በዩኒስኮ የዓለም ቅርስነት ዝርዝር ውስጥ በማስመዝገብ ለቅርሱ እውቅና፣ እንክብካቤና ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሐሊማ መሐመድ። 1973። “ለባሌው ሼኽ ሁሴን የተገጠሙ ግጥሞች።” የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ፣ (ያልታተመ)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል።

ሐሰን ሰዒድ እና ሐሰን ሙሐመድ። 2008። *እስላማዊ ቅርሶች ዓይነትና ስርጭት ከሰሜን ሸዋ እስከ ደቡብ ወሎ*። አዲስ አበባ።

መሐመድ ሼሀ ሁሴን ዳውድ። (አመት የለውም)። *ለላሁመ-እርሐም ሼክና ሁሴን ቁጥበል-ሐበሹ*። ሐዋሳ።

መርስዔሀዘን ወልደቂርቆስ። 1999። *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ።* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕረስ።

*መጽሐፍ ቅዱስ፤ አዲሱ መደበኛ ትርጉም።* 1993። አዲስ አበባ፣ ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር።

ሙሐመድ ዐሊ። (አመት የለውም)። *ሸይኽ ዐብዱልቃድር ጂላኒ*። አዲስ አበባ፤ ነጃሺ ማተሚያ ቤት።

ሰሎሞን ተሾመ። 2002። “የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት በስሬ ኦሮሞዎችና አማራዎች-ንጽጽራዊ ጥናት።” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሐፍ ትምህርት ክፍል።

________። 2007። *ፎክሎር፤ ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ።* አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት።

ስቡሕ አድምጤ። 1997። *ሺሕ ዓመትና ሐሳዌ መሲሕ።* አዲስ አበባ፤ ኢትዮ-ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት።

ብሩ ጸጋዬ። 2008። *የስልጣኔ አፍሪካዊ ምንጭና በተረት መጋረጃዎች የተደበቁ እውነቶች*። አዳማ፤ በድር ማተሚያ ቤት።

ቅዱስ ቁርኣን። 1997። ሁለተኛ እትም። ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት።

ተክለጻዲቅ መኩሪያ፡፡ 1966፡፡ *የግራኝ አሕመድ ወረራ፡፡* አዲስ አበባ፡፡

አለማየሁ ኃይሌ፡፡ 2000፡፡ *በገዳ ስርዓት የቱለማ ኦሮሞ ፖለቲካ፡፡* ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ ፍንፍኔ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

አዕምሮ ንጉሤ፡፡ 2000፡፡ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ (ከቅራት- ዘመናዊ ፖሊስ)*፡፡ አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ. ማተሚያ ቤት፡፡

አጽመ ጊዮርጊስ (አለቃ)፡፡ 2008፡፡ *የኦሮሞ ታሪክ*፡ አዲስ አበባ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፡፡1987፡፡ *የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት*፡፡

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ 1998፡፡ *የኦሮሞ ታሪክ፣ እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን*፡ ሁለተኛ አርትኦት፡፡ ፊንፊኔ፡፡

________፡፡ 2000፡፡ *በገዳ ሥርዓት የቱለማ ኦሮሞ ፖለቲካ*፡ የመጀመሪያ እትም፣ ፍንፍኔ፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፡፡ 2002፡፡ "በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎች ታሪክ፡፡" (*ያልታተመ*)፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጤና ጥበቃ ማዕከል አመታዊ *ሪፖርት*:: 2006፡፡ (*ያልታተመ*)

የጎሎልቻ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት አመታዊ *ሪፖርት*:: 2006፡፡ (*ያልታተመ*)

የጎሎልቻ ወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤት አመታዊ *ሪፖርት*:: 2006፡፡ (*ያልታተመ*)

ያለው እንዳወቅ፡፡ 2004፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ይልማ ዴሬሳ፡፡ 1959፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በአሥራስድተኛው ክፍለ ዘመን*፡ አዲስ አበባ፡፡

ድሪቢ ደምሴ፡፡ 2007፡፡ *የኦሮሞ የማንነት ታሪክ*፡ ፍንፍኔ፡፡

ዳንኤል አባተ፡፡1984፡፡ “በሰኪና የኑር ሁሴን ስርዓተ-አምልኮና ድራማዊ ገጽታ፡፡” የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ፣ (ያልታተመ)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል፡፡

ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)፡፡ 2006፡፡ *አራቱ ኃያላን፤ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል፣ አቡነ ፊልጶስ፣ አቡነ አኖሪዎስ እና አቡነ አሮን*፡ አዲስ አበባ፤ አማኑኤል ማተሚያ ቤት፡፡

______፡፡ 2010፡፡ *ራእየ ዮሐንስ፣ የዓለም መጨረሻ*፡ ክልስ ዕትም፣ አዲስ አበባ፤ አግዮስ ማተሚያ ቤት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ 1991፡፡ *የሥነ-ቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Abbas H. Gnamo. 2014. *Conquest and Resistance in the Ethiopian Empire, 1880-1974*. Leiden: Koninklijke Brill NV.

Abinet Eshete. 2011. “Impacts of Pilgrimage Tourism: The Case of Bale Dire Sheikh Hussein.” (Unpublished Master’s Thesis), Addis Abeba University, Department of Archeology and Heritage Management.

Ahmed Zekaria. 1997. “Some Note on the Account Books of Amir Abd Al-Shakur B, Yusuf (1983-1794) of Harar.” *Sudanic Africa 8*, PP. 17-36.

Akinade, E. Akinoyunde. 2004. “Haji” In Frank A. Salamone (Ed) *Encyclopedia of Religious Rite, Rituals, and Festivals.* 159-166, London: Routledge.

Alexander, C. Jeffrey. 2006. “Cultural Pragmatics: Social Performance between Ritual and Strategy” In *Social performance Symbolic Action, Cultural Pragmatics and Ritual.* Edited by Jeffrey C. Alexander, Bernlard Glesen and Jason L. Mast. Cambridge University Press.

Aminorishe, U. Nathaniel. 2014. “Current Trends in Theories of Religious Studies: A Clue to Proliferation of Religious Worldwide.” *Global Journal of Arts, Humanities and Social Science,* Vol *2* (7), PP 27-46.

Andrzejewski, B. Witalis. 1972. “Allusive Diction in Galla Hymns in Praise of Sheikh Hussien of Bale.” *The School of Oriental and African Studies,* African Language Studies XIII.

_______. 1975. "A Genealogical Note Relevant to the Dating of Sheikh Hussein of Bale." *Bulletin of the School of Oriental and African Studies 38*. (1). PP 139-40.

Arab Faqih. 2003. *Futùh Al-Habaŝa: The Conquest of Abyssinia [16th Century]*, Translated by Paul Laster Stenhouse United State of America: Tsehai Publishers.

Areba Abdella, Abel Gezahegn and Ibrahim Kaso. 2003. "Dirre Sheik Hussien Shrine to be Inscribe in the Regional, National and World Heritage List." (Unpublished), Bale Robe: Bale Zone Culture and Tourism Office.

Asmarom Legesse. 1973. *Gada, Three Approaches to the Study of African Society*. New York: A Division of Macmillan Publishing Press.

Baird, Robert. 2004. "Syncretism and the History of Religion." In *Syncretism in Religion: A Reader.* Anita M. Leopold and Jeppe S. Jensen (Ed), 48-58, London: Equinox.

Bairu Tefla. 1975. "Ras Darge Sahla-Sellase, C. 1827-1900." *Journal of Ethiopian Studies,* 13*(2):* 17-37.

Bartels, Lambert. 1990. *Oromo Religion: Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia: an Attempt to Understand*. Berlin: Dietrich Reimer Verlag.

Bascom, William. 1965. "The Form of Folklore: Prose Narratives." *Journal of American Folklore*, *78* (307), 3-20.

Bauman, Richard. 1975. "Verbal Art as Performance." *American Anthropologist, New Series (77)*.2. PP 290-311

_______. 1983. "The Field Study of Folklore." In Richard M. Dorson (Ed). *Hand Book of Folklore*. Bloomingston: Indiana University Press, PP 362-369.

_______. (Ed). 1992. *Folklore, Cultural Performance and Popular Entertainments. Communications Centered Hand Book.* New York: Oxford University Press.

_______. 2004. *A Word of Others' World: Cross-Cultural Perspectives on Intertextuality.* Oxford-Malden: Blackwell.

Bauman, Richard and Charles L. Briddgs. 1990. "Poetics and Performance as Critical Perspective on Language and Social Life." *In Annual Review of Anthropology (19)*. PP 59-88.

Baxter, Paul. 1987. “Some Observations on the Short Hymns Sung in Praise of Sheikh Nur Hussein of Bale.” In Ahmed al-Shahi (Ed), *The Diversity of the Muslim Community: Anthropological Essays in Memory of Peter Lienhardt*, PP 139-152.

Bell, Catherine. 1997. *Ritual. Perspectives and Dimensions*. New York: Oxford University Press.

Berger, L. Peter and Luckmann, Thomas. 1966. *The Social Construction of Reality: A Treatise in the Sociology of Knowledge.* USA: Penguin Book Publisher.

Berhanu Matthews. 2016. “Mânzuma of the Gâriba.” *Journal of Ethiopian Studies*, Vol *49*, Addis Abeba, PP 57-78.

Bloor, Michael and Wood Fiona. 2006. *Keywords in Qualitative Methods: A Vocabulary of Research Concepts*. London: SAGE Publications.

Bollas, Christopher. 1987. *The Shadow of the Object: Psychoanalysis of the Unthought Known.* London: Free Association Book.

Boyer, Pascal. 1990. *Tradition as Truth and as Communication: A Cognitive Description of Traditional Discourse.* Cambridge: Cambridge University Press.

Braukämper, Ulrich. 1977. “Islamic Principalities in Southeast Ethiopia between the Thirteenth and Sixteenth Centuries.” *Ethiopianist Notes, 1* (1).

_____. 1984. “The Islamization of the Arsi-Oromo.” In Taddesse Beyene and *et al* (Eds) *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*. Addis Abeba: Addis Abeba University Press.

______. 1989. “The Sanctuary of Shaikh Husayn and the Oromo- Somalia Connections in Bale (Ethiopia).” *International Congress of Somalia Studies Frankfurter Afrkanistische Blätter (1).*PP 108-134.

______. 1992. “Aspects of Religious Syncretism in Southern Ethiopia.” *Journal of Religion in Africa. 22* (3), PP 194-207.

______. 2004. *Islamic History and Culture in Southern Ethiopia: Collected Essays*. London: LIT Publishers.

Cerulli, Enrico. 1922. “The Folk-Literature of the Galla of Southern Abyssinia.” *In Harvard African Studies, Varia Africa 3*, PP 9-22.

______. 1971. *Islam, Yesterday and Today*. Translated by Emiran M. Waber.

Cooke, Bernard and Macy, Gary. 2005. *Christian Symbol and Ritual. An Introduction*. New York: Oxford University Press.

Chernet Tilahun. 1990. "Trace of Islamic Material Culture in North-Eastern Shoa." *In Proceedings of the First National Conference of Ethiopian Studies*, Addis Abeba: Institute of Ethiopian Studies, Addis Abeba University, PP. 303-320.

Doresse, Jean. 1959. *Ethiopia: Ancient Cities and Temples*. Translated by Elsa Coult, New York: Frederick Ungar Publishers.

Dorson, M. Richard. (Ed). (1972). *Folklore and Folk life: An Introduction*. Chicago: The University of Chicago Press.

Dundes, Alan. 1965. "The Study of Folklore in Literature and Culture. Identification and Interpretation." *In Journal of American Folklore*. *78*(308). PP 136-142.

Durkheim, Émile (1995[1912]). *The Elementary Form of Religious Life*. New York: The Free Press

Eliyas Teha. 2012. "Understanding Rituals and Analyzing Songs Performed at Dirre Sheikh Hussein." (Unpublished Master's Thesis), Department of Social Anthropology, Addis Abeba University.

Eriksen, H. Thomas. 2001. *Small Places, Large Issues: An Introduction to Social and Cultural Anthropology.* 2nd Ed, London: Pluti Press.

Eliade, Mircea. 1959. *The Sacred and the Profane: the Nature of Religion*. Translated by Willard R., New York: Harcourt Brace & Co.

Ellewood, S. Robert and Alles D. Gregory. 2007. *Encyclopedia of World Religion*. Revised Edition, Infobase Publishing: United State of America.

Erlich, Haggai. 1994. *Ethiopia and the Middle East*. London: Lynne Rienner Publishers.

_____. 2007. *Saudi Arabia and Ethiopia, Islam, Christianity, and Politics Entwined*. Lynne Rienner Publishers.

Eshetu Setegn. 1973. "Shaikh Hussayn of Bale and His Followers." (Unpublished Senior Essay), Department of History, Faculty of Art, Haile Selassie I University.

Evans-Pritchard, Edward. 1956. *Nuer Religion.* London: Oxford University Press.

Fakhry, Majid. 2004. *A History of Islamic Philosophy*. 3rd Ed, Colombia University Press: New York.

Feyisa Demie. 1998. "The Origin of the Oromo: a Reconsideration of the Theory of the Cushitic Roots. *Journal of Oromo Studies,* 5 *(1&2).* PP 155-172.

Fickeler, Paul. 1962. "Fundamental Question in the Geography of Religion." in *Readings in Cultural Geography*, University of Chicago Press: Chicago. PP 94-117.

Fine, C. Elizebeth. 1984. *The Folklore Text from Performance to Print*. Indianapolis: Indiana University Press.

Finnegan, Ruth. 1977. *Oral Poetry: Its Nature, Significance and Social Context.* Cambridge: Cambridge University Press.

______. 1992. *Oral Traditions and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices.* New York: Routledge Publishing Company.

Firth, Raymond. 1967. *Tikopia Ritual and Belief*. Boston: Beacom Press.

Friedman, A. B. 1961. "The Formulaic Improvisation Theory of Ballad Tradition- a Counterstatement." *Journal of American Folklore,* 74.

Gadamer, Hans-Georg. 1976. *Philosophical Hermeneutics*. Translated by David E. Linge; University of California Press: Los Angeles.

Galwash, A. Ahmed. 1966. *The Religion of Islam: A Standard Book*. Vol, 2, Alexandria.

Gebru Tareke. 1977. "Rural Protest in Ethiopia, 1941-1970: A Study of Three Rebellions." PhD Thesis, Sycracuse University, New York.

Geda Melbaa. 1966. *Oromia: An Introduction*. Khartoum.

Geertz, Clifford. 1966. "Religion as a Cultural System." in *Anthropological Approaches to the Study of Religion*. Edited by Michael Banton, PP 1-46. London.

_____. 1973. *Interpritation of Cultures.* New York: Basic Books.

Gemetchu Megerssa. 1994. “Knowledge, Identity and the Colonizing Structure, the Case of the Oromo in East and Northeast Africa.” (Unpublished PhD Dissertation), School of Oriental and African Studies, University of London.

Gemechu J. Geda. 2013. “Pilgrimages and Syncretism: Religious Transformation among the Arsi Oromo of Ethiopia.” (Unpublished PhD Dissertation), A Dissertation Submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Doctor of Philosophy in Religious Studies; Germany University of Bayreuth, Faculty of Cultural Studies.

Given, M. Lisa. (Ed). 2008. *Encyclopedia of Qualitative Research Methods*. Vol 1 and 2. London: A SAGE Publications.

Gluckman, Max. 1962. *Essays on the Ritual of Social Relations*. Manchester: Manchester University Press.

Goba Municipality. 1984. “Historical Investigation of the Revolution.” (Unpublished Paper).

Goldstein, Kenneth. 1974. *A Guide for Field Workers in Folklore*. Detroit: Gale Research Company.

Green, A. Thomas. (Ed). 1997. *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art.* California: ABC-CLIO.

Grimes, L. Ronald. 1982. “Defining Nascent Ritual.” *In Journal of the American Acadamy of Religion, 50*. (4): Oxford University Press.

Gruenwald, Ithamar. 2003. *Ritual and Ritual Theory in Ancient Israel*. Vol 10. Leiden: Koninklijka Brill NV.

Gulevich, Tanya. 2004. *Understanding Islam and Muslim Traditions: An Introduction to the Religious Practices, Celebrations, Festivals, Observances, Beliefs, Folklore, Customs, and Calendar System of the World’s Muslim Communities, Including an Overview of Islamic History and Geography*. Michigan; Omnigraphics, Inc.

Hailemelekot Agizew and Mulugeta Abegaz. 2015. “The Dirre Sheikh Hussein Religious, Cultural and Historical Heritage Site Management Plan.” (Unpublished), Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage, Addis Abeba.

Henn, Matt, Weinstein, Mark and Foard, Nick. 2006. *A Short Introduction to Social Research.* New Delhi: SAGE Publications.

Huntingford, G.W.B. 1955. *The Galla of Ethiopia; The Kingdome of Kafa and Janjero.* Ethnographic Survey of Africa: London.

Hussein Ahmed. 2001. *Islam in Nineteenth- Century Wallo, Ethiopia*. Leiden: Bill.

_____. 2006. "Coexistence and/ or Confrontation: Towards a Reappraisal of Christian- Muslim Encounters in Contemporary Ethiopia." *Journal of Religion in Africa, 36(1),* PP 4-22.

Hussein Indhessa. 2008. *Seenaa Qabosoo Ummata Oromoo Baalee fi Ollaa Isaa (1891-1991 ALA).* Finfinnee.

Ibn Ishaq, Muhammad. 1955. *The Life of Muhammad (Sirat Rasul Allah).* Translated by Guillaume A, Lohore: Oxford University Press.

Iqabal, M. Siddiqi. *The Ritual of Animals Sacrifice in Islam*. India.

Jackson, Bruce. 1987. *Field Work*. Chicago: University of Illinois Press.

Jafferson, Gail. 1978. "Sequential Aspect of Story Telling in Conversation." in *Studies in the Organization of Conversational Interaction.* Jim Schenkein (ed), New York: Academic: Press. PP 219-248.

Jeylan W. Hussein. 2005. "The Functional of African Oral Arts: The Arsi-Oromo Oral Arts in Focus." *In African Studies Monographs, 26*(1). PP 15-58.

_____. 2016. "The Social-Psychology and Phenomenological Construct of Spirituality in the Culture of Dhikr in Eastern Ethiopia." *Journal of Culture and Psychology*. 0(*0*), PP 1-23.

Joyner, W. Charles. 1975. A Model for the Analysis of Folklore Performance in Historical Context. *The Journal of American Folklore, 88*(349). PP 254-265.

Kane, Ross E. 2017. "The Syncretism of Tradition: Reappraising Cultural Mixture in Christianity." A Dissertation Presented to the Graduate Faculty of the University of Verginia in Candidacy for the Degree of Doctor of Philosophy: University of Verginia.

Kaplan, Steven. 2010. "Christian Pilgrimage." In *Encyclopedia Aethiopica*. Vol 4 Siegbert Uhlig (Ed). 151-153, Wiesbaden: Harrassowith.

Ketebo Abdiyo. 1999. "A Historical Survey of. the Arsi- Oromo Ca, 1910- 1974. (Unpublished Master's Thesis), A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Abeba University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree Master of Art in History, Addis Abeba.

Ketema Meskela. 2001. “The Evolution of Land-Ownership in High-Land Bale, a Case Study of Goba, Sinana and Dodola to 1974.” MA-Thesis in History, Addis Abeba University, Addis Abeba.

Kippenberg, Hans. 2004. “In Praise of Syncretism: The Beginning of Christianity Conceived in the Light of a Diagnosis of Modern Culture.” in *Syncretism in Religion: A Reader*. Anita M. Leopold and Jeppe S. Jensen (Ed), 29-38, London: Equinox.

Khanam, Farida. 2009. *Sufism an Introduction*. India: Goodword.

Knutsson, E. Karl. 1963. *Authority and Change: A Study of the Kallu Institution among the Mecca Galla of Ethiopia*. Goteborg.

Kothari, R.C. 2004. *Research Methodology*. New Delhi: New Age International Publisher.

Kyriakidis E. 2007. *The Archaeology of Ritual*. Los Angeles: Cotsen Institute of Archaeology.

Leeming, A. David. (2010). *Creation Myths of the World, An Encyclopedia.* 2nd ed. California: Greenwood Publication Group.

Lewis, I.M. 1955. *Peoples of the Horn of Africa: Somalia, Afar and Saho*. Ethnographic Surveys of Africa. London.

_____. 1966. *Islam in Tropical Africa*. Indiana University Press: Indiana.

_____. 1980. “The Western Somalia Liberation Front (WSLF) and the Legacy of Sheikh Hussein of Bale.” *Proceeding of the fifth International Conference of Ethiopa: Nice*.

Levine, N. Donald. 1974. *Greater Ethiopia: The Evolution of A Multiethnic Society.* Chicago: University of Chicago Press.

Makonnin Raggaasaa. 2008. “Xiinxala Ayyaanafi Fakkoommiiwwan Sirna Raawwii Muuda Dirree Sheek Huseen.” Waraqaa Qorannoo Ulaagaa Digrii Lammaffaa (MA) Afaan Oromoofi Ogbarruu Barsiisuun Gamiisaan Guuttachuuf Qophaa’ee Muummee Afaan Oromoo Hogbarruufi Fookilariitii Kennamu. Kolleejjii Namoomaa Qo’annoo Afaanii Jornaalizimiifi Qunnamtii Yunivarsitii Finfinnee.

Martine, Luther and Leopold, M. Anita. 2004. “New Approaches to the study of Syncretism.” New Approaches to the Study of Religion: A Textual Comparative, sociological, and Cognitive Approaches. Vol 2, Peter Antes, Armin Geertz, Randi Warne (Eds), New York: Walter de Gnyter, PP 93-108.

McCauley, N. Robert. 2010. *Cognition, Religious Ritual, and Archaeology*. Queen’s University Belfast Press.

Merid Wolde Aregay. 1971. "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508-1708, with Special Reference to the Galla Migrations and their Consequences." Thesis Submitted for the degree of Ph.D, School of Oriental and African Studies at the University of London.

Mindaye Abebe. 2005. "The Oromo of Bale: A Historical Survey to 1974." MA-Thesis in History, Addis Abeba University, Addis Abeba.

Mohamed Hassen. 1990. *The Oromo of Ethiopia:* A History 1570-1860. Cambridge.

______. 2005. "Pilgrimage to the Abba Muudaa." *Journal of Oromo Studies 14(1-2),* PP 142-157.

______. 2008. "The Oromo in Medieval Muslim States of Southern Ethiopia." *Journal of Oromo Studies 14(2),* PP 131-155.

______. 2015. *The Oromo and the Christian Kingdom of Ethiopia 1300- 1700*. United States of America: Boydell and Brewer Ltd.

Momen, Moojan. 1985. *An Introduction of Shi'I Islam*. New Haven: Yale University Press.

Muhaammadkiyaar Mahmud. 2008. "Qaacceessa Fayyadama Afaanii Baaroo Dirree Sheek Huseen Keessatti." Waraqaa Qorannoo Ulaagaa Digrii Lammaffaa (MA) Afaan Oromoofi Ogbarruu Barsiisuun Gamiisaan Guuttachuuf Qophaa'ee Muummee Afaan Oromoo Hogbarruufi Fookilariitii Kennamu. Kolleejjii Namoomaa Qo'annoo Afaanii Jornaalizimiifi Qunnamtii Yunivarsitii Addis Ababaa.

Muhammad, Rabee' Ibn Haadee Al-Madkhalee. 1404. *The Reality of Sufism in Light of the Qur'aan and Sunnah*. Mekkah.

Muhammad Sayid Abdulrahmaan. 2004. *Seenaafi Qabsoo Oromootaa*. Finfinnee.

Neumann, Oscar. 1902. "From the Somali coast through Southern Ethiopia*". In Geographical Journal, XX.*

O'Leary, De Lacy. 1927. *Arabia before Muhammad*. London: Trubner & Co.

O'Leary, Zina. 2004. *The Essential Guide to Doing Research.* London: SAGE Publications.

Østebo, Terji. 2009. "Religious Change and Islam, The Emergence of the Salafi Movement in Bale, Ethiopia." *In Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies,* Edited by Svein Ege and *et al*, Trondheim, PP 463-476.

______. 2012. *Localising Salafism: Religious Change among Oromo Muslims in Bale, Ethiopia.* Boston: Brill NV Publications.

______. 2014. "Claims for Authority at the Shrine of Shykh Husayn, Ethiopia." *Journal of Islamic Studies.* PP 1-27.

Pankhurst, Richard. 2005. "Faraqasa." In Siegbert, Uhlig (Ed), *Encyclopaedia of Aethiopica*. Wiesbaden Harrassowitz, Vol II, 493-494.

Payne, Geoff and Payne, Judy. 2004. *Key Concepts in Social Research*. New Delhi: SAGE Publications.

Pentikäinen, Juha. 1997. "Ritual." In Thomas A. Green (Ed), *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art*. California: ABC-CLIO,Inc

Punkhurst, Alula. 1994. "Reflections on Pilgrimage in Ethiopia." New Trends in Ethiopian Studies: *In Proceeding of the 12th International Conference of Ethiopian Studies.* Edited by Harold G. Marcus, and *et al* PP 933- 953, New Jersey: Red Sea Press INC.

Rahaman, Hasibul. 2016. "Religious Syncretism Conversion and Practices among the Muslims: a Case Study of Hussain Dighi of Utter Dinajpur District of West Bengal." *Islam and Muslim Society, A Social Science Journal*, Vol 9 *(1-2).*PP. 51-57.

Rappaport, A. Roy. 1992. "Ritual." In Richard Bauman (Ed). *Folklore, Cultural Performance and Popular Entertainments. Communications Centered Hand Book.* New York: Oxford University Press. PP 249-260.

_____. 1999. *Ritual and Religion in the Making of Humanity*. Uk: Cambridge University Press.

Renard, John. 2005. *Historical Dictionary of Sufism: Historical Dictionary of Religions, Philosophies, and Movement*, No, 58, Oxford.

______. 2009. *The A to Z of Sufism.* N0, 44, UK: The Scarecrow Press.

Ross, Eric. 1996. "Túbâ: An African Eschatology in Islam." a Thesis Submitted to the Faculty of Graduate Studies and Research in Partial Fulfillment of the Requirements of the Degree of Doctorate of Philosophy, Institution of Islamic Studies, McGili University: London

Rudolph, Kurt. 2004. "Syncretism: From Theological Invective to A Concept in the Study of Religion." In Anita M. Leopold and Jeppe S. Jensen (Ed). *Syncretism in Religion: A Reader*. Edited by; PP 68- 85. London.

Saheed, A.R. 2009. "Teaching and Learning in Early Islam: A Discourse on an Intellectual Tradition." *in Correlated of Islam*. Akintola L. (Ed), PP 186-211.

Sahlins, Marshall. 1976. *Culture and Practical Reason*. Chicago: Chicago University Press.

Salamone, A. Frank (Ed). 2004. *Encyclopedia of Religious Rite, Rituals, and Festivals.* London: Routledge.

San, K. Chan. 2001. *Buddhist Pilgrimage*. Malaysia: Majujaya Indah Press.

Sa'id Mohammad. 2016. *Qooda Huseen Suuraa: Qabsoo Oromoo Keessatti.* Minnesota: USA.

Schenchner, Richard. 2004. *Performance Theory*. London: Routledge.

Setargew Kenaw. 2017. "Spiritual Entrepreneurship in Zar: A Study on Spirit Medium ship and Religion." *Ethiopian Journal of Religious Studies.* 1(*1*), PP 99-132.

Sims, C. Martha and Stephens, Martine. 2005. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions.* Utah: Utah State University Press

Sintayehu Kassaye. 1985. "Goba: Foundation, Growth and Development to 1974." (Unpublished Senior Essay), Department of History, College of Social Science, Addis Abeba University.

Sintayehu Tola. 2001. "The Conservation of Dirre Shaikh Hussein Heritage Site." (Unpublished), Oromia Culture and Tourism Bureau.

Skinner, B.F. 1948. "Superstition in the Pigeon. " *Journal of Experimental Psychology*. PP 168-172.

Smith, Donaldson. 1896. "Expeditions through Somaliland to Lake Rudolf". *in Geographical Journal*. London.

Smith, Jane and Haddad, Yazbeck. 1981. *The Islamic Understanding of Death and Resurrection*. Albany: State University of New York.

Stoddard, Robert. 1997. "Defining and Classifying Pilgrimages." *In Geoscience and Man*, Vol *34*. Louisiana State University: Baton Rouge, PP 41-60.

Spsford, Roger and Jupp, Victor. (Ed). 2006. *Data Collection and Analysis*. [2nd Edition], New Delhi: SAGE Publications.

Taddesse Tamrat. 1972. *Church and State in Ethiopia, 1270-1527*. London: Oxford University Press.

Temam Haji-Adam. 2002. "Islam in Arsi, Southeast Ethiopia (Ca, 1840-1974)." (Unpublished Master's Thesis), A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Abeba University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree Master of Art in History, Addis Abeba

_____. 2010. *Qarooma Kuush, Seenaa Ummata Oromoo fi Gahee Dirree Sheek (Nuur) Huseen*. Haraamayaa: Halif Publications.

Teshome Amenu. 2008. "The Rise and Expansion of Islam in Bale of Ethiopia: Socio- Cultural and Political Factors and Inter- Religious Relations." (Unpublished Master's Thesis), A Thesis submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Philosophy in a Religious Education at Norsk Laererakademi: Norway.

Tilahun Gamta. 1989. *Oromo- English Dictionary*. Addis Abeba: Addis Abeba University Printing Press.

Titon, T. Jeff. 1992. Music, Folk and Traditional. In Richard Bauman (Ed), *Folklore, Cultural Performance and Popular Entertainments*: *A Communications Centered Hand Book* (PP. 167- 171). New York: Oxford University Press.

Tremlin, Todd. 2006. *Mind and Gods, the Cognitive Foundations of Religion*. Oxford University Press.

Trimingham, J. Spencer. 1952. *Islam in Ethiopia.* London: Oxford University Press.

Turner, Victor. 1967. *The Forest of Symbols: Aspects of Ndembu Ritual. Ithaca*, New York: Cornell University Press.

______. 1969. *The Ritual Process: Structure and Anti-Structure*. New York: Aldina De Gruvter.

Tylor, Edward. 1979[1873]. *Animism. In Reader in Comparative Religion*. 4th Edition. Edited by William A. Lessa and Evon Z. Vogt, PP 9-19. New York.

Ullendorff, Edward. 1960. *The Ethiopians: An Introduction to Country and People.* 2nd Ed, Oxford University Press: London.

Umer Nure. 2006. "The Pilgrim to Dirre Sheikh Hussein: Its Social Organization and Overhaul Roles." (Unpublished Master's Thesis), Department of Social Anthropology, Addis Abeba University.

Vergot, Antoine. 1997. *Religion, Belief and Unbelief: A Psychological Study*. Leuven University Press.

Zena Ayele. 2014. *Culture and Ethno-History of Halaba*. Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Bureau of Culture and Tourism, Hawassa.

## አባሪ፤- የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር

### በሰንጠረዡ የቀረቡ ምህጻረ ቃላት መግለጫ፣

የድ/ሼ/መ/ቅ/ባ/ቱ/ሰ -- የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኛ

የባ/ዞ/ባ/ቱ/ሰ-- የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኛ

የድ/ሼ/መ/ቅ/መሪ-- የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መሪ

የኡሌ/መ/ሙ/ባ-- የኡሌ መንፈሳዊ ሙዚቃ ባለሙያ

የፕ/ አስተባባሪ-- የፕሮግራም አስተባባሪ

የኦ/ተ/ቤ/የባ/ሀ/ት/ሰ- - የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የባሌ ሀገረ ስብከት ሰራተኛ

የባ/ሀ/ስ/ት/የተ/ገ/አ- - የባሌ ሀገረ ስብከት የቅዱስ ተክለኃይማኖት አንድነት ገዳም አበመኔት

| ተ.ቁ | የመረጃ ሰጪዎች ሙሉ ስም | ጾታ | እድሜ | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ | ስራ ወይም ማህበራዊ ኃላፊነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ነስሩዲን ሰዒድ አህመድ | ወ | 30 | አናጂና ቀበሌ | - |
| 2 | አቶ አብዱልናስር አህመድ | ወ | 37 | ›› ›› | የድ/ሼ/መ/ቅ/ባ/ቱ/ሰ |
| 3 | አቶ ኑማን ሼኽ መሀመድ | ወ | 28 | ›› ›› | የድ/ሼ/መ/ቅ/ባ/ቱ/ሰ |
| 4 | አቶ መሃመድ ሰዒድ አህመድ | ወ | 32 | ›› ›› | የድ/ሼ/መ/ቅ/ባ/ቱ/ሰ |
| 5 | ሼኽ ሰይፈዲን ሀጂ ዑስማ | ወ | 60 | ›› ›› | |
| 6 | ሼኽ መሃመድ ሼኽ ኢድሪስ | ወ | 66 | ›› ›› | |
| 7 | ወ/ሮ ነስራ አደም | ሴ | - | ›› ›› | |
| 8 | ወ/ሮ ሰሚራ - | ሴ | - | ›› ›› | |
| 9 | ወ/ሮ ተሚማ ሼኽ ሰዒድ | ሴ | 45 | ›› ›› | |
| 10 | ወ/ሮ ቀመርያ ዩሱፍ | ሴ | 50 | ›› ›› | |
| 11 | ወ/ሮ ከዲጃ ኡመር | ወ | - | ›› ›› | |
| 12 | ሼኽ አህመድ ሼኽ መሃመድ | ወ | 59 | ›› ›› | |
| 13 | ወ/ሮ ሀሊማ - | ወ | - | ›› ›› | |
| 14 | ሼኽ ፈይሰል ሼኽ ኡመር | ወ | 36 | ›› ›› | የድ/ሼ/መ/ቅ/መሪ |
| 15 | ኡሌ መሃመድ አልይ | ወ | - | ›› ›› | የኡሌ መ/ሙ/ባ |
| 16 | አቶ አቡሽ ኃይሉ | ወ | 36 | ቢሾፍቱ ከተማ | |
| 17 | ሼኽ ከዲር መሃመድ | ወ | 60 | አናጂና ቀበሌ | የፕ/አስተባባሪ |
| 18 | አቶ መሃመድ ሼኽ ሁሴን | ወ | 56 | አዲስ አበባ | ጸሐፊ |
| 19 | ሼኽ አሕመድ ሼኽ ኤልያስ | ወ | - | አናጂና ቀበሌ | |
| 20 | ሼኽ አሕመድ ሀጂ ከዲር | ወ | 52 | ›› ›› | |
| 21 | ሼኽ መሃመድ ሀጂ ሙሃመድ | ወ | 73 | ›› ›› | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 22 | ሼኽሙሃመድ ሀጂ አብዱልቃድር | ወ | 55 | ›› ›› | |
| 23 | ወ/ሮ ሰሚራ ሀጂ ከዲር | ሴ | - | ›› ›› | |
| 24 | ወ/ሮ ሀሊማ ዑስማን | ሴ | - | ›› ›› | |
| 25 | ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ | ወ | - | ›› ›› | |
| 26 | ወ/ሮ ፋጤ ዳውድ | ሴ | - | ›› ›› | |
| 27 | ሼኽ ቃሲም ሼኽ አደም | ወ | 52 | ›› ›› | |
| 28 | ወ/ሮ ኑሪያ - | ሴ | 39 | ›› ›› | |
| 29 | ኡሌ አደም | ወ | 49 | ›› ›› | |
| 30 | አቶ ስንታየሁ | ወ | 35 | ›› ›› | |
| 31 | ሼኽ ከዲር ሼኽ ኢብራሂም | ወ | 58 | ›› ›› | |
| 32 | አቶ ከተማ መስቀላ | ወ | - | ሮቤ ከተማ | የባ/ዞ/ባ/ቱ/ቢ/ሰ |
| 33 | ሼኽ ተማም ኢድሪስ | ወ | - | አናጂና ቀበሌ | |
| 34 | ሼኽ አደም ገመዳ | ወ | 32 | ሮቤ ከተማ | |
| 35 | ሼኽ አሊይ ሱራ | ወ | - | ›› ›› | |
| 36 | ሼኽ ጀይላን አመኖ | ወ | - | ›› ›› | |
| 37 | ሊቀህሩያን አድማሱ - | ወ | 49 | ጎባ ከተማ | የኦ/ተ/ቤ/የባ/ሀ/ት/ሰ |
| 38 | ቀሲስ ስንታየሁ አሻግሬ | ወ | - | ›› ›› | የኦ/ተ/ቤ/የሀ/ት/ሰ |
| 39 | አባ ወልደሚካኤል ገ/እግዚአብሔር | ወ | 45 | ›› ›› | የባ/ሀ/ስ/ተ/ገ/ት |
| 40 | ግራዝማች ኃይሌ ወ/ሰንበት | ወ | 71 | ›› ›› | |
| 41 | አቶ መንግስቴ አሸኔ | ወ | 58 | ሮቤ ከተማ | |